


# ከመስከረም እስከ መስከረም

የኢፌደሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)
ከመስከረም 24 ቀን 2015 ዓ.ም እስከ መስከረም 24 ቀን 2016 ዓ.ም
ድረስ ያደረጓቸው ንግግሮች እና ያስተላለፏቸው መልእክቶች

ቅፅ ፮ | Vol 6 የካቲት ፣ 2016

# ከመስከረም 2015 እስከ መስከረም 2016 ዓ.ም

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)
ከመስከረም 24 ፣ 2015 ዓ.ም እስከ መስከረም 24 ፣ 2016 ዓ.ም
ድረስ ያደረጓቸው ንግግሮች እና ያስተላለፏቸው መልእክቶች

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

የካቲት 2016 ዓ.ም

ቅንብር፣ አርትዖትና ዝግጅት

- የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ፕሬስ ሴክረታሪያት ክፍል

ISBN 978-99990-52-51-1

ISBN 978-99990-52-51-1
Copyright © 2024 Office of the Prime Minister – Ethiopia
የካቲት 2016 ዓ.ም. ታተመ

# ማውጫ

*መግቢያ* I

ክፍል አንድ - የአማርኛ ንግግሮች እና መልዕክቶች

1. የኢትዮጵያ ሳይንስ ሙዚየም ምርቃት 1
2. በአማራ ክልል ማዕከላዊ ጎንደር ዞን የማሳ ጉብኝት 3
3. በቡራዩ የተሰጥዖ ማበልፀጊያ ትምህርት ቤት የምረቃ ሥነ ሥርዓት 7
4. የቀዳማዊት እመቤት ጽ/ቤት በጂማ ዞን አኮ ወረዳ ያስገነባው ትቤት የምረቃ ሥነ ሥርዓት 13
5. በእንጦጦ የሥነጥበብ ማዕከል የተዘጋጀው ዐውደርዕይ ጉብኝት 15
6. በጠቅላዩ ሚኒስቴር ጽ/ቤት አቅራቢያ ለሕፃናትና ለወጣቶች የሚሆን የስፓርት ማዘውተሪያ አበርክቶ 21
7. በምሥራቅ ሸዋ ዞን ዱግዳ ቦራ በኩታ ገጠም የለማ የስንዴ ማሳ ጉብኝት 25
8. በደቡብ ክልል፣ በጎፋ ዞን የተካሄደ ጉብኝት 31
9. በአርባምንጭ ከተማ የተካሄደ ጉብኝት 35
10. 17ኛው የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን አከባበር በሃዋሳ 43
11. በብላቴ ወንዝ ተፋሰስ የተካሄደ ልማት ጉብኝት 49
12. በወላይታ ሶዶ የዱቄትና ዳቦ ፋብሪካ ምርቃት 55
13. በሐዋሳ ከተማ የዳቦና የዱቄት ፋብሪካ ምርቃት 63
14. የፖለቲካ ገበያን (Political Marketplace) አስመልክቶ የቀረበ 67
15. በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ የተከፈቱ ኢንዱስትሪዎች ጉብኝት 75
16. በአዋሽ አርባ በተደረገ የምድር ጦርና አየር ኃይል የተቀናጀ የጦር ልምምድ ላይ የተላለፈ መልዕክት 79
17. በሰላምና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ዙሪያ የተሰጠ ማብራሪያ 83
18. የስንዴ ኤክስፖርት ማስጀመሪያ ሥነሥርዓት 95
19. በ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተና ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች የሽልማት መርሃግብር 99
20. የታክስና የጉምሩክ ሕግ ተገዥነት ሀገራዊ ንቅናቄ ማስጀመሪያ ዝግጅት 105
21. የመደመር ትውልድ የመጽሐፍ ምረቃ ሥነ-ሥርዓት 111
22. ከጉራጌ ሕዝብ ተወካዮች ጋር የተካሄደ ምክክር 123
23. የአጼ ፋሲል ቤተመንግሥት ጉብኝት 133
24. በዳጋ ቅዱስ እስጢፋኖስ የአባቶች አንድነት ገዳም የተካሄደ ጉብኝት 137
25. በጎርጎራ ፕሮጀክት የተላለፈ መልዕክት 141

26. የኢትዮጵያ ወታደራዊ አካዳሚ ያሰለጠናቸውን ዕጩ መኮንኖች በሁርሶ የኮንቲጀንት ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት የምረቃ በዓል 145
27. '' ጦርነት ይብቃ፤ ሰላምን እናጽና'' በሚል ርዕስ በተዘጋጀው መርሃ ግብር ላይ የተላለፈ መልዕክት 149
28. የስካይላይት ሆቴል ምዕራፍ ሁለት መክፈቻ ሥነሥርዓት 157
29. 'ኢትዮጵያ ታምርት' ኤክስፖ ላይ ተገኝተው ያስተላለፉት መልዕክት 161
29. በሳይንስ ሙዚየም በተካሄደው የግብርና ዐውደ ርዕይ መክፈቻ ሥነ ሥርዓት 169
30. በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር በልጽጎ ሥራ ላይ የዋለ የውጭ ሀገር የሥራ ሥምሪት መረጃ ሥርዓት ጉብኝት 175
31. አዋሬ አካባቢ የአቅመ ደካሞችን ቤት የማደስ መርሃግብር ማስጀመሪያ 179
32. 3ኛው የሀገር አቀፍ የክህሎት ውድድር መርሃግብር ላይ ያደረጉት ንግግር 181
33. የአንድነት ፓርክ የዕጽዋት ማዕከል፣ የአንድነት ቤተ መዛግብትና የሕክምና ማዕከል ምረቃ 185
34. የአረንጓዴ ዐሻራ የሁለተኛው ምዕራፍ መርሐግብር ማስጀመሪያ መልዕክት 191
35. ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት አመራርና ሠራተኞች ጋር የአረንጓዴ ዐሻራ ተከላ መርሐ ግብር 195
36. ሀገር አቀፍ የጤና ዐውደ ርዕይ መክፈቻ ሥነሥርዓት 199
37. የላቀች ኢትዮጵያን ለመገንባት፤ ቀድመን የላቁ ትምህርት ቤቶችን አብረን እንገንባ! 203
38. በጌድዮ ዞን የተካሄደ የልማት ስራዎች ጉብኝት 207
የአርባምንጭ 'ገበታ ለትውልድ' ማስጀመሪያ መርሐግብር 211
39. ኛንጋቶም ወረዳ የልማት ስራዎች ጉብኝት 213
40. በኮንሶ የልማት ሥራዎች ጉብኝት 217
41. የ500 ሚሊየን ችግኝ በአንድ ጀምበር የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብርን ማሰጀመሪያ 219
42. በየካ ተራራ ከሚገኙ የ1ኛእና የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች ጋር የ500 ሚሊየን በአንድ ቀን የአረንጓዴ ዐሻራ የችግኝ ተከላ 221
43. የ500 ሚሊየን ችግኝ በአንድ ጀምበር የመዝጊያ መርሃ ግብር 223
44. የኢትዮጵያ ትልቁ ኤሌት ኃይል የምረቃ ሥነ ሥርዓት 229
45. ኢትዮጵያ የብሪክስ አባል ሆነች 233
46. ሀገር ከማገልገል በላይ ጀግንነት የለም 235

47. በጎነት መሰፈርት የለውም፤ ከማይነጥፍ የመልካምነት እሴት
የሚቀዳ እንዲሁ በነጻ የሚሰጥም ነው 239
48. የኢትዮጵያዊያን ብርቱ እጆች በጽናት ታሪክ መስራት ቀጥለዋል 241
49. የመስቀል እና የመውሊድ በዓላትን ምክንያት በማድረግ የጠቅላዩ
ሚኒስትር ጽ/ቤት በሚያሠራቸው ፕሮጀክቶች ላይ ለሚሠሩ ሠራተኞች
የእንኳን አደረሳችሁ ዝግጅት 243
50. የኢትዮጵያን አምቅ አቅም የሚገልጠው "ገበታ ለትውልድ" ጃማ 245
51. የዜጎችን ሕይወት የሚቀዩሩ የልማት ሥራዎች በጂማ ዞን 249
52. በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ቤንች ሸኮ ዞን ውሎ 253

## መልዕክቶች

53. እንኳን ለመውሊድ በዓል አደረሳችሁ 259
54. የፀረ ሙስና ብሔራዊ ኮሚቴ መቋቋም 261
55. እንኳን ለ17ኛው የብሔር ብሔረሰቦች በዓል (የኢትዮጵያዊነት ቀን)
አደረሳችሁ። 265
56. እንኳን ለኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል አደረሳችሁ! 269
57. እንኳን ለብርሃነ ጥምቀቱ በሰላም አደረሳችሁ! 273
58. "የትናንት ዘር፣ የዛሬ ፍሬ፣ የነገ ስንቅ!" 277
59. እንኳን ለ127ኛው የዐድዋ ድል በዓል በሰላም አደረሳችሁ! 281
60. "ከጊዜያዊ መፍትሄ ዘላቂ ጥቅም አይገኝም!" 287
61. እንኳን ለኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤ በዓል አደረሰን፣ አደረሳችሁ! 293
62. እንኳን ለዒድ አል ፈጥር በዓል በሰላም አደረሳችሁ! 297
63. ሐሳብን በሐሳብ ማሸነፍ ያቃታቸው አካላት የወንድማችንን የግርማ
የሺጥላን ነፍስ ነጥቀዋል። 301
64. እንኳን ለዐርበኞች ቀን (የድል በዓል) አደረሳችሁ 303
65. እንኳን ለታላቁ የዒድ አል አድሃ በዓል አደረሳችሁ! 305
66. 500 ሚልዮን ችግኞች በአንድ ጀንበር 309
67. ዓላማችን ሪከርዳችንን መስበር ነው! 312
68. ታሪክ ሠርታችኋል 313
69. እንኳን ለ2016 አዲስ ዓመት አደረሳችሁ 315
70. እንኳን ለመውሊድ በዓል አደረሳችሁ 317
71. እንኳን ለብርሃነ መስቀሉ አደረሳችሁ! 319

## ክፍል ሁለት ፤ የኦሮምኛ መልዕክቶች


72. Boqochuu Doktara kabajaa Artisti Alii Birraan Gadda keessookoo ibsaa 325
73. Akkuma Kaleessaa Har’as Qormaatota Injifin noon Ceenee, Harka Keenya Galataaf ni Bal’ifna 329
74. Akkuma Kaleessaa Har’as Qormaatota Injifinnoon Ceenee, Harka Keenya Galataaf ni Bal’ifna 337
75. Baga Ayyaana Injifannoo Adwaa 127fatiin nagaan isin gahe! 341


## ክፍል ሶስት ፡ የእንግሊዝኛ ንግግሮች እና መልዕክቶች


76. Speech Delivered at Tana Forum 351
77. Speech at the Closing Ceremony of the First African Youth Summit 355
78. Expression of Gratitude on the Conclusion of Peace Talks 358
79. Remarks during the Abu Dhabi Sustainability Summit 361
80. Remarks at the Opening of the 17th Internet Governance 365
81. Acceptance Statement for the Outstanding African Leadership Award 371
82. Statement at the 36th Ordinary Session of the Assembly of the African Union 375
83. Statement at the Pan-African Forum 383
84. Statement on Africa Day 2023 385
85. Speech on the First Extraordinary Session of the General Assembly of the Organization of Education Cooperation 389

86. Remarks at the ‘Summit of all Neighboring Countries of Sudan’ in Egypt. 393
87. Remarks at the UN Food Systems Summit +2

Stocktaking Moment. 397
88. BRICS Summit Remarks 403

## ክፍል አራት ፤ የሲዳምኛ መልዕክቶች

89. Ayidde cambalaalla! 409

## ክፍል አምስት ፡ Arabic Statements

الشعب السوداني يتمتع بالحكمة والقدرة الكافيتين لحل الأزمة الحالية 413
أثيوبيا تحذر الجهات التي تعمل في التحريض والوقيعة بينها وبين السودان الشقيق 415

# መግቢያ

<አንበሶች የራሳቸውን ታሪክ እስካልጻፉ ድረስ የአዳኝና ታዳኝ ትረካ ምንጊዜም ለአዳኙ ማድላቱ የማይቀር ነው> የሚል ቁጭት የተሞላ የአፍሪካውያን አባባል አለ። በአፍሪካ የታሪክ አጻጻፍ አውሮፓውያን ተጽዕኖ አድርገዋል። አብዛኘው የታተመ የአፍሪካውያን ታሪክ የተጻፈው በአውሮፓውያን ቅኝ ገዥዎች ነው። በዚህ የተነሣ በአውሮፓ ቅኝት የተጻፉ፣ ለአፍሪካውያን ሥልጣኔና የነጻነት ትግል ዋጋና ክብር የማይሰጡ አያሌ የታሪክ ድርሳናት አሉ። <የዚህ ዋናው ምክንያት እኛ አፍሪካውያን የራሳችንን ታሪክ ስለማንጽፍ ነው> የሚለው ቁጭት በአፍሪካውያን ለተሰነዱና ለታተሙ የአፍሪካ ታሪኮች ዓይነተኛ ምክንያት ሆኗል።

ታሪክ የክንውኖችን ወይም የክንውን ሠሪዎችን ተከትሎ ይጻፋል። የራሳችንን ታሪክ ከምንጽፍባቸው መንገዶች መካከል አንዱ የመሪዎችን ድርጊቶች፣ ንግግሮች፣ ስምምነቶች፣ ጉብኝቶች፣ ሐሳቦች፣ ግንኙነቶች፣ ወዘተ. በየጊዜው መመዝገብ፣ መሰነድና ማሳተም ነው። እነዚህ ነገሮች ሥራዬ ተብለው በየጊዜው ባለመሰነዳቸውና ባለመታተማቸው በቅርብ ጊዜው የሀገራችን ታሪክ እንኳን ብዙ አከራካሪ የታሪክ ክሥተቶች አሉን። <ነው/ አይደለም፤ ተደርጓል/ አልተደረገም፤ ተብሏል/ አልተባለም፤> እያልን የምንከራከርባቸው። አስገራሚ ነገር ደግሞ እነዚህ ነገሮች ዐሥር ወይም ሃያ ዓመት ያልሞላቸው ናቸው። የዚህ ዋናው መነሻ በጊዜው መዝግቦና አትሞ የማቅረብ ችግር ነው።

የአንድ ሀገር መሪ ንግግሮች ቢያንስ ሦስት ነገሮችን ያመለክታሉ። የመሪውን አቋምና ሐሳቦች፤ የሀገሪቱን አቅጣጫና ፖሊሲ እንዲሁም የዘመኑን ታሪክና ሁኔታ። በዚህ መጽሐፍ የተካተቱት የ2015 ዓም የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶር) ንግግሮች የታተሙበት ምክንያት እነዚህን ሦስት ነገሮች ስለያዙ ነው።
የመሪ ታሪክ የሀገር ታሪክ አካል ነው። ይሄ መጽሐፍ በኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ ውስጥ በ2015 ዓም የተደረጉትን ንግግሮችና የተላለፉትን መልእክቶች በቅደም ተከተላቸው መዝግቦ አስቀምጧል። እነዚህን ንግግሮች ታሪክ አጥኝዎች፤ ፖሊሲ አውጪዎች፤ ሥነ ጽሑፍ አጥኚዎች፤ የፖለቲካ ተመራማሪዎች፤ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ነገር የሚገዳቸው ሁሉ ይፈልጓቸዋል።

በዚህ መጽሐፍ የታተሙት ንግግሮችና መልእክቶች በቦታ ደረጃ የተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎችንና ከኢትዮጵያ ጉዳዮች ጋር የተገናኙ የውጭ ሀገራትን ይሸፍናሉ። በጉዳይ ደረጃ በፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ወታደራዊ እና በውጭ ግንኙነት ጉዳዮች ላይ ያተኩራሉ። በቋንቋ ረገድ በአማርኛ፣ በኦሮምኛ፣ በሲዳምኛ፣ በዓረብኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች የቀረቡ ናቸው። በመጽሐፉ ውስጥ በክፍል አንድ 71፤ በክፍል ሁለት 4፤ በክፍል ሦስት 13፤ በክፍል አራት 1፤ በክፍል አምስት ደግሞ 2፤ በጠቅላላው 91 ንግሮችን/ መልእክቶችን ቀርበዋል።

መጽሐፉ በራሱ ካለው ፋይዳ በተጨማሪ በዚህ ረገድ መሰነድና መታተም ለሚገባቸው ሌሎች ጉዳዮቻችንም አርአያ ይሆናል። በየተቋማቱ ኢትዮጵያ ታሪክ በመሥራት ላይ ናት። ታሪኳን በወቅቱ መመዝገብና ማሳተም፤ ለትውልድም ማትረፍ ደግሞ የአፍሪካውያንን ቁጭት መመለስ ነው።

መልካም ንባብ

# ክፍል አንድ

## የአማርኛ ንግግሮች እና መልዕክቶች




The Road to Science


Science and Technology Museum



# የኢትዮጵያ ሳይንስ ሙዚየም ምርቃት

መስከርም 24 ቀን 2015 ዓ.ም

ዛሬ በጣም ድንቅ የሆነ የሳይንስ ሙዚየም በአዲስ አበባ እምብርት ከወዳጅነት አደባባይ ቀጥሎ ተከፍቷል። ከሙዚየምነቱ ባሻገር የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ፣ ኢትዮ ቴሌኮምና የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር በጋራ በመሆን እጅግ ውብ የሆነ ኤግዚቢሽን አዘጋጅተዋል። እንደዚህ አይነት ስፍራና ኤግዚቢሽን ለረጅም ዓመታት ስንመኝ በተለያዩ ሀገራትም ስናይ የሚያስቀኑን ሁነቶች ነበሩ። ዛሬ በሀገራችን በማየታችን እጅግ ከፍተኛ ደስታ ይሰማናል።

ዋናው መልዕክቴ ይህ የልጆቻችን ስፍራ ነው። ልጆቻችን በቪዲዮ፣ በፊልም ቨርቹዋል የሚያዩዋቸውን ነገሮች በአካል ለመንካት የሚያስችል አውድ ተፈጥሯል።

ይህ ኤግዚቢሽን ምናልባት ለአሥራአምስት ወይም ሃያ ቀን ክፍት ሆኖ ስለሚቆይ ሁሉም የሚችል ቤተሰብ ልጆቹን እያመጣ እንዲያሳይ ራሱም እንዲያይ አደራ ማለት እፈልጋለሁ። ልጆቻችን እንደዚህ አይነት ድንቅ ነገር እያዩ ካደጉ ለመፍጠር፣ የተሻለች ኢትዮጵያን ለመስራት በእጅጉ የሚያነሳሳቸው ነው።

ልጆች ትናንሽ ነገር ኢንስፓየር ስለሚያደርጋቸው እዚህ ውስጥ በርካታ ነገር ሲያዩ የትኛው እነሱን እንደሚያነቃቃ ስለማይታወቅ ቤተሰቦች ጊዜ ወስደው ይህ ቦታ ቀኑን ሙሉ ክፍት ስለሚሆን እየመጡ ማየት አለባቸው፤ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎቻቸውን ማሳየት አለባቸው፤ ተቋማት እየመጡ ማየት አለባቸው። እዚህ ቦታ የሚታየው ኤግዚቢሽን ስለ ግብርናም፣ ስለ ኢንደስትሪም ፣ ስለ ማዕድናት ማውጣት እና ስለ ቱሪዝም የማይነካው ሴክተር ስለሌለ ብዙዎቻችን የምንማርበት፣ የምንደመምበት ምናልባትም ደግሞ ሃሳቦች ካሉን የምናጋራበት የቢዝነስ ሃሳብ ያላቸው ሰዎችም እዚህ ካሉ የፈጠራ ሃሳቦችን (start-up) ከሚያቀርቡ ወጣቶች ጋር በመሆን በመተባበር የጋራ ኩባንያ፣ የጋራ ቢዝነስ የሚፈጥሩበት አውድ ስለሆነ ኢትዮጵያዊያን ይህን እድል በስፋት እንዲጠቀሙበት ማሳሰብ እፈልጋለሁ። እኔ እጅግ በጣም ደስተኛ ነኝ።

ከዚህ ቀደም በቻይና ወይም በዱባይ የማየውን ነገር በሀገሬ ማየት ችያለሁ።

ዛሬ ይህም ስለሆነ እግዚአብሔርን እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ። ኢትዮጵያዊያን እንኳን ደስ ያላችሁ ! እየመጣችሁ በዚህ ስፍራ እንድትማሩ፣ እንድታስተምሩ፣ ሃሳብ እንድታጋሩና ልጆቻችሁን ኢንስፓየር እንድታደርጉ አደራ ማለት እፈልጋለሁ።
አመሰግናለሁ።

**መስከርም 24 ቀን 2015 ዓ.ም**
**የኢትዮጵያ ሳይንስ ሙዚየም**

# በአማራ ክልል ማዕከላዊ ጎንደር ዞን የማሳ ጉብኝት

ጥቅምት 7 ቀን 2015 ዓ.ም

የመንግስታችን ዋነኛ ፍላጎትና ዓላማ ሁለንተናዊ ልማት ነው። ሁለንተናዊ ልማት ስንል ከዚህ ቀደም ይታወቅ የነበረውን የቡና፣ የአበባ፣ የጫት ወጪ ንግድ ማስፋት ነው። በስንዴም፣ በአኩሪ አተርም፣ በሰሊጥም፣ በጥጥም፣ በሩዝም ዘርፍ ከውጭ የምናስገባውን ብቻ ማስቀረት ሳይሆን ወደ ውጭ ለመላክ የሚያስችል አቅም ኢትዮጵያ ውስጥ አለ። የሰው ኃይሉም፣ መሬቱም፣ ውሃውም ስላለ፤ ያን በመጠቀም ያለንበትን የተረጂነት፣ የለማኝነትና የሴፍቲኔት መንፈስ ማጥፋት ነው። በጣም አደገኛው በሽታ እዚህ ሀገር ላይ ሰው የሚያየው አኩሪ አተሩን ነው፤ የማያየው ነገር ግን ይህን የመሰለ ለም አፈር ይዘን ነው ስንዴ የምንለምነው። ይህን የመሰለ ለም አፈር ይዞ ስንዴ ከመለመን በላይ የከፋ ሃጥያት የለም። ዓለም ላይ እኛ ስንዴ የምንለምናቸው እንደኛ አይነት ለም የሆነ እንደ ዳቦ የሚቦጨቅ አፈር የላቸውም።

እኛ በተፈጥሮ የታደልን ህዝቦች ነን፤ ትንሽ መንፈሳችንን ሰብሰብ አድርገን ውስጣችንን አረጋግተን አንድ ሆነን ብንለፋ፣ ብንሰራ ከኢትዮጵያ ተርፎ ለሌሎች የሚበቃ ነገር እንዳለን የሚያሳዩ ብዙ ምልክቶች አሉ። ለምሳሌ አኩሪ አተርን ብንወስድ አምና በአማራ ክልል የታረሰው ሰማንያ ሺህ ሄክታር ገደማ ነበር። ዘንድሮ ከሁለት መቶ አርባ ስምንት ሺህ ሄክታር በላይ ነው፤ ይህም ሶስት እጥፍ ማለት ነው።

ስንዴም አምና ከታረሰው ከእጥፍ በላይ ነው እየታረሰ ያለው። ይህ የሚያሳው አሁንም በአማራ ክልል ማልማት ከምንችለው ገና ብዙ ያልተነካ እንዳለና ውስን አቅማችንን ብቻ መጠቀማችንን ነው። ዘንድሮ ኢትዮጵያ ስንዴ ለውጪ ገበያ ታቀርባለች ሲባል ብዙ ሰዎች ግር ይላቸዋል፤ ግር እንዳይላቸው ወጣ ብለው ማየት ነው። ሲፈልጉ ወደ ሶማሌ፣ ሲፈልጉ ወደ አፋር፣ ሲፈልጉ ወደ ኦሮሚያ፣ ሲፈልጉ ወደ አማራ ሁሉም ቦታ ላይ እንደዚህ አስደማሚ ማሳ አለ። በእዚህ ቦታ በጣም የገረመኝና ደስም ያለኝ ነገር የአኩሪ አተር መመረት አይደለም ኩታ ገጠም መሆኑ ነው። ኩታ ገጠም ለግብዓት የሚመች፣ ለማሽነሪ የሚመች፣ አርሶ አደሩ በሄክታር የሚያመርተውን ምርት በከፍተኛ ሁኔታ የሚጨምር ነው።

እንደምታውቁት ዓለም ሁሉ የሚፈልገው ስለ አኩሪ አተር፣ ስለ ቡና፣ ስለ አበባ እንድናወራ አይደለም። ዓለም ሁሉ የሚፈልገው ሌላ ጉዳይ ነው። እኛ ያለንበት ዘመቻ ግን አኩሪ አተርን ማስፋት፣ ስንዴን ማስፋት፣ በቆሎን ማስፋት፣ ጤፍን ማስፋት፤ ኢትዮጵያዊያንን ማጥገብ ከዚያም ሲተርፍ ደግሞ ለሌሎች የሚፈስ ማድረግ ነው።

ደግሞም እንችላለን፤ አምና እና ዘንድሮ ያለው የውጤት ልዩነት ይህን ያመላክታል። በሀገር ደረጃ አምና ክረምት 63 ሚሊዮን ኩንታል ገደማ ስንዴ ነው ያገኘነው፤ ዘንድሮ 110 ሚሊዮን ኩንታል በላይ እናገኛለን። ይህም እጥፍ ማለት ነው። ይህንን ያሳካነው የግብርና ዘርፉን የሚመሩ ወጣት ምሁራንን ከየዩኒቨርሲቲው እያሰባሰበን፣ ከአርሶአደሮች ጋር ተቀራርበን የሙያ ድጋፍ እያደረግን፣ ሁላችንም እንደምናውቀው አቅም በፈቀደ መጠን መንግሥት ማዳበሪያ ላይ ከፍተኛ ድጋፍ በማድረግ ከህዝባችን ጋር በመሆን ነው የሚያጠግብ ምርት እያመረትን ያለነው ። ከህዝባችን ጋር ሆነን ጠላትን እናሸንፋለን፣ ከህዝባችን ጋር ሆነን ድህነትን እናሸንፋለን፣ ከህዝባችን ጋር ሆነን ጠግበን እናጠግባለን፤ ከህዝብ ስንነጠል ግን ያ ሁሉ ይቀራል።

እናም ሚኒስትሮቻችን በጎንደር በነበረው የመጀመሪያ የሩብ ዓመት የሥራ ግምገማ ላይ ያለንን የሥራ አፈጻጸም አይተናል፤ በመስክ ደግሞ ያለው የአርሶ አደሮቻችን ጥረት ይህን ይመስላል። ይህን አርሶ አደር መደገፍ፣ ካመረተ በኋላ ገበያ ማመቻቸት፣ ሸጦ ህይወቱ እንዲቀየር ማድረግ፣ መንገድ፣ ውሃ፣ መብራት እንዲያገኝ ማድረግ የእኛ ቀዳሚ ተግባር መሆን አለበት። መስራት አለብን ፣ መሸጥ አለብን ፣ ማትረፍ አለብን፣ ህይወትን መቀየር አለብን። ይህ ጅማሮ ለኢትዮጵያ ብልጽግና እውን መሆን የሚያስችል መሰረት እየተጣለ መሆኑን ያሳያል ። ባየነው ነገር በጣም ደስተኞች ነን፣ እጅግም ኮርተናል፤ እንኳንም ጠገዴ እንደዚህ አይነት የጥጋብ፣ የምርት፣ የልምላሜ ሀገር ሆነ። ነገር ግን ገና ብዙ ያልተነካ ወንዝ ደግሞ አይተናል፣ ብዙ ጅረቶች አሉ፣ ወንዞች አሉ። እነሱን በፓምፕ በመጠቀም እንደዚህ አይነት ሰብል ብቻ ሳይሆን ፍራፍሬም ቴምርም ቢሞከር ተስፋ ያለው ይመስለኛል። አዳዲስ ምርቶች እየጨመርን ለገበያም እንዲሆን ለእኛም የምግብ አማራጭ እንዲሆን አድርገን ብንሰራ ባጠረ ጊዜ ውስጥ ራሳችንን እንችላለን።

ኢትዮጵያ ውስጥ ምርት ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ጥጋብ ፣ ኢትዮጵያ ወስጥ የተትረፈረፈ ነገር ማምረት እንደሚቻል ብዙዎች አያምኑም ፤ እንኳን እነሱ እኛም ራሱ አላመንም። በዓለማቀፍ ዜና ላይ ሰምታችሁ እንደሆን፤ ዘንድሮ በምስራቅ አፍሪካ ድርቅ ይከሰታል

ነው የሚባለው፤ በሌላ በኩል በምስራቅ አፍሪካ በተለይም በኢትዮጵያ እንደዘንድሮ ክረምት እስከ ጥቅምት አጋማሽ ዘንቦ ግን አያውቅም። እስከ ጥቅምት አጋማሽ ዘንቦ ምርት እንደዚህ ተትረፍርፎ እያየን፤ እነሱ ግን ድርቅ ነው ይሉናል። እኛ ድርቅ የለብንም እየሰራን እየለፋን ነው፤ ያለንን ተካፍለን በልተን ጠግበን እናድራለን። የቸገረው ካለም እናካፍላለን። ዋናው የምንፈልገው ግን በእኛ ጉዳይ እየገቡ የሌለውን ነገር እንዳለ አስመስለው የሚያንቦጫርቁ ኃይሎች እጃቸውን ይሰብስቡ፤ ኢትዮጵያ ምንም ደሀ ብትሆን ክብሯን የምትጠብቅ ሀገር ስለሆነች ሠርታ መብላትም የሚያስችል ብቃትም ስላላት ይሄንን ተገንዝበው በተከባበረ መንፈስ አብረን ለመኖር ዝግጁ መሆናችንን ለተቀረው ዓለም መግለጽ እፈልጋለሁ። እጅግ ደስ የሚል ሥራ ነው፤ እንኳን ደስ ያላችሁ! በርቱና አምርቱ፣ ህዝባችንን እናጥግብ፣ ሸጠን እናትርፍ፣ ልጆቻችን ይደጉ፣ ሀገር ደግሞ በብልጽግና ትቁም። ለዚህ ደግሞ የእናንተ ጥረት እጅግ አስፈላጊ ስለሆነ በርቱ ተበራቱ፤ በጣም ደስ ብሎናል ።

**ጥቅምት 7 ቀን 2015 ዓ.ም**
**ማዕከላዊ ጎንደር ዞን**





# በቡራዩ የተሰጥዖ ማበልፀጊያ ትምህርት ቤት የምረቃ ሥነሥርዓት

ጥቅምት 10 ቀን 2015 ዓ.ም

**ክቡር አቶ በለጠ ሞላ፤**
**ክቡር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ፤**
**የተከበራችሁ እንግዶች፤**

ይህንን አካባቢ በልጅነቴ ነው የማውቀው። በርከት ያሉ ቤተሰቦቼና ዘመዶቼ እዚህ አካባቢ ስላሉና ቡራዩ ከማርያም እስከ ገፈርሳ፣ ከገፈርሳ እስከ መናገሻ በጣም አስቸጋሪ መንገድ ነው የነበረው፤ በሎንችና ነበር የሚኬደው። አሁን ተለውጣ እንደዚህ በማየቴ በጣም ደስ ብሎኛል። የቡራዩ ሰዎችም እንኳን ደስያላችሁ። እንግዲህ ታለንት ወይም ልዩ ተሰጥኦ ሁሉም ሰው አለው፣ ሁሉም ሰው የማይቆጠር አቅም (infinite potential ) አለው ፣ ልዩ ችሎታ የሌለው ሰው የለም። ነገር ግን ደግሞ ከመቶ ሺህ፣ ከሚሊዮን አንድ እጅግ ወጣ ያለ ተሰጥኦ ያላቸው ሰዎች አሉ። እነዚህ ሰዎች sub-conscios የአእምሯቸው ክፍል የሌለን ለሰዎች ማስረዳት የማይችሉትን ነገር ያያል imaginary አቅማቸው ከፍ ያለ ማለት ነው። ያን ያዩትን ነገር ለሌሎች ለማሳየት ሲሰቃዩ ይጠፋሉ፣ ሌሎች ሳያዩላቸው እነሱ አይተውታል፣ ያዩት የማይጨበጥና የማይዳሰስ በጭንቅላት ውስጥ ያለውን ምስል ለሌሎች ለማሳየት መከራ ይበላሉ፤ ብዙዎች ይጠፋሉ። በፈጠራ ሥራዎቻቸው የሚታወቁት ቶማስ ኤዲሰን፣ አልበርት አንስታይን፣ ኒኮላ ቴስላ ሀገሮቻቸው ስላልተመቿቸው ሌላ ሀገራት ሄደው ነው የፈጠሩት። ብዙዎቹ አካባቢያቸው ለመፍጠር ስላማይመች መሰደድ ግድ ይሆንባቸዋል። እንደ አሜሪካ ሻል ያለ ሀገር የተወለዱ ሰዎች ደግሞ ያለው የትምህርት ሥርዓት የነሱን ፈጠራ ለማውጣት ስለማይመች ከሥርዓቱ ይወጣሉ።

ግልን የፈጠረው ሰው ትምህርቱን ያቋረጠ ሰው ነው፣ አልጨረሰም ሲስተሙ አያስቀጥልም።

አፕልን የፈጠረው ሰው የዩኒቨርሲቲ ትምህርቱን መጨረስ አልቻለም፣ አቋርጧል፤ ምክንያቱም ሥርዓቱ አያስቀጥልም። በትምህርት ሚኒስቴር ሥርዓት ብቻ ከቀጠልን

ብዙ የፈጠራ ሰዎች ይሞታሉ፤ ትምህርት ፈጠራን የሚያበረታታ ብቻ ሳይሆን ፈጣሪዎችንም የሚገድል አውድ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም እዚያ ያለው መምህርና ህልሙን ያየው ሰው አንድን ነገር እኩል ስለማያዩ ነው። አማራጭ የታለንት ሴንተር ያስፈልገናል። ይሄ ብዙዎችን መፍጠር እንደሚችል ዛሬ ያየነው በቂ ነው። ለምሳሌ ግብርናን በሚመለከት የኮምፖስትን፣ ማዳበሪያ ላይ ጥረት የሚያደርጉ ሰዎችን፣ ውሃ የሚቆፍሩ ለመስኖ የሚውል ሥራ የሚያሳዩ ሰዎች፣ በቆሎ የሚፈለፍሉ፣ ቡና የሚፈለፍሉና በጣም በርካታ ለግብርና ሥራ የሚውሉና የኢትዮጵያን አርሶ አደሮች ሥራ የሚያቀሉ ነገሮችን አይተናል። ሳይንስ ብትሉ ላውንቸር አለ፣ ስፔስ አለ፣ ድሮን አለ፣ መኪና አለ፣ ኤሌክትሮኒክስ ሙከራዎችም አሉ። በዚህ ስፍራ ዞረን እንኳን ያየነው እጅግ ተስፋ ሰጪ ነው።

ይሄ ነገር ኢትዮጵያ ውስጥ መበራከት አለበት፣ የኢትዮጵያን የድህነት ምስጢር የሚያውቁ፣ አርቀው የሚያዩ ኢማጅነሪ አቅም ያላቸውን ሰዎች መቀበል አለመቻሏ ብቻ ነው። አትቀበልም ኢትዮጵያ ። የተለየ ሲሆን ወይ በሃይማኖት ወይ በፖለቲካ ታገላለች። እነሱ ሲጠፉ ባለበት ሂድ ዳዴ ይሆናል። ስለሆነም በርከት ያሉ  የሚችሉ ሰዎች ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳሉ የኢትዮጵያ  የለውጥ ሀብት ደግሞ እነሱ እንደሆኑ፣ ሀገራችን እንድትቀየር ወጣ ያለ ሃሳብ ያላቸውን ሰዎች የሚያበረታታ አውድ መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን አምነን በእጅጉ ማገዝ ይኖርብናል። ክቡር አቶ በለጠ ይህ ቦታ በቂ አይደለም። ኢትዮጵያ ቢያንስ አስር፣ ሃያ ያስፈልጋታል። ይሄ የዘገየበትን ምስጢር እርስዎ ስለገለጹ መልሼ አልገባበትም። ነገር ግን ዶ/ር ጌታሁንን፣ ዶ/ር አብርሃምን እንዲሁም አቶ በለጠን እጅግ አድርጌ ማመስገን እፈልጋለሁ።

ይህን ሃሳብ ሳይንስ ሚኒስቴር እያለሁ ነበር የጀመርነው። ያው የኢማጂነሪ አቅም ውጤት ነው። ማጨናገፍ ብቻ ስለሚፈለግ ነበር፣ ያኔ ሥራው እንዳያልቅ ነበር እኔ የተባረርኩት። ግን ቀጥሎ የመጡ ሰዎች ማስጨረስ ስለቻሉ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ። የአሁን የሳይንስ ሙዚየም ሰሞኑን ያያችሁትም እዛው ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር እያለሁ የተጀመረ ነገር ነው። ግን ማስቀጠል ችግር ስለነበረ ነው እድል ሲገኝ እንደገና መስራት የተሞከረው። በየቦታው ሳይንስን፣ እውቀትን፣ የተለየ ሃሳብ ያላቸውን ሰዎች መሸከም መቻል መልመድ አለብን።

የተከበራችሁ የቡራዩ ሰዎች እኔ በፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ እና በአቶ በለጠ ሞላ መካከል ቁጭ ብዬ ስለ አንድ ፕሮጀክት ስናውራ ማየትን በቀላሉ መውሰድ የለባችሁም።

ኢትዮጵያ ይሄ ልምምድ የላትም፤ ኢትዮጵያ ባለፉት ሰላሳ፣ አርባ፣ ሃምሳ ዓመታት የተለየ ሃሳብ ያላቸውን ሰዎች አብሮ ለመስራት፣ አብሮ ለመቀመጥ፣ ለመደማመጥ ዝግጁ ስላልነበረች ብዙ መከራ አይተናል። ይሄ ልምምድ ማደግ አለበት። የተለያየ ሃሳብ ያላቸው እምነትና ፍላጎት ያላቸው ሰዎች ለአንድ ሀገር በጋራ የሚሰሩበትን ነገር ማስፋት ያስፈልጋል።

እኛ ባለፈው ዓመት መንግሥት ስንመሰርት ለሙከራ የጀመርነው ነገር እጅግ ውጤታማ ሆኖ ነው ያየነው። አቶ በለጠ ሞላ የአማራ ብሄራዊ ንቅናቄ ሊቀመንበር ናቸው አብን እና ብልጽግና ጎን ለጎን መቀመጥ የሚቸገሩ ናቸው። ታውቃላችሁ የነበረውን ውጥረት። ነገር ግን አቶ በለጠ ሞላ ይህን የመሰለ ተቋም እንዳይሞት፣ እንዲያብብ፣ ፍሬ እንዲያፈራ እንዲሁም ውጤታማ እንዲሆን ቀጥተኛ አመራር ሰጥተዋል። ስለዚህ አብን መሆን ለኢትዮጵያ ማገልገልን የሚከለክል አለመሆኑን በተግባር አሳይተዋል።

ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋም እንዲሁ በሀገራቸው መኖር እስኪሳናቸው ድረስ በሚያፈልቁት እሳቤ ከመንግሥት ጋር ሳይሆን በከተማቸው መኖር ተስኗቸው ነበር። ሸፍተውም ነበር እንደምታውቁት። ከዛ ከሸፈቱበት ቦታ ከመጡ በኋላ የትምህርት ሥርዓቱን ለማዘመን ለመቀየር እያደረጉ ያለው ጥረት አሁን መላው የኢትዮጵያ ህዝብ የሚገነዘበው ይመስለኛል። የሚያውቁ ሰዎች ብልጽግናም ባይሆኑ፣ የሚያውቁ ሰዎች የእኛን አስተሳሰብ ተከታይ ባይሆኑም በጋራ መስራት መለማመድ ያስፈልጋል።

ከዚህም ባሻገር ቡራዩ በጣም የሚያምር መልክዓ ምድር ያለው ቦታ ነው፤ ገፈርሳ እዚሁ ቅርብ ነው ያለው፣ መናገሻ ብትሄዱ ሱባን የመሰለ እጅግ አስደማሚ ደን አለው። ሱባ ሶስት መቶና አራት መቶ ዓመታት የቆዩ በጣም እድሜ ጠገብ የሆኑ ዛፎች ያሉበት ቦታ ነው። አንድ ሰው አሁን ከዚህ ተነስቶ ሱባ ቢሄድ በጣም ቅርብ ነው ቦታው። ኢትዮጵያ ውስጥ ነው ብሎ አያስብም። እጅግ አስደማሚ የተፈጥሮ ጸጋ ያለበት ነው። ነገር ግን ከመናገሻ ጀርባ ጀምሮ ወደ ሱባ አካባቢ ብትሄዱ አርሶ አደሮች ንጹህ ውሃና መብራት ዛሬም የላቸውም፤ በጨለማ ውስጥ ይኖራሉ ፣ ስልክ የላቸውም እዚሁ መናገሻ ውስጥ። ይሄ የሚቀየረው በፖለቲካ ወሬ አይደለም በፈጠራ ነው፤ ይሄ የሚቀየረው መፍጠር የሚችሉ ሰዎችን ይበልጥ ሃሳባቸውን የሚያሳዩበት አውድ መፍጠር በመቻል ነው።

ቅድም እንዳያችሁት ከደምቢዶሎ የመጡ ድሮን፣ ሮኬት ላውንቸርና በርካታ የፈጠራ ስራዎች የሚሰሩ ልጆች አይተናል። ደምቢዶሎን ሰው የሚያስበው በግጭት ነው። ወለጋ ውስጥ ብዙ መፍጠር የሚችሉ ሰዎች አሉ። በየቦታው ያሉትን ሰዎች

አስሰን አውጥተን ሃሳባቸውን ማሳየት እንዲችሉ ካደረግን እነሱም ይጠቀማሉ፤ እኛም እንደሀገር እናተርፋለን። ዋናው ነገር የሰከነ፣ የሚደማመጥ፣ አብሮ መቆም የሚችል፣ በዘርና በሃይማኖት የማይገፋፋ፣ አቃፊ የሆነ አስተሳሰብና አሠራር ያስፈልጋል። እናም ይህ አቃፊነት የቡራዩን ስም በመፍጠር በመቀየር ወደፊት ማሳየት የሚችል አካባቢ እንደሚሆን ተስፋ አለኝ። የሚገርመው ነገር በጣም ብዙ ጀግኖችና የተለየ እሳቤ ያላቸው ሰዎች የተፈጠሩባት አካባቢ ናት። ቡራዩ በጣም ታሪክ ጠገብ አካባቢ መሆኗን ተገንዝበን እዚህ ከየትኛውም የኢትዮጵያ ጫፍ የምትመጡ ልጆች ወደ ትክክለኛው መናገሻችሁ እየመጣችሁ እንደሆነ ማወቅ አለባችሁ። መናገሻ የሚለው ስም ራሱ ለብዙዎች መዳረሻ የነበረ መሆኑን የሚያመላክት ስለሆነ ቡራዩ ለሁሉም የሚተርፍ እጅግ ውብ የሆነ ቦታ መሆኑን ተገንዝባችሁ መጥታችሁ እንድትማሩ የዚህ አካባቢ ሰዎች ደግሞ በማቀፍ ስለማትታሙ ልጆቹን እያስተማራችሁ።

ክቡር አቶ በለጠ ሞላ እንኳን ለዚህ ቀን አበቃህ፤ ትልቅ ሥራነው የሰራኸው። የአንዱ ተቃዋሚ ፓርቲ ሊቀመንበር በቅርቡ የትምህርት ስርዓት ፈተናን ለማዘመን እጅግ ድንቅ ሥራ ሠርተዋል። የሌላው ተቃዋሚ ፓርቲ ደግሞ ይህን የመሰለ ማዕከል ጨርሰው አስመርቀዋል። እንዲህ እየተባበርንና እየተከባበርን አብረን ኢትዮጵያን የምናበለጽግ እንድንሆን አደራ እላለሁ።

ላረጋግጥላችሁ የምፈልገው ነገር ግን የኢትዮጵያን ብልጽግና ማቆም የሚችል ማንም ኃይል የለም ፤ ይሄ በጭንቅላታችን ያየነውን ብልጽግና ለብዙዎች እንዲያዩት የምናደርገው ትግልና አንተም በንግግርህ ስህተት ሳይሆን የማሳየት ሂደት እንዳልከው ብልጽግናችንን በእኛው እድሜ እናያለን ተባብረን እንስራ፣ አንድ እንሁን፣ በዘር አንከፋፈል፣ በሃይማኖት አንከፋፈል። ኢትዮጵያ በቂ ሀገር ናት፤ እንዋደድ እንከባበር። በዚህ መንገድ የብልጽግናችን ጉዞ የፈጠነ ይሆናል፤ ቅርብም እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ።

በሰሜን ኢትዮጵያ የተፈጠረው ነገር ይቋጫል፣ ሰላም ይሆናል ኢትዮጵያ ሰላም ትሆናለች፤ እንዲሁ እንደተዋጋን አንቀጥልም። በሰላምና በልማት የትግራይ ወንድሞቻችን ደግሞ ለማልማት በጋራ የምንቆምበት ጊዜ ቅርብ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ። እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ።

**ጥቅምት 10 ቀን 2015 ዓ.ም**

**ቡራዩ**







# የቀዳማዊት እመቤት ጽ/ቤት በጅማ ዞን አኮ ወረዳ ያስገነባው ትቤት የምረቃ ሥነ ሥርዓት

ጥቅምት 11 ቀን 2015 ዓ.ም

ክቡር ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን፣
ክብር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ የትምህርት ሚኒስትር፣
የተከበራችሁ ሚኒስትሮች፤

እንደምታዩት እጅግ ውብ ወደ ሆነች ሀገር ነው የመጣችሁት። ጂማ እጅግ ውብ ናት የውቦች ሀገር ናት። ቀዳማዊት እመቤት ባለፉት ሦስት ዓመታት ከዚህኛው ጋር 26 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ገንብተዋል። ለነዚህ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ግንባታ የበጀት ምንጭ ከመንግሥት ተቋማት እንደ ኢትዮ ቴሌኮም፣ አየር መንገድ ያሉትን አንጠቀምም። ሙሉ በሙሉ የፋይናንስ ምንጩ ከመጽሐፍ ሽያጭ የምናወጣው ነው። በቅርቡም ሦስተኛ መጽሐፍ የመደመር ትውልድ የሚል ትውልዱን የሚያንጽ፣ ትውልዱን የሚገነባ፣ ኢትዮጵያዊነትን የሚያደረጅ እጅግ ጠቃሚ የሆነ መጽሐፍ በዚህ ዓመት ታትሞ ይወጣል። ይህም መጽሐፍ ሲሸጥ ሙሉ በሙሉ ገቢው ለትምህርት ቤቶች ግንባታ ነው የሚውለው። የቀዳማዊት እመቤት ጽ/ቤት በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት የሚሠሯቸውን ትምህርት ቤቶች ወደ ሃምሳ የማሳደግ ፍላጎት ስላላቸው ለዚህ የፋይናንስ ምንጭ እንዲሆን፣ ህዝቡም እንዲታነጽበት የተዘጋጀው መጽሐፍ በቅርቡ ለገበያ ይውላል። ትምህርት ሚኒስቴር፣ ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲሁም በየደረጃው ያሉ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ ግለሰቦችና ተቋማት በትብብር ትምህርት ላይ አተኩረን እንሠራለን።

ትምህርት ቤት እንገነባለን፣ ፈተና እንዳይሰረቅ ጠንከር ያሉ ሥራዎችን እንሠራለን፣ ዩኒቨርሲቲዎቻችን የትምህርት ጥራት ላይ እንዲያተኩሩ እናደርጋለን፤ የሀብት ምንጫችን የሆነው የሰው ኃይል ደግሞ መማር አለበት። ሰው እንዲማር የምንፈልግበት ዋነኛው ዓላማ፣ የብልጽግና ራዕያችን ዋነኛው ዓላማ በሬና ገበሬን መለያየት ነው። በሬና ገበሬ ያላቸው ትስስር ለምግብነት እንጂ ለእርሻ መዋል የለበትም። የኢትዮጵያ አርሶ አደር በሬ መግፋት የለበትም የሚል ታላቅ የሆነ ህልም አለን። ይህም እንዲሳካ ልጆቻችን

መማር አለባቸው። ትራክተር፣ ኮምባይነር ሙያ ይጠይቃሉ። ካልተማርን አይሳካም፤ ከተማርን ግን ምርታማነት ያድጋል። ጂማ በጀመረችው መንፈስ ትምህርት ላይ፣ እርሻ ላይ፣ አግሮ ኢንደስትሪ ላይ አበክራ ትሠራለች ። ጂማ ከተማም የምዕራብ ኢትዮጵያ ፈርጥ ትሆናለች፤ ነበረችም ትሆናለችም።

የጂማ ከተማን በማድቀቅና በማዳከም የምዕራብ ኢትዮጵያን የማደህየቱ ፖሊሲ አብቅቷል። ጂማ ወደ ነበረችበት ከፍታ እንድትመለስ ከማንም የተለየ ሀብት አያስፈልግም። የጂማ ከተማን ወጣቶችና ባለሀብቶች በመያዝ ሃሳብ በማፍለቅ ጂማ ከተማንም፣ ጂማ ዞንንም፣ ኦሮሚያንም፣ ኢትዮጵያንም መቀየር ይቻላል። ነገር ግን የሀብት ምንጫችን ከኢትዮጵያ ውጭ ከየትም አይመጣም፣ የእውቀት ምንጫችን ከኢትዮጵያ ውጭ ከየትም አይመጣም። ከውጭ መጠበቁን ትተን በተሰጠን ፀጋ ተባብረን ኢትዮጵያን እንድናለማ አደራ ማለት እፈልጋለሁ። ክብርት ወ/ሮ ዝናሽ ታያቸው ለሃያ ስድስተኛው ትምህርት ቤት እናመሰግናለን። በቅርቡ ሃምሳ ትምህርት ቤቶች ላይ ደርሰሽ እንደምንገናኝ ተስፋ አደርጋለሁ፤ ኡልፋዳ።

**ጂማ ዞን አኮ ውረዳ**
**ጥቅምት** 11 **ቀን** 2015 **ዓ.ም**

# በእንጦጦ የሥነጥበብ ማዕከል የተዘጋጀው ዐውደርዕይ ጎብኝት

ጥቅምት 15 ቀን 2015 ዓ.ም

አሁን የምንገኘው እንጦጦ ፓርክ ውስጥ የአርት ጋለሪ ተብሎ በተሰራው ስፍራ ነው። በዚህ ቦታ ከዚህ ቀደም የተለያዩ የአርት ስራዎች ለኤግዚቢሽን ቀርበዋል፤ የአሁኑ ግን ከእስከ አሁኑ በእጅጉ የተለየ አቀራረብ ያየሁበት ነው። ቀደም ሲል እንደጎበኘነው የላሊበላን አካባቢና የተሰሩትን አብያተ ክርስትያናትና የታየውን ጥበብ በቨርቹዋል ሪያሊቲ እዛ እንዳለን በስፍራው እንደምንገኝ አድርገው ነው ያዘጋጁት። እናም በጣም ያስደምማል። እኔ ላሊበላን አንድ ሁለት ጊዜ የማየት እድል አግኝቻለሁ። እዚያ ስፍራ እንኳን ስንሄድ በቀላሉ የማናገኛቸውን መረጃዎች ጭምር የያዘ ውስጥ እንዳለን፣ ከሃሳቡ፣ ከአሰራሩና አሁን ያለበትን ደረጃም ወደፊት ምን መደረግ እንዳለበትም በሙሉ የሚያመላክት እጅግ አስደማሚ ሥራ ነው።

እንግዲህ በላሊበላ ሥራ ውስጥ ትውልድ መማር ያለበት፣ መጥቶ ማየት ያለበት፣ ወላጆችም ልጆቻቸውን ማሳየት ያለባቸው አንደኛ የምስለ እይታን (imaginary) አቅም ሰዎች እንዲገነዘቡ ነው ። በእውቀት በኢንፎርሜሽን ብዛት ሳይሆን አንድን የሌለን ነገር በምስለ እይታ በመመልከት እንዴት ሀገርን መለወጥ እንደሚቻል ትምህርት ይወሰድበታል ። ምስለ እይታ (imagination) ግን ብቻውን በቂ አይደለም። ያን ያየነውን ነገር ብዙዎች ያላዩትን ነገር እንዲሆን፣ እንዲከወን አልቆ ተፈጽሞ እንዲታይ ደግሞ መሰጠት (devotion ) ያስፈልጋል፣ ጠንካራ የሥራባህል ያስፈልጋል። እነዚህ ሰዎች የሠሩት ሥራ እንዲሁ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ድፍን አለት፣ ምንም ነገር የሌለው አለት አይተው ከዚህ ውስጥ ቤት፣ ቤተክርስትያን አስደማሚ የሆነ ታሪካዊ ቦታ ሊገነባ ይቻላል ብለው ማመናቸው፤ ያን ለመገንባት ደግሞ ቀን ከሌት መድከማቸው፣ ከደከሙ በኋላም ለአጭር ጊዜ የሚቆይ ነገር ሳይሆን ለመቶ ዓመታት፣ ለሺህ ዓመታት የሚቆይ ነገር ሠርተው አቆይተውናል።

ሶስተኛው ቁልፍ ነገር ያየሁት ከማይታይ ነገር ማየት፣ ያዩትን ሠርቶ ለማሳየት መሞከር ብቻ ሳይሆን በውበት (esthetics) የሚሠሩትን ሥራ አሳምረው አስውበው

መስራት ፤ መስራት ብቻ በቂ አይደለም እምር አድርጎ ለእይታ እንዲሆን አድርጎ መሥራትን በደንብ በላሊበላ ውጥንና ሥራ ውስጥ ይታያል። ከዚህ ትውልድ መማር አለበት። አንደኛ ኢማጂን ማድረግ አለብን ከአለት ውስጥ ፈልቅቀን ተዓምር ልናወጣ እንደምንችል ማየት አለበት። ሁለተኛ ካየን በኋላ ያን ያየነውን እውን ለማድረግ መትጋት አለብን። ከግራ ከቀኝ ያሉትን ድምጾች ሳንሰማ ጆሯችንን ደፍነን መስራት አለብን ካልሰራን ይደናቀፋል። ሶስተኛው ስንሰራ ለአሁን፣ ለዛሬ፣ ለእኔ ሳይሆን ለነገ፣ ለከነገ ወዲያም እንዲሆን አድርገን አርቀን አስውበን ማኖር ይኖርብንናል። እነዚህ ጉዳዮች በጣም አስፈላጊ ናቸው።

አሁን በየቦታው የምናየው ችግር ሌላ ቦታ ያየነውን ነገር መድገም ሳይሆን የሆነ ቦታ ያየነውን ነገር አልቀን ማስቀመጥ መቻል አለብን። ላሊበላ ሃሳቡ እየሩሳሌም ኢትዮጵያ ውስጥ ሊሰራ ይችላል፣ እየሩሳሌም አካባቢ ያሉ ታሪካዊ ነገሮች በላሊበላ አካባቢ ሊቀመጡ ይችላሉ የሚል ቢሆንም ሥራው ግን እጅግ ድንቅ ነው። እየሩሳሌም ውስጥ እንደዚህ አይነት ድንቅ ሥራ ማግኘት የሚቻል አይመስለኝም፤ በጣም  አስደማሚ በመሆኑ መጠበቅ አለበት፣ ማደግ  አለበት። ልክ እንደዚሁ ሰው ወደ መካ ለሃጂ ከሚሄድ እዚሁ መሆን አለበት የሚል ደግሞ ወደ ባሌ አካባቢ ድሬ ሼህ ሁሴንና ሶፍ ኡመር አካባቢ የሚያስደንቅ ሥራ አለ። ኢትዮጵያዊያን ቀደምት አባቶቻችን አንድ ነገር ሌላ ቦታ ሲያዩ ሄዶ ማድነቅ ብቻ ሳይሆን ትምህርት ቀስመው ሀገራቸው ውስጥ ለማኖር፣ አልቀው አሳምሮ ለመስራት ይሞክሩ ነበር። ያነገር አድጎ እንዲቀጥል ባለማድረጋችን ነው ዛሬ ችግር ውስጥ ያለነው። እናም የዛሬው ትውልድ መማር ያለበት ነገር የሆነ ሀገር  ስንዴ ያምራል እኛም ስንዴ ማምረት እንችላለን፣ የሆነ ሀገር አፕል፣ አቮካዶ፣ ፓፓያ ያምራል ያን ማምጣት ሳይሆን ማምረት ይቻላል ፣ የሆነ ሀገር ህንጻዎች ያምራሉ፣ ቴክኖሎጂው ያምራል ለእይታ ይጋብዛል፤ እኛም ሀገር ያን ማድረግ እንችላለን። ይህ ሀገር ውብ ነው።

ውብ ሆኖ እንዲቀጥል ደግሞ የእኛን ኢማጂን የማድረግ አቅምና ሥራ ይጠይቃል የሚለውን ነገር ማሰብ በእጅጉ ይጠይቃል። እንደው መመኘት ብቻ፣ ወደ ሩቅ መሰደድ ብቻ ሳይሆን ያየነውን ነገር በአካባቢያችን ማስቀመጥ እንደሚቻል ጥልቅ እውቀት ይገኝበታል። ብዙዎች መጥተው እንዲጎበኙት አበረታታለሁ፤ በጣም ድንቅ ሥራነው። ቴክኖሎጂ አለ፣ ታሪክ አለ፣ ሥነ ህንጻ አለ፣ ከዚያ ባሻገር አርቆ የማየትና የመተግበር ጉልበት አለ። ሰዎች ይሔን ሁሉ ደምሮ ማየትና ከዚህ ውስጥ ጥቂቱን እንኳን መተግበር ከቻሉ ድንቅ ሀገር መስራት ይቻላል። ዋናው ምስጢር ግን የኢትዮጵያ ብልጽግና፣

የኢትዮጵያ ልማት፣ የኢትዮጵያ እድገት፣ የኢትዮጵያ ሰላም የሚረጋገጠው በልጆቿ ብቻ ነው። ማንም ዋጋ ከፍሎ፤ ጊዜውን ጉልበቱን አጥፍቶ እኛን ሊቀይር አይችልም። እኛ የምንቀየረው በልጆቻችን ነው ብለን ማመን፣ ያ ደግሞ እንዲከወን መተባበር፣ ህልሞች አለማጨናገፍ፣ ራዕዮች አለማጨናገፍ፣ አንዱ ኢማጂን ካደረገ ያን እንዲፈጸም አብሮ መቆም ያስፈልጋል። ሁሉም ሰው ላያይ ይችላል፤ ጥቂቶች ያያሉ፤ አብዛኛው ደግሞ ያን የታየውን ነገር እንዲታይ አድርገው ይሰራሉ። በዚያ መንገድ ሀገር ሊገነባ እንደሚችል እጅግ ተስፋ ሰጪ ነገር ነው ያየሁበት። ጅማሮችን ከዚህ ጋር ይቀራረባል ወደ ኋላ ማየት ካልቻልክ ወደፊት መራመድ ስለሚከብድ።

መኪና ምንም እንኳን ወደፊት የምናይበት ትልቅ መስታወት ቢኖረውም ግራና ቀኝ ትናንሽ እስፖኪዮዎች አሉት፤ ወደፊት ለመንዳት ግራና ቀኝ ወደኋላ የሚያሳዩ እስፖኪዮዎች ያስፈልጋሉ ። ወደኋላ መለስ ብለን እያየን ወደፊት ብንወነጨፍ የለማች፣ የበለጸገች፣ የምታስቀና ብዙዎች የሚጓጉላት ሀገር መፍጠር እንደሚቻል የሚያሳይ ኤግዚቢሽን ነው። ሰዎች መጥተው እንዲያዩ በጣም አበረታታለሁ፣ እኔም በጣም ደስ ብሎኛል። ይህ ልማድ እንዲቀጥል ሌሎቹም ታሪኮችና ታሪካዊ ቅርሶች እንዲሁ እየወጡ ሰዎች ማየት፣ መማር ከዚያ ተነስተው ሀገራቸውን መገንባት እንዲችሉ የምናደርግበት ስፍራ እንዲሆን እመኛለሁ። እንጦጦ በትክክል ሥራውን እየሠራ ነው፤ እጅግ ደስ ብሎኛል አመሰግናለሁ።

**ጥቅምት 15 ቀን 2015 ዓ.ም**
**እንጦጦ ፓርክ - አዲስ አበባ**






ETHIOPIA



# በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት አቅራቢያ ለሕፃናትና ለወጣቶች የሚሆን የስፖርት ማዘውተሪያ አበርክቶ

ጥቅምት 17 ቀን 2015 ዓ.ም

ይህ የክረምት በጎ ፍቃድ ሥራችን አካል ነው። ይህች አነስ ያለች ሜዳ ለረዥም ጊዜ የሰፈር ልጆች የሚጫወቱባት እና አካባቢ የምትገኝ ሜዳ ነች ፤ አቧራማ ነበር፣ አሁን እንደምታዩት የተሻለ ገጽታ ይዟል። ነገር ግን መልዕክቱ ከተማ በህንጻ ብቻ አይገነባም ፣ ከተማ በመንገድ፣ በብሎኬትና በመሰረተ ልማት ብቻ አይገነባም። ለልጆቻችን መዋያ የሚሆን ስፍራ ማበጀት ለአንድ ከተማ ውበትና ለማህበራዊ ትስስር አስፈላጊነቱ ከፍተኛ ነው። አንድ ሰው ሰፈሬ ቀበና ነው፣ ጦር ኃይሎች ነው፣ አራት ኪሎ ነው ብሎ ስም የሚጠራው በዚያ ሰፈር ሲጫወት ሲቦርቅ፣ ከጓደኞቹ ጋር ሲውል፣ የሰፈሩን የአነጋገር ዘዩ፣ የሰፈሩን ባህል፣ በሰፈሩ የሚገኙትን ትላልቅ ሰዎች ስም፣ ምግባር ሲያውቅ ነው።

አሁን ከሀገረ ወጣ ሲል ሰፈሬ ቀበና ነው ሲል ማንን ታውቃለህ ይባላል ፤ የሜዳ ስም ይጠራል፣ በደመራ ጊዜ ያለውን ጨዋታ፣ በኢድ ጊዜ ያለውን ጨዋታ እየተጋራ ነው ሰው ራሱን ከአንድ አካባቢ ጋር አጣብቆ፣ አመሳስሎ፣ አቀራርቦ የሚያየው። ለዚያ ደግሞ እንደዚህ አይነት ቦታ በጣም ያስፈልጋልና ስንገነባ ህንጻ ብቻ፣ ፓርክ ብቻ ሳይሆን የነገው ትውልድ የሚውልበት፣ ጊዜውን የሚያጠፋበት በመልካም የሚታነጽበት አካባቢ መገንባት ከሁላችንም ይጠበቃል።

እንግዲህ አዲስ አበባ ውስጥ ካሉት ኤምባሲዎች ሃያ ወይም ሰላሳው ኤምባሲ ይህችን የምታክል ትናንሽ ስቴዲየም ቢሰራ ሙሉ አዲስ አበባ ውስጥ ወጣቶች መዋያ አይቸገሩም ማለት ነው። ሁለተኛው የግል ሴክተር ባለሀብቶች ህንጻ የሚገነቡ ሰዎች፣ መኪና የሚገዙ ሰዎች መጠንቀቅ ያለባቸው ነገር ለልጆቻችን መዋያ የሚሆን ነገር ካላበጀን እኛ የምንገነባውን ነገር ያፈርሳሉ። ለምሳሌ ባለመኪናዎች አዲስ አበባ ውስጥ ስፖኪዮ ተሰረቀብን ይላሉ። ወደፊትም ማህበረሰብ እንደ ማህበረሰብ ለወል ሃብት ጥበቃ የማያደርግ ከሆነ በፖሊስ ጥበቃ ብቻ ስፖኪዮ መጠበቅ አይቻልም። ስፖኪዮ የምትጠብቀው ልጆች እንዳይሰርቁ፣ ትምህረት ቤት እንዲሄዱ፣ ትምህርት ቤት ሲሆዱ ምግብ እንዳያጡ ምግብ ካቀረብክላቸው፣ መማር ከቻሉ፤ ሰፈር ሲመጡ የሚጫወቱበት

የሚገናኙበት ቦታ ካላቸው ተስፋ ይሰንቃሉ፤ ተስፋ የሰነቀ ሰው ወደ ሌብነት አይገባም። እናም ስፖኪዮ እንደይሰረቅ የምንፈልግ ሰዎች፣ ቤት እንዳይሰረሰር የምንፈልግ ሰዎች፣ ከኪስ ገንዘብ እና ሞባይል እንዳይጠፋ የምንፈልግ ሰዎች ወጣቶች መዋያ ያስፈልጋቸዋል፣ መልካም ነገር ማየት ይገባቸዋል፣ ሊጋሩት የሚገባ እሴት፣ ተስፋ የሚሰጥ እና እድገትን የሚያመላክት መሆን አለበት ብለን ካልሰራን በስተቀር፤ ትውልድ መዋያ ካጣ ሰው ህንጻ እያየ በደስታ መኖር ያስቸግራል። ሁለተኛው በዚህ አካባቢ እንደሚታየው ገስት ሃውሶች እና ህንጻዎች አሉ። እነዚህ ህንጻዎች ለኔ የውበት ምንጭ መሆን አለባቸው እኔም ለእነሱ ውበት ምንጭ መሆን አለብኝ፤ እነሱም እኔን ነው የሚያዩት እኔም እነሱን ነው የማየው አንዱ ለሌላው ቪው ነው።

አንዱ ለሌላው መዝናኛ ነው፤ እኔ ህንጻ ሠርቼ በአካባቢዬ ልጆች አቧራ ላይ ኳስ የሚጫወቱ ከሆነ፣ ዛፍ የማይተከል ከሆነ፣ ፊትለፊት ያለው ቤት መስታወት የሚያንጸባርቅ ከሆነ የራሴን ቤት እጠላዋለሁ ፤ የእኔን ቤት እንድወደው ጎረቤቴ እኔን መምሰል አለበት፣ የኔ ቤት በሰላም እንዲያድር የሰፈር ልጆች መዋያ፣ መጫወቻና መማሪያ ስፍራ ሊኖራቸው ይገባል። እናም በበጎፈቃድ በድፍን ኢትዮጵያ በርከት ያሉ መዋዕለህጻናት እየተገነቡ ነው፣ አንደኛ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እየተገነቡ ነው፣ ዛሬ ላይ ከዘጠኝ ሚሊዮን በላይ ተማሪዎችን በሀገርአቀፍ ደረጃ በቀን ሁለት ጊዜ እንመግባለን፤ ፓርኮች እየሰራን ነው። እንዲዚህ ያሉ ቦታዎች ደግሞ እየተበራከቱ ሲሄዱ ልጆቻችን መዋያ ሲያገኙ ከጥፋት ይመለሳሉ ። የአዲስ አበባ ከተማ ይህንን ሥራ እንደምሳሌ በመውሰድ እንደሚያስፋፋው ፤ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ያሉ ኤምባሲዎች ይህንን ሥራ እንደምሳሌ በመውሰድ እንደሚያስፋፉት፤ ሃብታሞችም እንዲሁ እንደሚያደረጉ ተስፋ አደርጋለሁ።

እንደዚህ እያደረግን ከሄድን ትውልድ ይገነባል፣ እንደዚህ እያደረግን ከሄድን ኢትዮጵያዊነት ፈር እየያዘ መስመር እየያዘ ፣ መሰረት እየያዘ ይሄዳል ። አሁን ያሉብን መከራዎችና ችግሮች ባልተገነባ ትውልድ፣ ባልተሰራ ትውልድ የሚመጣ መሆኑን አውቀን ነገ ሰላም፣ ብልጽግና እንዲመጣ ከፈለግን መጪውን ትውልድ መገንባት ያስፈልጋል። ለዚያ ደግሞ እንደዚህ ያሉ ነገሮች እጅግ አስፈላጊ ናቸው። ብዙ ዋጋ የሚጠይቅ ሳይሆን ረከስ ባለ መንገድ የተሰራ ነው ፤ የነበረውም የህዝብ ነው የሰፈር ልጆች መጫወቻ ነው አሁንም የእነሱ ነው ። እኛ ያደረግነው ነገር ዛፍ ተከልን፣ አጥር አጠርን፣ የተወሰኑ መቀመጫዎችን ሰራንላቸው፣ ሻወር መታጠቢያ አዘጋጀንላቸው፣ ይህንን ሰው ሰራሽ ሳር አለበስንላቸው። ባጭሩ ልጆች መጥተው ሲጫወቱ ጉዳት

ሳይደርስባቸው፣ በሰፈራቸው በሃገራቸው ኮርተው እንዲሄዱ የሚያደርግና ለሌሎችም ትምህርት የሚሆን ነገር ነው የተሰራው። እንግዲህ ያየነው ነገር እንዲሰፋ አዲስ አበባ ውስጥ መቶ ሁለት መቶ፣ ሶስት መቶ ያስፈልጋል፤ በየሰፈሩና በየትምህርት ቤቱ። ብዙዎች ይህንን ሥራ እንደምሳሌ ወስደው እንዲረባረቡና ትውልድ እንድናንጽ፣ ትውልድ እንድንገነባ፣ ተስፋ እንድንሰንቅ እና ወደ ላቀ ደረጃ ለመሸጋገር እንድንዘጋጅ ነው አደራ ማለት የምፈልገው።

በተደጋጋሚ እንዳልኩት ስለ ኢትዮጵያ ያላቸው ትርጓሜ እኛ ካለን ጋር በጣም የተለያየ ነው፤ ብዙዎች የሚያወሩት ስለመራባችን ነው፤ እኛ የምናወራው ስለመበልጸጋችን ነው። ብዙዎች የሚያወሩት ስለመደህየታችንና መሰደዳችን ነው፤ እኛ የምናወራው ብዙዎችን መሳብ የሚያስችል አቅም ያላት ኢትዮጵያ እንዳለች ነው። የማንኛው አሸንፎ እንደሚወጣ አብረን እናያለን። ኢትዮጵያ ትበለጽጋለች፣ የኢትዮጵያ ሰላም ይረጋገጣል፣ የኢትዮጵያ ልጆች ይፈጥራሉ፣ በሳይንስ ይታነጻሉ፤ የበለጸገች ያደገች የአፍሪካ ኩራት የሆነች ኢትዮጵያን ለልጆቻችን ለማስረከብ ነው የምንጣጣረው፤ የሚሆነውም እሱ ነው። እናም እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ። ደስ ብሎኛል ልጆቻችን መልካም ጊዜ ይሁንላችሁ፤ ተጫውተው ጠንክረው በርትተው ሀገር ለመጠበቅ፣ ለመርዳት ለማነጽ የሚበቁ ያድረጋቸው፤ አመሰግናለሁ።

**ጥቅምት 17 ቀን 2015 ዓ.ም**
**አዲስ አበባ**




CLAAS
TUCANO

# በምሥራቅ ሸዋ ዞን ዱግዳ ቦራ በኩታ ገጠም የለማ የስንዴ ማሳ ጉብኝት

ጥቅምት 19 ቀን 2015 ዓ.ም

ለኢትዮጵያ ህዝብ መናገር የምፈልገው <<እንችላለን>> እኛ ኢትዮጵያዊያን ማሰብ እንችላለን፣ ያለንን ጉልበት እውቀትና ሀብት ማሰባሰብ እንችላለን፣ መደጋገፍ እንችላለን፣ አብረን መቆም እንችላለን፣ ያሰብነውን ለማሳካት መትጋት እንችላለን ። ብዙዎች ቢያናንቁትም እኛ ሰብሰብ ብለን አብረን ተጋግዘን መቆም በመቻላችን አስደማሚ ውጤት ልናመጣ እንችላለን። ዛሬ በስንዴ ያየነውን ውጤት ነገ በብዙ ዘርፍ መድገም እንችላለን፤ ፎርሙላው አንድ ነው፤ ፎርሙላው ሀሳብ ያለን፣ እውቀት ያለን፣ ጉልበትና ያለን አቅም ሰብሰብ ማድረግ፣ በጋራ መትጋትና ለአንድ ራዕይ መቆም ከቻልን በብዙ ዘርፎች የተሳካ ሥራ ልንሠራ እንደምንችል በቂ ማመላከቻ ነው ዛሬ ምናየው። ብዙ ጊዜ ሰዎች ስንዴ፣ ስንዴ ሲባል ግራ ይጋባሉ። እኛ ደጋግመን እንደ መግቢያ ነጥብ (entry point) የመጀመሪያ ስራችን ስንዴ ያልንበት ምክንያት ስንዴ ብስኩት ነው፣ ስንዴ ዳቦ ነው፣ ስንዴ መኮረኒ ነው፣ ስንዴ ቆሎ ነው፣ ቂንጬ ነው ለብዙ ምግብነት መዋል የሚችል ነገር ነው።

እኛ ባለን ጥናት ከአሥራሁለት አይነት በላይ የምግብ አይነቶች ከስንዴ ውስጥ ይወጣሉ፤ ኢትዮጵያዊያን ደግሞ ባላቸው ማዕድ ላይ በአንድም ወይም በሌላ መንገድ ቀላል የማይባል ድርሻ ያለው ስለሆነ ነው ስንዴን እንደመጀመሪያ የወሰድነው። እንጂ በቡናም በጣም የሚገርም ነገር ነው ያለው። ዛሬ ኢትዮጵያ  አምና ከለቀምነው ቡና ከግማሽ ቢሊየን ዶላር በላይ የሚበልጥ ቡና ወደ ውጭ ለመላክ የሚያስችል አቅም አላት፣ ያልወጣ አቅም። የቡና ወደ ውጭ የመላክ አቅም ብቻ ሳይሆን ምርት የምንሰበስብበት አቅምም በከፍተኛ ደረጃ አድጓል፤ ነገር ግን ስንዴን ከቡናም፣ ከማንጎም፣ ከአቡካዶም፣ ከፓፓያም ለየት አድርገን የተነሳነው በማዕዳችን ላይ ከምናያቸው ምግቦች ውስጥ በአንድም ይሁን በሌላ የሚታይ ስለሆነ ነው።

ሁለተኛው ሃሳብ በምግብ ራስን መቻል ያልንበት ምክንያት እርዳታ እንደ ማስታገሻ (antipain) ነው። ሲያመን ለጊዜው ማስታገሻ የሚሆነን ነገር ነው። የማስታገሻ መድሃኒቶች መጥፎ ነገር ደግሞ በተደጋጋሚ ስንወስዳቸው ሱስ የሚሆኑብን መሆኑ

ነው። አንድ ሰው ራሱን አሞት በተደጋጋሚ አድቪል የሚወስድ ከሆነ ከአድቪል ጋር ይለማመድና ልክ እንደ ሲጋራ ሱስ ይሆንበታል። ማስታገሻዎች ሱስ ከሆኑን ሰው ከተላማመዳቸው በኋላ እግር ከወርች የሚያስቀምጡ ናቸው። በርካታ ወጣቶቻችን ለጥናት ብለው እንደዋዛ ጫት ይጀምራሉ፤ እንደዋዛ ሲጋራ ይጀምራሉ፤ እንደዋዛ የጀመሩት ጫትና ሲጋራ በእድገታቸው በጉዟቸው ውስጥ እንቅፋት እየሆነ እግር ከወርች እያሰራቸው ወደ ራዕያቸው እንዳይደርሱ፤ ወደ ሙላት እንዳይደርሱ ይጋርዳቸዋል። እናም አደንዛዥ ማስታገሻን ከአደንዛዥ እጽ ለይተን የማናይበት ዋናው ምክንያት የልምምድ ጉዳይ ሆኖ ቀስቀስ እያለ ዛሬ ማስታገሻ የሆነው ነገ አደንዛዥ እጽ ይሆናል። ማስታገሻው ለጊዜው ያለብንን ህመምና ስቃይ መቋቋም ተስኖን የጀመርነው ማስታገሻ የዘላለም ልምምድ ይሆናል። ስቃዩን መቋቋም ይበልጥ የተሻለ ይሆናል፤ ምን ማለት ነው? ይሄ በእርዳታ ዘላቂ ጥቅም፣ ዘላቂ ለውጥና ዘላቂ እድገት ያመጣ አንድም ሀገር የለም። በእርዳታ ዘላቂ ጥገኝነት ብቻ ነው ያለው።

ዘላቂ ጥገኝነት ማለት ፓራሳይት መሆን ማለት ነው። ራስን ችሎ አለመቆም ማለት ነው፤ ጨክነን ሰብሰብ ብለን መስራት ብንችልና ከእንደዚህ አይነት ጉዳይ ራሳችንንና ህዝባችንን ነጻ ብናወጣ አሁን ባለው ሁኔታ ሉዓላዊነት ከምግብ ተለይቶ አይታይም። በምግብ ራስን መቻል ማለት የአንድን ሀገር ሉዓላዊነት ማረጋገጥ መቻል ማለት ነው። ልጆቻችን ወንድሞቻችን የሀገር ክብር ተነካ ብለው ህይወታቸውን ሲሰጡ የቀረን ብዙዎቻችን ላባችንን ሰጥተን ተግተን ሠርተን ሉዓላዊነት ማስከበሪያ ከሆነው መንገድ አንዱ የሆነውን በምግብ ራስን መቻልን መከወን አይሳነንም። ይህ ደግሞ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው፤ ሌሎች የሚያግዙን ሀገራት በተደጋጋሚ የጠየቅናቸው አሁን ርቦናል ለአንድ ጊዜ የሚሆን ማዕድ፣ ለአንድ ጊዜ የሚሆን ምግብ ከምትሰጡን ለአንድ ጊዜ የሚሆን አሳ ከምትሰጡን አሳውን እንዴት ማጥመድ እንደምንችል አሳዩን ነው። አንዴ አሳውን እንዴት ማጥመድ እንደምንችል ብታስተምሩን ራሳችንን ብቻ ሳይሆን ሌሎችን መመገብ እንችላለን። በየጊዜው ግን የተጠበሰ አሳ አንዳንዴ የደረቀ አንዳንዴ የተበላሸ ማዕዳችን ላይ ማስቀመጥ ለጊዜው ህይወታችንን ያቆይ እንደሆነ እንጂ በዘላቂነት ራሳችንን እንድንችል አያደርገንም።

ኢትዮጵያን ማገዝ የሚፈልግ ኢትዮጵያዊም ይሁን የውጭ ሀገራት እንዴት አምርተን፣ በልተን፣ ጠግበን፣ ሸጠን፣ ማካፈል እንደምንችል የሚያግዘን መሆን አለበት። ከዚህ አንጻር የኢትዮጵያ ርዳታ ሲነሳ የሚነሳው ቁጥር ያስደነግጣል። ለኢትዮጵያ ይህን ያክል ቢሊዮን ዶላር እየረዳን ነው የሚባለው በርግጥ ኦዲት አናደርገውም። ይህን

ገንዘብ በስም ነው የሚጠራው፤ ከሚጠራው ገንዘብ አስር እና አምስት መቶኛውን ለሁለት ዓመት በማዳባሪያ፣ በማሽንና ፓምፕ ቢያግዙን ለመቶ ዓመታት ራሳችንን መመገብ የምንችል ሀገር ሆነን ልንሰራ እንችላለን። በየዓመቱ ቢሊየኖችን ከመጥራት ከሱ ትንሿን ማምረት የሚያስችል ሥራ ላይ ማዋል ይጠቅማል። እንግዲህ ኢትዮጵያ እንደ ሌላ ሀገር አይደችለም። በጣም ሰፊ መሬት አለን። እንደሰማችሁት በክረምት 13 ሚሊየን ሄክታር መሬት ነው ያረስነው፤ 20 ሚሊየን ልናደርሰው እንችላለን። ሰፊ የሆነ የሰው ኃይል አለ። ከእርሻ ጋር ልምምድ አለን፤ እርሻን ከጀመሩት ሀገራት አንድ ሁለቱ ከተጠሩ አንደኛዋ ኢትዮጵያ ናት። ልምምዱ አለ፣ መሬት አለን፣ ጉልበት አለን፣ አስደማሚ የሆነ የከርሰ ምድርና የዝናብ ውሃ አለን። ይሄንን ግብዓት ጨምረንና ማሽን ጨምረን መስራት ከቻልን ራሳችንን መቻል ሳይሆን ለሌሎችም መትረፍ እንችላለንና የሚያግዙን እንዴት አሳውን እንደምናጠምድ ነው ለእኛ የሚበጀን እንጂ በየጊዜው የተጠበሰ አሣ ቢቀርብልን ችግራችንን በዘላቂነት ሊፈታው አይችልም። አሁን እያየነው ያለነው ነገር ኢትዮጵያ ከጨከነች፣ ከወሰነች ራሷን ለመመገብ የምትችገር ሀገር አለመሆኗን አመላካች ውጤት ነው።

ለኢትዮጵያዊያን መልእክት አለኝ። በሀገራችን ሽምገል ያለ ሰው ሲለምን ሆዳችን ይራራል፤ ደክሟልና ቢታገዝ እንላለን፤ ወይም ወላጅ አልባ ህጻን ብናይና ቢለምን ለመርዳት እንንጓጓለን ያሳዝናል ምክያቱም ህጻን ነውና። ወጣት አፍላ ጉልበት ያለው ቢለምን ግን ያበሳጫል። ይህ የኢትዮጵያዊያን ከሞላ ጎደል የሁላችም እሳቤ ነው። አሁን እየሆነ ያለው ይሄ ነው። ኢትዮጵያ እንደሀገር ወጣት ሀገር ናት፤ ኢትዮጵያ የምትለምናቸው ሀገራት ደግሞ የሸመገሉ ሀገራት ናቸው። እኛ እንደ ህዝብ ወጣት ሆነን የኢትዮጵያዊያን ህዝቦች እንዴት ከሸመገሉና መጦር ከሚገባቸው ህዝቦች እንለምናለን ነው ጥያቄው። አንድ ባንድ ያለውን እሳቤ ሰፋ አድርገን ማየት ነው። ኢትዮጵያን ስንዴ የሚረዱ ሀገራት አያቶቻችን የሚሆኑ ቢያንስ ቢያንስ አባቶቻችን የሚሆኑ በእድሜያቸው እኛ የምንለምናቸው ህዝቦች ደግሞ ልጆቻቸው የምንሆን ወጣት ህዝቦች ነን። ወጣት ሲለምን አያምርበትም፤ ወጣት ህዝብ፣ ወጣት አስተዳደር፣ ራዕይ ያለው መንግሥት ያለባት ሀገር መለመን አያምርባትም።

ልመና እጅግ ጸያፍ ነገር ነው። ኢትዮጵያዊያን እንደምንም ተባብረን በግራ በቀኝ ከሚከፋፍለን ሃሳብ ሰብሰብ ብለን በጋራ ቆመን ራሳችንን መቻል ብንችል ብዙ ጉዳዮች ይፈታሉ። ልመና ያታክታል፣ ልመና ያስጠላል የሰው ፊት ማየት ከባድ ነገር ነው። እንደ ሀገር የሰው ፊት እያየን እየለመንን ደግሞ ክብር የለም፤ እንደሀገር እየለመንን

ነጻነትና ሉአላዊነት የሚባል ነገር ሊነሳ አይችልም። ሀገሩን የሚወድ፣ ነጻነቱን የሚወድና ሉዓላዊነቱን የሚወድና ወጣት መሆኑን የሚያምን ኢትዮጵያዊ የማያግባቡን ጉዳዮች ቢኖሩ እንኳን በእነሱ እየተነጋገርን በብሄራዊ ጥቅም ጉዳይ ሀገራችንን በጋር በሚያቆም ጉዳይ በጋራ ሆኖ ከልመና ነጻ መሆን በእጅጉ አስፈላጊ ነገር ነው። ይህንን ካደረግን ብዙ ጉዳዮቻችን ይፈታሉ። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሊፈታ የሚገባው ነገር ገጠር አራሽ፣ አርሶ አደር አራሽ ከተሜው ሸማች ተመጋቢ መሆን አደገኛና ያረጀ ፋሽን ነው። ገጠር ሰፋ ያለ መሬት ስላለው ስንዴ ይመረታል፤ ከተማ አነስተኛ ቦታ ስላለው ከብት ያረባና ወተት ይሸጣል፣ ማንጎና አቡካዶ፣ ሰላጣ፣ ቆስጣ መሬት ቆጣቢ በሆነ መንገድ ያመርታል። ከተማው ሰላጣና ቆስጣ ይሸጣል ገጠሩ ደግሞ ስንዴ ይሸጣል፣ ከተማው ወተት ይሸጣል ገጠሩ ስንዴ ይሸጣል። እንዲህ እየተቀያየርን ነው የምንኖረው እንጂ አንዱ አምራች አንዱ ሸማች ከሆነ እንደ ሀገር የተሟላ በምግብ ራስን መቻል ሊረጋገጥ አይችልም።

ሁላችንም አምራች ነን። አንዳንዶቻችን ማሽን እናመርታለን፤ አንዳንዶቻችን ስንዴ እናመርታለን፤ አንዳንዶቻችን ወተት እናመርታለን እሱን በመቀያየር ህይወታችንን እናቀላለን። ከመራብ፣ ከመለመን፣ ከመታረዝ ነጻ እንወጣለን። እንግዲህ እኛ እንደሀገር ያለን ተስፋ ስንዴን ካሳካን ሌላ በርከት ያሉ ኢንሽቲቮች አሉን። እንደ መንግሥት እነሱን በመጀመር በሚቀጥሉት አራት ዓመታት በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ያገኘነውን ተርም ስንጨርስ ኢትዮጵያ ውስጥ ስንዴ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ወተት፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ማር፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ስጋ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ እንቁላል ሀሳብ የማይሆንበትን፤ ሰው ሠርቶ ገንዘብ ካገኘ በኋላ ገዝቶ መመገብ የሚችልበትን አውድ መፍጠር እንፈልጋለን። ያለን ጊዜ በጣም አጭር ነው፤ ይህ መንግሥት ያለው አራት ዓመት ያልሞላ ጊዜ ነው። እንደከዚህ ቀደሙ እድሜልክ የሚባል ነገር የለም። በተርም ነው በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ነው፣ ቃል በገባነው መሰረት የማናስረክብ ከሆነ፤ የብልጽግናን መሰረት የማንጥል ከሆነ፤ የኢትዮጵያ ህዝብ አይሸከመንም ሊሸከመንም አይገባም። ያን የሚያምን እያንዳንዱ ካድሬ እያንዳንዱ አስተዳዳሪ ማመን ያለበት ስንት ስብሰባ አካሄድኩ በሚለው አይደለም። ምን ያህል ስንዴ አመረትኩ፣ ምን ያህል ማሳ አረስኩ፣ ምን ያህል ፍራፍሬ በአንተ አካባቢ ተመረተ የሚል ነው መመዘኛው መሆን ያለበት። አምራች እንዲያመርት አስቻይ የሆነ አመራር በቦታው ከፈጠርን እናመርታለን፤ መመዘኛው እሱ ይሆናል እድገት ይረጋገጣል። እንደከዚህ ቀደሙ አስር ቀን ሰብስቤያለሁ ሃያ ቀን ሰብስቤያለሁ፣ ጉንጭ አልፋ ወሬ አውርቻለሁ በሚል መመዘኛ ግን ሀገር ልናለማ አንችልም። ይሄ ዞን፣ ከዛኛው ዞን፣ ይህኛው ክልል ከዛኛው ክልል የሚወዳደርበት ምን ያክል ስንዴ፣ ምን ያክል ቡና፣ ምን ያክል አቮካዶ አመረትክ በሚለው መሆን አለበት፤ እኛም መመዘን ያለብን በዚሁ አግባብ ነው።

ማወቅ ያለባችሁ ነገር ኢትዮጵያ ዘንድሮ በዓለማቀፍ ደረጃ የተቋቋመችው ጫና፣ የተቋቋመችው ግፍ የተሞላበት ጫና ምስጢር አንድ መሆን፣ የሀገርን ጉልበት አቅም ማንቀሳቀስ ይቻላል በሚል ጽኑ እምነት ነው።

ለብዙዎች ምስጢሩ እንዴት ቻላችሁት ነው። የመቻላችን ምስጢር ፈጣሪያችንና ህዝባችን ነው። በፈጣሪ ታምነን ህዝባችንን አሥተባብረን ከሰራን የማናሸንፈው ጠላት፣ የማንሻገረው ገደል፣ የማንወጣው ተራራ አይኖርም። ኢትዮጵያዊያን ግድ የላችሁም ቀልባችንን ሰብስብ አድርገን በዘር፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በአልባሌ ወሬና በሃሰተኛ መረጃ መባላቱን ትተን በማንግባባቸው ጉዳዮች እየተከራከርን እየተወያየን፤ ነገር ግን በሚያግባቡን በሀገራዊ ጉዳይ አብረን መቆም ብንችል ኢትዮጵያ እና ረሃብ ኢትዮጵያ እና ርዳታ የሚለያዩበት ጊዜ አጭር ይሆናል።

ስንዴ ወደ ውጭ እንልካለን፣ ወደ ውጭ የሚላክን ቡና መጠን እንጨምራለን፣ ግብዓቶችን የምናመርትበት መንገድ ላይ እንሰራለን፣ ኢትዮጵያን እንደተለመደው የጥጋብ ሀገር እናደርጋታለን፣ ለአፍሪካ ምሳሌ እንሆናለን፣ ለብዙ ሀገራትም ምርት እንልካለን፤ ይህንን ለማድረግ በጋራ መቆም እጅግ አስፈላጊ ነው። ይህን በማድረግ የተገኘውን ውጤትም በእጥፍ ማባዛት ነው፤ መኩራት አያስፈልግም። እንደ ስኬት ማየትና ድል ማውራት ብቻውን አያስፈልግም፤ ገና ብዙ ጥረት ይጠበቅብናል። አሁን ያለውን ምርት እየሰበሰብን ሌላኛው ማሳን ደግሞ አሁን ማረስ እንጀምራለን፤ ሌላው ላይ ደግሞ እንዘራለን። በዚህ መሰል የማይቋረጥ ድግግሞሽ ውስጥ ኢትዮጵያ ያሰበችውን ታሳካለች ብልጽግናዋም ይረጋገጣል።

ይህን ዓለም እየተገነዘበ ነው፣ ኢትዮጵያዊያን እየተገነዘቡ ነው፣ እኛ እየተገነዘብን ነው። ኢትዮጵያዊያን ልመና ይብቃ፣ ልመና በእኛ አያምርም፤ ባይሆን እስካሁን የረዱንን ሰዎች እንደውለታ ቆጥረን የምንረዳበት ዘመን እንዲመጣ ተግተን እንሥራ ማለት እፈልጋለሁ። እጅግ በጣም ደስ የሚል ነገር ነው፤ ይሄው እንዲቀጥል ነው ህልማችን እና ፍላጎታችን።

**ጥቅምት 19 ቀን 2015 ዓ.ም**
**ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል፣**
**ምስራቅ ሸዋ ዞን፣ ዱግዳ ቦራ**



# በደቡብ ክልል፣ በጎፋ ዞን የተካሄደ ጉብኝት

ጥቅምት 23 ቀን 2015 ዓ.ም

እጅግ ተከበራችሁ እና የምንወዳችሁ የጎፋ፣ የሳውላ እንዲሁም አካባቢው ነዋሪዎች በሙሉ

ዛሬ የኢትዮጵያዊነት ምልክትና ምሳሌ በሆነው በወይላ ተራራ ስር ኢትዮጵያዊነትን ዳግም ለማድመቅ በመገናኘታችን የተሰማኝን ልባዊ ደስታ ልገልጽላችሁ እወዳለሁ። ወይላ የኢትዮጵያዊነት ምልክት ነው፤ ወይላ ብቻ ሳይሆን አልባዙማም እንዲሁ የኢትዮጵያዊነት ምልክት ነው። ዛሬ እዚህ የመጣነው በወይላ ተራራ ስር እናንተ ጀግኖች ህዝቦችን፤ ኢትዮጵያን የምትወዱ ህዝቦችን፤ በችግሯ ቀን ካለስስት ልጆቻችሁን ሰጥታችሁ ኢትዮጵያን ባለድል ያደረጋችሁ ጀግኖች ህዝቦችን እናመሰግናችኋለን ለማለት ነው።

ልጆቻችሁ ኢትዮጵያ በፈለገቻቸው ጊዜና ችግር በገጠማት ጊዜ ካለስስት ህይወታቸውን ገብረው ደማቸውን አፍሰው ኢትዮጵያ የማትደፈር፣ የማትበተን አንድ ሀገር መሆኗን ስላረጋገጡ የጎፋ ህዝቦች፣ የጋሞ ህዝቦች፣ የወላይታ ህዝቦች ፣ የዳውሮ ህዝቦች ፣ የጂማ ህዝቦች አጠቃላይ እዚህ አካባቢ ያሉ ህዝቦች ሁሉ እንደሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ከፍተኛ ኩራት ሊሰማችሁ ይገባል። ወይላም ኢትዮጵያዊ ነው፣ ሸሬም ኢትዮጵያዊ ነው፣ ጎንደርም ኢትዮጵያዊ ነው፣ በሻሻም ኢትዮጵያዊ ነው። እኛ ሁላችን ኢትዮጵያ በምትሰኝ ድንቅ ስም፣ ድንቅ ጥላ ሥራ ያለን ህዝቦች የየራሳችን ቋንቋ፣ የየራሳችን ባህል፣ ራሳችን እምነት ያለን ቢሆንም፤ ይህ ሁሉ ተሰባስቦ በኢትዮጵያዊነት ስር የሚቆምና የሚያብብ መሆኑን ወይላ ተራራ ዛሬ ምስክር ሆኖ ዳግም ያረጋግጥልናል።

የጎፋ አካባቢ ቀደም ሲል እንደተገለጸው በእርሻ በእጅጉ የሚታወቅ በርከት ያሉ የሰብል ምርቶች የሚመረቱበት እንዲሁም ቅመማ ቅመም በስፋት የሚገኝበት አካባቢ ነው። ከከብት ርባታ ጋር ተያይዞም ከፍተኛ አቅም እንዳለው ይታወቃል። ከሁሉ በላይ በቱሪዝም መስክ እጅግ ድንቃ ድንቅ የሆኑ የዚህ አካባቢ ቦታዎች በተለይም የማዜ ብሄራዊ ፓርክ ከጨበራ ጩርጩራ ጋር ተያይዞ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለዓለም ቱሪስቶች በእጅጉ መስህብ መሆን የሚችል ቦታ ስለሆነ የወንባ ፏፏቴን፣ ቱርማ ዋሻን ትክል ድንጋይን ጨምረን ጎፋን፣ ዳውሮን፣ ሶዶን እንዲሁም ኮይሻን አሰባስበን የደቡብ ኢትዮጵያ

ፈርጥ፣ የኢትዮጵያዊነት ምልክት፣ የቱሪስት መስህብ እንዲሆን በጋራ ለመስራት ያለን ቁርጠኝነት ከፍተኛ መሆኑን ልገልጽላችሁ እወዳለሁ።

አንድ ማስተካከያ ብቻ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው የመጣነው ለሚለው እንደምታውቁት እኔ የኮይሻ ልጅ ስለሆንኩ፣ ኮይሻ ደግሞ አንድ መቶ ኪሎሜትር ስለሆነ ጎረቤት ለመጀመሪያ ጊዜ መጣህ አይባልም። ወደፊት መሪዎች ሲመጡ ብቻ እንደዚያ ቢባል ይሻላል። ጎፋ ሁልጊዜ በልባችን ውስጥ አለ። የጎፋ ልጆች በቢሯችን በአካባቢያችን ከእኛ ጋር አሉ።

እንደምታውቁት፤ ሁሌም እናስባችኋለን ከእናንተ ጋር ሆነን በጦርነት ያገኘነውን ድል በሰላም መድገም ይኖርብናል። በጦርነት የተገኘ ድል በሰላም ካልተደገመ ፣ በሰላም የተገኘ ድል በብልጽግና ካልተደገመ ኢትዮጵያ ህልውና በአንድ ወይም በሌላ መልኩ መደፈሩ ስለማይቀር በአንዱ ድል ሳንኩራራ በጦርነት ያገኘነውን ድል በሰላም መድገም በሰላም የሚገኘውን ድል ደግሞ በብልጽግና መድገም የማትደፈር፣ የተከበረች፣ ለልጆቿ ምቹ የሆነች ኢትዮጵያን በጋራ እንድንፈጥር አደራ ልላችሁ እወዳለሁ።

አንዳንድ ወዳጆቻችን በተደጋጋሚ ለኢትዮጵያ መንግሥት እና ለኢትዮጵያዊያን የሰው ልጆች መብት፣ የሰው ልጆች በክብር የመኖር መብት ይከበር የሚል ጥያቄ አልፎ አልፎም ክስ ያሰማሉ። የሰው ልጅ መብት መከበር አለበት የሚል ወቀሳና ክስ ይቀርባል። ለእነዚህ ወዳጆቹ ያለኝ መልዕክት ኑና ጎፋን፣ የጎፋን አካባቢና የጎፋን ህዝብ ተመልከቱ። እኛ ኢትዮጵያዊያን እንኳን የሰው ልጆች መብትና በክብር የመኖር መብት ቀርቶ በማዜ ብሄራዊ ፓርክ የዝሆን መብት፣ የእንስሳ መብት እና የጫካ መብት የምንጠብቅ ህዝቦች ነን። ተፈጥሮን አክብረን ተራራን አክብረን፣ ተፈጥሮን አክብረን፣ ጫካን ጠብቀን፣ ማዜን የመሰለ ፓርክ ጠብቀን፣ አንበሳ እና ዝሆን ጠብቀን የሰው ልጅ መብት የሰውን በክብር የመኖርን መብት የምንቸገር ህዝቦች አይደለንም። ይህ ክስ ለኢትዮጵያ አይሰራም። እኛ ጫካ እናከብራለን፣ ተራራ እናከብራለን፣ ዱር እንስሳትን እናከብራለን፣ ተፈጥሮን በሙሉ እናከብራለን፣ ፈጣሪንም እናከብራለን፣ ለኢትዮጵያዊያን ብቻ ሳይሆን ለመላው ዓለም ዜጎች መብት የምንቆም ቆመንም ያሳየን ህዝቦች ስለሆንን አላግባብ ክስ ለእኛ አይገባም። ምስክር ከፈለጋችሁ መጥታችሁ የወይላ ተራራን፣ የጎፋን ህዝብ ተመልከቱ፤ ኑና የማዜን ፓርክ ተመልከቱ የሚል መልዕክት ከዚህ ስፍራ ላስተላልፍ እፈልጋለሁ።

ኢትዮጵያን ስለምትወዱ፣ ለኢትዮጵያ ዋጋ ስለከፈላችሁ፣ ልጆቻችሁ በደም በአጥንታቸው ኢትዮጵያን ባለ ድል ስላደረጉ የኢትዮጵያ ህዝብና የኢትዮጵያ መንግሥት ያለውን ክብር ደጋግሞ እየገለጸ፤ አሁን በትብብር፣ አንድ በመሆን፣ በመደመር፣ በእርሻ (በሙዝ፣ በኮረሪማ ) በከብት ርባታ (በወተት፣ ዶሮ በማርባት) ኢትዮጵያን ከምግብ ጥገኝነት ለማውጣት የጎፋ ህዝብ ታጥቆ እንዲነሳና ትናንት በደሙ ያስከበራትን ኢትዮጵያ ዛሬ ደግሞ በላቡ ማስጠበቅ እንዲችል በታላቅ ትህትና አደራ ልላችሁ እወዳለሁ። ኢትዮጵያ አትፈርስም፣ ኢትዮጵያ ትበለጽጋለች፣ ኢትዮጵያ የልመና ታሪኳን በቅርቡ ታቆማለች፣ ኢትዮጵያ የምትጠግብ ብቻ ሳይሆን የምትረዳ ሀገር መሆኗን ለዓለም የምታሳይበት ጊዜው ደርሷል።

አንድ እንሁን፣ እንዋደድ፣ እንከባበር፣ አንዳችን ለሌላችን ምሶሶ እንሁን፤ ጋሻ እንሁን። በሰሜን ያለውን ጦርነት በድል እያጠናቀቅን ስለሆነ ሰላም ለማምጣት፣ ልማት ለማምጣት የኢትዮጵያን ብልጽግና በማረጋገጥ ሩቅ ሆነው ኢትዮጵያን የሚያባሉ ኃይሎች እንዲያፍሩ እናደርጋቸዋለን። መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በጦርነት ያገኘነውን ድል በሰላም ለመድገም ፣ በልማት ለመድገም የኢትዮጵያን ነጻነትና ክብር ለማስቀጠል አብሮ እንዲቆም በዚህ አጋጣሚ ጥሪዬን አቀርባለሁ። እጅግ አድርጌ እወዳችኋለሁ፣ አከብራችኋለሁ፣ ስለተገናኘን ደስ ብሎኛል። ፓርኮቻችን ይጠበቁ፣ ተራሮቻችን ይጠበቁ፣ ኮይሻ ላይ እንገናኛለን፤ እዚህም ይቀጥላል እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ፣ ተባረኩ ሰላም ሁኑ።

ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ትኑር
መልካም ጊዜ ሁሉ ከፊታችን አለ

**ጥቅምት 23 ቀን 2015 ዓ.ም**
**ጎፋ ዞን፤ ጎፋ**





# በአርባምንጭ ከተማ የተካሄደ ጉብኝት

ጥቅምት 24 ቀን 2015 ዓ.ም

**ክቡር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ የኢፌዲሪ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር እና የአርባ ምንጭ ልዩ አምባሳደር ፤**
**ክብር አቶ ደመቀ መኮንን የኢፌዲሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ፤**
**ክብር አቶ አደም ፋራህ የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዝዳንት፣**
**ክቡር አቶ ታገሰ ጫፎ የጋሞ ሽበላ፣**
**የተከበራችሁ የሁሉም ክልሎች ፕሬዝዳንቶች፣ ሚኒስትሮች፣ ከንቲባዎች፣**
**እዚህ ስፍራ የተገኛችሁ እንግዶች በሙሉ**

በአካል ብቻ ሳይሆን ዐይን ማጥገብ ብቻ ሳይሆን፤ ለመንፈስ እረፍት ወደምትሰጠው ውቧ ገነቷ አርባ ምንጭ እንኳን በሰላም መጣችሁ። ብዙ ቦታ ለአካል እረፍት ይሰጣል፤ ዐርባምንጭ ጨንቻ ግን ለመንፈስም እረፍት ይሰጣል፣ የአርባምንጭ ሙዝ፣ አፕል፣ ወተት፣ የእጅ ጥበብ የሆነው ሽማ ብለው ለዘመናት ሲናገሩ ነበር። ዛሬ ልነግራቸው የምፈልገው ግን የአርባምንጭ ጣእም ያለው ሰላምና መንፈስ ይጨመርበት። ትናንት ወደ ጨንቻ ሄደን ወተትና አፕል በየጓሮው የሚታይበት፣ ደጋግ አርሶ አደሮች ያሉበት፣ የኢትዮጵያዊነት ኩራት የሆነበት ስፍራ ለማየት እድል አግኝቻለሁ። ጨንቻ፣ አርባምንጭ፣ ሳውላ፣ ሶዶ፣ ዳውሮ፣ ጂንካ፣ ጂማ በጋራ የምንቆምባትን ኢትዮጵያን የሰጠን ፈጣሪ የተመሰገነ ይሁን።

ከጥቂት ዓመታት በፊት በምዕራብ ኢትዮጵያ የንግድ፣ የፈጠራ፣ የኢትዮጵያዊነት ምሳሌ ወደሆነችውወልቂጤ ከተማ የመሄድና የመጎብኘት እድል ነበረኝ። የወልቂጤ ህዝብ ዛሬ በአርባምንጭ እንደምናየው በከፍተኛ ደስታና ሰላም መንፈስ ተቀብሎን እዚያው እያለን የኢትዮጵያና ኤርትራ የሰላም ዜና ለመጀመሪያ ጊዜ በወልቂጤ ከተማ ነበር የሰማነው። እንደጉራጌ ህዝብ ሰላም ወዳድ ሥራ ወዳድ እና አርቆ አሳቢ በኢትዮጵያዊነቱ ጽኑ አቋም ያለው የአርባምንጭ ህዝብ ከልቡ ቸርነትና ደግነት የተነሳ እዚህ እያለን የኢትዮጵያ የሰሜን ጦርነት የሚያበቃበት ሰላም ትናንት ተነገረ።

እኛ ሰላም የምንወድ ህዝቦች፣ እኛ ሰላምን የምንሻ ህዝቦች እጅግ በምንወዳት ገነት በሆነችው የፍቅር ከተማ ውስጥ የሰማነው ዜና ሁልጊዜ የማይረሳን በመሆኑ ጋሞዎች እንኳን ደስ ያላችሁ። ዛሬ እዚህ የተገኘነው ለሁለት መሰረታዊ ዓላማ ቢሆንም ሶስተኛ ጉዳይ ተጨምሯል።
አንደኛው የጋሞ፣ የጎፋ፣ የወላይታ፣ የጉራጌ፣ የስልጤ ፣ የሃዲያ ፣ የከምባታ የዚህ አካባቢ ህዝቦች በሙሉ ኢትዮጵያ ስትደፈር የኢትዮጵያ ልጆች በግፍ ሲገደሉ ይህንን ለመስማትና ለማየት ዝግጁ አይደለንም ብላችሁ በፈቃድ ፣ በደስታ በልጆቻችሁ ደምና ህይወት የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለማጽናት ትልቅ ዋጋ ስለከፈላችሁ ሁሉንም አመራሮች እናመሰግናችኋለን ለማለት ነው የመጡት።
ሁለተኛው ፕሮግራማችን ከዚህ ፕሮግራም በኋላ የሚጀምር ስለሆነ እሱን እዚህ አልገልጸውም። ሶስተኛው ግን ትናንት የሰማችሁት፣ የሰማነው የሰላም ድርድር ጉዳይ ቀደም ብዬ ካነሳኋቸው ዓላማዎች የሚያንስ ስላልሆነ በተወሰነ ደረጃ ነካ አድርጌ ለማለፍ እወዳለሁ።

እንደምታስታወሱት የዛሬ ሁለት ዓመት ባልተገባ መንገድ ከወንድሞቻችን እጅግ አሳዛኝ ጥቃት ተሰንዝሮብን ነበር። የኢትዮጵያ ወንድና ሴት ልጆች በገዛ ወንድሞቻቸው ባልተገባ ሁኔታ በተኙበት ታርደው፣ ተገድለው፣ ተገፍተው ነበር።
ያ ሁኔታ ሁላችንንም ያስቆጣ፣ በኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና አንድነት አንደራደርም፣ ቢሮ ተቀምጠን መምራት ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ክብር ከመጣ የጥይት አረር በግንባራችን ለመቀበልና ሉዓላዊነታችንን ለማስከበር ዝግጁ መሆናችንን ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ ሳይሆን ለመላው ዓለም ህዝብ ያስገነዘብን ሲሆን፤ ነገር ግን ጦርነት እንኳን እርስ በርስ በወንድማማቾች ቀርቶ በማንኛውም ሀገር መካከል ቢሆን የሚወደድ፣ የሚፈለግና ሚናፈቅ ነገር አይደለም። ጦርነት የሰው ህይወት ይቀጥፋል፣ እጅ እግር ያሳጥራል፣ ንብረት ያወድማል፣ ጥላቻን ያበዛል ከዚህም የተነሳ ለፈጣሪ ምስጋና መስጠት የሚገባው ህዝብ የርግማን ምንጭ ይሆናል ።

ጦርነትን እኛ አብዝተን እንጠላለን፤ እኛ የምንፈልገው ሰላምንና ብልጽግና ነው።
በደቡብ አፍሪካ በነበረው የሰላም ድርድር ጀግኖች የጋሞ ልጆች፣ ጀግኖች የኢትዮጵያ ልጆች በመሬት ላይ ያስገኙትን ታሪካዊ ድል የሚያስረግጥ የሰላም ድል ማግኘት ተችሏል። ከተገኙ ዋና ዋና ድሎች መካከል አንደኛ፤ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት እና የግዛት አንድነት ለድርድር አይቀርብም በሚለው በሁለቱም ወገን ተቀባይነት አግኝቷል። ለኢትዮጵያ አንድነት የሞቱ፣ የቆሰሉ ባልተገባ ሁኔታ የወደቁ ጀግኖች

እንኳን ደስ ያላቸው ህልማቸው እውን ሆኗል። ሁለተኛ፤ በሰለጠነው ዓለም እንደጋሞ ሽማግሌዎች ባሉበት ሀገር ያደገ ህዝብ ነገር በንግግርና በምክክር እንደሚጨረስ ስለሚያውቅ በአንድ ሀገር ውስጥ ከአንድ መከላከያ በላይ አያስፈልግም የሚለው ጉዳይም ከስምምነት ተደርሷል። ሦስተኛ፤ ህጋዊ እና ህጋዊነትን ማስፈን ለአንድ ሀገር ህልውና መሰረት ስለሆነ የራሳችንን ህግ የማናከብር፣ ማሻሻል ሲኖርብንም በህግ አግባብ የማናደርግ ከሆነ ተቋማዊነትና ሀገር የሚለው ቁመና ስለሚሸረሸር ህገወጥ በሆነ መንገድ የተደረገው ምርጫ በህጋዊ ምርጫ መተካት አለበት የሚለውም በሁለቱም ወገኖች ተቀባይነት አግኝቷል።

ከዚህ በተጨማሪ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የይገባኛል ጥያቄ የሚነሳባቸውና አከራካሪ የሆኑ ቦታዎች ዳግም የሰው ልጅን ህይወት ሳይጠይቁ በሰላም፣ በድርድርና በሀገሪቱ ህግ መሰረት ብቻ ምላሽ እንዲያገኙ በሁለቱም ወገኖች ከትምምን ላይ ተደርሷል። ደቡብ አፍሪካ ላይ በነበረው ድርድር ኢትዮጵያ ያቀረበችው ሃሳብ መቶ በመቶ ተቀባይነት አግኝቷል። ታዲያ የጋሞ ጀግኖች ጀግንነት ማለት ማሸነፍ ብቻ አይደለም ጀግንነት ማለት ከድል በኋላ ደግነት ማለት ነው፣ ከድል በኋላ ይቅር ማለት ነው፤ እኛ ጀግኖች ብቻ ሳንሆን ፈጣሪን የምንፈራና የምናከብር ሰዎች ስለሆንን ያገኘነውን የሰላም እድል በታላቅ ክብር የምንቀበልና በሙሉ ልብ ይቅር ብለን የኢትዮጵያን አንድነትና ሰላም በመመለስ የልመናን ጣጣ ለማፍረስ ስለምንፈልግ እጅግ የምወዳችሁ የጋሞ ህዝቦች እንዲሁም በመላው ኢትዮጵያ የምትገኙ ዜጎች የተገኘው የሰላም እድል ታላቅ ድል ስለሆነ፣ በኢትዮጵያ ብዙ እጃቸውን ያስገቡ ጠላቶቻችን ያፈሩበት ስለሆነ በሙሉ ልብ ትግራይን የትግራይ ህዝብን ለመገንባትና ወደ ቀደመው የሀገሩ ስሜት ለመመለስ አብረን እንድንቆም በታላቅ ትህትና እጠይቃችኋለሁ።

የአማራ ጀግና፣ የአፋር ጀግና፣ የኦሮሞ ጀግና፣ የሶማሌ ጀግና፣ የደቡብ ምዕራብ ጀግና፣ የደቡብ ጀግና ጀግንነታችን የሚረጋገጠው ካለን አካፍለን በትግራይ የተጎዱ ወገኖቻችንን ማጉረስ ስንችል ነው። ካለን አካፍለን በማጉረስ፣ ፍቅር በመስጠት ኢትዮጵያዊነት የሚሻል ኢትዮጵያዊነት የላቀ ምስጢርና ጥበብ መሆኑን እርስ በርሳችን ብቻ ሳይሆን ለዓለም ተጨማሪ ትምህርት መስጠት ስለሚኖርብን እናንተ ያሸነፋችሁ ጀግኖች ልባችሁን ከፍታችሁ ወደኋላ ሳትመለከቱ ኢትዮጵያን ለመገንባትና አንድነቷን ለመጠበቅ ያላችሁን በመስጠት፣ በጉልበት በማገዝ፣ ፍቅር በማጋራት፣ ክፉ ከመናገር በመቆጠብ ደጋግ ጀግና የኢትዮጵያ ልጆች እንድትሆኑ በታላቅ ትህትና ደግሜ ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ። ለሀገር አንድነት ህይወት ከከፈልን ለሀገር አንድነት

ደማችንን ካፈሰስን አጥንታችንን ከከሰከስን ለሰላምና ለአንድነት ላባችንን ብናፈስ፣ ከኪሳችን ብናወጣ ጸጋ በረከት እንጂ ጉድለት ስላልሆነ ኢትዮጵያዊያን ልባችሁ ይስፋ ወደኋላ አትመልከቱ፤ ሰላማችን ወደኋላ እንዳይመለስ በጸሎታችሁም፣ በሃሳባችሁም፣ በድርጊታችሁም ከእኛ ጋር በመቆም ዘላቂ ሰላም እንዲረጋገጥና ኢትዮጵያ እፎይ እንድትል የበኩላችሁን ሚና እንድትጫወቱ አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ፡ለትግራይ ህዝብ በተደጋጋሚ ትግራይ ሀገራችን ህዝቡም ህዝባችን ነው ስንል መቆታችን ይታወቃል።

ብዙ ያልተገባ መቆሳሰል፣ ያልተገባ መደማማት፣ ያልተገባ ጉዳት በእያንዳንዳችን ደርሷል። ከሁሉ በላይ በኢትዮጵያ ደርሷል። የመጨረሻው መልዕክቴ ለትግራይ ህዝብ ነበር። የትግራይ ህዝብ በተደጋጋሚ ህዝባችን ምድሩም ምድራችን እንደሆነ ስንገልጽ ቆይተናል። ተጠቃ ብለን ስናስብ በትግል የልጅነት ወቅታችንን ያጠፋንና ትግራይን የተከላከልን መሆናችንን ታሪክ ይመሰክራል። ዛሬም ያ ልባችን በቦታው ነው ያለው ። ለመላው የትግራይ ህዝብ ማስተላለፍ የምፈልገው መልዕክት አላስፈላጊ ጦርነት፣ አላስፈላጊ ጉዳት፣ አላስፈላጊ ኢትዮጵያን አጋልጦ የመስጠት ሂደት በዚህ ይብቃን፤ ብዙ መከፈል የማይገባው ዋጋ ተከፍሏል፣ ብዙ ደም ፈሷል፣ ንብረት ወድሟል፣ ኢትዮጵያን የዓለም ሚዲያዎች የሚያውቁም የማያውቁም፣ ትልቁም ትንሽም በከፍተኛ ደረጃ አንኳጠዋታል ፣ አሳንሰዋታል ይብቃን። ብዙ ጊዜ ከሰላም ድርድር በኋላ ሽፍጦች፣ ተንኮሎችና ደባዎች ይታያሉ። እናም የተከበርከው የትግራይ ህዝብ እኛ ልባችንን ከፍተን ሰላምን ለማምጣት ዝግጁ ስለሆንን ይህንን የገባነውን ቃል ለመጠበቅ ከሌሎች ወንድም ህዝቦች ጋር በመሆን የበኩልህን ሚና እንድትወጣ፤ ተንኮል፣ ክፋትና ሸር እዚህ ጋ እንዲበቃ፣ ጥቂቶች እየሸረቡ ኢትዮጵያዊያንን ዳግም አደጋ ውስጥና ጦርነት ውስጥ እንዳያስገቡ ህዝባዊ፣ ኢትዮጵያዊ እና ዜግነታዊ ሚናችሁን እንድትወጡ ለትግራይ ወንድሞቻችን እና እህቶቻችን በታላቅ ትህትና አደራ ማለት እወዳለሁ።

ኢትዮጵያዊያን ተጣልተዋል ይገዳደላሉ ገንዘብ ብናቀብል፣ ሚዲያ ብናቀብል፣ የጦር መሳሪያ ብናቀብል ኢትዮጵያ ትፈርሳለች ብላችሁ ብዙ የተጋችሁ የቅርብና የሩቅ ሀገራት ኢትዮጵያ የማትፈርስ፣ የጸናች፣ የምትበለጽግ፣ የአፍሪካ ፈርጥና ኩራት ስለሆነች እኛ ኢትዮጵያዊያን እያለን ኢትዮጵያን ማፍረስም ማሳነስም፣ በኮሎኒ መግዛትም የማይታሰብ ስለሆነ ስላወጣችሁት ወጭ፣ ስለ ድካማችሁ፣ ስለልፋታችሁ ፈጣሪ ይቅር ይበላችሁ ልላችሁ እወዳለሁ ። በዚህ ጭንቅ ጊዜ ኢትዮጵያን አንጥልም ብለው እጅግ ጥቂት ሀገራት ለማመን በሚያስቸግር ሁኔታ እንደ አንድ የኢትዮጵያ ክልል ሆነው በመከራ፣ በችግር፣ በጫና ከእኛ ጋር መቆማቸው ብቻ ሳይሆን ያላቸውን

ያካፈሉ ጓዳችንን ያበሱ፣ የቡሃቃችንን መጉደል አይተው የሞሉ ጥቂትም ቢሆኑ አስደማሚ ወዳጆች እንዳሉን ያየንበት ጊዜ ስለሆነ ለእነሱ ኢትዮጵያ ታሪክ የምትሰራ፣ ታሪክ የማትረሳ ሀገር ስለሆነች ብድራታችሁን የምትከፍል መሆኗንና ታላቅ ምስጋና እንዳላት ልገልጽላችሁ እወዳለሁ።
አንተ የተከበርክ ለህይወትህ የማትሳሳ ሁለት ወር ሙሉ በብርድ፣ በዝናብ፣ በየጫካው የተኛህ አንተ የኢትዮጵያ ኩራት የሀገር መከላከያ፣ አንተ የኢትዮጵያ ወኔ፣ አንተ የኢትዮጵያዊነት ምልክት፣ አንተ የጀግንነት ምልክት በአንተ ድካም በአንተ መቁሰል ባንተ ህይወት ኢትዮጵያ ዳግም ቆማ በክብር መናገር ስለቻለች መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ለሀገር መከላከያ ያላንን ታላቅ አክብሮትና ፍቅር ካላንበት በመቆም እንድናሰማ በታላቅ ትህትና እጠይቃለሁ። አመሰግናለሁ።

ሰው ይፈጠራል፣ ይኖራል፣ ይሞታል። ጀግና ግን ይፈጠራል፣ ለልጆቹ ሀገር ያጸናል፣ እርሱ መስዋዕት ይሆናልና እናንተ ጀግኖች ሞታችሁ ሞት አይደለም፤ የደማችሁ መፍሰስም ደም መፍሰስ አይደለም፤ የኢትዮጵያ መጽናት ነውና እንወዳችኋለን እናከብራችኋለን። ክብርና ምስጋና ለተሰውት ጀግኖች እንዲሆን፤ የተቀራችሁም ጀግኖች ክብር እንዲሰማችሁ ለመግለጽ እወዳለሁ። የጋሞ ሽማግሌዎች ሲመርቁ እንደሚታጨደው ሳር ሳይሆን እንደሚበቅለው ሳር ያልምልመህ ይላሉ። ኢትዮጵያ እንደሚታጨደው ሳር ሳይሆን እንደሚበቅለው ሳር እንድትለመልም፣ እንድትበለጽግ፣ የአፍሪካ ኩራት የሆነች፣ የሁላችን መታፈሪያ የሆነች ብርቅዮ ሀገር አገልጋይ መሆን ብቻ ሳይሆን ዜጋ መሆን ትልቅ ክብር ነውና የተሰማኝን ክብርና ፍቅር ልገልጽላችሁ እወዳለሁ።

በመጨረሻም ከእኛ የተለየ የፖለቲካ እሳቤ ያላችሁ ግለሰቦችና ቡድኖች በተከበረው ጋሞ ህዝብ ፊት ጥሪ ላቀርብላችሁ እፈልጋለሁ። እንኳን በአንድ ሀገር በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ብዙ የማያግባቡ ጉዳዮች አሉ እንከራከር፣ እንነጋገር፣ እንወያይ ግን የኢትዮጵያን ጥቅም ለታሪካዊ ጠላቶቿ አሳልፈን የምንሸጥ ባንዳዎች አንሁን።
ከባለፈው እንማር። ብልጽግና የተመረጠው ህጋዊ መንግሥት ብቻዮን መንግሥት ካልሆንኩ፣ ብቻዬን ኢትዮጵያን ካልገዛሁ የሚል እብሪትና ትእቢት ያለበት መንግሥት አይደለም።

በጀመርነው አካታች ምክክርና ውይይት ሁላችንም እንሳተፍ። ለኢትዮጵያ የሚበጅ ሃሳብ እናምጣ፤ ህዝባችንን እናወያይና ዳግም መገዳደል መሰዳደብ የሌለባት፣ የምትበለጽግ፣ ሰላማዊት ኢትዮጵያን በጋራ እንድንገነባ በታላቅ ትህትና ጥሪ

ላቀርብላችሁ እፈልጋለሁ። ኢትዮጵያዊያን መሰዳደብ፣ መገዳደል፣ መገፋፋት ይብቃን፤ ሴት፣ ወንድ፤ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግሬ፣ ወላይታ፣ ጋሞ ፣ ጎፋ፣ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ አፋር፣ ሶማሌ ሳንል ቤንሻንጉል ጋምቤላ ሳንል እንደ አንድ ሰው በመካከላችን ያለውን ልዩነት አክብረን ኢትዮጵያን እንድንገነባ እንድናበለጽግ አደራ እያልኩ፤ የኢትዮጵያዊነትን ሽታ የኢትዮጵያዊነትን ጣዕም ማወቅ የፈለጋችሁ ወደ ጨንቻ እንድትመጡ እጋብዛችኋለሁ።

ይህች ታይታ የማትጠገብ በየቀኑ ምስጢር የሆነች የፈጣሪ ድንቅ ሥራ ተሰጥቶን አደራ መቀበል የማንችል ህዝቦች እንዳንሆን ልብ እንግዛ፣ ስሜታችንን እንቆጣጠር፣ እንደማመጥ፣ ስለፍቅር፣ ስለአንድነት እና ስለብልጽግና ብቻ የምንናገር ይሁን፤ ከአፋችን ከአንደበታችን የማይረባ ነገር፣ የስድብ ቋንቋ አይውጣ። ግድየላችሁም ኢትዮጵያ የአፍሪካ ፈርጥ ትሆናለች። እንደማመጥ፣ እንከባበር በጋራ እንቁም። በዚህ ውይይት ውስጥ ለኢትዮጵያ የሚጠቅም ማንኛውም ሃሳብ፣ ለኢትዮጵያ የሚበጅ ማንኛውም ሃሳብ ከመጣ ብልጽግና በሁሉም መስክ ዝግጁ መሆኑን በተከበረው በጋሞ ህዝብ ፊት ቃል ልገባላችሁ እወዳለሁ። ስንዴ፣ አቡካዶ፣ ሙዝ፣ ፓፓያና ቡና አረንጓዴ አሻራ ስንል ቆይተናል። ዛሬ በምድረ ገነቷ አርባምንጭ የሌማት ትሩፋት ለመላው ኢትዮጵያ ህዝብ የሚታወጅበት አዲስ የልማት ዘመቻ በጋራ የምንጀመርበት ስለሆነ አርባምንጮች እንኳን ደስ ያላችሁ።

ለምን አርባምንጭን ፈለጋችሁ ከተባለ ልማቱ የሚታይበት፣ ጸሎቱ የሚሰማበት ለምለምና ምድረ ገነት ስለሆነ ነው። ጋሞዎች ስለፍቅራችሁ ስለአሳያችሁን ትህትና፣ ስለ ልጆቻችሁ መስዋዕትነት ኢትዮጵያ ለዘላለም ታከብራችኋለች። እኔም ልጃችሁ፣ ወንድማችሁ እጅግ አድርጌ አመሰግናችኋለሁ።

ሰላም ለኢትዮጵያ ፣ ሰላም ለአፍሪካ ፣ ሰላምና ብልጽግና ለመላው ዓለም ይሁን፤ ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር፤

**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ህዝቦቿን ይባርክ፤**

**አመሰግናለሁ።**

**ጥቅምት 24 ቀን 2015 ዓ.ም**

**አርባምንጭ**







# 17ኛው የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን አከባበር በሃዋሳ

ጥቅምት 23 ቀን 2015 ዓ.ም

**የተከበሩ የኢፌዲሪ ፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባዔ አቶ አገኘሁ ተሻገር፣**
**የተከበሩ የኢፌዲሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አቶ ታገሰ ጫፎ፣**
**የተከበሩ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን፣**
**የተከበሩ የሲዳማ ክልል ፕሬዝዳንት አቶ ደስታ ሌንዳሞ፣**
**የተከበራችሁ የክልል መስተዳደሮች፣**
**የተከበራችሁ የሃዋሳ ከተማና የአካባቢው ነዋሪዎች፣**
**የተከበራችሁ የታላቋ ኢትዮጵያ ምልክት እና ተወካይ ሆናችሁ የቀረባችሁ ቡድኖችና ግለሰቦች፣**
**ከሁሉ በላይ እጅግ በሚያምረው አስደማሚው ሲዳማ ባህል በቄጤላ መልዕክቶቻችሁን ያስተላለፋችሁ የሀገር ሽማግሌዎች፣**
**ክቡራትና ክቡራን፣**

ኢትዮጵያ በድምቀትና በምልዓት የምትታይበት የኢትዮጵያዊነት ቀን፣ በኢትዮጵያዊነት አሻራና ምልክት በሆነው ሲዳማ ህዝብ በሃዋሳ ከተማ ለማክበር እንኳን በሰላም መጣችሁ፤ እንኳን ተገናኘን ለማለት እወዳለሁ።

ኢትዮጵያ የሁላችን ቤት ናት። በኢትዮጵያ ውስጥ በጋራ የምናድግበት፣ በጋራ የምንበለጽግበት፣ በጋራ በሰላም የምንኖርበት ሁኔታ መፍጠር ካልቻልን ማናችንም መኖር፣ መበልጸግ፣ ወጥተን መግባት አይሆንልንም። የእያንዳንዳችን ችግር ሊፈታ የሚችለው የኢትዮጵያ ችግር ሲፈታ ብቻ ነው። በተናጠል የራሱን ወረዳ፣ የራሱን ዞን፣ የራሱን ክልል፣ የራሱን ከተማ ችግር መፍታት የሚያስብ ማንኛውም ግለሰብ እና ቡድን ከኢትዮጵያ ችግር በፊት ቀድሞ የሚፈታ የሰፈር ችግር እንደሌለ መገንዘብ ተገቢ ነው። በዚህ ቀን የሁላችን ታሪክ፣ የሁላችን ቅርስ፣ የሁላችን እሴት የኢትዮጵያ ሀብትና ኩራት ሆኖ የሚታይበት፤ ሁላችን ለኢትዮጵያ እጅግ አስፈላጊ መሆናችንና

በኢትዮጵያ ጥላ ስር ውበታችን ጎልቶ የሚታይበት መሆኑን የምንማርበት በመሆኑ የኢትዮጵያዊነት ቀን የመማማሪያ ቀን ስለሆነ እንኳን ደስ ያላችሁ ልላችሁ እወዳለሁ።

ሀገር በቤት ይመሰላል ማገሩ፣ ወራጁ፣ ቋሚው፣ ጣሪያው ተሰናስለው ቤት እንደሚሆኑት ሁሉ ሁሉም ብሄሮች፣ ሁሉም ዜጎች፣ ሁሉም ባህሎች፣ ሁሉም ታሪኮች እያንዳንዳቸው ሰበዝ ሆነው ሲደመሩ ታላቋን ውቧን ኢትዮጵያን የሚያሳዩን ስለሆነ በተናጠል ጎልተን ለመታየት ሳይሆን በጋራ ለማበብ ልባችን ቀናና አእምሯችን የሚያስተውል እንዲሆን ላሳስባችሁ እወዳለሁ። ትናንት ያለፈና ያመለጠ ታሪክ ነው፤ ትናንትን ለመማሪያ ብቻ መጠቀም ከቻልን ነጋችን ያማረ ይሆናል።

ዛሬ የትናንትናውን ጉዳይ እያነሳን ብንወቅስና ብናወድስ ሰዎቹ የሉምና አይሰሙንም፤ ያጠፉትም ያለሙትም አልፈዋል ። እኛ መልካም ነገን ለልጆቻችን ለመገንባት፣ መለስ ብለን ከነገ የምንማር፣ የተሻለች ነገን የምንሰራ ቢያንስ መጪው ትውልድ ከልመና የተገላገለ ሠርቶ የሚበላ፣ ጎረቤቱን የሚወድ ፣ የሌላውን ቋንቋ ለመማር የሚጥር በኢትዮጵያ ህዝብ አንድነትና የጋራ እሴት የሚኮራ እንዲሆን ወደኋላ መለስ እያልን መሰዳደቡን ፣ መገፋፋቱን ፣ መጣላላቱን ተወት ብናደርገው ለእኛም ለልጆቻችንም የሚበጅ ስለሆነ ማስተዋል አይንፈገን ልላችሁ እወዳለሁ።

ኢትዮጵያ ውስጥ ከግራ እስከ ቀኝ ዋልታ የረገጡ ሃሳቦች አሉ፤ ከትናንትና መላቀቅ ያልቻሉ፣ ነገ የሚሰራበትን እያንዳንዱን ብሎኬት ዛሬ የሚያፈርሱ፣ በጋራ መኖር ሳይሆን መገፋፋትን የሚመርጡ፣ በራሳቸው አጀንዳ ሳይሆን በሰዎች አጀንዳ የተገዙ፣ በንጹኃን ደም ፖለቲካ ሠራን ብለው የሚያስቡ ጥቂት ግለሰቦችና ቡድኖች እንዲሁም የሚዲያ ሰዎች አሉ። ለእነዚህ ለጊዜው ለሳቱ ወንድሞችና እህቶች ያለኝ ምክር ዛሬም ኢትዮጵያ ትፈተናለች እንጂ አትሸነፍም። ደጋግመን በኢትዮጵያ አንድነትና በኢትዮጵያ አሸናፊነት ልናስታውሳቸው እንደሞከርነው ሁሉ አሁን የገጠመን ፈተና ምንም እንኳ አሳዛኝ ቢሆንም በተባበረ ክንድ ሀገርና የነገን ትውልድ መገንባት በሚፈልጉ ዜጎች ትብብር ይህንን ፈተና እናሸንፋለን፣ ኢትዮጵያም ትበለጽጋለች።
የያዝነውን እውነት፣ የያዝነውን ፍቅር፣ የያዝነውን መደመር በአልባሌ ተረት ተረት ሊያጠለሹ የሚሞክሩ ቡድኖች የያዝነውን እውነት ማጥፋትም፣ ማጠልሸትም ስለማይችሉ ኢትዮጵያ በልጽጋ በከፍታ ማማ ላይ ተቀምጣ ለልጆቻችን የምናሸጋግራት መሆኑን ዳግም ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ።

የኢትዮጵያ ብልጽግናና ልዕልና የሚመነጨው ከእውነትና ከፍቅር ነው ። የተሸናፊዎች አጀንዳ ጥላቻ፣ ግድያ፣ መገፋፋት፣ ንጹሃንን ማጎሳቆል ነው። ከግራም ከቀኝም ያሉ ዋልታ የረገጡ እሳቤዎች ለኢትዮጵያ ስለማይበጁ እጅግ የተከበራችሁ የኢትዮጵያ ዜጎች ወጣቶች የተማራችሁም ያልተማራችሁም ኢትዮጵያዊያን ለእያንዳንዱ አጀንዳ ምላሽ ከመስጠታችሁ በፊት የአጀንዳውን ባለቤትና ምንጭ ለማወቅ እንድትሞክሩ፤ በሰከነ መንገድ ነገር እንድታዩ፤ ኢትዮጵያን ለመናድ ለአንድ ወር እንኳን ሰላም እንዳትሆን አዳዲስ አጀንዳ እየፈጠሩ ለሚያውኩን ሰዎች ጆሮ የምትሰጡ እንዳትሆኑ፤ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በትብብር፣ በህግ፣ በአንድነት ሰላማችንን አንድነታችንን ማስከበር እንድንችል የበኩላችሁን ሚና እንድትወጡ በታላቅ ትህትና አደራ ልላችሁ እወዳለሁ።

በሰሜን ኢትዮጵያ የጀመርነው ሰላም ዘላቂና አስተማማኝ እንዲሆን በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል የሚጠበቅብንን ሁሉ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት እያደረግን ስለሆነ ሰላም ለሰሜን፣ ሰላም ለምዕራብ፣ ሰላም ለምስራቅ፣ ሰላም ለደቡብ ሰላም ለኢትዮጵያ፣ ሰላም ለአፍሪካ እንዲሆን በጋራ፣ በትብብርና በፍቅር እንድንቆም ከታላቅ ትህትና ጋር አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ።

እጅግ የተከበራችሁ የኢትዮጵያ ህዝቦች ምንም ድንግዝግዝ ምንም ጨለማ የሚመስሉ ጉዳዮች ቢታዩም አሁንም እኔ በጉልህ የሚታየኝ የኢትዮጵያ ብልጽግና፣ የኢትዮጵያ ጽናት፣ የኢትዮጵያ ታላቅነት፣ የኢትዮጵያ ከፍታ ስለሆነ ሪቫን የምትቆርጡ እንጂ ተስፋ የምትቆርጡ ዜጎች አትሁኑ። ሰዎች ለከፋ እሳቤዎቻቸው፣ ለእኩይ ሥራዎቻቸው ጊዜያቸውን፣ ገንዘባቸውን፣ ጉልበታቸውንና ህይወታቸውን እያጠፉ ስለሆነ እኛ ለታላቋ ኢትዮጵያ ሰላምና ብልጽግና አስር ቦታ ብንበጣጠስ ልጆቻችን ቀጣጥለውና አጉልተው የሚያሳዩት ማንነት ስላለን ለኢትዮጵያ ሰላም፣ ለኢትዮጵያ ፍቅር፣ ለኢትዮጵያ አንድነት ያላችሁን ሁሉ ሰጥታችሁ በትጋት እንድትሰሩ በታላቅ ትህትና አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ። ዛሬም እንደትናንቱ ይህንን ፈተና ለጥንካሬ፣ ለብርታት፣ ለመሻገር፣ ለማሻገር ተጠቅመንበት በአዲስ ድል በቅርቡ እንደምንገናኝ ቅንጣት ታክል ጥርጣሬ የለኝም።

ለጠላቶቻችን ትንሽ ከፍ ያለ ጠንካራ ሃሳብ እስኪኖራችሁ ድረስ ተረጋጉ፤ አሁኑ አጀንዳችሁ ኢትዮጵያን ማፍረስ ቀርቶ ሊነቀንቃት ስለማይችል በደንብ ተዘጋጅታችሁ እንድትምጡ ምክር እለግሳችኋለሁ ። በትናንሽ ሃሳብና አጀንዳ የምትቆም ኢትዮጵያ

የዛሬ አራት ዓመት ቆማለች፤ ዛሬ ያለችው ኢትዮጵያ ጠንካራ መከላከያ ሰራዊት ያላት፣ ጠንካራ የፖሊስ ሰራዊት ያላት፣ በአዲስ ትውልድ ውስጥ ከፍተኛ ፍቅርን፣ መደመርን፣ ይቅርታን የዘራችና በቀላሉ የማትናወጥ ስለሆነ ይህን የከሸፈ አጀንዳችሁን ዳግም አሸንፈን በኢትዮጵያ ብልጽግና፣ ልዕልና አሸናፊነት ዳግም እንደምንገኝ ያለኝን ሙሉ እምነት እየገለጽሁ፤ የሃዋሳ ከተማ ነዋሪዎች፣ የሲዳማ ክልል መንግሥት እንዲሁም የሲዳማ የሀገር ሽማግሌዎች በቄጤላ ባጠቃላይ ላደረጋችሁልን አቀባበል ለነበረን ቆይታ ኢትዮጵያ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት፣ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በእጅጉ ያመሰግናችኋል።

ሃዋሳ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ከተማ፣ መቀሌ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ከተማ፣ ባህርዳር የሁሉም ኢትዮጵያዊ ከተማ፣ ጅግጂጋ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ከተማ፣ ሰመራ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ከተማ፣ ጂማ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ከተማ፣ ጋምቤላ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ከተማ፣ አሶሳ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ከተማ፣ ሐረር የሁሉም ኢትዮጵያዊ ከተማ፣ ቦንጋ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ከተማ፤ ኢትዮጵያ የሁሉም አፍሪካ መናኸሪያና መዳረሻ እስከምትሆን ስራችን ይቀጥላል። ኢትዮጵያ የአፍሪካ እምብርት ስለሆነች ሁሉንም የአፍሪካ ህዝቦች ለመቀበል ለማስተናገድ የሚያስችል መሬት፣ የውሃ፣ የሀብት ብቃት አላትና በድህነት በጥላቻ ሳንሞላ በመደመር በፍቅር አቅፈን የምንሻገር፤ የምናሻግር መልካም ሀገር ለልጆቻችን የምናወርስ እንድንሆን ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን፣ ምድራችንን፣ ሰማያችንን፣ ቅጥራችንን በሙሉ እንዲባርክ እንጸልያለን።

**ኢትዮጵያ ታሸንፋለች፣ ትሻገራለች፣ ትበለጽጋለች**

**እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ ።**

**ህዳር 29 ቀን 2015 ዓ.ም**

**ሃዋሳ ከተማ**









# በብላቴ ወንዝ ተፋሰስ የተካሄደ ልማት ጉብኝት

ታህሳስ 18 ቀን 2015 ዓ.ም

ዛሬ እያየን ያለነውን የብላቴ ፍራፍሬ የእርሻ ማሳን ከሰባት ስምንት ወራት በፊት የማየት እድሉ ገጥሞኝ ነበር። ያኔ ስናየው እርሻው ውስን በሆነ ሄክታር መሬት ላይ ስለነበር ተጨማሪ እንዲስፋፋ አቅጣጫ ስለሰጠን ሥራው ምን ላይ እንደደረሰ ለማየት ነው ዛሬ የመጣነው። እንግዲህ ዛሬ ስናይ  እንድናስታውስ ያደረገን ነገር አንድ የሚገርም አባባል መጽሐፉ ምሳሌ ላይ አለ እጅግ የሚገርም አባባል ነው << በድሆች ማሳ ላይ ብዙ ሲሳይ አለ፤ በፍርድ መጉደል በተነሳ ግን ይጠፋል>> ይላል። በድሆች ማሳ ላይ ብዙ ሲሳይ አለ፣ የሚትረፈረፍ ፍሬ አለ፣ ያ ፍሬ እንዳይታጨድ፣ እንዳይበላ፣ ለውጤት እንዳይበቃ የሚያደርገው የፍርድ መጓደል ነው የሚል እሳቤ አለው። በኢትዮጵያ ማሳ ላይ በኢትዮጵያ እርሻ ላይ እጅግ በሚያስገርም ሁኔታ ብዙ ሲሳይ አለ፣ ብዙ ፍሬ አለ። ኢትዮጵያን ከፍሬዋ ተቋዳሽ እንዳትሆን፣ ከፍሬዋ በልታ የምትጠግብ እንዳትሆን፣ ለማኝ እንድትሆን ያደረጋት ነገር የፍርድ መጓደል፣ ዜጎችን በእኩል ዐይን አለማየት፣ ወንድማማችነትን አበርትቶ አለማየት ጥላቻን መዝራት፣ ጸብን መዝራት፣ መገፋፋትን መዝራት ከመብዛቱ የተነሳ ነው።

ከዚህ ብንቆጠብ ብላቴ ሁላችሁም እንደምታውቁት በረሃ ነው፤ የሚሞቅ በረሃ ነው፤ እንኳን ልትቆምበት እጅግ የሚሞቅ፣ የውሃ ችግር ያለበት የወባ በሽታ የሚገኝበትና ወታደር ማሰልጠኛ ካምፕ የነበረበት አካባቢ ነው ። ባለፈው ዓመት ገደማ ነው ይህ ወታደራዊ ካምፕ ዙሪያው በሙሉ ወደ እርሻ ይቀየር ያልነው። ዛሬ ምን እያየን ነው? ሙዝ፣ ፓፓያ፣ አቡካዶ፣ ሎሚ፣ መንደሪን፣ ሮማን፣ የወይን ፍሬ ያላየነው ፍራፍሬ አይነት የለም፤ ሁሉም ደግሞ አስደማሚ ነው። ባለቤቱ እንደነገረን በቀን በርከት ያሉ መኪናዎችን ይጭናል የቀን ገቢ ሶስት አራት ሚሊዮን ብር ገደማ ነው ያለው።
በኢትዮጵያ ውስጥ በብዙ ቦታ ይህን ማድረግ ይቻላል በረሃ ነው ብልን የጣልነው ቦታ ብዙ ነው፣ ከምንሰራበት የማንሰራበት ቦታ ይበልጣል። ሥራ መስራት ስንችል፣ መልማት ስንችል፣ ማደግ ስንችል ከተማ ውስጥ ሥራፈት ሆነን የምንጨቃጨቅና የምንገፋፋ፣ የምንበላላ ለምን እንሆናለን። ለምን ማስተዋል እናጣለን? ሰው የልብ ንጽህናና ቅንነት ከሌለው የሚሰራው ሥራ አይከናወንለትም። እዚህ የምናያቸው ሰዎች የእጃቸው ሥራ ተባርኮ፣ ተከናውኖ የምናየው ከልባቸው ጋር የሚያያዝ ጉዳይ ነው።

እዚህ ጋር ሁለት አርሶ አደሮች እናያለን ዳኜ የሚባል የኦሮሚያ ክልል ተወላጅ እና በላይነህ ክንዴ የሚባል የአማራ ክልል ተወላጅ፤ አባቴ ነው፣ ልጄ ነው፣ ወንድሜ ነው እየተባባሉ በጋራ የሚሰሩትን ሥራ አይተናል። ሰው በጋራ መስራት ፍላጎት ካለው ከወንዝ ማዶ እና ከወንዝ ወዲህ የሚለው ጉዳይ አይከፋፍለውም። ሰው በጋራ ሠርቶ ለመለወጥ ህልም ካለው ከተራራ ማዶ ያለው ጠላቱ ሊሆን አይችልም። ኢትዮጵያዊያን ልንገነዘብ የሚያስፈልገው ነገር ከወንዝ ማዶ የአጎትህ ልጅ ነው ያለው፣ ከተራራ ማዶ የአክስትህ ልጅ ነው ያለው፣ ባዳ የለም ቤተሰብ ነው።

እኔ ያለኝ መልክ፣ እኔ ያለኝ ቁመናና እኔ ያለኝ የአነጋገር ዘዬ አንተ የለህም፣ አንተ ያለህ እኔ የለኝም። ያ ማለት ሰዎች አይደለንም ማለት አይደለም። እያንዳንዱ ሰው፣ እያንዳንዱ ጎረቤት፣ እያንዳንዱ ሰፈር፣ እያንዳንዱ ክልል የራሱ ሆነ ጸባይ አለው። ከልምምድ የመጣ ጸባይ፣ ከኑሮ ዘዴ የመጣ ጸባይ ቋንቋው፣ ባህሉ፣ አነጋገሩ፣ አለባበሱ ከብዙ ልማድ የመጣ ነው። ያ ነገር ግን ሰውነቱን የሚያሳጣው አይደለም።
ሰው ሰው መሆኑን አምኖ ከሰው ጋር በሰላም መኖር ያለውን ፋይዳ አምኖ፤ ከሰው ጋር በሰላም መኖር ለልጆቹ ሰላማዊና የጸናች ሀገር እንደሚቻል አምኖ ከአልባሌ ወሬና ጭቅጭቅ ራሱን ማራቅ አለበት። የሚያዋጣን ልማት ነው። ታስታውሳላችሁ አረንጓዴ አሻራ ስንል ስንዴ የሚከናወን አልመሰለውም ነበር ብዙ ሰው። አሁን ፍራፍሬ ስንልም ብዙ ሰው አልመሰለውም። ይኸው በዓመት ተኩል ተዓምር እያየን ነው። በዚህ በረሃ ላይ ልክ ይህን እንዳየነው በዓመት፣ ዓመት ተኩል ደግሞ የወተቱም፣ የማሩም፣ የዶሮውም፣ የእንቁላሉም ጉዳይ እንዲሁ ይሆናል። ለምንድን ነው የሚሆነው ከተባለም የልብ ንጽህና ካለ የሠራኸውን ሥራ የሚያከናውን ፈጣሪ አለ። ልባችን ንጹህ ሁኖ በእውነተኛ ልብ በንጹህ አእምሮ፣ በንጹህ እጅ በእውነተኛ ማንነት ለመለወጥ ብንሠራና ብንተጋ ፈጣሪ ያግዘናል። ከዛ ውጭ ያለው መሻትና ጥማት ግን ኪሳራ ነው።
ወንድም ወንድሙን ገድሎ፣ ወንድም ወንድሙን ሰድቦ፣ ወንድም ወንድሙን ገፍቶ እንደዚህ አይነት የረባ ነገር ሊያይ አይችልም። ወንድም ወንደሙን አቅፎ ሲሰራ ግን እጅግ የላቀና ያማረ ነገር ሊፈጠር ይችላል።

የተከበረው የተወደደው በድህነት በችግር በርሃብ የሚታወቀው የኢትዮጵያ ህዝብ ብዙ ሀብት በእጁ አለ። ዓይናችን ይገለጥ፣ ልባችን ይጽዳ መገፋፋት እና ሰፈርተኝነት እንተው፣ ትልቅ ሀገር ነው ያለን አንዳችን ሌላችንን እንደሌለ ማሰብ አንችልም፤ ስንፈጠር የተፈጠርነው በዚህ መንገድ ነው። አብረን በጋራ ተከባብረን ብንኖር ግን መሬታችን ሰፊ ነው፣ በረከታችን ሰፊ ነው፣ ማሳችን በሲሳይ የተሞላ ነው። ያንን ሲሳይ

ያንን ፍሬ እንዳንበላ የሚያደርገን የጥላቻ፣ የዘረኝነት፣ የጽንፈኝነት፣ የዋልታ ረገጥ አስተሳሰብ ቀርፈን፣ ሰክነን፣ መሬት ረግጠን ከሰማይም ፈራጅ እንዳለ አውቀን ብንሰራ መልካም ነው። ብዙ ጊዜ የምንታወክባቸው ጉዳዮች ፍሬ አልባ ናቸው። የምንጣላበቸው ጉዳዮች በትክክለኛ ሚዛን ላይ ስናስቀምጣቸው እዚህ ግባ የሚባሉ አይደሉም። ላባ በሆነ ሃሳብ አንባላ፣ ሚዛን በሚደፋ እርሻ ሥራዎች የሌማት ትሩፋት ላይ፣ አረንጓዴ አሻራ ላይ፣ ስንዴ ላይ፣ አካባቢን ማልማት ላይ፣ በልቶ መጥገብ ላይ፣ ጎረቤት ማካፈል ላይ፣ ለድሃ ማካፈል ላይ ብንበረታ ጥሩ ነው።

ሌብነት ካንሰር ነው። መጀመሪያ ትሰርቃለህ፣ ከዚያ ሰርቆ መኖር ስለማይቻል ግጭት ትፈጥራለህ፣ ግጭት ከፈጠርክ በኋላ ደግሞ ግጭት ስለሚያራርቅ ከትልቅ ሀገር ወደ ትንሽ ሀገር ትጠባለህ። ትልቅ ሀገር መሆን ስትችል መጀመሪያ ሌብነት እያሳሳቀ ይገፋሃል፣ ግጭትን ይስባል፣ ግጭት ደግሞ ይበትነናል እንዳንበተን አንጋጭ፤ እንዳንጋጭ የጥቅም ግጭት እንዳይፈጠር አንስረቅ ነገር ግን በተሰጠን ጊዜ በንጹህ ልብና አእምሮ እንስራ። ያ ሲሆን መልካም ነገር ይመጣል። የደካማና የሰነፍ ሰዎች ችግር አጀንዳ መቅረጻቸውና መስነፋቸው ሳይሆን በነሱ ደካማ አጀንዳ ውስጥ መላው ኢትዮጵያ ታጥሮ እንዲቀመጥ ያደርጋሉ። የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ንቃ በልማት ጉዳይ ሲሆን ተሰለፍ፣ በሰላም ጉዳይ ሲሆን ተሰለፍ፣ በሚጠቅም ጉዳይ ሲሆን ተሰለፍ፣ ለድሃ ማጋራት ሲሆን ተሰለፍ፣ ከዚያ ውጭ ባለው ሆያ ሆዬ ሲሆን ግን ጊዜ አታባክን፤ ሆያ ሆዬ ኢትዮጵያን ያራቆተ፣ ኢትዮጵያን ያደኸየ እንጂ የሚጠቅም አይደለም። የሚጠቅመን አሁን መተሳሰብ፣ መተዛዘን፣ ይቅር መባባል፣ አርቆ ማየት፣ ለልጆቻችን መልካም ሀገር መተው፣ በጋራ መቆም ነው። በጋራ ስንቆም እንበረታለን፣ እንጸናለን። ቻይና 1.4 ቢሊየን ህዝብ በጋራ እየቆመ ህንድ 1.4 ቢሊየን ህዝብ በጋራ እየቆመ፤ አሜሪካ 300 ሚሊየን ህዝብ የሁሉም ብሔር ህዝብና ቋንቋ ስብስብ አንድ ላይ እየቆመ ኢትዮጵያን ለሺህ ዘመናት አብረን ኖረን ከመቶ ያነሰ ቋንቋ ልዩነት ይዘን እንዴት መኖር ይሳነናል።

አፍሪካ ላይ እኮ ታንዛኒያ፣ ናይጄሪያ ብንሄድ ከእኛ በላይ የቋንቋ ስብጥር አለ። ቋንቋ የሚያባላ አይደለም፣ መልክ የሚያባላ አይደለም። ይልቁንም አንዱ ከአንዱ ተምሮ አንዱ ከአንዱ ተቋድሶ ጠንክሮ በርትቶ እንዲኖር የሚያስችል ነውና ልባችንን ወደ ቀናው ነገር ብንወስድ አእምሯችንን ከክፉ እሳቤ ብንጠብቅ የሰው ልጅ ያለውን ክብር ብንገነዘብ፣ ለማገልገል የተሰጠንን እድል ብንጠቀም ኢትዮጵያ ሲሳይ የሞላባት፣ የተረፋት፣ የተትረፈረፋት ብዙዎች ያዩት፣ እኛ ግን ልንገነዘበው ያልቻልናት ሀገር ናት

እናም እንድንነቃ፣ እንድንበረታና ወደሚጠቅመው፣ ፍሬ ወደሚያፈራው፣ ሲሳይ ወደ በዛበት ነገር፣ ፍርድ ወደማያጓድልበት ነገር እንድንሄድ አደራ ማለት እፈልጋለሁ።
እጅግ አስደሳች ሥራ ነው የተሠራው። አሁንም ተጨማሪ ሥራ እንዲሰራ ድጋፍ እናደርጋለን። በሁሉም ቦታ ፍራፍሬ ይብዛ፣ ስንዴ ይብዛ፣ ጤፍ ይብዛ፣ በቆሎ ይብዛ፣ ምግብ ይብዛ፣ ውሃ ይብዛና ይህ ነው ለኢትዮጵያ የሚያስፈልገው። እኔ እንደማስበው አሁን በጀመርነው መንገድ ኢትዮጵያዊያን ልባችንን አንድ አድርገን አንድ አምስት ዓመት ብንሰራ ከኢትዮጵያ በእርዳታ የቀረበ (Ethiopian Aid) ብለን የምንረዳበት ጊዜ ከፊታችን ቅርብ ነው። የመረዳት ታሪካችንን በመርዳት የምንቀይርበት ታሪካችን ቅርብ ነው። የድህነት፣ የልመና፣ የታሪክ እጥፋት እየተከናወነ ነው። የታሪክ እጥፋት ደግሞ ጉልበት ድካም ፍትጊያ ይጠይቃል። እንዲሁ በከንቱ የታሪክ እጥፋት አይፈጠርም። የታሪክ እጥፋታችን ስንዴ እንለምን ነበር፤ ስንዴ እንረዳለን፣ ብርቱካን፣ ሙዝ፣ አቮካዶ እናስገባ ነበር፤ እንሸጣለን ይሄ ሲፈጠር ኢትዮጵያ ልኳ ኢትዮጵያ ቦታዋ ይረጋገጣል። እናም ኢትዮጵያን የምትወዱ ሁሉ በቀና ልብ፣ በትብብር መንፈስ፣ በይቅር ባይነትና በአስተዋይነት አብረን እንድንቆም አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

ሰላም ለኢትዮጵያ ይሁን፤ ፍቅርና አንድነት ለኢትዮጵያ ይሁን፣ መተሳሰብ ለኢትዮጵያ ይሁን፣ መበልጸግ ለኢትዮጵያ ይሁን፣ መርዳት ለኢትዮጵያ ይሁን። የእኛ መሻትና ፍላጎት ይሄ ነው።

**ታህሳስ 18 ቀን 2015 ዓ.ም**
**ብላቴ**







# በወላይታ ሶዶ የዱቄትና ዳቦ ፋብሪካ ምርቃት

ታኅሣሥ 14 ቀን 2015 ዓ.ም

**ክቡር አቶ ርስቱ ይርዳው የደቡብ ክልል ርዕሰ መስተዳድር፣**
**ክቡር አቶ ተስፋዮ ይገዙ የደቡብ ክልል ም/ርዕሰ መስተዳደር ይህ ፕሮጀክት እንዲሳካ ከፍተኛ ጥረት ያደረጉ ወንድማችን፣**
**የተከበራችሁ የሀገር ሽማግሌዎች፣ እናቶች፣ እህቶች፣ ወንድሞች፣**

እንዲሁም ከዚህ ቀደም በደግነታቸው የምናውቃቸው ብዙ የረዱ ወንድማችን አባታችን ሼክ ሙሃመድ አላሙዲን ጀማል የሚባል ጥሩ ልጅ ካገኙ በኋላ ሀብታቸው አልባሌ ቦታ ከመበተንና ከመርጨት ለድሃ እንዲደርስ ዳቦ ብቻ ሳይሆን አዲስ አበባ ውስጥ ብዙ መመገቢያ ቦታዎች በትክክለኛው ሀብት ሊፈስ የሚገባበት ቦታ እንዲደርስ ያደረገውን ጀማል እንዲሁም ሼክ ሙሃመድ አላሙዲን ለዚህ ፕሮጀክት ድጋፍ ስላደረጉ ማመስገን እፈልጋለሁ፡፡

ክብርት ቀዳማዊት እመቤት ከግራ ከቀኝ የተገኘው ሁሉ ለድሃ አቅመደካሞች እንዲገለገሉበት፤ ለአቅመ ደካሞች ቤት በመስራት፣ የዳቦ ፋብሪካ እንዲገነባ በማድረግ፣ ትምህርት ቤቶችን በማሰራት፣ ለዐይነ ስውራን ረጂ የሆነ መነጽር ለአካል ጉዳተኞች ዊልቸር፣ አብዛኛውን በማህበራዊ ችግር ለሚስተጓጎሉ ወንድና ሴት ልጆቻችን እርዳታ የሚሆን ነገር በማድረግ ስላላት ልብ፣ ስላላት መሰጠት፣ ስላላት ድጋፍ በሶዶ ከተማ ህዝብና በናንተም ስም እጅግ አድርጌ ላመሰግናት እወዳለሁ፡፡

ቀዳማዊትን በዚህ መልኩ የማመስግናት ብዙ ቀዳማዊቶችን የማወቅ እድል ስላለኝና ልቧን በቅርበት ስለማውቅና ድሃን የሚወድ፣ ድሃን የሚረዳ ሰው እጅግ ጥሩ ስለሆነ የእኔም ብትሆን በግልጽ ብትመሰገን አይከፋም ብዬ ነው፡፡

እንግዲህ ዛሬ የምናስመርቀው ሶዶ ዳቦ ፋብሪካ ከመሰረቱ ሃሳቡን መገንዘብ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ የዛሬ አራት ዓመት አዲስ አበባ ውስጥ ሶስት መቶ ሺህ ዳቦ አይጋገርም፤ ፋብሪካዎቹ ሁሉ ተደምረው ሶስት መቶ ሺህ ዳቦ የመጋገር አቅም አልነበራቸውም፡፡ ዛሬ አዲስ አባባ ውስጥ በሚሊየን የሚቆጠር ዳቦ ይጋገራል፤ አዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን ዋና ዋና ከተሞችም እንዲሁ ሰፋ ያለ ቁጥር ያለው ዳቦ

የሚያመርት ፋብሪካ ኢትዮጵያ ይኑራት ተብሎ ዛሬ በሶዶ፣ ነገ በሃዋሳ በቅርቡ በጎንደር፣ በሐረር፣ በቦንጋና በሌሎች ዋና ዋና ከተሞች ይመረቃል። ይህ ኢትዮጵያን የዳቦ ቅርጫት የማድረግ ህልማችን ፍላጎታችን የመጀመሪያው ጡብ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ዛሬ በአርባምንጭ አየር ማረፊያ በ2011 ዓ.ም የተከልናቸው ችግኞችን የማየት እድል አግኝቼ ነበር። ዛሬ ላይ ጫካ ሁነዋል፤ ጫካ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን በእናንተው ዞን ወላይታ ዞን እዚሁ በብላቴ አንድ ዓመት ተኩል በሆነ ጊዜ የተከልናቸው የፓፓያ፣ የሙዝና የብዙ ፍራፍሬ አይነቶች ብላቴ የተሰኘውን በረሃ እንዴት ገነት እንዳደረጉት እናንተም እኛም ማየት ችለናል።

ስንዴ በበቂ ሁኔታ ማምረት ብቻ ሳይሆን ለጎረቤት ሀገሮች ኤክስፖርት ለማድረግ እየሰራን እንደሆነ ይታወቃል። እዚህ ላይ ዳቦ ፋብሪካ ሲጨመርበት ስንዴውን በትራክተር አርሰን፣ በፋብሪካ ጋግረን በቀላሉ መብላት የምንችልበት እድል ሲፈጠር ቀጥሎ የሚነሳው ጥያቄ ዳቦ ብቻ በቂ አይደለም፣ ወተት ይፈልጋል፣ ማር ይፈልጋል፣ አቩካዶ ይፈልጋል፣ ፓፓያ ይፈልጋል። ኢትዮጵያ በዳቦ ብቻ ረክታ የምትቀም ሳይሆን ዳቦ የሚያባላ ማርና ወተት ማምረት ትችላለች ተብሎ የሌማት ትሩፋት በስፋት ተጀምሯል።

ወትትና ማር የሚፈልቅባት የተባለችው ሀገር እንደተጠበቀች ሆና የእኛዋም ሀገር ወተትና ማር እንዲፈልቅባትና ጠግባ የምታካፍል እንድትሆን ሁላችንም በተስማማና በተባባረ ክንድ አብረን ልንሠራ ይገባል። ለልማት፣ ለትምህርት፣ ለዳቦ የሚሰራው ሥራ ለትውልድ የሚሰራ ሥራ ነው። ዛሬ 9.2 ሚሊየን የሚሆኑ ተማሪዎች በቀን ሁለት ጊዜ በነጻ ምግብ እያገኙ ነጻ ትምህርት ይማራሉ ሲባል ይህ የዳቦ ችግር ሳያቆመው በነጻ የሚማር ዘጠኝ ሚሊየን ተማሪ ነገ የኢትዮጵያ መሰረት እና አጽኝ ሆኖ ይቆማል ማለት ነው። ያልተማረ ሰው ሀገር አይቀይርም ደቡብ ኮሪያ፣ ጃፓን፣ ታይዋን የሚባሉ ሀገራት በጥቂት አስርት ዓመታት ውስጥ እንደኛ ደሃ ነበሩ ያለፉት ሃምሳ ዓመታት ላይ የደረሱባቸውን አስደማሚ የእድገት ደረጃዎች የደረሱት በልጆቻቸው ላይ አበክረው በትምህርት በምግብና በጤና ስለሰሩ ነው። ይህ ሥራ ዛሬ ፍሬው በጉልህ ባይታይም ነገ ኢትዮጵያን የሚያጸናና ከትልልቆች ተርታ የሚያሰልፍ ስለሆነ አሁን ያለው ትውልድ ነገን እያሰበ እንዲሰራ አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

ሁላችሁም እንደምታውቁት ሰዎች ዛፍ ላይ ድንጋይ የሚወረውሩት ዛፉ የሚጣል የደረሰ ፍሬ ያለው እንደሆነ ነው። ሰው ባህርዛፍ ላይ ድንጋይ አይወረውርም፣ ሾላ ላይ ድንጋይ ይወረውራል፤ ፍሬ ስለሚወድቅ፣ ፍሬ የሌለው ነገር ላይ ሰው ድንጋይ አይወረውርም።

ዛሬ ኢትዮጵያ ላይ የሚወረወረው ሁሉም ድንጋይ ኢትዮጵያ ፍሬ እንዳላት የገባቸውና ድንጋይ ቢወረወር የሚንጠባጠብ ነገር አለ ብለው የሚያምኑ ሰዎች በመኖራቸው መሆኑን ማወቅ አለብን። የሚወረወረውን ድንጋይ ብቻ ሳይሆን ፍሬያማ ሀገር እንዳለን መገንዘብ ያስፈልጋል። ፍሬ በሌላቸው ሀገሮች ማንም ድንጋይ ሲወረውር ስለማይገኝ። በእኛም ሁኔታ በየቀኑ አጀንዳ እየተፈጠረ ይጥቀም አይጥቀም፣ የአጀንዳው ባለቤት ይታወቅ አይታወቅ ሰላም የሚባል ነገር ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይሰማ የሚፍጨረጨሩ ኃይሎች ዋናው ዓላማ እኛ ሰላም ካገኘን በየቀኑ የዳቦ ፋብሪካ የሚባል ፍሬ፣ ስንዴ፣ አቩካዶ፣ ፓፓያ የሚባል ፍሬ እንዳለን ስለሚያውቁ ነው ድንጋይ የሚወረውሩት እንጂ እጃችንን አጣጥፈን ብንቀመጥና ከእኛ የሚፈልቅ ፍሬ ባይኖር ማንም ጊዜ አጥፍቶ ድንጋይ ሲወረውርብን አይገኝም።

ድንጋይ እየተወረወረብን ያለው ፍሬ ስላለን ነው፤ የእኛ ሥራ መሆን ያለበት የሚወረወርብንን ድንጋይ ማየት ሳይሆን ፍሬያችንን ማባዛትና ያላግባብ እንዳይረግፉ መጠበቅ መሆን አለበት። ፍሬያችን እንዳይረግፍ መጠበቅና ማብዛት ከቻልን የሚወረወረው ድንጋይ ቢወረወርም ጥቂቱን አራግፎ ብዙውን ማትረፍ እንችላለን። ሁለተኛ፤ እየበረከተ ሲሄድ ደግሞ ለመከላከልም ጉልበት ስለሚሆን ኢትዮጵያን የምንወድ በእኩልነት፣ በወንድማማችነት አብሮ መኖርን አናጎልም፤ እንሻል ይሆናል እንጂ አናከስርም ብለን የምናስብ ሰዎች ሁሉ ፍሬያችን እንዲበዛ የሚወረወርብን ድንጋይ እንዲቀንስ አጀንዳ ሲፈጠር ማን ፈጠረው ለምንስ ተፈጠረ፣ ግቡስ ምንድን ነው ብለን አስልተን እርምጃ የምንወስድ እንድንሆን መጀመሪያ እርምጃ ወስደን በኋላ የምናስብ እንዳንሆን አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ።

ኢትዮጵያ ውስጥ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሰላም አየር መተንፈስ የሚያስችል እድል እየተፈጠረ ነው። በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የነበረው እጅግ አስከፊ፣ አሳዛኝ የነበረው የወንድማማቾች እልቂትና ጦርነት የሚቆምበትና የሰላም አየር የምንተነፍስበት እድል እየተፈጠረ ይገኛል። ይህ እድል እንዳይበላሽ እንዳይመክን እያንዳንዱ ዜጋ አበክሮ ሊሰራ ይገባል። ሰላም ኢንቨስትመንት ይፈልጋል፤ ጊዜ፣ ጉልበት፣ ሀብት ኢንቨስት ካላደረግን እንዲሁ በዋዛ ሰላምን መጠበቅ አይቻልም። ሁላችሁም እንደምታውቁት በአፍሪካ እንዲሁም በእኛም ሀገር ሰላምን መገንባት እጅግ አስቸጋሪ ነገር ነው።
ጦርነትን ማስጀምር ቀላል ነገር ነው ልንዋጋ ነው ሲባል ብዙዎች ለምን እንኳን ሳይባል ሆ ብለው ይሰለፋሉ፤ ሰላም ሊመጣ ነው ሲባል ግን አኩራፊው ይበዛል፣ ሰላም እጅግ አድካሚ ሥራ ነው፣ ግን ፍሬው ያማረና ጠቃሚ ነው። ለዚህ ሰላም ሁላችንም በተባበረ

ክንድ እንድንሰራ አደራ ልላችሁ እወዳለሁ። ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ሁለት አደገኛ ዋልታ የረገጡ እሳቤዎችና ትናንሽ ቡድኖች ይታያሉ። ኢትዮጵያን የምንወድ በጋራ በትብብር በሰላም አብረን በማደግ የምናምን ሰዎች፣ ለኢትዮጵያ ቀናኢ ልብ ያለንና ልጆቻችን ሀገር አልባ እንዳይሆኑ የምንፈልግ ሰዎች በወላይታ ሶዶም፣ በድፍን ኢትዮጵያም የምንገኝ ሰዎች ያማረች፣ የተመቸች፣ የተሻለችና የበለጸገች ኢትዮጵያን ለሁሉም ኢትዮጵያዊ መፍጠር እንዳለብን የምናስብ ሰዎች ከሁለት ዋልታ የረገጡ እሳቤዎችና የኢትዮጵያን ካርታና ቅርጽ ከሚቀይሩ፣ ኢትዮጵያን ማስቀጠል ከማይችሉ፣ በመገፋፋት ከሚያምኑ ሰዎች መጠንቀቅና መታገል ይኖርብናል።

እነዚህ ሁለት ኃይሎች የኦሮሞ ሸኔ እና የአማራ ሸኔ ናቸው። የኦሮሞ ሸኔ እና የአማራ ሸኔ ቦታቸው ይለያይ እንጂ የሁለቱም ሃሳብ እኔ የምፈልጠው የምቆርጠው ኢትዮጵያ ካልሆነች በእኩልነት ኢትዮጵያን ማየት አልፈልግም የሚል እሳቤ ያላቸው፣ ሰላም የማይፈልጉ፣ በመሰዳደብ፣ በመበሻሸቅ፣ በመገዳደል ስልጣን የሚገኝ እንደሆነ የሚያስቡ፤ ያ ስልጣን ግን ሀገር ያጽና አያጽና ነገን አሻግረው የማያዩ ናቸው ። የኦሮሞ ሸኔ እና አማራ ሸኔ የኢትዮጵያን ካርታ የሚቀይሩ፣ በጋራ የማያኖሩ፣ ትናንሽ አጀንዳ የሚያጎሉና የሚበትኑ  በመሆናቸውን አውቀን በተለይም የኦሮሞ እና አማራ ህዝብ እንዲሁም ሰፊው ህዝብ ከጽንፈኝነት ዋልታ ከረገጠ በግድያ ከማሸነፍ አመለካከት እንዲጠበቅ፣ ማንኛውም ነገር ካለ በንግግር፣ በምክክርና በውይይት ለማስተካከል ልባችን የተከፈተ አእምሯችን የተከፈተ እንዲሆን አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ።
እልህ፣ ጸበኝነት፣ እኔ ብቻ የሚል እሳቤ አሁን ላለችው ኢትዮጵያ አይበጅም። የአማራ ሸኔ የኦሮሞን ሸኔ ማሸነፍ አይችልም፣ የኦሮሞ ሸኔ የአማራን ሸኔ ማሸነፍ አይችልም፣ የኦሮሞ ሸኔ እና የአማራ ሸኔ በጋራ ሆነው ኮንሶን ማሸነፍ አይችሉም። ኮንሶን ካላከበርክ በስተቀር፣ ዳሰነችን ካላከበርክ በስተቀር ደፍጥጠህ መኖር የሚባል ነገር ኢትዮጵያ ውስጥ አብቅቷል። ዳሰነች የኢትዮጵያ ኩራት፣ ፈርጥ፣ ወንድም ኮንሶ የኢትዮጵያ ፈርጥ፣ ኩራት፣ ወንድም ሌላውም እንዲሁ ብሎ የሚያስብና ከተከባበርን የበለጸገች የዳቦ ቅርጫት የሆነች ኢትዮጵያን መፍጠር ይቻላል። የማንም የበላይነት ሳይሆን የሁላችንም እኩልነት ነው የሚያስፈልጋት።

በእኩልነት ኢትዮጵያ አታከስርም፣ በእኩልነት የሚያከስር ብሄር የለም፤ ነገር ግን ስንገፋፋ፣ ስንሰዳደብ፣ ስንገዳደል፣ አንዳችን ሌላችንን ስናረክስ ያሸነፍን ይመስለናል እንጂ ግማሽ ጎኑን ቆርጦ ቆሞ መሄድ የሚችል ሰው የለም። አንዳችን ለሌላችን ግማሽ ጎን መሆናችንን አውቀን ሆን ተብሎ የሚፈጠሩ አጀንዳዎች፣ ፍሬ አልባ አጀንዳዎች ፍሬ የሌለው ዝም ብሎ አየር ላይ የሚናፈስ ማንኛውም ጸብ አጫሪ እሳቤን በጋራ

መታገል ያስፈልጋል። ያንን ካደረግን ልማታችን ብልጽግናችን ይረጋገጣል፣ ያንን ካደረግን ሀገራዊ አንድነታችን ይረጋገጣል፤ ያን ማድረግ ካልቻልን ግን ዋልታ የረገጡ አሳቤዎች ያፈርሱናል፣ ዋልታ የረገጡ ሃይሎች በጋራ መቆም እንዳንችል ያደርጉናል። ኢትዮጵያ በጣም ሀብታም ሀገር ነች። ሀብቷን ማየት የተሳናቸው ልጆቿ ቢያደኸይዋትም ብላቴ በረሃ የተባለው ቦታ ገነት መሆን ከቻለ፣ ወላይታ ውስጥ ብዙ ፍራፍሬ በየጓሮው እያያችሁ ነው እሱን ካበዛን፣ መሰረተልማት ከዘረጋን፣ የብላቴ አውሮፕላን ማረፊያ ካለቀ፣ መንገድ ከተገናኘ፣ ያመረትነውን መሸጥ የሌለንን መግዛት ከቻልን አስቡት እዚህ አካባቢ ያለውን እድል ጋሞ፣ ጎፋ፣ ወላይታ፣ ዳውሮ ምን ሊሰራ እንደሚችል አስቡት። እያንዳንዱ እጅግ ሰፋፊ በረከት አለው። ከሁሉ በላይ ደግሞ እጅግ ጨዋና ታታሪ ህዝብ አለው። ይህን ይዘን ተባብረን መስራት እንጂ መገፋፋት መገዳደል አያስፈልገንም። ሸክ ሙሃመድ አላሙዲን ወላይታ አይደሉም ግን ኢትዮጵያዊ ናቸው። ኢትዮጵያዊ ስለሆኑና ሠርተው ማትረፍ ስለቻሉ ለወላይታም የሚተርፍ ነገር ማድረግ ችለዋል። ወላይታ ብቻ በመሆን ሳይሆን ኢትዮጵያዊ በመሆን መተጋገዝ፣ መደጋገፍና አብሮ መቆም ስለሚቻል የተከበራችሁ የኢትዮጵያ ህዝቦች ማስተዋልን፣ ማሰብን ደጋግሞ ማጤንን እንድትለማመዱ አደራ እላለሁ።

እንደዋዛ የሚጀመሩ ግጭቶችና መገፋፋቶች እንዳይበታትኑን በእጅጉ ስለምሰጋ ብዙ ስድብ፣ ብዙ መገፋፋት፣ ብዙ መገዳደል፣ ብዙ መናናቅ መጨረሻችንን እንዳያበላሽ በትኩረት ኢትዮጵያን አስቀድመን፣ በጋራ መኖርን አስቀድመን፣ የጋራ ህልውናንና እድገትን አስቀድመን፣ ለመቀማት ሳይሆን ለመስጠት፣ ለመዝረፍ ሳይሆን ለመርዳት የሚያስብ ልብ እንዲኖረን አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ። ለምንድን ነው ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን አጀንዳ እየተፈጠረ ዋልታ የረገጡ ቡድኖች ኢትዮጵያን ለማመስ የሚፍጨረጨሩት ያላችሁ እንደሆነ ሲያቀብጠን ሌብነትን እንታገላለን ብለን ስንጀምር እነዚህ ጫፍና ጫፍ ያሉ ኃይሎች ብዙ ፋይናንስ የሚያደርጋቸውና የሚያስተባብራቸው ጉልበት ከውስጥም ከውጭም በዛ። ሌብነቱ ሩቅ አይደለም ጉያችን ስር ነው ያለው፤ ጉያችን ስር ያለውን ሌብነት እነማን ቢያስተባብሩ ትኩረታችንን ስራችንን ማጨናገፍ እንደሚችል ያውቃሉ። አሁን የምታዩት ነውጥ ሁሉ የሌብነት ዘመቻው ይቁም የሚል ነው። ኢትዮጵያ የሌብነት ዘመቻውን አጠናክራ ካልቀጠለች በሌላ መንገድ የሚገጥማት ፈተና በሌብነቱ መንገድም ስለሚገጥማት ሌብነት መታገሉንም አጠናክረን እንቀጥላለን። ትናንትና ተሳስታችሁ በስህተት ሰርቃችሁ ሀብት ያከማቻችሁ ሰዎች ካላችሁ መፍትሄው ቀላል ነው፤ ብዙ የዳቦ ፋብሪካዎችን ስለምንፈልግ ብዙ ትምህርት ቤቶችን ስለምንፈልግ ፋብሪካዎችን ከሠራችሁ ሰላም ይመጣል።

ብር አጭቀን ስለያዝን ፌስቡከርና ዩቱዩበር መቅጠር ስለምንችል፣ አስርና ሃያ ወጣት አስታጥቀን ሰው መግደል ስለምንችል፣ የሌብነት ዘመቻው ይቆማል ብላችሁ የምታስቡ ግን ሞኛሞኞች ናችሁ። ኢትዮጵያ ሌብነትን በፍጥነትና በኃይል ካልተዋጋች በስተቀር ብልጽግናዋን ልታረጋግጥ አትችልም።

ብልጽግና ካልተረጋገጠ ደግሞ የተራበ 120 ሚሊየን ዜጋ አንድ ሆኖ ሀገሩን ሊጠብቅ ሊታደግ አይችልም። ዜጎቻችንን ለማብላት ስንል አብዝተን ልማት ላይ እንሰራለን፣ አብዝተን ሌብነትን እንጸየፋለን እንታገላለን። ብር አይምጣ አይደለም ብር ሊመጣ ይችላል በሎተሪም በስጦታም ሊመጣ ይችላል። ያንን ብር ግን ለህዝብ ጥቅም ካዋልን አያጣላንም፤ ብር ግን ለውስኪ እና ለግል ጥቅም እየዋለ ኢትዮጵያን በማመስ ቤትን ብቻ ማደስ የሚያስቡ ሰዎች እንደዚህ አይነት ዘመን አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ማስተናገድ ስለማንችል ዘመቻው ይቀጥላል። መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጸረ ሌብነት ትግሉን አጧጡፎ በባለፈው ስህተት በባለፈው ጥፋት የምንቆዝም ሳንሆን ያን በይቅርታ አርመን አርቀን ለልጆቻችን ያማረች ሀገር እንድንተው በጋራ እንድንቆም በከፍተኛ ትህትና አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ።

በመጨረሻም ህልማችን የዳቦ ቅርጫት የሆነች ኢትዮጵያን ማየት ነው፣ ህልማችን ፍሬያማ ኢትዮጵያን ማየት ነው፣ ህልማችን የጸናች ለሁሉም ኢትዮጵያዊ የምትመች ኢትዮጵያን ማየት ነው፣ ህልማችን መናገር ብቻ ሳይሆን ጨርሰን ማሳየት ነው፣ ህልማችን ዳቦ ፋብሪካ እንሰራለን ማለት ሳይሆን ዳቦ ፋብሪካ ጨርሰን ማስረከብ ነው። ለዚህ የኢትዮጵያ ህዝብ ምስክራችን፣ ፈጣሪያችን ደግሞ ረዳታችን ስለሆነ የያዝነውን የቀና ሃሳብና የቀና ልብ፣ ከሌብነት የጸዳ እጃችንና ህዝባችንን ይዘን ኢትዮጵያን እናጸናለን፣ ኢትዮጵያን እናበለጽጋለን፣ ለልጆቻችን ያማረች የተዋበች ሀገር እናስረክባለን። ሌቦች ይጠፋሉ ወይንም ይቀንሳሉ ጽንፈኞች ይጠፋሉ ወይንም ይቀንሳሉ፤ ዋልታ የረገጠ እሳቤ ከኢትዮጵያ ይጠፋል። ኦሮሞም፣ አማራም፣ ትግራይም፣ ወላይታም፣ ጋሞም፣ ጎፋም፣ ሐረሪም፣ አፋርም እኩል የኢትዮጵያ ዋልታና እኩል ባለመብት የሆኑባት ኢትዮጵያን እንፈጥራለን። ይህን ለማድረግ የሚያስችል የእሳቤ ጥራት፣ አሰራር፣ አደረጃጀት፣ ጀምሮ የመጨረስ ልምድና የምንወደውና የተገነዘበን ህዝብ ስላለን በብዙ ፈተናዎች አልፈን እንደመጣን ሁሉ አሁን እየገጠመን ያለውን ፈተና እንዲሁ አሸንፈን የጸናች ያማረች ኢትዮጵያን ለልጆቻችን እንደምናስረክብ በድጋሚ ላረጋግጥላችሁ እፈልጋለሁ።

**ታኅሣሥ 14 ቀን 2015 ዓ.ም**

**ወላይታ ሶዶ**




ከተማ በደህና

# በሐዋሳ ከተማ የዳቦና የዱቄት ፋብሪካ ምርቃት

ታኅሣሥ 15 ቀን 2015 ዓ.ም

**የተከበራችሁ ሚኒስትሮች፣**
**የሀገር ሽማግሌዎች፣**
**እዚህ የተገኛችሁ የተከበራችሁ እንግዶች በሙሉ፤**

ኢትዮጵያ ውስጥ ዳቦ ብርቅ መሆን የለበትም፤ ስንዴ አምርተን የዳቦ ፋብሪካ ገንብተን ልጆቻችን ቢያንስ ዳቦ በወተት፣ ዳቦ በማር መብላት የሚችሉባትን ኢትዮጵያ እንፍጠር የሚለው ራዕይ ጅማሮ የሆነው አራተኛው የዳቦ ፋብሪካ ዛሬ በሃዋሳ እየተመረቀ ነው። ቀደም ሲል በአዲስ አባባ እስከ አንድ ሚሊየን ዳቦ በቀን የሚጋገር በቀዳማዊት እመቤት መስሪያ ቤት የተገነባ ፋብሪካ አለ። ከዛ በኋላ በአጋሮ፣ ትናንት በወላይታ ሶዶ ዛሬ እዚህ ሃዋሳ ላይ እያስመረቅን ነው። በቅርቡ ሌሎችም ይከተላሉ። እነዚህ የዳቦ ፋብሪካዎች ማሳያ ናቸው። ለሃዋሳ አንድ የዳቦ ፋብሪካ በቂ አይደለም። ብዙ የዳቦ ፋብሪካዎች ያስፈልጉናል ፤ መስራት እንደምንችል መቀየር እንደምንችል ለማመላከት የሚሰሩ እንጂ በቂ የሚባሉ አይደሉም።

ከአንድ መቶ ሚሊየን በላይ ህዝብ ያለባት ሀገር ገና አስርና አስራምስት ፋብሪካ ገንብተን ምንም አልተነካም፤ በዚያ ቁጥር ልክ ከዚያም በላይ ማምረት የሚያስችል ብቃት መፍጠር ይኖርብናል። ትናንት የሌማት ትሩፋት ሥራዎችን ለማየት በዚሁ አካባቢ አንዳንድ ቦታዎችን ጎብኝተን ነበር። በዚህ ወቅት ከሰማንያ ያላነሱ ላሞች በቀን በመቶዎች የሚቆጠር ሊትር ወተት እያመረቱ ለሃዋሳና ለአካባቢያቸው የሚያቀርቡ ጅማሯቸው በጣም ትንሽ የሚመስል ግን ፍጻሜያቸው ያማረ፣ ያበበ ሥራ፣ ለሌሎች የተረፈ በግቢያቸው ውስጥ አልፋ አልፋ በመጠኑ የሚያመርቱና መኖ እያዘጋጁና ከብቶቻቸውን እያረቡ በቂ የሆነ ወተት ማምረት የቻሉ አንድ ብርቱ የሆኑ ሴት አይተን ነበር። ከዚያ በኋላ በዚሁ ፋብሪካ አቅራቢያ የእንቁላልና የዶሮ ምረት የሚያሳልጥ ፋብሪካ ሊባል የሚችል በጣም ዘመናዊ የሆነ የዶሮ ማርቢያ ቦታና የዶሮ መኖ ማቀነባበሪያ ቦታ ለማየት ችለናል።

እንደምታስታውሱት የሌማት ትሩፋትን ስንጀምር፣ ልክ እንደ አረንጓዴ አሻራ የሌማት አሻራን ስንጀምር ለሲዳማ ክልል ቢያንስ አራት ሚሊየን እንቁላል ማምረት አለባችሁ

የሚል ኮታ ተሰጥቷቸው ነበር። የሲዳማ ክልል ባለፋት ጥቂት ወራት በሰሩት ሥራ አሁን አንድ ሚሊየን ደርሰዋል። ይህ ዓመት ሲጠናቀቅ የተሰጣቸውን አራት ሚሊየን ኮታ እንደሚያሟሉ ይጠበቃል። አራት ሚሊየን እንቁላል፣ ዶሮ፣ ጫጩት በስፋት ማምረት ከቻልን ፍራፍሬ ማምረት ከቻልን፣ ወተት ማምረት ከቻልን፣ ዳቦ በፋብሪካ የሚጋገር ከሆነ ሰዎች ካለችግር ለእለት ጉርስ የሚሆናቸውን ነገር እያገኙ ስራቸውን ሊሰሩ ይችላሉ። ይህን የመሰለ መሬት ፣ ይህን የመሰለ ውሃ ይዞ ከዚህ ያነሰ መልከዓ ምድር ካላቸው አካባቢዎች ለምግብነት የሚሆን ምርት አስገብቶ ገዝቶ መብላት አሳፋሪ ነገር ነው። ይህን አሳፋሪ ትልቁን አጀንዳ አስቀምጠን በማያስጨንቅ ነገር ጊዜ እናባክናለን፤ የሌማት ትሩፋት፣ የግሪን ሌጋሲ የጀመርናቸው በምግብ ራስን የመቻልና ተርፎ የማካፈል ራዕይ እንዲሳካ ሁሉም ሰው በትብብርና በተገለጸ ዐይን መስራት ይጠበቅበታል ። ድሮ በሀገራችን ራቅ ካለ መንደር ሰው ለትዳር ጥያቄ የሚያቀርብ ከሆነ ሽማግሌዎች ማን ነው፣ ከየት ነው ብቻ አይሉም እሰኪ ጓሮውን እንመልከት ይላሉ። ጓሮው ውስጥ ሽንኩርት የማይተክል፣ ድንች የማይተክልና የማይኮተኩት ከሆነ ይህ ሰው ቤቱን ሊያኖር አይችልም። ምንም እንኳን መልኩ ያማረ ቢሆንም ቤቱን ሊያስተዳደር አይችልም። ቢጀምረውም አይጨርሰውም ይላሉ ወላጆች።

የከተማ ከንቲባዎች መንገድ፣ ውሃ፣ መብራት ብቻ ሳይሆን በከተማ ውስጥ ስንት ዳቦ ይመረታል፣ ስንት ሊትር ወተት ይመረታል፣ ስንት እንቁላል ይመረታል ማለት ካልቻላችሁ፣ በከተማችሁ ውስጥ ባለው ነዋሪ ልክ ምግብ ማምረትና ማቅረብ ካልቻላችሁ አስፓልት ብቻውን አይበላም፣ መብራት ብቻውን አይበላም። የከንቲባዎች ዋነኛው ሥራ በቂ የሆነ ምግብ በከተማቸው የሚመረት መሆኑን ማረጋገጥ ነው፤ የሃዋሳ ከተማ ከንቲባ ይህ ፋብሪካ ሲሰራ እንደባለቤት ቆሞ በማሠራት ፋብሪካው ደረጃውን ጠብቆ እንዲሠራ በማድረግ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። ነገር ግን ለሃዋሳ ይህ ፋብሪካ በቂ አይደለም ። ትልቅ ከተማ ነው፣ እያደገ ያለ ከተማ ነው፣ ብዙ የሚራወጡ ሰዎች ያሉበት ከተማ ነው። ከንቲባችን ጥቂትም ቢሆኑ ቅሪት የሆኑ ባለሃብቶች ስላሉ እነሱን በማገዝ የፕራይቬት ሴክተሩን በማስተባበር ተጨማሪ ፋብሪካ ሊከፍቱልን ይገባል ይህን ለማድረግ ትናንት በሶዶ እንዳነሳሁት ይህንንም የሶዶውንም ፋብሪካ ያገዙን ሸክ ሙሃመድ አላሙዲን የአማራ ክልል ተወላጅ ናቸው፣ ፕሮጀክቱን በማስተባበርና በመምራት ያገዙን አቶ ጀማል ጉራጌ ናቸው፤ ትናንት ያየነውን እርሻ የሚያሰሩት አቶ በላይነህ ክንዴ አማራ ናቸው፣ አቶ ዳኜ ኦሮሞ ናቸው። ይህ የሚያመላክተው ጥቂትም ቢሆኑ ከሰፈራቸው ተሻግረው የሚሰሩ፣ የሚያለሙና የሚረዱ ሰዎች እንዳሉ ያመላክታል።
እነዚህን ቅሪት ሰዎች መጠበቅ ያስፈልጋል፣ ማገዝ ያስፈልጋል ጥቂቶች ሀገር የሚያለሙ፣

ወገን የሚያግዙ ከወንዝ ማዶም ቤተሰብ አለን ብለው የሚያስቡትን መደገፍና ማገዝ ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም ጭንቅላታቸውንና እውቀታቸውን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ያንን በማድረግ የሲዳማ ክልል በብላቴ አቅራቢያ ከሃያ ሺህ ሄክታር በላይ በፍራፍሬ ሊለማ የሚችል የተዘጋጀ መሬት አለው፤ ይህን ቦታ በፍጥነት የሌማት ትሩፋት፣ የአረንጓዴ አሻራ ሥራ አካል በማድረግ በቂ የሆነ ፍራፍሬ ቢመረት ሃዋሳ እንደምታውቁት ለአዲስ አበባ ቅርብ ነው፤ ከሁሉም የክልል ከተሞች ከአዲስ አበባ የሚያገናኝ የፍጥነት መንገድ ያለው ሃዋሳ ነው፣ እዚህ የሚመረት ምርት በቀላሉ ወደ መሃል ሀገር መሄድ ይችላል፡፡ ፍራፍሬውም፣ ዳቦውም፣ እንቁላሉም ፡፡ መችም ፍራፍሬ ከዚህ አይሄድም እንዳትሉኝ ከግብጽ ስለምናመጣ ሊሄድ ይችላል፡፡ በዚያ እሳቤ ከእናንተ በላይ ከእናንተ ባሻገር ሠርታችሁ ጠግባችሁ ሀገራችሁን እንድታጠግቡ አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ ባልተገለጠ ዐይን መሬት ጦም እያደረ፣ ውሃ በረሃ ውስጥ እየፈሰሰ፣ ጉልበት ሰፈር ውስጥ እንዲሁ እየተንገዋለለ እኛ እንራባለን እንለምናለን፡፡ በተደጋጋሚ የታሪክ እጥፋት የምለው ኢትዮጵያ ሲባል ድርቅ፣ ኢትዮጵያ ሲባል ለማኝነት፣ ኢትዮጵያ ሲባል ጦርነት ወደ ሰዉ አእምሮና ጭንቅላት የሚመጣውን ነገር መቀየር ያስፈልጋል፡፡ ቢያንስ ጠግቦ በማካፈል ሠርቶ አልምቶ የእጅን ፍሬ በማጣጣም ከዚህ ቀደም የነበረውን የልመና ታሪካችንን መቀየር ይቻላል፡፡ መቀየርም አለብን፡፡ ለዚህ ኢትዮጵያዊያን ልባችሁ የሰፋ መሆን አለበት፡፡ ሁሉም ሰው ማወቅ ያለበት ለብዙ ዓመታት ስንገፋፋ፣ ስንሰዳደብ፣ ስንረጋገም ኖረናል ውጤቱ ድህነት ነው ውጤቱ ልመና ነው፡፡ ያን የተለመደውን ፋሽን ከምንደግም አዲስ ነገር እንሞክር፡፡ ያን እናውቀዋለንና ኖረንበታል፡፡ አሁን የሚያስፈልገን መተባበር፣ መደጋገፍ፣ ይቅር መባባል፣ በዩቲዩብ ነጋዴዎች አለመታለል፡፡ ብዙ ወሬ ነጋዴዎች ኢትዮጵያ ውስጥ አሉ፡፡ እነዚህን የወሬ ነጋዴዎች ገበያ የምናሳጣው በርከት ያሉ እጆች ሥራ መስራት እንዲችሉ ስናደርግ ነው፡፡ ሰዎች ሥራ የለም ይላሉ የኢትዮጵያ ምድር ደግሞ የሠራተኛ ያለህ ይላል፡፡ የኢትዮጵያ መሬት የኢትዮጵያ ውሃ የሠራተኛ ያለህ የሚጠቀምበኝ አጣሁ ይላል፤ ወደ ሥራ መግባት መተባበር ያስፈልጋል፡፡ ገንዘቡ በአንድ ጀምበር የሚገኝ አይደለም፡፡ በጊዜ ሂደት ውስጥ እያደገ ይሄዳል ከክፋትና ከሌብነት መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡

የሚያስፈልገን መድፍና ታንክ ሳይሆን ማረሻና ትራክተር መሆን አለበት፤ ወደዛ ለመሄድ ሰላምን አብዝተን የምንወድ፣ ለሰላም የምንሰራ፣ ለልማት የምንሰራ፣ ለትብብር የተዘጋጀን ብንሆን ኢትዮጵያን መቀየር ይቻላል፡፡ ይህ የለውጥ መንግስታችን ባለፉት አራት ዓመታት በዓለማቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ውርጅብኝ የደረሰበት ነው፡፡ በሀገር ውስጥም

እጅግ ፈታኝ የሚባል ጊዜ ያሳለፈ ነው። ያለፍንባቸው መከራዎች አሸናፊ እንድንሆን ብቻ ሳይሆን በቀላሉ እንዳንናወጥም ብቃት ሆነውናል። በቀላሉ የሚናወጥ መንግሥት የለም፣ በቀላሉ በአስር ሰዎች ሽብርና ግድያ የሚቀየር ነገር የለም። የሚቀየር ነገር ካለ በንግግር በምክክር እንዲሆን ከሽብር፣ ከጥፋት፣ ሳይሰሩ እንዲሁ ከመብላትና ከመስረቅ እሳቤ ወጥተን ወደ ልማት እንድንሄድ፣ መንግሥት ሲባል ግለሰቦች ሳይሆኑ ተቋማት እንዲጠነከሩ ግብርናችን እንዲዘምን፤ ኢንዱስትሪ እንዲስፋፋ የሚሰራ ሰው ካለ ከኮሪያም፣ ከቻይናም፣ ከጃፓንም፣ ከአሜሪካም ይምጣ እንኳን ከክልል አልሚ ሰው ከሆነ፣ የማይሰርቅ ከሆነ መጠቀም ያስፈልጋል እንደዛ ያደረጉ ሀገራት አድገዋል። እኛም በዛ መንገድ ማደግ እንድንችል፣ ልባችን የሰፋ እንዲሆን ለተደረገልን የፋብሪካ ግንባታ ቀዳማዊት እመቤትን አብዝተን እናመሰግናለን። እንደዚህ አይነት ሥራ እንዲበዛ እንዲበራከት እንጠይቃለን፤ የጀመራችሁ ሰዎች እስከትጨርሱ አትተኙ። መጀመር ቀላል ነው መጨረስ ነው ዋናው ለመጨረስ እንትጋ። በተደጋጋሚ እንዳልኩት ሰላማችንን አስጠብቀን፣ ብልጽግናችንን አረጋግጠን፣ ወንድማማችነታችንን ዳግም በማይናወጥ መሰረት ላይ አኑረን የበለጸገች ኢትዮጵያን ለልጆቻችን ለማስረከብ በጋራ እንድንሰራ አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ።

በትናንሽ ነገር አንናወጥ እንጽና፣ ኢትዮጵያን እናጽና። ይህ ሲሆን የተሻለ ጊዜ ይፈጠራል። በእኔ እድሜ ኢትዮጵያ <<ከኢትዮጵያ ተለገሰ>> (Ethiopian Aid) ብላ ስንዴ ለሌሎች የምትረዳበትን ጊዜ እናያለን።

ያ እንዲሆን በርትተን በጋራ እንስራ። የረዱንን እንረዳለን፣ ያበደሩንን እንከፍላለን፣ ያልረዱንን ደግሞ ረድተን እርዳታ እናስተምራቸዋለን።

**አመሰግናለሁ።**

***ታኅሣሥ* 15 *ቀን* 2015 *ዓ.ም***

***ሃዋሳ***

# የፖለቲካ ገበያን (Political Marketplace) አስመልክቶ የቀረበ

ታህሳስ 24 ቀን 2015 ዓ.ም

የፖለቲካ ሥርዓት ሦስት ዋነኛ ውቅሮች አሉት። << The Three I >> ይባላሉ። አንደኛው ሃሳብ (Iidea) ነው ፤ አይዲያ ለምታደርገው ነገር ሁሉ የአይዲያ ዘር ነው። ሃሳብ ካለ ኢማጂን የማድረግ አቅም ካለ ፣ ያን የሚሸከም አንድ ግለሰብ ካለ፣ ግለሰቦችን የሚያባዛ ፍላጎት ካለ ፍላጎትን መከወን ይቻላል። ሁለተኛው ግለሰብ (Individual) ነው ያን ሃሳብ የሚሻከም ግለሰብ ነው። ሶስተኛው በታላቅ አላማና እሳቤ ውስጥ ግለሰብ - ግለሰብ ስለሆነ በርከት ያሉ ቡድኖች ተቋማዊ በሆነ መንገድ ካልተፈጠሩ በስተቀር ትልቅን ሃሳብ መከወን አይቻልም። አንድ ሰው ሊያስብ ይችላል የራሱን ድርሻ ሊሰራ ይችላል። ነገር ግን ሀገራዊ የሆነ ሥራ በሚሰራበት ወቅት ተቋም ያስፈልጋል። ሃሳብ፣ ሃሳብን የሚሸከም ግለሰብ ከዛም ግለሰቦችን እንደ አንድ አሰናስሎ የሚያሰማራ ተቋም ያስፈልጋል። ተቋም መገንባት ለእኛ ዋነኛው አስፈላጊ ነገር የሚሆንብት ምክንያት ሀገረመንግሥት ግንባታን የሚሸከመው ዋናኛው ነገር ተቋም ስለሆነ ነው። ተቋም ካልተገነባ ሀገረመንግሥት ግንባታን ማሳካት ያስቸግራል። ይሄ መሰረታዊ ሦስት ውቅር ለዲሞክራሲያዊና ለፖለቲካዊ ገበያ ያለውን ልዩነት ጎን ለጎን ማየት ነገሩን አጥርቶ ለማየት ያግዘናል።

ሃሳብ በዲሞክራሲ ልምምድ ውስጥ (market place of idea) ስለሆነ ማንም ጥሩ ሃሳብ ያላው ሰው ከየትኛውም ዘር፣ ሰፈር፣ እምነት ቢመጣ በሃሳቡ ምክያት ተቀባይነት ይኖረዋል፤ ምክንያቱም የፖለቲካ መድረኩ በሃሳብ ላይ የቆመ ስለሆነ። የፖለቲካ ገበያ ላይ የከረረ ሽኩቻ ባለበት ግን ታማኝነት የለም፣ ሃሳቡ ምን አይነት ነው ሳይሆን ማን ተናገረው ነው። አንድን ቋንቋ አደም ሲናገረው፣ አብዩ ሲናገረው፣ ደምቀ ሲናገረው ተቀባዩ ጋ ሲደርስ ደመቀን አይቶ፣ አደምን አይቶ የሚቀበል ከሆነ ሃሳቡን ሳይሆን ሰውየን ነው የሚያየው፤ ተገዢነቱ ለሃሳብ ሳይሆን ለግለሰቡ ነው። ለዚህ ነው ሃሳብ በዲሞክራሲ የገበያ ምህዳሩ ውስጥ ሃሳብ ላይ የተመረኮዘ ነው ሲባል በፖለቲካ ገበያ ላይ ደግሞ ታማኝነት፣ ኔትወርክና ትስስር ነው። የሃሳብ ግዝፈቱ ሳይሆን ሃሳቡ ምንጭ ማን ነው በሚል የሚወሰን ነው። ሁለተኛ ግለሰብ ላይ ሲመጣ ዴሞክራሲ ከሆነ ከግል ፍላጎት የወጣ ተቋማዊ ግንኙነት እንገነባለን፤ በፖለቲካዊ ገበያ ውስጥ ግን ግላዊ ነው፤ የጋራ አላማን ለማሳካት እንደሚሞት ሳይሆን ማን በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በቋንቋና በሌሎች ነገሮች ከእኔ ጋር ይቀራረባል በሚል እሳቤ ግላዊ ይሆናል።

ተቋምን ስንመለከት በዴሞክራሲ ውስጥ ሚዛናዊ የሆነ ውድድርና ትብብር ባለበት ስርዓት ውስጥ ማንም ሰው ብልጽግናን ለማረጋገጥ ቢናደድ፣ ቢበሳጭ፣ ቢቆጣና ቢናገር በተቋሙ ሥርዓት ውስጥ ነው የሚናገረው። ለብልጽግና እቆረቆራለሁ ብሎ ከተቋሙ ውጭ ከተጫወተ ለብልጽግና አልቆመም የተለየ ፍላጎት አለው ማለት ነው ።
ብልጽግናን እየወጋህ ለብልጽግና ቆምኩ ማለት አትችልም፤ ኢትዮጵያን እየወጋህ ለኢትዮጵያ ቆምኩ ማለት አትችልም ፤ ይሄ የሞራል ህዝበኝነት ( moral populism) ነው ። ህዝበኝነት ነው ግን የሚገነባው በሞራል ነው። ዝም ብሎ አልተመደብኩም፣ ስልጣን አልተሰጠኝም፣ ጥቅም አላገኘሁም አይልም፣ <<እኔ የእነ እንትና ሰፈር ተወካይ ነኝ፣ እኔ ካልተናገርኩ ማን ይናገርላቸዋል>> በሚል ሞራል የተደበቀ ህዝበኝነት ነው።

ተቋማዊ ካልሆነ በስተቀር ይሄ የብልጽግና ጉዞን ያደናቅፋል፣ ያፈርሳል ሀገረመንግሥት አይገነባም ፣ ተቋምም አይገነባም። የፖለቲካ ከባቢው ከገበያነት ወጥቶ ሃሳብን የሚሸከምና ግለሰብን ከሃሳቡ ነጥሎ የሚያይ መሆን አለበት። ብዙ ጉዳዮች አሉ በቅደም ተከተል የሚታዩ ለምሳሌ ሚዛናዊ ውድድርና ትብብር ባለበት የመደመር እሳቤ ውስጥ መጀመሪያ ተቋማዊ አካሄድና ሰላማዊ ነው የሚሆነው ምንም የግል ጉዳይ ስለሌለ። ፖለቲካዊ ምህዳሩ የሸቀጥ በሚሆንበት ሰዓት ግን አለመተማመን ስላለ የሚፈጠረው ማንኛውም ነገር የሚከፋፍል ነው የሚሆነው።
ሂደቱ ብልጽግናን ማጠናከር፣ ኢትዮጵያን ማጠናከር ወይም ወደፊት መጓዝ ከሆነ ምንም መጓተት አያስፈልግም፤ ተቋም ተከትሎ ችግሮችን ማረቅ ብቻ ነው።

ሽኩቻ ካለ የግል ፍላጎት አለ ማለት ነው ቢደበቅም ጊዜ የሚያወጣው። መንገዱ መለኪያው ተቋማዊ ከሆነና የማይከፋፍል ለግዙፉ ዓላማ የሚተጋ ከሆነ እሱ ዲሞክራሲያዊ ነው። በመደመር ላይ እንዳስቀመጥነው እኛ ፍጹም ትብብርም ሆነ ፍጹም ፉክክር አንፈልግም። ከዚህ ይልቅ ሚዛናዊ የሆነ ትብብርና ፉክክር እንፈልጋለን። ጤነኛ ያልሆነ ትብብርም ፉክክር ካለ ወይም ጤናኛ ያልሆነ ትብብርም ካለ ጥፋት ነው። ሂስ የምንደራረገውም ለጋራ ተቋማችን ህልውና መከናወን መሆን አለበት ከዚያ ባሻገር በሚሆንበት ሰዓት የፖለቲካዊ መገበያያው ስፍራ የፖለቲካ ምህዳሩን እያበላሸው ነው ማለት ነው። ፖለቲካ ውስጥ ሁልጊዜም የግለሰቦች ውሳኔ አለ፤ ነገር ግን ተቋማዊ አካሄድ ከሌለ ጥፋት ነው። አንድ ሰው የክልል ፕሬዘዳንት ከሆነ እሱ ክልል ነው፣ ሚኒስትር ከሆነም ሚኒስቴሩን በእጁ የያዘ ሰው ነው ተቋም የለም፤ ፖሊሲ፣ የግለሰቦች ውሳኔ ተቋማዊ አሰራር ካልያዘው ለግለሰቦችና ለቡድኖች ጥቅም መዋሉ የማይቀር ነው። ስልጣን ተሰጥቶህ አትወስን አይባልም፤ ስትወስን ግን አሰራር ተከትለህ ሲሆን

ከሌብነትና መሰል ጥፋቶች ትታቀባለህ ማለት ነው። ፖለቲካዊ ገበያው ከነዚህ አሰራሮች ውጭ እየሆነ ያለበት መንገድ ካልተገራ ግን ሄዶ ሄዶ ሽቀጥ ስለሆነ ሀብታም ሚኒስትር ይገዛል፣ ሚኒስትር አክቲቪስት ይገዛል፣ ከዛም የፈለጉትን ያደርጋሉ ማለት ነው። ይሄ ደግሞ አሁንም እየሆነ ነው።

ግለሰቦችን ከሾምናቸው በኋላ እንዳይወስኑ ማድረግ ሽቀጥ ነው፣ ሲወስኑ ህግና አሰራርን ተላልፈው ራሳቸው ህግና ፖሊሲ አመንጪ እንዲሆኑና እንዲወስኑ ማድረግም ሽቀጥ ነው። ይህንን የሚያስታርቅ አካሄድ ያስፈልጋል። የፖለቲካን መልክ ቀለል ባለ መንገድ በሦስት ከፍለን ማየት እንችላለን። መልኩን እንዴት እንደቀየረ፤ በጥንት ጊዜ የዓለም ፖለቲካ የተዘወረበት መንገድ (patrimonialism) በዘመድ አዝማድ የሚሰራ ሥርዓት ማለት ነው። ከጥቂት ዓመታት በፊት ይሄ በጋብቻና አምቻ ይሰራል። ግን ይሄ የቤተዘመድ አሰራር አደገኛ ነው፣ መቀየር አለበት ብሎ አዲስ የቤተዘመድ አሰራር ተፈጠረ (neo patrimonialism) መጀመሪያው ልክ አይደለም በሚል ሁሉም ነገር በህግ መሆን አለበት የሚል ተቋምን አሰራር ታኮ የሚደረግ ሆነ ማለት፣ ሙስናን ህጋዊ አደረገው ማለት ነው። ሚዲያና ግለሰቦች እንደዚሁ ይገዛሉ ማለት ነው። በየትኛውም ዓለም ያለ ፖለቲካ ደግሞ ከእንደዚህ ያለ ሽቀጣ የወጣ አይደለም። ሶስተኛው እኛ ዘንድ እየተስተዋለ ያለውና ቶሎ መገራት ያለበት ነገር የፖለቲካ ገበያ ነው። ይህኛው አሰራር የሚመሰረተው በአቅርቦትና ፍላጎት ላይ ነው። በወቅቱ በተሰጠው አጀንዳ ላይ በተከፈለው ልክ የሚጮህ ወይም ገበያው የሚፈልገውን ብቻ የሚሰራ ማለት ነው።

ሦስተኛው እንደቀደመው እንደጋብቻና አምቻ የሚጸና አይደለም፤ እንደሁለተኛውም በህግና በስርዓት ታኮ የሚሄድ አይደለም፤ ለገበያ የሆነ ነው። ዝምድናውም ጊዜያዊ ነው፤ ጥቅም አገኛለሁ ብሎ ሲያስብ የሚገለባበጥ ነው ማለት ነው። ይህ ጊዜያዊ የሆነ በግብይት ሥርዓቱ ውስጥ እንደ ሽቀጥ የሚታየው ነገር ብዙ ባለድርሻዎች አሉት። ዝምብሎ እንደምናስበው ቀላል ነገር አይደለም። ግብረሰናይ ድርጅቶች፣ ዓለማቀፍ ተቋማት፣ ሲቪክ ሶሳይቲስ አሉበት፣ አክቲቪስትና ሚዲያም አሉበት። አንተን ከመስመርህ የሚያወጣና የሚያዘገይ ሃሳብ ያላቸው ግለሰቦች በንግዱ ውስጥ በመስጠትና በመቀበል ውስጥ ያሉ ሰዎች ሁሉ ይሳተፋሉ። የእኛን ሚዲያ ተመልከቱ፤ ሰው ታሰረ፣ ግጭት ተፈጠረ፣ ጦርነት ተፈጠረ፣ የማይደግፈን ቴፎዞ አለ እንዴ ከውጭና ከውስጥ? እንጦጦ ተመረቀ፣ ስንዴ ታረሰ፣ የሆነ መንገድ ልማት ተሰራ <<ለምን? ምን ያደርጋል? ለምን ያስፈልጋል?>> ይላል እንኳን ሊደግፈህ ዝም አይልህም። ቀጥሎ የሚመጣው ነገር ከነበረው የባሰ ነው የሚሆነው። አንድ ደረጃ ከፍ አድርገን አሸጋግረን መስጠት ካልቻልን በስተቀር አብሮ

መቀመጥም አስቸጋሪ ነገር ይሆናል። ሰብሰብ ያሉ አደጉ፣ የተበተኑ ወደቁ በሚባልበት ዓለም ውስጥ ውደቅ ውደቅ ካለህ ጠላት ነው ። ሰብሰብ ጠንከር በል ካለ ደግሞ ወዳጅ ነው።
ፖለቲካዊ ገበያው መልክ እየቀየረ ነው። አንድ ካድሬ በሀብታም ሲገዛ አላግባብ መሬት ይሰጣል ፣ አላግባብ መብት ይሰጣል ከዛ ሰው የሚወስደው ጥቅም ካለ ጥቅሙን ወስዶ ዝም አይልም። በጥቅሙ ደግሞ አክቲቪስት፣ ዩቲዩበርና ፌስቡከር ይገዛል፤ ከዛ ቦታውን ያደላድላል ማለት ነው። ሁለተኛው የቢዝነስ ግንኙነት ግን ገዢ ነው። በገንዘቡ መሬት፣ በገንዘቡ ሰው፣ በገንዘቡ የራሱ ሚኒስትር ይገዛል። የምንገዛው በህዝብ ሀብት ነው። በተሰጠን የህዝብ ሐላፊነት ማገልገል ሲገባን፥ መስራት ሲገባን በወንበራችን ምክንያት ገዝተን ወንበራችንን ለማጽናት የምንሸጠው ነገር በከፍተኛ ደረጃ ተቋም ግንባታና ሀገር ግንባታ ላይ አደጋ ያስከትላል።

ለምሳሌ፤ <<ሙስና አደገኛ ነገር ነው፣ ጥፋት ነው፣ መታረም አለበት>> ስንል <<ልክ ነው መታረም አለበት>> ካልን በኋላ አንደኛው ቡድን <<ልክ ነው መታረም አለበት፣ ጊዜውም አሁን ነው>> በሚል በሚዲያ <<እነእከሌን ነው መምታት ያለበን>> ይላል። ሌላው ደግሞ <<ግዴለም ይህ ትናንሽ ነው፣ ትልልቁን እየፈለግን እንደተቋም እናፈርሳቸዋለን>> ይላል። ሌላው ደግሞ ይህን መሰል መረጃን ላይክ በማድረግና በማሰራጨት ይተባበራል። በእርግጠጥኝነት የምነግራችሁ ብልጽግና ውስጥ ተቋማዊ ሙስና የለም። ቢኖር ኖሮ ይህን ሁሉ አሁን የምናደርገውን እንቅስቃሴ ማድረግ አንችልም ነበር፤ ነገር ግን ሌብነት አለ፤ ይህም መታረም አለበት፤ ትንሽም ቢሆን እሱ ነው ህዝብን የሚያስመርረው። ለእያንዳንዱ አገልግሎት ስሙኒ መልቀም አለ፤ ከፍ ሲል ደግሞ  ከሀብታም ጋር ከመሬት ጋር ተያይዞ የሚሸቀጥ ሸቀጥ አለ። ሦስተኛ ደግሞ ኮንትራት የሚሸጡ፣ የሚገዙ ጥቂት ቡድኖች በጋራ ሆነው የሚያጭበረብሩት ሌብነት አለ።

የፖለቲካ ልሂቅ፣ የቢዝነስ ልሂቅና የዓለማቀፍ ልሂቅ ሚናቸውን ለይተን ሁሉም የሚሻሻጡበትን መንገድ ጥፋቱን ቀንሰን ባለሀብቱን ከፖለቲካ አመራሩ ለይተን ካስቀመጥነውና የጀመርነውን ሪፎርም ካስቀጠልን የሚጠረጥሩን ሰዎች ከሚገምቱት በላይ ኢትዮጵያ ብልጽግናዋን በፍጥነት ማሳካት ትችላለች። የምናረጋግጠው ግን የጋራ ሀሳብ ኖሮን በጋራ የምንለፋ ከሆነ ነው። እጃችንን የምንሰበስብ ከሆነ፣ በመትጋት በመልፋት ኪሳራ የለም። ልጆቻችን የተሻለ ሀገር ይኖራቸዋል ብለን የምንነሳ ከሆነ በእርግጠኝነት ብልጽግናችንን ማሳካት ይቻላል። ፖለቲካዊ አቅምና ገንዘብ የሌላቸው

ሰዎች በዚህ ሽቀጣ ውስጥ መሪ ተዋንያን መሆን ይቸገራሉ ምክንያቱም ስልጣን ወይም ገንዘብ መያዝ ስላለብህ። እኛ ጋ ሌብነት አደገኛ ነው መጠንቀቅ አለብን የምንለው ስልጣኑ ስላለን በቀላሉም ልንገዛው ስለምንችል ነው። ሁለቱም ደግሞ ወደ እኛ ዘንድ ከመጣ ስቴት ካፕቸር (state capture) ይፈጠራል። ከዛ በኋላ በብዙ የአፍሪካ ሀገራት የምናየውን አይነት በሽታ እናመጣለን። ተራማጅ፣ ተለዋጭና አዳጊ ማህበረሰብ አንፈጥርም። <<እኔ የለሁበትም እኔን አይመለከትም>> ብለን ማለት አንችልም ምክንያቱም ስልጣን ነው የያዝነው ምክንያቱም አንዳንዱ በእምነቱ፣ አንዳንዱ በብሄር፣ አንዳንዱ በሰፈር ወይም በሆነ ጉዳይ ይመጣብናል ከዛም ይይዘናል። በእርግጥ ስንወርድ ማንም አይፈልገንም፤ ምክንያቱም አንተን ሳይሆን የያዝከውን ስልጣን ነው የሚፈልገው። በያዝከው ስልጣን ውስጥ ሰርተህበት ትርፍ እንድታመጣለት ነው እንጂ ካንተ ጋር አይደለም ጉዳዩ።

በዚህ ውስጥ ያለንን ሚና እንደ ጋራም እንደግልም በተገቢው መንገድ ማየትና ማረቅ ካልቻልን የፖለቲካ ገበያው ይዞን የሚጠፋ ጉዳይ እየፈጠረ መሄዱን እንረሳና ከዋነኛው ግባችን ከብልጽግና ጉዟችን ያደናቅፈናል። የዚህ ገበያ አውድ ምንድን ነው ያላችሁ እንደሆን ሶስቱ ''C'' ይባላሉ። አአንደኛው ሙስና ነው (Corruption) እጁ ንጹህ ሆነ ሰው፣ በስልጣኑ ማግበስበስ የማይፈልግ ሰው የሆነ ሀብታም ሊይዘው አይችልም። ነጻ ስለሆነ የራሱን ነጻነት የሚወድ ሰው ስለሚሆን በሆኑ ኃይሎች ሊጠለፍ አይችልም፤ ሊሳሳት ይችላል ነገር ግን ሊጠለፍ አይችልም።
ሌባና ሙሰኛ የሆነ ሰው ግን በሆነ ጥቅም ታገኘዋለህ። ሁለተኛው ሙስና ብቻ የፈለገውን አያሳካለትም ግጭት (Conflict) ይፈልጋል። ግጭቱ ግለሰባዊ ወይንም የሆነ ቡድን አፈነ፣ ገደለ በሚል አማጺ እንዲኖር ይፈልጋል። ያ ከሌለ እሳት ሆኖ የማይቀጣጠል እንደማለት ነው። ያ ገንዘብ የተገኘውም በአመጽና በግጭት ነው የሚውለውም ለግጭት ለአክቲቪስቱ፣ ለዩቲዩበሩ የሚወጣ ይሆናል። ይህም እዚሁ ሀገራችን ውስጥ ጭቅጭቅ ያለበት አውድ ይፈጥራል። ከሙስና እና ግጭት በኋላ የሚመጣው ነገር (Capture) ነው አካባቢን፣ ሰፈርን፣ ወርቅን፣ ብርንና ስልጣንን መያዝ ነው። በሰፈር ደረጃ capture አለ በፖለቲካ ደረጃም capture አለ። ስለዚህ ሙስና ይመጣል፣ ግጭት ይመጣል ከዛም ስልጣን ይበትናል፣ ሀገራዊ ፍላጎትን ይበተናል፣ ሀገራዊ ህልምን ይበትናል፣ የስልጣን ቅደም ተከተልን ያፈርሳል ከዛም ተቋማትን ያፈርሳል። ቀስ ቀስ እያልን የምናደርገው ድርጊት በጊዜ ሂደት ውስጥ ተቋም የሚያፈርስ ከሆነ ሀገር ልንገነባ አንችልም። የሀገረ መንግሥት ግንባታውም አደገኛ ችግር ውስጥ ይገባል። በእኛ ሁኔታ ውስጥ የፖለቲካ ገበያው አዝማሚያው ምን እንደሚመስል ካየን አንደኛው ደርሶ

አክራሪነት ነው፤ ኦሮሞ ትናንት የተፈጠረ ይመስል ኦሮሞ ውስጥ ኖሮ፣ ኦሮሞ ውስጥ አድጎ፣ ለኦሮሞ እታገላለሁ ሲል ቆይቶ አሁን የኦሮሞ ብቸኛ ጠበቃ መሆን ይፈልጋል፣ የሰፈር ጠበቃ መሆን ይፈልጋል፣ አክራሪነት በዝቷል።

ሁለተኛው ሌብነት ነው ጊዜ፣ ገንዘብ፣ መሬትና ሌሎችን መስረቅ ቅድም በገለጽሁት መንገድ ነው። ሦስተኛው ዓለማቀፍ ተጽእኖ ነው። ይህ ተጽእኖ ቅድም እንዳነሳሁት አጀንዳ እየቀረጸ በውስጣችን ሰላምና ህብረት እንዳይኖር ያደርጋል። ይህ ተግዳሮት የማህበራዊ ሚዲያ አካውንቶችን ብትመለከቱ ነገሩ ፍሬ አፍርቶ ባይታይም በየጓዳው ሁለት ሶስት ሰው ተቧድኖ አንዳንድ ነገር ማለቱን፤ ከዛም ካለፈ ፌስቡክ ላይ ደፋር ከሆንክ በስምህ ካልሆነም በሌላ ስም መጻፍ፤ ከፈራህ ላይክ እና ሼር እያደረግህ የዚህን የፖለቲካ ገበያ ብልሽት ታፋጥናለህ። ነገር ግን የፖለቲካ ገበያው ሲበላሽ ለውጥን የሚመሩ መሪዎች ሥራቸው ነገሮችን ማስታመም (babysitting) ነው፤ ልጅ ሲስቅ አቅፈህ ፣ ሲያለቅስ እንቹ እዘይው ካልክ የለውጥ መሪ አይደለህም። ልጅ ይስቃል፣ ያለቅሳል እነዚህን ጉዳዮች እያስማማን፣ እያግባባን፣ እንዳንጠፋፋ አድርገን ካልሄድን በስተቀር ለውጡ አደጋ ውስጥ ይገባል። ሚናችንን መለየት አለብን፤ አንድ ቀን አማራ፣ አንድ ቀን ኦሮሞ፣ አንድ ቀን ትግሬ፣ አንድ ቀን ወላይታ፣ አንድ ቀን ጉራጌ ይህን እያስማማህ ኢትዮጵያዊነት እንዳይፈርስ አድርገህ ብልጽግና እንዲመጣና ሰዎች በሃሳብ ልዕልና እንዲቆሙ ማድረግ አለበኝ፤ የዚህ ዘመን መሪ ነኝ ብለህ ማሰብ ነው፤ ሮጠህ በራስህ ሸለቆ ከገባህ ግን ነገሩ ተበላሸ ማለት ነው።

የፖለቲካ ገበያው ከጋብቻ፣ ከእምቻ፣ ከተቋማዊ ውቅር ውጭ ወጥቶ በአቅርቦትና ፍለጎት ላይ መሰረት አድርጎ እየተሸቀጠ አጠቃላይ ጉዟችንን አደጋ ላይ እያስገባ መሆኑን መገንዘብ ብቻ በቂ አይደለም። የዚህ የፖለቲካ ገበያ አደጋ ምንድን ነው ብለን ማወቅ አለብን። አደጋው ለውጥ ንጥቂያ ነው፤ ለውጥን ነው የሚሻማው። ለውጥ ንጥቂያ ማለት የምታደርጋቸውን ማንኛውም የሪፎርም እሳቤዎችና ሥራዎች ከግል ጉዳይ ጋር ማያያዝ፤ ድል ሲሆን መንጠቅ፣ ጥፋት ሲሆን መስጠት ነው። አንደኛው ብልጽግናን በሀብት ቅርምት መተካት ነው። የሆነ ሰው ህንጻ ስለሠራ የሆነ ሰው መኪና ስለገዛ ኢትዮጵያ አትበለጽግም። የኢትዮጵያ ብልጽግና የሚረጋገጠው በርከት ያለ ቁጥር ያለው ህዝብ መካከለኛ ገቢ ያለው ስናደርግ ነው። መካከለኛ ገቢ ያለው ሰው በሚሊየን ስናበዛ ነው ብልጽግና የሚረጋገጠው። የኢትዮጵያ የነፍስ ወከፍ ገቢ አራትና አምስት ሺህ ዶላር ከገባ አሁን በሰፈር የምታጣላውን የሚሰማህ የለም እርሳው። አራትና አምስት ሺህ እስኪገባ ድረስ አስታመው፤ እዛ ከደረሰ በኋላ ግን ሰው ጊዜ የለውም

ሞርጌጅ አለበት፣ ነዳጅ አለበት ስላንተ ወሬ ጊዜ የለውም። እዛ ደረጃ እስኪደርስ ግን አምጠን ካላደረስነው በስተቀር ወደኋላ ሲመለስ በነበረበት አይቆምም። በብዙ መጠን ወደኋላ ሄዶ ወደ ጠለቀው የችግር ምንጭ ይገባል።
ሁለተኛው ተቋምን በጥቅም ትስስር መቀልበስ ነው።

ተቋም ከሌለ ሀገር አይገነባም ግለሰቦች ተቋም ሆነው ግለሰቦች ተሳስረው የሚወጡ ከሆነ የሀገር ግንባታ ከመጀመሪያው ሞተ ማለት ነው። የሀገር ግንባታ መሰረት ተቋም ስለሆነ። ሦስተኛው ሉዓላዊነትን በውክልና ጦርነት ለማፍረስ መጣር ነው። እንግዲህ ለኢትዮጵያ ነጻነት፣ ለኦሮሞ እኩልነት ወይ ሌላው እታገላለሁ ብለህ በውክልና ኢትዮጵያን የሚያፈርስ ሥራ የምትሰራ ከሆነ ተቃራኒ ነው። አራተኛ ሰላምን በዓመጽ፣ በጭቅጭቅ፣ በንትርክ በመበረዝ ሰላም እንዳይኖር፣ ውይይት እንዳይኖር ማድረግ ነው። ይህ ለውጥ ንጥቂያ በፖለቲካ ገበያ ውስጥ አደጋ ነው፤ የምናስበውን ዓላማ አናሳካም። በአስር ዓመት ውስጥ እንገነባታለን ብለን የምናስባትን ሀገር አንገነባም፣ ያን የማንገነባ ከሆነ ደግሞ መሰብሰቡም፣ መዳረቁም ትርጉም የለውም። ኢትዮጵያ ካላችበት ችግር ወጥታ ቢያንስ ራሷን መግባ፣ ልጆቿን አስተምራ፣ ክብሯንና አንድነቷን ጠብቃ ወደኋላ የማትመለስበትን ነገር ካልሰራን መዳረቁ ዋጋ የለውም ጊዜ መቁጠር ብቻ ነው የሚሆነው። ያን ለማምጣት ደግሞ የፖለቲካ ገበያው የራስህን ህልም፣ የራስህን ፍላጎት ሳታውቅ እየበላው እንደሆነ በንቃት ማየት ተገቢ ይሆናል። አሁን እየሄድንበት ያለነው አካሄድ ሁሉንም አላማችንን የሚቀለብስና የሚያጠፋ ነው ብሎ ማየት አስፈላጊ ይሆናል።

**ታህሳስ 24 ቀን 2015 ዓ.ም**
**አዲስ አበባ**


CORINO

# በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ የተከፈቱ ኢንዱስትሪዎች ጉብኝት

ታኅሣሥ 26 ቀን 2015 ዓ.ም

ሃሬ በገላን ከተማ አካባቢ ኢትዮጵያ ታምርት የሚለው ንቅናቄ አካል የሆኑ ሁለት በጣም አስፈላጊ የሚባሉ ፕሮጀክቶች እያየን ነው የዋልነው።
አንደኛው የሆራ ኢንደስትሪ ነው፤ ሆራ በጣም ወጣት የሆነ ሰው እጅግ አስደማሚ የሆነ ሥራ በአንድ ዓመት ተኩል ይሄን የሚያክል ኢንደስትሪ አቋቁሞ በማንኛውም ስታንዳርድ ከዚህ ቀደም የምናውቀውን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለ በማይመስል መንገድ ሦስት መሰረታዊ ሥራዎች ላይ ያጠነጠኑ ኢንደስትሪዎች ነው ያየነው። አንደኛው ከዚህ ቀደም በሀገራችን ቡና መቶ ሰዎች ተቀምጠው ከታጠበ በኋላ ይለያሉ፤ የቆሸሸ፣ የጠቆረ፣ ዝቅተኛ ጥራት ያለው ቡና ከፍተኛ ደረጃ ካለው ቡና ተሰጥቶ ነበር የሚለቀመው። ያን ሙሉ በሙሉ የሚለቅም ማሽን ገጥመው ኢንደስትሪ ሰርተዋል። ይህ ቦታ ቡና መለያ ብቻ ሳይሆን አሽገው በኮንቴነርም፣ በኩንታልም፣ በማዳበሪያም የሚያወጡበት ወጪ ንግድ የሚያዘጋጁበት እጅግ ዘመናዊ የሆነ ኮምፕሌክስ ነው። ማንም የቡና ገዥ መጥቶ ይህን ስፍራ ቢያይ ከዚህ ቦታ የሚመረት ቡና የጥራት ጥያቄ የሚነሳበት አይሆንም።

ከዚሁ ጋር የሚያያዝ ሁለተኛው ያየነው ደግሞ የከረጢት ፋብሪካ ነው፤ የሚመረተው ከረጢት ለሲሚንቶ ይውላል፣ ለቡና ይውላል አሁን ደግሞ ለስንዴ ኤክስፖርት ልንጠቀምበት እንችላለን። በጣም ከቸገረንና ከሚያስፈልገን ነገር አንዱ ፓኬጂንግ ነው። ጥሩ ብርቱካን አለን ፓኬጃችን አይረባም፣ ጥሩ ቡና አለን ፓኬጃችን አይረባም ያን የሚያመርት ኢንደስትሪ እዚህ ማምጣታችን እጅግ ተስፋ ሰጪ ነው።
ሦስተኛው የእሴት ጭመራ ነው። ቡናው እንዳለ ከሚላክ ተቆልቶ ታሽጎ እንዲወጣ የሚያስችል ኢንደስትሪ ነው ያየነው። ሦስቱንም በአንድ ዓመት ተኩል ነው ይሄ ወጣት ሰው የሠራው። እንደዚህ አይነት ኢንደስትሪዎች በየቦታው እየተበራከቱ ሲሄዱ ሥራ አጥነትን በመቀነስ ላይ የሚኖራቸው ሚና በጣም ከፍተኛ ነው። ከሥራአጥነት ባሻገር ደግሞ የወጪ ንግድ ላይ ያለንን ፍላጎትና የወጪ ምርትን በሀገር ውስጥ ምርት መተካት ላይ ያለንን ፍላጎት ለማሳካት ይህ ኢንደስትሪ በእጅጉ ጉልህ ሚና ይጫወታልና ወጣቶች በዚህ ዘርፍ ገብተው የሚያደርጉት ነገር ተስፋ ይሰጣል።

ቀደም ሲል ያየነው የአቶ በላይነህ ክንዴ የመኪና መገጣጠሚያ ነው። ቦቴና ትላልቅ ትራኮች ይገጣጥማሉ። ያ ደግሞ በሎጂስቲክስ ያለብንን ክፍተት ለመድፈን ይረዳል። እዚህ ተመረተው ቡና ከታሸገ በኋላ ወደ ባቡር ወደ ወደብ የሚሄድበት የትራንስፖርት ክፍተኛ እጥረት ኢትዮጵያ ውስጥ አለ። ምርቶች አሉ፤ ምርቶችን ወደ ከተማ ለማምጣትም፣ ወደ ወደብ ለማድረስም ያለውን ከፍተኛ ችግር የሚፈታ የተያያዘ ኢንደስትሪ ነው። አንደኛው በሎጂስቲክስ ያለብንን ክፍተት ይሸፍናል፤ ሌላኛው ደግሞ ያለንን ምርት በጥራት እሴት ተጨምሮበት ወደ ውጭ እንዲወጣ የሚያግዝ ነው። እንደነዚህ አይነት ጅማሮዎችን እያዩ መደገፍ ያስፈልጋል። የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በምናስበው ደረጃ ለመለወጥ በግብርና የጀመርነውን ሥራ ውጤታማ የሚያደርገው ኢንደስትሪው ነው። ግብርና ለኢንደስትሪው ግብዓት ነው። እዚህ ከተመረተ በኋላ ደግሞ ለዓለም ገበያም፣ ለእኛው ገበያም ሊውል የሚያስችል እድል ይፈጥራልና በጣም ተስፋ ሰጪ ሥራነው ያየነው። ቢሮዎቻቸው፣ ፋብሪካው፣ ግቢው እንዳያችሁት በማንኛውም መስፈርት ሌላ ዓለም ከምናየው የሚያንስ አይደለምና ይህን ሥራ የሠሩ ግለሰቦች ሊመሰገኑ ይገባቸዋል። እንደነዚህ አይነት ሰዎችም እንዲበራከቱ መንግሥት በከፍተኛ ትኩረት ድጋፍ እያደረገ ወጣቶች እንዲወጡ ማድረግ አለበት። በድምሩ ኢትዮጵያ ተስፋ አላት፤ ተስፋ ነው ያነው።

የሚወራው ወሬና ምድር ላይ የሚሰራው ሥራ ለየቅል ነው። ቀደም ሲል በእርሻ እንዳየነው አስደማሚ የእርሻ ውጤቶች እያየን ነው፤ በኢንደስትሪው ደግሞ ሰሞኑን መገመት ከምንችለው በላይ በዓመት፣ በዓመት ተኩልና በሁለት ዓመት አስደማሚ ሥራዎች እያየን ነው። ይህንን የገበያ ትስስር ፈጥረን ከወደብ ጋር አገናኝተን የወጪ ንግዳችንን ከፍ ካደረግን ባልነው ልክ ብልጽግና ይረጋገጣል። ያን ለማምጣት መሰረት የሚሆን ሥራ ነው ያየነው። እዚህም እዚያም የሚሰሙ ድምጾች፣ ችግሮች ከእንደነዚህ አይነት ስራዎች ትኩረታችንን እንዳያስነሱን ጥንቃቄ ያስፈልጋል። የድምጾቹ ዋና ዓላማ ሥራ እንዳንሠራ ነው። የሚረብሹን አካላት ዋና ፍላጎት በመሬት ላይ ሥራ እንዳንሰራ ነው። የእኛ ደግሞ ትኩረት መሆን ያለበት ስራችንን አለማቋረጥ ነው። የጀመርናቸውን ስራዎች መጨረስ፣ በፍጥነት በጥራት ማሳካት ነው፤ ይህንን ከማድረግ ሲያስቆሙን ይሳካላቸዋል። ስራዎቻችንን ማስቀም እስካልቻሉ ድረስ ደግሞ ሌላው ነገር ብዙ ጉዳት የሚያመጣ አይሆንምና ኢትዮጵያዊያን መንቃት ይኖርብናል።

ለማደግና ለመለወጥ እድል አግኝተናል እድላችንን አናበላሽ፣ ከተበላሸ ዳግሞ የማይጠገን ብልሽት ይፈጠራል። ያ እንዳይሆን ንቁ ሆኖ እያንዳንዱ ሰው ከራሱ ባሻገር ሀገሩን

እያየ፣ የጋራ ጥቅምን ይዞ መቆም ከቻለ ትልቅ ሀገር ነው ያለን መበልጸግ እንችላለን። እድላችንን ካበላሸን ግን ለዘመናት የሚጸጸተንና ወደኋላ ለመጠገን የሚያስቸግር ነገር ስለሚገጥመን በእንዲዚህ አይነት መልካም ሥራ ላይ ጊዜያችንን እንዳናባክን አደራ ማለት እፈልጋለሁ። የሆራ ኢንደስትሪ ኮምፕሌክስ ባለቤት ከዋናው ከኢንደስትሪ ባሻገር eco-friendly የሆነ ኢንደስትሪ በመፍጠር እጽዋትን፣ ዛፍ በመትከል ግቢያቸውንና የቢሮ ገጽታቸውን በማሳመር የኢትዮጵያን ስታንዳርድ ከፍ ስላደረጉ በተለየ መንገድ ላመሰግናቸው እፈልጋለሁ። በሌላውም ኢንደስትሪ እንደዚህ መለመድ አለበት። አቧራ፣ ጭቃ ብቻ ሳይሆን ጽድት ያለ የሥራ ከባቢ መፍጠር ለሰራተኛ ጤናም፣ የሚገዙ ሰዎች እንዲተማመኑብን ጠቃሚ ስለሆነ በዚህ መልኩ ያማረ ሥራ እንዲሰራ አደራ እላለሁ።

እንግዲህ ዛሬ በጣም፥ በጣም አስደሳች ነገር ነው ያየነውና ይሄው እንዲቀጥል ድጋፍ እናደርጋለን። በዚሁ እጅ ለእጅ ተያይዘን የኢትዮጵያን ብልጽግና ለማየት እንዲያበቃን እመኛለሁ፤ አመሰግናለሁ።

**ታኅሣሥ 26 ቀን 2015 ዓ.ም**

**ዱከም**





# በአዋሽ አርባ በተደረገ የምድር ጦርና አየር ኃይል የተቀናጀ የጦር ልምምድ ላይ የተላለፈ መልዕክት

ጥር 20 ቀን 2015 ዓ.ም

ሬ ባየሁት ነገርና እናንተንም ለማየት በመቻሌ በጣም፥ በጣም ደስ ብሎኛል። ታስታውሳላችሁ የዛሬ አራት ዓመት ገደማ አራተኛው ትውልድ የውጊያ ስልት ምን መልክ እንዳለው በንድፈ ሃሳብ ተነጋግረን ነበር። የአየር ኃይል፣ ከባድ መሳሪያ፣ የኤሊት ፎርስ ከእግረኛ ጋር ተቀናጅቶ ውጊያን በአጭር ማስቀረት የሚችልባቸውን መንገዶች በንድፈ ሃሳብ ያየናቸውን በጥቂት ዓመታት ውስጥ በዓይኔ ለማየት ስላስቻላችሁኝ እጅግ ከፍተኛ ኩራትና ክብር የተሰማኝ መሆኑን በድጋሚ ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ ።ዛሬ ያየነው ከአየር ኃይል አንጻር በትንሹ አምስት ገደማ ተግባራት አይተናል ፤ አንደኛው፣ ተግባር አየር ባየር እና ከአየር ወደ ምድር የነበረውን ውጊያ ሲያቀጣጥል አይተናል፤ ሁለተኛ፣ አየር ወለዶች ከአየር ላይ ወርደው ጦርነት የሚቀይሩ ሥራዎች ሲሰሩ አይተናል፤ ሶስተኛ፣ አየር ወለዶች በውጊያው ማብቂያ ላይ የቀረውን ጦር ሙሉ ድምሰሳ ለማድረግና የራሳቸውን ኃይል ለመደገፍ ሲወርዱ አይተናል።

የሄሊኮፕተር ተዋጊዎችም ሲሳተፉ አይተናል። በመጨረሻም እንደ ሎጂስቲክስ ቁስለኛ የሚያነሱ፣ ተጨማሪ ድጋፍ የሚያደርጉ ከምድር ጋር ተቀናጅቶ የሚሰራ የአየርን ተግባር የሚፈጽሙ የአየር ማሳያዎችን አይተናል ። ከዚህ በተጨማሪ በከባድ መሳሪያ መድፍ ፣ ሮኬት፣ ታንኮች እንዲሁም ሞርታርና ዲሽቃዎች በቡድን መሳሪያ ተሳትፈውበት በጣም ሰፊ የሚባል ቀጣና ባጠረ ጊዜ ውስጥ እንዴት ማፍረስ እንደሚቻል አይተናል። የአየር አቅማችን፣ የከባድ መሳሪያ አቅማችን ከኤሊት ፎርስ ጋር ሲቀናጅ ውጊያን ማሳጠር የሚያስችል አቅም የሚፈጥር ያልነውን በተግባር ያየንበት ቀን ነው።
ለዚህ በጣም ደስ ያለኝ ሲሆን ለጦር መኮንኖች መናገር የምፈልገው ነገር ዐይናችሁን ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያዊነት ላይ እንዳታነሱ፤ በየቀኑ ከምንፈልገው ህልምና ተግባራችን እንድናነሳ የሚሹ ኃይሎች በየቀኑ ፍላጎታቸው ኢትዮጵያን እንዳናስቀድም፥ ሰፈር እንድንገባ፥ ትልቁን ያየነውን ነገር እንዳናሳካ፣ የጀመርነውን እንዳንጨርስ፣ ሀገር መከላከል መጠበቅ ውጊያን ማስቀረት የሚችል ኃይል እንዳንገነባ የሚፈልጉ በትናንሽ አጀንዳ ላይ ታጥረን እንድንቀይ የሚፈልጉ ኃይሎች አሉ።

የጦር መኮንኖች ዋና ተግባር የሚሆነው ጦርነትን የሚያስቀር ኃይል መገንባት ነው፣ ጦርነት አንፈልግም የምንፈልገው ሰላም ነው፤ ሰላም ግን በምኞት አይመጣም በዝግጅት ነው የሚመጣው፤ የሚያስጠነቅቅ፣ የሚያደርግ አቅም በመገንባት ነው የሚመጣው። የእናንተ ሥራ በቀጣይነት ኃይል ገንብቶ ጦርነት ማስቀረት፣ የእናንተ ሥራ ትልቋን ኢትዮጵያ ማየት፣ የእናንተ ሥራ የኢትዮጵያ ብልጽግና የኢትዮጵያ ልማት እንዳይደናቀፍ አስተማማኝ ጥበቃ ማድረግ ነው። አሁን ዛሬ ያየነው የውጊያ ልምምድ ለሰፈር ውጊያ የሚውል አይደለም ጠንከር ያለ አቅም ነው።

እኛ በግልጽ ቋንቋ መናገር የምንፈልገው ኢትዮጵያን አትንኳት፤ ኢትዮጵያ መልማት መበልጸግ ትፈልጋለች፤ በግራ በቀኝ ኢትዮጵያን የሚያዳክም ሥራ የምትሰሩ ከሆነ በመላው አቅማችን ህይወታችንን ገብረን ሀገራችንን እንታደጋለን የሚል መልዕክት ለሚነካኩን ኃይሎች ማስተላለፍ እፈልጋለሁ። እኛን ከመንካታችሁ በፊት ደጋግማችሁ አስቡበት።

ለወዳጆቻችን ደግሞ እንደምታስቡት አይደለም ጠንካራ ተቋም እየገነባን፣ ጦርነት የሚሰሩ ጀነራሎች እየፈጠርን ነው፣ በልምምድ ወቅት ከጦርነት ማግስት እንደዚህ አይነት የተቀናጀ ሁሉን ቴክኖሎጂ የሚጠቀም ልምምድ ማድረግ የሚችሉ የጦር ወታደሮች ያሉት ሀገርና ተቋም ነው እያደረጀን በመሆኑ ወዳጆቻችን ደግሞ ክብር ይሰማችሁ፤ ኢትዮጵያ ራሷንም ቀጣናውንም ለመጠበቅ ትዘጋጃለች የሚል መልእክት ያለው ነው። ይሄ መቀጠል አለበት፤ በየቦታው፣ በየእዛችሁ ፣ በየኮሮች ፣ በየክፍለ ጦሮች በየደረጃው ስልጠና ልምምድ መቀጠል አለበት፣ መከላከያን ማጠናከር መቀጠል አለበት፣ ወንድማማችነትን ማጠናከር መቀጠል አለበት።

መከላከያ ከዘርና ከሰፈር በላይ ሆኖ ኢትዮጵያን እንዲጠብቅ አሻግሮ የሚመለከት የጦር ጀነራል ያስፈልጋል፣ ተራሮቹን ለማፍረስ በአየር በከባድ መሳሪያና በእግረኛ እንዴት እንዳቀዳችሁ ስትነግሩን እንደነበር ሁሉ በውስጣችንም ያለውን የመበልጸግ፣ የማደግና ከልመና የመውጣት የመሻት ትልምን አርቀን የምናይና የበረታን መሆን አለብን። ጠንካራ ኮማንደሮች የምንፈጥር መሆን አለብን። ከእናንተ በታች ያሉ ልጆች ደግሞ ከእናንተ የተሻለ እውቀት ይዘው ሀገራቸውን ማገልገል እንዲችሉ አዳዲስ ኃይል ልታፈሩ፣ አንድ እንድትሆኑና እንድትበረቱ አደራ እላለሁ።

አንድ ነጥብ አትርሱ በውጊያ ያሸነፍነው፣ ኢትዮጵያን ያስቀጠልነውና ልማቶቻችን እንዳይቋረጡ ያደረግነው አንድ ሆነን ነው። አንድነት ካለ እንሻገራለን በቀጣይነት

ተቋሙን እንገነባለን። በመግዛት ብቻ ሳይሆን በመፍጠር፤ እዚህ ያላሳየናቸው አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች አሉ። በመፍጠርም ጭምር ተቋሙን በማጠናከር የኢትዮጵያን ህልውና የሚጠብቅ ኃይል እናደርጋለን። ዛሬ የመድፍ፣ የአየር፣ የታንክ ጩኸት አይተናል። ወደፊት ደግሞ የትራክተር፣ የኮምባይነር ድምጽ እንደምንሰማ ተስፋ አደርጋለሁ። እንደምታውቁት ለመልማት ከፍተኛ ፍላጎት ስላለን መከላከያ በፍጥነት ወደ እንደዚህ አይነት ልማቶች እንደሚገባ ተስፋ አለኝ።

ወሳኝ ወሳኝ የሆኑ ባዶ ቦታዎች በሁሉም ቀጣና ስላሉ እያንዳንዱ እዝ የራሱን ቦታ ይዞ በስፋት በታንክ መሬት ማረስ ብቻ ሳይሆን በትራክተርም ማረስ እንዲጀምር፥ የተሰበሰቡ ስንዴዎች፣ አቮካዶዎች፣ ፓፓያዎች ማሳየት እንዲጀምር እንጠብቃለን። አሁን ቀጣይ ሥራችሁ ልማት ማፋጠን፣ ሠራዊት መገንባት፥ አቅም ማጠናከር ይሆናል። እዚህ ያላችሁ ኮማንደሮች ስላየኋችሁ በጣም፣ በጣም ደስ ብሎኛል፤ የኢትዮጵያ የኩራት ምንጮች ናችሁ። አመሰግናለሁ።

**ጥር 20 ቀን 2015 ዓ.ም**
**አዋሽ**

# በሰላምና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ዙሪያ የተሰጠ ማብራሪያ

**ጥር 24 ቀን 2015 ዓ.ም**

የሰላም ግንባታ አመለካከት (Attitude) ነው፤ ለሰላም የሚሰጥ ዋጋ ነው። የሰላም እሳቤ እንዲያድግ ዋነኛው መሰረታዊ ሥራ አመለካከት ላይ የሚሰራ ሥራ ነው፣ ሁለተኛው ህግ ማስከበር ነው፤ የትም ዓለም ሰላም በቸሮታና በፍቃድ የሚረጋገጥበት ምድር የለም፤ ቢኖር ኖሮ ህግ አያስፈልግም ፖሊስ አያስፈልግም። ሰላም በህግ ነው የሚከበረው። ለአብዛኛው ሰው በአመለካከት ግንባታ ያስፈልጋል፤ ከዚያ ወጣ ለሚለው ደግሞ ሰው ህግ አስከባሪና ህግ ያስፈልጋል። ሁለቱ ነገሮች ተጣጥመው መሄድ አለባቸው፤ ማስተማሩም ህግ ማስከበሩም።

በጣም ጎልቶ የወጣው ከሃይማኖት ጋር የሚያያዝ ጉዳይ ስለሆነ በእኔ መረጃና ምልከታ የሃይማኖት ተቋማት ከሦስት ነገር ቢጠበቁ ከብዙ ችግር ነጻ ይሆናሉ። አንደኛው ፖለቲካ፣ የሃይማኖት ተቋም የፖለቲካ እሳቤዎች መሸከሚያ ቦታ ባይሆን፤ ሁለተኛ፣ ሌብነት ዓለምን ያስቸገረው ሌብነት እነሱንም ባያስቸግራቸው፤ ሶስተኛ፣ ዘር የሃይማኖት ተቋማት ሁሉም ፖለቲካን፣ ሌብነትንና ዘርን ከውስጣቸው ቢያጠፉ ወይም ቢቀንሱ አብዛኛው ችግር ይፈታል። ይሄ ጉዳይ የአንድ ሃይማኖት ተቋም ችግር አይደለም የሁሉም ነው፤ ሁሉም ዘንድ ዘር አለ፣ ሌብነት አለ፣ ፖለቲካ አለ። ሌብነቱ ያስፈራል፣ ሲሰማ ያስደነግጣል። ሦስቱም አያስፈልጋቸውም የሚባልበት ዋነኛው ምክንያት እነሱ ዓላማቸው ዘላለማዊ ነው። ፖለቲካ ጊዜያዊ ነው፣ የሌብነት ጥቅም ጊዜያዊ ነው፣ ዘር እዚሁ የሚቀር ነው ከእነሱ እሳቤና ዓላማ ጋር አብሮ አይሄድ። ሰማያዊውን መንግሥት የሚጠብቁና የሚገነቡ ወታደሮች ስለምድራዊው ቢጨነቁ ራሳቸው ፍላጎታቸውን ስለሚቃረኑ ጥፋት ያመጣባቸዋል።

ይሄ ጉዳይ በኢትዮጵያ ውስጥ በተደጋጋሚ ታይቷል። በታየበት ጊዜ ሁሉ የታሪክ ስብራት የእድገት እንቅፋት፣ አብሮ የመኖር ጉዳት ብቻ ነው የሆነው ጥቅም አልነበረውም። አሁን በሰከነ መንገድ ማየት የሚያስፈልጉ ጉዳዮች አሉ። ሰሞኑን የጎላው የኦርቶዶክስ ጉዳይ ስለሆነ የኦርቶዶክስን ጉዳይ አነሳለሁ። ከጥቂት ወራት በፊት ሙስሊም ነበር እንዴት መከራችንን እንዳየን ታስታውሳላችሁ። የኦርቶዶክስን በሚመለከት በእኔ እይታ ጉዳዩ በጣም ቀላል ነው። በእኔ እይታ ምድራዊነትን፣ ማን አሕሎኝነትና እኔነት ከተተወ

ይፈታል ብዬ ነው የማስበው፣ ከባድ ነው ብዬ አልወስድም። በታሪክ እንደምታውቁት የኃይለሥላሴ መንግሥት ወደኋላ አካባቢ ነው የኢትዮጵያን ጳጳሳት በተለይም ፓትርያርክ መሾም የጀመረው። ቀደም ሲል ፓትርያርክ ከግብጽ ይመጣ ነበር። በንጉሱ ዘመን የመጨረሻው ፓትርያርክ ደርግ እንደመጣ ብዙም አብረው ሊጓዙ አልቻሉም። ጉዳዩ ብዙ ቢሆንም ለኃይለሥላሴ መንግሥት ቃለ መሀላ ፈጽመው ፓትርያርክ የሆኑት አባት ከመጣው አዲስ መንግሥት ጋር መጓዝ ተቸግረዋል። እሱን በጊዜው በዓይን ያዩ በጆሮ የሰሙ እማኞች በዝርዝር እንዲናገሩት የሚተው ቢሆንም ደርግ ያደረገው ግን ፓትሪያሪኩን ገድሎ የራሱን ፓትርያርክ ሾመ። ይሄ የኢትዮጵያ የትናንትና ታሪክ ነው። ቀጥሎ ኢሕአዴግ ሲመጣ በደርግ ጊዜ የነበሩት ፓትርያርክ ኢሕአዴግ የሚባል መንግሥት ሲመጣ አብሮ መቀጠልና መስራት በብዙ ምክንያት ስለተቸገሩ ኢሕአዴግ ከደርግ ሻል ባለ መንገድ ግድያ ሳይፈጽም በደብዳቤ ከሀገር አስወጣቸው።

እኛ ስንመጣ ግድያውም ትክክል አይደልም፣ የራስ ፓትርያርክ ማሾምም ትክክል አይደለም፣ ከሀገር ማስወጣትም ትክክል አይደለም ብለን ከሀገር ውጭ የነበሩትንና በሀገር ውስጥ ያሉትን ለማስታረቅና አንድ ለማድረግ ነው የሞከርነው። አንዱ መሰረታዊ ልዩነት ይሄ ነው። ይሄ ተራ ጉዳይ አይደለም፤ በአንድ መንበር ሁለት ሊቃነ ጳጳሳት አይቀመጡም። በአንድ መንበር አንድ ጳጳስ ያውም እስከ ህይወት ፍጻሜው ድረስ የሚል ቀኖና ህግ ቢኖርም በሁለቱም አባቶች በጎ ፍቃድ በእኛም ፍላጎትና ድጋፍ ያ ጉዳይ ተፈቶ ሁለት ቦታ ተከፍላ የነበረች ቤተክርስቲያን አንድ መሆን ችላለች። ይሄ ለየትኛውም የእምነት አባል ኢትዮጵያዊ ክብር ነው፣ ለየትኛውም የእምነት አባል ኢትዮጵያዊ መደረግ ያለበት ተግባር ነው። ኦርቶዶክስን ማፍረስ፣ ማዳከምና መጉዳት ጉዳቱ ለኦርቶዶክስ ብቻ ሳይሆን ለሁላችንም ነው፤ መከላከል፣ ማገዝና መጠበቅ ያስፈልጋል።

ሁለተኛው ከመንበር ጋር በተጨማሪ የነበረው ጉዳይ በአሜሪካ ሀገር ተሾመው የነበሩት ጳጳሳት በሲኖዶስ በሀገር ውስጥ ያልተሾሙ በመሆናቸውና ቁጥራቸውም በርከት ያለ ስለሆነ ሲመለሱ እንዴት ይሆናሉ የሚለውም ጉዳይም ነበር። እነዚያ ጳጳሳት ምንም እንኳን በነበረው ሁኔታ አሜሪካ ቢሾሙም አዲስ ከውጭ የመጡ ሰዎች ሳይሆኑ ከጵጵስና በፊት ባሉ ደረጃዎች እዚያው ቤተክርስቲያን ውስጥ ያደጉ ናቸው። እነሱን እንደ ጳጳስ መቀበልና ሰላሙን ማምጣት ካለው ችግር አይብስም መቀበል ይሻላል የሚደገፍ ነገር ካለ እንደግፋለን በሚል እርቅ ተፈጸመ። እርቅ ሲፈጸም ደርግ የወረሰው፣ ኢሕአዴግ ያልሰጠው ከአርባ ዓመት በላይ የኢትዮጵያ መንግሥት ንብረት የሆኑ ሁለት

ትላልቅ ህንጻዎች አራት ኪሎ ያሉ መንግሥት ለኦርቶዶክስ መልሶ ሰጥቷል። በሰላሙ ምክንያት በአንድነቱ ምክንያት ኦርቶዶክስ ክብር፣ ጥቅም እንጂ ጉዳት አታመጣም ብለን የገባነውን ቃል ለመፈጸም በተግባር ምላሽ ሰጥናል።

ሁለተኛው መሬት ነው። አንዳንድ ሰዎች መንግሥት ኦርቶዶክስን እንደዚህ ያደርጋል፣ እንደዚህ ያደርጋል ይላሉ እሰማለሁ። ግን እንደኛ መንግሥት ኦርቶዶክስን በቅርበት የደገፈ ከንጉሡ ሥርዓት ውጭ ምንም ሥርዓት ኢትዮጵያ ውስጥ አልነበረም። የክልሎችን ትቼ የአዲስ አበባን ብቻ ባለፉት አራት ዓመታት የነበረውን የመሬት ስጦታ ወይም የመሬት ክፍፍል ለማንሳት እሞክራለሁ። ካቶሊክ፣ ሙስሊም፣ ወንጌላዊያን፥ ቃለህይወትን፣ መካነየሱስን፣ ሙሉ ወንጌልንና ሰባተኛው ቀን አድቬንቲስትን ጨምሮ ትልልቆቹን በጣም ብዙ ተከታይ ያላቸውን ማለት ነው ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የእምነት ተቋማት በሙሉ ከኦርቶዶክስ ውጭ 350ሺ ገደማ ካሬ ሜትር መሬት በካርታ ባለፉት አራት ዓመታት ወስደዋል ። ኦርቶዶክስ አንድ ሚሊየን 45ሺ ካሬ ሜትር ወስዳለች፤ የሁሉ ሃይማኖት ተደምሮ ሦስት እጥፍ ገደማ የሚሆን መሬት በካርታ ተሰጥቷታል ባላፉት አራት ዓመታት። መንግሥት አጠቃላይ የሃይማኖት ተቋማትን ይደግፋል፣ ታክስ አይቀበላቸውም፣ ሱቅ ቤት ሲከፍቱ ግብር አያስከፍላቸውም ብቻ ሳይሆን መሬት በነጻ በስፋት በካርታ ያቀርብላቸዋል በሊዝ አይደለም። ለምድን ነው ያን የሚያደርገው ተቋማቱ ለሀገር በጣም አስፈላጊ ስለሆኑ ነው። ተቋማቱ ቅድም ካልኩት ከዘር፣ ከፖለቲካና ከሌብነት የጸዱ ሆነው ዜጎችን በዚያ መንገድ ቢያንጹ ጠቃሚ ስለሆነ።
ይሄ ብቻ አይደለም፤ የላሊበላ ቤተክርስቲያን ሁላችሁም እንደምታውቁት ልክ እንደግድቡ ወይንም እንደሆነ ልማት የኢትዮጵያ ቅርስ የኢትዮጵያ ሀብት ነው ተብሎ በነበረን ቅርርብ ለፕሬዘዳንት ማክሮን ጥያቄ አቅርበን እሳቸውም ተስማምተውበት ለማገዝ በዩኔስኮ ምክንያት ሰፊ ግዜ የወሰደ ቢሆንም ድጋፍ አግኝተን ቤተክርስቲያኑን የማደስ ሥራ በቅርቡ ይጀምራል። ይሄ በቀጥታ የመንግሥት ጉዳይ ስለሆነ ሳይሆን ቅርስነቱ፣ ተቋሙ አስፈላጊና መደገፍ ያለበት ነው ከሚል የመጣ ነው ። በአረቡ ዓለም እስካሁን ድረስ በተለይ ዩናይትድ አረብ ኢ.መሬትስ ኦርቶዶክስም፣ ጴንጤውም ሌላውም በሰዓት እየተከራዩ በየአዳራሹ ከሚያደርገው አገልግሎት ውጭ የራሱ ይዞታ የለውም። የአቡዳቢን መንግሥት ለምነን በጣም ሰፊ ቦታ አምስት ወይም ስድስት ሄክታር አካባቢ ቦታ ሰጥቶን ኦርቶዶክስ ይዞታውን ይዛ ለግንባታ ሀብት ለማፈላለግ ጥረት እያደረገች ነው። እሱን ማገዝ አለብን፣ ያስፈልጋል ቅርስ ነው፣ የሁላችንም ነው፣ የዛ እምነት ተከታይ መሆን አለመሆን አይፈልግም ቅርስ ነው።

በአረቡ ዓለም ቤተክርስቲያን እንዲኖር፣ ቀድሞ የነበረው ላሊበላ እንዲታደስ፣ የተወረሰ ህንጻ እንዲመለስ፣ መሬት በስፋት እንዲሰጥ፣ ሁለቱ ሲኖዶሶች እንዲታረቁ ሌሎች አሁን የማልዘረዝራቸወን ድጋፎች ሁሉ የኢትዮጵያ መንግሥት ሲያደርግ የነበረው የተቋሙን አስፈላጊነት ከልብ ስለሚያምን ነው። አሁን ደርሶ ሰው ኦርቶዶክስን አልደገፋችሁም ብሎ የፖለቲካ አጀንዳ ማድረግ አይቻልም። የትኛውንም የታሪክ መዝገብ ቢያገላብጥ የብልጽግናን ያክል የሃይማኖት ተቋማትን የደገፈና አብሮ የቆመ መንግሥት ሊያገኝ አይችልም የንጉሶቹ ሌላ ጉዳይ ነው። በዚህ ምክንያት ተቋሙን እንፈልገዋለን፣ ተቋሙን ደግፈነዋል፣ በዚህ ምክንያት ምንም ወደኋላ የምንልበት ጉዳይ የለንም፣ ብናደርግ ኖሮ የሚል ቁጭት የለንም። ሰሞኑን ያጋጠመው ምንድን ነው? ከሁለት ወይንም ሦስት ዓመት በፊት ሊሆን ይችላል ጊዜውን እርግጠኛ አይደለሁም፤ በኦሮምኛ ቋንቋ ኦሮሚያ ውስጥ መገልገል ባለመቻላችን ብዙ ምዕመን ብዙ አገልጋይ ወደ ሌላ እምነት እየፈለሰ ስለሆነ በቋንቋችን ማገልገል የሚችሉ ሰዎች ይሾሙ የሚል እንቅስቃሴ ነበር። ጥያቄውም እንቅስቃሴም ነበር። ምን አደረግን እኛ፤ ይሄ ጉዳይ ጥሩ አይደለም፣ በሰከነ መንገድ ተነጋገሩ፣ የሚገሰጽ ካለ ገስጹ፣ የሚሾም ካለ ሹሙ ፣ የሚመከር ካለ ምከሩ በቤታችሁ ፍቱ አልን ። እነሱም እግዚአብሔር ይስጣቸው ቁጭ ብለው ተነጋግረው ተመካክረው አስተካክሉት ጠፋ ያ ነገር፤ ዓመት ሁለት ዓመት የሚሆን ብዙም ጉዳይ አልነበረውም።

አሁን ተመልሶ ጉዳዩ እንደገና ተነሳ። አሿሿም ላይ አድሎ አለ፣ ህገመንግሥታዊ መብታችን በአፍ መፍቻ ቋንቋችን በብዙ ትግል ያገኘነው መብታችንን እንዳንጠቀም ጫና አለብን የሚሉ ጥያቄዎች መጡ። እኛም የመንግሥት ሃላፊዎች ወክለን ላክን። እባካችሁን አታጋግሉት ቀስ ብሎ በሰከነ መንገድ ፍቱት፣ በውይይት ፍቱት ምክንያቱም ጉዳዩ እንዲሁ በቀላሉ የሚቋጭ ነገር አይደለም፤ ቤተክርስቲያን  አባቶችን አስቀምጣ ገስጻ፣ መክራ  ችግር ካለባትም አርቃ፣ አርማ ብትፈታው የእኛ መሻታችን ነው ብለን ችግሩ ባጋጠመ ሰሞን መጀመሪያ በመንግሥት ምክር ለግሰናል።
ምክራችን አልተደመጠም፣ አልተተገበረም፤ እኛ ማዘዝ አንችልም፤ መምከር ነው የምንችለው። መፍትሄው ተቀራርቦ መነጋገር ነው። ኦሮሚያ ውስጥ በኦሮመኛ ቋንቋ አገልግሎት ይሰጠኝ ብሎ የሚጠይቅን ምዕመን አይሰጥህም ልለው አልችልም እኔ። እኔ አይደለሁም ለኦሮሞ በቋንቋው የመጠቀም መብቱን ያጎናጸፍኩት፤ ያን መብቱን መቃረን ሳይሆን፣ መፋረስ ሳይመጣ በንግግርና በምክክር በጊዜ ሂደት በአንድ ቀን ላይሆን ይችላል፣ በጊዜ ሂደት መልክ እያበጁ መሄድ ነው። ለምሰሌ በድፍን ኦሮሚያ አሁኑኑ መቶ ሰው ተሹሞ ላይባል ይችላል፤ ቀስ እያሉ የምዕመኑን ፍላጎት ደረጃ በደረጃ እየመለሱ የቋንቋ፣ የዘርና የፖለቲካ ጉዳይ ትልቁን ተቋም እንዳያፈርስ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

ጥያቄው በትግራይ ክልል ያሉ ምዕመናን በቋንቋቸው ይገለገላሉ፣ በትግራይ ክልል ላይ ያሉ አባቶች በቋንቋቸው ያስተምራሉ ብቻ ሳይሆን ከዓመት ሁለት ዓመት በፊት የትግራይ ክልል ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ወጥቻለሁ ሲል አንድ ሰው እንኳን <<ኧረ ባካችሁ አይደረግም>> አላለም እንኳን መግለጫ፣ እንኳን ይሄ ሁሉ ግር ግር አንድ ሰው እንኳን ለምን ይደረጋል እኛ ከፖለቲካ ነጻ ነን፣ እኛ አብረን የኖርን ነን ብሎ ለመምከር እንኳን ጥረት አላደረገም። ለምን አሁን የሚል ጥያቄ ይነሳል። በአማራ ክልል በአማርኛ ነው ሰው የሚገለገለው በራሱ ቋንቋ። ደቡብና ኦሮሚያ ሲሆን እንደዛ አይደለም የሚል ጥያቄ ይነሳል። ይሄን መንግሥት በማዳፈን ማለፍ አይችልም፤ ቁጭ ብሎ በሰከነ መንገድ ተመካክሮ ተነጋግሮ የምዕመኑን ፣ የህዝቡን ፍለጎት መመለስ ነው።
ምክንያቱም ምእመኑ ሁሉም የኦርቶዶክስ ልጆች ናቸው ሰሜንም ይሁን፣ ምስራቅ፣ ምዕራብ ይሁን ደቡብ የትኛውንም ቋንቋ ይናገር በዛች ቤተክርስቲያን ጥላ ስር እስካለ ድረስ እምነቷን፣ ዶግማዎንና ቀኖናዋን እስከተቀበለ እናት ናት፣ እነሱም ልጆች ናቸው። ልጆች የሚያስፈልጋቸውን በህግ አግባብ መፍታት ያስፈልጋል።

የመጨረሻ ምክሬ ግን ለሁሉም አባቶች እንደ አባ ማቲያስ ሁኑ፤ ፓትሪያሪኩ ሁለቱን ቡድኖች በምናስታርቅበት ጊዜ የወሰዱት በጣም ብልህ የሆነ አቋም ቤተክርስቲያኒቷን ታድጓታል። ወንበሩ ላይ እኔ አለሁበት ተጨማሪ ሰው አይገባም ቢሉ አናስታርቅም ነበር፣ ችግር የለውም ይምጡ ስላሉ ነው መታረቅ የቻሉት። በመተው፣ በመሸነፍ፤ የነበረውን ጥላቻ የነበረውን ንግግር ሳይሆን ማለፍ ስለሚሻል። አሁንም መገፋፋቱ ትርጉም የለውም፣ ጥቅም የለውም ኢትዮጵያን ይጎዳል፣ የኢትዮጵያን መንግሥት ይጎዳል፣ ኦርቶዶክስን ይጎዳል ጥቅም የለውም። በሰከነ መንገድ ቁጭ ብሎ ተነጋግሮ፣ ተመካክሮ የጎደለ ካለም ሞልተው፣ የሚስተካከል ካለ አስተካክለው፣ የሚታረቅ ካለም አርቀው፣ ምክር የሚያስፈልገው ካለም መክረው የነበረውን ነገር ማስተካከል ነው የሚሻለው።
ምድር፥ ምድር መሸተት ሳይሆን ሰማያዊ ሽታ ነው የሚያስፈልገው። ለግል ክብር አይደለም፣ ለእምነት ነው የሚሰራው ለእግዚአብሄር ነው፤ ለግል ጥቅም፣ ለግል ክብር፣ ለግል ስልጣን አይደለም ምንም ፍጅት አያስፈልገውም ዘር አያስፈልገውም፣ ፖለቲካ አያስፈልገውም ዓላማው እሱ ስላልሆነ። እኛ የምንጣላው ለወንበር ሽሚያ ነው፣ ፖለቲካው ሌላ ትርጉም ነው ያለው። እዚህ ጋ እንደ አባት ሆኖ እልህን፣ እስቲ አሳይሃለሁ፣ አሳይሻለሁ ተትቶ በሰከነ መንገድ ተወያይተው ቢፈቱ መንግሥት ለእነሱ አንድነት፣ ሰላም፣ ምክክር ከሚጠበቀው በላይ ሲያደርግ እንደነበረው አሁንም ያደርጋል።

ግን እኔን ካልደገፍከኝ አልሰራህም ያንን ካልደገፍከው አልሰራህም የሚባል ነገር ብዙ ጥቅም የለውም። ታስታውሱ እንደሆን በሙስሊምም ይሄ ችግር አጋጥሞን በብዙ ልመናና ምክክር በውስጥ ውይይት እንዲፈቱ ነው ያደረግነው። አሁንም ያለን አቋም አንድ ነው። በተለየ የምንደግፈው፣ በተለየ የምንቃወመው ኃይል የለም። ሁለቱም ኃይሎች ኦርቶዶክሶች ናቸው፣ ሁለቱም ጋር ጥያቄዎችና እውነቶች አሉ፣ አንዱ ዘንድ ብቻ አይደልም ያለው የህዝብን መብት፣ የህዝብን በራስ ቋንቋ የመጠቀም መብት ሳያፍኑ መፍታት ይቻላል። ያንን ካደረጉ ለእነሱም ለእኛም እንደ ሀገር ጠቀሚ ነው፤ ከዚያ ውጭ ያለው አማራጭ ብዙ የሚፈይድ አይደለም፣ ብዙ እጃቸውን የሚያስገቡ ኃይሎች አሉ፣ ብዙ ናቸው።

እዚህ ያላችሁ የካቢኔ አባላት አንዳችሁም በዚህ ጉዳይ እጃችሁን ማስገባት አይፈቀድላችሁም፤ አንዳችሁም። አንድ ሰው እጁን እንዳያስገባ። በዚህ ጉዳይ እንደተቋም ከመንግሥት ጋር ተጋግዘን አንድነታችንን እንጠብቃለን ካሉና መንግሥት የሚያደርገው ነገር ካለ በጣም ዝግጁ ነን። በተናጠል ግን በዘር እየደወልክ፣ በሰፈር እየደወልክ የሚደረግ ጨዋታ ኢትዮጵያን ስለማይጠቅም፣ ስለሚጎዳ እኛም እጃችንን እንሰበስባለን። ለእነሱም ማዘዝ ባንችል ምክራችን እንደ አባ ማቲያስ ሆናችሁ ትታችሁ፣ ሰክናችሁ፣ ተመካክራችሁ ችግራችሁን ብትፈቱ አንድ ብትሆኑ ይሻላል።
አንድ ባይሆኑስ ሁለቱም ቡድኖች ይጎዳሉ፣ የሚያተርፍ ቡድን የለም። በዚህ አብሮ ለብዙ ዘመናት የኖረ ሰው ችግሩን ተነጋግሮ ፈቶ ተጠናክሮ መቀጠል ሲገባው መነጋገር ባለመፈለግና በእልህ ቢበተን ሁለቱም ተጎጂ ነው ጥቅም የለውም።

ወደዛ እንዳንሄድ የእኛ ፍላጎት በምክክር፣ በንግግር ችግራቸውን ፈተው እንዲቀጥሉ ነው። እንደመንግሥት ግን የትኛውም መንግሥት አድርጓቸው የማያውቃቸውን ድጋፎች አድርገናል፤ እንደመንግሥት ግን ጣልቃ ገብተን በየትኛውም ሃይማኖት ውስጥ እንትናን መሾም አለብህ፣ እንትናን መጣል አለብህ አንልም። እናውቃለን አባቶችም ያውቃሉ በነበሩ ሹመቶች ውስጥ መንግሥት ሳያዝ የሚሾም ሰው አልነበረም። ስም ተሰጥቶ መንግሥት የሚፈልጋቸው ሰዎች ይሾሙ ነበር። እኛ ሹመት ውስጥ አንገባም፤ የእኛ የምንለው የተለየ አባትም የለንም፤ ሁሉም አባት አባታችን ነው ። በጋራ ሆነው እንዲቀጥሉ ነው የምንፈልገው። ከዚህ ውጭ ከመስመሩ ውጭ ይህን ነገር በጣም በማራገብ የሚወሰደው ጉዳይ አሸናፊ አልቦ ሙግት ስለሆነ ጥሩ አይደለም፤ ወደ ውጤትም አያመጣም በዚህ አግባብ በሰከነ መንገድ መታየት አለባት።

አጠቃለይ ሰላምን በሚመለከት ያለው እሳቤ ኢትዮጵያ ውስጥ ትንሽ ችግር አለበት። ችግሩ ምንድነው፤ አጀንዳ በመፍጠር ሰው እንዲጋደል በማድረግ ያንን በማህበራዊ ሚዲያ እንዲራገብ በማድረግ መንግሥትን እንጥላለን፣ እናዳክማለን የሚሉ ሰዎች ይጠቀሙበታል፤ የፖለቲካው ገበያ ብልሽት አንዱ ውጤት እምነትን፣ ዘርን መጠቀሚያ አድርጎ በንጹሃን ደም ወደ ስልጣን መምጣት መፈለግ ነው። ይሄን በሌላ መድረክ አንስቼዋለሁ፣ ዛሬም እደግመዋለሁ። የደርግ መንግሥት የንጉሡን ሥርዓት የጣለው በመፈንቅለ መንግሥት ነው፤ ወታደሮች ተደራጅተው የመንግሥትን ስልጣን ይዘዋል። ከዛ በኋላ የመንግሥትን ስልጣን በመፈንቅለ መንግሥት እንይዛለን ብለው የመጡ ቡድኖች ሁለት ሦስት ጊዜ ተበልተዋል። ምክንያቱም የመንግሥቱ የመጀመሪያው ትልቁ ብቃት መፈንቅለ መንግሥት ነው። በሚያውቀው መንገድ ልትቀይረው አትችልም፣ አዲስ መንገድ ያስፈልጋል። በራሱ በሚያውቀው መንገድ መጥተው የተበሉ ብዙዎች መጥፋት የሌለባቸው ሰዎች ጠፉ።

ኢሕአዴግ በሽምቅ ውጊያ ነው የመጣው። ይሄው እነ ፕሮፌሰር ብርሀኑ እና አቶ ቀጀላ መርዳሳ በሽምቅ ውጊያ ኢሕአዴግን እንጥላለን ብለው እዛው ቀሩ። ምክንያቱም ኢሕአዴግ የመጣበት መንገድ ስለሆነ በዚያ መንገድ ኢሕአዴግን ማሸነፍ አይቻልም። ወደ እኛ ደግሞ ሲመጣ ብዙ ሙከራዎች ይታያሉ። በከተማ ውስጥ ግርግር፣ በብልጽግና ውስጥ ሁለት ሦስት ሰው በመቅጠር። ይህ መንግሥት መቸም እንደማይፈርስ ላረጋግጣላችሁ እወዳለሁ። እንዴት እንደሚሠራ እናውቀዋለን፣ እንዴት እንደሚረበሽ እናውቀዋለን፣ በዚያ መንገድ የሚያስብ ሰው ካለ ራሱን ይበላ እንደሆን እንጂ ለኛ ችግር የለውም።

ይሄ ነው በጣም አደገኛው ነገር። ኢትዮጵያ ውስጥ አዲስ ሃሳብና አዲስ ሲስተም ይዞ መጥቶ ነገር ከመለወጥ ይልቅ መንግሥት ሥራ እንዳይሰራ በየቦታው አጀንዳ እየፈጠርክ እያጋደልክ አንዳንዴ ኦሮሞ፣ አማራ፣ ወላይታ፣ ሲዳማ ሊሆን ይችላል አንዳንዴ ግን ወለጋ፣ ሸዋ ሊሆን ይችላል፣ ጎንደር ጎጃም ሊሆን ይችላል ማቆሚያ የለውም በየሰፈሩ ነው። አንዳንዴ ኦርቶዶክስና ጴንጤ ይሆናል፣ አንዳንዴ ኦርቶዶክስ በራሱ ይሆናል፣ አንዳንዴ ጴንጤ በራሱ ይሆናል፣ ያው እንደምታዩት ነው።

ይሄ ነገር አያዋጣም፤ ሀገር ከማፍረስ ሰው ከማበጣበጥ የንጹሃን ደም ከማፍሰስ መጠበቅ ያስፍልጋል። ጉዳዮቻችን በፖለቲካ ንግግር እንጂ በዚያ በመሰለ መንገድ ፍላጎታችንን ማሳካት ብዙም የሚያዋጣ ስላልሆነ ማሰብ ጥሩ ነው። በየጊዜው ጥርጣሬ መዝራት፣ እኩልነት እንደሌለ ማሳየት፣ ውሸት አጀንዳ እየፈጠሩ ሰው ውስጥ መጨመር ይሄ ነው

የተለመደው። እያንዳንዱ የሚፈጠሩ አጀንዳዎች ሃቅን በማጣራት ውሸት መሆናቸውን ታውቃላችሁ። ያው አብዛኛውን ስለምንወያይበት በዚያ መንገድ መሄድ አደገኛ ነው፤ ለእኛም፣ ለእነሱም፣ ኢትዮጵያን ለሚፈልግ ኃይልም ይሄን የሚያራግቡ ሰዎች ቅጥረኞች መሆናቸውን የማናውቅ ይመስላቸዋል።

በብዙ መንገድ ኢትዮጵያን ለማፍረስ የሚፈልጉ ኃይሎች ብዙ ዓይነት ሙከራ ያደርጋሉ። ከሙከራዎች አንዱ እንደዚህ አይነት አብሮ ያለመቀምን ሃሳብ ደጋግሞ እንዲነገር ማድረግ ነው። ሚዲያዎችም ቢያስቡበት ጥሩ ይሆናል። በእኛ በኩል ህዝብ እናወያያለን፣ ያሉ እውነታዎችና ዳታዎችን ለህዝብ እንገልጻልን፣ በአሰራር መስተካከል የሚገባቸው ጉዳዮች ካሉ አሰራሮችን እናስተካክላለን። ለምሳሌ በቅጥር በሹመት ጉዳች ላይ ለሚፈጠሩ ነገሮች ህግ እናወጣለን ችግር የለውም፣ ሁሉም ሰው በእኩልነት የሚጠቀምባቸውን ስርዓቶች እንጠቀማለን።

ሚዲያን በሚመለከት የመጀመሪያው ሥራ እናስተምራለን፣ እንመክራለን፣ እንገስጻለን፤ ሁለተኛው ሥራ በህግ አግባብ እንጠይቃለን። ሚዲያ ነኝ ማለት ህዝብን ከህዝብ፣ እምነትን ከእምነት ማባላት የሚፈቀድበት አይደለም። ያን ለማድረግ የሚያስችል ደግሞ ዓቅም አለን፤ እንደመንግሥት አቅሙን መመንዘር አያስፈልግም ብለን ተውነው እንጂ አቅሙን መመንዘር የሚያስችል በቂ አቅም አለን። ስለዚህ የሚዲያ ተቋማት በኃላፊነት በህግ አግባብ መስራታቸውን ማረጋገጥ ጠቃሚ ይሆናል።
ህግ አስከባሪ አካላት እስካሁን ብዙውን ነገር በትዕግስት እንዲያልፉ የሚፈለግበት ምክንያት በህግ አስከባሪ አካላትና በዜጎች መካከል የነበረው አይነት ቅራኔ እንዳይቀጥል ነው። ትርፍ ነገር ማድረግ አያስፈልግም ሰዎች በህግ አግባብ የሚጠየቁበትንና ህግ የሚከበርበትን መንገድ መከተል ያስፈልጋል። እንደው በአላፊ አግዳሚው እንደፈለጉት መቀጠል አይቻልም ። እኔም ትርፍ በሆነ መንገድ ያንኛውን መሳደብ የለብኝም፤ ያንኛውም ሌላውን መሳደብ የለበትም፤ ተከባብረን፣ ተደማምጠን በጋራ መኖር ያስፈልጋል።

ሀገር የእጅ አዙር ጦርነት አውድማ እንዳትሆን ትብብርን በማብዛት ፋክክርን መቀነስ ያስፈልጋል፤ ሁሉ ነገር በፋክክር ከሆነ ጥፋት ያመጣል። አብዛኛው ሰው ውስጥ ኃይለኛ ቁጣ ይፈጠራል፤ ኃይለኛ ቁጣ ውስጥ ሆነህ መረጋጋት አይቻልም። ቁጣን መጫን ያስፈልጋል፤ የምትቆጣበትን ምክንያት ማወቅ ያስፈልጋል፣ የሚያስቆጣ ነገር መኖሩን ማወቅ ያስፈልጋል፣ ዝም ብሎ ከፌስቡክም ከሌላም አይቶ ከመቆጣት ቁጣን መቆጣጠር ያስፈልጋል። እንደኛ ደግሞ የስልጣን ኃይል ያለው ሲሆንና ሲቆጣ

ጥፋቱ ከፍተኛ ስለሚሆን ቁጣን መቆጣጠር ያስፈልጋል ። በጠመንጃ ኃይል ስልጣን፣ በጠመንጃ ኃይል ፍላጎትን ማሳካት አይቻልም። በተደጋጋሚ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ግድያ እንፈጽማለን እያሉ ከአንዳንድ ኃይሎች ጋር እየተቀናጁ የሚገቡ ቀላል ቁጥር የሌላቸው ሰዎች አሉ። እያደንን ስለምንያዛቸው ነው። አሁንም በቅርቡ እንደዚህ አይነት ሙከራዎች አሉ፤ ሰው መግደል ኢህአፓ ሞክረው እኮ ደርግ ላይ አልሰራም፤ የእኛ ግን ይብሳል ጥሩ ስለማይሆን አስር ጊዜ ቆሞ ማሰብ ጥሩ ነው። ሰው ገድዬ፣ ሰው አሸማቅቄ፣ ዋሽቼ፣ ቀጥፌ የሚባል ነገር ቀርቶ ሃሳብ ይዤ፣ በሃሳብ አሳምኜ ይህን መንግሥት ልቀይር እችላለሁ ሊባል ይችላል። ለስልጣን ላለን ፍላጎት ሲባል ሰው እየበላን መሄድ ትክክል አይደለም። እንደ ማህበረሰብም ሰው ጠባሳውን አጠፋለሁ ብሎ ቆዳውን አይፍቅም፣ ጠባሳዎች እዚህም እዚያም አሉ። ጠባሳን ለመደበቅ ጠባሳን ለማጥፋት ይበልጥ ቆዳን የሚልጥ ሰው ይበልጥ ጠባሳ ያመጣል እንጂ ከነበረው ቁስል አይድንም።
ብዙ ጠባሳ ያለበት ብዙ ቁስል ያለበት ሀገር ተጨማሪ በጥልቀት እየቆፈሩ ቁስል ማብዛት ጥፋት ነው የሚያመጣው። እኛ እንደ መንግሥት እሳትን በእሳት፣ ውሃን በውሃ የሚል አቅጣጫ ብቻ አንከተልም። አንዳንዴ እሳትን እያዩ መሸሽ፣ አንዳንዴ ውሃን እያዩ ከፍታ ቦታ መያዝ፣ አንዳንዴ ውሃን መገደብ፣ አንዳንዴ እሳትን በውሃ ወይም አፈር ማልበስ ያጠፋው ይሆናል በማለት አማራጮችን ጉዳት ለመቀነስ መጠቀም እንዳለብን እናስባለን። እሳትን በእሳት ውሃን በውሃ የሚባል ከሆነ ጥፋቱ ብዙ ይሆናል። ለዛ ደግሞ በቂ ልምድ አለ ኢትዮጵያ ውስጥ። ስለ ሰላም ያለን ግንዛቤ አናሳ የሚሆንበት ምክንያት ችግርን በፌስቡክ ነው የምናውቀው፣ ጦርነትን በዩቲዩብ ነው የምናውቀው፣ ቀረብ ብለን አደጋውን ለማየት እድል አላገኘንም።

የአንዲት ጠብታ ውሃ ዋጋዋ የሚገባው በረሃ ውስጥ የውሃ ሽታ የናፈቀው ሰው ነው። በረሃ ውስጥ የሚንከራተት ወታደር፣ የሚንከራተት የረጅም ርቀት ነጋዴ ውሃ አጥቶ ጠብታ ውሃ እንኳን ቢያገኝ ዋጋ አለው። ውሃ ሲፈስ ለምናይ ሰዎች ብዙም ቦታ የለውም። የሞትን አስከፊነት የሞትን አደገኛ ህመም የሚያውቁ ሰዎች በሰላም አብረው እየተጓዙ ጓደኛቸው ከአጠገባቸው ሲቀር ያዩ፣ እህታቸው ወንድማቸው ቀርቶ ለመቅበር እንኳን የሚያግዛቸው ሰው ያጡ፣ የሰው ያለህ ሰው ሞቶብኝ ልቀብር አልቻልኩም የሚሉ ሰዎች፣ አብረው እየተጓዙ ከጎናቸው ወንድማቸው ሲወድቅ አፈር ለማልበስ እንኳን እድል አጥተው የሸሹ ሰዎች የሞትን ክፋት ያውቁታል። አሁን በፌስቡክ ስናይ ይቀላል፤ ቤታችን ሲመጣ ከባድ ነው ። የሰላምን ዋጋ በእጅጉ ተገንዝበን ለሰላም የማንሰራ ከሆነ ሁሉም ኃይል የልማት ኃይል የለውም ለጥፋት ግን ስላለው መጠፋፋት ይሆናል። ይህ እንዳያጋጥም በተቻለ አቅም እኛ እንደመንግሥት በትዕግስት፣ ሁሉንም በማድመጥ፣

ሁሉን በማቀራረብ ተረጋግቶ አሁን ካለበት ችግርና እሳቤ ብልሽት ወጥቶ ወደ ተሻለ ጉዳይ እንዲያመራ ጥረት እናደርጋለን።

አቅማችን በፈቀደ መጠን ለሁሉም እኩል አደራ እንዳለበት መንግሥት እናገለግላለን፤ እያንዳንዱም ቡድን ይሄን ተገንዝቦ መሄድ አለበት። ሲፈልግ መንግሥትን የሚቀርብ፣ ሲፈልግ የሚገፋ ሳይሆን ሁሉም ሐላፊነትና የሥራ ድርሻ እንዳለው አምኖ የሚሄድ መሆን አለበት። ይሄ ከሆነ አብዛኛው ችግር ይፈታል፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የገጠሙን ፈተናዎች ችግር ቢመስሉም ተምረንበት፣ በስለንበት፣ ልምድ አግኝተንበት እንደሀገር እንድንወጣ ብዙ እድል ያመጡ ናቸው፤ አሁንም ያሉት ፈተናዎች እንደዛ ናቸው። እያንዳንዱን ፈተና እንማርበታለን፣ ቆም ብለን ራሳችንን እንፈትሽበታለን፣ ችግሮቻችንን እናያለን ፣ መውጫ መንገድ እናያለን እንዲሁም እናድግበታለን።
የእኛ ቀዳሚው ፍላጎት ባቅማችን ልክ ማደግ ነው፤ መቆም አይደለም። በየቀኑ እንማራለን፣ እንመረምራለን፣ እንጠይቃለን በዚያ ውስጥ የሚገኝ እድገት ካለ እንቀጥላለን እንጂ ቆመን በተገኘ ድል የምንኩራራ፣ በተገኘ ችግር የምንፈራ ሰዎች አይደለንም። ያ ቢሆንማ እዚህ እንዴት እንደርሳለን። ችግርም አያቆመንም ድልም አያቆመንም፣ ከድላችን እንማራለን ከችግራችንም እንማራለን፣ እንመረምራለን፣ እናርቃለን፣ እናርማለን እንገሰግሳለን። በዚህ አግባብና እምነት ነው የምንሄደው።
የውስጥ ንጽህና ከሌለ፣ ውስጥ የሃሳብ ችግር ካለ ግን ውጥንቅጥ ነው፤ ብዙ ጉዳይ ይበላሻል። እናም አብዛኞች በአጠረ መንገድ ፍላጎት፣ ጉጉት አለ፣ መሻት አለ። መሻት ጥሩ ነው፣ ለመሻት ደግሞ ትክክለኛ የሆነ እቅድ ለዚያ ደግሞ መሰጠትና ሥራ ይፈልጋል። እንደው አንድ ጊዜ መንግሥት ገልብጠህ ማታ በህልምህ አይተህ ሰውና ሰው አጋጭተህ መንግሥት ሆነህ እንደዛ አይሆንም።

ከፍተኛ ህዝባዊ መሰረት ያለው፣ ከፍተኛ አቅም እየፈጠረ ያለ ኃይል ነው። እናም በዚህ መንገድ የሚያስቡ ኃይሎች ቆም ብለው በማሰብ በንግግር፣ በምክክር በማድረግ ጅምራችንን ጭላንጭል የዴሞክራሲና አብሮ የመስራት ነገር ማስፋት ይገባል። አሁን እኮ ፕሮፌሰር ብርሀኑ አለ፣ ዶ/ር በለጠ አለ፣ አቶ ቀጀላ አሉ በሚቀጥለው አስርና አሥራ አምስት ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ይሄ ጥሩ ልምድ ነው፤ የሀገርን ኢኮኖሚ፣ የሀገርን ሰላም በጋራ የምናይበት ዐውድ ፈጥረን አብረን መምራት ከተለማመድን እየሰፋ ከሄደ ቀላል ነው።

በእርግጠኝነት አቶ ቀጀላና ዶ/ር በለጠ ይሄ ነገር ተፈጥሮ እንደዚህ አብራችሁ መስራት ከመጀመራችሁ በፊት አብን ሲባልና ኦነግ ሲባል መቸም የምታስቡትን ነገር አስቡት። ሰው ሲቀራረብ፣ ሲወያይ በንግግር ሲያምን፣ ሃሳብ ሲለዋወጥ ብዙ ነገር ይማማራል፣ ኢንፈሎዌንስ ይደራረጋል። ለንግግር በር መክፈት አለብን፣ ሁልጊዜ ለግጭት መሆን የለበትም፣ ለይቅርታም ልባችን ክፍት መሆን አለበት፤ ለመተው፣ አንዳንዴ ተሸንፈን ብዙዎችን ለማሻገርም፣ ዝቅ ብለን ብዙዎችን ከፍ ለማድረግም የምናስብና የምንሰራ ካልሆንን በስተቀር በሁሉም ጉዳይ እኔ የማስበውና እኔ የምለው ብቻ ካልን አደገኛ ነገር ነው። እናም ኢትዮጵያን የመሰለ ትልቅ ሀገር፣ ብዙ ህዝብ ያለበት ሀገር እንድንመራ እድል ስናገኝ ብዙ ትዕግስት፣ ብዙ ማስተዋል፣ ብዙ መማር፣ ብዙ መጠየቅ፣ ብዙ ራስን መፈተሽና ብዙ እያሻሻሉና እያረሙ መሄድ የሚጠይቅ ሥራ ስለሆነ አሁን ያለውንም ችግር በዚሁ አግባብ እያየን መፍትሄ እያበጀን እንሄዳለን ለማለት ነው።

**ጥር 24 ቀን 2015 ዓ.ም**

**ሃላላ ኬላ**



# የስንዴ ኤክስፖርት ማስጀመሪያ ሥነሥርዓት

የካቲት 5 ቀን 2015 ዓ.ም

ዛሬ ባሌ ላይ ያየነው ስንዴን ኤክስፖርት ለማድረግ የማስጀመሪያው ሂደት ለኢትዮጵያ ከሚገባትና ማድረግ ከሚገባን ትንሹ ደረጃ ነው። መላው የኢትዮጵያ ህዝብ መገንዘብ ያለበት እኛ የምናልም ያለምነውን የምንናገር፣ ለተናገርነው ጉዳይ ቀን ከሌት የምንሠራ፣ የሠራነውንም ፈጽመን የምናሳይ እንጂ እንዲሁ የምንቃዥ ሰዎች አይደለንም። ከጅምሩ እናልማለን፣ ይህም በቅጡ እንናገራለን፣ ለዚያም ተግተን ፣ አሳክተን እኛም ዓለምም በጋራ ማየት እንድንችል እናደርጋለን፤ በብዙ ጅምሮቻችን ላይ ይህንን ለኢትዮጵያ ህዝብ በተግባር ማሳየት ተችሏል። ነገር ግን የአረንጓዴ አሻራ ስንል፣ ህዳሴን እንጨርሳለን ስንል፣ ፕሮጀክቶችን እንጨርሳለን ስንል ከነበረው ፈተና በላይ ስንዴ ከእንግዲህ ወዲያ ኢትዮጵያ ከውጭ አታስገባም የሚለው ራዕይ ለብዙዎች በቀላሉ የሚቀበሉትና የሚዋጥላቸው አልነበረም። ደግሞ ኢትዮጵያ ከልመና ወጥታ፣ ገዝታ አስገብታ ከመብላት ወጥታ፣ እርሳ ራሷን አብልታ፣ ከዛም አልፋ ወደ ውጭ መላክ ይቻላታል የሚለው በህዝባችን ብቻ ሳይሆን በርከት ያሉ አመራሮች ይህን ሃሳብ ተጋርተው ለመስራት ተቸግረው ነበር።

ነገር ግን በእርሻ የማናውቀው ሶማሌ ክልል ሳይቀር ለማመን በሚቸግር ሁኔታ ስንዴን በዘመናዊ መንገድ ማረስ፣ ማምረትና ለመብላት ብቻ ሳይሆን ለመሸጥም የሚያበቃ ምርት ማየት እንድንችል አድርገዋል። በአማራ ክልል በግብርና ዘርፍ እጅግ አስደናቂ ውጤት መጥቷል። የክረምቱን ትተን በዚህ በጋ ብቻ ከሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ ሄክታር በላይ ስንዴ ዘርተዋል። በኦሮሚያም፣ በደቡብም የታየው ይህ አስደናቂ ውጤት መላውን የኢትዮጵያ ህዝብ አጥግቦ ከእኛም አልፎ ለጎረቤቶቻችን ተሸጦ ከዛም አልፎ ቀደም ሲል እንዳስቀመጥነው ከኢትዮጵያ የተለገሰ (Ethiopian Aid) ብለን ለተቸገሩት ለመርዳት የሚያስችል የተሟላ አቅም ኢትዮጵያ አላት። ተግተን ብንሰራ የምንፈታው የሚጨበጥ ችግር በእኛ መፍትሄ ደግሞ የብዙ ሰዎች ህይወት ከአደጋና ከሞት ሊድን ይችላል ፤ ይህ አንድ ጉዳይ ነው። በሌላ መንገድ እኛ ተናግረን ሠርተን ከማሳ ወጥተን ለሌሎች ተቋማት የሚሸጥ ስንዴ ለማየት ስለበቃን መከናወን ሁሌም የሚሰጠው ከፈጣሪ ስለሆን የረዳንን ፈጣሪ እጅግ አድርገን እናመሰግናለን።

ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ በየእለቱ የሚሰሙ አሳዛኝ ዜናዎች ከግራም ከቀኝም ያሉ ቢሆንም ኢትዮጵያዊያን መበልጸግ ስለምንፈልግ ዐይናችንን ከሰላም፣ ከልማትና ከብልጽግና ሳናነሳ በወንድማማች ስሜት ተደማምጠን ተከባብረን የአንደኛውን መሻት አንደኛው እያደመጠና እየተወያየን የበለጸገች ለራሷ የምትበቃና ለሌሎች የምትተርፍ ሀገር መፍጠር አለብን። ችግር ኮሽ ባለ ቁጥር የምናኮርፍ ሳይሆን ለምን ተፈጠረ ብለን አስተውለን፤ በጽሞና ገምግመን፤ ለምን ተፈጠረ ብለን መፍትሄ ለማምጣት የምንተጋ መሆን አለብን። ከየትም ቦታ አንድ ድርጊት ሲከወን ለዚያ ምላሽ ለመስጠት የምንሮጥ መሆን የለብንም።

ድርጊትና ለድርጊት የሚሰጥ ግብረ መልስ ለየቅል ነው ፤ ድርጊት ታስቦ ታቅዶ ለሆነ ዓላማ የሚፈጸም ተግባር ነው፤ ግብረመልስ ግን ግብታዊ ነው። ድንገቴ ነው፣ ድንገቴ ስለሆነም ሎጂክ ይስታል፣ እውነትን ያዛባል፣ ጥፋትን ያመጣል። እኛ ግብረመልስ የምንሰጥ ሳይሆን አስበን አልመን የምንፈልገውን ነገር የምንፈጽም መሆን አለብን። ይህንን ስናደርግ በስንዴ ኤክስፖርት፣ በአረንጓዴ አሻራና በመሰረተ ልማት ስራዎች የጀመርናቸው ስራዎች ተሰናስለው ውጤት እያመጡ የበለጸገች ያደገች ኢትዮጵያን እንፈጥራለን።

ልክ እንደ ስንዴው የኢትዮጵያ መንግሥት ፍላጎት በቀደመው መንግሥት የተጫነባትን ከፍተኛ እዳ ማቃለል ነው። ትልቁ የዚህ መንግሥት ህልም በምግብ ራስን መቻል፣ በርከት ላለ ሰው ሥራ መፍጠርና የተሻለ የአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት (GDP) ማምጣት ብቻ ሳይሆን የእዳ ቀንበር ያጎበጣትን ኢትዮጵያን እዳዋን ማቅለል ነው። ከዚህ ቀደም በብዙ መስክ ተናግረን እንዳከናወንነው ሁሉ የኢትዮጵያን እዳ እናቃልላለን፣ ኤክስፖርቷን እናሳልጣለን፣ አንድ የሆነች የምትዋደድ፣ የምተከባበር፣ ትውልድ አርቆ የሚያይባት ኢትዮጵያን እንሰራለን። ለዚህ ቅዱስ ዓላማ አንተኛም፣ ለዚህ ቅዱስ ዓላማ ስኬት ፈጣሪያችንና ህዝባችን ከጎናችን ይሆናሉ። ዛሬም እንደትናንቱ ላረጋግጥላችሁ የምፈልገው ኢትዮጵያ አትፈርስም፣ ኢትዮጵያ አትለያይም፣ ኢትዮጵያ ያሰበችውን ከማሳካት ማንም አያቆማትም።

ለዚያ በቂ ዝግጅት ያደረግን በብዙ ችግር ውስጥ የተማርን ስለሆንን ግራ ቀኝ በሚሰሙ ነገሮች ሳትናወጡ ዐይናችሁን ከልማት ሳታነሱ፣ ዐይናችሁን ከኢትዮጵያ ሳታነሱ፣ ከወንድም ህዝቦች ጋር በጋራ ለመኖር፣ ለመተጋገዝ ምናልባት የከፋቸው ወገኖች፣ ቡድኖች፣ ግለሰቦች ካሉም ለማድመጥና ለማገዝ ቀና ልብ እንዲኖረን መንገድ

እንዳትስቱ፤ መንገዳችን ልማት ነው፣ ብልጽግና ነው፣ አንድነት ነው፣ መንገዳችን አንዷት ኢትዮጵያ ናት ከዚህ የሚያዛንፍ ኃይል ሲመጣ መፍቀድ የለብንም።

በጋራ የበለጸገች ኢትዮጵያን ማየት እንድንችል በሌሎች ዞኖችም መሰል ሥራዎች ተከናውነው ማየት እንድንችል ከሁሉ በላይ የሰከነ የተረጋጋ ከህልሙ የማይዛነፍ፣ የሚያልመውን የሚናገር፣ የሚናገረውን ተግቶ የሚከውን ሰዎች ያድርገን። በእኛ በኩል የበለጸገች ያደገችና አንድ የሆነች ኢትዮጵያን ለልጆቻችን እናሸጋግራለን። ይህን መለወጥ የሚችል ኃይል በምድር ላይ የለም።

**አመሰግናለሁ።**

**የካቲት 5 ቀን 2015 ዓ.ም**
**ባሌ ዞን**


MINISTRY
ATION

# በ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተና ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች የሽልማት መርሃግብር

የካቲት 22 ቀን 2015 ዓ.ም

**ክቡር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ፣**
**ክቡራን ሚኒስትሮች፣**
**እንዲሁም ለዚህች ድንቅ ቀን የበቃችሁ ተማሪዎች፤**

ከሁሉ አስቀድሜ እንኳን ደስ ያላችሁ ልላችሁ እወዳለሁ። ዛሬ እዚህ ለመገኘት ያስብኩበት ዋናው ምክንያት በርከት ያሉ ተማሪዎችን አስተምረንና አስፈትነን ከእነሱ መካከል እናንተ ላቅ ያላችሁ አድማጨችና አስቀማጨች መሆን ስለቻላችሁ ነው። ላቅ ያለ አድማጭና አስቀማጭ ማለት ላለፉት ሦስትና አራት ዓመታት መምህራኖቻችሁ የነገሯችሁን መረጃ በትክክል ያዳመጣችሁና ያስቀመጣችሁ፣ ስትጠየቁም ካስቀመጣችሁበት በማውጣት በትክክል ማሳየት ስለቻላችሁ ብቻ ማለት ነው። ይህ ምን ማለት ነው መረጃ መሰብሰብ የቻላችሁ ወደ እውቀት ለመቀየር ገና ብዙ ይቀራችኋል ማለት ነው። እስካሁን ያሳያችሁን ብቃት አንደኛ ትኩረት ማድረግ መቻላችሁን ፣ አሁን የምትኖሩ መሆናችሁን፣ ክፍል ውስጥ ስትሆኑ ክፍል ውስጥ መሆናችሁን፣ መጽሐፍ ስታነቡ ከመጽሐፉ ጋር ብቻ የምትነጋገሩ የማትረበሹ ሰዎች መሆናችሁን አሳይታችኋል። ትኩረት ማድረግ መቻላችሁን መረጃ ለመሰብሰብ ብቻ ሳይሆን ነገ እውቀት ለማድረግ ከዚያም አልፎ የጥበብ ባለቤት ለመሆን ትኩረት ማድረግ አስፈላጊ ነው። እስካሁን ያየነው ትኩረት ማድረግ መቻላቸሁን እና መረጃን በትክክል በቦታው ላይ ማስቀመጥ የምትችሉ ስትጠየቁም mind maping ብቃት ያላችሁ ለጠያቂዎቻችሁ ካስቀመጣችሁበት አውጥታችሁ ምላሽ መስጠት የቻላችሁ በመሆናችሁ ባለፉት ሦስትና አራት ዓመታት በርካታ ዳታዎችን ሰብስባችኋል። እነዚያ ዳታዎች ተሰብስበው ኢንፎርሜሽን ይሆናሉ ኢንፎርሜሽንን ወደ እውቀት ለመቀየር ግን ሰፊ የሆነ ጥረትና ሥራ ይፈልጋል።

ኢንፎርሜሽንን ወደ እውቀት መቀየር ወደሚቀጥለው ደረጃ የሚደረገውን ጉዞ የቀለለ ያደርገዋል። ማልኮም ኤክስ የተባለው በአሜሪካ ለጥቁሮች መብት በመታገል የሚታወቀው አክቲቪስት ትምህርትንና እውቀትን የመኀኀዣ ፓስፖርት ነው ይለዋል። እናንተ ወደሚቀጥለው ደረጃ ለመኀዝ ፓስፖርት አግኝታችኋል። ህጋዊ የሆነ ፓስፖርት

መያዝ የቻላችሁ ሰዎች ስትሆኑ እውቀትን ለማደራጀት ግን ከዚህ ቀደም ስታደርጉት እንደነበረው ገና በርከት ያለ ሥራ ይጠበቅባችኋል ማለት ነው። የኔ ምክር እውቀትን ብቻ ሳይሆን አብዝታችሁ ጥበብን እና እውነትን የምትፈልጉ እንድትሆኑ ነው።

ሁለት መቶ ሰባ ሶስት ትኩረት ያላቸው አላማቸውን የሚያውቁ ተማሪዎች አሉን። እነዚህ ተማሪዎች ጥበብን እና እውነትን አብዝተው የሚፈልጉ ከሆነ የነገይቱ ኢትዮጵያ ተስፋ አላት ማለት ነው። ሁለት መቶ ሰባ ኢትዮጵያውያን ኢንጂኒየር ማድረግ የሚችል መሃንዲስ ሆኖ በራሱ ፍላጎት እና መሻት መስራት የሚችል ብዙ ሳይንቲስት ብዙ ሃኪም፣ ብዙ ተመራማሪ መፍጠር የሚችል ጉልበት እናንተ ውስጥ አለ ማለት ነው።

ጥበብን አብዝቶ መፈለግ የግራ እና የቀኝ ጭንቅላታችሁን በእኩል መጠቀም ይጠይቃል ፤ እስካሁን የቆያችሁበት የትምህርት ስርዓት የግራ ጭንቅላታችሁን በብቃት መጠቀማችሁን የሚያሳይ እንጂ ዋናውን የእውቀት ቋት የሆነውን ቀኝ ጭንቅላታችሁን መጠቀማችሁን አያሳይም ። የግራ ጭንቅላት ማለት ነገሮችን በምክንያት መረዳት (logical thinking ) ማለት ነው የቀኝ ጭንቅላት ነገሮችን በምናብ ማየት ( visualize) ማድረግ መቻል ወይም imagenetion የሌለን ነገር ከማይታይ ነገር መካከል አውጥቶ ማየት ማለት ነው። ተስፈኛ ማለት ተስፋ ባለበት ጊዜ ሳይሆን የተስፋ ጭላንጭል በሌለበት ጊዜ ማለት እንደሆነው ሁሉ ፤ የቀኝ ጭንቅላትን የሚጠቀሙ ጥቂት ሰዎች የሌለን ነገር የማየት እና ያን ያዩትን ለማሳየት የሚተጉ ናቸው። እንደዚያ ለመሆን ጥበብን አብዝታችሁ የምትፈልጉ መሆን አለባችሁ፤ ጥበብ በፊዚክስ ብቻ ሳይሆን በሜታፊዚክስ የሚገኝ ነው። ሜታፊዚክስ ከቁስ ባሻገር የሆኑ ነገሮችን ማየት መቻል ማለት ነው ።

ከተጻፉት ያነበብነውና ስንማር ያዳመጥናቸው ነገሮች ወደ ሜታፊዚክስ ወደማይታይ ወደማይዳሰሱ እውቀቶች የማይወስዱን ከሆነ ምናልባት በህልም ዓለም የምንኖር ሰርቲፊኬት የደረደርን እንጂ ህልማችንን የምንኖር ሰዎች አያደርገንም። ሜታፊዚክስን ታዋቂው አማኑኤል ካንት « A Dark Ocean without a Shore»ይለዋል፡፡ አንደኛ ጨለማ ነው፣ ሁለተኛ ጠል መሬት የለውም ። ውቂያኖሱ ጨለማ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በቁስ ማንነታችሁ ቁማችሁ ለማየት ከዚያ ውስጥ ያለን እውቀትና ብቃት ለማውጣት አያስችልም። አንደኛ ጨለማ ነው፣ ሁለተኛ መቆሚያ ምድር የለውም ። ይህ ማለት በምናብ መጓዝን ይጠይቃል ማለት ነው።

በአካል ተጉዘን የምንቆምበት ጠል መሬት ስለሌለው በምናብ ተጉዘን ከማይታዩ ነገሮች የሚታዩ ነገሮችን ማውጣት የሚጠይቅ የትምህርት፣ የእውቀት፣ የማስተዋል የማሰላሰል የማሰብ ዘርፍ ነው።

ከአማኑኤል ካንት በተጨማሪ ዊሊያም ጀምስ የተባለው ታዋቂው ፈላስፋ ሜታፊዚክስን <<Unusual way of thinking>> በተለምዶ ማሰብ ሳይሆን ወጣ ያሉ እሳቤዎች፣ ወጣ ያሉ የማሰቢያ መንገዶች መፍጠሪያ አቅም ነው ይለዋል። በሜታፊዚክስ የደረጀ እውቀት ያላችሁ እንደሆነ ከማይታይ ነገር እውቀት መፍጠር ትችላላችሁ ማለት ነው። ወደዚያ አይነት የእውቀት ዘርፍ ዝንባሌያችሁን ማሳደግ፣ የኢማጅነሪ አቅማችሁን ማሳደግ፣ የቀኝ አእምሯችሁን አቅም ማሳደግና መጠቀም መቻል፣ ሰብ ኮንሸስ (sub-conscious) የሆነውን የአእምሯችሁን ክፍል በተሻለ መጠን መፈተሽና መበርበር ይኖርባችኋል። ያ ከሆነ ወደ ጥበብ ትቀርባላችሁ፣ ወደ ጥበብ ከቀረባችሁ ደግሞ ዓለም ባይረዳችሁም የእናንተ ጥበብ ለዓለም ይተርፋል። ብዙዎች ጥበበኞች እነሱ ለዓለም ተረፉ እንጂ ዓለም እነሱን አልተረዳቸውም። ዓለም የሚረዳቸው በግራ ጭንቅላት በኮንሸስ ኖውሌጅ (conscious knowledge) ነው። እሱን የሚረማመዱት በቀኝ አእምሯቸው ጥበብ በተሞላው ማንነታቸው በሚሆንበት ሰዓት ተራ ተርታው ህዝብ አይረዳቸውም።

ትውልድ ግን ከእነሱ የጥበብ ምንጭ ከተቀዳው ፍሬ ተጠቃሚ ይሆናል። በዚያ መንገድ ጥበብን የምትፈልጉ መሆን አለባችሁ።

ሁለተኛው እውነት ነው። እውነትን አብዝቶ የፈለገ ሰው ውስጣዊ ሰላም ይኖረዋል፣ ተኝቶ ያድራል። አሁን ባለው ትውልድ ውስጥ ኢትዮጵያ ውስጥ እውነትን መፈለግ ሳይሆን ለውሸት የዳቦ ስም ሰጥቶ ውሸትን እውነት የመሰለች አስመስሎ ውስጣችን እያወቀም ቢሆን መከተል ነው። ይህ መዳርሻው ጥፋት ነው። እውነትን የምትፈልጉ እውነትን በእውነትና በማስረጃ በአመክንዮ የምታምኑ ከሆናችሁ የጥበብ መንገዳችሁ ቀላል ይሆናል። ሁለቱን ነገር ማሳካት ስትችሉ እናንተ የነገይቱ ኢትዮጵያ መሃንዲሶች ትሆናላችሁ። መሃንዲስ ማለት በግንባታ ዘርፍ የተሰማራ ማለት ሳይሆን የኢትዮጵያን እጣ ፈንታ የሚወስን፣ ኢንጂነር የሚያደርግ፣ ጥቂት ግን ብዙ ከውስጣችሁ የሚፈልቅ ሰዎች ትሆናላችሁ። ያን ለማድረግ ከፊታችሁ ብዙ ትግል እንዳለ፣ መድከም እንደሚጠይቅ፣ ከዓለም ተነጥሎ ጥበብን መፈለግ እንዲሁ በዋዛ የሚገኝ ነገር እንዳልሆነ እያሰባችሁ እንድትሰሩ አደራ ልላችሁና ላሳስባችሁ እወዳለሁ።

ሁለተኛው መልዕክቴ ትውልድን በወጉ መገንዘብ የምንችል እንሁን። ትውልድ በሦስት ጎራ ይከፈላል እየሄደ ያለው፣ እየጨረሰ ያለውና ኤግዚት (Exit) የሚያደረገው ትውልድ አለ። አሁን ያለ አሁን ባለው አውድ ውስጥ የሚሰራ አግዚስት (Exist) የሚያደርግ ትውልድ አለ፣ የሚመጣ ከኋላ ያለ ኢመርጅ (Emrege) የሚያደርግ ትውልድ አለ። የሄደው ኤግዚት ያደረገ ትውልድ ማለት ጎረቤት የደረሰ የአባይ ውሃ ማለት ነው። ጎረቤት ሀገር የደረሰ የኣባይ ውሃ ሰውም ይዞ ይሂድ፣ አፈርም ይዞ ይሂድ፣ ግንድም ይዞ ይሂድ ከንፈር ከመምጠጥ ያለፈ ምንም ማድረግ አይቻልም።
ጎረቤት ሀገር የደረሰን የአባይ ውሃ መማሪያ ብቻ ነው ማድረግ የሚቻለው፤ እንዴት አድርግን ሰውን፣ አፈርን፣ ዛፍን ይዞ እንዳይሄድ ማድረግ እንችላለን ከሚል ትምህርት ከመቅሰም ያለፈ ከካርቱም መልሰን መጠቀም አንችልም።

ሁለተኛው አሁን ያለ ትውልድ ማለት በህዳሴ ግድብ ውስጥ ያለ ውሃ ማላት ነው ፤ በህዳሴ ግድብ ውስጥ ያለ ውሃ ሁለት እድል አለው። አንደኛው ተርባይን መቶ ኢነርጂ ፈጥሮ ተፈጥሯዊ ፍሰቱን እንዲሄድ ማድረግ ነው። ሁለተኛው ግን ተርባይን እንዲመታ ዝግጅት ፣ የምንሞላበትም መሻት ከሌለ የታችኛው ማስተንፈሻ በሚባለው መውጫ ምንም ሥራ ሳይሰራ ወደሚቀጥለው ሀገር እንዲጓዝ ማድረግ ነው፤ ወይም በተርባይን ወይንም በማስተንፈሻው ይወጣል። ይህን የሚወስነው ግድቡን ኦፕሬት የሚያደርግ ሰውየ ነው። ውሃው በእጁ ስላለ ወይ ኃይል ያመነጭበታል ወይንም እንዲሁ ያፈሰዋል። ገና የሚመጣው ትውልድ ማለትስ፤ ከምንጩ ከጣና ያልተነሳ ውሃ ማለት ነው። ከጣና ያልተነሳን ውሃ ግድቡ ውስጥ ካለው ውሃ የሚለየው ምንድን ነው? ፍጥነቱን ለመወሰን ምን እንሥራ፣ በየት በየት በኩል አልፎ ግድባችን ጋ ይድረስ፣ ምን ቁም ነገር እየሰራ እዚህ ቦታ ይድረስ የሚለውን ለመወሰን ሁሉ እድል የሚሰጥ ነው።

አሁን እናንተ የምትመደቡት ከጣና ከምንጩ ያልተነሳ የአባይ ውሃ ተደርጋችሁ ትወሰዳላችሁ፣ በትክክል ከተዘራባችሁ እናንተም የተዘራባችሁን በትክክል ካበቀላችሁ እንዲሁ ግንድና አፈር ይዞ የሚጓዝ ወንዝ ሳይሆን ለሀገሬው ለህዝብ ቁምነገር ጠቀሜታ መስጠት የምትችሉ ወንዝ መሆን ትችላላችሁ ። ጠቀሜታ ለመስጠት ራሳችሁን ማሸነፍ ያስፈልጋል፣ ጠቀሜታ ለመስጠት በትህትና መሞላት ያስፈልጋል፣ ጠቀሜታ ለመስጠት ከሰፈር ባሻገር ማሰብ ይጠይቃል፤ እናንተ ዩኒቨርሲቲ እየገባችሁ ነው። ዩኒቨርሳል ሰዎች ናችሁ ዩኒቨርሳል እሳቤ ያስፈልጋችኋል ፣ ከሰፈር ባሻገር የምታስቡ መሆን አለባችሁ። ይህንን ካደረጋችሁ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለዓላም የምትጠቅሙ ትሆናላችሁ ።

ኢትዮጵያ ውስጥ ጥቂትም ቢሆኑ ስመጥር ሰዎች ነበሩ፤ ለምሳሌ በሳይንሱ ዘርፍ ቢያንስ ዶ/ር አክሊሉ ለማን መጥራት እንችላለን። ከእናንተ ውስጥ በርከት ያለ አክሊሉ ለማ እንዲወጣ ህዝባችንና መንግሥታችን ይመኛል። ከእናንተ ውስጥ በርከት ያሉ ሐኪም ወርቅነህ እንዲወጡ መንግሥታችን ይመኛል፣ ወላጆቻችሁ ይመኛሉ፣ መምህራኖቻችሁ ይመኛሉ። ከእናንተ ውስጥ በርከት ያለ ጸጋዬ ገብረመድህንን እንድትሆኑ እንመኛለን። ጥብብን የምትጠሩ፣ በጥበብ መንገድ እውቀትን የምትዘሩ እንድትሆኑ እንመኛለን። ከእናንተ ውስጥ ጥቂቶቹ ነጋድራስ ባይከዳኝን እንድትሆኑ ፈላስፋ እንድትሆኑ እንመኛለን፣ እንጠብቃለን፣ ከእናንተ ውስጥ ጥቂት የማይባሉት ከበደ ሚካኤልን ወይም ተክለሃዋርያትን ተክለማርያምን ሆነው ዘመናዊት ኢትዮጵያን የሚመኙ እንዲሆኑ እንፈልጋለን፣ እንመኛለን።

እነዚህ አባቶቻችንን የመሳሰሉ ከነሱም የላቁ እንደሚወጡ ተስፋ እናደርጋለን ። ሁለት መቶ ሰባ ሶስት ተማሪዎች ብዙ መቶ ሺህ አስፈትነን በጣም ልዩ የሆነ መረጃ የማከማቸት ብቃት አሳይተዋል ብዬ ለአንድ ወዳጄ ነገርኩት። ያ ወዳጄ ሼ ሙሃመድ ቢን ዛይድ ይባላል፣ የዩናይትድ አረብ ኢመሬት ፕሬዘዳንት ነው። ለሁለት መቶ ሰባ ሶስቱም ታታሪዎች ሙሉ የትምህርት እድል ሰጥቷቸዋል። ለኢትዮጵያ፣ ለአፍሪካ፣ ለዓለም ሁሉ የምትተርፉ ቅኖች፣ ደጋጎች፣ አስተዋዮች፣ በትህትን የተሞላችሁ፣ ታላቅን የምታከብሩ፣ መነሻችሁን የማትረሱ ትሁታን እንድትሆኑ አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ። በአዲስ ድል በአዲስ ተስፋ እንደምንገናኝ ያለኝን ተስፋ እየገለጽኩ አመሰግናለሁ።

በቅርቡ የመደመር ትውልድ የተባለው አዲሱ መጽሐፍ በሚቀጥሉት ሁለት ሦስት ሳምንታት ይመረቃል። በአማርኛ፣ በኦሮምኛና በእንግሊዘኛ የተዘጋጀ ነው። በከፍተኛ ደረጃ ትወልድ እንዴት መሰራት እንዳለበትና የትውልድ ስብራትን ያሳያል። እናንተ ተማሪዎች ስለሆናችሁ እኔ ገዝቼ በፕሮፌሰር ብርሃኑ በኩል እልክላችኋለሁ፣ እንድታነቡ አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ። መልካም የትምህርት ጊዜ እንዲሆንላችሁ እመኛለሁ፥ እስከምትሄዱ ባላችሁ ጊዜ የቋንቋ ችሎታችሁን ለማሻሻል ራሳችሁን እንድታዘጋጁ አደራ እያልኩ መልካም ጊዜ ይሁንላችሁ፤ አመሰግናለሁ።

የካቲት 22 ቀን 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ





# የታክስና የጉምሩክ ሕግ ተገዥነት ሀገራዊ ንቅናቄ ማስጀመሪያ ዝግጅት

የካቲት 24 ቀን 2015 ዓ.ም

ዛሬ ግጥምጥሞሹ <<ግብር ለሀገር ክብር>> በሚል መሪ ቃል የሚደረገውን ይህንን ድንቅ ፕሮግራም ስንካፈል ጠዋት የአድዋ ድል መታሰቢያ የሆነውን ቀን አክብረን በመሆኑ ግብር ለክብር የሚለውን በቀጥታ ከአድዋ ጋር አቆራኝቶ ማየት የሚጠቅም ይመስለኛል። አድዋ ለአፍሪካና ለጥቁር ህዝቦች በሙሉ ክብር ነው፣ የነጻነት ቀንዲል ነው፣ በአድዋ ኢትዮጵያዊያን አብዝተን ልንኮራ ይገባል። አፍሪካዊያን እንዲኮሩበት የአድዋን ምስጢር ማሳየት ማስገንዘብ ያስፈልጋል። አድዋ የኢትዮጵያዊያን ብቻ ሳይሆን የሁሉም የጥቁር ህዝቦች ድል ስለሆነ በዚያ ልክና መጠን ማክበርና ማስታወስ ለሁላችንም ጠቃሚ ይሆናል።

አድዋ ክብር ነው፣ አድዋ ነጻነት ነው ስንል የዛሬ አንድ መቶ ሃያ ምናምን ዓመታት አፍሪካን የገጠማትን ፈተና፣ የጥቁር ህዝቦች የገጠመንን ፈተና የኢትዮጵያ ህዝብ ከጫፍ ጫፍ ተሰናስሎ አንድ ሆኖ አልገዛም፣ አልምበረከክም ብሎ ግማሽ ማንነቱን ያሳየበት እለት በመሆኑ ነው። ኢትዮጵያ ለመበልጸግ አቋሟና አቅሟ መፈተሽ አለበት፤ አቋሟን በሚመለከት በአድዋ፣ በማይጨው፣ በካራማራ እና በባድመ በተደጋጋሚ ተፈትና አቋሟ የማይናወጥ መሆኑን አሳይታለች። አቋማችን ነጻነት ነው፣ አቋማችን እኩልነት ነው፣ አቋማችን ህብረብሔራዊት ኢትዮጵያን መገንባት ላይ ነው። አሁን ፈተና ላይ ያለው አቅማችንን መገንባት ላይ ነው።

አቅማችን የሰው ኃይላችን ፣ አቅማችን ሊታረስ ሊለማ የሚችል መሬታችን ፣ ውሃን ፣ መልካምድራችን ሆኖ ሳለ ይህንን አቅም አውጥተን ደምረን ተጠቅመን ክብር ብቻ ሳይሆን የተሟላ ነጻነት ማምጣት ላይ የተፈተነች ሀገር ናት ኢትዮጵያ ። አቋሟን ለመቶ ዓመታት ያሳየች ሀገር ብትሆንም አቅሟን ለማሳየት ግን አሁን ላይ የምታደርገው ጥረት በብዙ ፈተና፣ በብዙ ችግር የተሞላ ነው። ሁላችሁም እንደምታውቁት ኢትዮጵያ የእዳ ቀንበር ያጎበጣት ሀገር ነች፤ የተቀበልናት ኢትዮጵያ ስልሳ በመቶ አጠቃላይ ሀገራዊ ምርቷ (GDP) እዳ ነው። እዳ ብቻ ሳይሆን ደግሞ ኮሜርሺያል የሚባለው እዳ የተከማቸባት ሀገር ናት። እዳዋን ማቅለል የተሟላ ነጻነት ለማግኘት ያግዛል፣ ከዚያም ባሻገር በየዓመቱ

ለልማት ለሥራ የሚውልን በጀት በውስጥ አቅም ማሟላት ስለማትችል ለበጀቷ ብድርና ርዳታ የምትለምን ሀገር ነች። ለበጀቷ ብድርና እርዳታ የምትለምን ሀገር፣ እዳዋን በበቂ ደረጃ ማቅለል ያልቻለች ሀገር በጦርነት ታሪኳ የተከበረች ብትሆንም በብልጽግና አቅሟ የተሟላ ነጻነት ያላት መሆን አትችልም።

አንድ ሰው አጥንትና ስጋ እንደማንኛችንም ኖሮት በየቀኑ ግን ለመራመድ ከወንድሙ፣ ከእናቱ፣ ከጎረቤቱ ደም እየለመነ የሚኖር ቢሆን ለአንድ ሳምንት ወይም ለአንድ ወር በታመመ ጊዜ የዘመዱን ደም እየተጠቀመ ይኖር ይሆናል እንጂ ሰው ተወልዶ ሙሉ ህይወቱን ኖሮ እስኪሞት ስጋና አጥንት ተሸክሞ ከሰው ደም እየወሰደ መኖር አይችልም። ሰው በተሟላ መንገድ እየተንቀሳቀሰ መኖር እንዲችል አጥንትና ስጋ ብቻ ሳይሆን ደም ያስፈልገዋል። ኢትዮጵያ የተሟላ ነጻነት እንዲኖራት እዳዋን ማቅለል ብቻ ሳይሆን የራሷን ወጭ በራሷ አቅም መሸፈን መቻል አለባት። በአቋማችን ያሳየነውን ኢትዮጵያዊነት በአቅማችን ለመድገም  የምንዘጋጅበት ጊዜ መሆን ይኖርበታል። ሁላችሁም እንደምታውቁት ኢትዮጵያ ስትነካና ስትደፈር ደረቱን ግንባሩን ለጥይት ለመስጠት የተዘጋጀ በሚሊየን የሚቆጠሩ ዜጎች ያሏት ሀገር ናት፤ አትንኩኝ ባይ የሆነ ሲነካ ለነጻነቱና ለክብሩ  ህይወቱን ሊሰዋ ዝግጁ የሆነ በሚሊየን የሚቆጠር ዜጋ ያላት ሀገር ናት። ይህች ሀገር እውቀቱንም ሳይሰስት የሚሰጥ ምሁር ትፈልጋለች። የኢትዮጵያን ገመና በርብሮ የሚሸጥ ምሁር ሳይሆን የኢትዮጵያን ገመና የሚሸፍንና እውቀቱን ለሀገር የሚያውል ምሁር ትፈልጋለች።

ኢትዮጵያ በጉልበቱ ሠርቶ የሚቀይራት ጉልበታም አፍላ ጎረምሳ ትፈልጋለች፣ ድንጋይ በመወርወር የተሰራ የሚያፈረስ ሳይሆን የተበላሸን ቦታ በጉልበቱ የሚያቀና፣ የሚያሳምር ጎረምሳ ትፈልጋለች፤ ኢትዮጵያ ለተፈጠሩበት ዓላማ መኖር የሚችሉ ባለሃብቶች መስራት፣ ሥራ መፍጠር፣ ሥራ ማሰራት ብቻ ሳይሆን ሀገር እንድትለማ ቆርሰው ከፍለው መስጠት የሚችሉ ታማኝ ባለሀብቶች ትፈልጋለች። ስንነካ ግንባራችንን መስጠት ብቻ ሳይሆን ሠርተን ካተረፍን  ለማካፈል የጀመርነውን አበረታች ልምምድ ማጠናከር ይኖርብናል። ኢትዮጵያ ሀገራችን እንደ እናት ናት። እናት የሚገባትን እንክብካቤ ማግኘት ካልቻላች ትጎሳቆላለች ትገረጣለች፤ የተጎሳቆለችና የገረጣች እናት ልጇን ማጥባት አትችልም። ጡት ብትሸከምም የነጠፈ ነው። ኢትዮጵያችን እንዳትጎሳቆልና እንዳትገረጣ ከእያንዳንዱ ዜጋ በጉልበት፣ ሀብቱን በማፍሰስ፣ በታማኝነት በማገልገል የሚጠበቅብንን በድምር መከወን ከቻልን ኢትዮጵያ ሀገራችን በአድዋ ያገኘችውን ድል በነጻነት ከድህነት በመገላገል መድገም የምትችል  መሆኗን ማየት ለሁላችንም

የሚደበቅ ምስጢር አይመስለኝም። ነገር ግን ለኢትዮጵያ ያለንን ፍቅር፣ ለኢትዮጵያ ያለንን ተቆርቋሪነት ማሳየት ያለብን በሥራ፣ በመስጠት፣ በመትጋትና ባለመስረቅ መሆን ይኖርበታል።

ሁላችሁም እንደምትገነዘቡት ሀገራችን ኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ ችግሮች አሉባት። የችግሮቹ ሁሉ ቁንጮ ደግሞ ድህንት ነው፤ ሠርቶ መግባት፣ ሰርቶ መኖርና ራሱን ማኖር የሚችል ዜጋ በብዛት መፍጠር ባላመቻላችን ሥራ ያጡ ወንድምና እህቶቻችን ወይንም ለሥራ ሲወጡ ምቹ ከባቢ ያላገኙ ወንድምና እህቶቻችን በድህነት ምክንያት የሚወዷትን ሀገር የሚጎዱበት ምክንያት ተበራክቶ ይታያል። ይህ ነገር እንዲቀንስ ድህነት ታሪክ ሆኖ ሰርተን ውለን መግባት ብቻ ሳይሆን በልተን ማካፈል የምንችል ዜጎች እንድንሆን፣ የድህነት ቀንበር እንዲሰበር ከምንጊዜውም በላይ በትብብር፣ በትዕግስትና በወንድማማችነት አብረን መቆም ያስፈልጋል።

የተከባራችሁ ታማኝ ግብር ከፋዮች ዛሬ የአድዋን ድል መታሰቢያ ስናከብር የሀገር መከላከያን፣ ፌደራል ፖሊስን ሁለንተናዊ አቅም ለማየት እድል ያገኛችሁ ይመስለኛል። ባላፉት አራትና አምስት ዓመታት በርካታ ፈታና ቢግጥመንም ለታማኝ ግብር ከፋዮች ምስጋና ይግባና ጠንካራ ሀገር የሚጠብቅ መካላከያ፣ ፖለሲና ሀገሩን መጠበቅ የሚችል የደህንነት ተቋም ለመገንባት ችለናል። ይህን የቻልነው በእናንተ ታማኝ ግብር ከፋዮች ቀጥተኛ የሆነ ድጋፍ ነው። የእናንተ ድጋፍ ባይታከልበት ኢትዮጵያ ዛሬ ያያችሁትን የመከላከያ ተቋም መገንባት አትችልም። በዚህ ብቻ ሳንወሰን በትምህርት ዘርፍ ጥራት እንዲፈጠር፣ በሸዎች የሚቆጠሩ የህጻናት መዋያ፣ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶችን ስንገነባ እንደቆየን ላላፉት ዓመታት ይታወቃል። በሚሊየን የሚቆጠሩ ተማሪዎችን ለመመገብና በምግብ እጥረት ምክንያት ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት መሄድ እንዳይሳናቸው ጥረቶች ተደርገዋል። የትምህርትን ጥራት ለመጠበቅ ፍኖተ ካርታ፣ ፖለሲዎች፣ ደንቦችና አሰራሮች እንዲሁም የፈተና ሥርዓትን ለማዘመን ጥረት ተደርጓል። በትምህርት ጥራት ላይ ለውጥ ለማምጣት የምናደርገው ጥረት ታማኝ ግብር ከፋዮች ግብር ባትከፍሉ ከሃሳብ አልፎ በተግባር የሚጨበጥ ስላልሆነ በትምህርት መስክ እያስመጣናቸው ላሉ ለውጦች ታማኝ ግብር ከፋዮችን ማመስገን እንወዳለን።
እንዲሁም በመሰረተ ልማት ግንባታ ብዙዎቻችሁ ከሀገር ወጣ ብላችሁ የማየት እድል ያላችሁ ስለሆናችሁ ኢትዮጵያ በውስጥና በውጭ ችግር በከፍተኛ ፈተና ላይ ያለች ቢሆንም በአፍሪካ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ በማልማትና በማደግ ላይ ያለች ሀገር ናት።
ይህንን እውነት የሚክድ ኢትዮጵያዊ ሥራ የማያውቅ ብቻ ነው። ሥራ የሚያውቅ

ሰው በደንብ የሚታይን ልማት መገንዘብ አይሳነውም፣ ብዙ የአፍሪካ ሀገራት የፈረሰ አስፓልቶቻቸውን መጠገን ተቸግረዋል። ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ በብዙ ሺህ ኪሎ ሜትር አስፓልት ኮንክሪት መንገድ እየገነባን ነው።
በቅርቡ አፍሪካ ህብረት ስብሰባ በነበረበት ወቅት ያገኛችኋቸው ሁሉም ከአፍሪካም ከአፍሪካ ውጭ የመጡ ሰዎች ያረጋገጡልኝ ነገር ከተሜነትና ለውጥ በአዲስ አበባ የሚነገር ሳይሆን የሚታይ ለውጥ መሆኑን ነው። ይህን የሚታይ እውነት ማራከስ ሳይሆን መጠበቅና ማፍጠን ይጠበቅብናል፤ ማፍጠን እና የተሟላ እንዲሆን የሁላችንም ጥረት ሊሆን ይገባል።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት በርካታ ችግሮች የገጠሙን ቢሆንም ህዳሴን ጨምሮ ፕሮጀክቶቻችን የምንሰራቸው ድልድዮችና አዳዲስ የመዳረሻ ፕሮጀክቶቻችን አንዳቸውም ሳይቋረጡ በመሰራት ላይ ይገኛሉ። ህዳሴ ግድብ በጦርነት ውስጥ፣ ህዳሴ ግድብ ባልተነገረ ማዕቀብ ውስጥ፣ ህዳሴ ግድብ በኮረና ውስጥ ሳይቋረጥ ሊሰራ የቻለው ታማኝ ግብር ከፋዮች በታማኝነት ግብራቸውን መክፍል ስለቻሉ ነው። በግብርናው ዘርፍ እያመጣን ያለነው ለውጥ ባለፉት ጥቂት ዓመታት በብዙ ሀገራት መመገብ፣ ለምግብ የሚሆን ነገር ማምረት ፈተና በሆነበት ጊዜ ውስጥ የጀመርናቸው መልካም ጅምሮች የታዩት እንዲሁ በእናንተ ታማኝ ግብር ከፋዮች ጥረት ነው።

በአካባቢ ጥበቃ፣ በአረንጓዴ አሻራ የተመዘገበው ውጤት ብዙዎች ጉልበታቸውን፣ ገንዘባቸውንና ጊዜያቸውን ሰጥተው በመስራታቸው ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ሊነገር የሚችል በርካታ ድል አለ። ድሎቻችን ድካሞቻችንን እንዳይሸፍኑ፣ ድሎቻችን የሚቀሩንን ስራዎች እንዳይሸፍኑ በመጠንቀቅ ድሎቻችንን በልኩ ችግሮቻችንን በልኩ እያየን በትጋት መስራት እንድንችል እንደዚህ ያለ መድረክ ታማኝ ግብር ከፋዮችንና ታማኝ ግብር ሰብሳቢዎችን የምናመሰግንበት እጅ ለእጅ ተያይዘን ለበለጠ ሥራ እንድንዘጋጅ የሚያደርጉ መድረኮች በእጅጉ ያስፈልጋሉ።

ከጠቀስኳቸው ሥራዎች በተጨማሪ በግብር ዘርፍ ቅድም እንደተገለጸው ባለፉት አራት ዓመታት ወይም ሦስት ዓመት ተኩል የነበረውን የግብር መጠን በእጥፍ ማሳደግ ተችሏል። በ2012 ዓ.ም ከነበረው በዚህ ዓመት የሚሰበሰበው በእጥፍ ያድጋል።
ይህ ትልቅ እድገት ነው በአሃዝ ሲታይ። ነገር ግን ኢትዮጵያ ካላት አቅም አንጻር ገና ብዙ ልንሰራ እንደሚገባ የሚያሳዩ እይታዎች ስላሉ ከታማኝ ግብር ከፋዮች እስከዛሬ ግብር ለመክፈል ፍላጎት የሌላቸው የሚሰሩ ሰዎች የሚጠበቀው ነገር ለተፈጠራችሁበት ዓላማ

መኖር አለባችሁ፤ እናንተ የተፈጠራችሁት ሥራ ለመፍጠር፣ እናንተ የተፈጠራችሁት ሀብት ለመፍጠር፣ የተፈጠራችሁት በፈጠራችሁት ሀብት ኢትዮጵያን ለመገንባትና ህዝቦቿን ለማብላት ነው። መስረቅና ማስቀረት የእናንተ ሥራ አይደለም ለዛ የተፈጠሩ ሰዎች አሉ። ሌሎችን ወደ እናንተ መሳብ እንጂ እናንተ ዝቅ ወዳለው መንገድ መውረድ የለባችሁም።

ሁላችንም ለተፈጠርንበት ዓላማ መኖር ስንችል፣ ኢትዮጵያን ቢያንስ በጥፋት እንዳትጠፋ እንዳትወድቅ መከላከል ይቻላል፤ በዚህ ዓለም ስንኖር ጥፋትም ልማትም፣ ማጥፋትም ማልማትም፣ ግንባታም ከግንባታ ውጭ ያለ ተግባርም፣ ሥራ መስራትም ቁጭ ብሎ መሳደብም ሁሉም አሉ። ምድር እስካለ ይቀጥላል። እያንዳንዳችን ቦታችንን መፈለግ ነው፤ ለልማት የተፈጠርን ሰዎች ማልማት አለብን፣ ለሥራ የተፈጠርን ሰዎች መስራት አለብን፣ ሰርተን አትርፈን ግብር ለመክፈል የተፈጠርን ሰዎች እንዲሁ ግብርን በታማኝነት መክፈል አለብን ሌሎቹን እንደተፈጠሩበት አላም እንዲኖሩ መፍቀድ ያስፈልጋል። በየቀኑ የምንመለከተው ይህንን ነው። ኢትዮጵያን በምኞት ሳይሆን በትጋት፣ በሥራ፣ በጥረት በመጠላለፍ ሳይሆን በመደጋገፍ፣ በመተባበርና አብሮ በመቆም፣ በመስራት፣ በመስጠት፣ በማካፈል፣ ሰላማዊና ህጋዊ በመሆን ብቻ ነው ብልጽግናዋን ማረጋገጥ የምንችለው። ከዚህ ውጭ ያሉ አማራጮች ለብዙ ጊዜ የሞከርናቸውና ያልተሳኩልን ስለሆኑ የተከበራችሁ እዚህ ያላችሁም ከዚህ ውጭ ያላችሁም መላው የኢትዮጵያ ህዝቦች ለኢትዮጵያ የሚያዋጣት ወንድማማችነት፣ መከባበር፣ ሰላማዊነት፣ ህግን ማክበር፣ ፍቅር፣ አብሮ መቆምና ኢትዮጵያ ህብረ ብሔራዊትና ውብ ሀገር መሆኗን አምኖ መቀበል ነው።

**የካቲት 24 ቀን 2015 ዓ.ም**
**አዲስ አበባ**



# የመደመር ትውልድ የመጽሐፍ ምረቃ ሥነ - ሥርዓት

ግንቦት 16 ቀን 2015 ዓ.ም

እንኳን በሰላም መጣችሁ፤ እንኳን የመደመር መንገድ መጽሐፍን በጋራ ለማስመረቅ አበቃችሁ ለማለት እፈልጋለሁ። ወደ ዋናው ሃሳቤ ከመግባቴ በፊት መጽሐፉን እንዲገመግሙ የተመደቡና በተሰጣቸው አጭር ጊዜ ውስጥ ከመጽሐፉ ውስጥ ብቻ ሳይሆን ከመጽሐፉም ባሻገር በርካታ ቁም ነገሮችን የዳሰሱትን አባቶች፣ እህቶችና ወንድሞች እንዳመሰግን ይፈቀድልኝ። ጋሽ ደቤ (አርቲስት ደበበ እሸቱ) ሁላችሁም እንደምታውቁት ጥሩ ጸሐፊ ነው፤ ጥሩ ገጣሚ ነው፤ ጥቂት ሃሳባቸውን ባስደናቂ መንገድ መግለጽ ከሚችሉ በእድሜው የያኔ ዘመን በልቡ ግን በጣም ተራማጅና የመደመር ትውልድ አባል የሆነ ሰው ነው። ወግ አጥባቂን ወክሎ ሃሳብ ቢያስቀምጥም ጋሽ ደቤ ተራማጅ፣ ሀገር የሚወድ፣ ትውልድ የሚወድ እንደ ትልቅ ስጦታ የምናየው ሰው ስለሆን በዚህ ቀን እንዳያችሁት እየደከመውም ቢሆን ለእኛ ከነበረው ልምድና እውቀት ለማካፈል ስለፈቀደ እባካችሁን አመስግኑልኝ።

ደራሲ ህይወት ተፈራ <<ማማ በሰማይ (Tower in the Sky)>> በሚለው መጽሐፏ ብዙዎቻችሁ የምታውቋት ይመስለኛል ፤ ኢህአፓን የምናውቅ ስለ ኢህአፓ ያነበብን ጌታቸው ማሩን በደንብ ለማወቅ ህይወትን እሷንና ጽሑፏን መገንዘብ እንዲሁም ብርሃነመስቀል ረዳን ደግሞ ለማወቅ  አምባሳደር ታደለች <<ዳኛው ማነው>> የሚለውን መጽሐፍ ያነበባችሁ ሰዎች ኢህአፓን ብቻ ሳይሆን ፍቅርን፣ የጸና አቋምን፣ ዘመን የማይሽረው የልብ ማህተምን የገለጹ ሁለት እህቶች ናቸው። ህይወት ተፈራ የመደመር መንገድን በዚህ መንገድ ለማቅረብና ካላት የህይወት ልምድ ውስጥ በጥቂቱ ለማካፈል በመካከላችን በመገኘቷ ትልቅ ክብር ይሰማኛል፤ እንድታመሰግኑልኝ እጠይቃለሁ። ዶ/ር ታምራት እና ዶ/ር መሳይ በእውቀት የተሞላ ሞጋችና ፍሬነገሩን ያስቀመጠ እንዲሁም የዩኒቨርሲቲ መምህራን ስለሆኑ ከትምህርት አንጻር መጽሐፉን ገምግመዋል። ሁለቱን ወጣት ምሁራንንም እንዲሁ እንድታመሰግንሉኝ እጠይቃለሁ። ዶ/ር ዮሴፍና ዶ/ር ታደሰ ሌንጮ የመደመር መንገድ ከገለጣቸው በላይ ቁም ነገሮች በኦሮምኛ ገልጸዋል፤ በሚገርም ሁኔታ ከጽሐፉ ባሻገር የሚጠቅም ሃሳብ አንስተዋል። ይህን ሃሰብ ኦሮምኛ ቋንቋ ለሚናገሩ ወንድም እህቶቻችን በስፋት እንደሚያስተምሩ ተስፋ አደርጋለሁ። የቋንቋ አጠቃቀማቸው ለነገሩ የሰጡት ትኩረትና ግንዛቤ እጅግ

የሚያስደንቅ ስለሆነ ዶ/ር ዮሴፍና ዶ/ር ታደሰ በመገምገም እንዳትወሰኑ እጅግ ብዙ መጽሐፍ ከእናንተ ይጠበቃል ማለት እፈልጋለሁ።

ዶ/ር መሃመድ ቀደም ብዬ እንዳነሳሁት እሳቸውም የጋሸ ደቤ ትውልድ አባል ቢሆኑም ብዙ ጊዜ በሚዛናዊ አስተሳሰባቸው፣ በቀና አስተሳሰባቸውና  አልፎ በሚሄድ ጎርፍ በማይወሰድ ማንነታቸው ይታወቃሉ። ዶ/ር መሃመድ እለተኝነትን የሚጸየፉና ሰው ተስፋኛ ሆኖ በተስፋ አርቆ ማየት እንዲችል የሚመክሩ፤ ጥቂት አሳቢያን ተብለው ከሚመደቡት ውስጥ የሚመደቡ ሰው ናቸው። ከሃይማኖታቸው፣ ከብሄራቸው እንዲሁም ከእድሜያቸው አልፎ አልፎም ከሀገራቸው ያለፋ ቁም ነገሮችንና እውነትን ለመግለጽ የሚጥሩ ሰው ስለሆኑ ታዳሚያን እንድታመሰግኑልኝ እጠያቃለሁ። የለውጥ ሂደትን በጊዜው መከተብ ታሪክ ከመጻፍ በላይ ነው፤ ህይወት ተፈራ ከብዙ አሰርት ዓመታት በኋላ መረጃ ሰብስባ፣ ማስታወሻዋን አገላብጣ፣ ሰዎችን ቃለ መጠይቅ አድርጋ ከጻፈችው ጽሑፍ ውስጥ ብዙ የዘነጋቻቸው ጉዳይ ሊኖር ይችላል። ነገር ግን የለውጥ ሂደትን በጊዜው መከተብ በጣም በርካታ ነገሮችን አሁን ላለው ትውልድ ብቻ ሳይሆን ለነገውም እንድንተው የሚያስችል አቅመ ብዙ የሆነ ከታሪክ በላይ የሆነ ቁም ነገርም በውስጡ የያዘ ነው።

ኩነቶችን በቦታና በጊዜ ሰድሮ ማስቀመጥ ያልተዛባ እውነትን ለማወቅና የትውልድን ቀጣይነት ለማረጋገጥ ያግዛል፤ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚያጣሉን ሳይሆን በማያጣሉን ጉዳዮች ስንባላ ስለምንውል ተከታታይነትን ለማረጋገጥ ኩነቶችን በቦታና በጊዜ ሰድሮ ማስቀመጥና ማሸጋገር ጠቃሚ ስጦታ ነው። በዓለም የውትድርና ታሪክ ውስጥ ሁለት አሳቢያን፣ ጸሐፊያን ሁሌም ይታወሳሉ፣ በወቅቱ ያስቀመጧቸው ጽሑፎች ዛሬም ድረስ ማጣቀሻ ሆነው ያግዛሉ። አንደኛው ሳንዙ ይባላል (The Art of War) የጦርነት ስልትን የጻፈው የቻይናው ደራሲ ማንም በውትድርና ያለፈና በጦር ኮሌጅ ተምሮ ያለፈ የሳንዙን መጽሐፍ ያላነበበ ወይም ያልሰማ አታገኙም። ከብዙ ዘመናት በፊት የተጻፈም ቢሆን ዛሬም ድረስ ለብዙዎች ማጣቀሻ የሆነ መጽሐፍ ነው።
ሁለተኛው ጀነራል ካርል ነው <<On War>> በተሰኘው መጽሐፉ የናፖሊዮንን የውጊያ አውድና የውጊያ ሁነት በትክክል ለማስቀመጥ በመቻሉ ወታደራዊ ነገሮችን የሚያነቡ፣ የሚጽፉና የሚፈትሹ ሰዎች እነዚህን ሰዎች ለማየት ይገደዳሉ ። በእኛ ሁኔታ የአድዋን ጦርነት በሂደት፣ በቦታ፣ በጊዜ መከተብ ብንችል ኖሮ ዛሬ አድዋን ለኢትዮጵያዊያን፣ ለአፍሪካዊያንና ለጥቁር ህዝቦች ከዚያም አልፎ ለነጻነት ለሚተጉ ህዝቦች የሚያኮራ ታሪክ እኛ ዘንድ ግን የሚያጨቃጭቅ ታሪክ ነው።

የአሉላ አባነጋን ታሪክ እንዴት ትግራዮች መጣያ ያደርጉታል፣ የአፄ ምኒሊክን እና የእቴጌ ጣይቱን ታሪክ እንዴት አማሮች መጣያ ያደርጉታል፣ የሀብቴ አባመላን ታሪክ፣ የባልቻ አባነፍሶን ታሪክ እንዴት ኦሮሞዎች መጣያ ያደርጉታል? ይሄ እኮ የሁላችንም ታሪክ ነው የአባቶቻችን የጀግንነት ገድል የታየበት ነው፤ ሁላችንም የሚያሰባስበን የሚደምረን አንድ አንኳር ታሪክ ካለን አንድ አድዋ ነው። ሁሉም ራሱን ፈልጎ የሚያገኝበት፣ ሁሉም በዚያ ውስጥ ማንነቱንና ኢትዮጵያዊ ወንድሙን አጉልቶ የሚያውቅበት ታሪክ ነው። <<ሰተቴ>> በተባለው ሶስተኛ መጽሐፌ ስለ ባልቻ አባነፍሶ አንስቼ ነበር። ባልቻ አባነፍሶ በመጀመሪያ በነበረው አድዋ ዘመቻ በጀግንነት ተሳትፈው በኋላ በነበረው ለውጥ መስማማት ተስኗቸው በግዞት ወደ ወሊሶ ከገቡ በኋላ ሁለተኛው የጣልያን ወረራ ሲመጣ በእርጅና ወራቸው <<እኔ ጸቤ ከጃንሆይ እንጂ ከኢትዮጵያ አይደለም>> ብለው ከጣልያን ጋር ተፋልመው የሞቱ ሁለቱንም ወረራዎች የተፋለሙ ጀግና ናቸው። እነዚህ ሰዎች የሚያኮሩንና የሚያሰባስቡን መሆን ሲችሉ የንድፍና የማዕቀፍ እጦትና አላስፈላጊ የታሪክ ሽሚያ ዛሬ የመደመር ትውልድ መስራት ሲገባው ሲጣላ ይታያል። በነገራችን ላይ አድዋን ካሸነፍን በኋላ ለተከታታይ ሰባት ዓመታት የድል ዝክረ በዓል በኢትዮጵያ ውስጥ አልነበረም። በሰባተኛው ዓመት አጼ ምኒሊክ ወታደሮቻቸውን አሰልፈው ነው ለመጀመሪያ ጊዜ ያከበሩት ፎቶውም አለ ጽሑፉም አለ፤ ዘንድሮ እኛም የደገምነው እሱን ነው።

ታሪክ መሰረዝ ሳይሆን ታሪክን መልሰን ማደስና ለማስዋብ ነው የፈለግነው። ትውልድ መንቃት፣ መጠየቅና መመርመር አለበት። እንዲሁ በከንቱ የሚፋጅ እንዳይሆን ንድፍና የማዕቀፍ ጽሑፎች በእጅጉ አስፈላጊ ናቸው። ዶ/ር መሃመድ እንዳነሱት በመደመር መጽሐፎች ዶ/ር ታደሰም እንዳነሳው ሃሳብን ሰድሮ በማዕቀፍ ለማስቀመጥ ሙከራ ተደርጓል። ዛሬ ልነግራቸሁ የምፈልገው ሶስቱም በመደመር መቆለፊያ ቃል ውስጥ የተያዙ መጽሐፎች ሙሉ በሙሉ ሃሳቤን አልገለጹልኝም። ገና ብዙ መጻፍ፣ መወያየት፣ መነጋገር፣ መሞገት የሚፈልጉ ሃሳቦች አሉት። የዛሬው መጽሐፌ በቁጥር ስምንተኛው ነው። ከዚህ በፊት ሰባት መጽሐፎች ያሳተምኩ ሲሆን ስድስቱ ለገበያ ውለዋል፤ አንደኛው ለገበያ አልዋለም። የመጀመሪያው ከመደመር ጋር የሚያያዘው መደመር በሚል የተጻፈው ጽሑፍ ፍልስፍናዊ፣ ርዕዮተ ዓለማዊ ብቻ ሳይሆን አዲስ አቅጣጫ (New Paradigim) ለማሳየት የሞከረ ነው። መደመር የጽሑፍ ሥርዓቱ ሃሳብ ላይ ብቻ ያጠነጠነ በመሆኑ ከፍተኛ የማንበብ ልምድ የሌላቸው ሰዎች መጽሐፉን ለማንበብ ይቸገራሉ። ሃሳብ እንጂ አጫዋች አይደለም የመደመር መንገድ ግን ከዛ ትንሽ ቀለል ብሎ መደመርን በጉዞ የሚገልጥ ነው፤ New Paradigim በፈለግ፣ በጉዞ፣

በጊዜና በምሳሌ (Metaphor) የሚገልጽ ነው። የአሁኑ የመደመር ትውልድ ደግሞ የትወልድ ግንባታን አሰናስሎ ለማሳየት የሚጥር ነው። የመደመር ትውልድ፤ ትውልድን በአምስት ከፍሎ ይበይናል።

የመጀመሪያውን ወግ አጥባቂ ይለዋል፣ ለውጥ የሚወደውን ሀገሩን የሚወደውን፣ ሃይማኖቱን የሚወደውን። ሁለተኛውን ህልመኛው ይለላዋል፣ በምናቡ ብዙ የሚያልም፣ ለህልሙም ህይወቱን የሚሰጥ፣ የሚተጋ፤ ህልሙን ለመፍታት ወንድሙን መውደድና ከወንድሙ ጋር መደመር እንደሚያስፈልገው ግን ያላወቀና የህልመኛው ፈጣሪዎችን የበላ ትውልድ ነው። ኃይሌ ፊዳን የበላ፣ ጌታቸው ማሩን የበላ፣ ብርሃነመስቀል ረዳን የበላና አሳቢዎችን የበላ ነው። ይህ ትውልድ ብዙ ልንማርበት የሚገባ ትጋትና ጥረት ያደረገ ነው። የምንወቅሰው ብቻ ሳይሆን ብዙ ልንማርበት የሚገባ ትውልድ ነው። ያኔ ብቻ ሳይሆን ህልሙን የኖረው ዛሬም ህልሙን መፍታት አቅቶት በየጊዜው የሽግግር መንግሥት የሚጠይቅ ትውልድ ነው። እንዲሁ እንዳለም የምንሰናበተው ትውልድ እንደሚሆን ጥርጥር የለኝም። ሦስተኛው ውል አልባው ትውልድ ነው። ውል የለውም ከነዚህ ሁለት ትወልዶች የተለየ ባህሪ አለው። አራተኛው ባይተዋሩ ትውልድ ነው። አምስተኛው የመደምር ትውልድ ነው።

ዶ/ር መሃመድ ላነሱት ሃሳብ በዚሁ መለሽ ለመስጠት፤ የመደመር ትውልድ የሚባለው አሁን እያበበ ያለው ትውልድ ካለ ጥርጥር ኢትዮጵያን ወደ ብልጽግና ያሸጋግራል። የመደመር ትውልድ በእርግጠኝነት በታሪኳ የገዘፈች ብቻ ሳይሆን በአሁናዊ ማንነቷ ትልቅ የሆነች ኢትዮጵያን ያረጋግጣል ምንም ጥርጥር የለውም። ይህን ማወቅ የፈለጋችሁ ሰዎች የሦስት፣ የአራት ዓመት ህጻናት ዘንድ ሂዱ በሚጣፍጥ ቋንቋ ኢትዮጵያ ይሏችኋል። አሁን ያለው ኢትዮጵያን የሚወድ የሚመስለው የኢትዮጵያን ታሪክ በቅጡ ያልመረመረውና ከነበሩ ስብራቶች ጋር ራሱን ማስታረቅ ያልቻለ ችግሮችን መቀበል ያልቻለው ሳይሆን የመደመር ትውልድ ያለጥርጥር ኢትዮጵያን ወደ ብልጽግና ያሸጋግራል።

ዶ/ር መሃመድ ከሶስቱ መደመሮች በኋላ ምን ይፈጠራል ብለው ጠይቀዋል።
ፈጣሪ ቢፈቅድና ብንኖር ምናልባት በሚቀጥለው ዓመት የሚቀጥለው አራተኛው መጽሐፍ በሦስት መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ አጠንጥኖ ይጠናቀቃል። አንደኛው መፍጠን ነው (Speed) ብልጽግና ማለም መሻት ብቻ ሳይሆን ያን የምናልመውን ለመጨበጥ መሮጥ እንደሚያስፈልግ የሚዳስስ ነው። ሁለተኛው መፍጠር ነው (Inovetive)

ሥራ ፈጣሪ የሆነ ማህበረሰብና መንግሥት መፍጠር አለብን፤ በግራ ጭንቅላቱ ብቻ የሚሰራ ሳይሆን ኢማጅን ማድረግ የሚችል የሚያይ ያየውን መፍጠር የሚችል ሥራ ፈጣሪ መንግሥት መፍጠር ያስፈልጋል። ሦስተኛው ደግሞ ይህ ጉዳይ እንዳይሆን ያለውን ፖለቲካ ሽቀጥ እንዴት ከመፍጠርና መፍጠን ሊያቀየን እንደሚችል የሚዳስስ ማጽሐፍ ነው። በሚቀጥለው ዓመት በጋራ እንደምናስመርቀው ተስፋ አደርጋለሁ።
ሦስት ዓመታት ይቀሩናል ተርማችን ለመጨረስ። ብዙዎች የሽግግር መንግሥት ቢሉም እግረ መንገድ እንደማይሳካ ለማረጋገጥ ነው። በነዚህ ሦስት ዓመታት ውስጥ ፈጣሪ ከረዳን የፖለቲካ ገበያ በሚል ርዕስ ቅድም ያነሳኋቸውን ነጥቦች የሚያነሳ፣ ከዛም <<ፍሪሊዮን>> በነጻ መስጠትን እውቀትን በነጻ ማካፈልን የሚመለከተው መጽሐፍ ምናልባት የመጨረሻው ባለፈው ዓመት የነበርንበትን የጦርነት አውድ ለትውልድ እውነታውን ለመተው በሚያስችል መንገድ የተዘጋጀ መጽሐፍ ይኖረናል።

ይህን የምናደርግበት ዋናው ምክንያት ነገርን በጊዜው ማስቀመጥ ለትውልድ ወሳኝ ነው በሚል እምነት ነው። የሚደመር ትውልድ መርሆዎች አሉት። መርሆዎቹም ማስተካከል፣ ማስፋትና ማበርከት በሚሉ ሦስት ፍሬ ነገሮች ታስረው ሊታዩ ይችላሉ።
ማስተካካል የሚለው በትናንትና ጉዷችን ግለሰብ፣ ቤተሰብ፣ ማህበረሰብ፣ ሀገርና አህጉር ስህተት እየሰራ ስለመጣ ያንን ስህተት ማስተካከል የመደመር ትውልድ ሃላፊነት እንደሆነ ያነሳል። ሁለተኛው ማስፋት ነው፤ ድሎችን ማስፋት ነው፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚያስደንቁ ድሎች አሉ የሚያጠብቅ የሚያሰፋ መሆን አለበት። ሰንዙ እያለ እያደነቀ ሎሬት ጸጋዬን ለመመርመር የሚቸገር ትውልድ መሆን የለበትም። ውጭ ናፋቂ፣ ውጭ አድናቂ ብቻ ሳይሆን ውስጥ መመልከት አለበት ምክንያቱም ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ሊነገሩ የሚችሉ ሊጠበቁ የሚገባቸው ድሎች አሉ እነሱን መዳሰስ፣ ማስፋትና መጠበቅ እንደ መርህ የሚያስብ ነው።

ሦስተኛው ማበርከት ነው፤ አሻራን በወርቅ የሚጽፍ ነው፣ በአቧራ የሚያስቀምጥ ብቻ ሳይሆን አሻራ የሚያስቀምጥ ነው። ለማን? ለሚቀጥለው ትውልድ። ማሰሪያው ነገር ከተናጠል እውነት ወደ ወል እውነት የሚሸጋገር ትውልድ መሆን አለበት። ዛሬ በሳይንስ ሰዎች ጸጉራቸው ሲመለጥ የሚያስተክሉት ባእድ ጸጉር ሳይሆን ከራሳቸው ጸጉር ውስጥ የተወሰነ ዘር ወስደው ነው የተመለጠ አካላቸውን የሚሸፍኑት። አንዳንዶች ኩላሊት ሲታመምባቸው ወይ ከወንድም፣ ወይ ከእህት ወይንም ቅርብ ከሆነ ዘመድ ነው ኩላሊት የሚያስተክሉት። የኦሮሞን ብልሽትና ድካም የማይጠግን አማራ፣ የአማራን ብልሽትና ድካም የማይጠግን ወላይታ፣ የወላይታን ብልሽትና ድካም የማይጠግን አፋርና ሱማሌ

ሊኖር አይችልም። ሳይንሱ የሚያሳየው ካንዱ ሰውነትህ ክፍል ሲበላሽብህ ከኀረቤቱ ውስድ ነው። ኢትዮጵያ በሰሜን ከኀደለባት ምዕራብ ሞልቶላት፣ ምዕራብ ከኀደለባት ሰሜን ሞልቶላት ነው ሙሉ የምትሆነው ማለት ነው፤ ሰፈርተኝነትን የሚጠየፍ ትውልድ መሆን አለበት። አሁን ችግር የሆነው ሰፈርተኞች ቀድመው ሰፈርተኛ ታርጋ መለጠፋቸው ነው፤ ቀድመው ታርጋ ለጥፈው በሰፈራቸው ቆመው በሰፈራቸው ሚዛን ሰው ይመዝናሉ። ከዚህ ውስጥ ለመውጣት የመደመር ትውልድ አሻግሮ የሚያይ መሆን አለበት።

ዓለምን ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያንም ስንዞር ታይተው የማይጠገቡ እጅግ አስደማሚ እውነቶች፣ እውቀቶችና ታሪኮች ኢትዮጵያ ውስጥ አሉ። ገና ያላወቅናቸውም እጅግ በርካታ ነገሮች አሉ። በቅርቡ አንድ ቦታ በማዕድን ዘርፍ በተደረገ ጥናት ከአንድ የወርቅ ማዕድን ፋብሪካ ጎን ብዙ ቶን ወርቅ ተገኝቷል። ፋብሪካውም አያውቀውም፣ ኢትዮጵያም አታውቀውም። ሁለት ቦታዎች ላይ ያገኘናቸው አሁን በቅርቡ ወጥተው ሥራ ላይ ሲውሉ ኢትዮጵያ እስካሁን ከምትሸጠው ሁለት ሦስት እጥፍ ወርቆች በዓመት መሸጥ ትችላለች። ገና ያላየናቸው፣ ያልጨበጥናቸው፣ ያልዳሰስናቸው በርካታ አቅሞች አሉ፤ የማን አቅም? የወል አቅም። የወል አቅም መሆናቸውን ለመገንዘብ ከተናጠል እውነት ወጥተን ወደ ወል እውነት መሸጋገር አለብን። የእኛ ሰፈር ችግር የሁሉም ሰፈር ችግር መሆኑን ለመገንዘብ ሚዛናዊ መሆን ያስፈልጋል ያንን ማድረግ ከቻልን እንደተባለው ኢትዮጵያን ለማሸጋገር እድል የሚሰጥ ሁኔታ እንዳለ ያሳያል።

ይሄ ሁሉ ሲባል የመደመር ትውልድ ፈተና የለበትም ወይ? ዶ/ር መሃመድ እንዳነሱት በምድር ላይ ያለው ሁኔታ በሃሳብ ከምናስበው ጋር ይሄዳል ወይ ያላችሁ እንደሆነ አንደኛ ፈተና ባይኖር ኖሮ የመደመር ትውልድን በዚህ ሃሳብ መቅረጽ አያስፈልግም፤ ፈተና ስላለና ፈተናውን እንዲያሸንፍ ነው ትውልዱን በዚህ መንገድ መቅረጽ ያስፈልጋል የሚል እሳቤ የተነደፈው። አንድ መንገድ የሚሰራ መሃንዲስ በሜዳ ላይ መንገድ እየቀየሰ ተራራ ላይ ሲደርስ ሶስት አማራጭ አለው።

አንደኛው አማራጭ ተራራን ፈርቶ መቆም ነው፣ የመንገድ ሥራዎን ማቋረጥ፣ ሁለተኛው አማራጭ ከተራራው በላይ ወጥቶ መንገድ ማስቀጠል ነው። ሶስተኛው አማራጭ ተራራውን ቦርቡሮ ሸለቆ ሰርቶ መንገድ ማስቀጠል ነው፤ ተራራን ፈርቶ የሚተው የመንገድ ቀያሽ መንገድ ይጀምራል እንጂ አይጨርስም። ተራራውን ባይፈጥረውም ተራራውን እሱ ወደሚፈልገው የማዞር ግን የዛ መሀንዲስ ግዴታ ነው።

የመደመር ትውልድ ሆይ በርካታ ችግሮች በርካታ ተራራዎች ከፊትህ ያለ ቢሆንም እነሱን ሲያስፈልግ ቦርቡረህ፣ ሲያስፈልግ ተሻግረህ ብልጽግናንና አድገትን ለኢትዮጵያ ማረጋገጥ እንጂ በፈተና መቆም አይቻልም። አንደኛው ውርስ ፈተና ነው፤ ጋሽ እንተና እና እንትና ተጣልተው ነበር፤ ተሰዳድበዋልና አሁን ሂሳብ እናወራርድ የሚባል የውርስ በሽታ ያለበት ሀገር ነው። ከዚያ ጸብ ትምህርት የሚቀስም ሳይሆን በዚያ ጸብ ውስጥ ራሱን አስገብቶ የሚጣላ የውርስ ጸብ፣ የውርስ ፈተናዎች።

ሁለተኛው ማህበራዊና ፖለቲካዊ አክራሪነት፣ ማህበራዊም አክራሪነት አለ ፖለቲካውም በአክራሪነት የተሞላ ነው። ይህንን ፈተና በውይይት በንግግር አርቆ በማየት ሰርቶ በመሻገር መፍታት የሚያስችለው የመደመር ትውልድ ሐላፊነቱ ድርብ እንደሆነ ሲገነዘብ ነው። የትናንትናውን ማስተካከል፣ አሁን ያሉ ድሎችን ማስፋት፣ ማላቅ ወደፊት ደግሞ አዳዲስ ድሎች ማበርከት የሚችል ትውልድ ሆኖ ራሱን ካዘጋጀ በመጽሐፋ በከፊል ሀሳቦቸን ለመግለጽ እንደሞከርኩት ይህ ትውልድ የኢትዮጵያን ችግር ይፈታል። ለትውልድ እዳ የሚተው ሳይሆን ለትውልድ ትርፍ የሚተው፣ በጥበብ የሚያምን፣ በሳይንስ የሚያምን፣ በምክንያት የሚያምን በImaginary Power የሚያምን፣ በማንበብ በመድከም የሚተጋ፣ በደርሶ ሂያጅ ስሜት የማይወሰድ ትውልድ ይሆናል። የመደመር ትውልድ አንድ አስምሮ ሊይዘው የሚገባው ጉዳይ ኢትዮጵያ ከነድካማቸውም ቢሆን በጥበብ የተሞሉ አባት እናቶቻችን ያቆዩልን ሀገር ስለሆነች በጥበብ ያቆዩልንን ሀገር በደርሶ ሂያጅ ስሜት ለማፍረስ መሞከር ተገቢ አይሆንም። ሀገራችንን ማጽናትና ማስቀጠል ከሁላችንም የሚጠበቅ ነገር እንደሆነ አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

የመደመር መንገድ ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ እንዳይሆን እንጂ ለማንበብ ያጓጓል። ብዙ ለማየት ያልቻልናቸውን ነገሮች ለማሳየት ይሞክራል፤ ያም ሆኖ ግን ሙሉ አይደለም። ምሁራን ስራቸው መሞገት ነው፣ መተቸት በጥላቻ ሳይሆን በምክንያታዊነት መነጋገር ነው። አንድ የመደመር መንገድ ልዩ ነገር እዚህ ውስጥ ያለን ሰዎች በየራሳችን መንገድ ብናነበው በውስጡ ራሳችንን እናገኛለን፤ ለትናንትናውም፣ ለዛሬውም፣ ለነገውም ሰው ይሆናል። ብዙ የሚያነጋግሩ እንዲያ ነበር እንዴ ብለን ዳግም እንድንፈትሽ የሚያስገድዱ ሃሳቦች በውስጡ ይዟል። የመደመር መንገድ ትናንትና ከዛሬ የሚያገናኝ መንገድ ብቻ ሳይሆን በሽያጩም የሚገኘው ገቢ በዚሁ መንገድ ትናንትንና ነገን የሚያስተሳስር ነው። ክብርት ቀዳማዊት ዝናሽ ታያቸው ባላፉት መጽሐፍት ገቢ በታማኝነት ትምህርት ቤት ለመገንባት ላደረገችው ጥረት እጅግ ከፍተኛ ምስጋና እያቀረብኩ፤ የመደመር መንገድ ሃሳቡም ትውልድ ይሰራል ገንዘቡም ትውልድ ይሰራል።

በዚሁ አግባብ ዶ/ር ይልቃል ከፋለ የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር የመደመር ትውልድ መጽሐፍን ይዘው ይመጣሉ (ይዘው ቀርበዋል)፤ የመደመር መንገድ እያልኩ ደጋግሜ ያነሳሁት ትውልዱ በዚሁ መንገድ ስለሚጓዝ ነው። ይህ የመደመር ትውልድ በአማራ ክልል ተሸጦ የሚገኘው ገቢ አንድ መቶ ፐርሰንት የፋሲል ቤተመንግሥትን ለመጠገን ይውላል። መቶ ፐርሰንት የፋሲል ቤተ መንግሥትን መጠገን የሚያስፈልገው ትውልድን ከትናንትና ማስታረቅ ስለሚያስፈልግ ነው። ዶ/ር ይልቃል የመደመር ትውልድን እንዲያነቡ፣ እንዲሸጡና ፋሲልን እንዲያድሱ በእናንተ ፊት አደራ ልላቸው እፈልጋለሁ።

አቦ ሽመልስ Dhaloota Ida'amuu ይዘው ወደዚህ ይመጣሉ (ይዘው ቀርበዋል) አቦ ሽመልስ መጽሐፉን በኦሮሚያ ሸጠው የሚገኘውን ገቢ እጅግ አስደማሚ የሆነውንና በእኛ ንዝህላልነት የረሳነውን የሶፍ ኡመር ዋሻን አድሰው ለጎብኝ የሚያዘጋጁበት ይሆናል። የሶፍ ኡመር ዋሻ ብዙ የሚያጓጉ ታሪኮች ያሉበት ቦታ ነው። ይህን መጽሐፍ በመሸጥ ይህንን ጥንታዊ ቦታ በማደስ ለትውልድ እንዲሸጋገር እንዲያደርጉት አደራ ልልዎት እፈልጋለሁ።

ሁለት ታሪክ ስለሆነ አንድ ታሪክ ለመጨመር ክብርት ከንቲባ አዳነች አቤቤ መጽሐፉን ይዘው ወደዚህ ይመጣሉ (ቀርበዋል) ክብርት ከንቲባ ይህንን መጽሐፍ በተለያየ መንገድ ከሸጡ በኋላ በሚገኘው ገቢ አዲስ አበባ ውስጥ ሁላችሁም እንደምታውቁት የነገው ትውልድ መዋያ መቦረቂያ እያጣ ስለሆነ እስካሁን ትናንሽ አራት ስታዲየሞች ያሰሩን ቢሆንም በዚህ መጽሐፍ ሽያጭ በሚገኘው ገቢ አዲስ አበባ ባስገባው ልክ መቶ ፐርሰንት አዲስ አበባ ውስጥ በየሰፈሩ ያሉ ትናንሽ ስታዲየሞች መልሰው ሰውን በምንሰራበት ስታንዳርድ መስሪያ እንዲሆን ከአደራ ጭምር እሰጣለሁ። የቅድሙ ታሪክ ነው ይህኛው ትውልድ ነው።

ቀጥሎ የሐረሪ ክልል ፕሬዘዳንት አቶ ኡርዲ ወደዚህ ይመጣሉ (ቀርበዋል) ሁላችሁም እንደምታውቁት በሐረር ከተማ ውስጥ ሰዎች ጅብን ስጋ ሲያበሉት ለማየት ይሄዳሉ፤ ቦታው ግን ለቱሪስት ምቹ አይደለም። ይህንን ቦታ ከዚህ መጽሐፍ ሽያጭ በሚገኝ ገቢ ለቱሪስት ምቹ አድርገው አቶ ኡርዲ እንዲሰሩት ከአደራ ጭምር ሰጥቻለሁ።
አቶ ደስታው የሲዳማ ክልል ርእሰ መስተዳድር ወደዚህ ይመጣሉ (ቀርበዋል) የሲዳማ ክልል መናገሻ የሆነችው ሃዋሳ ከተማ እጅግ ውብ ብትሆንም ወጣቶች የሚናፈሱበት ቦታ ስለሚያስፈልጋቸው ይህንን መጽሐፍ ሸጠው በሚያገኙት ገቢ ሙሉ በሙሉ የታቦር

ተራራን ውብ አድርገው እንዲሰሩበት አበረክታለሁ፤ ታቦር ለሃዋሳ ልጆች ብቻ ሳይሆን እኛም ስንመጣ ስለምንገበኘው በዚያው አግባብ እንዲሰራ አደራ እላለሁ።

አቶ አወል አርባ የአፋር ክልል ርዕሰ መስተዳደር ወደዚህ ይመጣሉ (ቀርበዋል) አቶ አወል አርባ ታሪክ ጠገብ የሆነችውን የአፋር ክልል የመምራት እድል ያላቸው ሰው ናቸው ፤ በአሳይታ የአፋር ሱልጣን ቤተ መንግሥት ከፍተኛ እድሳት ይፈልጋል።

በነገራችን ላይ የእኛው የአፋር ሱልጣን የእኛ ብቻ ሳይሆኑ የኤርትራም አፋር፣ የጅቡቲም አፋር ሱልጣን ስለሆኑ ይህንን ታሪክ መጠበቅና ማቆየት ስለሚያስፈልግ በአፋር ክልል በሚሸጠው የመደመር ትውልድ መጽሐፍ ሙሉ ገቢውን በአሳይታ የሱልጣኑን ቤተ መንግሥት እንዲያድሱና ታሪክ እንዲያሸጋግሩ አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

የሶማሌ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሙስጠፌ ወደዚህ ይመጣሉ (ቀርበዋል) በሰሜን የአድዋን ታሪክ እንደምንዘክረው ሁሉ በምስራቅ ካራማራን ማስታወስ በእጅጉ አስፈላጊ ስለሆነ ብዙ አባቶቻችን ደምና አጥንታቸውን ስለገበሩ መዘንጋት ስለሌለበት አቶ ሙስጠፌ ይህን መጽሐፍ በሀገር ውስጥና በውጭ ጭምር በመሸጥ በሚገኘው ገቢ ካራማራን ከነታሪኩ ለትውልድ እንዲያሸጋግሩ አደራ እላለሁ።

አቶ ርስቱ የደቡብ ክልል ርዕሰ መስተዳድር (ቀርበዋል) በደቡብ መጽሐፍ በስፋት ይነበባል። እናም የጢያ ትክል ድንጋይን ውብ አድርገው ለትውልድ እንዲያሸጋግሩበት ገቢውንም ብቻ ሳይሆን ሃሳቡንም ጥቅም ላይ እንዲያውሉት ከአደራ ጭምር አበረክታለሁ። በነገራችን ላይ የመደመር ትውልድ ለደቡብ በጣም ያስፈልጋል።

የደቡብ ምዕራብ ክልል ርዕሰ መስተዳደር ዶ/ር ነጋሽ (ቀርበዋል) በደቡብ ምዕራብ ብዙ ታሪኮች እጅግ ውብ የሆኑ ቦታዎች ያሉ ቢሆንም ታሪኮች ስላልወጡ በዚያ ክልል በሽያጭ በሚገኘው ገቢ አንድ ቆንጆ ቤተመጻሕፍት ተሰርቶ በዚያ አካባቢ ያሉ ብሄረሰቦች ማንነታቸው ታሪካቸው የሚታይበት ቤተመጻሕፍት ሆኖ እንዲሰራ አሰራሩ ግን በአዲስ አበባ ስታንዳርድ እንዲሆን አደራ እላለሁ።

የጋምቤላ ክልል ርዕሰ መስተዳደር አቶ ኡመድ (ቀርበዋል) አቶ ኡመድም እንዲሁ ጋምቤላ አካባቢ በጣም ብዙ ሊነገሩ የሚገባቸውና ያልወጡ ስላሉ አንድ ቆንጆ ቤተመጻሕፍት ጋምቤላ ላይ እንዲሰሩ ከአደራ ጭምር አስተላልፋለሁ።

አቶ አሻድሊ የቤንሻንጉል ክልል ርዕሰ መስተዳድር (ቀርበዋል)። አቶ አሻድሊ እድለኛ ስለሆኑ ህዳሴም ስለሚሰራ ህዳሴ አካባቢ ብዙ የሚታሰቡ ስራዎች ስላሉ ህዳሴን ጨምሮ ታሪካችንን የምናሳይበት ሙዚየም በዚህ መጽሐፍ ሽያጭ እንዲገነቡ ራሱ የህዳሴ ታሪክም በሙዚየም መልኩ መገለጽ ያለበት ስለሆነ ከዚህ በሚገኝ ገቢ ሙዚየም በማሰራት ኢትዮጵያዊያን መጥተው የህብታቸውን ከፋይ ማየት እንዲችሉ እንዲያደርጉ ከአደራ ጭምር አበረክታለሁ።

የድሬድዋ ከንቲባ መኖራቸውን እርግጠኛ አይደለሁም ከሌሉ እሳቸውም ድሬድዋ ውስጥ በሽያጩ ገቢ አንድ ቀንጆ ቤተመጻሕፍት እንዲሰሩ ከአደራ ጭምር እየተናገርኩ በአጠቃላይ የመደመር ትውልድ ሃሳቡ ለትውልድ በሽያጩ በሚገኝ ገቢ ልክ በየአካባቢው ለልማት የሚውል ስለሆነ የምናነብ ሰዎች ሁለት ነገር ታሳቢ እናድርግ።

በአንድ በኩል በክልላችን የሚሰራ ሥራ እየደገፍን ነው፤ በሌላ በኩል ደግሞ የምንሞግተው፣ የምንጠይቀውና የምናሰላስልበት ሃሳብ የምንገበይበት ስለሆነ በቀና ልቦና መጽሐፉን እንድናነብና በሃሳብ እንድንሞግት ከአደራ ጭምር እጠይቃለሁ።

ስለመጣችሁ፣ ይህን የመደመር ትውልድ ለመገንቢያ የሚውል መጽሐፍ ከእኛ ጋር ለማስመረቅ፣ ለመገምገም፣ ሃሳብ ለማካፈል ስለተገኛችሁ እኔም

ወ/ሮ ዝናሽ ታያቸውም እጅግ አድርገን እናመሰግናለን፤ ስለነበረን ጊዜ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ። ኑሩልን፣ ክበሩልን ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር።

**ግንቦት 16 ቀን 2015 ዓ.ም**
**አዲስ አበባ**



የመደመር ትውልድ


የጉራጌ ዞን ህዝቦች
የሰላምና የልማት የምክክር መድረክ



# ከጉራጌ ሕዝብ ተወካዮች ጋር የተካሄደ ምክክር

መጋቢት 17 ቀን 2015 ዓ.ም

ብዙ ሰዎች ጉራጌን በትክክል ስለማያውቁት በጉራጌ አጀንዳ እኛንና ጉራጌዎችን ነጣጥለው ማቆየት የሚችሉ ይመስላቸዋል፤ ግን ጉራጌን ስለማያውቁት ነው። እኛ ስንመጣ ጥሩ ውይይት እንደምናደርግና እንደምንግባባ ጥርጣሬ አልነበረንም፤ እኔ ወደዚህ ቢሮ ከመምጣቴ በፊት ቢያንስ በወር አንዴ እመጣ ነበር። ጉራጌ እዚሁ አሁን በተባለበት አካባቢ የቅድሙን የዋቤ ወንዝ እየተሻገርኩ እመላለስ ነበር። በደንብ ነው የማውቀው፤ ህዝቡንም አውቀዋለሁ፣ ሀገሩንም አውቀዋለሁ፣ አውቃችኋለሁ። በዚያ ስሜት ነው ስለ ጉራጌ የማስበውም ከጉራጌ ጋር የምነጋገረውም። ለውጡን በሚመለከት እናንተ እውነት ስለሆናችሁ ጥንቃቄ መደረግ ያለበት ከመርካቶ የወጣውን ጉራጌ ወደ መርካቶ የመለሰ ለውጥ ነው ይሄ ለውጥ፤ እንዳታናንቁት ከሚሰራበት አካባቢ ሲገፋ የነበረውን ጉራጌ ወደ ሥራ ቦታው የመለሰ፣ ኢትዮጵያ መግባት አትችሉም የተባሉ የጉራጌ ልጆች ኢትዮጵያ መግባት ብቻ ሳይሆን ለሚቀጥለው ምርጫ እንዲቀሰቅሱ እድል የሰጠ ለውጥ ነው።

እናም ለውጡ የእናንተ ነው፣ እውነት ነው ታግላችኋል፣ ለፍታችኋል፤ ለውጡም በዚያው ልክ የጉራጌን ሃሳብና ፍላጎት ለማድመጥ የሚሞክር ነው። በተሟላ መንገድ ነወይ የጉራጌ ጥያቄ የተመለሰው ካላችሁኝ? አይደለም። ዛሬም ነገም አይመለስም፤ ዱንያ ብላሽ እኮ የተባለው ስለማትሞላ ነው እኮ፣ የሚሞላ ዓለም የለም። እንጠይቃለን ይጨመራል፣ እንጠይቃለን ይጨመራል እንጂ የሚቆም ነገር አይደለም፤ ከቆመም ትክክል አይደለም መርካት አያስፈልግም። ለጉራጌ ህዝብ ያለውን ትርጉም እኔ ለመናገር በጣም እቸገራለሁ፣ በጉራጌ አባባል ‹‹ ምን ትበያለሽ ፍቅር፣ ምን ትለብሻለሽ ሰላም›› ይባላል፤ ይህን የሚል ህዝብን ስለ ሰላም ስለ ፍቅር መናገር እኔ እቸገራለሁ። ሰላምና ፍቅር የምትናገሩት ብቻ ሳይሆን የምትኖሩት ነው፣ በየቀበሌውና ወረዳው ኢትዮጵያ ውስጥ ብትኖሩ ትናንሽ ኪዮስክ የሚከፍት የጉራጌ ተወላጅ ዱቤ አበድሮ ብሩ ባይመለስልት ‹‹ዋ በህግ አምላክ ብዬሃለሁ ብሬን አምጣ›› ነው እንጂ የሚለው ልደባደብ አይልም። በገዛ ብሩም ቢሆን ህግ ይጠራል እንጂ አይደባደብም። ሰላም ወዳድ ነው፣ ይሄ የኖርንበት የምናውቀው፣ ያበላን፣ ያሳደገን ማህበረሰብ ስለሆነ

በልበሙሉነት መናገር እንችላለን። ስለ ሰላም ወዳድነቱ፣ ስለ ሥራ ወዳድነቱ ምንም ጥያቄ የለውም።

ቀደም ሲል እህቴም በርካታ ሰዎችም እንዳነሳችሁት ማንኛውም ጥያቄ በውይይት፣ በምክክር፣ በእርጋታ ወይም በሰብር ይፈታል። ሰብር ያስፈልጋል ለሁሉ ነገር። ያ ካልተከበረ በስተቀር ውሃ እየጠየቅን የቧንቧ መስመር የምንሰብር ከሆነ፣ መንገድ እየጠየቅን ድልድይ የምናፈርስ ከሆነ ወደምንፈልገው አያደርሰንም፣ ወደምንፈልገው ነገር የሚያደርሰን በተረጋጋ መንገድ ተወያይተን ተመካክረን ጊዜ ወስደን ምላሽ መስጠት ስንችል ነው። ለዚህ ነው ጉራጌ << የተሻለውን መንገድ ያወቀ አይጥ ከፈረስ ይቀድማል>> የሚለው። አይጥ ሲጓዝ ቀስ ብሎ ነው፤ ፈረስ ሲጓዝ ደግሞ ፈጣን ነው፤ ግን ዋናው ፍጥነት የሚወሰነው የተሻለውን መንገድ በማወቅ ነው፣ የሚያዋጣውን መንገድ በማወቅ ነው። ክልልን በተመለከተ ለሚነሳው ጥያቄ እዚሁ አዳራሽ ከዛሬ ሦስት አራት ዓመት በፊት መጥቼ ክልል እንሁን ስትሉኝ ጉራጌ እንዴት ክልል ይጠይቃል ኢትዮጵያም ትጠበዋለች ብያችሁ ነበር ታስታውሳላችሁ። ጉራጌ እንደማንኛውም አካባቢ ሙሉ መብት ሙሉ ብቃት አለው፣ ጉዳዩ የትኛው ይበጀዋል ብሎ ማሰብ ነው። ከዚህ ከእናንተ ከተመለስን በኋላ ኮሚቴ አቋቁመን በደቡብ ክልል ውስጥ ሰፊ የክልል እንሁን ጥያቄ ስላለ የጥያቄውን መነሾ፣ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ መርምራችሁ ሃሳብ አቅርቡ ብለን ጊዜ ወስደን በኮሚቴው ተጠንቷል።

አሁን ኢትዮጵያ ባለችበት ሁኔታ በርከት ያለ ሚሊየን የህዝብ ቁጥር የሌላቸው ክልሎች እንኳን የውሃና የመንገድ ጥያቄ ሊመልሱ የሠራተኛ ደሞዝ መክፈል አይችሉም፣ ልማት አያመጣም። ምክንያቱም ደርግ ወድቆ ኢ.ህአዴግ ስልጣን ሲይዝ የኢትዮጵያ መንግሥት ሰራተኞች ቁጥር 230 ሺህ ነበር። በሀገር ደረጃ ዛሬ 2.5 ሚሊየን በልጧል። ሠራተኛው በየቦታው ወረዳ፣ በየቦታው ዞን ስለሚባል። መጀመሪያ ዞን አድርገኝ ይላል፣ ቀጥሎ ኮብራ አምጣ ይላል።

ባለስልጣን እናበዛለን እንጂ ልማት አናመጣም፤ የህዝቡን ችግር አይፈታም። ሰብሰብ ሰብሰብ አድርገን እንደ ባህሉ እንደ ወጉ በሚያቀራርበው እናደራጅ በሚል ጥናት ቀረበ። ጉራጌን እኛ ያየነው እዚህ ወልቂጤ አካባቢ ያለውን የጉራጌን ቤተሰብ ትቼ ማረቆ፣ ቀቤና እነሱን ትቼ ሃላባ ጉራጌ የአጎቱ ልጅ ነው ርቀትም ቢሆን ቤተሰብ ነው፣ ሃድያ የርቀትም ቢሆን የአጎት ልጅ ነው፣ ከንባታውም ስልጤውም አጎት ልጁ ነው፤ ቤተሰብ ነው፤ ክልል ክልል እያለ ሲሄድ ይበልጥ ይራራቃል። ግን ሰብሰብ አድርገን

ብናደራጀው ጉራጌ ብቻ ሳይሆን የጉራጌ ጎረቤቶች ሁሉ ሥራ ወዳድ ስለሆኑ በፍጥነት የመልማት እድል አለው። አንደኛ አማካኝ ነው፣ ሁለተኛ ቂጥሩም ደሞዝ ለመክፈል እንኳን አይቸገርም ላስተባብር እንኳን ቢል ሰፋ ያለ የተማረም ሀብት ስላለው ቶሎ ልማት ሊያመጣ ይችላል።

ታች ደግሞ ኦሞ አካባቢ ያለውንም ሰብሰብ ብናደርግ፣ ምዕራብ አካባቢ ያለውንም ሰብሰብ ብናደርግ በአንድ በኩል በርቀት ምክንያት የመልካም አስተዳደር ጥያቄ የሚነሳባቸውን እንመልሳለን። በሌላ በኩል ደግሞ ልማት እናፋጥናለን። ከዚህ ሃዋሳ ከመሄድ ከ100 ኪሎሜትር ባነሰ አካባቢ ውስጥ ሴንተር እየፈጠርን ከሄድን ኦሞውም፣ የምእራቡም፣ የሸዋውም አይቸገርም። በቅርበት አገልግሎት ሊያገኝ ይችላል በሚል በቀና እሳቤ ነው ጥናቱ ቀርቦ ተውያይተን፣ ተመካክረን በርካታ ጊዜ ከተወያየን በኋላ ወደዚህ ውሳኔ የመጣነው።

ይህን ውሳኔ በሚመለከት እርስዎ ስለመጡ ዛሬ ምላሽ እንደምናገኝ ተስፋ እናደርጋለን ላላችሁት እኔ ብጠየቅ  የምመልሰው ጉዳይ አይደለም፣ ባለፈው ስታነሱ ህዝቡ ጥያቄ አለው አጥኑና ኑ እንወያይበት ይህን አደረጃጀት እንመልከተው ማለት ስራዬ ነው። ከዛ በኋላ ለእናንተ ቀርቦ ተወያይታችሁበት ይጠቅማል ይበጃል ካላችሁ ያን ሃሳብ የምትውስዱበት ፤አይበጅም ካላችሁ አማራጭ መንገድ የምትፈልጉበት እንጂ በየስብሰባው ተገናኝተን ዩኒቨርሲቲ እሺ፣ መንገድ እሺ፣ ክልል እሺ የምንል ከሆነ በየሄድንበት ጥያቄ አለ። የትኛውም የኢትዮጵያ አካባቢ ብትሄዱ ጥያቄ አልቦ ወረዳ፣ ጥያቄ አልቦ ቤተሰብ፣ ጥያቄ አልቦ ግለሰብ የለም። ሁሉም በጥያቄ የተሞላ ነው።
ግን በእርጋታ፣ በስክነት፣ በውይይት ማየት ይጠቅማል። የኔን ሃሳብ የጠየቃችሁኝ እንደሆን እንደ ባዳ ሳይሆን እንደ ቤተሰብ ሸዋ ክላስተር ለጉራጌ ይጠቅመዋል ብዬ አምናለሁ። ብዙ ነገር ስለማይ በደሞዙም በልማቱም ። እንበልና ተሳስቼ ከሆነ ሰው ስለሆንኩ ስቼ ከሆነ ምን ችግር አለው ሦስት ዓመት አራት ዓመት እናይና ተሳስተሃል የሚያዋጣው መንገድ እሱ አልነበረም የሚሻለው መንገድ ይሄ ነው ብለን መወሰን፤ መስከን፣ መረጋጋትና መወያየት እንጂ የሚያጨቃጭቅ ጉዳይ አይደለም። ምክንያቱም የመዋቅር አደረጃጀት ታክቲካል ነው፤ የሰውን ጥያቄ ሁሉ የሚመልስ አይደለም። አንዳንዴ አንዳንድ ወዳጆቻችን ሲናገሩ የፌደራል ሥርዓቱ አደረጃጀቱ አሁን ያለው አደረጃጀት ቢፈርስ ኢትዮጵያ ሰላም ትሆናለች ይላሉ። አትሆንም ምክንያቱም ኢትዮጵያ 14 ክፍለሀገር በነበረችበት ወቅት አደረጃጀቱ እንደ አሁኑ አልነበረም ነበር በሰሜን ጦርነት፣ በምስራቅ ጦርነት፣ በምዕራብም ጦርነት ነበር።

የኢትዮጵያ አደረጃጀት ሰላም የሚያመጣ ከነበር ለምን በደርግ ጊዜ ስንዋጋ ኖርን፣ አደረጃጀት አንዱ መስሪያ መሳሪያ እንጂ ጥያቄው ሁሉ መመላሻ አይደለም፤ ያኔም ውጊያ ነበር አሁንም ችግር አለ። ላለፉት ሃምሳ ዓመታት ከሞላ ጎደል ሰላም አግኝታ አታውቅም። ሙቀቱ ከፍ ዝቅ ይላል እንጂ ሰላም አግኝታ አታውቅም። አሁን የማህበራዊ ሚዲያ ስላለ በስፋት ስለተነገረ እንጂ ላለፉት ስልሳ ዓመታት ያልተቋረጠ ጭቅጭቅ፣ ግጭት፣ ውጊያ፣ ንትርክ ነበረ። አሁንም ሰክኖ ተወያይቶ ሁላችንንም የሚያስማማ ነገር ነው ማድረግ ያለብን። ለእሱ ደግሞ የውይይት መድረክ እየተፈጠረ ነው። በዚያ የሚታይ ጉዳይ ካለ ይታያል። አሁን ያለው ግን ብዙ የሚያስቸኩል ነገር አይመስለኝም። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለምንድን ነው አንዳንዴ ወልቂጤ አካባቢ ችግር የሚፈጠረው ያላችሁ እንደሆነ አንዳንድ ጉራጌን እንወክለዋለን ብለው የሚያስቡ ግለሰቦች ከሌሎች ኃይሎች ጋር በመቀናጀት ጉራጌን የህዳር አህያ ማድረግ ይፈልጋሉ። የህዳር አህያ ማለት ህዳር ማሳ የሚሰበሰብበት ወቅት ስለሆነ ሁሉም የሚያሽከመው ማለት ነው፣ ጉራጌ የሰው አጀንዳ ተሸክሞ መንገድ የሚወጣበት ምንም ጉዳይ የለውም። በራሱ ጉዳይ በራሱ ሃሳብ ተወያይቶ ሥርዓት አለው ተነጋግሮ፣ ቀጠሮ ይዞ የፈለገውን አጀንዳ ይዞ ሊቀርብ ይችላል። የሌሎች አጀንዳ ተሸካሚ ማድረግ ግን ትክክል አይደለም።

ልማትን በሚመለከት እዚህ ያላችሁ ሰዎች እንደትገነዘቡ የምፈልገው ከጉራጌ ዞን አንድ ብር የሚወሰድ የለም፤ የምታስገቡት ገቢ የሚውለው ለእናንተ ነው። ክልል ከእናንተ ግብር እየሰበሰበ ልማት እንደከለከላችሁ መታየት የለበትም። ሁለተኛው ጉራጌ በየቦታው ሀብታም አለው ለተባለው ማን ከለከለው ታዲያ ለምን መጥቶ ኢንቨስት አያደርግም፣ ኑ ጉራጌዎች እስኪ ወልቂጤ ኢንቨስት አድርጉ፤ ማን ይከለክላችኋል? ገንዘብ ያላችሁ ሰዎች ኢንደስትሪም ይሁን፣ ትምህርት ቤትም ይሁን፣ የንግድ ማዕከልም ይሁን ኑና ገንቡ። የኢትዮጵያ መንግሥት በዚህ ሁሉ ውጥረት ውስጥ የሚሰራው ሥራ በጣም የሚያስደንቅ ነው፤ በመንገድም ይሁን በማንኛውም ልማት። ይህን ደግሞ ድፍን የአፍሪካ ሰዎች ሲመጡ ይነግሩናል። በሺህ ኪሎሜትር የሚቆጠር አስፓልት እየሰራን ነው። እኛ ልማት እናመጣለን ብቻ ሳይሆን ደጋግሜ እንደነገርኳችሁ እርግጠኛ ሆኜ የምነግራችሁ እኛ ከህዝባችን አንድ ብር አንሰርቅም። ባለን አቅም ሁሉ ሀገራችንን ለማልማት፣ አንድ ለማድረግ፣ ሰላም ለማድረግ ከመጣር ባሻገር ሰርቀን የምንወስድበት ቦታ የለንም፣ አንሻም ፣ አንፈልግም።

ነገር ግን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው አቅም መንገድ በበቂ ሁኔታ መስራት ይችላል ወይ ያላችሁ እንደሆን አሁን እየተሰሩ ያሉ መንገዶች ኮንትራት አንድ ትሪሊዮን ብር ደርሷል።

ኢትዮጵያ ውስጥ እየተሰሩ ያሉትን የመንገድ ስራዎች ለማስጨረስ የሚያስፈልገው ገንዘብ አንድ ትሪሊዮን ደርሷል። የኢትዮጵያ መንግሥት የአንድ ዓመት በጀት እዚያ ላይ አልደረሰም፤ የጀመርነውን መንገድ አይጨርስም እንኳን አዲስ መንገድ ሊሰራ ጊዜ ያስፈልጋል ማለት ነው። አትርሱ ጦርነት ውስጥ ነበርን፣ የዓለም መንግሥታት በግልጽ ባይናገሩትም መደገፍ በሚገባቸው መንገድ ያልደገፉን ጊዜ ነበር፣ ድርቅ ያጋጠመን ጊዜ ነበር፣ ብዙ ወጀቦች ያሉበት ጊዜ ነው። እንደዚያም ሆኖ እየተሰሩ ያሉ ስራዎች ተስፋ የሚሰጡ እንጂ ተስፋ የሚያስቆርጡ አይደሉም።

አሁን ትንሽ ጊዜ መረጋጋት ከቻልን ነገሮች ወደ ሰላም እየሄዱ ስለሆነ በውስጥ ያለንንም አቅምና ከውጭ የምናገኛቸውን ድጋፎች ጨምረን በርካታ የልማት ሥራዎችን ለመስራት እንሞክራለን ከእናንተ ድጋፍ ጋር። የማንፈጽመውን አንናገርም ምክንያቱም ይሄ ዘመን ካለፈ በኋላ ወይ ለመስቀል ወይ ለአረፋ ልንመጣ ስለምንችል። ያኔ ስልጣን ላይ እያለችሁ ዋሽታችሁናል እንድትሉን አንፈልግም። የምንችለውን ብቻ ነው የምንናገረው፣ ካቃተን ደግሞ ያው ከእናንተ የምንደብቀው የለም።

አሁን ለጊዜው የተነሱ ጉዳዮች አሉ መንገድ ተነስቷል፣ ውሃ ተነስቷል፣ ትምህርት ቤት ተነስቷል። የትኛውን አሁን መመለስ እንዳለብን ባላውቅም ቢያንስ አንገብጋቢ በሆኑ ጉዳዮች ከክልሉ ጋር ተወያይተን በምንችለው ልክ አጣዳፊ በሆኑ ጉዳዮች ውስጥ የሆኑትን በተለይ እንደ ውሃ ያለውን ምላሽ ለመስጠት እንሞክራለን። ከዋቤ ጋር በተነሳው ጉዳይ እንደተባለው የዋቤ ወንዝ ክረምት ከበጋ የሚፈስ ወንዝ ነው፤ ለብዙ ልማት ሊውል ይችላል ጥያቄ የለውም። እኛ ህዳሴንና ኮይሻን የሚያክል ፕሮጀክት አስር ሚሊየን ዶላር (በአፍሪካ ደረጃ ካሉ አምስት ትላልቅ ፕሮጀክቶች ውስጥ ሁለቱ እዛው የሚቆጠሩ ናቸው) እንኳን ለመጨረስ እየተሰቃየን አዲስ ነገር እንጀምራለን ብዬ ልዋሻችሁ አልፈልግም። ህዳሴ ካለቀ በእኔ እሳቤና እይታ ህዳሴ ለጉራጌ ዋቤ ነው፣ ኮይሻ ካለቀ ለጉራጌ ዋቤ ነው፣ እነሱ ካለቁስ? ባትጠይቁም እፎይታ ስናገኝ ዋቤም ይሁን፣ ዴዴሳም ይሁን አይቀርም። አሁን ግን ህዳሴን የሚያክል ቀንበር ተሸክመን እሱን ፈቀቅ ሳናደርግ ዋቤ ብዬ ቃል ልገባላችሁ አልፈልግም። ብዙ ጊዜ እንደዛሬው አስፓልት ሳይሰራ ተመላልሼበታለሁ አውቀዋለሁ። ቢለማ ደስታውን አልችለውም፤ አሁን የኢትዮጵያ መንግሥት እንደዚያ አይነት አቅም አለው ብዬ ልሸነግላችሁ ግን አልፈልግም። የእኛ ዋናው ትኩረት ህዳሴን መጨረስ ነው። እሱ ሲያልቅ እፎይታ ስናገኝ የተቀሩ ቦታዎችን ማልማታችን አይቀርም።

አሁን ሁሉም ነገር ተጠይቆ ሁሉም ነገር ምላሽ እንደማያገኘው ሁሉ እንደነ ዋቤ ያሉ በዚያ ደረጃ ያሉ ውሃዎች ቢገደቡ ለመስኖም ለኃይል ማመንጫነትም ከጉራጌ በላይ ብዙ የሚጠቅሙ ስለሆኑ ጥቅም የላቸውም ብዬ አላስብም። አጠቃላይ ጉራጌን በሚመለከት ለመልማት ከፍተኛ አቅም አለው። ለዚህ ነው በቅርቡ አንዳንድ ባለሃብቶች ጋር ተነጋግረን ዘመናዊ እርሻ እየተጀመረ ያለው፤ ይስፋፋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። የክልሉ ፕሬዝዳንትም ብዙ ጥረት እያደረገ ስለሆነ ይሄ ቢሰፋ፣ ይሄ ኮሪደር ወሊሶን ጨምሮ እስከ ወልቂጤ ያለው አካባቢ በጣሊያን ጊዜ አንደኛ ስንዴ አምራች የሚባለው ይህ አካባቢ ነው። ደቡብ ምዕራብ ሸዋ የሚባለው ቀጣና ማለት ነው። አቅም አለው፥ የከርሰምድር ውሃም አለው፣ ወራጅ ውሃም አለው። እነዚህን ወደ ልማት ቀይረን ሀገራችንን የሚያጠግብ ምርት ማምረት አለብን። ፍራፍሬዎች ያስፈልጋሉ ትክክል ናችሁ። ጅማሮዎች ስላሉ እነሱን እናስፋፋለን። ፋታ ብቻ ካገኘን እናስፋፋለን። ትምህርት ቤት የሚገነባው፣ዳቦ ፋብሪካ የሚገነባው፣ ማእድ እናጋራ የሚባለው፣ ጓሯችንን እናልማ የሚባለው ሰው እንዳይቸገር ነው በጋራ እንድንለማ ነው። ወደፊትም እንደዚሁ ሰዎችን እያስተባበርን የልማት ስራዎችን እንሰራለን። በዚያ ውስጥ እናንተ በማልማትም ከልማት በመጠቀምም አካል ትሆናላችሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ነገር በአንድ ጊዜ ስለማይሆን በትዕግስትና በርጋታ ቀስ ቀስ እየተባለ ብንጠብቅ ልማቱ አይቀሬ ጉዳይ ነው። ብልጽግና ያልነው እኮ ልማት ስለሚያስፈልግ ነው። አሁን አዲስ አበባ ላይ ለውጥ ታይቷል ሥራ ሠርታችኋል ተብሏል። አዲስ አበባ ላይ ሥራ ሥንጀምር በሁለት ሦስት ዓመት የሚታይ የሚጨበጥ ለውጥ እናመጣለን ብለን ነው የጀመርነው፤ አሁን ሥራ ውስጥ ከገባን በኋላ ግን ሌላ አስር ሃያ ሰላሳ እጥፍ ሥራ እንደሚጠበቅብን ነው የገባን። ገባ ስትሉ ብዙ ጉድ ስላለ ማለት ነው። አዲስ አበባም ቢያድግ ጉራጌ አደገ፣ ኦሮሞ አደገ፣ አማራ አደገ ማለት ነው።

የሁላችንም ስለሆነ ወልቂጤ ውስጥ ስንት ሰው እንዳለ ታውቃላችሁ? ጉራጌ ብቻ ነው እንዴ ወልቂጤ የሚኖረው? አይደለም፣ ለሁሉም ነው ወልቂጤ የሚያድገው፣ ለሁሉም ነው ጂማ የሚያድገው፣ ለሁላችንም ነው ኢትዮጵያ የምታድገው። በዚህ እሳቤ አብረን ብንሰራ ጥሩ ነው። በየትኛውም ጊዜ ያልተመቻችሁ ነገር ሲኖር በሰላማዊ መንገድ ጥያቄ መጠየቅ መብታችሁ ነው።

የማትችሉት ነገር ድንጋይ መወርወር ነው፣ እሱን አትችሉም፣ ሰላማዊ ማለትና ድንጋይ መወርወር ተለያየ ነገር ነውና። በሰላም ይሄ ይገባናል ፣ ይሄ ይመለስልን ማለት ችግር የለውም። ከዚያ ያለፈ ነገር ግን ትክክል አይደለም። ምክንያቱም ከዚህም ከዛም ሰው

ይጎዳል፣ እየተዳማን ደግሞ አብሮ መኖር ከባድ ነው። እንደዚያ እንዳይሆን ሰላማዊነትን የተከተለ አካሄድ ብንሄድ ጥሩ ይመስለኛል። እንደዛ ካደረጋችሁ አብዛኛው ነገር መልስ ያገኛል። ባለፈው ለነበረው ስህተት ያው የደም ቅጫ ስላላችሁ ነው በእናንተው ስርዓት በእናንተው ደንብ መፍትሄ አብጁለት። በመጨረሻ መናገር የምፈልገው ጉዳይ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ቸሃ፣ እነሞርና ሶዶ እየተባለ የሚጠራው ነገር ሁሉም በሰፈሩ የራሱ ቋንቋ፣ ባህልና ቤተሰብ አለው ሊከበር ይገባል። ግን እያንዳንዱ ንግግራችን ሰብሰብ የሚያደርገንና የሚያጠናክረን መሆን አለበት እንጂ የሚያለያየን ሊሆን አይገባም። እንደዚያ ከሆነ እንጎዳለን አሁንም። የጉራጌዎች አባባል አለ << ሃረጉን ሳብ ዛፉ እንዲሰበሰብ ይላሉ>> ጫካ ውስጥ ሀረጉ ሳብ ሳብ ሲደረግ ዛፉ ሰብሰብ ይላል። እናንተም ሳብ ሳብ እያደረጋችሁ እዚህ ያለው ሰባት ቤት ማረቆውን፣ ቀቤናውን ራቅ ሲልም ሃድያውን፣ ከዛም ከራቀ በሻሻውን ሳብ እያደረጉ አማች እየሆኑ መስፋት ነው እንጂ መከፋፈል አያስፈልግም። ይሄ ማለት አንደኛው ሌላኛውን ያጥፋው ማለት አይደለም። ተከባብራችሁ፣ ተዋዳችሁ ኑሩ። በጣም የሚያሳፍረው ነገር የቀቤና ሙስሊም፣ የማረቆ ሙስሊም፣ የእነሞር ሙስሊም ወይም የሰባት ቤት የሆነ ሙስሊም ረመዳን ጾሞ በጋራ አተራዊ ይሰግዳሉ፣ ሙስሊሞች ስለሆኑ በጋራ ይሰግዳሉ።

<< አይ ማረቆ ስለሆንክ ከአንተ ጋር አልሰግድም ወይም ቸሀ ስለሆንክ ካንተ ጋር አልሰግደም>> አይሉም። መቸም ይህ አንድ የሚያደርጋቸው አንድነት ይበልጥ የሚያቀራርብ መሆን አለበት እንጂ የሚያራርቅ መሆን የለበትም። አሁን ፋሲካን የሚጾሙ ክርስትያኖች ከአንድ አካባቢ ብቻ ናቸው እንዴ? በየብሔሩ እኮ ክርስትያኖች አሉ በጋራ የሚጾሙ፣ አብረን ነው የሚያምርበን፣ ተውት የሰፈሩን ነገር፣ ተከባበሩ ቋንቋችሁ ይከበር፣ ችግር የለውም። እንኳን እዚህ ያለውን ማረቆ ተውና ከተቻለ ከበሻሻም የት ነህ ብላችሁ አምጡ። እሱ ነው የሚያዋጣ፣ ሰፋ ባለ ማዕቀፍ ውስጥ ባህል ስላላችሁ፣ ሥርዓት ስላላችሁ ከሁሉም የሀገር ሽማግሌ ተወጣጥቶ ቁጭ ብላችሁ ተወያዩ። አሁን ምን እያደረግን ነው ያለነው? ስንት ሺህ ዓመት አብረን ኖረን አሁን ምን እያደረግን ነው ያለነው? መሄጃስ አለን ወይ? አልተጋባንም? አልተዋለድንም? አብረን አልኖርንም? ብላችሁ ብትወያዩ ብትመካከሩ ጥሩ ነው።

በእኛ በኩል ጥያቄዎቻችሁን በሙሉ ይዘናል፣ ከክልል አመራሮችና ከሌሎች ክልሎች ጋር እንወያይበታለን። እንዴት አድርገን ነው የጉራጌን ህዝብ ጥያቄዎች በተራ መመለስ የምንችለው ብለን ከፍተኛ ማድረግ የምንችለውን ጥረት እናደርጋለን። በእናንተ በኩል ግን በትዕግስት መጠበቅን አትዘንጉ። ሌላው ዛሬ የውሃን ጥያቄ መለስን መንገድን ዛሬ ቢያቅተን ነገ እንመልሰዋለን፣ መንገድን ነገ መልሰን መብራት ነገ ቢያቅተን ከነገ ወዲያ

እንመልሰዋለን ችግር የለውም። ሰክነን ብቻ እንወያይ፣ በእርጋታ ብቻ እንወያይ። በዚያ መንፈስ ብንሄድ የሚጠቅመን ይመስለኛል። ጉራጌን ይዘን ወደ ሰላም፣ ብልጽግና፣ ፍቅርና ወደ አንድነት እንደምንሄድ ተስፋ አደርጋለሁ።

ነገር ግን የማህበራዊ ሚዲያውን በሚመለከት፤ ጉራጌዎች እንደምታውቁት በመንገድ ስትሄዱ መጥፎ ጠረን ያለው ነገር ከርቀት ይረብሻችኋል። ጥሩ ጠረን ያለው ግን ቀረብ ካላሉ አይገኝም። እኛም ካልቀረብን ጠረናችን እንደነዛ በቶሎ አይገኝም ወይም አይጮህም። ሰምታችሁናል መዐዛው የሚጣፍጥ፣ የሰከነ፣ ሀገር አንድ የሚያደርግ፣ በትጋት የሚያምንና በቅርበት የሚታይ ስብስቦች ነን። በመጮህ፣ በማስጮህ፣ በመሳደብና በመገፋፋት ኢትዮጵያ ውስጥ ድል አላመጣም፣ ሰላም አላመጣም ወደፊትም አይመጣም። ተከባብረን ተዋደን እንደ ወንድማማች ተደማምጠን ብንኖር ይሻለናል። ያ ነው መፍትሄ የሚያመጣው ብዬ የማስበው። በዚሁ አግባብ የጉራጌ ጉዳይ መስመር እየያዘ ይሄዳል። ስለመጣሁ በጣም፣ በጣም ደስ ብሎኛል። ደጋግሜ ለምምጣት ያብቃኝ።

**መጋቢት 17 ቀን 2015 ዓ.ም**
**ወልቂጤ**







# የአጼ ፋሲል ቤተመንግሥት ጉብኝት

መጋቢት 22 ቀን 2015 ዓ.ም

ዛሬ በፋሲለደስ ጥንታዊ ቤተመንግሥት ቅጥር ግቢ ውስጥ ነው የምንገኘው። በዚህ ስፍራ አባቶቻችን የሰሩት እጅግ አስደናቂ አስደማሚ ጥበብ የእጅ ሥራ ይታያል። እንግዲህ በጥንቱ ዘመን የአክሱምንም፣ የዛጉዌም ፣ የፋሲልንም ስናይ የተገለጠላቸው የገባቸው ኢማጇን ማድረግ የሚችሉ፣ በእጦት እሳቤ ያልተያዙ፣ አቅም፣ እውቀት፣ ጥበብ ካለበት ማምጣት፣ መሰናሰል፣ መደመር የሚችሉ አባቶች እንደነበሩን በደንብ ያሳያል። ቅድም እንደሰማነው ብዙ የሚገርሙ ነገሮች አሉ።

ስፋቱ ብቻ ሳይሆን የቦታ ምርጫው፣ ለእይታ ያለው ምቹነት፣ ከዛም ባሻገር ፈንክሽናሊቲው፣ መመገቢያው፣ ፈረስ ማሰሪያ ፓርኪንግ ነበር፣ በጣም በጣም ደግሞ የሚገርመው የመጸዳጃ ቤቶች ብዙ ጥንታዊ ቤተመንግሥቶች በምንመለከትበት ጊዜ አናይም። መጸዳጃ ቤት አውሮፓም የቆዩት እንደዛ ብዙ የላቸውም።

በጥንት ዘመን መመገቢያ ስፍራ ግን በተናጠል ሳይሆን በጋራ በአዳራሽ መመገብ፣ የትራንስፖርት ሲስተም ሲመጣ የሚቆይበት ቦታና ቤተመጻሕፍት ወይም የሃይማኖት ትምህርት የሚማሩበት ስፍራ፣ መኝታ ቤት አሠራራቸውና ለእይታ ያለው ምቹነት አጠቃላይ ዲዛይኑና ሥራው የሚያሳየው የተገለጠላቸው፣ የበራላቸው፣ የማይታየውን ማየት የሚችሉ ሰዎች እንደነበሩ ሥራው በሙሉ ያመላክታል። ከዚያ ባሻገር በገለጻው እንደሰማችሁት ከከምባታ አካባቢ በዚያ ዘመን የነበሩ ከድንጋይ ጋር የሚያያዙ ሙያዎችና ሥራዎች እዚህ ቦታ ተንጸባርቀዋል፣ ከጉራጌ ሊቃውንት መጥተዋል፣ ከኦሮሞ በውትድርና የሚያገለግሉ በዚህ ሥራ ተሳትፈዋል፤ ድሮ በጋራ፣ በትብብር፣ በአንድነት አንዱ ያለውን ከሌላው አምጥቶ ያማረ፣ የተዋበ፣ የላቀ ነገር መስራት ነበረ፤ አዲስ ነገር አይደለም።

የእኛ ችግር ያን በቅጡ መገንዘብና ጠቀሜታውን አውቆና አጉልቶ መጠቀም ላይ ውስንንት አለ። በቅርቡ አንድ የሚያስገርም ታሪክ ሰማሁ፣ ለዚህ ነገር የሚጠቅም። አንድ አባትና ልጅ ይጨቃጨቃሉ። አባት ‹‹የልጅነት ወጉ እንደዚህ አይደለም አነጋገርህ እንዲህ መሆን አለበት፣ አለባበስህ እንዲህ ነው የጸጉር ቁርጥህ መስተካከል

አለበት›› ብሎ ይመክረዋል ልጁን፤ ልጁ የተሻለ ሰው እንዲሆን አመጋገቡን፣ አለባበሱን፣ አዋዋሉን ይገስጸዋል፣ ይመክረዋል። እናም ልጁ አባቱ ብዙ እንዳልገባው፣ እንዳላወቀ፣ እንዳልሰለጠነ ለማስረዳት ስለፈለገ ‹‹አባቴ ምን መሰለህ የእኔና የአንተ አስተዳደግ ዘመን የተለያየ ነው። አንተ ባደግህበት መንገድ እኔ እንዳድግ አትጠብቅ፣ ባንተ ጊዜ ቴክኖሎጂ አልነበረም፣ ኮምፒውተር የለም፣ ቴሌቪዥን የለም፣ እንዲሁም ዘመናዊ መኪናዎች የሉም፣ አንተም ብዙ እድል አልነበረህም። አሁን እኔ የምኖረውን ኑሮ ለመኖር፣ የማድገውን እድገት ለማደግ እያነጻጸርክ አንተን እንድመስል አታድርገኝ›› ይለዋል ልጁ። አባትም አሰብ ያደርግና ‹‹እውነትህን ነው እኛ ስንማር ስናድግ ኮምፒውተር አልነበረም፣ ቴሌቪዥን አልነበረም፣ ዘመናዊ መኪናም አልነበረም አሁን የምታያቸው ምቹ ትራንስፖርት ሲስተሞች አልነበሩም፣ ብዙ ችግር ነበሩብን። ያንን ችግር ተገንዝበን ኮምፒውተር ፈጠርን፣ መኪና ፈጠርን፣ ቴሌቪዥን ፈጠርን። አንተ እኛ የፈጠርነውን በመጠቀምህ ከእኛ የላቅህ መስሎ ይሰማሃል ግን የፈጠረው የእኛ ትውልድ ነው። ለአንተ ትውልድ ክፍተት አይተን ሞላንልህ፣ አመቻቸንልህ እንጂ አልፈጠርከውም የፈጠርነውንም በአግባቡ መጠቀም አልቻልክም›› ብሎ መለሰለት ይባላል።

የእኛ ነገር እንደዚህ ነው። አባቶቻችን ፈጥረዋል፣ ኢማጅነሪ አቅምን አሳይተዋል፣ ብቃት አሳይተዋል። እኛ ግን እንዴት እንደሰሩትም አላወቅንም፣ የትብብር መንፈሳቸውን አላወቅንም፣ ሀገር ወዳድነታቸውን አላወቅንም፣ የሰሩትን መጠገን አልቻልንም እንደምናየው ፈርሷል። ነገር ግን እነሱን እንደማያውቁ እንዳልገባቸው አስበን፣ ሳናውቅ ያወቁትን ንቀን፣ ሳይገባን የገባቸውን አራክሰን፣ ሳይገለጥልን ያየን መስሎን እንዲሁ በከንቱ የምንባዝን መሆናችንን የሚያሳይ ነው። አሁን ወደ ቀልብ መመለስ ነው ያለብን። ፋሲል ኢትዮጵያዊያን ባለቸው ሃብት፣ ባላቸው አቅም፣ ባላቸው ስጦታ በዚያ ዘመን ተባብረው አስደናቂ ነገር አስቀምጠውልናል። እኛ ይህንን መድገም እንኳን ባንችል ጠግነንና አሳምረን ለትውልድ ማሸጋገር አለብን።
ለዚህ ነው የመደመር ትውልድ መጽሐፍ ገቢው ይህንን ሥራ ለመስራት እንዲውል የታሰበበት ምክንያት፣ ዋናው ዓላማ ይህንን ታሪክ መስራት እንኳን ባትችል ጥበቡ፣ የስራቱ መጠን፣ አስፈላጊነቱ ገብቶህ ጠግነህ ለትውልድ አሸጋግረው የሚል እሳቤ በውስጡ ስላለ ነው።

ዛሬ ባየሁት ነገር በጣም ተደስቻለሁ። ብዙ ጊዜ መጥቸ አይቼዋለሁ፣ ጎንደርን በደምብ አውቀዋለሁ፣ ፋሲልን በደምብ አውቀዋለሁ። የገባኝ ነገር የእኛ ትውልድ ይህንን

ነገር ወደነበረበት ከቻልንም አልቀን ማሸጋገር ግዴታችን እንደሆነ ነው። እናም ያለኝ ጥሪ የፖለቲካ አመለካከት፣ የእምነት ልዩነት፣ የቋንቋ ልዩነት፣ የሰፈር ልዩነት ሊኖር ይችላል። ፋሲል ግን ሀብታችን ነው፣ ተባብረን መጠገን አለብን፣ ተባብረን ማስዋብ አለብን፣ ተባብረን ማቆየት አለብን። እንዳይፈርስ ማድረግ አለብን።

ለዚህ የተነሳውን ልብ በፖለቲካ፣ በእምነትና በብሔር ካሳነስከው አንሰህ ትቀራለህ። አባቶችህ እንደዛ አልነበሩም፤ አባቶችህ ከንባታ ሄደው የድንጋይ ሙያ ያላቸውን ለማምጣት፣ ጉራጌ ሄደው ጥበበኞች ሊቆች ለማምጣት፣ ኦሮሞ ሄደው ለማምጣት ችግር አልነበረባቸውም፣ ከትግራይ ለማምጣት ችግር አልነበረባቸውም። ለምን ያ የተደመረ እውቀትና የተደመረ ጭንቅላት የላቀ ነገር እንደሚሰራ ስለሚያውቁ። ዛሬ እዚህ ያየነው ነገር እጅግ የላቀ ድንቅ ሥራ ነው። ለምን የተደመረ ጭንቅላት ውጤትና የማየት አቅም ያላቸው ሥራ ስለሆነ። እኛ ማየት እንኳን ቢሳነን እነዛን ያዩ ሰዎችን አድንቀን ማቆየት ግን ያነሰውን ሥራ በሐላፊነት መውሰድ፣ መስራት እንደሚጠበቅብን እምናለሁ እንሰራዋለን። ከህዝባችን ጋር በትብብር እንሰራዋለን። ተጀምሯል፤ መልካም ሥራ ሆኖ አምሮ ለትውልድ እንደሚሸጋገር ተስፋ አደርጋለሁ ። እጅግ በጣም ደስ ብሎኛል አመሰግናለሁ።

**መጋቢት 22 ቀን 2015 ዓ.ም**

**ጎንደር**

# በዳጋ ቅዱስ እስጢፋኖስ የአባቶች አንድነት ገዳም የተካሄደ ጉብኘት

*መጋቢት 22 ቀን 2015 ዓ.ም*

አሁን የምንገኘው ዳጋ ነው። ዳጋ እጅግ በጣም ታሪክ ጠገብ ተፈጥሮ ጠገብ፣ ለዐይን የምትማርክ በውስጡም ብዙ በረከት፣ እውቀትና፣ ታይቶ የማይጠገብ የተፈጥሮ ጸጋ ያለበት ቦታ ነው ። ከዛም ባሻገር ዳጋ በባህርዳርና በጎርጎራ መካከለኛ ስፍራ ላይ የሚገኝ ደሴት ሆኖ ቆሞ መንቀሳቀስ የሚያስችል ቦታ ነው። እንዳያችሁት ሲበዛ ጫካ ነው፣ ተራራው የተለየ ከፍታ አለውና ይህን ቦታ ከታሪኩ ባሻገር ባቀማመጡና ባለው ውበት ለብዙዎች እይታ ይጋብዛል። ውስጥ ግን ገባ ስንል አስደማሚ ታሪኮች ለማየት ችለናል። ዳጋ በትንሹ ሰባት መቶ ዓመት የሚጠጋ ታሪክ አቅፎ የያዘ ቦታ ነው።

ትናንትና የአጼ ፋሲልን ቤተ መንግሥት ማየት ችለን ነበር፤ ዛሬ ደግሞ አጽማቸውን እዚህ ማየት ችለናል። እንዲሁም ጎርጎራ የአጼ ሱስንዮስን ቤተመንግሥትና ከባቢውን አይተናል። የሳቸውንም አጽም እዚህ አይተናል። ከሳቸውም በፊት የነአጼ ዳዊትን አጽም እዚህ አይተናል፣ በርካት ያሉ የቀደሙ ነገስታት አጽም እዚህ ቦታ አለ። ይሄ የሚያስተምረን ነገር በዚያ ዘመን ቤተመንግሥት ስፍራ መርጠው ትልቅ በሆነ መንገድ መስራታቸው ብቻ ሳይሆን እነሱም ካለፉ በኋላ የዚያ ዘመን አባቶች አጽማቸው ሳይፈርስ ለማቆየት አንዳንዶች እንዳያችሁት ጥፍራቸው ሁሉ ይታያል። በዚያ ደረጃ ለማቆየት የሚያስችል ጥበብና የልብ ስፋት፣ ጥበብ ብቻውንም በቂ አይደለም የልብ ስፋትም ያለበት ዘመን እንደሆነ ያሳያል። ወደኋላ ተመልሰን ታሪካችንን ስንመረምር ብዙ መፈተሽ ያለብን ነገር እንዳለ ያመለክታል። መጻሕፍቱ በብዙ ኪሎግራም የሚመዝኑ፣ በእጅ የተጻፉና በብራና የተጻፉ መጻሕፍት አይተናል። ዛሬ እነዚህን ለማጻፍ ሳይሆን እነዚህን መጻሕፍት ለማንበብ እንኳን ትዕግስት ምን ያክል እንዳለን መፈተሽ ያስፈልጋል። በድሮ ጊዜ የነበረ ሰው ታሪክን፣ እውቀትን፣ እምነትን፣ የሀገር ሀብትን በዚያ መንገድ ቀዳ ገፎ፣ አለስልሶ፣ ቀለም አቅልሞ፣ ጽፎ ማኖር ሲችል እኛ ያንን አንብበን ለማወቅ እንኳን ያለን ጉጉትና መሻት ስናይ በብዙ ራሳችንን መፈተሽ እንዳለብን ያመለክታል። ነገር ግን ዛሬ ቅሪቶች አይተናል። እዚህ ስፍራ ላይ አባቶች የአባቶቻቸውን፣ የሀገራቸውን ታሪክ ለማቆየትና ለማሸጋገር ያላቸውን ጉጉትና ፍላጎት እንዲሁም ታማኝነት፣ ለሀገራቸውና ለእምነታቸው ያላቸውን ቀናኢነት በደንብ የሚያሳይ በውስጡ ጥልቅ ጥበብና እውቀት ያለበት ስብዕና ማየት ችለናል፤ ይህ በጣም ብዙ ያስተምራል።

ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ መናገር የምፈልገው ነገር በመጀመሪያ ታሪካችንን፣ ጅማሯችንን፣ መነሻችንን ማወቅ ያስፈልጋል፤ ለማድነቅም፣ ለመጠበቅም፣ ለመጠቀምም የመጀመሪያው ነገር ማወቅ ነው። ስናውቅ እዚያ ውስጥ ያለው የሀብት ጥግ፣ የእውቀት ጥግ፣ የጥበብ ጥግ እየገባን እየተገለጸልን ስለሚሄድ ካወቅን በኋላ ሁለተኛው ዋናው ተግባር ማልማት ነው። ይህ ቦታ እጅግ ውብ የነበር ቢሆንም ከለውጡ በኋላ ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ ነው ይህ ቤተክርስቲያን በአዲስ መልክ የታነጸው። አሁን የምናየው ቤተመጻሕፍትና ሙዚየም እጅግ የሚገርም ነው። ይህን ሁሉ ተራራ ሰው ድንጋይ ተሸክሞ፣ ብረት ተሸክሞ ይህን የሚያክል ህንጻ መገንባት ቀላል ነገር አይደለም፤ ስናየው ቀላል ይመስላል ሥራው ግን ከባድ ነው። እዚህ የሚሰሩ ሰዎች በሳምንት አንዴ እንኳን ወደ ከተማ ለመሄድ እድል አያገኙም። ሥራውን ለማየት፣ በሥራው ለመሳተፍ፣ ሥራውን ለመደገፍ ሲያልቅም ደግሞ ታሪካችንን ለማጽናት የተሻለ ስፍራ ስለሚሆን ለዚህ መታደላችንን በትልቅ ክብር ነው እኛ የምናየው። የመጀመሪያው ነገር ማወቅ ነው፤ ሁለተኛውና አሁን እየሆነ ያለው ደግሞ ማልማት ነው፤ ይህን ቦታ ከማወቅ አልፈን የመጣንባትን ቦታ በትክክል ብናለማው፣ ሙዚየሙን ብናለማው፣ አካባቢውን ብናለማው ከልማት በኋላ የሚመጡ ጥቅሞች አሉ። ያወቀና ያለማ ይጠቀማል። ይህ ቦታ ብቻውን የኢትዮጵያን ክብር ይገልጻል፣ የኢትዮጵያን የእምነት ጥግ ያሳያል፣ ብዙ ሀብት ያመጣል ፣ የሚንቁን እንዲያከብሩን፣ የማያውቁን እንዲያውቁን ለብዙዎች ትምህርት መስጠት የሚችል፣ በጣም ግዙፍ ሲያዩት ያነሰ የሚመስል፣ በጣም ትልቅ ሀብት በእምቅነት የያዘ ቦታ ነው። ከማልማት ቀጥሎ ሦስተኛው መጠቀም ነው የሚመጣው። በዚያ ታሪክ፣ በዚያ ጥበብ፣ በዚያ እውቀትና በዚያ የልብ ስፋት መጠቀም ያስፈልጋል። መማር ያስፈልጋል ትውልድ እዚህ ቦታ መጥቶ ታሪኩን ቢያይ፣ እዚህ ቦታ ያሉትን አባቶች ቢያይ ብዙ እውቀት የሚቀስም ይመስለኛል።

ካውቅን፣ ካለማንና ከተጠቀምን በኋላ ግን ማሸጋገር ደግሞ ያስፈልጋል፣ ለትውልድ የሚልቅ፣ የሚያልፍ መሆን አለበት። ሰባት መቶ ዓመት አቆይተዋል አባቶች ባልተመቸ ሁኔታ። ሌላ ብዙ ዓመታትን መቆየት እንዲችል ደግሞ አሁን ያለው ትውልድ ማስተካከል፣ ማሳመር፣ ማስዋብና ማስተዋወቅ ያለበት ይመስለኛል።

ኢትዮጵያ ውስጥ በትክክልም የበራለት፣ የገባ ፣ የተገለጸለትና ተፈጥሮን ያከበረ አምላኩን ያመነ ትውልድ ነበር ማለት ነው። አሁን የሚያስፈልገን ነገር መንሳፈፍ አይደለም፣ መሬት መርገጥ ነው። ተፈጥሮን ማወቅ፣ ራስን ማወቅ፣ ሀገርን ማወቅ፣ ከባቢን ማወቅ፣ ፈጣሪን ማክበርና መገዛት ነው። እነዚህን ነገሮች በምናደርግበት ጊዜ

ያ የነበረው ገናናነትና ትልቅነት በዚያ ደረጃ ብቻ ሳይሆን አሁን ያለውን ዘመን በሚዋጅ ልክ ልንሰራው እንችላለን።

ይሄ ለእኛ በጣም፣ በጣም ትልቅ ተስፋ ነው፣ ዳጋ ላይ የሚገነባውን ማየት ለግንባታው ድጋፍ ማድረግ ፣ የአጼ ፋሲል ቤተመንግሥትን ማደስ፣ ጎርጎራን መልሰን ማደስና እነዚህን ታሪክ ማገናኘት መቻላችን ትልቅ እድለኝነት ነው። ብዙዎች ለማየት አልታደሉም እንኳን ለመስራት። እኛ ለማየትና በሚገነባው ውስጥ ለመሳተፍ እድል ካገኘን እንደ ትልቅ በረከት፣ እንደ ትልቅ ጸጋ ነው የምንወስደው። ኢትዮጵያዊያን በየቦታው የሚያኮራ ሀብት አለን፣ በጣም የሚያስደንቅ ታሪክ አለን፣ የሚገርሙ ሰዎችም አለን፣ ሙሉ ህይወታቸውን ለታሪካቸው ለእምነታቸው የሰጡ ሰዎችም አሉን ፤ በከተማ እንደምንሰማው ብቻ ሳይሆን ሰው የሚወዱ ፣ ሰው የሚያከብሩ፣ በፍቅር የሚቀበሉ፣ ታሪካቸውን በእንክብካቤ የሚይዙ አባቶችንም አይተናል። ይሄ ሁሉ ትምህርት ስለሆነ ከዚህ ተምረን የተሻለውን የላቀውን ለመስራትና ለማሻገር የምንበቃ እንዲያደርገን፤ ከምንናገረው ከምናስበው ባሻገር ሃሳቦቻችን መሬት ነክተውና ተፈጽመው የምናይበት ጸጋና የመከናወን ብቃት ፈጣሪ እንዲሰጠን እንዲያድለን ነው መመኘት፣ መለመን ያለብን።

እጅግ በጣም ተስፋ የሚሰጥ፣ የሚያስደስት፣ የሚያኮራ ታሪክ ነው ዛሬ ያየነው። ግን ኢትዮጵያ ትልቅ ሀገር ናት፤ የማትጠገብ በውስጧ ብዙ የያዘች ታሪክ ጠገብ፣ ሀብት ጠገብ አስደናቂ ሀገር ናት። ይህችን ድንቅ ሀገር ዜጎቿ ስለሆንን፣ ለማልማት እድል ስላገኘን፣ እድሉን ለመጠቀም ደግሞ ፍላጎት ስላለን ከህዝባችን ጋር ሆነን ፈጣሪያችንን እየለመንን በታማኝነት በማገልገል የላቀች ኢትዮጵያ ለሚቀጥለው ትውልድ እናሸጋግራለን የሚል ሙሉ ተስፋ አለን። ባየነው ተደምመናል ተደንቀናል፤ በዚህ ውስጥ ለመሳተፍ እድል ስላገኘንም ፈጣሪያችንን እናመሰግናለን። በጣም፣ በጣም ደስ የሚል ጊዜ ነው ያሳለፍነው። ብዙዎች በማየት የዚህ ደስታ ተካፋይ እንዲሆኑ እጋብዛለሁ አመሰግናለሁ።

**መጋቢት 23 ቀን 2015 ዓ.ም**
**ዳጋ እስጢፋኖስ**



# በጎርጎራ ፕሮጀክት የተላለፈ መልዕክት

መጋቢት 23 ቀን 2015 ዓ.ም

ጎርጎራ የብዙ ነገሮች ድምርና ውቅር ውጤት ስለሆነ በዚህም ምክንያት ነው የገዘፈና ያማረ ነገር የምናየው። ጎርጎራ ውስጥ ታሪካችን አለ፣ እድላችን አለ፣ ህልማችን አለ። ትናንትናችን ታሪካችን ነው፣ ዛሬ እድል ነው፣ ነገ ደግሞ በምናብ የምናየው ህልማችን ነው። ይህን Imagination, Memory and Opportunity ደምሮ የያዘ ቦታ ነው። እነዚህን ደምሮ በመያዙ እጅግ የተዋበና ያማረ ነገር እናያለን። ሁላችሁም እንደምታውቁት ከአምስት መቶ ዓመታት በፊት ገደማ አጼ ሱሲኒዎስ የነበሩበት መናገሻ ነው፣ ቤተመንግሥትም ነበር ከታሪክ አንጻር ዝምብሎ የሚረሳ የሚዘነጋ ቦታ ሳይሆን ታሪካዊ ቦታ ነው። ነገር ግን ያ ታሪካዊ ቦታ በትውልድ ቅብብሎሽ መካካል መጠበቅ ባለማቻሉ ያለውን ግርማና መስህብ እያጣ የሄደበት ሁኔታ ነበር። ያን ግርማውን እንዲያጣ የተደረገውን ነገር ዳግም እንዲወለድ ዳግም መፈጠርን፣ ዳግም መታደስን፣ ወደ ነበረበት ክብር መመለስን ብቻ ሳይሆን ልቆ መታየትን ያሳየንበት ቦታ ነው። እዚህ ጋ ታሪካችን ስላለ ሰሞኑን ያየነው የአጼ ፋሲለደስ ቤተ መንግሥት የአጼ ሱሲኒዎስ ልጅ ነው። ያን ስንጠግን አባቱን ደግሞ ከነበረበት በላይ ስናወጣ ሁለቱን ስናስተሳስር ታሪክ መሰናሰልንና የትውልድ መደመር ውጤትን እናይበታለን።

ያ ታሪክ ሳይዘነጋ ለዛሬ ደግሞ በጣም ትልቅ እድል ነው፣ ትልቅ የሚያኮራ ሥራ ነው፣ ነገ በልጽጋ አምራ ተውባ የምናያትን ኢትዮጵያ የምናይበት ቦታ ነው። በድምሩ ሲታይ ትናንትትን ዛሬንና ነገን ያስተሳሰረ ድንቅ ሥራ ነው ማለት ይቻላል። ሁለተኛው እዚህ ላይ እንድናስበው የምፈልገው ጉዳይ ተራራ አለው፣ የሚያምሩ ዛፎች አሉት፣ የተዋቡ እጅግ ያማረ መስክ አለው፣ በዐይን የማይጠገብ ሃይቅ የማይመስል እጅግ ማራኪ ውሃ አለ። ይህ ውሃ ጨዋማ ሳይሆን ንጹህ ውሃ ነው። አሁን ይህን ውብ ቦታ ምንድን ነው የጎደለው ስትል የገባታ ለሃገር ፕሮጀክት ነበር የጎደለው። ይህ ፕሮጀክት ካልሞላ ማንም ሰው ይህንን ውበት ሊያይ አይችልም። ዛሬ ግን እጅግ ግዙፍ የሆነ ምናልባት በአፍሪካ ውስጥ በዚህ ደረጃ ትልቅ የሆነ ሪዞርት ለመኖሩ እርግጠኛ አይደለሁም። እነዚያን ነገሮች ደምሮ የያዘ በምንም መመዘኛ የሚያኮራ ትልቅ ነገር ነው የሆነው።

ብዙ ጊዜ አንድ አካባቢ ላይ ድንጋይ ስናይ፣ ሳር ስናይ፣ ውሃ ስናይ ካለምክንያት የተፈጠረ ይመስለናል። ነገር ግን ተፈጥሮ ሁሌም ትክክል ነው፤ እያንዳንዱ ነገር ተመጋግቦ አንዱ ለሌላው ግብዓት ሆኖ የተሰራ ነገር ነው፤ እኛ አስተውለን አይተን የጎደለ ሞልተን ማውጣት ቢሳነንም ተፈጥሮ ግን አይሳሳትም። ዛፉ፣ ተራራው፣ ውሃው፣ መስኩ የነበረ ነው። የእኛ ሥራ ሲጨመርበት የተዋበና አንዱ ለሌላው ጌጥ ሆነ፤ ዛፉ ለቤቶቹ፣ ቤቶቹ ለእያታ እጅግ ያማረና የተዋበ ቦታ ሆነ። ሌላው ጎርጎራ ላይ ማየት ማስተዋል የሚገባን ብዙ ነገር ብዙ ቦታ <<በወይም>> የተያያዘ ነው፤ ሰፊ ነገር ወይም ትንሽ ጥራት ያለው ነገር፣ በቴክኖሎጂ የመጠቀ ነገር ወይም ባህላዊ ነገር እንጂ ብዛትንና ጥራትን አስማምቶ የማየት ነገር የለም ቢያንስ በሀገራችን የለም።

ጎርጎራ ላይ እንዳያችሁት በጣም ትልቅ ነው፣ በጣም ትልቅ ሥራ ነው ብዛትን ይመልሳል። በሌላ መንገድ ደግሞ እያንዳንዱ ነገር በከፍተኛ ጥራት የተሠራች ነገር ናት፤ ታሪካዊም ነው፣ የአጼ ፋሲልን ቤተመንግሥት መስሎ ተሰርቷል። ውስጥ ስትገቡ ደግሞ በጣም ወደፊት የተራመዱ ቴክኖሎጂዎችን ይጠቀማል <<በወይም ሳይሆን በእና>> የተያያዘ ነው። ቴክኖሎጂውንም ታሪኩንም፣ ቅርሱንም፣ ጥራቱንም፣ ብዛቱንም ደምሮ የያዘ ነው። በጣም ግዙፍ መሆኑ የጥራቱን ደረጃ ዝቅ እንዲያደርገው አልተፈቀደለትም፣ ግዙፍ ነው ጥራቱም አለ፣ አረንጓዴ ነው የእግር መንገዶቹ ታይተው አይጠገቡም ፣ ውሃው ታይቶ አይጠገብም፣ እያንዳንዱ የቤት ስሪት ካለበት ቦታ ሆኖ አካባቢውን ለመቃኘትና ለማየት ተስተካክሎ የተሰራ ነው። የጎርጎራን ፕሮጀክት ስናይ፣ የገበታ ለሀገርን ፕሮጀክቶች ስናይ ታሪካችንን ፈልፍለው አውጥተው ትውልድ ሊሞላው የሚገባውንና የጎደለውን ነገር ሞልተው ያሳዩ ናቸው።

የትውልድ ሥራ የነበረን ማነጽ፣ ማላቅ ፣ ማስቀጠል የሚለውን ያሳዩ ናቸው። አሁን በአዲሱ ገበታ ለትውልድ ደግሞ እንደዚሁ ታሪካዊነታቸውን፣ እድል ሆኖ መጥቀማቸውን በምናብ የምናያትን የምንመኛትን የበለጸገች ኢትዮጵያን ሆኖ የሚሰራ ነው። በአጭሩ ጎርጎራ የትም ሀብታም ሀገር ንጉስ፣ ፕሬዝዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ወይም በሆነ መንገድ የሚታወቅ የድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ደግሞ ሀብት ያላቸው ታዋቂ ሰዎች ቢመጡ በማንኛውም መመዘኛ የሚያኮራ የኢትዮጵያን ልክ የሚያሳይ እንጂ ምንም የሚያሳፍር ነገር የለውም። እያንዳንዱ ሥራ እያንዳንዱ ነገር ለማንም ለትልቁም፣ ለብዙውም፣ ለትንሹም በሚሆን መንገድ የተሰራ ነው። እዚህ መጥቶ የኢትዮጵያን ታሪክ ለመማር፣ የኢትዮጵያን ልክ ለማወቅ፣ ኢትዮጵያን ውበት ለማድነቅ፣ የኢትዮጵያን ህልሞች ለመገንዘብ ምንም ነጋሪ ሳያስፈልግ ጎርጎራን ብቻ በማየት የምኞታችንን ልክ እንዲያውቁ የሚያደርግ ቦታ ነው።

የእኔ ምክርና ምኞት ኢትዮጵያውያን ጎርጎራን ማየት አለባቸው። የዛሬ ሦስት ወር ገደማ ለህዝብ ክፍት ይሆናል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። አሁን የምጠብቀው ወቅት ነው፤ ማለቅ የሚገባቸው ሥራዎች አሉ። ከማጠናቀቂያ ሥራዎች በተጨማሪም የተከልናቸው ዛፎችና ሳሮች ውሃ ስለሚፈልጉ ጊዜ የምንፈልግበት ወቅት ነው። ይሄ ተደምሮ ሰኔ፣ ሐምሌ አካባቢ በሙሉ ያልቃል። በተለይ በሚቀጥለው መስከረም፣ ጥቅምት፣ ህዳር አካባቢ ከክረምቱ በኋላ ብዙ ነገር ቦታ ቦታውን ስለሚይዝ እጅግ ውብ፣ አስደሳች፣ አስደማሚ ቦታ ይሆናል። ኢትዮጵያዊያን ማየት አለባቸው፣ ማሳየት አለባቸው፣ ማድነቅ አለባቸው፣ ሰዎች ደግሞ እንዲያደንቁ ማስተማር አለባቸው። ለምን የተባለ እንደሆን የታሪካችን ማሳያ ነው፣ ታሪካችንን የምናመላክትበት የምናስተምርበት ቦታ ነው፣ ተስፋችንንና ህልማችንን የምናሳይበት ቦታ ነው፣ ሁለቱን ደምሮ ይዟል።

እኛ የነበረውን ታሪክ ጠብቀን ይዘን፣ ውብ ስፍራ መሆኑን አይተን፣ በእኛ አቅምና ልክ ማስቀመጥ የሚገባንን አስቀምጠናል። ልጆቻችን ደግሞ ከእድገታቸው እየተነሱ ይበልጥ እያስዋቡ፣ የጎደለ እየሞሉ የበለጸገች፣ ያማረች፣ የተዋበች ለሁላችንም የምትበቃን ኢትዮጵያን በመስራት ረገድ የትውልድ ቅብብሎሽን ሚና ያሳዩበታል፣ ይገልጹበታል የሚል ተስፋ አለኝ ። እኔ በጣም በጣም ደስተኛ ነኝ፣ ስንጀምረው ካለኝ ግምት በላይ ውጤቱ አስደስቶኛል። ብዙ ጊዜ ሰዎች ያስቡና በወረቀት ያስቀምጣሉ፣ ማሰብና በወረቀት ማስቀመጥ ወይም ዲዛይን ማድረግ የተለመደ ጉዳይ ነው። እዚህ ቦታ ላይ ያየሁት ጉዳይ ግን ያሰብነውን በወረቀት ያስቀመጥነውን ሙሉ በሙሉ ቦታ ቦታ ይዞ አይተነዋል።

የጭንቅላታችንን እሳቤና መሻት ፍላጎት በወረቀት ሳይሆን በመሬት ላይ ከነሙሉ ቅርጹ ያየንበት ስፍራ ነው፣ በጣም የሚያኮራ ፕሮጀክት ነው፣ የዚህ ትውልድ ቅርስ ነው፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ቢያንስ እስከ ዛሬ ይሄን የሚያክል ሥራ የለም፣ በብዙ አፍሪካ ሀገራትም የለም፣ በአደጉ ሀገራትም እርግጠኛ አይደለሁም ግን ቢኖርም የሚተካከል እንጂ የሚያንስ አይደለም። የእኛ ሥራ ብቻ አይደለም፣ ተፈጥሮውም ይሄ ንጹህ ውሃ፣ እነዚህ ዛፎች የሚያምረው ስፍራና ተራራው የትም ቦታ ቢሆን ጥቂት የማረፊያ ስፍራ ታክሎበትና ለሰዎች ምቹ በሆነ መንገድ ተሰርቶ ማንም ቢያየው የሚያኮራ የሚያስደስት ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ እንደዚህ አይነት ብዙ ቦታዎች አሉ። ሶፍኡመር የሚያስደምም የሚያስደንቅ ውበት አለው፣ ጂማ ብንሄድ፣ ሃይቅ ብንሄድ፣ ወደ ትግራይ ብንሄድ፣ አፋር ብንሄድ፣ ሶማሌ ብንሄድ፣ ቤኒሻንጉል ብንሄድ፣ ሲዳማ ብንሄድ፣ ጋምቤላ ብንሄድ በሄድንበት ቦታ ሁሉ ደቡብ ምዕራብ ብንሄድ ገነት ነው፣ በየቦታው ፈልቅቀን እያወጣን

የእኛን ሚናና ድርሻ እያኖርን ብንሄድ በቅብብሎሽ ያማረች የተዋበች ኢትዮጵያን እንፈጥራለን።

የመጨረሻው ሃሳቤ ብዙ ሀገራት በሆነ ዘመን ጠንክረው፣ በርትተው ሠርተው አድገው ጫፍ ደርሰዋል። አሁን እያንዳንዱ ሃሳባቸው፣ ተግባራቸውና ሥራቸው እየቀነሰና እየወረደ ነው። እኛ እያንሰራራን እያደግን ወደነበርንበት ብቻ ሳይሆን ከዚያም ባሻገር ወደ መታደስ ወደ renaissance እየመጣን ነው ያለነው። እነዛ እየወረዱ እኛ እየወጣን ያለንበት ጊዜ መሆኑን ትውልድ ተገንዝቦ ያማረ፣ የሚሸጋገርና የማያሳፍር ነገር በየአካባቢው መስራት እንዲቻል አደራ ማለት እፈልጋለሁ። በተለይ ከውበት አንጻር ጎርጎራ ላይ የተሰራው እጅግ፣ እጅግ የሚያኮራ ነው። ተደስተናል ኮርተናል ኑ እና የደስታችን ተካፋይ እንደትሆኑ እጋብዛለሁ፤ በጣም፣ በጣም የሚያምር ሥራ ነው፤ የሚያምር ቦታ ነው፣ ለእኛ ለኢትዮጵያዊያንም ብቻ ሳይሆን አፍሪካዊያንም መጥተው እንዲዝናኑበት ብናደርግ የኢትዮጵያን ልክና ውበት እንዲገነዘቡ ያደርጋል። በጣም ደስ ብሎኛል እንኳን ደስ ያላችሁ ማለት እፈልጋለሁ። አመሰግናለሁ።

**መጋቢት 23 ቀን 2015 ዓ.ም**

**ጎርጎራ**

# የኢትዮጵያ ወታደራዊ አካዳሚ ያሰለጠናቸውን ዕጩ መኮንኖች በሁርሶ የኮንቲጀንት ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት የምረቃ በዓል

መጋቢት 30 ቀን 2015 ዓ.ም

**ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ**
**የተከበራችሁ ጄነራል መኮንኖች**
**እንዲሁም የቀድሞ የዚህ አካዳሚ ምሩቆች እና ጄነራል መኮንኖች**

ከሁሉ በላይ ደግሞ ለዛሬው ምረቃ የበቃችሁ የምክትል መቶ አለቃ ተመራቂዎች እንኳን ደስ ያላችሁ እንኳን ለዚህ ቀን አበቃችሁ ለማለት እፈልጋለሁ። የዛሬው ምርቃት በሁለት ምክንያት ከዚህ ቀደም ከነበሩ ምርቃቶች ለየት ያደርገዋል፤ እስካሁን ሰዎች በጊዜያቸው፣ በእውቀታቸውና በገንዘባቸው ተምረው ሲመረቁ አይተናል፣ አስመርቀናል። ነገር ግን ጊዜን፣ እውቀትንና ገንዘብን ብቻ ሳይሆን ህይወታቸውን አስይዘው ሲመረቁ ያየናቸው የዛሬዎችን ምሩቃን ስለሆኑ እናንተ በሁሉም መስፈርት ለምርቃት የሚያበቃ ዝግጅት ስላደረጋችሁ ተጨማሪ ኩራት ሊሰማችሁ ይገባል። ይህን ያልኩበት ምክንያት መስመራዊ መኮንን ከሲቪል የማሰልጠን ልማድ ብቻ ሳይሆን ባሳለፍነው ወሳኝ ሁኔታ ውስጥ የተሳተፉ የተዋጉ፣ ያዋጉና ውጊያን በመጽሐፍ ብቻ ሳይሆን በተግባር ያዩና ከዚያ የተግባር ልምምድ በኋላ የውጊያ ሳይንስንና ጥበብን ለመማር ወደዚህ የመጡ ምሩቅ መኮንኖች በመሆናቸው ከዚህ ቀደም ከነበረው በእጅጉ ልዩ ያደርገዋል።

ሁለተኛው ታላቅ ስም የያዘ ተመራቂ መሆኑ ነው። ጉባ እንደስሙ የታሪክ እጥፋት ያመጣ ብቻ ሳይሆን ጀምረን የጨረስንበት፣ ታላቅነትን በተግባር ያሳየንበት፣ የዓለምን ጫና ለብሔራዊ ጥቅማችን እምቢኝ ያልንበት፣ ዘንድሮ የመጨረሻውን የውሃ ሙሌት ብቻ ሳይሆን የመጨረሻውን የውሃ በላይ መፍሰስ የምናስተናግድበት፣ ለአንዲት ቀን፣ ለአንዲት ሰዓት ያልቆመና እጅግ የሚያኮራ ስራችን በመሆኑ በጉባ የተጀመረውና በጉባ የሚጠናቀቀው ግድባችንን ስም የያዛችሁ በመሆናችሁ ልክ እንደ ጉባ ግድብ የምትጀምሩ የምትጨርሱ፣ ለኢትዮጵያ የታሪክ እጥፋት የምታመጡና የማትቆሙ፣

ፈተና የሚያበረታችሁ እንጂ ሽብረክ የማያደርጋችሁ መኮንኖች እንደምትሆኑ ያለኝን ተስፋ በዚህ አጋጣሚ ለመግለጽ እወዳለሁ።

ኢትዮጵያ በእናንተ ገጽታ ላይ ትታያላች፣ የእናንተ ገጽታ ጠንካራነት፣ አይበገሬነት፣ ጽኑነት የሚታይበት ስለሆነ የእኛ ኢትዮጵያ የማትበገር የጸናች ለልጆቿ እዳ የምታሸጋግር ሳይሆን ወረት የምታሸጋግር የነገው ትውልድ የሚኮራባት፣ ታሪካዊት፣ ጥንታዊት ብቻ ሳይሆን የበለጸገችና ያማረች በታሪኳም በአሁናዊ ቁመናዋም የምታስደስት ሀገር መሆኗን ለመገንዘብ የእናንተን ገጽታ ማየት በቂ ነው። እናንተ መኮንኖች እጅግ እድለኞች ናችሁ። ታሪክ፣ ሀብት፣ ጀግንነት በሁሉም መስፈርት የሚያኮራ ሀገር ጠባቂዎች ስለሆናችሁ በድጋሚ እንኳን ለዚህ ክብር ታጫችሁ፤ እንኳን ደስ ያላችሁ ልላችሁ እወዳለሁ።

የጀግኖች ሀገር በነጻነት ትጸናለች ትቆማለች፣ ኢትዮጵያ ጀግኖች ስላሏት በነጻነት መቆየት ትችላለች፣ የታታሪዎች ሀገር ትበለጽጋለች። የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች በርተትው እየተጉ ከልመና ሊያወጡን ስለሆነ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በመጣር፣ በመድከምና በጥረት ብቻ ማደግ እንዳለ አምኖ ታታሪ እንዲሆን በዚህ አጋጣሚ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ። የአሳቢያን ሀገር ሃሳብ ታፈልቃለች። ኢትዮጵያ ሃሳብ ለማፍለቅ የሚጥሩ፣ የሚተጉ ጀግኖች ልጆችና እናንተን መሰል ጀግኖች ልጆች ስላሏት የምትጸና፣ የምታኮራና ትውልድ እንኳን ተወለድሁባት ብሎ የሚመካባት ሀገር እንድትሆን የእናንተ ሚና እጅጉን ከፍተኛ ስለሆነ ለዚህ ታላቅ ሐላፊነት ራሳችሁን በአንድ ምርቃት ሳይሆን በብዙ ምርቃቶች በተደጋገመ ድል ዳግም እንድታረጋግጡ አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ ። መርከብ ያለ ባህር፣ ሀገር ያለ ወታደር በወጉ በስፈራው ብቃቱን ሊያረጋግጥ አይችልም። መርከብ በዚህ አስፋልት ላይ ብናቆመው የቆመ ግዙፍ እቃ ከመሆን አልፎ በባህር ላይ የሚያሳየውን ብቃት ማሳየት አይችልም። ጠንካራ ሀገር ካለ ወታደር፣ ጠንካራ ሀገር ወታደራዊ ጠገጉን የጠበቀ፣ የስልጣን ተዋረዱን የጠበቀ፣ ሳይንስ፣ ጥበብንና ዲሲፕሊኑን የሚያውቅ ወታደር ከሌላት በስተቀር የጸናች፣ የበለጸገችና የቆመች መሆን አትችልም። እናንተ ወታደሮች አንድ ህይወት አላችሁ፣ እሱም ህይወታችሁ ኢትዮጵያ ሀገራችሁን መጠበቅ ነው።

ኢትዮጵያ ሀገራችሁን ከመጠበቅ የዘለለ የምታከብሩት፣ ዋጋ የምትከፍሉለትና የምትሰዉለት ዓላማ የላችሁም። ትልቁ አላማችሁ ኢትዮጵያን ማስቀጠልና ማጽናት ነው። ወታደር ወጥቶ የሚያድር ነው ይባላል። ወጥቶ ማደር ግን ጀግንነት ይጠይቃል፤

እንኳን ወጥቶ ማደር ጨለም ሲል በረንዳ ወጥቶ መጋፈጥም ድፍረትና ዝግጁነት ይጠይቃል።

ወታደር ማለት < ወ > የሚወክለው የወትሮ ዝግጁነትን ነው ሁሌም የሚዘጋጅ ፣ ሁሌ የሚሰለጥን ፣ ሁሌም የሚያነብ ፣ ሁሌ የሚያስብና ከሁልጊዜ ጥረት ያልተቆጠበ ማለት ነው። < ታ> ታታሪ ማለት ነው፣ ቀን ከሌት የሚተጋ፣ እንቅልፋን የሚሰዋ፣ ጊዜውን የሚሰዋ፣ ተራራን በዐይኑ ብቻ ሳይሆን በእግሩ የሚያሸንፍ፣ የሚጥር ማለት ነው። <ደ> ደፋር ማለት ነው፤ ጥይት ቢተኮስ፣ ነውጥ ቢነሳ፣ ከግራ በቀኝ ጫጫታ ቢሰማ የሚደፍር የማይፈራ ማለት ነው ። የመጨረሻው <ር> እርግጠኛ ማለት ነው፤ ወታደር ወደ አንድ ውጊያ ሲገባ በሰለጠነው ስልጠና እንደሚያሸነፍ እርግጠኛ ሆኖ እንጂ በድንገት የሚገባ አይደለም። እንደ እናንተ ጦርነትን በመጽሐፍ ብቻ ሳይሆን በተግባር በብቃት የሚያውቅ፣ ሳይንስን የተማረና በብቃት የተመረቀ  የሚገነባው ወታደር፣ የሚገነባው አሃድ ለሚሳተፈው ማንኛውም ግዳጅ እርግጠኛ የሆነ መሆን አለበት። ወታደር ስንል ዝም ብሎ ወጥቶ የሚያድር ብቻ ሳይሆን ወጥቶ ለማደር የሚያበቃ አካል፣ የአእምሮ ዝግጁነት ያለው ልባም ደፋር፣ ሲወጣም የወጣበትን ማስታገስ፣ ማስቆም የሚችል ማለት ነው። ዛሬ መኮንኖች እንደዚህ ያለ ተቋም እንደምትገነቡ ኢትዮጵያ በቆዳ ስፋቷ፣ በቁጥሯና በህልሟ ልክ ጠንካራ ወታደር ያላት የተፈራችና የተከበረች እንድትሆን የእናንተ ሚና የጎላ እንደሚሆን ጥርጥር የለኝም።

ከእናንተ መካከል ብዙ ጄነራሎች እንጠብቃለን፣ ከእናንተ መካከል ብዙ ኮሎኔሎች እንጠብቃለን። የነገው ጄነራል እንደዛሬው አይደለም? ዘመን እየተቀየረና እየዘመነ ስለሆነ የነገው ጄነራል ብዙ የሚጠበቅበት እውቀት ስላለ ማንበብና መማር ይጠበቅባችኋል። ዶክተር፣ ምክትል መቶ አለቃ ዛሬ ማየት እንደቻልነው ብዙዎቻችሁ በውትድርና ማዕረግ ጄነራል በትምህርትም ደግሞ ከፍተኛውን የምትይዙና ዘመናዊ ጦርነትን ለመምራት የሚያስችል ብቃት ያላችሁ እንደምትሆኑ ሙሉ እምነት አለኝ። ብዙዎቻችሁ ከብዙ ምርቃት በኋላ በብዙ ማዕረግ፣ በከፍተኛ ጀግንነት እንደአለቆቻችሁ የከበረን ማዕረግና የሀገር ክብር የምትጎናጸፉ እንድትሆኑ ያላኝን ተስፋና ምኞት እገልጻለሁ። ጀግና ማለት ራሱን ለሚበልጥ ዓላማ የሰጠ ማለት ነው፣ እኔ እና እናንተ አላማችን የላቀች፣ የጸናች፣ የበረታች ትናንትናዋን ብቻ ሳይሆን ነገዋን የምትዋጅ ኢትዮጵያን መፍጠርና ለትውልድ ማስረከብ መሆኑን አምነን የምንሳሳላት ሀገር የሚከፈልላት ማንኛውም ዋጋ ካለ ለመክፈል ዝግጁ ሆነን ኢትዮጵያን ማጽናት፣ ኢትዮጵያን ማበልጸግ፣ ኢትዮጵያን በአፍሪካ ብቻ ሳይሆን በዓለምም እንደ ታሪኳ ገናና ሆና እንድትቀጥል ማድረግ ነው።

ከዚህ ውጭ ያሉ አሉባልታዎችና ወሬዎች አያናውጡንም። ጸንተን የምንወዳት ሃሀገራችንን እናሻግራለን።

ይህ እንዲሆን የእናንተ ሚና ከፍተኛ ስለሆነ ሚናችሁን በእውቀትና በጥበብ እንድትውጡ አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ።
ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር ! መልካም ምርቃት !

**እንኳን ደስ ያላችሁ።**
**መጋቢት 30 ቀን 2015 ዓ.ም**
**ሁርሶ**



# "ጦርነት ይብቃ፤ ሰላምን እናጽና" በሚል ርዕስ በተዘጋጀው መርሃ ግብር ላይ የተላለፈ መልዕክት

ሚያዚያ 23 ቀን 2015 ዓ.ም

**የተከበሩ ሙሳ ፋኪ መሀመት የአፍሪካ ህብረት ሊቀ መንበር ፣**
**የተከበሩ ፓፓ አባሳንጆ የዚህ የሰላም ሂደት ሰብሳቢና ልዩ ሚና የተጫወቱ አባት፣**
**የተከበሩ ኡሁሩ ኬኒያታ የቀድሞ የኬንያ ፕሬዝዳንት ፣**
**የተከበሩ ምክትል ፕሬዝዳንት ሁሞላንቦ**
**የተከበሩ የደቡብ አፍሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር አንዶ ፣**
**የተከበሩ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ታገሰ ጫፎ ፣**
**የተከበሩ የፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አቶ አገኘሁ ተሻገር ፣**
**የተከበሩ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት አቶ ቴዎድሮስ ምህረት**
**የተከበሩ የቀድሞ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ፣**
**የተከበሩ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር በኢፌዲሪ ወገን ይህን የሰላም ቲም የመሩ ሽልማታቸውን በጓዳ የተቀበሉ ደመቀ መኮንን ፣**
**የኢጋድ ዋና ጸሐፊ ዶ/ር ወርቅነህ ገበየሁ**
**የተከበራችሁ የክልል ርእሳነ መስተዳድሮች ፣**
**በተለየ መንገድ የትግራይ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ጌታቸው ረዳ እና ከትግራይ የመጣችሁ ልኡካን ፣**
**የሀገር ሽማግሌዎች ፣**
**የእምነት አባቶች**
**በዚህ ስፍራ የተገኛችሁ ታዳሚዎች**

ፈጣሪ እንኳን ይህቺን ቀን በጋራ አሳየን፣ እንኳን ደስ ያላቹችሁ ልላችሁ እወዳለሁ።

እንደዚህ ያለውን ድንቅ ቀን እንዲሁ አቅልሎ መቀበል ተገቢ አይደለም። ካለፍንበት መከራ አንፃር ይህንን ቀን የሰጠን ይህንን ቀን እንድናይ ያደረገንን ፈጣሪ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲያመሰግን ከአደራ ጭምር ላሳስብ

እወዳለሁ። ጠብ አቁሞ ሰላም ለመፍጠር በቂ ያልሆነ ምክንያት ትክክለኛ ያልሆነ ጊዜ የለም፤ ሰላም ምክንያት አይፈልግም፣ ሰላም የተለየ ጊዜ አይፈልግም። በዚህም ምክንያት ዛሬ እየሆነ ያለው የሰላም መቋጫ የምስጋናና የአዲስ ምዕራፍ መጀመርያ ማብሰሪያ ዕለት ምክንያትም የተገደበ ጊዜ ሳይሆን ዛሬውኑ መሆን ያለበት እንደሆነ ይሰማኛል። ጥላቻ ያፈርሳል፣ ያናቁራል፣ ያገፋፋል፤ ፍቅር ይገነባል፣ ያሳስባል፣ ያስቃል፣ ጦርነት ያወድማል፣ ይገላል፣ ያፈርሳል፣ ሰላም ያለማል ያበለጽጋል ወጥቶ መግባትን በቀለለ መንገድ እንዲቻል ያደርጋል፤ ጦርነት ጨለማ ነው። ጦርነት ክፉ ነው። ከአፍ የሚወጣ ከአፈሙዝ የሚወጣው ውስጥንና ስጋን የሚገድል ነው። ሰላም ብርሃን ነው። ሰላም የነገር ሁሉ መጀመሪያ ነው። ስለሆነም ለዚህ የሰላም ቀን እንድንበቃ ያደረጋችሁ ግለሰቦች፣ ቡድኖች፣ ወዳጅ ሀገራት ኢትዮጵያ ከነበረችበት ጨለማ ወደሚገባት ብርሀን ለመሸጋገር ፈቅዳ የጀመረችበት እለት ስለሆነ እንኳን ደስ ያላችሁ ለማለት እወዳለሁ።

እኛ ኢትዮጵያዊያን በቂ የጦርነት ታሪክ አለን፤ የበቃና የሚነገር የሰላም ታሪክ ግን የለንም። ጦርነት በሁለት ሰላሞች መካከል የሚፈጠር ሁኔታ መሆን ሲገባው ለኛ ለኢትዮጵያዊያን ግን ሰላም በሁለት ጦርነቶች መካከል የሚገኝ እፎይታ ብቻ ሆኗል። የረዘመ ሰላም አልፎ አልፎ ግጭት የተለመደ ቢሆንም የኛ ኢትዮጵያዊያን ግን የበዛ የማይፈለግ ጎጂ ጦርነትና አልፎ አልፎ የሚገኝ የሰላም እፎይታ ብቻ ሆኗል።

የተከበራችሁ ኢትዮጵያዊያንና ታዳሚዎች፤

ሁለት ዓመት ከመዋጋት ሀያ ዓመት መወያየት ይሻላል። ሁለት ዓመት ስንዋጋ ብዙ እናወድማለን፣ ብዙ እንገላለን፣ ውስጣችን ይሞታል፣ የመፍጠር አቅማችን ይዳከማል። ሀያ ዓመት ስንወያይ የፈለግነው የተመኘነው፣ ባጭር ያልተከወነ ይሆን ይሆናል፤ ነገር ግን በሒደት ሰው ሳንጎዳ ንብረት ሳናወድም ለመማር እድል የሚሰጥ ስለሆነ ኢትዮጵያዊያን እንንቃ፣ በውይይት በምክክር ችግሮቻችንን መፍታት የስልጣኔ ሀሁ እንደሆነ እንገንዘብ። ከምክር ይልቅ መከራ የሚመክረው ህዝብ አንሁን።

እኛ ኢትዮጳያዊያን በምክክር በውይይት ችግራችንን መፍታት ተስኖን መከራ በሚያስከፋ ሁኔታ የሚያስተምረን ሞኝ ህዝቦች አንሁን። በዚህም ብዙ እናጣለንና ትላንት ብዙ አምልጠናል፤ ብዙ የተበላሹ ነገሮች አሉ፤ ነገር ግን ከተበላሸው ትላንት የተሻለ ነገር፣ ያማረ ነገር፣ የተዋበ ነገር፣ ለትውልድ ተስፋ የሚሰጥ ነገን መፍጠር እንችላለን። ትላንትናን እያሰብን ቁስል እያከክን የምንቆም ሳይሆን ትላንትናን ተሻግረን የተሻለ ነገ ለመፍጠር የምንተጋና የምንሰራ እንድንሆን አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ። ጦርነት ማስቀረት፣ ስድብ ማስቀረት፣ መገፋፋት ማስቀረት የይቅርታ ዋነኛ ተልዕኮ ነው። ዕርቅ ግን ማረም ነው። ዛሬ ይቅርታና ዕርቅ ስለሆነ ማስቆም ብቻ ሳይሆን ወደኋላ የተበላሸውን

ማረም ይጠበቅብናል የተሰበረ መጠገን፣ የቆሰለን ማከም፣ መብል የተቸገረን ማብላት፣ ትላንትናን በተሻለ ፍቅር ማደስንና ማስቀጠል የሚያስችል መሰረት መጣል ይኖርብናል።

**የተከበራችሁ ታዳሚያን፣**
**መላው የኢትዮጵያ ህዝብ፣**

በውጊያ የላቁ፣ በጀብድ የደመቁ በሀገር ፍቅር ያሸበረቁ ለሀገር የሚበቁ ዘወትር የነቁ ኢትዮጵያን በልባቸው ያነገሱ በአይተኬ ህይወታቸው እንኳን ለኢትዮጵያ የማይደራደሩ የበቁ የፀጥታ ኃይሎች አሉን። እነዚህ በሞያቸውና በእውቀታቸው አገራቸውንና ህዝባቸውን እንዲጠብቁ ከአፈሙዝ ጋር የሚያያዘውን ሥራ ለነሱ እንተውላቸው። ለነቁ ለበቁ ሀገር ለሚወዱ የጸጥታ ኃይሎች ዲሞፍተሩን ትተን እኛ ሞፈር እናንሳ። ሁሉም ዲሞፍተር አንሺ ከሆነ ሞፈር የሚጨብጠው እጅ ያጣል፤ ኢትዮጵያን የሚያስፈልጋት ሞፈር ነው። በእርግጥ የሚጠብቃት የተማሩ፤ የነቁ ዲሞፍተር የጨበጡ የሚያስፈልጋት ቢሆንም ብዙዎቻችን ግን ሞፈር የምንጨብጥና ሞፈር የሚጨብጡትን የምንደግፍ ብንሆን ከልመና ነፃ እንወጣለን። ማንዴላ በህይወቴ ተሸንፌ አላውቅም ይላሉ። በገጠሙኝ ፈተናዎች ባለፋኳቸው ተግዳሮቶች አንዳንዴ አሸንፌያለሁ ብዙ ጊዜ ግን ተምሬያለሁ።

የገጠመን ፈተና ያሸነፍንበት ብለን የምንኮራበት ባይሆንም እንደ ኢትዮጵያዊያን የተማርንበት፣ የምንማርበት፣ የምንሻገርበት ግን ሊሆን ይገባል። እጅግ በቂ የሆነ ትምህርት ያገኘንበት የጥፋት ጊዜ ስላሳለፍን ከንደዚህ አይነት ተግባር ተቆጥበን ተምረን ልጆቻችን የሚቀጥለው ትውልድ ያማረችና ያሸበረቀች የምትሰጥ ኢትዮጵያ ማውረስን እንድንችል ከጥላቻ፣ ከመገፋፋት፣ ከመዋጋት ራቅ እንድንል በታላቅ ትህትና አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ። ኢትዮጵያዊያን አንድ አባባል አለን <<ሲታረቁ ከሆድ ሲታጠቡ ከክንድ>> የሚል። እኛ ስንዋጋ ከልባችን ነበር የተዋጋነው፤ ከዛሬ ጀምሮ ግን ከልባችን መታረቅ ይኖርብናል። ኢትዮጵያዊያን በጦርነት ጀግኖች መሆናችንን ዓለም ይመሰክራል። በሰላም ጀግኖች ለመሆን ግን ከልብ መታረቅ ብቻ ሳይሆን የተጎዳው ሁሉ ወገኔ ነው ብለን በሙሉ ልብና በአንድነት እንድንሰራ፣ ያጎደልነውን ያበላሸነውን በአጠረ ጊዜ እንድንሞላ ሁላችሁንም በታላቅ ትህትና ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ። ዛሬ የመረጃ ምንጭ ብዙ ነው። ብዙ ሰዎች መረጃ ማመንጨት ይችላሉ።

በዚህም የተነሳ ጠዋት ተገናኝታችሁ ከተስማማችሁ በኋላ ከሰዓት ሰዎች ሀሳባቸውን ይቀይራሉ። የውሳኔ መነሻው መረጃ ነው። ኢንፎርሜሽን በጣም በስፋት በሚሰራጭበት

በዚህ ዓለም ጥዋት ያገኛቹት ወንድማቸሁ ማታ ሌላ አቋም ሊይዝ ይችላል፤ በዚህ አውድ ውስጥ የምንኖር ትውልዶች ልንማር የሚገባው ጉዳይ ዛሬ የሚያዋጣው መቻቻል ብቻ መሆኑን ነው። ምክንያቱም በየቀኑ የሚቀያየር ባህሪ ስላለን በመቻቻል፣ በመደማመጥ፣ በመወያየት የበለጠውን የላቀውን በመመኘትና ለዚያ በመትጋት መስራት ይኖርብናል። በተለዋዋጭ ዓለምና በበዛ ኢንፎርሜሽን የአቋም ልዩነት ሲፈጠር ሰክኖ መወያየት መነጋገር ያስፈልጋል። አቶ ጌታቸው <<ሰላም ያመጣነው ጀግነን ነው>> ብሏል። ዛሬ በመላው ኢትዮጵያ ህዝብ ፊት አቶ ጌታቸውን የምጠይቀው ጀግኖ ወደ ባህር ዳር እንዲሄድና ወንድሞቹን ማቀፍ እንዲችል ነው። ዶ/ር ይልቃልን የምጠይቀው ጀግኖ ወደ መቀሌ እንዲሄድና ወንድሞቹን እንዲያቅፍ ነው።

ሰላም እንዲሁ በቀላሉ የሚገኝ አይደለም፤ መስራት መትጋት መጀገን ይፈልጋል። የተከበረው የትግራይ ህዝብ ከተከበረውና ከወንድሙ ከአማራ ህዝብ ጋር ጠንካራ የደም ትስስር ያለው ቢሆንም በፖለቲካ ብልሽት ምክንያት የተፈጠረውን አለመግባባት ለመፍታት አቶ ጌታቸው እና ዶ/ር ይልቃል መጀገን ይጠበቅባችዋል። አቶ አወሉ በዚህ፣ በዚህ አይጠረጠሩም ብዬ ነው። ዛሬ ለኢትዮጵያ እጅግ አስደሳች ቀን ነው። ከዚያ የጦርነት ነጋሪት፣ ፉከራና ጥፋት ወጥተን ስለ ሰላምና መልሶ ግንባታ የምንነጋገርበት ቀን ነው። ይህ ለኛ ደስታ የሆነው ቀን እጅግ ለምንወደው፣ ለደጉ በቸገረን ጊዜ ሁሉ መጠጊያችን ለሆነው፣ ኢትዮጵያን አብዝቶ ለሚወደው ለሱዳን ህዝብ ይህችን ቀን ማየት እንዲችል ያለንን ከፍተኛ ምኞት እየገለጽኩ፤ ወንድሜ ጄነራል ቡርሀንና ወንድሜ ጄነራል ሀሜቲ ከኢትዮጵያዊያን ተምረው ሰክነው ተነጋግረው በሱዳን ያጋጠመውን መገዳደል እንዲያስቆሙ በዚህ አጋጣሚ ጥሪ ላቀርብላችሁ እፈልጋለሁ።

ኢትዮጵያ ለወንድም ህዝቦች ሰላም የምትመኝ፣ ሰላም አስከባሪ የምትልክ ብቻ ሳትሆን ለሱዳን ህምሳ ሺ ኩንታል ስንዴና በርከት ያሉ መድኃኒቶች ለመላክ የተዘጋጀ መሆኑን ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ በደስታ ለማብሰር እወዳለሁ። የሱዳን ህዝብ ከወንድም የኢትዮጵያ ህዝብ ድጋፍ ይፈልጋል። ኢትዮጵያዊያን እንደ ድሮ ማንነታችን ተርፎን ሳይሆን ከጎደለ ማንነታችን በማካፈል ወንድም ህዝብን ለማጽናናት ጊዜው አሁን ስለሆነ እኛ ኢትዮጵያዊያን ለማስታረቅና ለመርዳት ከፍተኛ ዝግጁነት እንዳለን አውቀው የሱዳን አመራሮች ይህን መሰል ፕሮግራም በካርቱም ለማዘጋጀት እንዲታደሉ ያለኝን ታላቅ ተስፋና ምኞት ልገልጽላቸው እወዳለሁ።

በሚቀጥለው ሳምንት ሁለት ኩነቶች ይከናወናሉ። አንደኛው የሁሉም ክልል ርዕሳነ መስተዳድሮች በፓርቲያችን ምክትል ፕሬዝዳንት እየተመሩ ወደ መቀሌ ይሄዳሉ። መቀሌ የሚሄዱት ያነቡ ዐይኖችን ለማበስ፣ የተበላሹ የፈረሱ ቦታዎችን ለመጠገን፣

ክልሎች እንደ ወንድም ህዝቦች ካላቸው ለማጋራትና ይህንን የሰላም ጅማሮ በተግባር ለማስቀጠል ነው። ይህ ጉዞ ዛሬ የምናደርገውን ንግግር የተግባር ማስጀመሪያና ወንድም የትግራይ ህዝብ ከጎኑ መሆናቸውን ሁሉም ክልሎች የሚያሳዩበት እለት ስለሆነ ልክ እንደዛሬው ቀን በከፍተኛ ጉጉት የምንጠብቀው ይሆናል።

ሁለተኛው ከኦነግ ሸኔ ጋር የሚደረገው ድርድር ከነገ ወዲያ በታንዛኒያ ይጀመራል። ይህን ድርድር የኢትዮጵያ መንግሥትና ህዝብ አብዝቶ ይፈልገዋል። በዚህ ድርድር የሚሳተፉ ወገኖች ሁሉ የዛሬዋን ቀን እያሰቡ ከግጭትና ከጦርነት እንደማናተርፍ አውቀው ህግና ሥርዓትን ተከትለን ይቅር ተባብለን ሀገራችንን በጋራ ለማነጽና ለመገንባት እንድንችል፣ የወለጋ ህዝብ አሁን ካለበት ስቃይ እፎይ ማለት እንዲችል ሁሉም ወገን የበኩላቸውን እንዲያደርጉ ከወዲሁ ጥሪዬን አቀርባለሁ። የኛ የሰላም ሂደት እንዲሳካ ከፍተኛ እገዛ ያደረጉ የወዳጅ ሀገራት፣ የአፍሪካ ህብረት፣ ኢጋድ እንዲሁም አንዳንድ ግለሰቦች ከሁሉ በላይ የህውሃት አመራሮች፣ የብልጽግና አመራሮች፣ መላው የትግራይ ህዝብ፣ የአማራ ህዝብ ፣ የአፋር ህዝብ ፣ የሶማሌ ህዝብ ፣ የኦሮሚያ ህዝብ ፣ የሲዳማ ህዝብ ፣ የደቡብ ሁሉም ብሔሮች ፣ ጉራጌ ፣ ስልጤ ፣ ወላይታ ፣ ሀድያ ፣ ከንባታ ፣ ዳሰነች ፣ ዳውሮ ፣ ኮንታ የተቀሩትን በሙሉ፣ የጋምቤላ ህዝብ፣ የደቡብ ምዕራብ ህዝብ፣ የቤኒሻንጉል ህዝብ ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ህዝብ ላደረጋችሁት ድጋፍ፣ ጸሎትና ምኞት በኢፌዲሪ መንግሥትና በራሴ ስም በተለይም የኢትዮጵያ እናቶች ለነበራችሁ ጭንቀትና ጸሎት ያለኝን ከፍተኛ ምስጋናና አክብሮት በዚህ ታሪካዊ ቀን ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ።

**ውድ ኢትዮጵያዊያን፤**

ኢትዮጵያ ትበለጽጋለች፣ ኢትዮጵያ ትጸናለች፣ ኢትዮጵያ ትቀጥላለች፣ ኢትዮጵያን የሚያስቆማት ምን ኃይል የለም። ኢትዮጵያን የሚያስቆማት ኃይል የኛ መጠላላት ብቻ ነው። ከዛሬው ቀን እንማር፣ የማይወደድና የማይፈለግ የኢትዮጵያ ክፍል የለም። አንዳንዶች ኢትዮጵያ ትገነጣጠላለች ወይም አንዳንዶች ይገነጠላሉ ይላሉ። ኢትዮጵያ አትገነጣጠልም፣ ፀንታ ትቀጥላለች። ይልቁንም ለልማቷ፣ ለመጽናቷ፣ ለአንድነቷ የሚያስፈልጋትን የቀራትን ለማግኘት አብዝታ ትሰራለች።

ኢትዮጵያ በልጆችዋ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር! ፈጣሪ ኢትዮጵያና ህዝቦቿን ይባርክ አመሰግናለሁ።

**ሚያዚያ 23 ቀን 2015 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**


ጦርነት ይብቃ፤
ሰላምን እናጽና
PEACE FOR ALL
ሰላም ለሁላችን፡ሁላችንም ለሰላም


FOR ALL





# የስካይላይት ሆቴል ምዕራፍ ሁለት መክፈቻ ሥነሥርዓት

ሚያዝያ 28 ቀን 2015 ዓ.ም

**ክብር አቶ ታገሰ ጫፎ፣**
**የተከበራችሁ ክቡር የክልል ርዕሳነ መስተዳድሮች፣**
**የተከበራችሁ እንግዶች**

እንኳን ወደ አያታችሁ ቤት በሰላም መጣችሁ። አያታችሁ ነው ያልኩት ብዙዎቻችን አየር መንገድን ስናስብ ሳንወለድ፣ ተወልደን ሕፃን ሆነን፣ ታዳጊም ሳለን ይህ ባንዲራና ኢትዮጵያን የሚለው ስያሜው ከኛ ጋር ስለኖረ የአያትነት ስሜት ስላለው ነው የቆየ የተላመድነው። የምናውቀው የቅርብ የሆነ የቤተሰብነት ስሜት ስላለው እንደ አያት ይቆጠራል። ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ሁላችንም ልንማር የሚገባን አንድ ቁልፍ ነገር የተቋም ዘላቂነትና የተቋም ቀጣይነት ያለውን ፋይዳ ነው። ይህ ተቋም ከሰባ ዓመታት በላይ እድሜ ማስቆጠሩ ብቻ ሳይሆን እድገቱም ሳያቋርጥ ኢትዮጵያዊያን እየተቀባበሉ ሊያቆዩ በቻሉት ልክ መከላከያውም፣ ገቢዎችም ሌሎች መስሪያ ቤቶችም በሙሉ በዚህ መንገድ ሳይቆራረጥ የቀጠለ እድገት ቢኖራቸው ኖሮ ምን አይነት ተቋማት ኢትዮጵያ ሊኖራት እንደሚችል ማሰብ ያስፈልጋል።

ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ጋር ባቡር ጀምረናል ታውቃላችሁ፤ ከአዲስ አበባ ጁቡቲ የጀመርነው ዛሬ አይደለም። ለምንድነው የኢትዮጵያ አየር መንገድ በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ሼር ወስዶ እየሰራ ኢትዮጵያን፣ አፍሪካን ከዓለም እንዳገናኘ የኛ የባቡር ቴክኖሎጂ ሴኔጋል ያልደረሰው፣ ደብብ አፍሪካ ያልደረሰው ብለን መጠየቅ አለብን። በእድሜ ከሆነ አይለያዩም። በዚያ ልክ እድገቱ ቢረጋገጥ ኖሮ ዛሬ ከአዲስ አበባ ጅቡቲ ሳይሆን ከአዲስ አበባ ፕሪቶሪያ የባቡር መንገድ ይኖረን ነበር ማለት ነው። የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን እድሜው ከአየር መንገድ የሚያንስ አይደለም፣ ይበልጣል ለምንድነው የኬንያ፣ የናይጄርያ፣ የሴኔጋል ቴሌኮሚኒኬሽን ውስጥ እኛ ድርሻ የሌለን፤ በአየር ብቻ ሳይሆን በቴክኖሎጂ አፍሪካን የማናገናኘው ለምንድ ነው ብለን መጠየቅና መቆጨት ይፈልጋል። የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎትም እንደዚሁ ነው። እነዚህ ተቋማት አንዳንዶቹ

በሀገር ደረጃ ላቅ ያለ ሥራ ሠርተው በአፍሪካ ደረጃ ሚናቸው ጎልቶ የማይታይበት ምስጢር ምንድነው ያላችሁ እንደሆነ የዘላቂነት አለመኖር ነው።

ኢንስፓየር ማድረግ፣ ቪዥን ያለው ተቋምና ከሰዎችና መንግሥታት መቀያየር ጋር የማይቀያየር የእድገት ትራክ ውስጥ መግባት አለመቻላቸውን ያሳያል። ከዚህ አንፃር የኢትዮጵያ አየር መንገድ በብዙ የመንግሥት ስብራቶች ኮንቲኒቲ ላይ ያለውን እክል እየቀየረ እያስተካከለ ስለሆነ የቦርድ፣ የማኔጅመንት አባላትንና መላው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሰራተኞችን እንኳን ደስ ያላችሁ ለሁላችን አርአያና ኩራት ስለሆናችሁ ማለት እፈልጋለሁ። የኢትዮጵያ አየር መንገድ ላለፉት ዓመታት መተላለፊያ ነበር፣ ከአንድ ሀገር ወደ ሌላ ሀገር የሚያልፍ የሚያስተላልፍ ተቋም ነበር ፤ ዛሬ የሚያሳርፍ ሆኗል። መተላለፊያ መሆንና አትራፊ መሆን ለየቅል ስለሆነ ባለፉት ሦስት አራት ዓመታት በተጀመረው ሥራና 2035 የአየር መንገዱ ራዕይ መሰረት እንደዚህ አይነት ሜጋ ሆቴል በማስመረቅ ማሸጋገር ብቻ ሳይሆን ማሳረፍ የሚችል ተቋም ስለሆነ በድጋሚ ማኔጅመንቱን እንኳን ደስ ያላቸሁ ማለት እፈልጋለሁ ።

የቀጣይነት ምስጢር አንዱ ያለፉ ሰዎችን ማስታወስ ነው። በዚህ ቀን አቶ ተወልደን ሳናመሰግን ብናልፍ የቀጣይነት የተቋም እሳቤ ይበላሽብናል። አቶ ተወልደ ይህ ጉዳይ እንዲጠነሰስና 2035 ቪዥን እንዲጀመር ከፍተኛ ሚና የተጫወተ ስመ ጥር ሰው ነው። የአሁኑ ቦርድ ሊቀመንበር የሱ መሪና አስተማሪ የነበሩ ሰው ናቸው። አቶ ግርማ ዋቄ እሱም እንደዚሁ በዚህ አየር መንገድ ውስጥ ሰፊ አገልግሎት የሰጡ ይሄንም ሥራ ያስጀመሩ ናቸው። አሁን ያሉትም ቢሆን ከነሱ ጋር የተማሩ ስለሆኑ ይህን ኮንቲኒቲ የምናስብ ከሆነ የወጡትንም ማመስገን አስፈላጊ ስለሆነ አቶ ተወልደን እንድታመሰግኑልኝ እጠይቃለሁ።

ኢትዮጵያ ውስጥ ሆቴል ከጀመርን መቶ አሥራስባት ዓመት ሆነን የጀመርነው በጣይቱ መሆቴል ነው። የዛሬ መቶ አሥራ ሰባት ዓመት በኢትዮጵያ አቆጣጠር 1998 የመጀመሪያው ሆቴል ተሰርቶ መቶ ዓመት ሙሉ ከትናንሽ ሆቴልነት ወጥተን ሜጋ ሆቴል መፍጠር ለምን አልቻልንም? አንድ ሺ ሰው ማስተናገድ የሚችል ሆቴል በኢትዮጵያ ለምን የመጀመሪያው ሆነ? ከጀመርን እኮ መቶ ዓመት ሞላን። የዛሬው የሆቴል ምርቃት አየር መንገድ ስላሰራው ሳይሆን ከነበርንበት ስታንዳርድ በጥራትም በመጠንም ወደ ሜጋነት ስላሳደገን ጭምር ነው።

ምንም እንኳን መቶ ዓመት የፈጀ ቢሆንም ይህ ጅማሮ ለኢንቨስተር ኢትዮጵያውያን ፈር ቀዳጅ ስለሚሆን ከሠራንም ከዚህ የተሻለ እንድንሰራ እድል ይፈጥራል ይህን እድል ሁላችንም መጠቀም ይኖርብናል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተሻለ መስህብነት ያላቸው ሊጎበኙ የሚችሉ ቦታዎች አዳዲስ ሥራዎች ተጀምረዋል። ጎርጎራ ላይ የሚሰራው ሪዞርት ለዚህ አየር መንገድ ሌላ የገቢያ ምንጭ ሊሆን ይችላል። እጅግ ውብ በሆነ መንገድ የተሰራ ነው። በቅርቡ ሀላላ ኬላ ተመርቋል። ኮይሻና ወንጪ እንዲሁ በሚቀጥሉት ወራት ውስጥ ይመረቃሉ። እንደዚህ አይነት ሥራ እያስፋፋን ከሄድን በቱሪዝም ዘርፉ ላቅ ያለ ውጤት ልናመጣ እንደምንችል ሊሸጥ ሊታይ የሚገባው ገጸ በረከት ኢትዮጵያ ውስጥ ስላለ ያን ለመግለጽ እድል ስለሚሰጥ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የራሱንም የእነዚህና ሌሎች ሪዞርቶችን በማስተሳሰር የበኩሉን ሚና እንዲጫወት አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

ዛሬ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከመቶ ሰላሳ በላይ አውሮፕላኖች አሉት። ይህ በአፍሪካ ትልቁ የሚያደርገው ቢሆንም ከሁሉ በላይ እኔ የሚያጓጓኝና በተባበረ ክንድ አብረን እንድንሰራ ያስፈልጋል ብዬ የማስበው በ2035 የኢትዮጵያ አየር መንገድ ራዕይ ለማሳካት ዛሬ ያሉትን አውሮፕላኖች በእጥፍ በመጨመር ሁለት መቶ ሰባ ማድረስ ይገባል ይህ ትልቅ ራዕይ ነው።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ የቦርድ አባላት፣ የማኔጅመንት አባላትና ሰራተኞች ብቻቸውን አያሳኩትም። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ አያቱን የማስፋትና የማሳደግ ሐላፊነት እንዳለበት አስቦ የኢትዮጵያ አየር መንገድ አስተላላፊ ብቻ ሳይሆን አሳራፊም እንዲሆን፣ በቂ አውሮፕላን እንዲኖረው በአፍሪካ ብቻ ሳይሆን በዓለም ስመ ጥርና በቀላሉ የማይወድቅ ተቋም እንዲሆን ሁላችንም የበኩላችንን እንድንወጣ፣ እንድናግዝ ይህ ቪዥን እንዲሳካ እንድንሰራ በታላቅ ትህትና አደራ እላለሁ።

የኢትዮጵያን ብልጽግና የምናረጋግጠው ትልቅ በማሰብ፣ ትልልቅ ሥራ በማሰብ፣ በመስራት፣ በመጀመር ብቻ አይደለም በመጨረስ ነው፤ አስቡት አዲስ አባባ ውስጥ ስንትና ስንት ሆቴል የዛሬ አምስት፣ ስድስት እና አስር ዓመት ተጀምሮ ቆሞ እንዳለ። በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ይህንን የሚያክል ሥራ መስራት ከተቻለ ለምን ቆሙ? ሁሉም እንዲጠናቀቅ ምን ማድረግ አለብን? አሳይመንት ለሁላችን የሚተው ይሆናል። የመጨረሻው መልዕክቴ እንደ አየር መንገድ ልባችንና ራዕያችን ሰፍቶ በአፍሪካ የምንወዳደር፣ የምንልቅ ትልቅ ተቋም መሆን ሲገባን በሰፈር ፋክክር በአጭር እያስቀረን ያለው ቫይረስ ከኮረና የባሰ ስለሆነ ከሰፈር እይታ ወጥተን በአፍሪካ ገበያ ውስጥ ለመወዳደርና ለማደግ የምንችል ሰዎች ለመሆን አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

እንደ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊያን በራስ ላይ ማዕቀብ የጣለ፣ እንደ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያን በአፍሪካ ብቻ ሳይሆን በዓለም ስመ ጥር መሆን ሲችል ባልተገቡ ጉዳዮች በሰፈር ታጥሮ በድህነት ውስጥ የሚኖር ህዝብ ለመኖሩ እርግጠኛ አይደለሁም።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ በዓመት የሚያጓጉዛቸው ተሳፋሪዎች ከብዙ የአፍሪካ ሀገራት አጠቃላይ ህዝብ ይበልጣል። የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና ስራ አስፈጻሚ ማለት የብዙ የአፍሪካ ሀገራት ጥቂት ቁጥር ካላቸው አገራት በላይ ህዝብ ወይም ሰዎችን የሚያንቀሳቅስ ተቋም የሚመራ ማለት ነው። በዚያ ልክ ብንሰፋ፣ በዚያ ልክ ብናድግ ኢትዮጵያ ውስጥ እጅግ አስደማሚ ነገሮች ለማድረግ ምቹና አስቻይ ሁኔታዎች እንዳሉ ያሳያል። እዚህ የተገኛችሁ እንግዶች በቅርብ የተከፈተውን ሀላላ ኬላን እንድታዩ እጋብዛችኋለሁ። የኢትዮጵያ አየር መንገድ እዛ ያለውን አየር መንገድ እንዲያስፋፋውና ለእንግዶች ምቹ እንዲያደርገው ኮይሻን፣ ወንጪን፣ ጎርጎራን በዚህ እሳቤ እንዲያይ አዳዲስ ሥራዎችን እንሰራለን። የኢትዮጵያን ብልጽግና እናረጋግጣለን። ትልቅ ነበርን ትልቅም እንሆናለን ሳይሆን፤ ትልልቆች ከደረሱበት በላይና መፍረስ የማይችል ሀገር እናንፃለን። ለዚህ ኢትዮጵያዊያን ልባችን የሰፋ ይሁን። እኛ ለማኞች አይደለንም።

ሠርተን የምንለወጥ እንድንሆን፣ እንድንተባበር፣ ከሰፈር እይታ እንድንወጣ፣ የመተው የማለፍ የይቅርታ ልብ እንዲኖረን፣ ትልቁን ነገር አስብን ለዚያ እንድንተጋ አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

እንኳን ደስ ያላችሁ። ይህ ነገር እንዲቀጥል እንዲስፋፋ በትብብር የኢትዮጵያን ብልጽግና እንድናረጋግጥ አደራ እያልኩ የአየር መንገዱ ሠራተኞች፣ ማኔጅመንት፣ የቦርድ አባላት እንዲሁም መላው የኢትዮጵያ ህዝብ እንኳን ደስ ያላችሁ፣ እንኳን ደስ ያለን ማለት እፈልጋለሁ፤ አመሰግናለሁ።

**ሚያዝያ 28 ቀን 2015 ዓ.ም**
**ስካይ ላይት ሆቴል፤ አዲስ አበባ**

# ‘ኢትዮጵያ ታምርት’ ኤክስፖ ላይ ተገኝተው ያስተላለፉት መልዕክት

ሚያዝያ 28 ቀን 2015 ዓ.ም

**ክቡር አፈ ጉባኤ፣**
**የተከበራችሁ የክልል ርዕሰ መስተዳድሮች፣**
**የአምራች ኢንዱስትሪው ባለቤቶች፣ ሞያተኞች፣**

ኢትዮጵያ ታምርት የሚለውን ንቅናቄ የምትመሩ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሠራተኞችና አመራሮች በሙሉ፤

ኢትዮጵያ ታምርት የሚለውን ንቅናቄ ድጋሚ ተገናኝተን ውጤቱን ለማየት፣ ቀሪ ሥራዎች ለመገምገም ለቀጣይ ደግሞ አቅጣጫ እንድንወስድ ይህንን መድረክ ስላመቻቻችሁ የተሰማኝን ልባዊ ደስታና አክብሮት እገልጻለሁ። ኢትዮጵያ ታምርት የሚለው ሃሳብ በእጅጉ ለጊዜው ለሀገራችን የሚመጥንና የሚያስፈልግ ስለሆነ እንኳን ደስ ያላችሁ፣ እንኳን ደስያለን ማለት እፈልጋለሁ።

ኢትዮጵያ ታምርት የሚለው ሃሳብ ምን ታምርት ከሚለው ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው። ኢትዮጵያ ፍቅርን፣ ሰላምን፣ አንድነትን፣ ልማትን ማምረት ትችላለች። በሌላ መንገድ ጠብን፣ ጥላቻን፣ መገፋፋትን፣ አለመግባባትን አለማምረትን ትመኛለች። የመጀመሪያው ታመርታለች፣ ሁለተኛው ትመኛለች ምክንያቱም ምርት ግብዓት ይፈልጋል። ግብኣት አልባ ምርት አብቦ ለመታየት ፍሬ ለማፍራት አይበቃም። ኢትዮጵያ ማምረት ትችላለች ልማትን፣ አንድነትን፣ ህብረትን ስንል በቂ መሬት፣ በቂ ውሃ ሊያመርት የሚችል በቂ ወጣት አሁን አሁን ደግሞ ምርትን መደገፍ የሚችል ኢነርጂ፣ በንጽጽር ሻል ያለ የፋይናንስ አቅርቦት፣ አስቻይ የሆነ የማምረቻ አውድና ግብዓት ኢትዮጵያ ውስጥ አለ። ግብአቱ ስላለ፣ በማዕድን ዘርፍ የተጀመሩ ሥራዎች ለኢንዱስትሪው በከፍተኛ ደረጃ ግብዓት መሆን ስለሚችሉ፣ በግብርና ምርት የተጀመሩ ሥራዎች በከፍተኛ ደረጃ ለኢንዱስትሪው ግብዓት መሆን ስለሚችሉ ፍላጎት ስላለን የልማትን ምርት ማረጋገጥ እንችላለን።

ለኢንዱስትሪ ልማት አንዱ አስፈላጊ ነገር ኢነርጂ በመሆኑ ህዳሴያችን እጅግ አስተማማኝ በሆነ መንገድ እየተጓዘ ስለሆነ ትልቅ ግብአት ይሆናል። የፖሊሲ ጥራት በማዕድን ዘርፍ የነበሩትን መቀዛቀዞች በከፍተኛ ደረጃ በማነቃቃት በርካታ ለኢንዱስትሪ ግብዓት ሊሆኑ የሚችሉ ምርቶች እየተመረቱ ይገኛሉ። አንድ እንደ ምሳሌ ለማንሳት፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ የሲሚንቶ ችግር አለ። አሁን ላሉ የኮንስትራክሽን ሴክተር የልማት ሥራዎች ሲሚንቶ ይቸግረናል። በሚቀጥለው ዓመት በዚህ ጊዜ የሚመረቀውና በለሚ የሚሰራው አዲስ ፋብሪካ አሁን ኢትዮጵያ የምታመርተውን ሲሚንቶ ከሀምሳ በመቶ በላይ ያመርታል። የሚቀጥለው ዓመት በዚህን ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ የሲሚንቶ ችግር ይቃለላል ማለት ነው።

በርከት ባሉ ዘርፎች እንደዚህ አይነት ሥራ አለ። በግብርናው ዘርፍ ሰፋፊ የልማት ሥራዎች እየተጀመሩ ቢሆንም አሁን በጉብኝቱ እንዳየሁት ከዓመት ከሁለት ዓመት በፊት ለጨርቃጨርቅ ኢንደስትሪ ግብዓት የሚሆነው ጥጥ በበቂ ደረጃ አይመረትም ነበር። አሁን ጥጥ ለአንድ ሀገር ምርት በቂ ሆኖ ኤክስፖርት ካላደረግን በስተቀረ የሀገር ውስጥ ኢንደስትሪ ሊቀበለው አልቻለም። ጥያቄ እየቀረበ ነው። በግብርናው ዘርፍ ግብዓት አለ ማለት ነው። እነዚህ የምንችላቸው አስቻይ ሁኔታ ያላቸው፣ ብንሰራባቸው የሚበጁ ሲሆኑ ነገር ግን አስቻይ ሁኔታ የሌላቸው ለግጭት መሳሪያ ያስፈልጋቸዋል እኛ መሳሪያ ማምረት አንችልም ። ለግጭት ጥላቻ ያስፈልጋል እኛ ኢትዮጵያውያን ለመጠላላት የሚያበቃን ምክንያት የለንም። ለግጭት በልቶ የጠገበ፣ ጉልበት ያለው ሰው ያስፈልጋል። የምግብ ጥያቄ አለብን፣  ለግጭት የሚመች ባህል ያስፈልጋል፣ የኛ ባህል ለዛ ምቹ አይደለም። ግጭትን፣ ጥላቻን፣ መራራቅን ማምረት ትተን ልማትን፣ ፈጠራን ብናበረታታና ብንሰራ ኢትዮጵያ የማደግ ተስፋ አላት።

አሁን ያለው የዓለም ሁኔታ አስፈሪና አሳሳቢ ነው።እየተናጠ ያለ ዓለም ነው። የተዘጋጀ ሀገር፣ የተሰበሰበ ሀገር፣ የሰከነ ሀገር፣ ያመረተ ሀገር ይሻገራል። በዋዛ ጊዜውን የሚያባክንና የሚገፋፋ ሀገር ደግሞ አንዳንዶቹ ይጠፋሉ። መጥፋት ስለማንፈልግ ሰብሰብ ብለን፣ ልብ ገዝተን ወደማምረት እንሄድ። እየወጡ ያሉ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በዓለም ላይ ከፍተኛ እድገት እያመጡ ካሉት ሀገራት ጥቂቶች ውስጥ አንዱዋ ኢትዮጵያ ናት።

እድገታችን በከተሜነት ይቀጥላል፣ በኢንድስትሪ ይቀጥላል፣ በግብርናው ይቀጥላል፣ በማዕድን ዘርፍ ይቀጥላል። ከሁሉ በላይ የሰው ኃይል ልማታችን በትምህርት ጥራት ላይ የጀመርነውን አጠናክረን በመቀጠል ይቀጥላል።

እነዚህ ጉዳዮች ግን ፈተና አልባ አይደሉም፤ እንፈተናለን። በህብረት እያሸነፍን የበለጸገችና የጸናች ኢትዮጵያን ለትውልድ እናሸጋግራለን። ኮሽ ባለ ቁጥር ለመፍጠር፣ ችግር ለመፍታት የሚነሳሳ ትውልድ እንጂ የሚሸማቀቅ መሆን የለብንም። ችግርና ፈተና ለመፍጠር በጣም ጠቃሚ ናቸው። ነገ በሳይንስ ሙዚየም እንዲሁ የግብርና ቴክኖሎጂና ምርት ሂደት በይፋ ክፍት ይሆናሉ። ሰሞኑን በቱሪዝም ዘርፍ ሀላላ ኬላ ፣ ትናንትና የአየር መንገድን አስመርቀናል አዳዲስ ሥራዎች ናቸው። ዛሬ በኢንዱስትሪ ያየነው በጣም ተስፋ ሰጪ ነው። ክቡር ሚኒስትሩ እንዳሉት ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትየጵያ ፋብሪካ ኤክስፖርት ልታደርግ ነው። ምርት (product) አይደለም ፋብሪካ። ይሄ ትልቅ ድልና ዜና ስለሆነ ሁላችሁም የለፋችሁ፣ የሠራችሁ፣ ያሳካችሁ ግለሰቦች እንኳን ደስ ያላችሁ ማለት እፈልጋለሁ።

ማምረታችን ይቀጥል፣ ህብረብሄራዊ መሆናችን ይቀጥል፣ በሰሜን፣ በምዕራብ፣ በምስራቅ፣ በደቡብ የምትሰሚቸው ድምጾች ፀጥ ረጭ ካሉ ኢትዮጵያ ትበለጽጋለች።

**አመሰግናለሁ።**
**ሚያዝያ 28 ቀን 2015 ዓ.ም**
**አዲስ አበባ**











# በሳይንስ ሙዚየም በተካሄደው የግብርና ዐውደ ርዕይ መክፈቻ ሥነ ሥርዓት

ግንቦት 7 ቀን 2015 ዓ.ም

ይህ መስሪያ ቤት በሚኒስቴር ደረጃ ከተቋቋመ ዛሬ ዓመት ከመንፈቅ ገደማ ቢሆነው ነው። ዋነኛው ዓላማ የነበረው ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ቁልፍ ችግር ሠራተኛ እና ስራን ማገናኘት ስለሆነ የሚፈለግ ሙያ፣ ሙያ ከሚፈልጉ ሰዎች ጋር ማገናኘት ነው። ለዚህ ደግሞ ተቋሙ በሚኒስቴር ደረጃ ሆኖ የተሰጠው ዋናው ተልዕኮ ሲስተም እንዲዘረጋ፣ ስትራቴጂ እንዲቀይስ፣ ስትራክቸር እንዲሰራ ነው። ከዚህ አንፃር የአንድ ዓመት ከመንፈቅ ተቋም አይመስልም፣ በጣም አስደሳች ሥራ ሠርተዋል። አንደኛው የሥራ አካባቢው ለደንበኛ የሚመች ሳይሆን ለሌብነት፣ ለድለላ፣ ለእጅ መንሻ የሚመች የአሰራር ሥርዓት ስለነበረው ያን ቀይረዋል። ኤሪጎኖሚክስ ወይንም የስራአካባቢ የምንለው በሃሳብ ደረጃ ያለውን በተጨባጭ መሬት ላይ ለማየት የሚያስችል ሥራ ሰርተዋል። ሁለተኛ የሥራ ባህልና ሥነምግባርን ቀይረዋል። ዛሬ እሁድ ቢሆንም እየሰሩ ነው ያገኘናቸው፣ እስከ ምሽቱ ሁለት ሰዓት ይሰራሉ፣ ቅዳሜና እሁድ ። እንደዚህ አይነት የሥራ ባህል ለኢትዮጵያ ያስፈልጋታል። ወጣቶች ናቸው፣ ደስ ይላል ስቀው ተቀብለው አስተናግደው ሲሸኙ ማየት በጣም ተስፋ የሚሰጥ ነገር ነው። የሥራ ባህሉም መሻሻሉና ማደጉ በራሱ ሌላ ተስፋ የሚያጭር ጉዳይ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

ሦስተኛው ግን ሲስተም ነው ። ኢትዮጵያ ውስጥ ስንት ሰው ነው ሥራ የሚፈልገው? በግምት የሚነገር ነገር አለ፣ ስንት ሰው ነው ሥራ ይዞ ያለው? በግምት የሚነገር ነገር አለ። ወደ ውጭ ሀገር መሄድ የሚፈልግ ሰው ፈላጊው ማነው፣ የት ሀገር ነው? ምንም የሚታወቅ ግልፅ የሆነ አስራር አልነበረም። አሁን ያየነው ዴቭሎፕ ያደረጉት ሲስተም በተለይ ለውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት ሙሉ በሙሉ ሥራ ጀምረዋል። ከውጭ ሀገር ማንም ሰው ፍላጎቱን በሲስተም ነው የሚልከው። ይህን ያክል ሹፌር እፈልጋለሁ፣ የቤት ሠራተኛ እፈልጋለሁ፣ ይህን ያክል ኢንጂኒየር እፈልጋለሁ ብሎ ይልካል። ያን ፍላጎት እነሱ ካላቸው ቋት ውስጥ አውጥተው ተጨማሪ ከህሎት የሚፈልግ ከሆነ ማሰልጠኛ ተቋማት ያላቸውን አሰልጥነው ወደዛ ይልካሉ። ይሄ ጥቅሙ ምንድ ነው፤ ወደ ውጭ አገር የሚሰማሩ ኢትዮጵያውያን በምን ያክል ደሞዝ እንደሚሰሩ፣ የት ሀገር እንደሚሰሩ፣

ከማን ጋር እንደሚሰሩ ዝርዝር መረጃ ስላለ አንድ አደጋ እንኳን ቢያጋጥማቸው ማን እንደወሰዳቸው ይታወቃል፣ የት እንደነበሩ በአሻራ ማወቅ ይቻላል።

ሰዎቹ ቢጎዱ እንኳን ይሄ ብዙ ሰዎች የደረሰባቸው ከዚህ ቀደም የምናውቃቸውን ጉዳት ለመቀነስ ትርጉም አለው። ከውጭ ሀገራት ጋር አሁን ያለው እንደ ድሮ ሳይሆን ግልጽ የሆነ ስምምነት እየፈረምን፣ አንድ ሰው ዝቅተኛ የሚያገኘው ገቢ እየወሰንን ስለሆነ የሚሄደው ከውጭ አገር አንፃር በጣም በጣም የተሳካ ሥራ ተሰርቷል።

ከሀገር ውስጥ ምዝገባ አንጻር ጀምረዋል፤  ግን ይሄ በአንድ ወቅት የሚሆን ሳይሆን በጣም ሰፊ የሆነ ህዝብ ነው የሚይዘው። ከአሥራ አምስት ዓመት እስከ ስልሳ አራት፣ ስልሳ አምስት ዓመት እድሜ ያሉ ሰዎች ስልሳ ሰባ ሚሊየን ይጠጋሉ። ከኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት አንጻር ሲታይ ያን የሚያክል ሰው ነውና የሚይዘው  ጊዜ ይጠይቃል።
ነገር ግን ሁለተኛ ደረጃ፣ ኮሌጅ ያጠናቀቁ ሰዎች እየተመዘገቡ ሲሄዱ በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ማን ሥራ እንዳገኘ፣ ማን ሥራ እንደሚፈልግ፣ ምን አይነት ሥራ እንደሚፈልግ፣ በቀላሉ እንድንገነዘብ ያደርገናል። የተሳሳተ ሪፓርት አቅርቦት ለመቀነስ ያግዛል። በብዙ ሀገራት ስናይ መንግሥታት በየሁለት ቀኑ፣ በየሰዓቱ ምን ያህል ሥራ እንደተገኘና እንዳልተገኘ ያውቃሉ። ከዛ ተነስተውም ሀሳብ ለማመንጨት ይጠቀሙበታል። በኛ ሁኔታ ብዙ ጊዜ ሪፖርቱ በቋሚና ጊዜያዊ ሥራ የሀገር ውስጥ ሥራ በደንብ የሚያሳይ ስላልሆነ ትክክል ያልሆኑ ፖሊሲዎች እንዲመነጩ ሊያደርግ ይችላል ፤ ከዳታ አንፃር ዳታ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው።

ያየሁት ነገር ተስፋ ሰጥቶኛል። እንግዲህ በአስር ዓመት እቅዳችን ላይ አንደኛ ማዕድን ነው ትኩረት ይሰጠው ያልነው፣ ሁለተኛው ኢንደስትሪ ነው፣ ሦስተኛው ግብርና ነው፣ አራተኛው ቱሪዝም ነው፣ አምስተኛው አይቲ ነው፣ አራቱንም ይደግፋል። አሁን ወደ ማዕድን ስንሄድ ምን ያህል አይቲ መስሪያ ቤቱ ውስጥ እየተስፋፋ እንደሆነ እናያለን፣ ኢንዱስትሪ ስንሄድ በኮሚሽን ሰፊ ሥራ እየሰሩ ነው ያሉት ፣ ቱሪዝም ላይም አብዛኛው ሥራ ከአይቲ ጋር የሚያያዝ ነው። ግብርና ላይ በሳይንስ ሙዚየም ኤግዝቢሽን እንደቀረበው የአይቲ ሚና ከፍተኛ ነው። ምን ያክል እንደተመረተ፣ ማሳ ላይ ምን ያክል ምርት እንዳለ በርቾዋል ዳታ ለመሰብሰብ የተጠቀሙባቸው ሲስተሞችና እነዛ የትኩረት መስኮች ሲስተም ከመዘርጋታችን ጋር ተያይዘው ፈር እየያዙ ነው ። ይሄ ደግሞ በሂደት ተቋም ለመገንባት የሚያስችል አቅም እንድንፈጥር ያደርጋል። የተቋም ግንባታው ወሳኝ ነው ስላልን። ለምሳሌ በኮሆርሲቭ ፖወር መከላከያ ላይ ፣ ደህንነት

ላይ ፣ ፖሊስ ላይ ያየነው ተቋም ጥራት በናሬሽን ፓወሩ ለምሳሌ ኢ.ቢ.ሲ. እየሰራ ያለውን መሰረተ ልማት ሲታይ በኢኮኖሚክ ፓወሩ ሲታይ ደግሞ ቅድም የጠቀስኳቸው አምስት ሴክተሮች እየሰሩ ያሉት ሥራ እነዚህ ሲደመሩ ዲፕሎማሲውን ጠንካራ ያደርጋሉ ፣ ፖለቲካውን ጠንካራ ያደርጋሉ፣ ሰላሙን ጠንካራ ያደርጋሉ።

ወጣት ተምሮ ሥራ የሚያገኝበት ነገር ካመቻቸንና ሥራ ካለው የያንዳንዱ ዜጋ ገቢ እያደገ የሚሄድ ከሆነ አብዛኛው የምናያቸው ችግሮች እዛ ውስጥ እየመከኑ ይሄዳሉ። በጣም ተስፋ ሰጪ ነገር ነው። ሁሉም ተቋማት የሥራ አካባቢያቸውን ማስተካከል አለባቸው። የሥራ ባህል ማዘመን አለባቸው፣ ሞቲቬሽን መጠቀም አለባቸው። ቁልፍ ጥንቃቄ የሚያስፈልገን ነገር አሁን አይቲን በስፋት የመጠቀም ነገር እየሰፋ ስለሆነ በየቦታው የምናስቀምጣቸው ዳታዎች ምን ያክል ደህንነታቸው የተጠበቁ ናቸው የሚለውን ማሰብ ያስፈልጋል። ድሮ በወረቀት ነበር አሁን ሁሉም ዲጅታል እያደረገ ነው፤ ይህ ለሌላ ጥፋት እንዳያጋልጠን ዳታዎቻችንን እንዴት መጠበቅና መከላከል አለብን የሚለውን ነገር ማወቅ አለብን። ዜጎቻችን ስንት ሰው ሥራ ይፈልጋል፣ ከየት ይፈልጋል በምን አይነት ሙያ፣ ማንም ሰው በፈለገው ጊዜ አክሰስ ማድረግ የሚችለው ሆኖ እንዳይጠፋ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል ። በጣም ተስፋ ሰጪ ነገር ነውና ሚኒስቴሩ አዲስ ተቋም አይመስልም። በወጣት የተሞላ ነው፣ ከቴክኖሎጂ ጋር እየተረማመድን ነው፣ ይሄን እያስፋፋን የኢትዮጵያን ብልጽግና ለማረጋገጥ እንደ አንድ ምሰሶ ሆኖ የሚጠቀምበት ተግባር ይሆናል የሚል እምነት ነው ያለኝ። ደስ ብሎኛል ጥሩ ጅምር ነው።

**ግንቦት 7 ቀን 2015 ዓ.ም**
**አዲስ አበባ**









# በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር በልጽጎ ሥራ ላይ የዋለ የውጭ ሀገር የሥራ ሥምሪት መረጃ ሥርዓት ጉብኝት

ግንቦት 7 ቀን 2015 ዓ.ም

ይህ መስሪያ ቤት በሚኒስቴር ደረጃ ከተቋቋመ ዛሬ ዓመት ከመንፈቅ ገደማ ቢሆነው ነው። ዋነኛው ዓላማ የነበረው ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ቁልፍ ችግር ሠራተኛ እና ስራን ማገናኘት ስለሆነ የሚፈለግ ሙያ፣ ሙያ ከሚፈልጉ ሰዎች ጋር ማገናኘት ነው። ለዚህ ደግሞ ተቋሙ በሚኒስቴር ደረጃ ሆኖ የተሰጠው ዋናው ተልዕኮ ሲስተም እንዲዘረጋ፣ ስትራቴጂ እንዲቀይስ፣ ስትራክቸር እንዲሰራ ነው። ከዚህ አንፃር የአንድ ዓመት ከመንፈቅ ተቋም አይመስልም፣ በጣም አስደሳች ሥራ ሠርተዋል። አንደኛው የሥራ አካባቢው ለደንበኛ የሚመች ሳይሆን ለሌብነት፣ ለድለላ፣ ለእጅ መንሻ የሚመች የአሰራር ሥርዓት ስለነበረው ያን ቀይረዋል። ኤሪጎኖሚክስ ወይንም የስራአካባቢ የምንለው በሃሳብ ደረጃ ያለውን በተጨባጭ መሬት ላይ ለማየት የሚያስችል ሥራ ሰርተዋል። ሁለተኛ የሥራ ባህልና ሥነምግባርን ቀይረዋል። ዛሬ እሁድ ቢሆንም እየሰሩ ነው ያገኘናቸው፣ እስከ ምሽቱ ሁለት ሰዓት ይሰራሉ፣ ቅዳሜና እሁድ ። እንደዚህ አይነት የሥራ ባህል ለኢትዮጵያ ያስፈልጋታል። ወጣቶች ናቸው፣ ደስ ይላል ስቀው ተቀብለው አስተናግደው ሲሸኙ ማየት በጣም ተስፋ የሚሰጥ ነገር ነው። የሥራ ባህሉም መሻሻሉና ማደጉ በራሱ ሌላ ተስፋ የሚያጭር ጉዳይ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

ሦስተኛው ግን ሲስተም ነው ። ኢትዮጵያ ውስጥ ስንት ሰው ነው ሥራ የሚፈልገው? በግምት የሚነገር ነገር አለ፣ ስንት ሰው ነው ሥራ ይዞ ያለው? በግምት የሚነገር ነገር አለ። ወደ ውጭ ሀገር መሄድ የሚፈልግ ሰው ፈላጊው ማነው፣ የት ሀገር ነው? ምንም የሚታወቅ ግልፅ የሆነ አሰራር አልነበረም። አሁን ያየነው ዴቨሎፕ ያደረጉት ሲስተም በተለይ ለውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት ሙሉ በሙሉ ሥራ ጀምረዋል። ከውጭ ሀገር ማንም ሰው ፍላጎቱን በሲስተም ነው የሚልከው። ይህን ያክል ሹፌር እፈልጋለሁ፣ የቤት ሠራተኛ እፈልጋለሁ፣ ይህን ያክል ኢንጂኒየር እፈልጋለሁ ብሎ ይልካል። ያን ፍላጎት እነሱ ካላቸው ቋት ውስጥ አውጥተው ተጨማሪ ክህሎት የሚፈልግ ከሆነ ማሰልጠኛ ተቋማት ያላቸውን አሰልጥነው ወደዛ ይልካሉ። ይሄ ጥቅሙ ምንድ ነው፤ ወደ ውጭ አገር የሚሰማሩ ኢትዮጵያውያን በምን ያክል ደሞዝ እንደሚሰሩ፣ የት ሀገር እንደሚሰሩ፣

ከማን ጋር እንደሚሰሩ ዝርዝር መረጃ ስላለ አንድ አደጋ እንኳን ቢያጋጥማቸው ማን እንደወሰዳቸው ይታወቃል፣ የት እንደነበሩ በአሻራ ማወቅ ይቻላል።

ሰዎቹ ቢጎዱ እንኳን ይሄ ብዙ ሰዎች የደረሰባቸው ከዚህ ቀደም የምናውቃቸውን ጉዳት ለመቀነስ ትርጉም አለው። ከውጭ ሀገራት ጋር አሁን ያለው እንደ ድሮ ሳይሆን ግልጽ የሆነ ስምምነት እየፈረምን፣ አንድ ሰው ዝቅተኛ የሚያገኘው ገቢ እየወሰንን ስለሆነ የሚሄደው ከውጭ አገር አንፃር በጣም በጣም የተሳካ ሥራ ተሰርቷል።

ከሀገር ውስጥ ምዝገባ አንጻር ጀምረዋል፤ ግን ይሄ በአንድ ወቅት የሚሆን ሳይሆን በጣም ሰፊ የሆነ ህዝብ ነው የሚይዘው። ከአሥራ አምስት ዓመት እስከ ስልሳ አራት፣ ስልሳ አምስት ዓመት እድሜ ያሉ ሰዎች ስልሳ ሰባ ሚሊየን ይጠጋሉ። ከኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት አንጻር ሲታይ ያን የሚያክል ሰው ነውና የሚይዘው ጊዜ ይጠይቃል ። ነገር ግን ሁለተኛ ደረጃ፣ ኮሌጅ ያጠናቀቁ ሰዎች እየተመዘገቡ ሲሄዱ በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ማን ሥራ እንዳገኘ፣ ማን ሥራ እንደሚፈልግ፣ ምን አይነት ሥራ እንደሚፈልግ፣ በቀላሉ እንድንገነዘብ ያደርገናል። የተሳሳተ ሪፖርት አቅርቦት ለመቀነስ ያግዛል። በብዙ ሀገራት ስናይ መንግሥታት በየሁለት ቀኑ፣ በየሰዓቱ ምን ያህል ሥራ እንደተገኘና እንዳልተገኘ ያውቃሉ። ከዛ ተነስተውም ሀሳብ ለማመንጨት ይጠቀሙበታል። በኛ ሁኔታ ብዙ ጊዜ ሪፖርቱ በቋሚና ጊዜያዊ ሥራ የሀገር ውስጥ ሥራ በደንብ የሚያሳይ ስላልሆነ ትክክል ያልሆኑ ፖሊሲዎች እንዲመነጩ ሊያደርግ ይችላል ፤ ከዳታ አንፃር ዳታ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው።

ያየሁት ነገር ተስፋ ሰጥቶኛል። እንግዲህ በአስር ዓመት እቅዳችን ላይ አንደኛ ማዕድን ነው ትኩረት ይሰጠው ያልነው፣ ሁለተኛው ኢንደስትሪ ነው፣ ሦስተኛው ግብርና ነው፣ አራተኛው ቱሪዝም ነው፣ አምስተኛው አይቲ ነው፣ አራቱንም ይደግፋል። አሁን ወደ ማዕድን ስንሄድ ምን ያህል አይቲ መስሪያ ቤቱ ውስጥ እየተስፋፋ እንደሆነ እናያለን፣ ኢንዱስትሪ ስንሄድ በኮሚሽን ሰፊ ሥራ እየሰሩ ነው ያሉት ፣ ቱሪዝም ላይም አብዛኛው ሥራ ከአይቲ ጋር የሚያያዝ ነው። ግብርና ላይ በሳይንስ ሙዚየም ኤግዝቢሽን እንደቀረበው የአይቲ ሚና ከፍተኛ ነው። ምን ያክል እንደተመረተ፣ ማሳ ላይ ምን ያክል ምርት እንዳለ በርቀዋል ዳታ ለመሰብሰብ የተጠቀሙባቸው ሲስተሞችና እነዛ የትኩረት መስኮች ሲስተም ከመዘርጋታችን ጋር ተያይዘው ፈር እየያዙ ነው ። ይሄ ደግሞ በሂደት ተቋም ለመገንባት የሚያስችል አቅም እንድንፈጥር ያደርጋል። የተቋም ግንባታው ወሳኝ ነው ስላልን። ለምሳሌ በኮሆርሲቭ ፖወር መከላከያ ላይ ፣ ደህንነት

ላይ ፣ ፖሊስ ላይ ያየነው ተቋም ጥራት በናሬሽን ፖወሩ ለምሳሌ ኢ.ቢ.ሲ. እየሰራ ያለውን መሰረተ ልማት ሲታይ በኢኮኖሚክ ፖወሩ ሲታይ ደግሞ ቅድም የጠቀስኳቸው አምስት ሴክተሮች እየሰሩ ያሉት ሥራ እነዚህ ሲደመሩ ዲፕሎማሲውን ጠንካራ ያደርጋሉ ፣ ፖለቲካውን ጠንካራ ያደርጋሉ፣ ሰላሙን ጠንካራ ያደርጋሉ።

ወጣት ተምሮ ሥራ የሚያገኝበት ነገር ካመቻቸንና ሥራ ካለው የያንዳንዱ ዜጋ ገቢ እያደገ የሚሄድ ከሆነ አብዛኛው የምናያቸው ችግሮች እዛ ውስጥ እየመከኑ ይሄዳሉ። በጣም ተስፋ ሰጪ ነገር ነው። ሁሉም ተቋማት የሥራ አካባቢያቸውን ማስተካከል አለባቸው። የሥራ ባህል ማዘመን አለባቸው፣ ሞቲቬሽን መጠቀም አለባቸው። ቁልፍ ጥንቃቄ የሚያስፈልገን ነገር አሁን አይቲን በስፋት የመጠቀም ነገር እየሰፋ ስለሆነ በየቦታው የምናስቀምጣቸው ዳታዎች ምን ያክል ደህንነታቸው የተጠበቁ ናቸው የሚለውን ማሰብ ያስፈልጋል። ድሮ በወረቀት ነበር አሁን ሁሉም ዲጅታል እያደረገ ነው፤ ይህ ለሌላ ጥፋት እንዳያጋልጠን ዳታዎቻችንን እንዴት መጠበቅና መከላከል አለብን የሚለውን ነገር ማወቅ አለብን። ዜጎቻችን ስንት ሰው ሥራ ይፈልጋል፣ ከየት ይፈልጋል በምን አይነት ሙያ፣ ማንም ሰው በፈለገው ጊዜ አክሰስ ማድረግ የሚችለው ሆኖ እንዳይጠፋ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። በጣም ተስፋ ሰጪ ነገር ነውና ሚኒስቴሩ አዲስ ተቋም አይመስልም። በወጣት የተሞላ ነው፣ ከቴክኖሎጂ ጋር እየተረማመድን ነው፣ ይሄን እያስፋፋን የኢትዮጵያን ብልጽግና ለማረጋገጥ እንደ አንድ ምሰሶ ሆኖ የሚጠቀምበት ተግባር ይሆናል የሚል እምነት ነው ያለኝ። ደስ ብሎኛል ጥሩ ጅምር ነው።

**ግንቦት 7 ቀን 2015 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**





# አዋሬ አካባቢ የአቅመ ደካሞችን ቤት የማደስ መርሃግብር ማስጀመሪያ

ግንቦት 7 ቀን 2015 ዓ.ም

ክረምት ከመግባቱ በፊት ለአቅመ ደካሞች ቤት የማደስ ተግባር የዘንድሮውን ዛሬ ጀምረናል። ይህ ተግባር ከፍተኛ የውስጥ እርካታ የሚሰጥ፣ ያለንበትን ችግር ተጋግዘን ለማለፍ የሚያግዝ በጎ ተግባር ነው። በዚህ በጎ ተግባር ላይ አቅምና ጉልበት ያላቸው ሰዎች ሁሉ በየሰፈራቸው በየአካባቢያቸው ፈርሶ የሚሰራም ከሆነ ባለበት የሚጠገን ከሆነ የአቅመ ደካሞች፣ የአዛውንቶች፣ ልጆች የሌላቸው መበለቶች ቢታገዙ በምድሩም በሰማዩም ጠቃሚ ስለሚሆን በየዓመቱ ስናደርግ የነበረውን ተግባር በዘንድሮም እንድንቀጥል ነው። አንድ ተግባር መጀመር ሁሌ ይቻላል። በታማኝነት ያን ነገር እስከመጨረሻው መፈፀም ነው ችግሩ። ፍፃሜው ያማረና ምርጥ የሚሆነው በታማኝነት ነው፤ ያንን ነገር መከወን ሲቻል ነው።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት በዚህ መሰል ተግባር በአዲስ አበባ ውስጥ ከስምንት ሺ ቤት በላይ ተሰርቷል። በብዙ መልካም ዜጎች ትብብር የብዙ ሰዎች ቤት ተቀይሯል። ዘንድሮ ተረባርበን ደግሞ ቁጥሩን ከፋ ብናደርገውና ልማድ ቢሆን, በየዓመቱ ያላቸው የሌላቸውን ቢያግዙ፣ አቅመ ደካሞችን ጉልበታሞች ቢያግዙ፣ አገራችን ውስጥ አሉ የምንለውን ችግር ለመቀነስ ፣ ለመቅረፍ ያግዛል። እንግዲህ ቁጭ ብሎ ከመጠየቅ፣ ከመውቀስ፣ ከመርገም የሚሻለው ይህ ነው።

የራስን ድርሻ አስተዋጽኦ ማድረግ ነውና እጅግ መልካም ነገር ስለሆነ በተባበረ ክንድ አቅመ ደካሞችን ብናግዝና ብንሰራ መልካም ነው። አሁን ጊዜው እንደሚታየው ባለፉት ጥቂት ሳምንታት ዝናብ አላቋረጠም። ምናልባት በሚቀጥሉት ሦስት ሳምንታት ፋታ ስለሚገኝ ትክክለኛው ጊዜ አሁን ነው። ፈጥነን እስከ ሰኔ መጨረሻ ድረስ ይህንን ተግባር ብንፈጽም ከዚያ የአረንጓዴ አሻራ ሥራ አለብን። እንደዚህ እንደዚህ እያልን ነው አገር የሚታነጸውና ዛሬ የጀመርነው ሥራ የዛ መልካም መሰረት ወይም ጅማሮ ተደርጎ ተወስዶ ክረምቱን በሙሉ የምንሰራው ይሆናል። መላው የሀገራችን ዜጎች በዚህ መልካም ተግባር ላይ እንዲተባበሩ፣ አብረው እንዲቆሙ፣ እንዲሰሩ አደራ ማለት እፈልጋለሁ፣ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

**አመሰግናለሁ።**

**ግንቦት 7 ቀን 2015 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**


3ኛው አገር አቀፍ የክህሎት ውድድር
Ministry
and Skills


የክህሎት ውድድር

# 3ኛው የሀገር አቀፍ የክህሎት ውድድር መርሃግብር ላይ ያደረጉት ንግግር

ግንቦት 15 ቀን 2015 ዓ.ም

ዛሬ የተገናኘንበት ዋነኛ ዓላማ የተለያየ ብቃትና ችሎታ ያላቸው ወጣቶች በየአካባቢው የፈጠሯቸውን የፈጠራ ማቴሪያሎች ይዘው ለውድድር የሚቀርቡበትና ችግሮቻችን እንደዚሁም መፍትሔዎች የሚያፈላልጉበት ለአንድ ሳምንት ጊዜ የሚቆይ የውድድር፣ የመማሪያ፣ ትስስር የመፍጠሪያ፣ የገበያ መፈለጊያ፣ ያለንን ብቃት ማሳያ እጅግ በጣም ወሳኝ የሆነ ፕሮግራም ነው።
የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ከተቋቋመ አንድ ዓመት ተኩል ገደማ የቆየ ሲሆን ዋነኛ ተልዕኮውም ሥራ ፈጣሪ (skilled) የሆኑ፣ ብቃት ያላቸው፣ መስራት የሚችሉ ሰዎችን በብዛት መፍጠር፣ ለመፍጠር የሚያስችል አውድም ማመቻቸት ነው።
ከዚህ አንፃር ሚኒስቴሩ የጀመራቸው ሥራዎች ተስፋ ሰጭ መሆናቸውን ለማየት ዛሬ በኤግዚቢሽን የተለያዩ ወጣቶች ያቀረቧቸው ሥራዎች ያመላክታሉ።

ኢትዮጵያ በርከት ያለ ችግር ያለባት ሀገር ናት። እነዚህን ችግሮች ተገንዝበን በመፍጠር የሰውን ልጅ ኑሮ ማቅለል ፍላጎትና ፍቃድ ካለን ደግሞ ለሁሉም የፈጠራ አይነቶች ሙሉ ግብዓትን ማቅረብ የምትችል ሀገር ናት። ኢትዮጵያ ውስጥ ኢንደስትሪን አስቦ፣ ግብርናን አስቦ፣ ቱሪዝምን አስቦ ወይም አይሲቲን አስቦ፣ ሌላ ግብዓት የሚፈልግ ሰው አይኖርም። ሁሉም አይነት ግብዓቶች ኢትዮጵያ ውስጥ አሉ። ነገር ግን እነዚያ ግብዓቶች ያልተሳሰሩና በሚፈለገው ጥራት ያልተመረጡ በመሆናቸው አንዳንዴ ቤት ለመስራት ኢትዮጵያ ድንጋይ ከውጭ አገራት ታስመጣለች። ሸክላ፣ ሲራሚክ ከውጭ ታስገባለች ከፍተኛ ጥራት ያላቸው እብነበረዶች ማምረት የምትችል ሀገር ግን መፍጠር የሚችሉና ሥራን የሚያቀሉ ሰዎች ስላልበዙላትና ስላልተጀመረ ስራው ከተለያዩ ሀገራት ኢምፖርት ታደርጋለች።

ይሄንን ነገር ለማስቀረት ነው የዚህ መገናኘት፣ የዚህ ፎረም ዋና ዓላማ። እነዚህ ሥራ የሚፈጥሩ ሰዎች መገንዘብ ያለባቸው ፈጠራ የራሱ የሆነ ችግር ያለበት፣ ፈጠራን ስንፈጥር የሚያምር ቢሆንም  የነበረ ነገር ግን የሚያፈርስ (disruptive) ነው ። አንድ ሰው ፈጠረ ማለት የነበረን ነገር አፈረሰ ማለት ነው። ለምሳሌ የሰው ልጅ ከመቶ ሰላሳ፣ ከመቶ ሀምሳ ዓመት በፊት አብዛኛው ለመጓጓዣነት የሚጠቀምባቸው

ነገሮች የጋማ ከብቶች ነበሩ ። የጋማ ከብቶች ሲጠቀም ፈጠራ ማለት ሰው ሌጣ ፈረስ ላይ ከሚሳፈር ኮርቻ መስራት ሰው ለመወጣጫነት እንዳይቸገር የሚያስችላቸውን ብረት ማዘጋጀት በኋላም እያደገ ሲሄድ ጋሪ፣ ሰረገላ መፍጠር ነበር። የዚያ የጋማ ከብት የትራንስፖርት ስርዓት ከጋሪና ሰረገላ በኋላ የፈጠራ አቅሙን እየጨረሰ ሲመጣ ነው የእንፋሎት ቴክኖሎጂ የተፈጠረው። እንፋሎት ሲመጣ በአብዛኛው የነበረው የትራንስፖርት ሲስተም ባቡር ነው።

እንደ ትላንትና ሰረገላ የሚሰሩና ኮርቻ የሚሰሩ ሳይሆኑ ፋርጎ የሚሰሩ፣ ሀዲድ የሚያነጥፉ፣ ብረት የሚያቀልጡ አዳዲስ ሞያተኞች ይዞ መጣ። እነዚህ አዳዲስ ሞያተኞች ሲመጡ ቀድሞ ኮርቻ የሚሰሩት እንኳን መጣችሁልን ብለው አይቀበሏቸውም። ያፈርሳል፣ ቢያለማም የሚያፈርሰው ነገር አለ። ከእንፋሎት ቴክኖሎጂ በኋላ የአውቶሞቢል ቴክኖሎጂ ሲስፋፋ መኪና ሲፈጠር ያ የእንፋሎት ብቃት የነበራቸው በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሞያተኞች ባጭር ጊዜ ውስጥ ሥራ አጥ የሚያደርግ ኤሌክትሪካል መካኒክ የሚባል ሞያን ተፈላጊ የሚያደርግ አዲስ ነገር ተፈጠረ። አዳዲስ ነገር ሲፈጠር ጥቂቶች ብልሆች ለውጥን እንደማይቋረጥ የሚያውቁ ብልሆችን ተከትለው ይማራሉ፤ (adapting) ናቸው። ብዙዎቹ ግን አቃቂር እያወጡ የኛ ይሻላል እያሉ አዲሱን ለመቀበል ሲቸገሩ ጊዜ ጥሏቸው ይሄዳል ። የመኪና ቴክኖሎጂ ሲፈጠር መኪና የፈጠሩ ሰዎች ሳይሆኑ ነዳጅ እንዳላቸው እንኳን የማያውቁ አገራት በመኪና መፈጠር ምክንያት ከፈጠሩት ሰዎች እኩል በልፅገው ዛሬ እጅግ የለሙ ሀብታም ሀገሮች ሆነዋል።

አሁን ደግሞ አየር አለ፣ አሁን ደግሞ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ አለ፣ ፈጠራ ሲመጣ በፍጥነት መማርና መከተል ካልቻልን የነበረውን ነገር እንደሚያበላሽ እንደሚያጠፋ አምነን ካልተቀበልን አዳዲስ ለውጦችን  ካልተቀበልን በሚመጣውና በሚጠፋው መካከል የቆየ ፍትጊያና ትግል ይደረጋል። አዲስ ነገር መፈጠሩ አይቀርም፣ አሮጌን ነገር ማዳከሙ አይቀርም። ይሄንን አውቀን ለመፍጠርና ለማቅለል የምንተጋ መሆን አለብን : : የሚፈጥሩ ሰዎች አንደኛ ፈጠራ በራሱ የተለየ ማሰብና ብቃት ይጠይቃል ፤ ሁለተኛ የነበረን ያፈርሳል፤ ሦስተኛ ቢሮክራሲው፣ ካፒታሉና አስተሳሰቡ ለአዲስ ነገር ሁሌም ምቹ ስላልሆነ ለፈጠራ ያስቸግራል። በብዙ ችግሮች የተከበበ ነገር ነው። ነገር ግን የምትፈጥሩት ሰዎች መገንዘብ ያለባችሁ እነዛ ችግሮች እንደ ስፕሪንግ ቦርድ ናቸው። ስፕሪንግ ቦርድ ባለበት ሌብል ላይ ሲቀመጥ ማስፈንጠር አይችልም፣ ዝቅ ስናደርግ ነው ወደ ከፋታ የሚያስፈነጥረን። ብዙውን አሁን የያዙን ችግሮች እንደማስፈንጠሪያ ተጠቅመን ግብርናችን፣ ኢንደስትሪያችን፣ በማዕድንና ኮንስትራክሽን ሴክተር ዛሬ

ያየናቸው ቴክኖሎጂዎች ወደ ውጤት ለማስገባት ይህን የፈጠራችሁ ሰዎች ያለባችሁ ፈተና፣ ያለባችሁ ችግር፣ ያለባችሁ ያልተመቸ ከባቢ እንደመስፈንጠሪያንት መጠቀም አለባችሁ። ይህንን ማድረግ ከቻላችሁና መፍትሄ ተኮር ከሆናችሁ ኢትዮጵያ ለማደግ ለመለወጥ ብዙ እድል ያላት አገር ስለሆነች የናንተ ፈጠራ በእጅጉ የሚያግዘን ይሆናል። መፍትሄ ተኮር መሆን ማለት ምንድ ነው፤ በርከት ያሉ ችግሮች አሉ። እፈጥር ነበር ፋይናንስ አጣሁ፣ እፈጥር ነበር ቦታ አጣሁ፣ እፈጥር ነበር ዲሞክራሲው አላገዘኝም እያልን ችግሩን ብቻ የምናወራ ሰዎች መፍትሄ አናመጣም። ችግሩ አለ እንዴት ነው ከዚያ ችግር ውስጥ መልካም ነገር መዘን ማውጣትና ውጤታማ የምንሆነው ብለን ውጤት ተኮር፣ መፍትሄ ተኮር ከሆንን ግን ከችግር ውስጥ የማይጠበቁ አመርቂ ውጤቶች ሊመጡ ይችላሉ ። ውጤት ላይ ማተኮር ማለት በቀለለ ነገር የቸገረን ነገር መሻገር እንድንችል የሚያስችል ነገር ማለት ነው። ስለሆነም ፈጠራ እጅግ ያስፈልገናል የእጅ ጥበብ ያላቸው እጃቸውን ልባቸውን አእምሯቸውን አስተሳስረው የሚሰሩ ሰዎች ያስፈልጉናል። ግብርናችን አልዘመነም፣ ኢንደስትሪው አልዘመነም፣ ኮንስትራክሽን አልዘመነም። ብዙ ሴክተር በመፍጠር ሥራን ማቅለል የሚያስችል ሁኔታ መፍጠር የሚቻልበት ሀገር ነው ያለን።

ይህንን ለማድረግ ግን የምናያቸው በከባቢያችን ያሉ ፈተናዎች ተግዳሮቶች እንዳያቆሙን በተባበረ፣ በተደመረ፣ በተሳሰረ ችግርን ብቻ በሚያወራ ሳይሆን መፍትሄ በሚያመጣ እሳቤ በመፍጠር፣ ግብርናችንን በመፍጠር፣ ኢንደስትሪያችንን እንድናዘምን አደራ ልላችሁ እወዳለሁ። ዛሬ ያየሁት የወጣቶች የፈጠራ ውጤቶች ባለፈው ሳምንት በኤግዚቢሽን ማእከል በኢንደስትሪ ሚኒስቴር የተዘጋጀውን ኤግዚቢሽን ስናይ ምን ያክል ሊተሳሰሩና ሊደጋገፉ እንደሚችሉ ያመላክታል። አሁንም ሳይንስ ሙዚየም ካለው የግብርና ኤግዚቢሽን ጋር እንዲሁ የሚቀናጅ ነው። እንበርታ እንፍጠር፣ ፈተናን ችግርን ለማለፍ መፍትሄ ላይ የምናተኩር እንሁን፣ በዚህ መንገድ የበለፀገች የተሻለች አገር ለመፍጠር ሁላችንም በየሞያችንና ብቃታችን የምንረባረብ እንድንሆን አደራ እላለሁ። ባየሁት ነገር እጅግ ተስፋ ሰንቄያለሁ። ይህም ኢንደስትሪ ሁለት፣ ሦስት ዓመት፣ አምስት ዓመት ሲቆይ የተሻለ ውጤት እንደሚያመጣ ያለኝን ተስፋ እየገለፅኩ፤ በቆይታችሁ የምትታወቁበት የምትማማሩበት በሠራችሁት ሳትረኩ አዳዲስ ነገር የምታክሉበት ጊዜ እንዲሆንላችሁ እመኛለሁ።

**አመሰግናለሁ።**

**ግንቦት 15 ቀን 2015 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**




አንድነት
እፅዋት ማዕከል
“ ሀገር የትውልድ ትምምር
ዉጤት ናት ”
አንድነት
እፅዋት ማዕከል

# የአንድነት ፓርክ የዕጽዋት ማዕከል፣ የአንድነት ቤተ መዛግብትና የሕክምና ማዕከል ምረቃ

ግንቦት 29 ቀን 2015 ዓ.ም

**ክቡራን አፈ ጉባኤዎች፣**
**ክቡራን ምክትል ፕሬዝዳንቶች፣**
**የተከበራችሁ የብልጽግና ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት፣**

ዛሬ እዚህ የተገናኘነው ብልጽግና ያለውን ኀልጉሎ የማውጣት፣ ያለውን የማወቅ፣ ያወቀውን ወደ ጥቅም የመቀየር ልምዱን ማሳያ የሚሆኑ ሁለት ወሳኝ ፕሮጀክቶች ለማስመረቅ ነው። ሁላችሁም እንደምታውቁት የዛሬ አራት ዓመት፣ አራት ዓመት ተኩል ገደማ ሥራችንን የጀመርነው ቢሮ በማደስ ነው። ቢሮ አድሰን ወደ ግቢ እናስፋው ስንል ወደ ግቢ የጀመርነው እዚህ ፊት ለፊት የሚታየው የዩኒቲ ፓርክ መልክዓ ምድርን (landscape) በማስዋብና እንደዚህ አይነት ታሪካዊ ቦታዎችን በማደስ ነበር።

በዚያ ጊዜ በርከት ያሉ ትችቶች ተነስተዋል፤ ምን ያደርጋል? ዩኒቲ ምን ያደርጋል? አሁን ቤተመንግሥት ማደስ? የሚሉ ትችቶች ተሰንዝረዋል። የትችቶቹ መነሻ ልክ ሥራ እንደጀመርን በርከት ያሉ የውጭ ሰዎች (አሁን አገር እና ስም አልጠራም) እየመጡ ''ዩኒቲ ፓርክ ይህንን ቤት ማደስ፣ ላንድስኬፕ ማደስ፣ ምን ያረግላችኋል? ይልቁንስ በርከት ያለ ዶክመንት የያዘ አርካይቭ ስላላችሁ እሱን ወደ ዘመናዊ መልክ እኛ እንቀይርላችሁ፤ ገንዘብም አለን ሞያተኛም አለን እናሻሽልላችሁ'' የሚል ጥያቄ በስፋት ያነሱ ነበር። በተደጋጋሚ ጥያቄ ሲነሳ ቤተ-መዛግብቱን ለማየት ስንሞክር እንደተባለውም በሺህ የሚቆጠሩ በጣም ወሳኝ የሆኑ መረጃዎችና ማስረጃዎች የኢትዮጵያ የሶፍት ፓወር መገለጫ የሆኑ ታሪካዊ ዳታዎች ምናልባት ወደፊት የኢትዮጵያ ኃይል መገለጫ የሚሆኑ በርከት ያሉ ሀብቶች በውስጡ እንዳሉ ነገር ግን ከአያያዝ ጉድለት የተነሳ አንዳንዶቹ ሊጠፉ እንደሚችሉ ተገንዝበን።

ለምንድነው የውጭ ሰዎች ''ገንዘብ አለን፣ እውቀት አለን ሌላውን ተዉትና ይሄን እንስራላችሁ ብለው ተረባረቡ'' ብለን ጥርጣሬ ስላደረብን በርካታ ታሪካዊ ቅርሶችና

መዛግብት የተሰረቁበት ሀገርም ስለሆነ ከምናሰርቅ እንዳለ እናቆይ፣ ከቻልን የራሳችንን ሰዎች ብቻ አስተምረን ሞያውና ብቃቱ ሲኖረን ስንፈጥር እንሰራዋለን አልን። ከዚያም ቲም አደራጅተን በተለያዩ ሀገሮች ስልጠናና ጉብኝት አድርገው የተሟላ አቅም ከፈጠርን በኋላ ቀደም ሲል ያየነው አርካይቭ ሙሉ በሙሉ  በኛ ልጆች የተሰራ ነው። ይህ ሥራ እንዲሥራ እነ ዶ/ር ታምራትና ከነሱ ጋር ያሉ በርካታ ሞያተኞች ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። ዛሬ አምሮ ተውቦ እንዳየነው ሳይሆን ገብቶ ለማየት የሚመች ቦታ አልነበረም። የዶክመንቱ አቀማመጥና ጥራት ምቹ አልነበረም። ይህ ዶክመንት እጅግ ለኢትዮጵያ አስፈላጊ ነው። ነገ ልጆቻችንን በስማ በለው ወሬ ከሚያደምጡ ስለ ኢትዮጵያና ስለ መንግሥት ግንኙነት ማወቅ የፈለጉ መጥተው ማጥናትና መመራመር፣ ለማስተርስ ወይም ለዶክትሬት ትምህርት የጥናት ግብዓት የሚሆኑ ማስረጃዎችና መረጃዎች ሊገኙበት የሚችሉ ቦታ ሆኖ ለኢትዮጵያዊያን ተሰርቷል።

ይህ ለብልጽግና አዋራን ማራገፍ፣ አሻራን ማስቀመጥ ያልነው መርህ አካል ስለሆነ የተከበረው የብልጽግና ማእከላዊ ኮሚቴ በሙሉ እንኳን ደስ ያላችሁ ማለት እፈልጋለሁ። ሁለተኛው ልብ እንድንል የምፈልገው ጉዳይ የዩኒቲ ፓርክ ስፋት 40 ሄክታር ገደማ የሚገመት ነው፤ ቤተ-መንግሥት ከአራት ዓመት በላይ ፈጀብን እድሳቱ። ሰው ዩኒቲ ፓርክ ከተከፈተ ጊዜ ጀምሮ ያለቀ ይመስለዋል። ነገር ግን የተከፈተ ጊዜ ምናልባት 20 በመቶ የሚጠጋው የግቢው አካል ብቻ ነው የተመረቀው። መካነ አራዊት የተሰራው ከዛ በኋላ ነው። ከዛ በኋላ በርከት ያሉ የእርሻ ቦታዎች ተሰርተዋል፣ አዳራሽ ታድሷል። አሁን ዩኒቲ ፓርክ ውስጥ ምንም ያልተነካ ቦታ የለም፣ መቶ በመቶ መዋል ለሚገባው አገልግሎት ግቢው ተዘጋጅቷል። ዛሬ የምመኘው ነገር ኢትዮጵያዊያን  ሳይከለከሉ በነፃ መኪናቸውን ግቢ ፓርክ አድርገው፣ እዚህ ግቢ ምሳ በልተው መዋል ቢችሉ? እንደዚህ ያለ ነፋሻማ ገነት የሆነ ቦታ በአዲስ አባባ መካከለኛ ስፋራ አለ ብሎ ብዙ ሰው አያስብም።

ብልጽግና ያረጀውን የሚያድስ ብቻ ሳይሆን ብቻውን መገልገልም የማይፈልግ ስለሆነ እንናፍቃለን የኢትዮጵያ ህዝብ ገብቶ ይህንን ነገር ለማየት፣ ለመማር፣ ለመዝናናት የሚችልበትን ጊዜ። ከዚያም በተጨማሪ ለአዲስ አበባ ከተማ ከፍተኛ የቱሪዝም መስህብ ሊሆን ይችላል። እጅግ ውብ የሆነ ቦታ ነው። እውነቱን ለመናገር በዚህ ስፋት በዚህ ሁሉ ሀብት ጥርቅም መካነ አራዊት አለው፣ በጣም ውብ ታሪካዊ ቦታዎች አሉት፣ አሁን እንዳያችሁት ቤተመዛግብት አለው፣ ቦታኒክ ጋርደን አለው፣ የፊልም ማሳያ አዳራሽ አሉት ፣ የሾፒንግ ሞል የሆኑ ቢሮዎች አሉት። ለከተማው ለበርካታ ሰዎች የሥራ እድል

የሚፈጥር ፣ ለከተማው መስህብ የሚሆን በርካታ ሰዎች ይህንን የኑሮ ዘይቤ እንዲከተሉ ትምህርት የሚሰጥ ነው። ከዚህ አንፃር የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድርና የአዲስ አበባ ነዋሪዎች አንድነት ፓርክ ሙሉ በሙሉ ክፍት እስከሚሆን ድረስ ልጆቻችሁን በተለይ ተማሪዎች በፕሮግራም ዛሬ የተመረቀውን አርካይቭና ቦታኒክ ጋርደን (botanic garden) እያዩ እንዲማሩ፣ እንዲመራመሩ ክፍት መሆኑን ለመግለጽ እወዳለሁ።

ቦታኒክ ጋርደንን በሚመለከት አቶ ካሌብ ምንውየለት ሙሉ በሙሉ ወጭውን ፋይናንሱን ሸፍኖ በከፍተኛ ትጋት ላለፉት ሁለት ዓመታት የተሰራ ነው። የጎበኘነው አስር ደቂቃ ሊሆን ይችላል፣ ሥራው የወሰደው ግን ሁለት ዓመት ነው ፤ በአይነቱ ከፍ ያለ ደረጃ ያለው በሀገራችን የመጀመርያው ምንናልባት ብዙ ሀገርም በዚህ መጠን ማግኘት የሚቻል አይመስለኝም። ነገር ግን ከኛ ሁኔታ አንፃር እንድናስተውል የሚያስፈልገው ነገር ኢትዮጵያ ከስድስት ሺ በላይ ሀገር በቀል እጽዋት አሏት። እነዚህ እጽዋት የፕላንት ሳይንስ ተማሪዎች ብቻ የሚያውቋቸው ከሆኑ አይጠበቁም። የኢትዮጵያ ጤፍ በዓለም አቀፍ መድረክ የኢትዮጵያ አይደለም። የኢትዮጵያን ጤፍ ባለቤት ሆኖ የፓተንት ራይት ያስመዘገበው  ሌላ ሀገር ነው። ጤና አዳም፣ ጌሾ፣ ግራዋ፣ ኮሰረት ብዙ ነገሮች ቅመማ ቅመም እዚህ የምናቃቸው ከዚህ የተወሰዱ ሌላ ሀገር በሌላ ሀገር ስም ሊመዘገቡ ስለሚችሉ የኛ የሆነውን ማወቅና መጠበቅ፣ በሌላ በኩል እኛ በገጠር በመጠኑም ቢሆን ባደግንበት ሰፈር የምናውቃቸው እጽዋት ያሉ ቢሆንም በኛ ደረጃም ቢሆን የደጋው ሰው የቆላውን አያውቅም፣ የቆላው ሰው የደጋውን አያውቅም። ልጆቻችን ግን ከዚያ በባሰ አብዛኛውን ነገር አያውቁትም። ልጆቻችን ተክሎችን ማወቃቸው ለምን አስፈለገ ያላችሁ እንደሆነ የሰው ልጅ ምግብና መድሃኒት የሚገኘው ከተክሎች ውስጥ ነው። እጽዋት በትክክል የማያውቅና በትክክል የማይንከባከብ ሀገር መድሃኒትና ምግብ እየሸመተ ለመኖር ይገደዳል ።

ቀደም ሲል እንዳያችሁት ቡና አለ፤ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ምንጫችን ነው። ፓፓያ አለ፣ ማንጎ አለ በርካታ አትክልትና ፍራፍሬዎች እዛ ሰፈር ይገኛሉ። ተክል ሲባል ጥድና ባህር ዛፍ ብቻ አይደለም፤ የሚበላና ለመድሃኒትነት የሚውል ነገር በውስጡ አለ። ጥድ እና ባህር ዛፍ የራሳቸው ጠቀሜታ እንዳላቸው ይታወቃል። ስለሆነም ልጆቻችን ይህንን እያወቁ ቢያድጉ ተመራማሪዎች ሊመራመሩ፣ ወደፊት መድሃኒት በገፍ የምናስገባ ሳንሆን ለኛ መልክዓምድር፣ ለኛ በሽታ ሁኔታ ከተፈጥሮ መድሃኒት ለማግኘት የሚያስችል ለብዙ ምርምር ግብዓት የሚሆን ቦታ ነው።

ታድያ ይህንን ጉዳይ የብልጽግና ማእከላዊ ኮሚቴ አባላት በተለየ ሁኔታ ለውጥ አስፈለገ የተባለ እንደሆነ ቅድም ያየነውን ነው። አርካይቭ ቤተ-መዛግብት ዶክመንት ሁሉ ቦታ አለ። በየክልሉ በየወረዳው በየዞኑ አለ፣ ዶክመንት ያለው እዚህ ብቻ አይደለም። ከዚህ ትምህርት ቀስመን ከዚህ ጋር መሰል ሥራ እንድንሰራ ነው። ቦንጋ ከተማው ራሱ በጋርደን የተሞላ ነው። ለዶ/ር ነጋሽ ይህንን ቦታ ማየት ትርጉም ላይሰጠው ይችላል። ነገር ግን ዶ/ር ነጋሽ ጋ  ቦንጋ ያለው ተክል በቦንጋ ኢኮሎጂ ብቻ የሚገኝ ነው። ሌላውን ክፍል አይሸፍንም። እዚህ ግን የቆላውም አለ፣ የደጋውም አለ፣ የወይና አደጋውም አለ። አንድ ሰው የቆላን አትክልት ለማየት ቆላ ድረስ መሄድ የለበትም እዚህ መጥቶ ትምህርት ሊወሰድ ይችላል።

በየአካባቢያችን መሰል ሥራ ብንሰራ ለልጆች፣ ለምርምር በርካታ እውቀት ለመቅሰም የሚያግዝ ስለሆነ ከዚህ የማእከላዊ ኮሚቴ አባላት ትምህርት ቀስመን በየሄዱበት መሰል ተግባር ሊፈጽሙ እንደሚችሉ በማመን ነው። በጥቅሉ በብልጽግና መርህ ውስጥ ትላንትና ውስጥ ያለ አቅም፣ ትላንትና ውስጥ ያለ እውቀት፣ ትላንትና ውስጥ ያለን ጥበብ አላውቅህም፣ አላየሁም ሳይሆን ጎርጉሮ አውጥቶ አስውቦ መጠቀምን መሪ ያደርጋል፣ ያለንን ካላወቅን ማስዋብ አንችልም። በመካከለኛው ምስራቅ የአረብ ሀገራት ለአንድ ሺ ዘመን የሚጠጋ ወይም ከዚያ በላይ በነሱ ምድር በነሱ ከርስ ምድር ውስጥ ነዳጅ ነበር። ግን  ሳይተዋወቁ ለሺህ ዘመናት ተቸግረው ተርበው ደህይተው ኖረዋል። በከርሰ ምድር ያላቸውን ሀብት ያወቁ እለት እና የዓለም ሁኔታ የተመቸ እለት ግን ከዚያ የተገኘው ሀብት ለነሱ ብቻ ሳይሆን ለብዙ ሀገራት የሚውል የዜጎቻቸውን ህይወት ያዘመነ የቀየረ መሆን ችሏል። ያለንን ማወቅ ማለት የሚገባን ተሰጥቶናልና መርምረን ማየት የምንችል ከሆነ ለኛ በቂ የሆነ ምግብ፣ በቂ የሆነ መድሃኒት፣ በቂ የሆነ ሀብት ሊገኝበት ይችላል።

ትላንትናን አስተውሎ፣ መርምሮ፣ አስውቦና አሳምሮ ለትውልድ ማሸጋገር አስፈላጊ ነው። ሁለተኛው ቀጣይነት ነው። አራት ዓመት ሙሉ አንድ ግቢ ውስጥ ምን ሲሰራ ነበር ያላችሁ እንደሆነ ቀድመን የሠራነውን እየጠበቅን መሄድ፣ አዳዲስ እየጨመርን ማስቀጠል ነው። ሦስተኛው ኢኖቬሽን ነው፤ ይህ ቦታ መካነ አራዊት፣ ቦታኒክ ጋርደን፣ አርካይቭ በጣም ሊታዩ የሚችሉ ታሪካዊ ቦታዎች ኖረውት አይደለም። ከዚህ ቀደም ባለው ላይ ተጨምሮ ነው። ያለንን ነገር ማስዋብ ብቻ ሳይሆን አዳዲስ ነገር መጨመር በመላው ሥራችን ውስጥ የሚያስፈልግ ስለሆነ ትምህርት እንደሚገኝበት በመተማመን ቀሪው ደግሞ እሁድ ስለሆነ በጋራ ማእድ እንድንቆርስ ታስቦ ነው።  መልካም የእራት

ጊዜ ይሁንላችሁ። ስለመጣችሁ እጅግ አድርገን እናመሰግናለን። ሠርታችሁ ስትመርቁ ደግሞ መጥተን እናይላችኋለን።

**ግንቦት 29 ቀን 2015 ዓ.ም**
**የአንድነት ፓርክ አዲስ አበባ**



# የአረንጓዴ ዐሻራ የሁለተኛው ምዕራፍ መርሐግብር ማስጀመሪያ መልዕክት

ሰኔ 1 ቀን 2015 ዓ.ም

በዚህ ዓመት የምንጀምረው የሁለተኛው ዙር የመጀመሪያው ዓመት የአርንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር መሪ ቃል ''ነገን ዛሬ እንትከል'' ይላል ። በዚህ ስፍራ እንደምታዩት ይህ ውብ የማንጎ ዛፍ ልክ እንደ ቤት ጥላ ሆኖ ላይን ይማርካል፣ ፍሬው ይበላል፣ ከዚያም አልፎ ልክ እንደ ቤት ያገለግላል። ይህንን ምርጥ ቦታ ያየነው አርቀው በሚያዩ ኢትዮጵያዊን ነው። ትላንት የተከልነው ዛሬ ለኛ ውብ መሰብሰቢያ ቦታ የተውሉን፣ እኛም ለሚቀጥለው ትውልድ የሚተው መልካም ነገር ማኖር ካለብን አንደኛውና ቀላሉ ነገር ነገን ዛሬ መትከል ነው።

ያደላቸው የበረቱ ሀገራት ለልጆቻቸው መሰረተ ልማት ሠርተው፣ ገንዘብ በባንክ አስቀምጠው፣ ጥሪት አኑረው፣ ወረት አኑረው ለልጆቻችን ለሚቀጥለው ትውልድ ይኑር ይላሉ። እኛ ኢትዮጵያዊያን ቢያንስ ቢያንስ ለልጆቻችን ባንክ ገንዘብ ማስቀምጥ ባንችል በየመስኩ በየተራራው የምናኖረው ዛፍ ቢኖር ይህ ዛፍ ምግብ ይሆናል፣ ይህ ዛፍ መድሃኒት ይሆናል፣ ይህ ዛፍ ዓለምን ከሚያሰጉ ዋና ዋና ጉዳዮች ውስጥ አንደኛና ዋነኛ የሆነው የአየር ነብረት ለውጥ በሚመለከት ሊመጣ ያለውን አደጋ ለማስቀረትም በከፍተኛ ደረጃ የሚያግዝ ስለሆነ ዛፍ መትከል መድሃኒት መትከል፣ ዛፍ መትከል ምግብ መትከል፣ ዛፍ መትከል ውበትን መትከል፣ ዛፍ መትከል ኃይለኛ ውሃ ተቀናጅቶ ሊያጠፋን ሲመጣ የሚከላከል አጥር ድንበር መስራት፣ ዛፍ መትከል ከተፈጥሮ ጋር መስማማትና መግባባት ነው።

በዚህ ምክንያት ከምንሰራቸው አንኳር ሥራዎች መካከል አንደኛውና ዋነኛው ተደርጎ የሚወሰድ፣ ለሁላችን የሚጠቅም፣ ለልጆቻችን ደግሞ የሚያኮራ ውርስ ስለሚሆን እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሴት ወንድ፣ ትልቅ ትንሽ፣ መምህር ተማሪ፣ አርሶአደር ነጋዴ፣ ባለስልጣን በተቀናጀና በተደመረ መንገድ ሁላችንም ልንሰራው ልንከውነው የሚገባ አንድ ሀገራዊ ቁም ነገር የወል እውነት ካለ ለልጆቻችን መልካም የሆነና አረንጓዴ የሆነች ኢትዮጵያን መተው ነው። በዚህ ጉዳይ ሁላችንም መረባረብ ይኖርብናል። ባለፉት አራት ዓመታት 20 ቢሊየን ችግኝ ለመትከል አቅደን 25 ቢሊየን ችግኝ

ተክለናል። በዚህኛውም በሚቀጥሉት አራት ዓመታት የዚህን ክረምት ጨምሮ ተጨማሪ 25 ቢሊየን ችግኝ በመትከል በድምሩ ከዓለም አንደኛው ደን የመትከል ፕሮጀክት 50 ቢልየን ችግኝ የመትከል ሥራ ይሆናል።

ከዓለም በድህነት፣ ከዓለም በችግር፣ ከዓለም በድርቅ የታወቅንባቸው ብዙ አሉታዊ ዕውቅና ያገኘንባቸው ጉዳዮች ያሉ። ቢሆንም ቢያንስ 50 ቢሊየን ችግኝ በመትከል በዓለም የመጀመሪያው ከባቢን የመጠበቅ አኩሪ ተግባር ሠራተኞች ስለሆንን እኔም እናንተም እንኳን ደስ ያለን። ለዚህ እድል፣ ለዚህ ክብር ስላበቃን ይሄም በታማኝነት የምንፈጽም ለመሆን ደግሞ እንዲያበቃን እመኛለሁ።

ዘንድሮ የምንጀምረው ሁለተኛው ዙር ከዚህ ቀደም የተከልናቸው የሚለየው በብዛት ብቻ ሳይሆን ጥራት ላይ ያተኮረ መሆኑ ነው። ፍራፍሬ ላይ ባለፉት ሁለት ሦስት ዓመታት በተለይም ማንጎ፣ ሙዝ፣ ፓፓያ፣ አቡካዶን ጨምሮ ሻል ያለ ውጤት አስመዝግበናል። በዚኛው አራት ዓመት ማተኮር ያለብን መንደሪን፣ ጊሽጣ፣ ኮክ ከሁሉ በላይ ደግሞ አፕል ማስፋፋት ይኖርብናል። አፕል በወይናደጋና ደጋ ከፍተኛ ቦታዎች ላይ በስፋት ሊመረት ይችላል። የኛ ከፍተኛ ቦታዎች ደግሞ እንደምታውቁት ለምግብነት የሚውል ዛፍ የላቸውም። አዲስ አበባና ዙሪያዋን ጨምሮ በከፍተኛ መጠን መትከል ያለብን አንድ የፍራፍሬ ዝርያ አፕል ይሆናል ። አፕል በሀገር ውስጥም ከሀገር ውጭም በእጅጉ ያስፈልጋል። እነዚህ ፍራፍሬዎች በምግብ ራስን ለመቻል ያለንን መሻት ለመከወን የሚያግዙ ስለሆነ እየተከልን እግረ መንገድ የምግብ ፍላጎታችንን ለመመለስ የሚያስችል ሥራ እንሰራለን።

ሁለተኛው ትኩረት የሚሆነው አገር በቀል ዛፍ ነው ። የምንተክላቸው ዛፎች ከኛው ጋር የተፈጠሩ፣ የሚኖሩ የሚገጥሙንን መከራ የሚቋቋሙ እንዲሆኑ በአብዛኛው አገር በቀል እንዲሆኑ ይመከራል። በጥራት ላይ ስናተኩር ምግብና አገር በቀል ላይ ካተኮርን ካለምንም ጥርጥር ልጆቻችን ተመራምረው በርከት ያለ መድኃኒት ከዚያ ውስጥ ሊያገኙ ይችላሉ። ጥራትን መሰረት ያደረገ 50 ቢሊየን ችግኝ ኢትዮጵያ ላይ እስከሚቀጥለው ምርጫ ይህ መንግሥት ማሳካት ከቻለ አንድ በዘመናት መካከል የማይናወጥ አሻራ አስቀመጥን ማለት ነው። ይህንን በከፍተኛ የሀላፊነት ስሜት መምራት ስለሚያስፈልግ የሐይማኖት አባቶች፣ መምህራን፣ ተማሪዎች፣ ሙሽሮች ሁሉም ኢትዮጵያዊ በያለበት ስፍራ ይህንን ተግባር በመፈፀም ለልጆቹ አንድ የሚጨበጥ ነገር የመተውን ሥራ እንዲማሩና እንዲያስተምሩ ማድረግንም የህይወት አካል ልምምድን እንዲያደርጉ እዚህ

ያላችሁ ሐላፊዎች መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በከፍተኛ ሐላፊነት ስሜት እንድንከውን አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ።

ዛሬ የምንጀምረው ተከላ በየቀኑ እስከ መስከረም የሚከናወን ይሆናል። በጥራት እንተክላለን፣ በጥንቃቄ እንተክላለን፣ የመብቀል ምጣኔውም ዘንድሮ፣ አምና፣ ካቻምና ከነበረው ሻል እንዲል እናደርጋለን። ይህ የዝናብ መጠንን ይጨምራል፣ የአየር ፀባይ ያረጋጋል፣ የምግብ ፍላጎታችንን በስፋት ለመመለስ ያግዛል። እንደዚህ መልካም አይነት ተግባር ላይ የሚሳተፉ ዜጎች በሙሉ ክብር ሊሰማቸው ይገባል። ከምናጠፋው በርካታ ጊዜ ውስጥ ውስኑን ቀንሰን ኢትዮጵያን በማልበስ ነገን ዛሬ እንድንተክል ሁላችሁንም በታላቅ ትህትና እጠይቃለሁ። መልካም ጅማሮ ያማረ ፍፃሜ ይሁንልን አመሰግናለሁ።

**ሰኔ 1 ቀን 2015 ዓ.ም**
**አፋር ክልል**





# ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት አመራርና ሠራተኞች ጋር የአረንጓዴ ዐሻራ ተከላ መርሐ ግብር

ግንቦት 15 ቀን 2015 ዓ.ም

የዘንድሮ የአረንጓዴ አሻራ መሪ ቃል ''ነገን ዛሬ እንትከል'' ነው የሚለው። ለመትከል ብቻ ሳይሆን አስተማማኝ ነገር መትከላችንን ማረጋገጥ አለብን። ሁለተኛ የዘንድሮ የአረንጓዴ አሻራ ትኩረት ጥራት ነው። ጥራት በፍራፍሬ በአትክልቶች እንደገና በአገር በቀል ዛፍ ላይ ያተኮረ ጥሪትን ማዕከል ያደረገ ሥራ ነው የተሰራው። እዚህ ጋ በምታዩት ቦታ ሙሉ በሙሉ ተራራ ላይ የነበረውን ባህር ዛፍ አስነስተን አፕል ነው የተከልነው። ጨንቻ ነው ያዘጋጀነው፤ ዛሬ አሥር ሺ የአፕል ችግኝ እዚህ ቦታ ተተክሏል። የኛ እቅድ መቶ ሺ አፕል ተክለን በደንብ ተንከባክበን ዘጠና አምስት ሺ ወይም ዘጠና ስምንት ሺ እንዲያበቅል ካደረግን በከፍተኛ ደረጃ ነገን ባስተማማኝ ሁኔታ ለተወሰነ ሰው በምግብ ትርጉም ያለው ውጤት ያመጣል።

ሌላ ቦታ ብርቱካን፣ ሌላ ቦታ መንደሪን፣ ሌላ ቦታ አቡካዶ፣ ሌላ ቦታ ፓፓያ እያደረግን ከሄድን ለምግብ ያለን እጥረት ነገ ላይ ምላሽ እያገኘ ይሄዳል ማለት ነው። ባህር ዛፍ ትላንት ጠቅሞ ሊሆን ይችላል፤ ከአፕል አንፃር ግን ጥቅሙ ያነሰ ነው። አንደኛ አገር በቀል አይደለም የሚጎዳው ነገር አለ። ጥቅሙ እንደተጠበቀ ሆኖ በሌላ መንገድ ደግሞ ከምግብ ዋስትን አንፃር ዛሬ በባህር ዛፍ የተያዘውን ቦታ በአፕል ብናስይዝ ባንድ በኩል አረንጓዴ ይሆናል። ጨንቻ አይታችሁ እንደሆነ በጣም ነው የሚያምረው ራሱ ዛፉ ልክ እንደ ጫካ ነው የሚሆነው። በሌላ መንገድ ደግሞ አፕል እዚህ አካቢቢ እንጠብቃለን፤ ምግብም ከውስጡ እንዲገኝ እናደርጋለን፤ ብዙ ሰው ሥራ ያገኝበታል፤ ቢዝነስ ይሆናል። አፕል የኛ ከፍተኛ አካባቢዎች ላይ በስፋት መትከል ከቻልን ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ለአካባቢም በጣም ተፈላጊ ምርት ስለሆነ ውጤታማ ያደርገናል ።

የኛ ዋናው ትኩረት መጀመሪያ ተክለን ነበር፣ መቆፈሩ ችግር ነበር፣ ችግኝ ማዘጋጀት ችግር ነበር፣ ሰው ማስተባበር ችግር ነበር ። አሁን ብዙ ሰው በየቤቱ መትከል ጀምሯል። አሁን ግን በእውቀት እናድርገው። በእውቀት ሲባል የምንተክለው ነገር አንደኛ የሚበቅል መሆኑን ማረጋገጥ፣ ሁለተኛ የምንተክለው ነገር አካባቢያችንን የማይጎዳ መሆኑን ማረጋገጥ፣ የምንተክለው ነገር በሁለት፣ በሦስት፣ አራት ዓመት ውስጥ የምንበላው ነገር መሆኑን ማረጋገጥ፣ የምንተክለው ነገር አካባቢን የሚጠብቅ የሚያስውብ ብቻ ሳይሆን

ሥራ የሚያሲዝ፣ ምግብ የሚሆን መሆኑን ማረጋገጥ፤ ወደዚህ ደረጃ እያደገ ከሄደ ለሚቀጥሉት አራት ክረምቶች 50 ቢሊየን ችግኝ እንተክላለን ከ50 ቢሊየን ውስጥ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት ቢሊየኑ የሚበላ ከሆነ ከፍተኛ የሆነ ውጤት ያመጣል ።

አሁን እንኳን በአቡካዶ ምርት፣ በአቡካዶ ችግኝ ማስፋፊያ በአረንጓዴ አሻራ ብቻ ከአፍሪካ ከፍተኛ ተብለናል። በዚህች ሁለት ዓመት ውስጥ እንቀይረዋለን። ይህን በግሪን ሌጋሲ ጉዳይ፣ በፍራፍሬ ጉዳይ፣ በምግብ ጉዳይ 2ተኛ 3ተኛ መሆንን መቀበል የለባትም። ኢትዮጵያ ብዙ ቦታ አለ፣ ብዙ ሰው አለን፤ የፖሊሲ ግልጽነ አለ። ጨክንን ከሰራን ውጤት እናመጣለን፤ ውጤት ካመጣን ደግሞ ስማችንን ይቀየራል። በዚህ ጉዳይ ላይ የፖለቲካ ልዩነት፣ የወቅታዊ አጀንዳዎች፣ የህብት ጉዳይ ሁሉ ትርጉም የለውም። ይህን የሚሰራ ሰው የሚሰራው ለልጆቻችን ነው። ለነገ ትውልድ የሚሰራው ለልጁ ለመትከል ዛሬ ስለተጋጨ፣ ዛሬ ስላኮረፈ ዛሬ ስለተቀየመ ልጁን ማስቀየም የለበትም። ያለውን ነገር በእርቅ እንፈታዋለን፣ በተግሳፅ እንፈታዋለን፣ በካሳ እንፈታዋለን ጊዜ ይፈተዋል። ልጆቻችን ግን የኛን ዳፋ፣ የኛን ችግር አሸጋግረን የምናስቸግራቸው መሆን የለባቸውም። በትላንትና ዕዳ፤ ፖለቲካ ዕዳ፣ ኢካኖሚ እዳ ነው። ዛሬን ሥራ ተቸግረን እንድንኖር እያደረጉ ያለው እኛም ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ልጆቻችን ላይ እዳ እንዳናሸጋግር ጥንቃቄ ማድረግ አለብን፤ የምንሰራው ሥራ ለልጆቻችን ነው።

ለትውልድ የምንሰራው ሥራ ለሀገራችን ነው። ሀገር ደግሞ የወል እምነት ናት፣ የወል ሀብት ናት ፤ ትውልድ ደግሞ የወል እምነት ነው የወል ሀብት ነው። ስለዚህ የወል የሆነ ሀብት ላይ ምንም አይነት ምክንያት አያስፈልግም። ማድረግ ነው የሚያስፈልገው። የማንተክለው አሁን ያለው መንግሥት ስለማይመቸን ነው፤ የማንተክለው እኮ አሁን ያለው ፖለቲካ ስለ ማይመቸን ነው የሚሉ አይነት አመለካከቶች ትክክል አይደሉም። ማንም ሰው የውጭ ሀገር ሰው ዜጋ ሲመጣ ማስተከል አለብን። ዲያስፖራ ሲመጣ እርግጠኛ መሆን ያለበት 10 ወይም 15 ችግኝ ተክሎ መሄድ ነው። እኛ ከቦታ ቦታ ስንንቀሳቀስ ይሄንን መትከላችንን ማረጋገጥ አለብን። ለትውልድ ጠቃሚ የሆኑ ፍሬ መሰረት መጣላችንን ማረጋገጥ አለብን። ይሄ ደግሞ እንደ ሰው ርካታ ይሰጠናል፤ እንደ ሀገር ደግሞ ጠቀሚታው ብዙ ነውና። በዚህ እሳቤ በአረንጓዴ አሻራ ላይ በከፍተኛ ትኩረት መስራት ይጠበቅብናል ። የምታስታውሱ ከሆነ አምናና ካቻምና ባዶ ቦታ እየፈለግን ነበር የምንተክለው። አሁን ደግሞ እንደምታዩት ባህር ዛፍ እያነሳን እንተክላለን ለዚህ አላማው ረዘም ላለጊዜ የሚዘልቅና ውጤታማ የሚያደርግ ነው።
እኛ ጨክነን ይዘነዋል እንደተለመደው እናሳካዋለን።

**ሰኔ 17 ቀን 2015 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**






PHILIPS

# ሀገር አቀፍ የጤና ዐውደ ርዕይ መክፈቻ ሥነሥርዓት

ሰኔ 13 ቀን 2015 ዓ.ም

የሳይንስ ሙዚየም ሲመረቅ ዓላማውን እንደገለጽነው፣ የዚህ ሙዚየም መገንባትና መመረቅ ዋነኛ ዓላማ ለትውልድ የሚሆን ነገር መጣል ነው። ትናንትናን መለስ ብለን ማየት የምንችል፣ ዛሬን አበክረን የምንሰራ፣ ነገን ግን የምንዋጅ መሆን ካልቻልን ነገር ሁሉ ዛሬ ከሆነ እዳና ገፊት ለልጆቻችን ስለሚሸጋገር እንደዚህ ያለ ሙዚየም ሠርተን ዓለም ላይ አሁን እያጋጠሙ ያሉ ፈተናዎች፣ ችግሮችና ተግዳሮቶች እንዴት ትውልድ ተገንዝቦ ራሱን ከዚያ መታደግ እንደሚችል ለማስተማር ነው።

ዓለም ላይ በማንኛውም ሰዓት ሊያጋጥሙ ይችላሉ ተብሎ የሚያስፈሩ አራት፣ አምስት ነገሮች አሉ። አንደኛው የአየር ሁኔታ ለውጥ ሲሆን በማንኛውም ሰዓት የከፋ ችግር ሊያስከትል ይችላል። ከዚህ አንጻር አፍሪካ በተሻለ ልትሰራ የምትችለው ነገር ቢኖር የአየር ሁኔታ የሚያስከትለውን አደጋ መካላከል ነው ። ለዚህ ነው የአረንጓዴ አሻራ ሃምሳ ቢሊየን ችግኝ እንተክላለን ብለን ዘንድሮ ሰላሳ ሁለት ቢሊየን ለመድረስ ጀምረናል። እንደምታውቁት የምንተክለው ምግብ ነው፣ የምንተክለው መድሃኒት ነው፣ የምንተክለው ሀገር በቀል የሆኑ ዝርያ ያላቸውን ዛፎች ነው። ይሄ ለኢትዮጵያም ብቻም ሳይሆን ለአፍሪካም ፊር ቀዳጅ በጣም ወሳኝ የሆነ ሥራ ነው። ይህን ተግባር ታስታውሱ እንደሆን በዚሁ የሳይንስ ሙዚየም የግብርና ኤግዚቢሽን ለአንድ ወር ታይቷል ፤ የኤግዚቢሽኑ ዓላማ አሁን ስንዴ እናምርት፣ ሩዝ እናምርት ብቻ ሳይሆን አሁን ዛፍ እንተከልና ከሚመጣው የአየር ንብረት አደጋ ራሳችንን እንከላከል የሚል አንድምታና መልዕክት ለልጆቻችን ያለው ነው።

ሁለተኛውና የሚያስፈራው በቅርብ ርቀት ላይ ያለው አደጋ ከቴክኖሎጂ ጋር የሚያያዝ የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ (ሰው ሰራሽ አስተውሎት) ማንኛውም የሰው ልጅ መረጃ ወደ አንድ ቋት በሚገባበት ሰዓትና ያ የመረጃ ቋት ሲጠቃ የሚያስከትለው አደጋ ከመጀመሪያው የሚያንስ አይደለም። ለዓለምም ከፍተኛ ስጋት ነው ። ከዚህም አንጻር የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ተቋም ተቋቁሟል። ከዚህ ቀደም እንደነበረው በሌሎች ቴክኖሎጂዎች ውራ እንደቀረነው አይሆንም። በጣም የሚያኩራራም ባይሆንም

ጅማሮው በጣም ጥሩ ነው። በዚሁ ሳይንስ ሙዚየም ውስጥ ከአንድ ወር በላይ የቆየ የቴክኖሎጂ አውደ ርዕይ ነበር። በዚያ ልጆቻችንን ማስተማር የፈለግነው አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ የሚያስገኛቸውን ጥቅሞች፣ አደጋ ቢያስከትልብን ደግሞ እንዴት መከላከል እንደምንችል ለማሳየት ነው። እነዚህ ጅምሮዎች ብዙ ሰው እያየ እየተማረ፣ እየጠየቀና እያስተማረ ሲሄድ ቢያንስ እንደ ሀገር በዚህ ዘርፍ ከሚመጣ አደጋ ራሳችንን ለመከላከል ያስችላል ማለት ነው።

ሶስተኛው በጣም የሚያሰጋው ጉዳይ ወረርሽኝ ነው። ኮቪድ ትንሽ ምልክት አሳይቷል፣ ከዛ የከፋው ግን ሊመጣ ይችላል ። አፍሪካን፣ ኢትዮጵያን የሚያሰጋው ነገር በወረርሽኝ የሚመጣ ያልተጠበቀ ያልተዘጋጀንበት አይነት ወረርሽኝ ነው። ከዚህ አንጻር የጤና ሚኒስቴር ብዙ ነገሮች ጀምሯል። ዛሬ በዚህ ኤግዚቢሽን ያየነው ነገር እጅግ ተስፋ ሰጭ ነው። ግን ሊመጡ ካሉ አደጋዎች አበክረን ልንሰራበት ከሚገባው ዋነኛ ጉዳይ አንዱ ጤና ነው ። ጤና ማለት ሆስፒታል ማለት ብቻ አይደለም፣ ጤና ማለት መድሃኒት ብቻ ማለት አይደለም። ጤና ማለት የአኗኗር ዘይቤ ነው አመጋገብ፣ አኗኗር፣ አሰፋፈር፣ የከተማ ፕላን፣ ስፖርት፣ ስለጤና ስለ አመጋገብ ያለን ግንዛቤ ይሄ ሁሉ ተደምሮ በጤናችን ላይ ተጽእኖ አለው። እንደዚያ አይነት ግንዛቤ ልጆቻችን እንዲቀስሙ የሚያስችል ኤግዚቢሽን ነው ይሄ፣ መጥተው ቴክኖሎጂ እንዲያዩና መጥተው ሐኪም የመሆን ህልማቸውን እንዲናገሩ፣ ብቻ ሳይሆን ጤና ማለት የአኗኗር ዘይቤ መሆኑን አውቀውና ተገንዝበው በሁሉም ስፍራ በትምህርት ቤት፣ በሰፈሮቻችንና በእምነት ተቋማት ላይ ሁሉ ልንነጋገርበት ልንማማርበት  የሚገባ ርዕሰ ጉዳይ እንደሆነ ለመገንዘብ ነው።

የጤና ጉዳይ በጣም፣ በጣም ወሳኝ ነው። አሁን ካለው በላይ ደግሞ አደጋው ሲመጣ አስቸጋሪ ነውና ዝግጅት ስለሚያስፈልግ የአሁኑ ኤግዝቢሽን ዋና ትኩረት መሆን ያለበት ትውልድ ላይ ነው። ልጆቻችን ስፖርት መስራት፣ የአመጋገብ ሥርዓታችንን መፈተሽ፣ ጤና ላይ ያለንን ትኩረት በትምህርት ቤት ብቻ ሳይሆን ቤትም መወያየት እየቀጠልን እየተነጋገርን ንጽሃናን መጠበቅ የምንችልበትን እድል ልጆቻችን እንዲፈጥሩ ማድረግ የሚያስችል ነው።

አራተኛው የሚያሰጋው ነገር ጦርነት ነው። በሀገር ውስጥም በሀገር ውጭም በጣም የሚያሰጋ ነገር ነው ጦርነት ፤ ጦርነትን በሚመለከት በቅርቡ ታስታውሱ እንደሆን የደህንነት፣ የፖሊስና የአየር ኃይል ፊልሞች ታይተዋል፤  ይሄ ዝም ብሎ ድንገት የሆነ ሳይሆን ተቋሞቻችን እንዲታዩ ለማድረግ ነው። በእነሱ የሚፈለግ ቴክኖሎጂ እነሱ ሳያውቁት በአንድ ሃይስኩል ወይም ኮሌጅ ሊኖር ይችላል። ለማገናኘት የምንችለው

አጥር አጥረን አትድረሱብኝ በማለት ሳይሆን ተቋማቱ ራሳቸውን ግልጽ እያወጡ ሲሄዱ ተማሪዎች ለካ እንደዚህ ያለ ነገር መከላከያ ይፈልጋል፣ ደህንነት ይፈልጋል ለሀገር ደህንነት የሚያስፈልግ መሳሪያ ነው፣ ሊያስፈልግ ይችላል፣ እኔ ልሰራው እችላለሁ እያሉ እንዲመራመሩ ስለሚያስችል ነው። ይህንን ካጠናከርን ተቋሞችን ከገነባን በሀገር ውስጥ ጦርነትን ለማስቀረት፣ ከውጭ ደግሞ የሚፈጠር ጦርነት ብዙ ነገር ስለሚረብሽ ቢያንስ እንደ ሀገር የመቀጠል እድላችንን ለማስፋት ያስችላል።

አምስተኛው ኢነርጂ ነው። በአረንጓዴ ታዳሽ ኃይል ላይ በአፍሪካ ግምባር ቀደም የምትባል ሀገር ናት። ዘጠና ስምንት በመቶ ገደማ የኃይል ምንጫችን ታዳሽ ነው። በውሃ ላይ እንሰራለን፣ በአየር ላይ እንሰራለን፣ በነፋስ ላይ እንሰራለን እንዲሁም በጂኦተርማል ላይ እንሰራለን። እነዚህን አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል። የኃይል ቀውስ በዓለም ደረጃም በአፍሪካም በተለይ በቅርብ ርቀት የምናየው ነው። የኃይል ፍላጎት ከህዝብ ቁጥር ጋር እያደገ ይሄዳል። በዚያ ልክ ለማምረት መዘጋጀት ከሌለ ደግሞ ሰው የኃይል ጥገኛ እየሆነ ስለሚሄድ በብዙ ይጎዳል ። እናም በህዳሴ፣ በኮይሻና በሌሎች የኃይል ምንጮች ላይ የምናደርጋቸው ኢንቨስትመንቶች ነገ እንደመደራደሪያ አቅም ኢትዮጵያን የሚጠቅሙ ይሆናሉ።

ምን አይነት አደጋ ከፊታችን አለ? እናም እነሱን ለመከላከል ትውልድን እንዴት እናንቃ በሚል እሳቤ ከሚሰሩ ስራዎች አንዱ የሆነው ትውልድን ታሳቢ ያደረገው የጤና ኤግዚቢሽን ዛሬ በይፋ ተጀምሯል። እዚህ ያለን ሰዎች ለማየት፣ ለመማር እድል አግኝተናል። ልጆቻችሁን እንድትጋብዙ፣ አዋቂዎችም እየመጣችሁ እንድታዩ እመክራለሁ። ይህ ልንወያይበትና ልንነጋገርበት፣ የአኗኗር ዘይቤያችንን ልንፈትሽበት የሚገባ ዛሬ በጣም አስፈላጊ ነገ ደግሞ ለልጆቻችን ከፍተኛ አደጋ ሊያስቀር የሚችል ጉዳይ ስለሆነ በሚቆይበት ቆይታ ውስጥ በርከት ያሉ ሰዎች መጥተው እንደሚያዩ፣ እንደሚማሩ፣ እንደሚመራመሩ፣ አንዳንዱ ደግሞ ህልማቸውን ፈልገው እንደሚያገኙ ተስፋ ይደረጋል። ባየነውና ባለው ጅማሮ በጣም ደስ ብሎናል። የጤና ሚኒስቴርና የጤና ማህበረሰብ በሙሉ ኢትዮጵያ ወረርሽኝ ላይ ስጋት ስላለባት አበክራችሁ እንድትሰሩ አደራ ማለት እፈልጋለሁ፤ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ።

**ሰኔ 13 ቀን 2015 ዓ.ም**

**ሳይንስ ሙዚየም**



# የላቀች ኢትዮጵያን ለመገንባት፤ ቀድመን የላቁ ትምህርት ቤቶችን አብረን እንገንባ !

ሰኔ 25 ቀን 2015 ዓ.ም

**የተከበሩ አቶ ታገሰ ጫፎ የኢፌዲሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ፣**
**የተከበሩ አቶ አገኘሁ ተሻገር የፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ፣**
**የተከበራችሁ የክልል ርዕሳነ መስተዳድሮች፣**
**ሚኒስትሮችና ጥሪ የተደረላችሁ እንግዶች፤**

እጅግ በጣም ወሳኝ በሆነ አጀንዳ ላይ ነው የተገናኘነው። ዛሬ ትምህርትንና ትውልድን የሚመለከት ጉዳይ ነው ። ከዚህ ቀደም ዘመናዊ ትምህርት በኢትዮጵያ ሲጀመር ሦስት አካላት የተለየ ሚና ተጫውተው ነበር ትምህርት እንዲስፋፋ። አንደኛው ህዝብ ነው። ቦታውን በመስጠት እንጨት ቆርጦ ክፍሎች በመገንባት የማይተካ ሚና ተጫውቷል፣ በየአካባቢው ትምህርት እንዲስፋፋ ከፍተኛ ድርሻ ነበረው። ሁለተኛው መንግሥት ነው። መምህራን በማዘጋጀት፣ የመማሪያ ቁሳቁስ በማሟላት፣ የትምህርትን ሥርዓት በማበጀት ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። ሦስተኛው በጎ አድራጊ ድርጅቶችና ግለሰቦች የትምህርት ቁሳቁስ አንዳንዴም በነጻ ማስተማርን ጨምሮ ኢትዮጵያ ውስጥ ዘመናዊ ትምህርት እንዲስፋፋና ቢያንስ ሰው በጽሑፍ መግባባት እንዲችል መሰረት ጥለዋል።

አሁን ያለንበት ዘመን ደግሞ ትንሽ አስቸጋሪ ነው፣ ነገር ሁሉ ቴክኖሎጂ እየሆነ ነው። እየመጣ ያለው ዘመን ያልተማረና የመማር መሰረት የሌለው ዜጋ ሀገር በዓለም አውድ ውስጥ መኖር ይቸገራል ። ለዚህም ሲባል መፍጠን አለብን፣ ፈጥነን ሙሉ ትውልድ የሚማርበትን፣ መማር ሲባል በተሻለ ካባቢ የሚማርበትን ነገር ካልፈጠርን በቀር ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ችግርና መከራ ይቀጥላል። ሰብሰብ ብለን ፈጥነን ብንሰራ ግን ለውጥ ማምጣት እንችላለን ከሚል እምነት የተነሳ ነው ትምህረት ለትውልድ የሚለው የክረምት ሥራችን ተጠናክሮ እንዲቀጥል የተፈለገው።

ባለፉት ሦስትና አራት ዓመታት ሙከራ አድርገን ነበር። ከመሰረቱ የህጻናት መዋያን ሳንገነባ፣ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤትን ሳናስፋፋ፣ የሁለተኛ ደረጃ ቅበላችንን ሳናሳድግ፣ የትምህርት ጥራትን ሳንፈጥር በዩኒቨርሲት ላይ ብቻ የምንሠራቸው ሥራዎች ውጤታማ አያደርጉንም በሚል በህዝብ ተሳትፎ ከአሥራ አምስት ሺህ በላይ የህጻናት መዋያዎች ተገንብተዋል። አንዳንድ አካባቢም ህጻናትን ሙሉ በሙሉ ትምህርት ቤት ለማዋል የሚያስችል አቅም ተፈጥሯል። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በሚመለከትም እንዲሁ በርከት ያሉ ተገንብተዋል። የጥራት ጉዳይ፣ የቀለም ጉዳይ፣ ቤቱ የተገነባበት ማቴሪያል ጉዳይ ሊፈተሽ ይችል ይሆናል ቢያንስ ግን መሰረት ተጥሏል። ሁለተኛ ደረጃን በተመለከተም አሁን የምንጀምረውን ጨምረን መጠነኛ ሥራ ብንሰራ በአጭር ጊዜ ውስጥ ኢትዮጵያ ውስጥ ህጻናት ትምህርት ቤት እንዲሄዱ የሚያስችል እድል እንዲያገኙ የሚያግዝ ተግባር ማከናወን ይቻላል።

እዚህ ጋ ሁለት ችግሮች አሉ። አንደኛው በድህነት ምክንያት ሰዎች ቁርስ መብላት ስለማይችሉ ትምህርት ቤት መሄድ ይቸገራሉ፤ ለነሱ ምግብ ማቅረብ ብንችል ወላጆች ልጆቻቸውን ማብላት ስለማይችሉ እነሱን ያግዛል። ከነሱ ውስጥ ደግሞ በርካታ ሳይንቲስቶች፣ ተመራማሪዎችና ሐኪሞች ሊፈጠሩ ይችላሉ። ኢንቨስት እናደርግባቸዋለን፣ ጊዜው ሲደርስ መልሰው ይከፍላሉ ማለት ነው። ሁለተኛው ትምህርት ቤት መዋል ብቻውን በቂ አይደለም መጻሕፍት ያስፈልጋሉ፣ ኮምፒውተር ያስፈልጋል፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ካልተሟሉ በስተቀረ አንድ ቦታ ህጻናት ተሰብስበው ውለው ቢመለሱ በበቂ ደረጃ ትምህርት መሰረት እንዲጥል አያስችልም።
ቁሳቁስ ማሟላትም ያስፈልጋል። ታዲያ ለምን ተገናኘን ዛሬ ያላችሁ እንደሆነ እዳ ስላለብን እዚህ ውስጥ ያላችሁ በየትኛውም የኢትዮጵያ ጫፍ የተማራችሁ ሰዎች አሁን እነዚያ ትምህርት ቤቶች ያሉበት ሁኔታ የእናንተን ድጋፍ ይፈልጋሉ ።

በሆነ ጊዜ ትውልድ ኢንቨስት አድርጎባችሁ በነጻ የተማራችሁ ሰዎች አሁን ተባብረን በመንግሥት፣ በህዝብና በጎ ልብና አእምሮ ባላቸው ሰዎች ትምህርትን ማስፋፋት ካልቻልን በስተቀር በሚቀጥለው ዓለም ውስጥ ተወዳዳሪ ሀገር መሆን አንችልም። ኢትዮጵያ ውስጥ ለሰላም ያለው ፍላጎትና ጉጉት አነስተኛ የሆነው ለትምህርት ካለን ርቀት የተነሳ ነው። የሰላምን ዋጋ የማንገነዘበው በትምህርት ምክንያት ነው፣ እርሻን ማዘመን ያልቻልነው የትምህርት ስርዓታችን ባለበት ችግር ምክንያት ነው ። ራሳችንን የማንመግብ ፣ ሰላማችንን ማነጽና፣ በህብረት፣ በንግግር መኖር የማንችል ህዝቦች ያደረገን የትምህርት ሥርዓታችን ውስንነት ስለሆነ በሚታዩ የአገልግሎት ጥራት

ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የኢትዮጵያ ቁመና ከትምህርት ነው። ያን መሰረት ለመጣል የሚያስችል ንቅናቄ እናደርግ፤ ትምህርት መሰረት ከሆነ ሁለት ነገሮች እናሳካለን። በአንድ በኩል የሚፈጥሩ ሰዎች የመማር መሰረት ካገኙ ይበራከታሉ፣ የሚፈጥሩ ሰዎች ሥራ ፈጣሪ ከሆኑ ደግሞ ራሳቸውን ብቻ ሳይሆን ብዙ ሰው የሚቀጥሩ ይሆናሉ። ሁለተኛው ትምህርት የመፍጠር አቅም የሌላቸው ሰዎች እንኳን ቢሆኑ የመቀጠር አቅም ያላቸው ሰዎች ይፈጥራል፤ በሁለቱም መንገድ ሥራ ፈጣሪ ከፈጠረም፣ መቀጠር የሚያስችል አቅም ከፈጠረም ለሀገር በእጅጉ የሚያግዝ ስለሆነ ሥራ አጥነትን እንቀንሳለን ስንል የትምህርት መሰረት እንጥላለን ማለታችን ነው። ወይ የሚቀጥሩ ወይም የሚቀጠሩ ብቁ ሰዎችን ስለሚፈጥር፣ እርሻን እናዘምናለን ሲባል የትምህርት ሥርዓታችንን እንቀይራለን ማለታችን ነው። እናም ትምህርትን በተባበረ፣ በተጋገዘ ዓላማውን በተገነዘበ መንገድ በአንድ በኩል የተበላሹትን እንጠግናለን፣ የሚያንስ ቦታ እንሰራለን፣ ተሰርተው ቁሳቁስ የጎደለባቸው ቦታዎች ደግሞ ተደጋግፈን እናሟላለን። ቁሳቁስ ተሟልቶ መምህራን ሲያንሱ ደግሞ በጎ ፈቃደኛ በሆኑ የዩኒቨርሲቲ መምህራንና ተማሪዎች ያንን ክፍተት እንሞላለን ልጆቻችንን እናስተምራለን ማለት ነው።

አንዳንዱ በገንዘቡ፣ ሌላው በእውቀቱ፣ አንዳንዱም በመሬት፣ አንዳንዱም በሃሳብ ተባብረን የትምህርት መሰረት መጣል አለብን። የትምህርት ጥራት ማለት የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና አንድ ቦታ ሰብስቦ መፈተን ማለት አይደለም። መሰረቱን መጣል ስለሚያስፈልግ ለዚያ ተረባርበን የተሳካ ውጤት እንድናመጣ፣ የጉዳዩ አስፈላጊነትና አንገብጋቢነት ላይ የጋራ ግንዛቤ እንዲያዝ ከመፈለግም ጭምር ነው ። ፕሮፌሰር ብርሀኑ ነጋ ይህንን ጉዳይ ስላመቻቻችሁና መድረክ ስለፈጠሩ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ። ከጥቂት ወራት በኋላ በሸህ የሚቆጠሩ የህጻናት መዋያ፣ የመጀመሪያ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ገንብተን፣ አድሰን፣ ቁሳቁስ አሟልተን፣ የትምህርት ሥርዓታችን ካለበት ደረጃ ከፍ አድርግን በሪፖርት እንደምንገናኝ ተስፋ አደርጋለሁ ። መኖራችን ካልቀረ ቁምነገር ሠርተን እንለፍ፤ አመሰግናለሁ።

**ሰኔ 25 ቀን 2015 ዓ.ም**
**አዲስ አበባ**





# በጌድዮ ዞን የተካሄደ የልማት ስራዎች ጉብኝት

ሰኔ 28 ቀን 2015 ዓ.ም

**ክቡር አቶ ታገሰ ጫፎ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ፣**
**ክቡር የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ርስቱ ይርዳው፣**
**የተከበራችሁ ሚኒስትሮች፣**

አባ ገዳዎችና በዚህ ስፍራ የምትገኙ ወንድ እና ሴት ኢትዮጵያዊያን በሙሉ፤ ለምለም ወደሆነችው ሰላም ወዳጁ፣ ፈጣሪዋን አክባሪ፣ ከሁሉም ጋር በሰላምና በፍቅር መኖርን የምታምን፣ ተፈጥሮን ጠብቃ ይርጋጨፌን ለዓለም የሰጠችው ውቧ ጌድዮ እንኳን በሰላም መጣን፣ መጣችሁ ልላችሁ እፈልጋለሁ።

የጌድዮን ህዝብ ስናስብ ሁሌም የምናስበው ለሰላም የሚሰጠውን ዋጋ ነው። ጌድዮ በቋንቋው፣ በባህሉ፣ በንግግሩ፣ በአኗኗር ዘይቤው ለሰላም ትልቅ ዋጋ የሚሰጥ ከመሆኑም ባሻገር <<ናጊያኬ ሳማንታን >> ይላል ''ናጊያኬ ሳማንታ'' ማለት ''የተገኘን ሰላም ተሸምቶ ጠብቆ ማቆየት'' ማለት ነው። የሰላም ሽርፍራፊ እንኳን ብትሆን ጠብቆ መጠቀም እንደሚገባ የጌዲዮ ህዝብ ይናገራል፣ ያስተምራል፣ ይኖረዋል። ይህንን በርከት ያልን ኢትዮጵያዊያን ትምህርት መውሰድ ያስፈልገናል፤ የተገኘን ሰላም ተሻምተን መጠቀም እንጂ ማደፍረስ ተገቢ ስላልሆነ።

ጌድዮ እንዲሁ ዝም ብሎ የተገኘን ሰላም ተሻምተን መጠቀም አለብን ብቻ አይልም ትሩፋቱን ይናገራል፤ ያ በመሆኑ ሊገኝ የሚችለውን ትርፍም እንዲሁ በራሱ መንገድ ይገልጸዋል <<ናጌኪ አጌሳያሚርጋን>> ይላል ሰላም ለሰው ልጅ ብቻ ሳይሆን ለቤት እንስሳት፣ ለዱር አራዊት፣ ለከባቢ፣ ለአየሩ ጭምር እጅግ አስፈላጊ ነው። የሰላም ዋጋ እጅግ አብዝቶ የገባውና ትሩፋቱንም እያንዳንዳችን በሚገባን መንገድ መግለጽ ማስተማር የሚችል ህዝብ ስለሆነ መላው ኢትዮጵያዊያን ከዚህ ድንቅ ህዝብ ባህልና ልምምድ ትምህርት እንድንወስድ አደራ ማለት እፈልጋለሁ። ነገር ግን የጌድዮ ህዝብ በምኞት ብቻ አይደለም ሰላም እንጠብቅ፣ ከሰላም እናትርፍ የሚለው። ሰላምን ለመጠበቅ የሚያስከፍለውን ዋጋም በደንብ ይገነዘባል <<ኤሎ የኦንጌን ሄናን>>

ይላል ''ሰላም በነጻ አይገኝም ብዙ የማይመቻቸው የሚረብሻቸው ሰዎች እንኳን ካሉ ከእነሱ ጋር ተቻችሎ መኖር ግድ ነው'' ይላል። ምክንያቱም ሰላም ካለጥረት፣ ካለኢንቨስትመንት፣ ካለመተውና ካለማለፍ የሚገኝ ጉዳይ አይደለም። የጌድዮ ''ሰላም ያስፈልጋል፣ ጥቅምም አለው'' ሲል የሚያስከትለውንም ችግር ተገንዝበን እንድንመራው የሚያስችል ጥበብ የተላበሰ ህዝብ ስለሆነ ትልቅ ትምህርት ሊገኝበት ይችላል። ስለዚህ ሰላምን አብዝተን የምንጠብቅ መሆን ከሁላችንም ይጠበቃል።

ከዚህ ባሻገር ዝምብሎ እንዲሁ ሰላም የሚመኝ፣ የሚያስተምር፣ ዋጋውን የሚገነዘብ ብቻ ሳይሆን ተፈጥሮንና ፈጣሪን አብዝቶ የሚያምንና የሚያመሰግን ስለሆነ <<ኤ ኤ ኤ ማጌኖ >> ይላል ''ሰላም የሰጠንን ፈጣሪ ተመስገን'' ይላል። ኢትዮጵያም ስለተገኘው አጠቃላይ ድል ፈጣሪዋን ታመሰግናለች። ይህ ለሰላም ዋጋ የመስጠት፣ ካባቢን መጠበቅ እንዲሁ በከንቱ የመጣ ሳይሆን የገዳ ሥርዓት ሲወርድ ሲዋረድ ማህበረሰቡን ገንብቶ አስተምሮ የመጣበት አንድ አንኳር የጌድዮ ህዝብ ስጦታና ቸርነት የሚገለጥበት ስርዓት ነው። የገዳ ስርዓት አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ የምንታመስበትን አብዛኛውን ችግር ይፈታል ፤ ራስን በራስ ማስተዳደር፣ ችግር ሲኖር በውስጥ ባህል መፍታት፣ ከጎረቤት ጋር በሰላም መኖር ነባር የሚባል የዲሞክራሲን አሻራና መሰረት የሚያሳይ ስርዓት ነው። ልጆች ያዘጋጃል፣ ልጆች ያስተምራል፣ ስልጣን በሰላም ያሸጋግራል። እኛ ለኢትዮጵያ የምንመኘው ልክ እንደ ጌድዮ ሥርዓት በህግ ተመርጠን፣ በህግ ስልጣን ማስረከብ ሲሆን ለዚህም ደግሞ ልክ እንደ ጌድዮ ሰላምን አብዝተን የምንወድ፣ ሰላምን የምንጠብቅ፣ ለሰላም የምንሰራ፣ ነገር ግን ሰላም የማይፈልጉ፣ በህግና በሥርዓት ስልጣን መሻገር አለበት ብለው የማያምኑ፣ ይህንን ባህልና ልምምድ የሚንቁ ሰዎች ካሉ ደግሞ ለክብራችን፣ ለነጻነታችን መታገልን እንዲሁ ከጌድዮ ህዝብ እንማራለን።

ስለጌድዮ ስናስብ ከዚህ ሁሉ ባሻገር ስለ ተፈጥሮ ሀብት ያለው ጥበቃ ዛፍ መቁረጥ ነውር ነው ብሎ የሚያምን ነው። እንደምታዩት የዚህ ስፍራ ትልቁ አዳራሽ ዛፍ ነው። በዚህ አዳራሽ ውስጥ ሆነን የይርጋ ጨፌን አጣፍጠን ቀምሰን የማንጠግበውን የቡና ጣዕም እንዲሁም ልዩ ልዩ ፍራፌዎች በርከት ያለ ቦታ ላይ የማይታዩ ፍራፍሬዎች ፓፓያው በተለየ መንገድ ትልቅ ነው፣ ሙዙ ትልቅ ነው፣ ጊሽጣ ይታያል፣ ማንጎ ይታያል፤ ከነዚህ ባሻገር ከስድት ሺህ በላይ ትክል ድንጋዮች ያሉበት ቱቱፈላ፣ ቱቱቲቲ፣ ሰዴ በጌድዮ ምድር ይገኛሉ። ይሄ እንደተባለው ለቱሪስት ኢትዮጵያን ለማወቅ ጌድዮን ለማወቅ እጅግ ማራኪ የሆኑ የተፈጥሮ ጸጋዎችና ሀብቶች ያሉት አካባቢ ስለሆነ

ጌድዮ እያለ ያለው ይህንን ትሩፋት ኑና ተዝናኑበት፣ ተመልከቱት፣ ተማሩበት ነው። ኢትዮጵያ በብዙ ተስፋ፣ በብዙ ልምላሜ ውስጥ የምትጓዝ ሀገር እንዲሁም አልፎ አልፎ ስጋት የሚታይባት ጥቂቶች ሊያምሷት ሊረብሿት የሚፈልጓት ሀገር ናት። ይህን ተሻግራ መጥታለች። ጌድዮም ኢትዮጵያ ስትታመስና ስትቸገር ብቻውን ሰላም ሊያገኝ አይችልም ይጨነቃል፣ ያስባል፣ ይጸልያል። የእናንተ ሰላም የመላው ኢትዮጵያ ሰላም እንዲሆን ጌድዮ ጀባት፣ ጌዴኦ ናጌ ኤካቱሬ፣ ገለለቴ ፋታኖን እጅግ በጣም በጣም አመሰግናለሁ ሰላም ይብዛላችሁ፣ ፍቅር ይብዛላችሁ፣ ልምላሜ ይብዛላችሁ። ድንቋን፣ ውቧን ለሁላችን መኖሪያ የሆነችውን ኢትዮጵያን የምትጠብቁ፣ የምትንከባከቡ፣ የምታሳድጉ ከሁሉም ህዝቦች ጋር እንደተለመደው በሰላም በፍቅር፣ በመተባበር የምንኖር ህዝቦች ያድርግን አመሰግናለሁ።

**ሰኔ 28 ቀን 2015 ዓ.ም**
**ጌድዮ ዞን**





# የአርባምንጭ ‘ገበታ ለትውልድ’ ማስጀመሪያ መርሐግብር

ሐምሌ 8 ቀን 2015 ዓ.ም

**የተከበሩ አቶ ታገሰ ጫፎ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ፣**
**የተከበሩ አቶ ርስቱ ይርዳው የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ርዕሰ መስተዳድር፣**
**የተከበሩ ኢንጂኒየር ሀብታሙ ተገኝ የማዕድን ሚኒስትርና የአርባምንጭ ከተማ ሪዞርት ፕሮጀክት ሐላፊ፣**
**የተከበራችሁ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ወጣቶች እንዲሁም በዚህ ስፍራ ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች በሙሉ ’’ሰሮ አይሜሊ ሎዎ’’ እላችኋለሁ።**

የብዙ ሰላም የብዙ ደስታ ምንጭ የሆነች ከተማ ናት አርባ ምንጭ። እዚህ የመጣ ሰው ስጋው ብቻ ሳይሆን ነፍሱን አሳርፎ ነው የሚመለሰው። አርባምንጭ እጅግ ሲበዛ ውብ ሀገር ናት በተፈጥሮ ከታደለችው የመልክዐ ምድር አቀማመጥ በተጨማሪ እንደ ፈጣሪ ፈቃድ ሆኖ እዚህ አካባቢ ያሉ ህዝቦች ሲበዛ ሰላምና ፍቅር የሚወዱ፣ የሚመጣን አብልተው የሚጠግብ የማይመስላቸው፣ ከፊታቸው ሳቅና ደስታ እንደ ምንጩ ሁሉ የሚታይበት በጣም በፍቅር የተሞሉ ሰዎች ያሉበት አካባቢ ነው።

እዚህ ስፍራ እንደዚህ አይነት ሪዞርቶች ሠርተን ብዙ ሰዎች መጥተው እንዲያዩና እንዲደሰቱ፣ ውስጣቸው እንዲያርፍ ካላደረግን ንፉግነት ነው። ብዙ ቦታ ተሂዶ አይገኝም እንደዚህ አይነት ነገርና በዚህ ቦታ የሚሰራው ሥራ ለአርባምንጭ ሳይሆን ለኢትዮጵያ፣ ለአፍሪካ ለሁላችንም በረከት እንደሚያመጣ ይጠበቃል። በርከት ያሉ ባለሀብቶች በዚህ ስፍራ ከኛ በብዙ እጥፍ የተሻለ አዳዲስ ሪዞርቶች ለቱሪስት መስህብ ቦታዎች እንደሚሰሩ እምነት አለኝ። የአርባምንጭ ነዋሪዎች፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ነዋሪዎች መላው፣ የኢትዮጵያ ህዝብ አንድ መገንዘብ ያለበት ነገር አለ። ቱሪዝም ዛሬ በዓለም ላይ በዓመት አንድ ትሪሊየን ዶላር ያመነጫል። ቱሪዝም ዛሬ በዓለም ላይ ከኤሌክትሮኒክስ፣ ከመኪና፣ ከነዳጅ ዋና ዋና ከሚባሉ ገንዘብ ከሚያመርቱ ምንጮች እንደ አንድ የሚቆጠረው ትልቅ ሀብት የሚመነጭበት ሴክተር ስለሆነ። ቱሪዝምን የሚያናንቅ ቱሪዝም የሚያራክስ እሳቤ ትክክል አይደለም። እኛ ኢትዮጵያዊያን እውነት

ለመናገር ሊታዩ የሚችሉ በጣም ድንቃድንቅ ቦታዎች ያሉን ቢሆንም እስከ አሁን ግማሽ ሚሊዮን ዶላር እንኳን አናገኝም። ይሄን የተረሳ ንፁህ ሀብት ሊያመጣ የሚችል ብዙ ሰዎች ሥራ ሊያሲዝ የሚችል ብዙ ሰዎችን የሚያገናኘውን ሴክተር ቸል ማለት ትክክል አይደለም።

በተለይ እንደኛ በተፈጥሮ የታደለ ሀገር ሲሆን በእጅጉ ኢንቨስት መደረግ አለበት። አንዳንድ ሰው ያስፈልጋሉ ወይ ብሎ ጥያቄ ሲያቀርብ ይገርመኛል፤ ያለና የተረፈ ነገር አያስፈልግም የሌለ ነገር በጣም ያስፈልጋል። ማረፊያ ቦታ ፀዳ ያለና ምቹ ቦታ፣ የኮንፈረንስ ቦታ ማዘጋጀት በእጅጉ ያስፈልጋል። ጥቅሙን ደግሞ እናያለን። ሀላላ ኬላ ሲሰራ ያስፈልጋል ወይ ያላችሁ ሰዎች አሁን ሀላላ ኬላ ያች ትንሽ ሪዞርት ምን ያክል የከባቢውን ውበትና ታሪክ እንዳወጣች እያሳያችሁ ነው። እያንዳንዱ የሚሰራው ሥራ በሂደቱ የሥራ እድል መፍጠሩ ብቻ፣ እውቀት መፍጠሩ ብቻ አይደልም። በርከት ያሉ ሰዎች ስለሚያመጣ ሰውና ሰው ያገናኛል ሀብት ያገናኛል አዲስ የሥራ መስክና እድል ይፈጥራል። ልክ እንደ ልማዳችን ዛሬ ጀምረነዋል፣ ጨርሰን እናስመርቀዋለን። በዚህ ምንም አይነት ጥርጣሬ እንዳይገባችሁ በተደጋጋሚ እንዳልኩት እኛ ሳናይ አንናገርም ከተናገርን ደግሞ እንፈፅማለን። ቃላችንን መጠበቅ ተግባራችን ነው።

በአርባ ምንጭም በቅርበት እንከታተላለን፣ አስውበን አልቀን አሳምረን እንጨርሳለን። የምናስረክብበት ቀን በሰላም እንዲሁም በጋራ በደስታ እንገናኝ። የጀመርነውን እንዲያስጨርስ፣ ሰላማችን እንዲበዛ ተስፋችን እንዲለመልም ይህችን ውብ ድንቅ ሀገር ብዙዎች መጥተው እንዲያዩ ፈጣሪ ይርዳን አመሰግናለሁ።

**ሐምሌ 8 ቀን 2015 ዓ.ም**
**አርባ ምንጭ**

# ኛንጋቶም ወረዳ የልማት ስራዎች ጉብኝት

ሐምሌ 8 ቀን 2015 ዓ.ም

**የተከበሩ አቶ ርስቱ ይርዳው የደብብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ርዕሰ መስተዳድር፣**
**የተከበራችሁ ሚኒስትሮች፣**
**የሀገር ሽማግሌዎች፣ ወጣቶች፣**
**እጅግ ውብ የሆነው የኛንጋቶም፣ የባና፣ የፀማይ፣ የአሪ፣ የማሌ፣ የዳሰነች፣ የድሜ፣ የሙሌ፣ የኩይጎ፣ ሄርቤሪ፣ ሙርሲ፣ ባጫ፣ ባዴ፣ ካራ ፣ ቤራይሌና ሐመር ተወካዮችና ህዝቦች፣**

በዚህ ስፍራ ተገናኝተን እናንተን ለማግኘት፣ ያላችሁበት ሁኔታ ለማየትና አብረን የአርንጓዴ አሻራን ለማስቀመጥ እድል ስላገኘን የተሰማንን ልባዊ ደስታና ፍቅር ልገልጽላችሁ እወዳለሁ።

የዚህ አካባቢ ህዝብ ከጦርነት ይልቅ ሰላምን፣ ከበቀል ይልቅ ይቅርታን፣ ከግጭት ይልቅ እርቅን የሚፈልግ መሆኑ በብዙ መንገድ የተገለጸ ብቻ ሳይሆን የታየ ነው። ዛሬ የአርንጓዴ አሻራን ከእናንተ ጋር ማኖር የፈለግንበት ዋናው ምክንያት ከጥቂት ወራት በፊት ቦረና አካባቢ ድርቅ ተነስቶ ብዙ ከብቶችን እንደጎዳና የድርቁ ጉዳይ ሰፋ ያለ ዜና እንደነበር ታስታውሳላችሁ። ወራት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ዛሬ ቦረና በሺህ የሚቆጠር ሄክታር ላይ ስንዴ እያጨደ ይገኛል። ዛሬ ድርቅ ነው ማለት ነገ አንከላከለውም ማለት አይደለም።

በዚህ አካባቢ በቅርቡ ዝናብ አጠር መሆኑ ስጋት ነበር። እንደምታውቁት አሁን የተገኘውን እድል ተጠቅመን ይሄን የመሰለ የኦሞ ወንዝ እንዳያመልጠን፣ ዝናቡም እንዳያመልጠን፣ በመስኖ ፓፓያውን፣ ማንጎውን፣ ሀብሀቡን በመትከል እንደዚህ በፍራፍሬ የተሞላና ብዙዎች ለንግድ፣ ለኑሮ፣ ቱሪስቶችም ሲመጡ ምግብ የማያሳስባቸው አካባቢ እንዲሆን እጅግ ጊዜን መጠቀም ያስፈልጋል ። እዚህ አካባቢ ማዳበሪያ ባይኖር ውሃና መሬትን ብቻ አገናኝተን በርከት ያለ የምግብ፣ የመድሃኒትን፣ የባዮ-ዳይቨርሲቲን መጠበቅ የሚያስችሉ ተክሎችንና አገር በቀል ዛፎች በመትከል የከባቢያችን አየር ፀባይ መቀየር ይቻላል።

ይሄን ማድረግ ትችላላችሁ። ለናንተ ብዙ ሰው አያስፈልጋችሁም ሚንጊ የተባለው አደገኛ ባህል ብዙ ልጆች የሚቀጥፍ ባህል ብዙ ልጆች ጨክነን እንድንጥል የሚያደርግ ባህል ለመቀየር ላሊ የተባለ ግለሰብ የሰራውን ተአምር ታውቃላችሁ። ሚንጊን መቀየር ላሊ በተሰኘ የቁርጥ ቀን ልጅ መስራት ከተቻለ እዚህ አካባቢ ድርቅ እንዳይመጣ ዛፍ ተክለን በመስኖ አካባቢያችንን አልምተን የምግብ ዋስትናን አረጋግጠን የመጣ ሰው ሁሉ በአለባበሳችን፣ በባህላችን፣ በዘፈናችን ብቻ ሳይሆን በምግብ ትሩፋታችንም ደስተኛ ሆኖ እንዲመለስ ማድረግ ይቻላል።

ይህ አካባቢ በድርቅ እንዳይመታ፣ በድርቅ እንዳይቸገር አርንጓዴ አሻራን መለዮ አድርገው የሚሰሩ ወጣቶች ከኛ ውስጥ ወጥተው ከታገልን እንኳን ይሄንን መሬት አርንጓዴ ማልበስ ቀርቶ ሚንጊን ማስቀረት ችላችኋልና አሁንም እንደምትችሉ ሙሉ እምነት ያለኝ መሆኑን እገልጻልሁ። ተባብረን ደቡብ ኦሞን አረንጓዴ ምግብ የሞላባት፣ ባህሏ ታይቶ የማይጠገብ፣ የአዘፋፈን ሥርዓቷ ብዙዎችን የሚስብ በፍቅር የሞላች ከተፈጥሮ የተስማማች ውብ ሀገር ፣ ውብ ከባቢ ለማድረግ ሁላችሁም የበኩላችሁን እንድትወጡ አደራ እላለሁ።

ብንተባበር፣ አብረን ብንቆም፣ ባንናናቅ አንዳችን ከሌላችን መማር ብንችል፣ ኛንጋቶም ውስጥ ትምህርት እንዳለ፣ ዲሚ ውስጥ ትምህርት እንዳለ፣ ሙሪዴ ውስጥ ትምህርት እንዳለ ብናስብ፣ ፀብን ግጭት ብናርቅ፣ በጋራ ሆነን ሀገራችንን መቀየር እንችላለን የሚል እምነት ነው ያለን። መደመር ማለት ' ' ካቻ ካላዳ ኩቼ' ' ማለት ነው የናንተው ባህል ነው፣ የናንተው ሀሳብ ነው፣ የናንተው ጥበብ ነው። እንደመር አብረን እንሁን እንከባበር ሁሉም የራሱን እንዲያስተዳድር ፣ ቋንቋውን ባህሉን እንዲያዳብር በሰላም እንዲኖር፣ ከያንዳንዱ ከባቢ ትምህርትና ዕውቀት እንዳለ እያሰብን በጋራ መቆም ከቻልን አሁን በአርንጓዴ አሻራ በጀመርነው ንቅናቄና ሥራ መላው ዓለም በኛ ቀጣይነት ባለው ተጨባጭ ሥራ አላየሁም ብሎ ማለፍ እንዳይችሉ አድርጓቸዋል።

ማንም ሀገር ሀብታም ቢሆን ብዙ ህዝብ ያለው ቢሆን 50 ቢሊየን ችግኝ መትከል ቀላል ሥራ አይደለም። ብዙዎች 50 ቢሊየን ችግኝ ለመትከልና ከኢትዮጵያ ጋር ለመወዳደር ልክ እንደዚህ አካባቢ ህዝቦች ልባቸው የቀና፣ ሀገራቸውን የሚወዱ አርበኞች የበዙባት፣ ወጥተው ለመትከል ክፍያ የማይጠይቁባት ዜጎች ያስፈልጋሉ። ገንዘብ ችግኝ አይተክልም፣ ገንዘብ ያግዛል ልብ ይፈልጋል፣ ሀገርን መውደድ ይፈልጋል፣ በነፃ መስጠትን ይፈልጋል። የትኛውም ትልቅ ሀገር ዛሬ 50 ቢሊየን ችግኝ እንደዋዛ

መትከል ይቸገራል። ለዚህ ነው በዓለም ትልቁ ከባቢን የማልበስ ስራው አርንጓዴ አሻራ ነው ብለን በድፍረት የምንናገረው።

በቀላሉ አርንጓዴ አሻራን አልፎና ተሻግሮ አዲስ ሪከርድ ማስመዝገብ ለዓለም አስቸጋሪ ነው የሚሆነው። በአርንጓዴ አሻራ ያሳየነውን ህብረት፣ አንድነት፣ ትብብር፣ ትጋትና በነፃ መስጠት በስንዴ፣ በሩዝ ፣ በበቆሎ ፣ በጤፍ፣ በፓፓያ፣ በሙዝ በሁሉም መስክ ብንደግም ለብዙዎች የምንተርፍ ባለፀጋዎች እንሆናለን። የምናየው ነገር መልካም መልካሙን ከሆነ፣ የምንሰራው ነገር መልካም መልካሙን ነገር ከሆነ፣ ከጥፋት ልባችን፣ እጃችንና ዐይናችን ከተሰበሰበ፣ በመከባበር በጋራ ለመኖር ፍቃድ ካለን፣ መሻት ካለን እኛ ኢትዮጵያን ለማበልፀግ የሚያስችል ድንቅ ምድር፣ ድንቅ ተፈጥሮና ህዝቦች አሉን።

ዛሬ በደቡብ ኦሞ ከሚገኙ ደጋግ ህዝቦች ጋር በአርንጓዴ አሻራ ለትውልድ አንድ ነገር ለማኖር እድል ስላገኘን እጅግ ከፍተኛ ክብር ይሰማናል። ስላየናችሁ አብረናችሁ ስለምንተክል የተሰማኝን ልባዊ ደስታና ፍቅር እየገለጽኩ፤ አርንጓዴ አሻራን ከባቢን መቀየርን ዛሬም ነገም ደጋግማችሁ የየዕለት ሥራችሁ በማድረግ ድርቅን ከራሳችሁ፣ ረሃብን ከራሳችሁ፣ ችግርን ቸነፈርን ከራሳችሁ እንድታርቁ አደራ ማለት እፈልጋለሁ። ስለነበራችሁ አቀባበል፤ ስላለን ጊዜ እጅግ ከፍተኛ ደስታና ክብር ይሰማኛል።

**አመሰግናለሁ።**

**ሰኔ 30 ቀን 2015 ዓ.ም**

**ኛንጋቶም ልዩ ወረዳ**





# በኮንሶ የልማት ሥራዎች ጉብኝት

ሰኔ 30 ቀን 2015 ዓ.ም

ኮንሶ፤ ካንሳ ናጋይታው ዛሬ በዚህ ድንቅ ስፍራ ተገኝተን በጋራ ነገን ለመትከል፣ ለልጆቻችን መልካም ነገር ለመተው፣ ኮንሶን ለማልበስ እድል ስላገኘን የተሰማኝን ታላቅ ደስታና ፍቅር ልገልጽላችሁ እወዳለሁ። በተለያየ ምክንያት ስለ ኮንሶ ለማወቅ እድል ነበረኝ። የኮንሶ ህዝብ እርከን በመስራትና አፈርንና ውሃን በመጠበቅ ያለው ልምድና ብቃት ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ከፍተኛ የሆነ አስተማሪ ተግባር ነው። ከዚያም ባሻገር ዘር እያፈራረቁ ወቅትን ጠብቆ ከባቢን የማልማት በምግብ ራስን ለመቻል የሚደረገው ጥረት ለብዙዎቻችን ትምህርት ሆኖ ዛሬ በብዙ ቦታ እርከን ማስፋት፣ ችግኝ መትከል፣ ምግብ መትከል፣ መድሃኒት መትከል፣ አካባቢን መቀየር ከኮንሶ ታታሪ ህዝብ የተማር ነው ትምህርት ነውና እንኳን ደስ ያላችሁ ልላችሁ እፈልጋለሁ።

የኮንሶ ህዝብ በአንድ ታሪክ ይታወቃል። አንድ የኮንሶ አምባሳደር ምርጥ ሙዝ፣ ምርጥ ፓፓያ ወይም ምርጥ ዘር ካለው ጎረቤቱም እንደዛው ያን ምርጥ ነገር ተክሎ በጋራ ማድረግን የሚያምን ህዝብ ነው። ይህንን ደግሞ ከተፈጥሮ ጋር በማያያዝ በጐረቤት የተሻለ ዝርያ ያለው እርሻና ዘር ከሌለ የኔ ብቻ ከሆነ አንድም በነፋስ ምክንያት የሚመጣ ዝርያ ዘሬን ያበላሽዋል በሌላም መንገድ ብቻዬን ልበላ አልችልም ብሎ በማመን ፣ አካባቢውን ተራሮችን በሙሉ የሴት ልጅ ሹርባ በማስመሰል የሚታወቀው የኮንሶ ህዝብ ተፈጥሮን የሚታገልና የሚያሸንፍ ብቻ ሳይሆን ተፈጥሮን የሚያስወብና ለመጠቀም ምቹ የሚያደርግ ህዝብ ነው ። ለዚህ ምስክሩ በኮንሶ ዞን ብትሽከረከሩ መንግሥት የሠራው ሳይሆን የኮንሶ ወጣቶችና ብርቱ ልጆች የሰሩት በጣም በርካታ መንገዶች ይታያሉ። ተራራን በእርከን መንገድን ደግሞ በእጅ እየሰራ ለኑሮ ምቹ የሚያደርገው የኮንሶ ህዝብ ዛሬ ለኛም ትምህርት በሰጠን መንገድ ነገን ዛሬ ተክሎ የድርቅም የዝናብ አጠር ከባቢ ስያሜ በመቀየር ለምለም አርንጓዴ የለበሰ ኮንሶን ለልጆቹ ለማሸጋገር ዳግም ቃል የምንገባበት ቀን ይሆናል።

ኮንሶዎች በጥበብ የተሞሉ ናቸው። ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩበት ‘ ‘ ሩላንስ’ ’ የሚባል የአስተዳደር ሥርዓት አላቸው። የኮንሶ ህዝብ ጥንታዊ ህዝብ

ስለመሆኑ የጥንት የድንጋይ መሳሪያዎቹን ለማየትና ነባር ህዝብ መሆኑን ለማወቅ የሚፈልግ ሰው ሁሉ ዛሬ ዘመን አፈራሽ መሳሪያ ሳይሆን በጣም በርካታ ልማት የሠሩ የድንጋይ መሳሪያዎችን በኮንሶ አካባቢ ማየት፣ መማር የሚያስችል ጥንታዊነትን በተግባር በማስረጃ ያረጋገጠ ህዝብ ስለሆነ እንኳን ደስ አላችሁ ልላችሁ እፈልጋለሁ። የኮንሶ ሽማግሌዎች ከሞት አፋፍ ይታደጋሉ። የሚጋጭ፣ የሚገዳደል፣ የሚጠፋፋ ወጣት የማስከንና እድሜውን የመጨመር አቅም አላቸው <<ቂሞታ ቶሆታፋ ናማን ካሪራ >> ይባላል። ሽማግሌዎች ከሞት አፋፍ ከጥፋት አፋፍ ዜጎችን መታደግ ይችላሉና ኮንሶዎች ለኢትዮጵያ በሙሉ የሽምግልና አርአያ በመሆን ከመሬት ተነስቶ ጠብ የሚያምራቸው መገዳደል፣ መጠፋፋት የሚያምራቸው ግለሰቦች እንድትመክሩ እንድታስተምሩ በሰላም በፍቅር በትብብር ኢትዮጵያን አበልጽገን ሁላችንም የምንደሰትባት ሀገር እንድንፈጥር ካንሶዎች አስተማሪ ሚና እንድትጫወቱ በታላቅ ትህትና እጠይቃችኋለሁ።

ዛሬ ምግብ እንተክላለን፣ መድሀኒት እንተክላለን፣ ሀገር በቀል የሆኑ ተክሎች በመትከል አካባቢያችንን አርንጓዴ ። ልጆቻችን በፍጹም በከባቢ አየር ለውጥ ምክንያት የሚፈጠሩ ድርቅ አለ ሳይሆን የድሮ አባቶች እርከን ሠሩ፣ የአሁን አባቶች ደግሞ ምግብ ተከሉ ብሎ እንዲያመሰግን የሚያስችል አሻራ በጋራ ለመትከል እዚህ ተገኝተናልና ሁላችንም አካባቢያችንን አረንጓዴ በማልበስ እርከኑንና በተጨማሪ ምግብና መድሃኒት ለልጆቻችን በመትከል መልካም ኮንሶን እንድናሸጋግር አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ። ይሄንን በማድረግ ታሪክ እንደምትደግሙ ያለኝን ሙሉ እምነትና ተስፋ ልገልጽላችሁ እወዳለሁ።
ነጋይታ ኮንሶ ! በጣም በጣም በጣም አመሰግናለሁ።

አብረን እንትከል፣ አብረን እንሻገር፣ እንደመር ኢትዮጵያን እናጽና። አመሰግናለሁ።

**ሰኔ 30 ቀን 2015 ዓ.ም**
**ኮንሶ**

# የ500 ሚሊየን ችግኝ በአንድ ጀምበር የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብርን ማስጀመሪያ

ሐምሌ 10 ቀን 2015 ዓ.ም

ኢትዮጵያዊያን በተለይም ዛሬ በጠዋት በዚህ ዝናብ ወጥታቸሁ ችግኝ ለምትተክሉ አርንጓዴ ለምታለብሱ ብርቱ ዜጎች በሙሉ፤ ዛሬ ኢትዮጵያዊያን በህብረት ተዓምር የምንሰራበት ቀን ነው ። እኛ እንዲህ የቀለለን እንደዋዛ የምናየው ጉዳይ ብዙዎች ቢፈልጉም አልቻሉም። ህፃናት አሉ፣ አረጋዊያን አሉ፣ አካል ጉዳተኞች አሉ፣ ሴቶች አሉ፣ እናቶች አሉ። ኢትዮጵያዊያን በሙሉ በእድሜ፣ በፆታና በአካል ሁኔታ ሳይወሰን አገራቸውን አርንጓዴ አልብሰው ለነዚህ ልጆች መልካም ሀገር ለመተው መወሰን፣ መቁረጥ መስራት ትልቅ መታደል ነው፤ በየቦታው ሥራችንን መትከል ነው።

ዝናቡም ጥሩ ነው። ሁላችሁም እንዳያችሁት የተከልነው የአፕል ዛፍ ነው። በዚህ አካባቢ የምንተክላቸው የአፕል ዛፎች ወደፊት አዲስ አበባ ላይ ያለውን የፍራፍሬ እጥረት ለመቅረፍ ምግብ ሆነው የሚያገለግሉን፣ገበያ ሆነው የሚያገለግሉን፣ ሥራ አጥነትን የሚቀንሱ በቀጥታ ህይወታችንን የሚነኩ ጉዳዮች ስለሆኑ የተሻለ ሀገር ለመፍጠር ነውና እንኳን ደስ ያላችሁ፣ እንኳን ደስ አለን፣ ይቀጥላል በርቱ ማለት እወዳለሁ። እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ።

**ሐምሌ 10 ቀን 2015 ዓ.ም**
**አዲስ አበባ**



# በየካ ተራራ ከሚገኙ የ1ኛእና የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች ጋር የ500 ሚሊየን በአንድ ቀን የአረንጓዴ ዐሻራ የችግኝ ተከላ

ሐምሌ 10 ቀን 2015 ዓ.ም

ዛሬ በሀገር ደረጃ 500 ሚሊየን ችግኞች ለመትከል ኢትዮጵያዊያን ወስነን በጋራ ተነስተናል። ቀደም ሲል እንዳያችሁት አካል ጉዳተኞች፣ አረጋዊያን፣ እናቶች፣ ህፃናት ልጅ ያዘሉ እናቶች ኢትዮጵያዊ ሁሉ እንዳትቀር በተባለው መሰረት ወጥቶ እየተከለ ይገኛል። አሁን በእለቱ ካቀድነው በሀገር ደረጃ ከግማሽ በላይ ሄደናል። ካልነውም በላይ እንደምንሄድ የሚያመላክቱ ነገሮች አሉ። መትከል ይቀጥላል። እንዳያችሁት እኔም በጣም በርከት ያሉ ተክያለሁ አሁንም እቀጥላለሁ። ምንአልባት ቤታቸው የቀሩ ዝናቡ የአየሩ ሁኔታ ያስቀራቸው ሰዎች ካሉ፣ ሰንፈው የቀሩ ሰዎች፣ በሥራ ተይዘው በሌላ ምክንያት ተይዘው ያሉ ሰዎች ካሉ እንዳያመልጣቸው ግማሽ ቀን ነው ያለውና ወጥተው አሻራቸውን እንዲያሳርፉ ነገ እንዳይቆጫቸው እንደው አደራ ውጡና ትከሉ፣ ግድ የለም ደስ የሚል ሁላችንንም የሰበሰበን ያስተሳሰረን ተግባር ነው፤ እንደ በዓልም ነገር ነው። በጣም ጥሩ ትውስታም ስለሆነ ከልጆቻችሁም፣ ከቤተሰብ ጋር ብትተክሉ መልካም ነው ብለህ መልክት አስተላልፍልኝ እኔ ከልጄ ጋር እየተከልኩኝ ነው።

በጣም ጥሩ ጊዜ ነው ያለንና ኢትዮጵያዊያን በሙሉ የተከላችሁ እንድትደግሙ፣ ያልተከላችሁ እንድትወጡ አደራ ማለት እፈልጋለሁ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ።

**ሐምሌ 10 ቀን 2015 ዓ.ም**
**የካ ተራራ- አዲስ አበባ**



# የ500 ሚሊየን ችግኝ በአንድ ጀምበር የመዝገብ መርሃ ግብር

ሐምሌ 10 ቀን 2015 ዓ.ም

**መላው የኢትዮጵያ ህዝብ፤**

ከሁሉ አስቀድሜ እንኳን ደስ ያላችሁ፣ እንኳን ደስ ያለን ዛሬ ለኢትዮጵያ፣ ለአፍሪካም፣ ለመላው ዓለም ትልቅ ትምህርት የሚሰጥ እጅግ የሚያኮራ ተግባር ፈጽመናል። ለዚህም ሁላችንም እንኳን ደስ ያለን ማለት እፈልጋለሁ። የአየር ንብረት ለውጥ በዓለም ላይ ስጋት መሆኑ ታምኖ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ንግግር ከተጀመረ ዋል አደር ብሏል። በየቦታው ሰብሰባዎች ንግግሮች አሉ። ነገርግን ኢትዮጵያ በጀመረችው መንገድ በተግባር ችግሩን ለመፍታት የተደረጉ ሥራዎች እምብዛም ጠንካራዎች አይደሉም። ኢትዮጵያ ሀምሳ ቢሊየን ችግኝ እተክላለሁ ብላ አስባ ሀብቷን ሳይሆን ዜጎቿን ተማምና እጅግ የሚያኮራ ሥራ ጀምራለች። ውጤቱም ለኛም ለተቀረው ዓለምም እጅግ የሚያኮራ ነው።

ዛሬ አምስት መቶ ሚሊየን ችግኝ ለመትከልና 34 ሚሊየን ያላነሱ ዜጎችን ለማሳተፍ አቅደን ከጠዋት ጀምረን ስንተክል ውለናል። አሁን ከሲችዌሽን ሩም ባገኘሁት መረጃ መሰረት የተተከሉበት ቦታ የሚታወቁ (geo referenced የሆኑ)  ከዚህ ሆነን የት እንደተተከሉ የምናውቃቸውን ችግኞች ብቻ ነው የምገልጸው። ክልሎች በጂኦ ስፓሻል  ያልታቀፉ ዳታቸው በትክክል እኛ ዘንድ ያልደረሰ ቁጥሩ ከፍ ያለ ችግኝ ተክላችሁ ሊሆን ይችላል። በየጓሮውና በየበረንዳ የተተከለውን አይጨምርም። ይሄ አሁን ሪፖርት የማደርግላችሁ እያንዳንዱ ተክል የትቦታ እንደተተከለ የምናውቀውን ብቻ ነው። እና እስከዚህ ስዓት ድረስ 566 ሚሊየን 971 ሺህ 600 ችግኝ ዛሬ በ302,000 ሄክታር ላይ ተተክሏል።

ይህ እጅግ፣ እጅግ ትልቅ ድል ነው። ከክልሎች የመጣልን ሪፖርት 367,000 ገደማ ሄክታር ይደርሳል። ነገር ግን በጂኦ ስፖሻል እኛ ጋ የደረሰው 302,000 ስለሆነ ከዚህ ባሻገር የተከላችሁትን ችግኞች በጥቅሉ ደምረን በክረምት በያዝነው እቅድ ውስጥ ልናስገባው እንችላለን። ዛሬ ግን ሪፖርት የምናደርገው መቶ በቶ ቦታቸው የሚታወቁና በጂኦ ስፖሻል የተለዩትን ብቻ ነው። ያን የምናደርገበት ዋናው ምክንያት የምንተክለው ለብዙ ተግባር ነው። አካባቢያችንን አረንጓዴ ለማድረግ ብቻ አይደለም፣ በካርበን ሽያጭ ገንዘብ ማግኘት እንፈልጋለን። በዚህ ዓመት ሰምታችሁ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ፤ 52 ሚሊየን ዶላር ገደማ ካርበን ሽያጭ አግኝተናል። አረንጓዴ አሻራን እንደጀመርን በአየር ንብረት ለውጥ ላይ እንደምንሰራ ከታመነ በኋላ ከጥቂት ተቋማት ጋር ሁለት ስምምነቶች ተስማምተን 52 ሚሊዮን ዶላር አግኝተናል። ነገር ግን ከዛ በላይ ማግኘት የሚያስችል አቅም ኢትዮጵያ አላት። ይህን ለማድረግ ከሚጠየቀው መስፈርት አንዱ እያንዳንዱ ችግኝ የተተከለበት ቦታ ይታወቃል ወይ የሚል መረጃ እንደ ቅድመ ሁኔታ ይወሰዳል። አሁን በሪፖርት ያቀረብነው በዚያ መስክ በዓለም አቀፍ ስታንዳርድ ተቀባይነት ያለውን ብቻ መሆኑን ተገንዝባችሁ ከዚያ በላይ የተከላችሁ ክልሎችና አካባቢዎች በክልል ክረምት የድምር የአረንጓዴ አሻራ ፕሮጀክት አካል ተደርጎ ሪፖርታችሁ ሊታይ ይችላል።

ዛሬ ግን ከ566 ሚሊየን በላይ ችግኞች ተክለናል፤ ይህ ከዕቅዳችን ከፍያለ ነው። 33.5 ሚሊየን ገደማ ዜጎች ከህፃን እስከ አዋቂ፣ አረጋዊያን፣ አካል ጉዳተኞች በስፋት ተሳትፈውበታል። እጅግ ደስ የሚል ቀን ነበር። በየሄድንበት በጋራ ስንስቅ ስንጫወት ስንተክል ነው የዋልነው። ይህ እንግዲህ ትርጉሙና ውጤቱ የሚታወቀው በትውልድ ላይ ነው። በሀገራችን አንድ አባባል አለ ''ለልጆችህ ዛፍ እንጂ ደም አታውርስ'' ይባላል ፤ ደም የሚያወርሱ ቤተሰቦች ልጆቻቸው በሰቀቀን እንዲኖሩ ያደርጋሉ፣ ከዛሬ ነገ ሊበቀለኝ የመጣ ሰው በደጄ ይቆማል ብለው ሳይተኙ እንዳያድሩ ያደርጋቸዋል። ዛፍ ያወረስናቸው ትውልዶች ግን ቢያንስ ቢያንስ የሚበላ እንኳን ቢያጡ ከዛፉ ስር በጥላ ከዝናብ ከፀሐይም መጠለል ይችላሉና ለልጆቻችን ደም ሳይሆን ዛፍን፣ ችግኝን የተሻለ መልከዐ ምድርን የምናወርስ ዜጎች መሆናችን ሊያኮራን እንደሚገባ ላሳስባችሁ እፈልጋለሁ።

ዛሬ በመላው ኢትዮጵያ ህዝብ ጥረት  እጅግ ከፍተኛ የሆነ ኩራት ተሰምቶኛል፣ ሞራልም ሰጥቶኛል። እኛ ኢትዮጵያዊያን ብንሰበሰብ በሌሎች ችግሮቻችን ላይ ምን ማድረግ እንችላለን? ድህነት ላይ፣ ሰላማችን ላይ፣ በምንፈልጋቸው ሥራዎች ላይ፣

የደሆችን ህይወታቸውን የማሻሻል ጉዳይ ላይ ምን ያክል ጉልበት እንዳለን ያየሁበት እለት ነው። መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ዛሬ የሠራነውን አስደናቂ ገድል ለሌሎች መስኮች መድገም እንድንችል ከቁጡነት፣ ከኩርፊያ፣ ከፀብ፣ ከግጭት፣ ከጥላቻ፣ ከመገፋፋት ራሳችንን ጠብቀን፣ ስሜታችንን ገትተን የተሻለ ሀገር ለልጆቻችን ማሸጋገር እንድንችል ከዚህ ባሻገር ሰብሰብ ብለን ልናከውናቸው የሚገቡ ጉዳዩች እንዳሉ ይሰማኛል። በየቦታው ያልተዘጉ ፋይሎች አሉ። ሁላችሁም እንደምታውቁት ኢትዮጵያ በኢኮኖሚ ድህነትን፣ በሰላም ግጭትን ጦርነትን ያልተመለሱ በርካታ ጥያቄዎች የወረሰች አገር ናት። ይሄ ሁሉ ችግር እኛ ላይ መውደቁን እንደ እድል ወስደን ለመፍታት የምንተጋ ዜጎች ልንሆን ይገባናል። የመጀመሪያው ነገር ችግሩን መገንዘብ ያስፈልጋል። ለምሳሌ በአንዳንድ አካባቢ የወሰን ጥያቄ የሚነሳባቸው አካባቢዎች አሉ። ለወሰንና ለመሬት ሲባል ግን ከእንግዲህ በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ ሰው እንዲሞት መፍቀድ አይኖርብንም። ሰው እንዲሞት ከፈቀድን ያመሬት በራሱ ሰው የበላ መሬት ስለሆነ መልሶ ለጥቅም ማዋል የኔ ብሎ ለማሰብ ያስቸግራል። በጣም ጥሩ የሚሆነው በረጋና በሰከነ መንፈስ በውይይት ሁሉንም አሸናፊ በሚያደርግና በሚያስማማ ሁኔታ አብሮ በሚያኖር አካኋን በህግ መፍታትን መለማመድና መፍቀድ አለብን።

ከዚህ ውጭ ያለ አማራጭ በየጊዜው የሚያጣላን የሚያጋጨን ስለሆነ ግጭት ደግሞ የደም መሬት እንጂ የዛፍ መሬት ስለማያደርግ ደምን የምናሸጋግር እንጂ ዛፍን የምናሸጋግር ስለማያደርገን ፖለቲከኞች፣ አክቲቪስቶች፣ በተለያየ ክልል ያላችሁ ሰዎች በተደጋጋሚ እንዳነሳሁት ዛሬም በታላቁ ድል ቀን፣ ታላቅ ሥራ ባከናወንበት ቀን በድጋሜ በትህትና ልጠይቃችሁ የምፈልገው መባላት፣ መሰዳደብ፣ መዋጋት፣ መገፋፋት ይብቃን፣ ወደ ሰላም መጥተን ተባብረን ኢትዮጵያን ለመቀየር እንትጋ፣ እንሥራ ማለት እፈልጋለሁ። የኢትዮጵያ ህዝብ እያንዳንዱ ሰው ወጣ ብሎ በተለያየ የአፍሪካ ሀገር ምን እየተደረገ እንዳለ መገንዘብ ቢችልና ከራሱ ሁኔታ ጋር ቢያነጻጽር ስለ እውነት ለመናገር ኢትዮጵያ ተስፋ አላት፣ ኢትዮጵያ እያደገች እየተሰራች ያለች ሀገር ናት። ይህንን ነገር ለመገንዘብ ሁላችንም መዞር አንችልም፣ ሁላችንም አይተን አነጻጽረን መገንዘብ አንችልም፣ ያየን ሰዎች ስንናገር ያላየን ሰዎች ግን ቢያንስ በማመን መተባበር ይጠበቅባችኋል።

በአፍሪካ ውስጥ አመሪቂ ሥራ እየሰሩ ካሉ ሀገራት ምናልባት ከጥቂቶቹ አንዱዋ ኢትዮጵያ ናት። በዚያው ልክ ደግሞ ችግሯ፣ ጣጣዋ፣ መከራዋ ብዙ ሊሆን ይችላል። ልክ ዛሬ እንዳደረግነው ሰብሰብ ብለን እየመረጥን በጋራ የምንዘምት ከሆነ ግን ሁሌም እናሸንፋለን። በአድዋ ለአፍሪካ ትምህርት፣ ለዓለም ትምህርት ሰጥተናል።

ዛሬ አረንጓዴ አሻራ 566 ሚሊየን ችግኝ በአንድ ቀን የተከለ ሀገር ሌለ ታላቅ ታሪክ ሠርተን ለብዙዎች ትምህርት የሚሆን ለብዙዎች የሚተርፍ ድንቅ ሥራ ስለሰራችሁ ሁላችሁንም እጅግ አብዝቼ ላመሰግናችሁ እወዳለሁ። የሠራነውን ሥራ ውጤት ነገ ከነገ ወዲያ እናየዋለን፣ በልጆቻችን ህይወት እናየዋለን፣ በእኛም ሀገር እናየዋለን፣ እያየነው መጥተናል እናየዋለን፣ ዛሬ ከተከልነው ውስጥ 30 በመቶ ገደማ ለምግብነት የሚውል ፍራፍሬ ያለበት ነው።

ይህ አድጎ ፍሬ በሚሆንበት ሰዓት ምን ሊያመጣ እንደሚችል ሁላችሁም አስቡት። እኔ በዋልኩበት የካ አካባቢ 46,000 ሺህ የአፕል ችግኞች ተክለናል። 46,000 የአፕል ችግኝ ማለት ቀላል ነገር አይደለም። በርከት ባለ ስፍራ ሙዝ፣ ፓፓያ፣ ሀብሀብ እንዲሁም ማንጎ የተከሉ ዜጎች አሉ። በዛ በተከልነው ውስጥ ቡናን አናካትትም፣ ከቡና ውጭ ነው ሪፖርት እየቀረበ ያለው። እነዚህ ሁሉ የምንመገባቸው፣ ሽጠን ገንዘብ የምናገኝባቸው ስለሆኑ ለኛም የሚጠቅሙ፣ ለልጆቻችንም የሚሸጋገሩና የሚተርፉ እጅግ አስደማሚና ውጤታማ ሥራ ሥንሰራ እንደዋልን ይሰማኛል። በዚህ የተሳተፋችሁ በጣም በርካታ ዜጎች አላችሁ በማይመች ሁኔታ በዝናብ ውስጥ መኪና ሳይኖራችሁ በዝናብ ውስጥ ተጉዛችሁ በርከት ያለ ችግኝ የተከላችሁ ኢትዮጵያውያን እኛ እያንዳንዳችሁን አግኝተን ማመስገን አይቻለን ይሆናል። ግን ያው በትውልድ ውስጥ ስራችሁ ይታያልና ሁላችሁንም ከልብ ላመሰግን እወዳለሁ።

በዚህም በአርቲፊሻል ኢንተለጀንስና በኢነፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ቅጥር ግቢ ውስጥ ዛሬ መላው ሠራተኛና ኢንጂነሮች በድፍን ኢትዮጵያ የነበረውን ዳታ እያሰባሰቡ መጣል ያለበትን ከአስር በመቶ በላይ እየጣሉና የተጣራ ዳታ ሲያቀናጁ ውለው አሁን ከመሸ በኋላ የምናቀርበውን ሪፖርት ያዘጋጁ፣ ቀኑን ሙሉ የተጉ ሠራተኞችና መያተኞች እጅግ አድርጌ ማመስገን እፈልጋለሁ። ከ3000 በላይ የሚዲያ ሞያተኞች በሀገር ደረጃ ተሰማርተው የዛሬን ውሎ ሲዘግቡ ውለዋል። እነዚህን ሪፖርተሮች እጅግ አድርጌ ማመስገን እፈልጋለሁ።

የተሳተፉትን ዜጎች በሙሉ በሙያ፣ በመትከል፣ በማስተባበር ገዝቶ በመስጠት የተሳተፉትን ዜጎች በሙሉ እጅግ ከፍ ያለ ምስጋና ላቀርብ እፈልጋለሁ። የአፍሪካዊያን ወንድሞቻችን ከዚህ ድንቅ ተግባር ትምህርት ወስደው እነሱም በአካባቢያቸውና በሀገራቸው ይህንኑ ተግባር እንደሚደግሙ ተስፋ አደርጋለሁ። ኢትዮጵያ ብቻ ቢተከል

ትርጉም የለውም፣ በሁሉም ሀገር ዛፍ እንድንተክል በሁሉም ሀገር ንፁህ ውሃ ማበራከት እንድንችል፣ ውሃ የሁሉም ነገር ምንጭ ነው፣ የህይወት ምንጭ ነው፣ ውሃ ከሌለ ብዙ ችግር አለ፣ ውሃን ማብዛት ማበራከት መጠበቅ በእጅጉ አስፈላጊ ስለሆነ በብዙ ድሎቻችን ላይ የተጨመረ ታላቅ ድል ነውና እንኳን ደስ ያላችሁ። እንኳን ደስ ያለን ማለት እፈልጋለሁ ፤ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ።

**ሐምሌ 10 ቀን 2015 ዓ.ም**
**አዲስ አበባ**



# የኢትዮጵያ ትልቁ ኤሊት ኃይል የምረቃ ሥነ ሥርዓት

ነሐሴ 6 ቀን 2015 ዓ.ም

በዚህ ዓመት በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ኤሊት ኃይል በሀገር ውስጥና በተለያዩ ሀገራት አሰልጥነን ሙሉ የኮማንዶና የአየር ወለድ ብቃት አሟልተው የመጀመሪያውን ዙር ለማስመረቅ በመቻላችን የተሰማኝን ልዩ ክብር ልገልጽላችሁ እወዳለሁ። ኢትዮጵያ ትልቅ ኢኮኖሚ እየገነባች ያለች ትልቅ ሀገር ናት፣ ጠላቶቻችን እየመረራቸው ሊውጡት የሚገባው ጉዳይ ኢትዮጵያ የአፍሪካ የኃይል ምንጭ ናት፤ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ውስጥ ስመ ገናና፣ ሃያል፣ ተጽእኖ ፈጣሪ ሃያል ሀገር ናት። የዚህች ታላቅ ሀገር ሠራዊት ሆኖ ማገልገል የዚህች ታላቅ ሀገር ቀይ መለዮ ለባሽ መሆን ታላቅ ክብር ስለሆነ እንኳን ደስ ያላችሁ ልላችሁ እወዳለሁ።

የዚህ ኤሊት ኃይል አላማው ሁለት ነገር ነው፤ አንደኛው ውጊያን ማስቀረት ነው። ውጊያ ሰው ይበላል፣ ሀብት ያወድማል፣ ከጉዞ ያደነቃቅፋል፣ ጥፋት እንጂ ልማት ስለሌለው ውጊያን ማስቀረት ዲተር የማድረግ ስራን ዋነኛ ተልዕኮው እንደሆነ እያሰበ የሚሰራ ነው። ኮማንዶ አይመረቅም ከማሰልጠኛ ይወጣል እንጂ። ከዛሬ ጀምሮ በቀንም በማታም በማዕከል ያገኛችኋቸውን አካላዊ ስልጠናዎች በየምድብ ቦታችሁ ይበልጥ እያጠናከራችሁ ይበልጥ እየጎበዛችሁ አስተማማኝ ኃይል ለመሆን የማያቋረጥ ስልጠና ማድረግ ስላለባችሁ አንደኛው ዓላማ የሚሳካው ቀጣይነት ባለው ስልጠና ነው። ያም ውጊያን ማስቀረት ነው። ሁለተኛው አላማችሁ ውጊያን መጨረስ ነው። ዛሬ እንደትናንቱ ውጊያ ሰው ጀምሮ ሰው አይጨርሰውም። ውጊያን በቅርብ ርቀት ብቻ ሳይሆን በከፍተኛ ርቀት መጀመር መዋጋት የሚያስችል አቅም ፈጥረናል። የምንዋጋው በቴክኖሎጂ ነው፣ የምንጨርሰው ግን በእናንተ በኤሊት ኃይል ነው። እናንተ ናችሁ ቴክኖሎጂ የጀመረውን ውጊያ ጨርሳችሁ የተከበረውን የክቡር ህዝቦች አደራ የሆነውን ባንዲራ የምትሰቅሉት፣ ውጊያ ጨርሳችሁ ድል የምታበስሩት፣ ባንዲራችንን ባሸነፍንበት ቦታ ሁሉ እንዲውለበለብ የምታደርጉ ውጊያ ጨራሽ ሃይሎች ናችሁ።

ውጊያን ለማስቀረት ከአቅም በላይ ሆኖ ከመጣም ለመጨረስ የተሰራው ኤሊት ኃይል በኢትዮጵያ ታሪክ ደረጃ በዚህ ቁጥር ኮማንዶና አየር ወለድ በአንድ ጊዜ አሰልጥነን

አናውቅም ። ይህን ያደረግንበት ዋነኛው ምክንያት ትልቅ ሀገርን የሚመጥን ተለቅ ያለ ኃይል በመገንባት ውጊያን ማስቀረትና ሰላምን ማጽናት ስለምንፈልግ ነው። ይህ ኤሊት ኃይል ከዘመናዊ አስተሳሰብ እውቀትና ቴክኖሎጂ ጋር የተዋሃደ መሆን አለበት። እውቀት ያለው፣ አስተሳሰቡ የጸዳ፣ የማድረግ አቅሙን በየጊዜው የፈተሸና በብቃት የሚያሳይ ሀይል መሆን ይጠበቅበታል። ከእናንተ እንደ አርበኛ፣ እንደ ጀግና፣ እንደ ተዋጊ ሦስት ነገሮችን እንፈልጋለን አእምሯችሁን፣ ልባችሁንና እጃችሁን እንድታሰሩ። በአእምሯችሁ እንድታስቡ፣ በእጃችሁ እንድትከውኑና በልባችሁ የሀገር ፍቅርን እንድትሸከሙ ይጠበቃል ። ነገር ግን በአእምሮና በእጅ እንዲሁም በልብ ትስስር የሚሰራው የኤሊት ኃይል ከሦስቱ የሚመራው ልቡ መሆን አለበት። ልቡ የሀገር ፍቅር፣ የጓድ ፍቅር፣ የአሃድ ፍቅር ፣ የዓላማ ፍቅር ፣ የባንዲራ ፍቅርና የመለዮ ፍቅር ያላው በልቡ ፍቅር አእምሮውንና እጁን የሚያዝ መሆን ይጠበቅበታል።

እኔ እና እናንተ የምንታገለው ስለምንወዳት ኢትዮጵያ ሀገራችን ስንል እንጂ ስለምንጠላቸው፣ ስለማንፈልጋቸው ግለሰቦችና ቡድኖች ስንል አይደለም። እኛን የሚነዳን፣ እኛን የሚያቆመን እኛን የሚያጸናን ለሀገራችን ያለን ፍቅርና ለእውነት ያለን ቅርበት ነው። እውነትን በልቡ የያዘ በፍቅር የተሞላ፣ አእምሮውን የሚያሰራ፣ በእየእለቱ በስልጠና ብቃቱን የሚያዳብር፣ ውጊያ የሚያስቀር፣ ሲገባ ግን የሚፈጽም ኃይል መሆን ይጠበቅባችኋል፣ ይጠበቅብናል። ኢትዮጵያ የጸናችው ጠላቶቿን በማሳፈር ብቻ አይደለም። ጀግኖች አርበኞች ልጆቿን በመሰዋት ጭምር ነው።

ሁሌም የምናሸንፈው ጀግኖችን ሰውተን ጠላትን እያሳፈርን ነው፤ ጠላት ካፈረ ጀግኖች ደማቸውንና ላባቸውን አፍስሰዋል ማለት ነው። የእናንተ ዋነኛው ተግባር የጸናች ኢትዮጵያን አጽንቶ ማሸጋገር ነው፤ ኢትዮጵያ ጸንታለች፤ ጸንታም ትኖራለች።

ኢትዮጵያ ትበለጽገለች፣ ለአፍሪካ ወንድሚቿ ሁሉ ኩራት ትሆናለች፣ ኢትዮጵያ ለሁሉም ጎረቤቶቿ ኩራትና መከታ ትሆናለች፣ ኢትዮጵያ ለሁሉም ጎረቤቶቿ የሰላም ምንጭ እንጂ የጦርነት ምንጭ አትሆንም። ኢትዮጵያ በሚያስፈልጓት ነገር ሁሉ በድርድር በምክክር በሰጥቶ መቀበል የምታምን እንጂ ጎረቤቶቿን የአፍሪካ ወንድሞቿን ባላት ጉልበት አምበርክካ መንጠቅ የምትፈልግ የሰፈር ጎረምሳ ባህሪ ያላት ሀገር አይደለችም። ክብር ያላት፣ ባህል ያላት፣ መውደድ የምታውቅ፣ ለሰላም መትረፍ የምታውቅ ሀገር ናት። ይህንን ኃይል የሚያዩ የአፍሪካ ወንድሞቻችን ሁሉ በሚገጥማቸው ችግር ውስጥ ድንበር

ተሻግሮ ሰላም ለማስከበር የሚያስችል ብቃትና ስልጠና የወሰደ አስተማማኝ አፍሪካዊ ኤሊት ፎርስ እንደገነባን እንዲያስቡ ከዚህ ባሻገር ለብልጽግናችንና ለእድገታችን ስንል ቀዳሚ ፍላጎታችን ሰላም መሆኑን ለወዳጅም ለጠላትም በዚሁ አጋጣሚ መግለጽ እወዳለሁ።

በመጨረሻም ትናንት ኢትዮጵያ አትፈርስም ብለን ነበር። ያንን ሃሳብ ስንሰነዝር አርበኞች እንዳሏት ስለምናውቅ ነበር። ዛሬ በተከበረው የኢትዮጵያ ኩራት በሆነው ኤሊት ኃይል ፊት ደግሜ ማረጋገጥ የምፈልገው ኢትዮጵያ ትጸናለች፣ ኢትዮጵያ ትሸጋገራለች፣ ኢትዮጵያ ትበለጽጋለች፣ ኢትዮጵያ እንደለመደችው ጠላቶቿን ደጋግማ እያሳፈረች ወደ ግቧ ትገሰግሳለች፤ ኢትዮጵያን ከብልጽግናና ከመጽናት ሊያቆማት የሚችል ምንም ኃይል እንደሌለ በዚሁ አጋጣሚ ማስገንዘብ እፈልጋለሁ።
ኢትዮጵያዊያን ለሰላምና ለልማት ለአብሮነት አብረን ልንሰራ ይገባል። ዛሬም እንደትናንቱ መልዕክቴ ሁሉም ኢትዮጵያዊያ ዜጋ ወንድማማች ሆኖ፣ ተከባብሮ፣ ተስማምቶ፣ ተደምሮ ይችን ታላቅ ሀገር መጽናትና ማሸጋገር ብቻ ሳይሆን ለልጁ የላቀች፣ የበለጸገች፣ ሰላም የሰፈነባት ኢትዮጵያን ማሸጋገር የሚችል ሐላፊነት የሚሰማው፣ ምንጩን ከማያውቀው ጎርፍ ጋር ሁሉ የማይጓዝ፣ ቆሞ ማሰብ የሚችል ዜጋና ትውልድ እንድንሆን አደራ እያልኩ በነገር ሁሉ የረዳን፣ በነገር ሁሉ አሸናፊ እንድንሆን ያደረገን፣ የበለጸገች ኢትዮጵያን ለልጆቻችን እንድናሸጋግር የሚረዳን ፈጣሪ የተመሰገነ ይሁን።

ታላቁን ህዝባችንን የሰነቅነውን የፍቅር፣ የአንድነት፣ የመደመር ዓላማችንን ቀን ከሌት የመስራት ልምምዳችንን ከሁሉ በላይ ፈጣሪያችንን ይዘን የለመለመች፣ ያደገች፣ የተሻገረች አንድ የሆነች ኢትዮጵያን እናሻግራለን፣ ጠላቶቿን እናሳፍራለን፣ ለአፍሪካ ለዓለም ምሳሌ የሆነች ኢትዮጵያን ለልጆቻችን እናሸጋግራለን።
አመሰግናለሁ።

**ነሐሴ 6 ቀን 2015 ዓ.ም**

**ብላቴ የኮማንዶና አየር ወልድ ማሰልጠኛ ማዕከል**


BRICS
XV BRI
SUMM

# ኢትዮጵያ የብሪክስ አባል ሆነች

ነሐሴ 18 ቀን 2015 ዓ.ም

ብሪክስ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዓላም ካሉ ስብስቦች መካከል በህዝብ ብዛት፣ በኢኮኖሚ አቅሙ፣ በመደመጥ አቅሙ እያደገ የመጣ ቡድን ነው። ይህ ቡድን እያደገ ከመጣ በኋላ ከአርባ የማያንሱ ሀገራት ብሪክስን ለመቀላቀል ፍላጎት አሳይተዋል። ከነዚህ ውስጥ ስድስት ሃገራት በአሁኑ መመዘኛውን አሟልተው የብሪክስ አባል መሆን ችለዋል ። ይህ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ህዝብ ብሎም ለአፍሪካ ትልቅ ኩራትና የዲፕሎማሲ ድል ነው። አንደኛ ኢትዮጵያ ስትመረጥ ታሪኳ፣ የህዝብ ብዛቷ፣ በተለይ አሁን በዓለም ላይ ከፍተኛ እድገት እያመጡ ካሉ ጥቂት ሀገራት መካከል አንዷ መሆኗ በነዚህ ሀገራት ስለታመነበት ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የአረንጓዴ አሻራ፣ የአረንጓዴ ታዳሽ ኃይልና በግብርናው ራስን ለመቻል እየተደረገ ያለው ጥረት እንዲሁም አጠቃላይ የሀገራዊ ምርት (GDP) እድገት፣ በዓለም ላይ በቁጥር ከሚጠቀሱ ከፍተኛ እድገት ካመጡ ሀገራት አንዷ በመሆናችን፣ የኢትዮጵያ የመደመጥ አቅም እያደገ በመምጣቱ፣ ኢትዮጵያን ማስገባት የደቡብ ደቡብ ትስስሩን እውን ያደርገዋል። የደቡብ ደቡብ ትብብሩ ኢትዮጵያ በሌለችበት ሙሉ አይሆንም በሚል አብዛኛው ባላቸው የጂ.ዲ.ፒ አቅም ከፍ በሚል ሀገራት የተወሰዱ ቢሆንም ኢትዮጵያ ባላት ተስፋና አጠቃላይ የእድገት ሂደት ለመመረጥ በቅታለች።

ብዙዎች ለመካተት የሚፈልጉበት መድረክ ነው። በብዙ ትግል በብዙ ንግግር የተገኘ ድል ነው ለዚህም ቻይናን በእጅጉ እናመሰግናለን፤ ከፍተኛ እርዳታ አድርገውልናል፣ ህንድን በብዙ እናመሰግናለን፣ ሩሲያን በብዙ እናመሰግናለን፣ ብራዚል እንዲሁም ደቡብ አፍሪካን አብዝተን እናመሰግናለን ። ከሁሉም ጋር በነበረን ውይይት የኢትዮጵያ የብሪክስ ቤተሰብ አባል መሆን ለአፍሪካም፣ ለደቡብ ደቡብ ትብብርም፣ በዓለም ላይ ባላት የዲፕሎማሲ መደመጥ አቅምም ወሳኝ መሆኑን አምነዋል። ከዚህም ባሻገር ከፕሬዘዳንት ሺ ጋር በነበረን ውይይት የሚቀጥለው ዓመት የእዳ ክፍያ አጠቃላይ የእዳ ማሸጋሸግ እስኪከናወን ድረስ ለአንድ ዓመት እፎይታ ሰጥተውናል፣ በብዙ መስኮች የትብብር ስምምነት አድረገናል፤ ያም በጣም በጣም ትልቅ ውጤት ነው።
ዛሬም እንደሰማችሁት ከህንድ ጠቅላይ ሚንስትር ሙዲ ጋር በነበረን ስብሰባ በሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ በወታደራዊ፣ በንግድና በኢንቨስትመንት አብረን ለመስራት ተስማምተናል።

አጠቃላይ የሚታየው ድባብ ኢትዮጵያ ትልቅ ሀገር ናት፣ ታሪክ ጠገብ ሀገር ናት፣ ተስፋ ያላት ወጣት ሀገር ናት፤ አሁን እየተመዘገባ ያለውን ድል፣ እየተመዘገበ ያለውን ኢንቨስትመንት፣ እየተመዘገበ ያለውን ለውጥ ኢትዮጵያዊያን በውል ባይረዱትም ዓለም በደንብ ተገንዝቦት በዚያ ደረጃ እውቅና እየሰጠ ይገኛል። እንደሰማችሁት ዓለም በሙሉ በከፍተኛ አድናቆትና ምስጋና ነው እየተቀበለ ያለው። ለእኛም ትልቅ ድል ነው። ኢትዮጵያ ባለፉት ጥቂት አስርት ዓመታት ከተመዘገቡ ትላልቅ ዲፕሎማሲያዊ ድሎች አንደኛውና ዋነኛው ሊባል ይችላል። ዝም ብሎ መግባት ሳይሆን በኢኮኖሚ እድገት፣ በህዝብ ብዛት፣ በዓለም በመደመጥ አቅማችን፣ ወደፊት ባለን ተስፋ፣ በአፍሪካ ውስጥ ትልቅ ተደማጭነት ያላት ሀገር ናት እሷን ጥለን አፍሪካን አካተትን ማለት አንችልም የሚል ድምዳሜ ተደርሶ ጭምር ስለሆነ የገባነው፤ ቡድኑ ውስጥ መቀላቀላችን ብቻ ሳይሆን በቡድኑ ውስጥ ባሉ አባላት ያለን ተደማጭነትና ያለን ግንኙነት ጠንካራ እንዲሆን አድርጓል ። ይህ በጣም ትልቅ ድል ነው፤ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ እንኳን ደስ ያላችሁ፤ እንኳን ደስ ያለን ማለት እፈልጋለሁ።

በተደጋጋሚ እንዳልኩት ወደፊትም ይቀጥላል። ኢትዮጵያ ትበለጽጋለች፣ የአፍሪካ የኃይል ምንጭ ትሆናለች፣ በአፍሪካ ውስጥ ትልቅ ተደማጭነት ካላቸው ሀገራት ትሆናለች፣ ባልገባንባቸውና መግባት በሚገባን መድረኮች ሁሉ እየተሳተፈች ድምጿ በአህጉር ደረጃና ለዓለም ደረጃ የምታስደምጥ ሀገር ትሆናለች። በውስጣችን ጥቃቅን ችግሮች አሉ፣ ያልገቡን ነገሮች አሉ፣ እነሱ እየገቡን እየተፈቱ አንድ እየሆንን እየተደመርን ታላቋን ለልጆቻችን የኩራት ምንጭ የሆነች ኢትዮጵያን መፍጠር ይኖርብናል። ጉዟችን ይህንን ነው የሚያመላክተው። በስንዴ ያገኘነውን ድል፣ በአረንጓዴ አሻራ ያገኘነውን ድል፣ በከተሜነት እየፈጠርን ያለውን ድልና አጠቃላይ በጂ.ዲ.ፒ ያመጣነውን እድገት አሁን በዲፕሎማሲ እየደገምን ነው። ይህን አጠናክረን እንቀጥላለን። እንኳን ደስ ያላችሁ እንኳን ደስ ያለን ማለት እፈልጋለሁ ፤
አመሰግናለሁ።

**ነሐሴ 18 ቀን 2015 ዓ.ም**
**ደቡብ አፍሪካ**

# ሀገር ከማገልገል በላይ ጀግንነት የለም

ነሐሴ 18 ቀን 2015 ዓ.ም

**እንዴት አረፈዳችሁ፤**
**መልካም አዲስ ዓመት ይሁንላችሁ ይሁንልን፤**

በመጀመሪያ እንደዚህ ያለመለማችሁ በእድሜ በጤና ያቆያችሁ ፈጣሪ የተመሰገነ ይሁን። በመጀመሪያ ማገልገል በቤት እናትን አባትን፣ በሰፈር ጎረቤትን ከዚያም እልፍ ሲል ሀገርን ማገልገል መታደል ነው። ሁሉ አይታደለውም እናንተ እድለኞች ስለሆናችሁ እንኳን ደስ ያላችሁ ልላችሁ እፈልጋለሁ ።

ከሰላሳ ስምንት ዓመታት በላይ ማገልገል ቀላል ነገር አይደለም። ከሰላሳ ስምንት ዓመታት በላይ ብዙ መንግስታት፣ ብዙ እሳቤዎች፣ ብዙ አሰራሮችና ብዙ ሹመኞች ተቀያይረዋል። እናንተ ግን በታማኝነት ኢትዮጵያን አገልግላችኋል ። ይህ እድል ከእናንተ አልፎ ለብዙዎች እንዲደርስ የምንመኘው ቢሆንም እናንተ ዛሬ በኢትዮጵያ የሲቪል ሰርቪስ ታሪክ ውስጥ ረዘም ላለ ጊዜ ያገለገላችሁና በህይወት ያላችሁ ሰዎችን ኢትዮጵያ አመስግና አዲሱን ዓመት እንኳንም ዘራሁ፣ እንኳንም ሠራሁ ለሀገሬ ብላችሁ እንድታስቡ ነው ይህ ፕሮግራም የተዘጋጀው። ማገልገል መታደል ማገልገል ልዩ ስጦታ ያንን ስጦታ ደግሞ በወጉ በታማኝነት መልሶ መስጠት የሚያስችል ብቃት ስላሳያችሁ በተግባር ስላስተማራችሁ ብዙዎች የእናንተን ፈለግ ስለሚከተሉ በድጋሚ እንኳን ደስ ያላችሁ ማለት እፈልጋለሁ።

ማገልገል የህይወት ዘመን ኢንቨስትመንት ነው። እናንተ ሰላሳ ስምንት፣ ሰላሳ ዘጠኝ ፣ አርባና አርባ አንድ ዓመት ኢንቨስት አድርጋችኋል ኢትዮጵያ ላይ። ብዙዎች ምን ዋጋ አለው ቤት እኮ የላችሁም፣ መኪና እኮ የላችሁም፣ የበቃ ገቢ እኮ የላችሁም ይሉ ይሆናል። እውነት ነው እንደዛ የተንደላቀቀ ሀብት አይኖራችሁ ይሆናል። ግን ታላቋን ኢትዮጵያ ለሚቀጥለው ትውልድ አሸጋግራችሁ አደራ የማትበሉ ታማኞች መሆናችሁን አሳይታችኋል ። ኢትዮጵያ ኖራ በእሷ ላይ ብር ቢጨመር፣ መኪና ቤት ቢጨመር ጥሩ ነው፤ ግን እናንተ ባለመኪና ሆናችሁ ለትውልድ ሀገር ባታሸጋግሩ እሱ ባዶ ነው፤ ትልቁን አሳክታችኋል ። የቀረ የቁስ ጉዳይ ሊኖር ይችላል፣ ትልቁን ስላሳካችሁ ኢትዮጵያም ዛሬ ያንን ተገንዝባ ቢያንስ በየቤታችሁ ከልጆች ከጎረቤት ጋር ‘ ’ኢትዮጵያን

አገልግዬ ኢትዮጵያም አስታውሳ አመሰግናለሁ አለችኝ’ ’ በሚል አንድ የደስታ ቀን በህይወታችሁ ላይ መጨመር ቢቻል ለእኛ ትልቅ ክብር ስለሆነ ስለሰጣችሁን እድል እኛ አብዝተን እናመሰግናችኋለን።

የእናንተን ፈለግ ተከትለው ዛሬ በአዲስ አበባ የሚገኙ የታክሲ ማህበራትና ሾፌሮች ለተወሰነ ሰዓት በነጻ አገልግሎት እንሰጣለን ብለው ትናንትና አውጀው ዛሬ በነጻ ሲያገለግሉ እንደነበር ሰማሁ፤ በጣም አስደነቀኝ። የታክሲ ሾፌሮች የተረፋቸው አይደሉም፣ የበቃቸውም አይደሉም፣ ስለተረፋቸው አይደለም እየሰጡ ያሉት በመስጠት ውስጥ ያለን መባረክ፣ በመስጠት ውስጥ ያለን ደስታ ተገንዝበው ምናልባትም ከእናንተ በተግባር ተምረው ስለሚሆን እናንተ በቁጥር ብታንሱም ብዙዎች የእናንተን ፈለግ እንዲከተሉ፣ ከእናንተ እንዲማሩ እናንተን እንዲመስሉና ሀገር እንዲያሸጋግሩ በተግባር ማስተማር ስለቻላችሁ በድጋሚ እንኳን ደስ ያላችሁ ማለት እፈልጋለሁ ።

በእኛ መስሪያ ቤት ቅድም ሲሸለሙ እንዳያችሁት ሰላሳ ስምንት፣ አርባ፣ አርባ ሁለት ዓመት ያገለገሉ ታላላቅ ወንድሞች አሉን። የሚገርመው ነገር ዛሬ በጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ቢሮ ከሚገቡ ብዙ ኀረምሶች መካከል ሶስቱ ቅድም የሸለምኳቸው ኀረምሶች ናቸው። ዛሬም በታማኝነት አንድ ሰዓት ገብተው ሀገራቸውንና ህዝባቸውን በታማኝነት ያገለግላሉ። እነዚህን ሰዎች እንድታመሰግኑልኝ እጠይቃለሁ። ዛሬ ብዙ ሰዎች ስጋት አላቸው፣ ስለ ኢትዮጵያ ሲያስቡ። ልነግራችሁ የምፈልገው ነገር አትስጉ ኢትዮጵያ በሚያሰጋ ሁኔታ ላይ አይደለችም።

በእርግጥ አንድ እናት ስትጸንስ በመጀመሪያው ሳምንታት በሽታ የለም ደስታ ብቻ ነው ያለው፣ ለባል፣ ለእናት፤ ለአባት የሚነገረው ጸንሻለሁ፤ ከሦስት ወር ጀምሮ እስከሚወለድበት ጊዜ ድረስ ድካም እየጨመረ፣ ማቅለሽለሽ እየጨመረ፣ በግራ ወጋኝ በቀኝ ወጋኝ እየጨመረ እንጅ እየቀነሰ አይሄድም። በዚህ ሁሉ ጊዜ ውስጥ የእናትን ስቃይና ህመም መካፈል የሚችል ማንም የለም። ባልን ጨምሮ ማንም የእሷን ስቃይና ህመም አይገነዘበውም። በመጨረሻው እጅግ የሚያስመርር፣ የሚያንገፈግፍ፣ ስቃይ የሞላበት ምጥ ይመጣል፤ ያችን የምጥ ጊዜም እናትም ባልም አይካፈሉም ብቻዋን ያንን መከራ ታልፈውና ልክ ስትወልድ እናት፣ ታላቅ እህት፣ ጥሩ ጎረቤት ያላት እንደሆነ የመጀመሪያ ሥራቸው በአናቷ ላይ ቅቤ ያስቀምጣሉ፣ ሁለት ወር ሦስት ወር ትታረሳለች። ያንን መከራ ያንን ችግር ያንን አድካሚ ጊዜ አልፋ አንድ መልካም ነገር ሰጥታለች ተብሎ ባልም ቤተሰብም ይንከባከባል።

ኢትዮጵያ በዚህ ጉዞ ላይ ነው ያለችው አልተወለደም ግን ይወለዳል፤ አልተወለደም ሰላም ይወለዳል፣ ብልጽግና ይወለዳል፣ ልማት ይወለዳል። ከሁሉ በላይ ኢትዮጵያ ትቀጥላለች ለልጆቻችን የተሻለች ሀገር እናስረክባለን ።

**አመሰግናለሁ።**

**ጳጉሜ 1 ቀን 2015 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

# በጎነት መስፈርት የለውም፤ ከማይነጥፍ የመልካምነት እሴት የሚቀዳ እንዲሁ በነጻ የሚሰጥም ነው

ጳጉሜ 3 ቀን 2015 ዓ.ም

**እንዴት አደራችሁ፤**

በመጀመሪያ በዚህ ዓመት የነበሩብንን ዘርፈ ብዙ ችግሮች፣ ፈተናዎች እና ተግዳሮቶች አልፋችሁ ብሩህ ተስፋ፣ ብሩህ እድል፣ የሚጨበጥ እድል ወደምናገኝበት አዲሱ ዓመት በሰላም እንኳን አደረሳችሁ ልላችሁ እወዳለሁ። 2016 ዓ.ም የጀመርናቸውን በርካታ ፕሮጀክቶች የምናስመርቅበት፣ በኢኮኖሚ ረገድ የገጠሙንን ፈተናዎች የምናቃልልበት ኢትዮጵያ ጸንታ የቆመች ለአፍሪካ መከታ የሆነች ሀገር መሆኗን ለብዙ ዜጎች የምናሳይበት ፣ እጅግ ትላልቅ ድል የምናስመዘግብበት፣ ዛሬም ጸንተን የምንሻገርበት ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ የአፍሪካ የኃይል ምንጭ መሆኗን የምናረጋግጥበት ዘመን ነገ ሊመጣ ነውና እንኳን ደስ ያላችሁ።

በጎነት መስፈርት አልባ ነው ፣ በጎነትን በመስፈርት መለካት አይቻልም፣ በጎነት እንዲሁ ከማይነጥፍ ምንጭ እየቀዱ መስጠት ነው ። ምንጩ ከማይነጥፍ በጎ አምላክ ዝናብ በነጻ እንደሚሰጠን ሁሉ እኛ በነጻ ጤንነትና አፍላ ጉልበት የተሰጠንን ያህል በመጀመሪያ ለእናት አባቶቻችን ፣ ለእህት ወንድሞቻችን ፣ ለጎረቤቶቻችን ለሰፈራችን ፣ ከዚያም አለፍ ሲል ለሀገራችን ለአፍሪካ አህጉራችን ጭምር ሳይከፈለን በነጻ የምናገለግልበት የምንሰጥበት እሳቤና የተግባር መነሾ ስለሆነ በጎነት ለዚህ ታላቅ ዓላማ ተሰልፋችሁ፣ ተሰማርታችሁ ትላልቅ ድል ለሠራችሁ ወጣቶች በድጋሚ እንኳን ደስ ያላችሁ ልላችሁ እፈልጋለሁ። በጎነት ቀብድ አይጠየቅበትም፣ በጎነት ወለድ አይሰላበትም፣ በጎነት ቀስቃሽ የሚያበረታታ ኃይልም አያስፈልገውም። በጎነት ግን ነጻ አይደለም ዘር ነው። ዛሬ የዘራችሁ ወጣቶች ካለምንም ጥርጥር በማምሻ እድሜያችሁ ታጭዱታላችሁ። ክፉ የዘራም የዘራውን እንደሚያጭደው ሁሉ በመልካምነትና በበጎነት የምትሰሩ ወጣቶች እንዲሁ ከመልካም ሥራችሁ ታጭዳላችሁ።

ድሮ በሀገራችን አንድ እንግዳ ራቅ ካለ ስፍራ ሲመጣ የእግዜር እንግዳ ነው <<ኬሱማ ረቢ.ቲ>> ይባላል ። የእግዜር እንግዳ ወይም ኬሱማ ረቢ የሚባለው ግለሰብ ቤት ሲመጣ እንደዋዛ አይቀበልም። ተቀባዩ ከሌለው ቆርሶ ከፍሎ አጥቦ፣ አብልቶ፣ አስተኝቶ፣ ሸኝቶ መልሶም ስለመጣና ስለመረጠው አመስግኖ ነው የሚለያዩት ያ ባህል ይጠቅመናል ።

አሁንም የምንቀበል የምንካፈል ፣ የምንሰጥ ቸር የሆንን ብንሆን የላቀ ነገር እንቀበል ይሆናል እንጂ አናጣምና ወጣቶች አልከሰራችሁም መልካም ዘር ዘርታችኋል። በጎ ሥራ የምትሰሩ ወጣቶች በጎ ከማይሰሩ ሰዎች ለመማር አታስቡ። ፍሬ ሊያፈራ ያልተፈቀደለት፣ ያልተፈጠረ ዛፍ ምንም ግንዱ ቢረዝም፣ ምንም ቅጠሉ ቢሰፋ፣ ምንም ስሩ የሰደደ ቢሆንም እንዲሁ ረዥም ዛፍ እናያለን እንጂ ፍሬ አናይም። እናንተ ግን መልካም ፍሬን የምትዘሩ ወዳችሁና ፈቅዳችሁ ለኢትዮጵያ በነጻ የሰጣችሁ ወጣቶች አንድ ነገር ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ። አንደኛ አንሸነፍም፣ ሁለተኛ የጸናች፣ የቆመች፣ የበለጸገች ኢትዮጵያን እናስረክባችኋለን። ሶስተኛ መልካምነት፣ በጎነት፣ መስጠት፣ መትጋት ፈቅደን ወደን የተቀበልነው ስለሆነ ሰዎች ሲነካኩን አንቀይረውም። ዛሬም ለሚጠሉን ፍቅር፣ ለማይሰሩ ሞራልና ብርታት፣ ለታመሙ ደግሞ እረፍትና ፈውስ ፣ ለኢትዮጵያ ብልጽግና፣ ለኢትዮጵያ ሰላምና ለኢትዮጵያ አንድነት እንመኛለን።

ኢትዮጵያን ከማበልጸግ፣ የጀመርነውን ከመጨረስ፣ በድል ለልጆቻችን ከማሸጋገር ሊያቆመን የሚችል ምድራዊ ኃይል የለም። ወጣቶች ህልመኞች እንድትሆኑ እመክራችኋለሁ፤ ህልመኞች ሁኑ፣ ለህልማችሁ ትጉ ህልማችሁን ለመጨበጥ፣ ህልማችሁን ፈታችሁ ለማየት የምትተጉ ሁኑ። ነገር ግን ከኢትዮጵያ በመስረቅ፣ ከኢትዮጵያ በማጉደል፣ ኢትዮጵያን በማጉደል ማንም ተጠቃሚ መሆን ስለማይችል፤ ልባችን የሰፋ፣ አእምሯችን የሰከነ የሚያስተውል በአሉባልታና በወሬ ሳይሆን በሚታይ ነገር በሚጨበጥ ነገር የሚመራ ይሁን። የሚያወሩ ያውሩ፣ የሚሳደቡ ይሳደቡ ነገር ግን እኛ ለኢትዮጵያ በጋራ እንትጋ።

**አመሰግናለሁ ።**
**ጳጉሜ 3 ቀን 2015 ዓ.ም**
**አዲስ አበባ**

# የኢትዮጵያዊያን ብርቱ እጆች በጽናት ታሪክ መስራት ቀጥለዋል

መስከረም 7 ቀን 2016 ዓ.ም

የአረንጓዴ አሻራ በአፋር ክልል ማስጀመራችን ይታወሳል። በዚያ ስንጀምር የነበረን ህልም ከሰባት ቢሊየን ያላነሰ ለመትከልና ዘንድሮ 32 ቢሊየን ለመድረስ አቅደን በክረምቱ ሰባት ነጥብ አምስት ቢሊየን ችግኝ አሁን በድምሩ 32.5 ቢሊየን ችግኝ መድረስ ችለናል። ይህም በዓለም እጅግ ትልቁ ከተረት ተረት፣ ከኮንፈረንስ፣ ከስብሰባና ከአበል መሰብሰብ ያለፈ የተግባር (Aforestetion) ደን የመትከል ሥራ ነው ። እስካሁን በዓለም ላይ ሥነምህዳርን በሚመለከት በጣም ብዙ ኮንፈረንሶች ተካሂደዋል፣ ብዙ ውይይቶች ተካሂደዋል። በዚህ ደረጃ ተግባራዊ ሥራ የሠራ ኢንሸስት ያደረገ ሀገር ግን የለም። ኢትዮጵያ ከዚህ አንጻር ቀዳሚና አርአያ የሆነ እጅግ የሚያኮራ ተግባር ፈጽማለች። ነገር ግን ያቀድነው ሃምሳ ቢሊየን ችግኝ መትከል ነው ቀሪ ሶስት ዓመት አለን። በየዓመቱ ስድስት ስድስት እንኳን ብንተክል 18 ቢሊየን መትከል እንችላለን፣ ሰባት ሰባት መትከል ብንችል 21 ቢሊየን መትከል እንችላለን። እንደልማዳችን ካቀድነው በላይ ለመትከል የሚያስችል አቅም እንዳለን አፈጻጸማችን ያመላክታል።

መላው የኢትዮጵያ ህዝብ አሁን አካባቢውን በአረንጓዴ የማልበሱን ተግባር ዛፍ በመትከል ብቻ ሳይሆን ምግብ መትከል ፣ መድሃኒት መትከል ፣ ዝናብ መጥራት፣ ማር ማብዛት፣ ለከብቶች በቂ የሆነ መኖ ማሰናዳት፣ የአፈር መሸርሸርን መከላከል ለልጆቻችን ካሉን ሀብቶች መካከል እጅግ ዋነኛው የሆነውን መሬታችንን፣ የተፈጥሮ ሀብታችንን፣ ንጹህ ውሃችንን ማሸጋገር ስለሆነ ይህን ትልቅ ትልም፣ ትልቅ ሃሳብ በኢትዮጵያዊያን የተባበረ ክንድ እየተሰራ ያለ ታሪክ ስለሆነ ባቀድነው ባሰብነው ልክ እስክንፈጽም እንደከዚህ ቀደሙ የጸና አቋምና ትጋት ከሁላችን ይጠበቃል ።

አሁን ያለንበት ስፍራ የዛሬ ሦስትና አራት ዓመት ገላጣ ቦታ ነው። የዚህ አካባቢ ወረዳ ህዝብ በትብብር ከባቢውን በጥቂት ዓመታት ውስጥ አረንጓዴ ማድረግ ችሏል። አሁን ደግሞ የማር ቀፎ እያስፋፋ ይገኛል። አረንጓዴ ማድረጋችን፣ አፈር መጠበቃችን ዝናብ ማከላችን፣ ሥነ ምህዳሩን ሰላማዊ ማድረጋችን ብቻ ሳይሆን ገንዘብ የምናገኝበት ሆኗል።

ይህ ሥራ በፍራፍሬ፣ በቡና፣ በሻይ በተለያዩ እጽዋት መጠናከር አለበት። የኢትዮጵያን ብልጽግና የምናረጋግጠው አፈር፣ ምድራችንንና ውሃችንን በመጠበቅ ጭምር ስለሆነ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ባለፋት ጥቂት ዓመታት ያሳየውን ትጋት፣ ብርታት፣ የሥራ ተነሳሽነትና ውጤት መንግሥት በእጅጉ ያከብራል። ሁሌም እንደምንናገረው አረንጓዴ አሻራን ባቀድነው፣ ካቀድነው በላይ እናሳካለን፣ ህዳሴን እናሳካለን፣ በስንዴ የጀመርነውን ልማት እናሳካለን፣ አሁን በሌማት ትሩፋት ዶሮ ላይ፣ ማር ላይ፣ ስጋ ላይ፣ ወተት ላይ፣ እንቁላል ላይ እጅግ ተስፋ ሰጪ ጅማሮ ጀምረናል። የሌማት ትሩፋት በቅርቡ ድጋሚ ገምግመን የምናጠናክረውና ከፍተኛ ውጤት የምናመጣበት ይሆናል።

በሚቀጥሉት ዓመታት ኢትዮጵያ ውስጥ ከስንዴ ብዛት የተነሳ ዳቦ፣ ከዶሮ ብዛት የተነሳ ደግሞ ስጋ የማይወደድበት ሀገር ለመፍጠር ያለን ትልም ይሳካል። ውድ ኢትዮጵያዊያን ከቅዠት የወጣ ህልመኛ የሆነ፣ የሚተገበር፣ በእቅድ በዝግጅት ላይ የተመሰረተ እንደዚህ አይነት አስደሳች ሥራ እንድንሰራና የኢትዮጵያን የድህነት ታሪክ፣ የልመና ታሪክ በሚጨበጥ የታሪክ እጥፋት ወደ ብልጽግና ጎዳና እንድንወስዳት አደራ እላለሁ። ኢትዮጵያ የጀመረችውን የብልጽግና ጉዞ፣ ኢትዮጵያ የጀመረችውን ሁለንተናዊ ለውጥ የማጽናት ጉዞ ሊያቆመው የሚችል ምድራዊ ኃይል የለም። እንበለጽጋለን ፣ እንጸናለን ፣ እንቀጥላለን ለልጆቻችን ውብ ሀገር እንስረክባለን።
አመሰግናለሁ።

**መስከረም 7 ቀን 2016 ዓ.ም**
**ኦሮሚያ ክልል፤ ምስራቅ ሸዋ ዞን**

# የመስቀል እና የመውሊድ በዓላትን ምክንያት በማድረግ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በሚያሠራቸው ፕሮጀክቶች ላይ ለሚሠሩ ሠራተኞች የእንኳን አደረሳችሁ ዝግጅት

መስከረም 17 ቀን 2016 ዓ.ም

ሰሞኑን መውሊድ እና መስቀል ተመካክረው እኛን በጋራ ለማዋል ስለመጡ ከእኛ ጋር የሚሰሩ ሙስሊሞች እና ክርስትያኖች በዓላቸውን ከእኛ ጋር ቢያከብሩ ብለን ነው ዛሬ የጠራናችሁ። ስለመጣችሁ እጅግ አድርገን እናመሰግናለን። አብዛኛው የተጋበዘው ሰው በተለያዩ ፕሮጀክቶች የሚሳተፍ የቀን ሠራተኞች፣ ከእኛ ጋር የሚሰሩ የፕሮጀክት ሃላፊዎች እንዲሁም ኮንትራክተሮች ይገኙበታል። ዋናው መልእክቴ ሥራ ሲጀመርና ሥራ መሃል ላይ እያለ ሳቢ ነገር አይደለም፣ የሚመች ነገር አይደለም፣ አድካሚ ነው፣ አታካች ነው፣ ጭቃ ማቡካት ነው። ሥራ የሚያምረው ሲያልቅ ነው። እናንተ ውስጥ የመጨረስ እልህና የመጨረስ ጉልበት እንዲፈጠር እስካሁን ለነበረው ትጋት በተለይም ቅዳሜና እሁድ ማታ ለምትሰሩ ሠራተኞች ሴቶች እጅግ ከፍ ያለ ምስጋናና ክብር ያለኝ መሆኑንን እየገለጽሁ፤ ግን አሁንም መትጋት፥ ብዙ መትጋት መስራትና መጨረስ ይኖርብናል ።

ጭካ ላይ የምትሳተፉ ሠራተኞች ከዚህ ቀደም እንዳነሳሁላችሁ ጭካ ለእኔና ለእናንተ የሚገባ ሥራ አይደለም ልጆቻችን ግን ይገባቸዋል። ይህች ሀገር ትበለጽጋለች ፣ ትለወጣለች ያኔ አባቶች ምን አሻራ ጥለው አለፉ የሚል ጥያቄ ሲነሳ ልክ ከዚህ ቀደም ትላልቅ አባቶች ቁምነገር ሠርተው እንዳለፉት የእኛም ሥራ ያኔ የሚታወስ ይሆናል ። ከዚህ ቀደም ነግሬያችሁ ሊሆን ይችላል፣ በኢትዮጵያ የነበሩ ነገሥታት የሚታወቁት በውጊያ ነው፣ ጦር በማዝመት ነው ። እናም ላሊበላ ከነገሱ በኋላ ውቅር አብያተክርስቲያናት በተለየ መንገድ ለመስራት አቅደው ሥራ ሲጀምሩ ብዙዎች ያንጓጥጡ ያሾፉባቸው ነበር። ድንጋይ መቆርቆርና መስራት የስንፍና ምልክት፣ ሄዶ መዋጋትና የጠላትን አንገት ቆርጦ መምጣት ደግሞ የጀግንነት ምልክት ተደርጎ ይታሰብ ነበር። ግን ክፋቱ ያኔ የተቹትም፣ ያኔ የተዋጉትም ተረስተዋል። ያልተረሱት እሳቸው ቁምነገር ሠርተው ያለፉት ብቻ ናቸው።

እናንተም እንደዚሁ አሁን ያለውን አየር፣ አሁን ያለውን ሙዚቃ ሳይሆን አሻራ ጥላችሁ የምታልፉ መሆናችሁን ማሰብ ይኖርባችኋል። ጫካ ለሙስሊምም፣ ለክርስቲያንም፣ ለአማራውም፣ ለኦሮሞውም፣ ለትግሬውም፣ ለወላይታውም፣ ለሲዳማውም ለሁላችንም የሚሆን ነገር ነው። በዘርና በእምነት መነጽር መታየት የለበትም። ማሰብ ያለባችሁ ጉዳይ በተለይም እዛ ስፍራ የምትሰሩ ሰዎች ባለፉት ሃያ፣ ሰላሳ፣ አርባ ዓመታት አዲስ አበባ ውስጥ መሬት ችግር ሆኖ ሰው ጉድጓድ ውስጥ፣ የውሃ ሸለቆ ውስጥ ሳይቀር በላስቲክ በቆርቆሮ ቤት እየሰራ ከተማውን ቤት በቤት ባደረገበት ሀገር ውስጥና ከተማ ውስጥ ጫካን የሚያክል ቦታ እንዴት ተደብቆ ቆየ? ቅርብ ነው እንደምታውቁት። ያን የሚያክል ስፍራ እንዴት ተደብቆ ቆየ ሲባል የእናንተን እጅ እየጠበቀ ነበር። የእናንተን መልካም ሥራ እየጠበቀ ነበር። መልካም ሥራ ሰርተን ኢትዮጵያን እንድናኮራ፣ መልካም ሥራ ሠርተን ልጆቻችን ከእኛ የተሻለ ሀገር እንዲረከቡ ለማድረግ የሁላችንም ርብርብ ይጠይቃል።

ሀገራዊ ስሜታችን የዳበረ ስለኢትዮጵያ የሚገደን የምንሰራውም በዚያ መነጽር እንዲሆን፣ በታሪክ እይታ ውስጥ ሥራችን ሲመዘን የማያሳፍር እንዲሆን ህብረትና ጠንካራ የቡድን ሥራ ይጠበቅባችኋል። ይህ ዓመት በጣም በርካታ ድሎች ይመዘገቡበታል። አብዛኛው ፕሮጀክቶቻችን ያልቃሉ፣ ያለውም አቧራ ቀስ ቀስ እያለ ይሰክናል። ኢትዮጵያዊያን ወንድማማቾች ልብ ይገዙና ሰክነው በምክክር፣ በውይይት፣ በስክነት ሀገራቸውን መገንባት ይጀምራሉ። እንደ ሁልጊዜውም የማረጋግጥላችሁ ከተረከብናት በእጅጉ የተሻለች፣ የበለጸገች፣ የጸናች ያማረች ብዙዎችን የምታኳኳ ኢትዮጵያ እናስረክባለን። በዚህ የቀና ዓላማ ውስጥ ተሳታፊ ለመሆን እድል ያገኛችሁ ሰዎች በሙሉ ልብ ልትሰሩ ይገባል ። ሰዎች ችግኝ እንትከል ሲባል ጉልበት የላቸውም፣ ከተማ እናጽዳ ሲባል ጉልበት የላቸውም፣ የድሃ ቤት እንሥራ ሲባል ጉልበት የላቸውም። ወንድማቸውን ለመግደል፣ ወንድማቸውን ለመስደብ፣ ከተማ ለማጥፋት ጉልበት አላቸው። በጥፋት ላይ በሰለጠነው ልክ በመልካም ነገር ላይ ብንተባበር ምን ልናደርግ እንደምንችል አስቡት። መልካም ነገር ነው የሚያዋጣው፣ እዚህም ስንሄድም ለውስጥ እርካታችንም መልካምነት ጥሩ ነው። ስንሄድም ቢያንስ በፍርድ ፊት የማናፍር ስለምንሆን በንጹህ ልብ በትብብር የጀምርናቸውን ሥራዎች በውጤት ጽድት አድርገን የምናጠናቅቅ እንድንሆን አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ።

እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ መልካም በዓል።

**መስከረም 17 ቀን 2016 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

# የኢትዮጵያን እምቅ አቅም የሚገልጠው "ገበታ ለትውልድ" ጂማ

መስከረም 18 ቀን 2016 ዓ.ም

በኢትዮጵያ ባጠቃላይ እጅግ ውብ የሆኑና በርካታ ሊታዩ ይበልጥ ሊሰራባቸው፣ ሊዋቡና ለቱሪዝም መስህብ ሊሆኑ የሚችሉ በጣም በርካታ ቦታዎች አሉ ። በተለይ ደግሞ ምዕራብ ኢትዮጵያ የሚባለውና ከዚህ ጂማን አንስቶ ዳውሮን፣ አርባምንጭን፣ ወላይታ ሶዶን፣ ሚዛን ተፈሪን፣ ቦንጋን፣ ኢሉአባቦራን እስከ ጋምቤላ አካባቢ ድረስ ያለው፣ በደሌን፣ ከፊል ወለጋን ጨምሮ የሚታየው ስፍራ ቡና በስፋት ያለበት ጫካ፣ ደን በስፋት ያለበት፣ ተራራማ ነገር ግን በዛፍ የተሞላ ነው። ይህን ከባቢ አዲስ አበባ አካባቢ ካለው የሚለየው ምንድን ነው ቢባል ቢያንስ በ1000 ሜትር የባህር ጠለል ያንሳል። ይህ ከ1500 ሜትር ብዙ አይበልጥም፤ ያ ግን 2000 ሜትር ነው። ዝቅ ማለቱ የሙቀት አቅሙን ከፍ ያደርገዋል፣ የምትተክለው ነገር ሁሉ በቶሎ ይበቅላል ማለት ነው። ከዚያ በተጨማሪ አሁን እዚህ ያለንበት ቦታ ተራራ አለ። ይህ ተራራ በውስጡ ሰፊ የቡና ጫካ ያለበት በትላልቅ ዛፍ የተሸፈነ በጣም፣ በጣም የሚያምር ቦታ ነው። እንደዚህ አይነት በርካታ ቦታዎች የምታገኘው በብዙ ችግር ነው ፤ ተራራውም አለ የሚታየው እይታ በርቀት በጣም ይገርማል  ቡናው አለ ዛፉ አለ ፤ ከዛ ደግሞ ስትወርድ ይህ ቦዮ ይባላል የጊቤና አዌቱ ወንዝ መገናኛ ቦታ ነው።

ሁለት፣ ሦስት ትላልቅ ሃይቆች ቀደም ሲል በጣሊያን ጊዜ ነበሩ፤ ይህ የምታየው የጣሊያን ቤት ነው። ጣሊያኖች ሃይቁ ዳር እየመጡ ይበሉ ፣ ይጠጡ ፣ ይዝናኑ ነበር ። እነሱ ከወጡ በኋላ አሁን ያለው ፋሽን፣ አሁን ያለው የከተማ ስሪት ፋሽን ላስቲክ ቤት፣ ቆርቆሮ ቤት አስፓልት ዳር መለጠፍ ስለሆነ እንደዚህ አይነቱን ውብ ጂማ ሳይሆን የተለጣጠፈውን፣ የላስቲኩን፣ ቆርቆሮውን ጂማ እንዲታይ ሆኗል። ውበትን የምናይበት፣ ውበትን የምንሰራበት፣ ውበትን የምናደንቅበት መንገድ የእኛን ልክ የሚገልጽና የሚያሳይ ነው። በቆሸሸ ነገር ውስጥ ምንም ገንዘብ አይገኝም ልል አልችልም፣ ነገር ግን በቆሸሸ ስፍራ ላይ የሚገኝ ገንዘብ አብሮ የሚገኝን በሽታ ለማከም ለመታደግ የሚያስችል አይደለም። እናም ውሃን ፣ ዛፍን ፣ ጫካን ፣ ሰፋፊ መስክንና የሚያምሩ ቦታዎችን በምናይብት ሰዓት ትናንሽ የሰው እጅ ሥራ ቢታከልበት ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል። አሁን ይህ ቦታ በአዲሱ የገበታ ለትውልድ ከተመረጡ ቦታዎች አንዱ ነው። ዛፉ አለ፣

ጫካው አለ እንዳየነው ትላልቅ ሃይቆች አሉ። ትናንሽ ሥራ ይፈልጋሉ፤ ይህ ሀይቅ በሳር ተሸፍኖ ስሩ ውሃ ቢሆንም በሳር ተሸፍኖ ጠፍቶ ነበር። አሁን እንዳዲስ የሸፈነውን ሳር ዝርያ በማንሳት ሃይቁን መልሰን ለማዳን ነው እየሰራን ያለነው።

ከሁለት ዓመት፣ ከሦስት ዓመት በኋላ በእርግጠኝነት በጣም የሚያምር ስፍራና የዚህ ሥራ ውጤት ያን ላስቲክ፣ ያን ቆርቆሮ፣ ያን ያልተመቸ የኑሮ ዘይቤ በከፍተኛ ደረጃ positively influence ያደርገዋል። ካልጠፋ ቦታ እዚህ ቀይ አፈር አለ፣ ሸክላ አለ፣ ቡና አለ፣ ሻይ አለ፣ ሩዝ አለ፣ ስንዴ አለ፣ በጣም በርካታ ፍራፍሬዎች አሉ። ከፍራፍሬ አንጻር እዚህ ቦታ ተክለህ የማይበቅል ነገር የለም። የሰው ልጅ ለምግብ ፍጆታ የሚሆነውን ነገር ተክሎ በቅርበት ማግኘት የሚችል ከሆነ፤ በሌላ መንገድ ከግንባታ አንጻር በርከት ያለ ድንጋይ አይገኝም ግን ቀዩ አፈር እሴት ተጨምሮበት በሸክላ አማካኝነት ለቤት ሥራም ለሌሎች ግንባታዎችም ሊውል ይችላል። እንጨት አለ፣ ሸክላ አለ መስታወት ነው ሊቸግርህና  የምታመጣው ነገር፤ እንዳየነው የእንጨት ሥራ ሶፋ፣ የበር ሥራ በሙሉ ጂማ አካባቢ ሙያውም አለ። እነዚህን ነገሮች አስተሳስረን መቀየር ያስፈልጋል ከባቢያችንን። ይህ ሲባል  ሥራው ቀላል ነገር አይደለም ጊዜ ይፈልጋል፣ ገንዘብ ይፈልጋል፣ ሃሳብ ይፈልጋል፤ ይህንንም ተከትሎ ወደ ተግባር መቀየር ይፈልጋል። አድካሚ አታካች ሥራ ነው፣ አድካሚ ያልሆነና የቀለለ ሥራ ደግሞ ላስቲኩ ነው። ከተማ ውስጥ ያየኸው፣ ቆርቆሮው ነው ስትሰራው ቀላል፣ ቆይታውም እጅግ ያጠረ ውበቱም እጅግ አስጠሊታ ነው።

እንደዚህ ውብ ነገር ስትሰራ ገንዘብ ይጠይቃል፣ ጊዜ ይወስዳል፣ ያደክማል፤ መላው የጂማ አካባቢ ሰው መገንዘብ ያለበት ይህንን ቦታ በመቀየር ልጆቻችን ያማረ፣ መልካም፣ ውብ ነገር ማየት፣ መስራት፣ ማለም፣ በዚያም መኖር የሚያመቻች ሁኔታ መፍጠር ይቻላል ። ይህች እርሾ ናት፣ ይችን እርሾ እያሰፋን ከባቢውን እንቀይራለን ። ሚዛን አማን ላይ የምናየው አዲስ የሚሰራው ሪዞርት ከዚህ ጋር ይያያዛል። የኩይሻ፣ ጨበራ ጩርጩራ በጣም ቅርብ ናቸው ሁለት ሰዓት ፣ ሁለት ሰዓት ተኩል ቢያስኬድ ነው። ቢያያዙ አጠቃላይ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክፍል በጫካው በውስጥ ለውስጥ በጣም የሚያማምሩ መንገዶች ከሠራህበት ለመንዳት የሚመች ስለሆነ ለብዙ ሰው ለሳምንት ለሁለት ሳምንት ያማረ ቆይታ ማድረግ የሚያስችል ቦታ ነው። እውነት ለመናገር ብዙ ቦታ እንደዚህ አይነት ውብ ነገር አታይም። የሰዎችን የእጅ ሥራ ታያለህ፣ በረሃ ላይ ጫካም ዛፍ ተክለው መንገድም ሠርተው ያሳመሩበት ቦታ አለ።

እኛ ተፈጥሮ የሰጠንን ውበትና ጸጋ ተጠቅመን ማልማት የሚያስችል እንቅስቃሴ መጀመር ይኖርብናል። እያደረግን ያለነውም እሱን ነው። በጥቂት ዓመታት ውስጥ ውብ ነገር በዚህ ስፍራ እንደምናይ እምነት አለኝ። የጂማ አካባቢ መስተዳድሮች ማህበረሰቡ ከፍተኛ ድጋፍ ነው እያደረገልን ያለው። እንደሚታየው ቤት በፍቃደኝነት ያነሳል፤ እዚህ አካባቢ ያለውን ህገወጥ ሰፈራዎች ለአዲሱ ዲዛይን ምቹ እንዲሆን በትብብር እያነሳ ነው የሚገኘው ይህ አስፈላጊ ነው ። ድህነትን መከፋፈል የለብንም፡ ውብ ነገር ሠርተን ብዙዎች ያን ውብ ነገር እንዲያምሩ ማድረግ አለብን እንጂ ሁላችንም በላስቲክ ድህነትን በመከፋፈል አካባቢውን ማበላሸት ተገቢ አይደለም።

ውሃ ቀብረን፣ ጫካ መንጥረን፣ በላስቲክ ኖረን ፣ አካባቢውን ገለን፣ አፈሩ እንደፈለገ እየሄደ ትውልድ ምን ይረከባል? ነገ ምን አይነት ሀገር ነው ለልጆቻችን የምንተወው የሚለውን ነገር ማሰብ ይጠይቃል። መልካም ጅማሮ ነው፣ በጣም ነው የሚያምረው፣ ይህን ውበት ትንሽ እጅ ሥራ ከተጨመረበት ለብዙ ኢትዮጵዊያን ኩራት የሆነ፣ ብዙ ኢትዮጵያዊያን ሥራ የሚያገኙበት፣ የሚሰባሰቡበት፣ የሚዝናኑበት ቦታ እንደሚሆን ተስፋ አድርጋለሁ።

ግን ኢትዮጵያዊያን ልባችንን ሰብሰብ ማድረግ ያስፈልጋል። ብዙ ሊሰራ የሚገባው ሥራ አለ፣ ችግር አለ ቆርጠን ሰርተን ለውጥ ማምጣት አለብን። እኛ የምንፈልገው ያማረች የተዋበች ኢትዮጵያን ማሸጋገር ነው። ለዚያም ጅምሮቻችን ፍሬ እንደሚያፈሩ በብዙ ሥራዎች አይተናል። በዚህ ዓመት በጣም በርካታዎች ይመረቃሉ። አዳዲሶች ይጀመራሉና ድል በድል፣ ሥራ በሥራ፣ ስኬት በስኬት፣ መከናወን በመከናወን፣ መጽናት በመጽናት ይቀጥላል ማለት ነው።

**መስከረም 18 ቀን 2016 ዓ.ም**
**ኦሮሚያ ክልል፤ ጂማ**

# የዜጎችን ሕይወት የሚቀይሩ የልማት ሥራዎች በጂማ ዞን

መስከረም 19 ቀን 2016 ዓ.ም

ዛሬ ከረፋድ ጀምረን ያለነው በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በቤንች ሸካ ዞን አካባቢ ነው። መቸም የምድር ገነትን ኢማጂን አድርጎ ማየት የሚፈልግ ሰው ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ቢመጣ፣ ቤንች ማጂ ቢመጣ ሊያይ የሚችል ይመስለኛል። ደኑ ታይቶ አይጠገብም፣ ተጉዘህበት አትጨርሰውም። የዛፉ አይነት የቅጠሉ ምሉዕነትና ወብት በጣም የሚያስደንቅ ነው። እንደዚህ አይነት ምድር አፍሪካ ውስጥ ኢትዮጵያ ውስጥ አለወይ የሚያስብል ነው፤ ግን እንዲሁ ውበት ብቻ አይደለም በውስጡ ያለው። ለምሳሌ አሁን ያለንበት በበቃ የቡና እርሻ አስር ሺ ሄክታር ገደማ ቡና የተተከለበት ነው። ይህ ቡና ከጥቂት ዓመታት በፊት በሄክታር አንድ ኩንታል ሁለት ኩንታል ይገኝበት የነበረ ነው። አሁን በምርጥ ዘር ተሻሽሎ እሰከ አስር ኩንታል ደርሰዋል አንዳንድ ቦታ በስፋትም ባይሆን  በጠብታ መስኖ እስከ ሃያ ኩንታል ደርሰዋል፣ የቡና ምርታማነት ብቻ ሳይሆን ጥራትም አድጎ ማለት ነው።

የተሰራው የቡና ምርታማነት እድገትና የምርምር ውጤት  የቡናን ምርታማነት የሚያሳድግ ስለሆነ የሚያበረታታ ነው። አሁን በበቃ የራሱን ብራንድ ይዞ ለስታር ባክስ የሚሸጥ ቡና ሆኗል። እዚሁ ጫካ ውስጥ ደግሞ ማር አለ፣ እዚሁ ዛፎች ላይ አይታችሁ ከሆነ ሃረጎችን ቁንዶ በርበሬ የሚባለው ቅመም እዚህ አለ፣ እርድ አለ፣ ጎማ ዛፍ አለ፣ ማር አለ በጣም ብዙ ነገር የሚታየው የጎማ ዛፉ እንዳየነው ራሱ ጎማው ታልቦ ነው የሚወሰደው። እርድን በሚመለከት በቅርብ ጊዜ ያሉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት እርድን መጠቀም የካንሰር በሽታን ለመቀነስ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ምርምሮች እየወጡ ይገኛሉ ። እናም በተፈጥሮ በከፍተኛ ስፍራዎች ላይ የተገኙ እርዶች፣ ቡናዎች፣ በርበሬዎች አጠቃላይ እዚህ አካባቢ ያለው የግብርና ውጤት ለጤና እጅግ በጣም ተስማሚ ነው። ለምሳሌ አናናሱን ወይም ሙዙን ቀምሳችሁት እንደሆነ እዚህ ያለው አናናስ በብዙ ቦታ እንዲሁ ቆርጠህ የምትበላው አይነት አናናስ አይደለም፣ በርከት ያለ ውሃ በውስጡ የያዘ ነው፣ በጣም ጣፋጭ ነው፣ ለምግብነት ያለው ጠቀሜታ በጣም ከፍተኛ ነው።

እንግዲህ ከቤንች ማጂ ትንሽ ዝቅ ስንል ዲማ የሚባል አካባቢ አለ። አኮቦ የሚባል ትልቅ ወንዝ በዚያ አካባቢ ያልፋል። የወርቅ በረከት ያለበት ባህላዊ ወርቅ የሚገኝበት ከባቢ ነው፤ እዚህ እንደዚህ አይነት ደን አለ መንገዱ በጣም ቆንጆ ነው። በርከት ያለ የቱሪዝም መስህብ መሆን ይችላል፣ ኢንቨስትመንት ሊስብ ይችላል፣ የህዝባችን የኑሮ ዘይቤ ሊያሻሽል ሊቀይር ይችላል ። እንግዲህ እኛ ዐይናችን በደንብ ስላልተገለጠ ያለንን ነገር አናውቅም። ከትናንት ጀምሮ በጂማ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የምናየውን ጫካ፣ የምናየውን ዛፍ፣ የምናየውን ቡና፣ የምናየውን ሙዝ ያየናቸውን የፍራፍሬ ምርቶች ብዙ ቦታ ለማየት ይከብዳል፤ ብዙ ቦታ በዚህ ልክና በዚህ ስፋት በዚህ ውበት መቶ ዓመት፣ ሁለት መቶ ዓመት የቆዩ ዛፎች እያዩ በዛው ውስጥ ደሞ ብር ከብርም በላይ ዶላር የሚታፈስበት ከባቢ እምብዛም የለም። ለምንድን ነው ይህንን ነገር ወደ ሀብት መቀየር ያልቻልነው ያልን እንደሆነ ሀብት በአንድ ሴክተር ብቻ የሚገኝ ነገር አይደለም። ግብርናውን በአገልግሎት ዘርፍ ማገዝ ያስፈልጋል፣ የአገልግሎት ዘርፍ ሲመጣ አብሮ የትራንስፖርት ዘርፍ አለ ቱሪዝም ይስባል። አሁን የደምቢ ሃይቅ ቅድም ያየነው ዛሬ ያስቀመጥነው መሰረት ድንጋይና በገበታ ለትውልድ የሚሰራው ሪዞርት ብዙ ሰዎች እዚህ ስፍራ መጥተው እንዲያዩ ያስገድዳል።

እዚህ ቦታ ደግሞ መጥቶ ያየ ሰው ኢንቨስት ለማድረግ የማናውቃቸውን ነገሮች ከከባቢው ለማውጣት ለመጠቀም የእውቀት ምንጭ ይሆናል። ለምሳሌ የጎንጂ ዛፍ የሚባለውን ረጃጅም ዛፍ እዚህ ጫካ ውስጥ አይታችሁ ከሆነ እዚህ በስፋት ነው የሚገኘው። በዓለም ላይ ግን እንደዝሆን ጥርስ ነው ። የዝሆን ጥርስና የጎንጂና ዛፍ መቁረጥ ተከልክሏል። ምክንያቱም ረዘም ላለ ጊዜ ይቆያል፤ ልክ እንደ ኮንክሪት በጣም ጠንካራ ነው በመሳሪያ እንኳን ለመቁረጥ ሰዓታት ይፈጃል። ያ የጎንጂ ዛፍ የሚያስፈልገው በጣም ጥንካሬ የሚፈልጉ መርከቦች የሚሰራበት ስለሆነ ነው፣ በቀላሉ የሚገኝ አይደለም እዚህ ግን በጣም በስፋት ነው ያለው። ጥቅሙን እንኳን በደንብ ተገንዝበን የምንጠቀምበት አይመስለኝም። ግን ከእንጨት ጋር የሚመረቱ መገልገያዎችን በሚመለከት ለረዥም ዓመታት የሚያገለግል ጠንካራ ዛፍ ነው የጎንጂ ዛፍ ። እንደዚህ አይነት በጣም በርካታ ዝርያዎች እዚህ ቦታ አሉ፤ እውነት ለመናገር ኢትዮጵያዊያን ሀገራቸውን ለማወቅ፣ ሀብታቸውን ለማወቅ፣ ሀብታቸውን ማወቅ ብቻ አይደለም ለመጠቀም፣ ለትውልድ ለማሸጋገር እንደነዚህ አይነት ስፍራዎችን ማወቅ በእጅጉ መገንዘብ አስፈላጊ ነው።

ምክንያቱም ሀገሩን ያላወቀ እናም ያልተጠቀመ እንዲሁ የባከነ ነው የሚሆነው፣ ከማባከን ተሰብስበን ለትውልድ የሚሸጋገር ነገር ለመተው የሚያስችለን ስናውቀው

ነው። አንተ በኪስህ ያለውን ገንዘብ የማታውቀው ከሆነ ወረቀት ነው፤ ኪስህ ገንዘብ እንዳለ ስታውቅ ነው ያንን ገንዘብ መንዝረህ የምትበላው፣ የምትጠጣው፣ የምትለብሰው፣ የምትጠቀምበት። ማወቅ ከሁሉም ይቀድማል፣ ካወቁ በኋላ ደግሞ መጠቀም ይለጥቃል፣ ለመጠቀም ማወቅ ባጣም ጠቃሚ ነገር ነው። እዚህ ቦታ ባየነው ነገር በጣም ተደምመናል። የኢትዮጵያን ስፋት፣ የኢትዮጵያን ሀብት፣ የኢትዮጵያን ገና ተመንዝሮ የማያልቅ የብልጽግና እምቅ አቅም ለመገንዘብ እድል ይሰጣል ብዬ አስባለሁ። እናም ሀብታችንን ማወቅ ፣ የቆዳ ስፋታችንን ማወቅ፣ በውስጡ ያለውን አቅም ማወቅ ለልጆቻችን ትምህርት ስናክልበት ወደ ሀብት ይቀየራል ። አንዱ የኢትዮጵያዊያን ችግር ስለ ኢኮኖሚ ያለን እሳቤ ነው። ኢኮኖሚ ማለት ወይም የኢኮኖሚ ጥናት በራሱ የእጥረት፣ የእጦት ጥናት ነው ፤ ጥናቱ በራሱ ይሄ ነገር ኢኮኖሚካል አይደለም አጠቃቀምህ ኢኮኖሚካል አይደለም ሲባል ዝቅ ያለ አይደለም የቀነሰ አይደለም ፣ ችግርን ታሳቢ ያደረገ አይደለም ማለት ነው። እኛ የምናስበው የዚያን ተቃራኒ እሳቤ ነው በእጥረት ላይ ሳይሆን መትረፍረፍ ላይ፣ በድህነት ሳይሆን ብልጽግና ላይ፣ በበሽታ ላይ ሳይሆን ጤና ላይ፣ እሳቤ ያደረገ ምርምር፣ በችግር ላይ ሳይሆን መፍትሄ ላይ ጊዜን፣ ገንዘብን፣ እውቀትንና እሳቤን ኢንቨስት ማድረግ ወደ ውጤት ይወስዳል የሚል እምነት አለን።

ከድህነት ይልቅ ብልጽግናን ለማየት፣ ከችግር ይልቅ ተድላን ለማየት፣ ከግጭት ይልቅ ሰላምን ለማየት፣ ከእጦት ይልቅ መትረፍረፍን ለማየት የእይታ ለውጥ ያስፈልጋል፣ የኢማጅኔሽን አቅም ይጠይቃል። ያ የኢማጅኔሽን አቅም ደግሞ በእጃችን ያሉ ወርቆችን ለማየትና ለመገልገል በር ይከፍታል ፣ ከማይታይ ነገር ውስጥ የሚታይ ነገር ፈልቅቆ ማውጣት ፣ ያን የታየውን ነገር ደግሞ ጥቅም ላይ እንዲውል አበክሮ መስራት ይጠይቃልና በየቀኑ እንበልጽግ ማለታችን ትክክል እንደሆነ ፣ በየቀኑ ለብልጽግና እጅግ ከፍተኛ የሆነ አቅም ያላት ሀገር፣ ትጉህ ህዝቦች ያላት ሀገር፣ መሆኗን እያየን ነው። ትናንት እና ዛሬ እንኳን ያየነውን ነገር በትክክል አስፋተን፣ አስውበን፣ አሳምረን፣ ለገበያ ምቹ አድርገን መስራት ብንችል ምን ልናመጣ እንደምንችል ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነገር ነው ። እንግዲህ አስበው ቡና ከጥቂት ዓመታት በፊት በሄክታር አንድ ፣ ሁለት ኩንታል የሚገኝበትን የነበረውን በጉንደላና አዳዲስ ዝርያ በመትከል አስር ደርሰናል። ግን ወደ ሃያ ማሳደግ እንችላለን ፤ በአንድ ሺህ ሄክታር በሄክታር አንድ ኩንታል ሲሆን አንድ ሺህ ኩንታል ነው የምታገኘው ፤ አስር ሲሆን አስር ሽህ ታገኛለህ። ሃያ ሲሆን ደግሞ ሃያ ሽህ ታገኛለህ። ይሄ በምርታማነት ላይ ከፍተኛ እመርታ የሚያመጣ ነው። በዚያው ልክ ደግሞ ጥራቱን ከሠራንበት ከፍ ያለ ገንዘብ ለማግኘት ያስችለናል።

በዚህ አካባቢ ሻይ አለ፣ ቡና አለ፣ በጣም በርካታ ፍራፍሬዎች አሉ፣ ለብዙ ሥራ የሚውሉ እንጨት ዝርያዎች አሉ። ለውበትም በገንዘብም ሊቀየሩ የሚችሉ ይህን መጠበቅ፣ ማስፋት፣ ማሳመር መጠቀም የእኛ የኢትዮጵዊያን ድርሻ ይሆናል።
ጠረፍ አካባቢ ላይ ያሉንን ሀብቶች ካወቅን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እንደዚህ አይነት ሀብት አለ፣ በአፋር አስደናቂ ሀብት አለ፣ በሶማሌ የሚገርም ሀብት አለ፣ በትግራይ ያላወቅነው በጣም በርካታ ሀብት አለ፣ በቤኒሻንጉል ጉምዝ ልዩ ልዩ ሀብቶች አሉ፣ በጋምቤላ ልዩ ልዩ ሀብቶች አሉ። እነዚህን ያወቀና ለመጠቀም ዝግጁ የሆነ ኢትዮጵያዊ እዛው ሰፈሩ ውስጥ ሲጨቃጨቅ አይውልም። ወጣ ብሎ ሰፋፊ ነገሮች እንዳሉት አስቦ ለመጠቀም ይበረታታልና በጣም ተስፋ ሰጭ ነገር ነው ያየነው እንሰራበታለን። ለሚቀጥለው የፖሊሲ ሃሳብ፣ ለሚቀጥለው የስትራቴጂ ሃሳብ፣
ለሚቀጥለው የውይይት ሃሳብ በጣም በቂ ከበቂም በላይ የሆነ መረጃ፣ እውቀት ሸምቻለሁ። ወደ ሥራ ለመቀየር እንግዲህ እንትጋ፣ እንበርታ። ይህን ወደ ውጤት እየቀየርን ኢትዮጵያችን እንደሁልጊዜው የበለጸገች፣ ያማረች ሆና ለልጆቻችን የምትተላለፍ ትሆናለች። እጅግ ደስ የሚል ጊዜ ነው ያሳለፍነው በጣም አድርጌ አመሰግናለሁ።

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ዜጎቻችን የክልልነት ጥያቄ ለረዥም ጊዜ ሲጠይቁ ቆይተው አሁን በቅርቡ ምላሽ አግኝተዋል። ግን የክልልነት ጉዳይ፣ የአገልግሎት ጉዳይ፣ የክብር ጉዳይ፣ የነጻነት ጉዳይ ብቻውን ምግብ አይሆንም። ክልል መሆን ጥሩ ነው፣ ሰብሰብ ብለን ሠርተን ደግሞ ወደ ልማት ቀይረን ልጆቻችንን አስተምረን ለውጤት እንድናበቃ አደራ ማለት እፈልጋለሁ። ከአንድ ዓመት ተኩል በፊት መጥቼ አይቻቸዋለሁ፤ አሁን ደግሞ መጥቼ በጣም ብዙ ለውጥ አይቻለሁ። ምናልባት ከአንድ ዓመት ወይም አንድ ዓመት ተኩል በኋላ ተመልሰን ደግሞ ዛሬ የጀመርናቸውን ጉዳዮች የዛሬ ዓመት ተኩል ሁለት ዓመት ገደማ የምናስመርቅ ይሆናል፤ እንኳን ደስ ያላችሁ፣ እንኳን ደስ ያለን። አመሰግናለሁ።

**መስከረም 20 ቀን 2016 ዓ.ም**

**ደቡብ ምዕራብ፤ ቤንች ሸካ ዞን**

# በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ቤንች ሸኮ ዞን ውሎ

መስከረም 20 ቀን 2016 ዓ.ም

ዛሬ ከረፋድ ጀምረን ያለነው በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በቤንች ሸካ ዞን አካባቢ ነው። መቸም የምድር ገነትን ኢማጂን አድርጎ ማየት የሚፈልግ ሰው ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ቢመጣ፣ ቤንች ማጂ ቢመጣ ሊያይ የሚችል ይመስለኛል። ደኑ ታይቶ አይጠገብም፣ ተጉዘህበት አትጨርሰውም። የዛፉ አይነት የቅጠሉ ምሉዕነትና ወብት በጣም የሚያስደንቅ ነው። እንደዚህ አይነት ምድር አፍሪካ ውስጥ ኢትዮጵያ ውስጥ አለወይ የሚያስብል ነው፤ ግን እንዲሁ ውበት ብቻ አይደለም በውስጡ ያለው። ለምሳሌ አሁን ያለንበት በበቃ የቡና እርሻ አስር ሺ ሄክታር ገደማ ቡና የተተከለበት ነው። ይህ ቡና ከጥቂት ዓመታት በፊት በሄክታር አንድ ኩንታል ሁለት ኩንታል ይገኝበት የነበረ ነው። አሁን በምርጥ ዘር ተሻሽሎ እስከ አስር ኩንታል ደርሰዋል አንዳንድ ቦታ በስፋትም ባይሆን በጠብታ መስኖ እስከ ሃያ ኩንታል ደርሰዋል፣ የቡና ምርታማነት ብቻ ሳይሆን ጥራትም አድጎ ማለት ነው።

የተሰራው የቡና ምርታማነት እድገትና የምርምር ውጤት የቡናን ምርታማነት የሚያሳድግ ስለሆነ የሚያበረታታ ነው። አሁን በበቃ የራሱን ብራንድ ይዞ ለስታር ባክስ የሚሸጥ ቡና ሆኗል። እዚሁ ጫካ ውስጥ ደግሞ ማር አለ፣ እዚሁ ዛፎች ላይ አይታችሁ ከሆነ ሃረጎችን ቁንዶ በርበሬ የሚባለው ቅመም እዚህ አለ፣ እርድ አለ፣ ጎማ ዛፍ አለ፣ ማር አለ በጣም ብዙ ነገር የሚታየው የጎማ ዛፉ እንዳየነው ራሱ ጎማው ታልቦ ነው የሚወሰደው። እርድን በሚመለከት በቅርብ ጊዜ ያሉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት እርድን መጠቀም የካንሰር በሽታን ለመቀነስ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ምርምሮች እየወጡ ይገኛሉ። እናም በተፈጥሮ በከፍተኛ ስፍራዎች ላይ የተገኙ እርዶች፣ ቡናዎች፣ በርበሬዎች አጠቃላይ እዚህ አካባቢ ያለው የግብርና ውጤት ለጤና እጅግ በጣም ተስማሚ ነው። ለምሳሌ አናናሱን ወይም ሙዙን ቀምሳችሁት እንደሆነ እዚህ ያለው አናናስ በብዙ ቦታ እንዲሁ ቀርጠህ የምትበላው አይነት አናናስ አይደለም፣ በርከት ያለ ውሃ በውስጡ የያዘ ነው፣ በጣም ጣፋጭ ነው፣ ለምግብነት ያለው ጠቀሜታ በጣም ከፍተኛ ነው።

እንግዲህ ከቤንች ማጂ ትንሽ ዝቅ ስንል ዲማ የሚባል አካባቢ አለ። አኮቦ የሚባል ትልቅ ወንዝ በዚያ አካባቢ ያልፋል። የወርቅ በረከት ያለበት ባህላዊ ወርቅ የሚገኝበት ከባቢ ነው ፤ እዚህ እንደዚህ አይነት ደን አለ መንገዱ በጣም ቆንጆ ነው ። በርከት ያለ የቱሪዝም መስህብ መሆን ይችላል፣ ኢንቨስትመንት ሊስብ ይችላል፣ የህዝባችን የኑሮ ዘይቤ ሊያሻሽል ሊቀይር ይችላል ። እንግዲህ እኛ ዐይናችን በደንብ ስላልተገለጠ ያለንን ነገር አናውቅም። ከትናንት ጀምሮ በጂማ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የምናየውን ጫካ፣ የምናየውን ዛፍ፣ የምናየውን ቡና፣ የምናየውን ሙዝ ያየናቸውን የፍራፍሬ ምርቶች ብዙ ቦታ ለማየት ይከብዳል፤ ብዙ ቦታ በዚህ ልክና በዚህ ስፋት በዚህ ውበት መቶ ዓመት፣ ሁለት መቶ ዓመት የቆዩ ዛፎች እያዩ በዛው ውስጥ ደሞ ብር ከብርም በላይ ዶላር የሚታፈስበት ከባቢ እምብዛም የለም። ለምንድን ነው ይህንን ነገር ወደ ሀብት መቀየር ያልቻልነው ያልን እንደሆነ ሀብት በአንድ ሴክተር ብቻ የሚገኝ ነገር አይደለም። ግብርናውን በአገልግሎት ዘርፍ ማገዝ ያስፈልጋል፣ የአገልግሎት ዘርፍ ሲመጣ አብሮ የትራንስፖርት ዘርፍ አለ ቱሪዝም ይስባል። አሁን የደምቢ ሃይቅ ቅድም ያየነው ዛሬ ያስቀመጥነው መሰረት ድንጋይና በገበታ ለትውልድ የሚሰራው ሪዞርት ብዙ ሰዎች እዚህ ስፍራ መጥተው እንዲያዩ ያስገድዳል።

እዚህ ቦታ ደግሞ መጥቶ ያየ ሰው ኢንቨስት ለማድረግ የማናውቃቸውን ነገሮች ከከባቢው ለማውጣት ለመጠቀም የእውቀት ምንጭ ይሆናል። ለምሳሌ የጎንጂ ዛፍ የሚባለውን ረጃጅም ዛፍ እዚህ ጫካ ውስጥ አይታችሁ ከሆነ እዚህ በስፋት ነው የሚገኘው። በዓለም ላይ ግን እንደዝሆን ጥርስ ነው ። የዝሆን ጥርስና የጎንጂና ዛፍ መቁረጥ ተከልክሏል። ምክንያቱም ረዘም ላለ ጊዜ ይቆያል፤ ልክ እንደ ኮንክሪት በጣም ጠንካራ ነው በመሳሪያ እንኳን ለመቁረጥ ሰዓታት ይፈጃል። ያ የጎንጂ ዛፍ የሚያስፈልገው በጣም ጥንካሬ የሚፈልጉ መርከቦች የሚሰራበት ስለሆነ ነው፣ በቀላሉ የሚገኝ አይደለም እዚህ ግን በጣም በስፋት ነው ያለው ። ጥቅሙን እንኳን በደንብ ተገንዝበን የምንጠቀምበት አይመስለኝም። ግን ከእንጨት ጋር የሚመረቱ መገልገያዎችን በሚመለከት ለረዥም ዓመታት የሚያገለግል ጠንካራ ዛፍ ነው የጎንጂ ዛፍ ። እንደዚህ አይነት በጣም በርካታ ዝርያዎች እዚህ ቦታ አሉ፤ እውነት ለመናገር ኢትዮጵያዊያን ሀገራቸውን ለማወቅ፣ ሀብታቸውን ለማወቅ፣ ሀብታቸውን ማወቅ ብቻ አይደለም ለመጠቀም፣ ለትውልድ ለማሸጋገር እንደነዚህ አይነት ስፍራዎችን ማወቅ በእጅጉ መገንዘብ አስፈላጊ ነው።

ምክንያቱም ሀገሩን ያላወቀ እናም ያልተጠቀመ እንዲሁ የባከነ ነው የሚሆነው፣ ከማባከን ተሰብስበን ለትውልድ የሚሸጋገር ነገር ለመተው የሚያስችለን ስናውቀው

ነው። አንተ በኪስህ ያለውን ገንዘብ የማታውቀው ከሆነ ወረቀት ነው ፤ ኪስህ ገንዘብ እንዳለ ስታውቅ ነው ያንን ገንዘብ መንዝረህ የምትበላው፣ የምትጠጣው፣ የምትለብሰው፣ የምትጠቀምበት። ማወቅ ከሁሉም ይቀድማል፣ ካወቁ በኋላ ደግሞ መጠቀም ይለጥቃል ፣ ለመጠቀም ማወቅ ባጣም ጠቃሚ ነገር ነው። እዚህ ቦታ ባየነው ነገር በጣም ተደምመናል። የኢትዮጵያን ስፋት፣ የኢትዮጵያን ሀብት፣ የኢትዮጵያን ገና ተመንዝሮ የማያልቅ የብልጽግና እምቅ አቅም ለመገንዘብ እድል ይሰጣል ብዬ አስባለሁ። እናም ሀብታችንን ማወቅ ፣ የቆዳ ስፋታችንን ማወቅ፣ በውስጡ ያለውን አቅም ማወቅ ለልጆቻችን ትምህርት ስናክልበት ወደ ሀብት ይቀየራል ።
አንዱ የኢትዮጵያዊያን ችግር ስለ ኢኮኖሚ ያለን እሳቤ ነው። ኢኮኖሚ ማለት ወይም የኢኮኖሚ ጥናት በራሱ የእጥረት፣ የእጦት ጥናት ነው፤ ጥናቱ በራሱ ይሄ ነገር ኢኮኖሚካል አይደለም አጠቃቀምህ ኢኮኖሚካል አይደለም ሲባል ዝቅ ያለ አይደለም የቀነሰ አይደለም፣ ችግርን ታሳቢ ያደረገ አይደለም ማለት ነው። እኛ የምናስበው የዚያን ተቃራኒ እሳቤ ነው በእጥረት ላይ ሳይሆን መትረፍረፍ ላይ፣ በድህነት ሳይሆን ብልጽግና ላይ፣ በበሽታ ላይ ሳይሆን ጤና ላይ፣ እሳቤ ያደረገ ምርምር፣ በችግር ላይ ሳይሆን መፍትሄ ላይ ጊዜን፣ ገንዘብን፣ እውቀትንና እሳቤን ኢንቨስት ማድረግ ወደ ውጤት ይወስዳል የሚል እምነት አለን ።

ከድህነት ይልቅ ብልጽግናን ለማየት፣ ከችግር ይልቅ ተድላን ለማየት፣ ከግጭት ይልቅ ሰላምን ለማየት፣ ከእጦት ይልቅ መትረፍረፍን ለማየት የእይታ ለውጥ ያስፈልጋል፣ የኢማጅኔሽን አቅም ይጠይቃል። ያ የኢማጅኔሽን አቅም ደግሞ በእጃችን ያሉ ወርቆችን ለማየትና ለመገልገል በር ይከፍታል ፣ ከማይታይ ነገር ውስጥ የሚታይ ነገር ፈልቅቆ ማውጣት፣ ያን የታየውን ነገር ደግሞ ጥቅም ላይ እንዲውል አበክሮ መስራት ይጠይቃልና በየቀኑ እንበልጽግ ማለታችን ትክክል እንደሆነ ፣ በየቀኑ ለብልጽግና እጅግ ከፍተኛ የሆነ አቅም ያላት ሀገር፣ ትጉህ ህዝቦች ያላት ሀገር፣ መሆኗን እያየን ነው። ትናንት እና ዛሬ እንኳን ያየነውን ነገር በትክክል አስፍተን፣ አስውበን፣ አሳምረን፣ ለገበያ ምቹ አድርገን መስራት ብንችል ምን ልናመጣ እንደምንችል ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነገር ነው። እንግዲህ አስበው ቡና ከጥቂት ዓመታት በፊት በሄክታር አንድ፣ ሁለት ኩንታል የሚገኝበትን የነበረውን በጉንደላና አዳዲስ ዝርያ በመትከል አስር ደርሰናል። ግን ወደ ሃያ ማሳደግ እንችላለን ፤ በአንድ ሺህ ሄክታር በሄክታር አንድ ኩንታል ሲሆን አንድ ሺህ ኩንታል ነው የምታገኘው ፤ አስር ሲሆን አስር ሽህ ታገኛለህ። ሃያ ሲሆን ደግሞ ሃያ ሽህ ታገኛለህ። ይሄ በምርታማነት ላይ ከፍተኛ እመርታ የሚያመጣ ነው። በዚያው ልክ ደግሞ ጥራቱን ከሠራንበት ከፍ ያለ ገንዘብ ለማግኘት ያስችለናል።

በዚህ አካባቢ ሻይ አለ ፣ ቡና አለ ፣ በጣም በርካታ ፍራፍሬዎች አሉ ፣ ለብዙ ሥራ የሚውሉ እንጨት ዝርያዎች አሉ። ለውበትም በገንዘብም ሊቀየሩ የሚችሉ ይህን መጠበቅ፣ ማስፋት፣ ማሳመር መጠቀም የእኛ የኢትዮጵዊያን ድርሻ ይሆናል። ጠረፍ አካባቢ ላይ ያሉንን ሀብቶች ካወቅን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እንደዚህ አይነት ሀብት አለ፣ በአፋር አስደናቂ ሀብት አለ፣ በሶማሌ የሚገርም ሀብት አለ፣ በትግራይ ያላወቅነው በጣም በርካታ ሀብት አለ ፣ በቤኒሻንጉል ጉምዝ ልዩ ልዩ ሀብቶች አሉ፣ በጋምቤላ ልዩ ልዩ ሀብቶች አሉ። እነዚህን ያወቀና ለመጠቀም ዝግጁ የሆነ ኢትዮጵያዊ እዛው ሰፈሩ ውስጥ ሲጨቃጨቅ አይውልም። ወጣ ብሎ ሰፋፊ ነገሮች እንዳሉት አስቦ ለመጠቀም ይበረታታልና በጣም ተስፋ ሰጭ ነገር ነው ያየነው እንሰራበታለን።

ለሚቀጥለው የፖሊሲ ሃሳብ፣ ለሚቀጥለው የስትራቴጂ ሃሳብ ፣ ለሚቀጥለው የውይይት ሃሳብ በጣም በቂ ከበቂም በላይ የሆነ መረጃ፣ እውቀት ሸምቻለሁ።
ወደ ሥራ ለመቀየር እንግዲህ እንትጋ፣ እንበርታ። ይህን ወደ ውጤት እየቀየርን ኢትዮጵያችን እንደሁልጊዜው የበለጸገች፣ ያማረች ሆና ለልጆቻችን የምትተላለፍ ትሆናለች። እጅግ ደስ የሚል ጊዜ ነው ያሳለፍነው በጣም አድርጌ አመሰግናለሁ ።

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ዜጎቻችን የክልልነት ጥያቄ ለረዥም ጊዜ ሲጠይቁ ቆይተው አሁን በቅርቡ ምላሽ አግኝተዋል። ግን የክልልነት ጉዳይ፣ የአገልግሎት ጉዳይ፣ የክብር ጉዳይ፣ የነጻነት ጉዳይ ብቻውን ምግብ አይሆንም። ክልል መሆን ጥሩ ነው፣ ሰብሰብ ብለን ሠርተን ደግሞ ወደ ልማት ቀይረን ልጆቻችንን አስተምረን ለውጤት እንድናበቃ አደራ ማለት እፈልጋለሁ። ከአንድ ዓመት ተኩል በፊት መጥቼ አይቻቸዋለሁ፤ አሁን ደግሞ መጥቼ በጣም ብዙ ለውጥ አይቻለሁ። ምናልባት ከአንድ ዓመት ወይም አንድ ዓመት ተኩል በኋላ ተመልሰን ደግሞ ዛሬ የጀመርናቸውን ጉዳዮች የዛሬ ዓመት ተኩል ሁለት ዓመት ገደማ የምናስመርቅ ይሆናል፤ እንኳን ደስ ያላችሁ፣ እንኳን ደስ ያለን። አመሰግናለሁ።

**መስከረም 20 ቀን 2016 ዓ.ም**
**ደቡብ ምዕራብ፤ ቤንች ሸካ ዞን**

# መልዕክቶች

# እንኳን ለመውሊድ በዓል አደረሳችሁ

መስከረም 28 ቀን 2015 ዓ.ም

በነቢዩ መሐመድ (ሰዐወ) መወለድ ዓለም እጅግ ተጠቅማለች። የዓለምን ታሪክ ቀይረዋል። የሰው ልጆችንም ሕይወት ለውጠዋል።

የመውሊድን በዓል የምናከብረው የዓለምን ታሪክና የሰው ልጆችን ሕይወት በመለውጥ መሆን አለበት። በግብርና እና በአምራች ኢንዱስትሪው ላይ እየሠራን ያለው ሥራ የሀገራችንን ታሪክና የሕዝባችንን ሕይወት የሚለውጥ ነው።

ኢትዮጵያን ከጦርነት በመገላገል ፊታችንን ሙሉ በሙሉ ታሪክና ሕይወት ወደሚለውጡ ዕቅዶቻችን እንዞራለን። የጀመርነው "የሌማት ትሩፋት" የቤተሰቦቻችንን ሥርዓተ ምግብ እንዲለውጥ ተግተን እንድንሠራ በዚሁ አጋጣሚ ጥሪ አቀርባለሁ።

**በድጋሚ መልካም የመውሊድ በዓል ይሁን**

**መስከረም 28 ቀን 2015 ዓ.ም**

# የፀረ ሙስና ብሔራዊ ኮሚቴ መቋቋም

ኅዳር 8 ቀን 2015 ዓ.ም

ሙስና ሀገርን የሚበላ ነቀዝ ነው፡፡ የሀገርን አንጡራ ሀብት እየቦረቦረ ጥሪቷን ባዶ ለማስቀረት ሌት ተቀን የሚማስን ተባይ ነው፡፡ ዋልጌ ባለሥልጣናት፣ በፍቅረ ነዋይ የታወሩ ደላሎች እና ባለሃብቶች አንድ ላይ ሲገጥሙ፤ ከነዚህ የሌብነት ፊታውራሪዎች ጀርባ ብዛት ያላቸው ዜጎች መሰለፍ ሲጀምሩ ሙስና የተባለው ነቀዝ ሀገርን እንደ ወረርሽኝ ያጠቃታል፡፡ ሙስና በየትኛው ቦታና በየትኛውም ዘመን ሊኖር ይችላል፡፡ ነገር ግን የሀገርን ልማት አጥንቱ ድረስ እስከ መጋጥ ከደረሰ ሙስና አንድ አደገኛ ወረርሽኝ ሆኗል ማለት ነው፡፡ ሙስና ሀገርን ሊያፈርስ የሚችል የደኅንነት ሥጋት መሆኑን ያስመሰከሩ ሀገሮችን በዘመናችን አይተናል፡፡ የአደንዛዥ ዕጽ፣ የኮንትሮባንድ፣ ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር፣ ሕገ ወጥ የጦር መሣሪያ ንግድ፣ የንግድ ማጭበርበር ሙስናን ለዓላማቸው ማስፈጸሚያነት ይፈልጉታል፡፡

በዓለማችን የተጀመሩ ጦርነቶች እንዳይጠናቀቁ፤ ግጭቶች እንዳይበርዱ፣ ሕዝቦች እርስ በርስ እንዲጋጩ፣ ከሚያደርጓቸው ምክንያቶች አንዱ ሙሰኞች ከዚህ አይነት ቀውሶች ስለሚያተርፉ ነው፡፡ ሙስና ዛሬ የሀገራችን የደኅንነት ሥጋት ሆኗል፡፡ ወደ ብልጽግና የምናደርገውን ጉዞ እጅ ተወርች አሥሮ ለመያዝ ከጠላቶቻች እኩል ሙሰኛው እየታገለን ነው፡፡ የተስተካከለ ቢሮክራሲ፣ የተቀናጀ መዋቅርና ዘመናዊ አሠራር ለሙስና ተጋላጭነትን ስለሚቀንሱ፣ እነዚህን ለማጥፋት ወይም ለማሰናከል ሙሰኛው ቀን ከሌት እየሠራ ነው፡፡ሕዝባችን በአገልግሎት አሰጣጥ፣ ከመሬት ጋር በተያያዙ አሠራሮች፣ በፋይናንስ ዘርፍ፣ በሽያጭና ግዥ ሂደቶች፣ በፍትሕ አደባባዮች፣ በተለያዩ የመንግሥት ተቋማት፣ የልማት ድርጅቶች፣ የህዝብ ተቋማት ወዘተ. በሚያጋጥመው ሙስና እየተማረረ ነው፡፡ በተለያዩ ጊዜያት ከሕዝብ ጋር በተደረጉ ውይይቶች ከጸጥታ ሥጋቶች እኩል ሙስና የብልጽግና ጉዟችን ዋናው ዕንቅፋት መሆኑን አንሥቷል፡፡

መንግሥት በየደረጃው የሚገኘውን መዋቅር በመፈተሽ፣ አዳዲስ አሠራሮችን በመዘርጋት፣ በቴክኖሎጂ የታገዙ ሥራዎችን እያሳለጠ ሥራዎችን ከእጅ ንክኪ ነጻ በማድረግ፣ በሙስና ወንጀል የሚሳተፉ አመራሮችንና ሌሎች ተዋንያንን ለሕግ በማቅረብ፣ ሙስና ምቹ ሁኔታ እንዳይፈጠርለት ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ነገር ግን

ሀገራችን ያጋጠማትን ጦርነትና ኮሮናን የመሳሰሉ ወረርሽኞች የመንግሥትን ትኩረት ወስደዋል ብለው ያሰቡ ሙሰኞች፣ በየቦታው ተሠግሥገውና ኔት ወርክ ዘርግተው፣ ኢትዮጵያን ለማጥፋት እየሠሩ መሆናቸውን በዝርዝር የቀረበው የጥናት ሪፖርት ያሳያል። መንግሥት በጸጥታው ዘርፍ እንዳደረገው ሁሉ በሙስና ላይ ጠንካራና የማያዳግም ኦፕሬሽን ማድረግ እንዳለበት የጥናቱ ውጤትና የሕዝብ ውይይቱ ግምገማ ያመለክታል። በአንድ በኩል የመንግሥት ሕጎች፣ደንቦች፣ መመሪያዎችና አሠራሮች ለሙስና ያላቸውን ተጋላጭነት የማጥፋት ሥራ ይሠራል። በሌላ በኩል ደግሞ የሙስና ተዋንያንን የማጋለጥና በሕግ የመጠየቅ ተግባር ይከናወናል።

መንግሥት በጥናት በደረሰባቸው የመንግሥት ሹመኞች፣ የመንግሥት ተቋማት ሰራተኞች፣ አቀባባዮችና ጉቦ ሰጪዎች ላይ ምርመራ እያደረገ ይገኛል። ነገር ግን ሙስና በባሕርዩ በረቀቀ መንገድ፣ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም፣ አንዳንድ ጊዜም በሕጋዊነት ሽፋን የሚካሄድ በመሆኑ በመንግሥት ጥናት የተደረሰባቸው አካላትን ብቻ ለሕግ በማቅረብ የሚፈታ አይደለም። ሙስናን ከሥር ከመሠረቱ ለመንቀል እንዲቻል ከሕግና ከአሠራር ማሻሻያዎች በተጨማሪ፣ የሙስና ተዋንያን ሁሉ ሙስናን እርም እንዲሉ የሚያደርግ ርምጃ ያስፈልጋል።መንግሥት በሙስና ላይ የሚያደርገውን ዘመቻ የሚያስተባብር፣ በጥናት ተለይተው ከቀረቡት በተጨማሪ ሌሎችንም ተዋንያን የሚለይና ለሕግ እንዲቀርቡ የሚያደርግ ብሔራዊ ኮሚቴ አቋቁሟል።

ብሔራዊ ኮሚቴው ሰባት አባላት ያሉት ሲሆን፣ እነርሱም፡-

1. አቶ ተመስገን ጥሩነህ
2. ዶ/ር ጌዴዎን ጢሞቴዎስ
3. አቶ ተክለ ወልድ አጥናፉ
4. አቶ ሰሎሞን ሶቃ
5. አቶ ደበሌ ቃበታ
6. ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ
7. አቶ አብዱሃሚድ መሃመድ ናቸው።

ይህ የፀረ ሙስና ብሔራዊ ኮሚቴ የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣትና ትርጉም ያለው ውጤት ለማምጣት እንዲችል የኅብረተሰቡ ሙሉ ትብብር እጅግ አስፈላጊ ነው። ኅብረተሰቡ በሙስና ላይ በሚደረገው ዘመቻ ሊሳተፍ እንደሚገባ በተለያዩ መድረኮች ሲያነሣ ቆይቷል። መንግሥትም ይሄንን የሕዝብ ተሳትፎ በእጅጉ ይፈልገዋል፤ ምክንያቱም ሙስና በዋናነት የሚጠፋው ሕዝብ አምርሮ ሲታገለው ነውና።

በመሆኑም ኅብረተሰቡ የሙስና ተዋንያንን በተመለከተ ያለውን መረጃ፣ ከቂምና ከበቀል ነጻ በሆነ መንገድ፣ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት አድራሻዎች ለብሔራዊ ኮሚቴው በመላክ ሙስናን ለማጥፋት በሚደረገው ትግል ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን ጥሪ እናቀርባለን። የሚቀርቡ ጥቆማዎች የጠቋሚዎችን ደህንነት ለማረጋገጥ ተገቢውን ጥንቃቄ እና ሚስጥራዊነት በጠበቀ መንገድ ተይዘው ይመረመራሉ። ብሄራዊ ኮሚቴው የሚወስዳቸው እርምጃዎች እና የእንቅስቃሴው ውጤት በየጊዜው ለህዝብ ይፋ ይደረጋል። የየክልሉ ርእሳነ መስተዳድሮች በየደረጃው የሚሠሩ ክልላዊ ኮሚቴዎችን በቅርቡ እንደሚያቋቁሙ በዚሁ አጋጣሚ እንገልጣለን።

ስልክ ፡ 9555
አጭር የፅሁፍ መልዕክት ፡ 9555
ድረ ገፅ ፡ http://www.9555pmo.et/
ኢሜይል: http://9555pmo.et/
ቴሌግራም ፡ https://t.me/PMOfeedback

**ኅዳር 8 ቀን 2015 ዓ.ም**

# እንኳን ለ17ኛው የብሔር ብሔረሰቦች በዓል (የኢትዮጵያዊነት ቀን) አደረሳችሁ።

ኅዳር 29 ቀን 2015 ዓ.ም

እንኳን ለ17ኛው የብሔር ብሔረሰቦች በዓል (የኢትዮጵያዊነት ቀን) አደረሳችሁ።

የዘንድሮው የብሔር ብሔረሰቦች በዓል (የኢትዮጵያዊነት ቀን) ‹ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችን ለዘላቂ ሰላማችን› በሚል መሪ ቃል ይከበራል። ዘላቂ ሰላም የሚኖረን ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችንን ማጽናት ስንችል ነው። ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ያለ ዘላቂ ሰላም፤ ዘላቂ ሰላምም ያለ ኅብረ ብሔራዊ አንደነት ሊሳካ አይችልም።

የብሔር ብሔረሰቦች በዓል የኢትዮጵያዊነት በዓል ነው። ኢትዮጵያዊነት የብሔር ብሔረሰቦች የጋራና የአንድነት መገለጫ ነውና። ኢትዮጵያዊነት ማለት የብሔር ብሔረሰቦች ዕሴቶች፣ ባህሎች፣ ታሪኮች፣ ቅርሶች፣ ቋንቋዎችና ጥበቦች በአንድነት የሚገለጡበት የጋራ ማንነት ነው። ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በዓለም መድረክ አሸናፊ ሆነው እንዲወጡ ከፈለግን ሁላችንም አሸናፊ የምንሆንበትን መንገድ መፍጠር አለብን። ጥያቄው እንዴት አድርገን ነው የምንፈጥረው የሚለው ነው።

ሁላችንም አሸናፊ መሆን የምንችለው ለሁላችን የምትሆን ኢትዮጵያን መገንባት ስንችል ነው። ባለፉት ዘመናት አልተደረጉም የምንላቸውን ነገሮች ማድረግ የምንችለው ነገ በምንገነባት ኢትዮጵያ ነው። ባለፉት ዘመናት መደረግ አልነበረባቸውም የምንላቸውን እንከኖችም ማረም የምንችለው ነገ በምገነባት ኢትዮጵያ ነው። ለሁላችንም የምትሆነውን ኢትዮጵያ በትክክል መገንባት የምንችለው ሁላችንም ነገ ላይ ትኩረት ካደረግን ነው።

ይህችን ኢትዮጵያ የምንገነባው በሁለት የጥበብ መንገዶች ነው። የመጀመሪያው ከሁላችንም እንዲቀነስብን በመፍቀድ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሁላችንም እንድናገኝ በማድረግ ነው። ለሌላው ወገናችን ህልውና፣ ሰላም፣ ክብር እና ፍትሕ ስንል የተወሰኑ ነገሮችን ከራሳችን ቀንሰን ለመሠዋት ፈቃደኞች መሆን አለብን። በጋራ መኖር የፈቃድ መሥዋዕትነትን ይፈልጋል። እንኳንስ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች ቀርቶ ባልና ሚስት

እንኳን በጋራ ለመኖር ከፈለጉ ለትዳራቸው ሲሉ በጋራ የሚከፍሉት መሥዋዕትነት መኖር አለበት። ይህ መሥዋዕትነት ግን ሁላችን ለሁላችን የምንከፍለው መሆን አለበት።

በግዳጅ አንድን ነገር ማጣት ቅጣት ነው። ያለ ፈቃድ አንድን ነገር ማጣት ጭቆና ነው። ሰውን በግድ መንጠቅ ግፍና ጥቃት ነው። በፈቃድ የሚደረግ ማጣት ግን የጋራ ቤት ለመሥራት የሚከፈል ታሪካዊ ዋጋ ነው። ሌላው ወገናችን እንዲኖር፣ እንዲከብር፣ ሰላምና ፍትሕ እንዲያገኝ ስንል የምንከፍለው የፍቅር ዋጋ ነው። ይሄንን ዋጋ ለመክፈል ካልተዘጋጀን ከመተባበር ይልቅ መገፋታተር፣ ከመደጋገፍ ይልቅ መጠላለፍ፤ ከአብሮነት ይልቅ ልዩነት፤ ከመከባበር ይልቅ መሰባበር ዕጣ ፈንታችን ይሆናል። የምንናገረውን ነገር፤ የምንሠራውን ሥራ፣ የምናወጣውን ሕግ፣ የምንዘረጋውን አሠራር፤ የምናከብረውን በዓል፣ የምንሰጠውን ሹመት፣ የምናካፍለውን ሀብት፣ ለሌሎችም እንዲሆን አድርገን ስናከናውነው የምናጣው ነገር ይኖር ይሆናል። ይህ ግን አብሮ ለመኖር፤ አንድ ሀገር ለመገንባት፤ ለሁላችን የሚሆን ብልጽግናን ለማረጋገጥ የተከፈለ ውድ ዋጋ ነው። ትውልድ ሁሉ ሲመካበትና ሲኮራበት የሚኖር ውድ ዋጋ ነው። በሌሎች መሥዋዕትነት ያልቆመ ማንም የለም። ሁላችንም የመሥዋዕትነት ውጤቶች ነን። ለዚህ ነው እኛም ለሌሎች ስንል መሥዋዕትነት መክፈል ያለብን።

ለእኔ ብቻ ብለን በምንሠራው ነገር ለጊዜው ያሸነፍን፣ የበለጥንና ያተረፍን ሊያስመስለን ይችላል። ሌላውን አግልሎ እና ሁሉንም ጠቅልሎ ከአንድ ምእራፍ በላይ መጓዝ ግን አይቻልም። የሰው ልጅ በታሪኩ የኖረው ምድር ለእርሱ ብቻ እንድትመች እያደረገ ነው። ለእንስሳት፣ ለዕጽዋትና ለሌሎች አካላት ብዙ ትኩረት ሳይሰጥ ነው ዕድገቱን የቀጠለው። በመጨረሻ ግን የተረዳው ነገር ቢኖር ብቻውን ሊኖር እንደማይችል ነው። ምድርን ለሰው ልጅ ብቻ ሳይሆን ለእንስሳት፣ ለዕጽዋትና ለሌሎች ሕይወት ያላቸው ፍጡራን ጭምር ምቹ እንድትሆን አድርጎ ካልተንከባከባት በቀር ሰው ብቻውን ደልቶት ምድር ላይ ሊኖር አይችልም። ሌላው ቀርቶ በዓይን የማይታዩ ፍጥረታት ጭምር ለሰው ልጅ ህልውና አስፈላጊ መሆናቸውንና ሰው ለእነርሱ ሲል ዋጋ መክፈል እንዳለበት ዘግይቶም ቢሆን ተረድቷል። የሰው ልጅ መድኃኒት እያጣላቸው የመጡ በሽታዎች የበዙት ሌሎችን አጥፍቶ ብቻውን ለመኖር ባደረገው የረዥም ጊዜ ትግል ምክንያት መሆኑን ከረፈደ ተረድቶታል።

**ውድ ኢትዮጵያውያን፣**

በምንም መልኩ አንዳችን ያለ ሌላችን ልንኖር፣ ልናድግና ልናሸንፍ አንችልም። ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሁሉም ሕዝቦች ሕዝቦቻችን ናቸው። ሁሉም ቋንቋዎች ቋንቋዎቻችን ናቸው። ሁሉም ባህሎች ባህሎቻችን ናቸው። ሁሉም በዓሎች በዓሎቻችን ናቸው። ሁሉም እምነቶች እምነቶቻችን ናቸው። ሁሉም ቅርሶች ቅርሶቻችን ናቸው። ሁሉም አካባቢዎች የሁላችን አካባቢዎች ናቸው። ሁሉም የተፈጥሮ ሀብቶች የሁላችንም ሀብቶች ናቸው። ለዚህም ነው በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል የጸጥታ ኃይሎቻችን ደማቸውን የሚያፈስሱት፤ አጥንታቸውንም የሚከሰክሱት።

በተቃራኒውም እንዲሁ። የማንኛውም ብሔር መገፋት የኢትዮጵያ መገፋት ነው። የማንኛውም ወገን ቁስል የኢትዮጵያ ቁስል ነው። የማንኛውም ሕዝብ የትናንት ስብራት የኢትዮጵያ ስብራት ነው። የማንኛውም ሕዝብ መዋረድ የኢትዮጵያ መዋረድ ነው። የማንኛውም ሕዝብ መገደል፣ መፈናቀልና ሰላም ማጣት የኢትዮጵያ መገደል፣ መፈናቀልና ሰላም ማጣት ነው።

ኢትዮጵያ እንደ ሰው ናት። እኛ ልጆቿ ደግሞ ልዩ ልዩ የሰውነት ክፍሎቿ ነን። ለአንዱ የሰውነት ክፍል የሚደረገው ነገር ሌላው የማይጎዳ መሆኑ መረጋገጥ ካልቻለ ጉዳቱ ዞሮ ይመጣል። አንዱን የሰውነት ክፍል አክብሮ ሌላውን አዋርዶ መሄድ አይቻልም። የአንዱ መታመም የሁሉም ሕመም ነው። አንዱ አካል ሲታመም ወደ ሕክምና የሚሄዱት ሁሉም አካላት ናቸው። እኛ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችም እንደዚሁ ነን።

ዛሬ ከግላዊ ፍላጎታችን ላለፈ ለጋራ ፍላጎታችንና ለአንድነታችን እጅ የምንዘረጋበት ቀን ነው፤ ዛሬ በልዩነት ውስጥ ውበት ሳይሆን በልዩነት ውጥ ህይወት እንዳለ የምንመሰክርበት ዕለት ነው። ዛሬ ከማገር የተጣላ ጣሪያ መሆናችን ያከትማል። ዛሬ በመኖሪያ ቤታችን ውስጥ የራሳችንን የማይተካ ቦታ እንይዛለን። ቤት በአገር ይመሰላል። ተነጣጥለን ከግብ እንደማንደርስ አውቀን በዕውቀት እና በፍላጎት ለጋራ ሕልውናችን በአንድነት እንቆማለን። አንዳችን ለአንዳችን መኖር የማናዳግም አማራጮች መሆናችንን ሳንዘነጋ እኩላችን ግርግዳ፣ እኩላችን ጣሪያ፣ እኩላችንም መዝጊያና መስኮት በመሆን አገራችንን ባማረ ሁኔታ እንገንባ።

**ውድ ኢትዮጵያውያን፣**

የብርሃን እና የፍካት ጊዜያችን ደርሷል፤ በትዕግስትና ተስፋ ባለመቁረጥ የንጋት ደውላችንን እንደውል። ከግባችን ሳንደርስ መቆም ትልቅ ኪሳራ ያመጣልና ፍጥነታችንን ጨምረን መጓዛችንን እንቀጥል። ያላለቀ ጉዞ ከንቱ ድካም ነውና የድካማችንን ፍሬ የመብላት ጊዜው ሳይደርስ በፊት ጉልበታችን አይዛል።

የመንግሥትነትና የታሪክ መሰረት የሌላቸው ሀገራት በአጭር ጊዜ ያማረ ሀገር እየገነቡ ባሉበት በዚህ ዘመን ላይ እንደ ኢትዮጵያ ያለች ባለ ጠንካራ መሰረት ሀገር ይዘን የተጀመረውን መጨረስ ሊሳነን አይገባም። ሌሎች ሀገራት ዛሬ በሚያወጧቸው ሕጎች ሁሉን የሚያቅፍ ሥርዓት መገንባት ከቻሉ እኛ ከእነሱ በተሻለ በእሴት ጭምር የመገንባት ሀገራችንን ማጽናት እንችላለን። የባለ ጠንካራ መሰረት ህዝቦች መሆናችንን የመዘንጋት ጊዜያችን ያብቃ፤ ልዩነታችንን ለሚና ካዋልነው አንድነታችን በእሴታችን ላይ ባማረ መልኩ ይገነባል። አንድነት እና ልዩነት አይጣሉብን፤ ልዩነት ያልተደፈነ ቀዳዳችንን የምንደፍንበት የሥራ ስማችን ነው፤ አንድነት ደግሞ የእውቀት ጉዟችን ይሆናል። እናም በህብረት አንድ ላይ በመቆም ብቻ ሳይሆን በመደመር ኃይላችንን ከቁጥራችን እናብዛ።

ሁላችንም የምንጠቀምበትን ፍኖት ካልተለምን በአንድ ሀገር ውስጥ እየኖርን የብቻ ጥቅማችን ዘላቂ ሊሆን አይችልም። ሁላችንም እኩል ካላሸነፍን፤ ማንም በዘላቂነት ሊያሸንፍ አይችልም። ሁላችንም ካልከበርን ማንም በዘላቂነት ሊከብር አይችልም። የምንሠራው እያንዳንዱ ሥራ ሌላውን የማይጎዳ፣ እንዲያውም ሌላውን ጭምር የሚጠቅም መሆኑን ርግጠኛ ካልሆን በስተቀር ልንሠራው አይገባም። የምናስብበት መመዘኛ ሁለት መሆን እንደሚገባው ልብ እንበል። መላው ኢትዮጵያን አሸናፊ የማያደርግ ነገር ሁሉ ይዋል ይደር እንጂ ጉዳት ማስከተሉ እንደማይቀር እንወቅ። ከዚህ በተቃራኒ ተጉዘን ስኬታማ እንሆናለን በማለት የሚደረግ ሩጫ የሕልም ሩጫ ይሆናል። በግላችን ሮጠን ድህነትን ከመካፈል ውጭ የምናሳካው ብልጽግና አይኖርም።
በድጋሚ እንኳን ለኢትዮጵያውያን ቀን አደረሰን፤ መልካም የብሔር ብሔረሰቦች በዓል ! !

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር !**

**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ !**

**ሕዳር 29፣ 2015 ዓ.ም**

# እንኳን ለኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል አደረሳችሁ !

ታህሳስ 28 ቀን 2015 ዓ.ም

በክርስቲያኖች ዘንድ የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል የዕርቅ መጀመሪያ ተደርጎ ይታሰባል። ከልደቱ በፊት በፈጣሪና በፍጡር፣ በሰማይና በምድር፣ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ታላቅ የጠብ ግድግዳ ተገንብቶ ለብዙ ዘመናት ቆይቷል። የልደት በዓል “ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ” የሚለው የፈጣሪ ቃል በተግባር መፈጸም የጀመረበት፤ በአምላክና በሰው ልጆች መካከል ዕርቅ የተወጠነባት ዕለት ናት።

ይህ በዓል መለያየት የጠፋበት፣ ኅብረትና አንድነት የጸናበት፤ መለኮትና ሥጋ፣ ህያውና ሟች፣ ዘላለማዊና ጊዜያዊ፣ ፈጣሪና ፍጡር፣ ሰማያዊና ምድራዊ፣ ምሉዕና ውሱን፣ በተዋሕዶ አንድ ሆነው አዲስ የምሥራች የተበሰረበት ነው። ክፉው በዘራው ዘር መለያየት ነግሦ፣ በሰማይና በምድር መካከል የማይሞላ ገደል ተፈጥሮ እንኖር ነበር። በጠብና በመለየት ምክንያት ኀዘንና ሰቆቃው በዝቶ በሰው ልጆች ታሪክ ጊዜው ዘመነ - ፍዳ ይሰኝ ነበር። የክርስቶስ መወለድ የራቀን አቅርቦ፣ የጠፋውን አግኝቶ፣ የፈረሰውን ገንብቶ፣ የፍዳውን ዘመን ወደ ምሕረት በመቀየር በዘላለማዊ ዕርቅ አንድ አደረገን።

የልደቱ ብሥራት እረኞችን ከሜዳ፣ ሰብአ ሰገልን ከሩቅ ከምሥራቅ ወደ አንድ አምጥቷል፤ ሰዎችን ከምድር ጠርቷል፤ መላእክትን ከሰማይ አውርዷል። ዕለቱ የሰማይና የምድር ፍጡራንን በደስታ ሞልቶ በቤተልሔም ከተማ በአንድነት እንዲዘምሩ አድርጓል። ተራርቀው የሚኖሩትን አሰባስቦ በአንድነት እንዲዘምሩ ያደረጋቸው ጉዳይ ከትናንት ለየቅል ታሪካቸው ይልቅ የነገ የጋራ ተስፋቸው ብሩህ ሆኖ ስለታያቸው ነው። እረኞችና ሰብአ ሰገል በትናንት ታሪካቸው የሚገናኙት በጥቂት ነው። ሰዎችና መላእክት በትናንት ሕይወታቸው የሚገናኙት በጥቂት ነው። የነገው ታሪካቸው ግን አዲስ፣ በደቦ የሚሠሩት፣ በጋራ የሚኖሩት፣ በአንድ የሚወርሱትና በሙላት የሚኖሩበት ነው። ለዚህ ነው ዛሬ የሁሉንም ታሪክ ከክርስቶስ ልደት ጋር አስተሣሥረን የምንተርከው።

ማን ነበርክ? ከሚለው ይልቅ ማን ለመሆን ትፈልጋለህ? የሚለው የአንድነታቸው መሠረት ነው። የነገውን በጋራ ከተጋሩት የትናንቱን በመተሳሰብ መቀበል

አይቸግራቸውም። በነገው ላይ ከተግባቡ በትናንቱ ላይ መስማማት አይፈትናቸውም። በረቷ የክርስቶስ በረት፣ እረኞቹ የክርስቶስ እረኞች፣ ጠቢባኑ የክርስቶስ ጠቢባን፣ መላእክትም የክርስቶስ መላእክት፣ ቀኗም የክርስቶስ የልደት ቀን፣ ዘመኑም የክርስቶስ ዘመን ሆነዋል። ያኛው የጥንቱ የብሉይ፣ ይሄኛው ደግሞ አዲሱ የሐዲስ ኪዳንና ታሪክ ሆነ። የጥንቱ በአዲሱ ምክንያት ታወቀ፤ የቀድሞው በአሁኑ ምክንያት ከበረ፤ የትናንቱ በዛሬው ምክንያት ታደሰ።

በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ መለያየት የመጣው እንዲሁ አይደለም። ሆን ተብሎ ተሠርቶበት ነው። ክፉው ሆን ብሎ የልዩነትን ዘር ዘርቶ፣ የልዩነትን እሾህ አብቅሎ፣ የጠላትነትን ፍሬ እንዲያፈራ አድርጓል። ልዩነቱም ከመለያየት አልፎ ወደ ጠላትነት እንዲሻገር ሠርቷል። ጠላትነቱም አዳምን ከገነት አፈናቅሏል። አቤልን በቃየል አስገድሏል። በምድር እሾህና አሜከላ አብቅሏል። የጥፋት ውኃን እልቂት አስከትሏል። ጦርነትና ግጭትን አትርፏል። በዚህ ሁሉ ጠላት እንጂ ማንም አልተጠቀመም።

አንድነትም የመጣው በብዙ ልፋትና መሥዕዋትነት እንጂ እንዲሁ በቀላሉ አይደለም። ከቤተልሔም እስከ ቀራንዮ፣ ከልደት እስከ ስቅለት፣ ከበረት እስከ ዕርገት ዋጋ ተከፍሎበት ነው። ዛሬ የምናከብረው ልደት ያስፈለገውም መለያየት ብቻ ሳይሆን በመካከላቸው ጠላትነት እንዲሰፍን የተሠራባቸውን ወገኖች አንድ ለማድረግ ነው። ይህን የወገኖች አንድነት ፍለጋ በሰማይ ያሉት ወደ ታች ወርደዋል። እነርሱ ይሄንን እንደ ውርደትም እንደ ውለታም አልቆጠሩትም። በምሥራቅ ያሉት ወደ ምዕራብ ሲመጡ እንደ ድካም አላዩትም። ሁሉም ሰጥቷል፤ ሁሉም ጎድሎበታል። ሁሉም አግኝቷል፤ ሁሉም ትቷል። ሁሉም ከፍ ብሏል፤ ሁሉም ዝቅ ብሏል። ሁሉንም በሁሉ ሆኖ የሞላውና ያሟላው የተወለደው ከሰማይ ወርዶ በግርግም የተወለደው ክርስቶስ ነው።

ኢትዮጵያውያን የነገዋን ኢትዮጵያ የተሻለች ለማድረግ ከዚህ የልደት ታሪክ ብዙ ትምህርት ብንወስድ ይጠቅመናል። ዛሬ እዚህም እዚያም የምናየው የመለያየትና የመጠፋፋት አባዜ የባህሪያችን አይደለም። የማናችንም ማንነት መገለጫ አይደለም። ይህ የተዘራብን ክፉ ዘር ውጤት ነው። የውስጥ የውጭ ባዳ አንድ ሆነው የዘሩብን ዘር ውጤት ነው። ያለንበት ዘመን ዘሩ የተዘራበት ጊዜ አይደለም።
አንዳንድ ሰዎች እንዲህ ይመስላቸዋል። ይህ ወቅት ዘሩ ጎምርቶ አፍርቶ ያየንበት ወቅት ነው። የታኅሣሥ መከር የሚዘራው በሐምሌ ነው። አንዳንድ ሰዎች ትናንትኮ እንዲህ ያለ ነገር አልነበረም ይላሉ። ዘሩ ከምድር በታች በመብቀል ላይ ስለነበረ አላስተዋልነውም።

ሰርዶው አድጎ እግር መጥለፍ ስላልጀመረ አልተቸገርንም። እንክርዳዱ በዝቶ ራስ ማዞር ስላልጀመረ አልታወቀንም። እሾሁ አፍጥጦ ሰውነት መቧጠጥ ስላልጀመረ አልለየነውም። አሜከላው በርክቶ እግር ለማድማት ስላልደረሰ ከቁብ አልቆጠርነውም። እንጂ ክፉው ዘርስ እየበቀለ ነበረ።

ወደ አዲሱ ዘመን፣ ወደ አዲሱ ብርሃን እንምጣ። ወደ አዲሱ ማንነት፣ ወደ አዲሱ ምእራፍ እንምጣ። አዲስ የጋራ ታሪክ ስንሠራ፤ የትናንቱ ታሪክ ያግባባናል። አዲስ መንገድ ስንጀምር የትናንቱ መንገድ አያጣላንም። አዲስ ዘመን ስንወጥን ያለፈው ዘመን አያለያየንም። አዲስ ዓላማ አንግበን ከተነሣን፣ የትናንቱ ዓላማ አያጨቃጭቀንም። የአንዳችን ጠላት ሆኖ የሌላችን ወዳጅ ሊሆን የሚችል የለም። አንዳችን ታምመን ሌላችን ጤነኛ መሆን አይታሰብም። አንዳችን ጎድሎብን ሌላችን ሙሉ ልንሆን አንችልም። አንዳችን ተከፍተን ሌላችን ደስተኛነትን ማጣጣም አንችልም። የሰው ልጅ ከገነት መውጣቱ የመላእክትን ደስታ ነጥቋል። የእንስሳትን ምቾት አጉድሏል። የምድርንና የሰማይን ክብር ገፍፏል። ገነትን ያለ ሰው አስቀርቷል። የሰው ልጅ ጠላት የሆነው ዲያብሎስ ለጊዜው በክፋቱ ስኬት በደስታ ፈንጥዟል። የሁላችንም ደስታ ሙሉ መሆን የቻለው ለሁሉም የሚሆነው ክርስቶስ ሲወለድ ነው።

የጠላታችን ዓላማ አንዳችንን ጠቅሞ ሌላችንን መጉዳት ሳይሆን ሁላችንንም ማጥፋት ነው። ዲያብሎስ መጀመሪያ አዳምና ሔዋንን አካሰሰ። ቀጥሎ ሰውን ከፈጣሪው ነጣጠለ። ከዚያ ሰውን ከመኖሪያው ከገነት አፈናቀለ። እሾህና አሜከላ እንዲበቅል አድርጎ ሰውንና ምድርን አቆራረጠ። ቃየልን በአቤል ላይ አስነስቶ አስገደለው። ጠላታችን አንዱን ሕዝብ ከሌላው በማጋጨት አይቆምም፤ አንዱንም ሕዝብ እርስ በርሱም ያባላዋል። ክልልን ከክልል፣ ዞንን ከዞን፣ ወረዳን ከወረዳ፣ ጎጥን ከጎጥ፣ ቤተሰብን ከቤተሰብ፣ ባልን ከሚስት፣ ልጆችን ከወላጆች እያባላ ዓለምን ሁሉ የግጭትና የጠብ ዐውድማ ማድረግ ነው ምኞቱ።

ስለዚህ ቆም ብለን እናስብ። መንገዱ ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ የሚበጅ፣ ለሁላችንም በቅቶ የሚተርፍ፣ አዲስ ማንነትን ይዘን እንደገና መወለድ ነው። ታሪክ ማለፋ አይቀርም። ታሪክ መለወጡም አይቀርም። ቁም ነገሩ የታሪክ ተከሳሽና ተወቃሽ ወይንስ ተዘካሪና ተሞጋሽ እንሆናለን? የሚለው ነው። ከሩቅ መጥተው መሲኹን እንደተገናኙት ጠቢባን ሰብአ ሰገል ታሪክ እንሠራለን ወይስ እንደ ሄሮድስ ታሪክን ለማጥፋት በንጹሐን ላይ ሰይፍ እናነሣለን? የሚለው ነው። እንደ ቅዱሳን መላእክቱ ለአዲስ ታሪክ አዲስ

የምሥራች እናበሥራለን ወይስ እንደ ዘመኑ የአይሁድ ልሂቃን ባለፈው ታሪክ ላይ ተተክለን የቀረበልንን ዕድል በንቀት እንገፋለን? የሚለው ነው። የእነዚህን ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ማግኘት፣ ኢትዮጵያ በአዲስ ልደት መንገድ እየተጓዘች የጌታችንንና የመድኃኒታችንን ልደት እንድታከብር ባለ በቂ ምክንያት ያደርጋታል።

መልካም የልደት በዓል ይሁንልን!

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!**

**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

**ታህሳስ 28፣ 2015 ዓ.ም.**

# እንኳን ለብርሃነ ጥምቀቱ በሰላም አደረሳችሁ !

ጥር 10፣ 2015 ዓ.ም

የጥምቀት በዓል ብዙ ትርጉሞችን ይዞ የሚከበር በዓል ነው። በአንድ በኩል ለክርስቲያኖች ትኅትናን የሚማሩበት፣ በእግዚአብሔር ማመናቸውን የሚያውጁበት፣ ንስሐና ድኅነት የሚያገኙበት ምልክት ሆኖ ያገለግላል። በሌላ በኩል እንደ ሀገር የጥምቀት ክብረ በዓል መልክ ብዙ የሆንን ኢትዮጵያውያን ኅብር ፈጥረን የምንደምቅበት በመሆኑ ታላቅ ቦታ ሰጥተን እናከብረዋለን።

በዓለ ጥምቀትና ትኅትና ተነጣጥለው የሚታዩ ጉዳዮች አይደሉም። ምክንያቱም ጥምቀት ፈጣሪ በፍጡር፣ አምላክ በሰው፣ ጌታ በአገልጋዩ የተጠመቀበት እለት ነውና። ከነበረበት ከፍታ ወርዶ ከሰው የተስተካከለበት፣ ከቆመበት የጌትነት ስፍራ ዝቅ ብሎ ትኅትናን ያሳየበት፣ ትእቢትን ሽሮ ለሰው ልጆች ትኅትናን ያስተማረበት አጋጣሚ ነው - ሥርዓተ ጥምቀቱ። በሥርዓተ ጥምቀቱ አጥማቂው ዮሐንስም ያሳየው ትኅትና እንዲሁ በምሳሌነት ይጠቀሳል። ፈጣሪው የሰጠውን ክብር እንደሚገባው ቆጥሮ በተዓብዮ ሳይታጠር፤ 'እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን?' ብሎ ማከላከሉ የመከበር ምሥጢሩ ትኅትና እንደሆነ፣ የኃይልና የብርታት ቁልፍ ታዛዥነት ውስጥ እንዳለ፣ የበላይነት መገኛውም ወደታች ወረዶ እያገለገሉ ጽድቅን መፈጸም እንደሆነ ያስተምረናል።

ሰዎች ከላይ የሆኑ ሲመስላቸው የታቹን የማያዩና የገዘፉ ሲመስላቸው በቅንነት ጎንበስ የማይሉ ከሆነ እነሱ የጥምቀቱ ትርጉም አልገባቸው። ትኅትናን ንቀው ትዕቢትን የመረጡ፣ ዝቅ ማለት ከብዷቸው ራሳቸውን ከፍ ከፍ ያደረጉ፣ ቅንነትን ጠልተው ግፍ መሥራት የወደዱ መጨረሻቸው ዕድገት ሳይሆን ቁልቁለት፣ ክብር ሳይሆን ውርደት መሆኑን በብዙ አጋጣሚዎች ዓለም አሳይታናለች።

በተቃራኒው የተሰጣቸውን ኃይል ለመልካም ዓላማ የተጠቀሙ ዘወትር ሥማቸው በጥሩ ሲነሣ ይኖራሉ። እንደ ሙሴ ያሉት የተሰጣቸውን በትር ባሕር ከፍለው ሕዝብን ወደ ተስፋ ሲያሻግሩ፤ እንደ ጎልያድ ያሉት ከሰው ሁሉ በላይ መግዘፋቸውን ለበደል ተጠቅመውታል፤ በዚህም ምክንያት ሙሴዎች ሲወደሱ ጎልያዶች በቀላሉ በጠጠር ወድቀዋል። ዓይናችንን ገልጠን ብንመለከት በዙሪያችን ከፍታቸውን ለክፋት፣ ኃይላቸውን

ለጭቆና በመጠቀማቸው አሳዛኝ ውድቀት የገጠማቸው ጎልያዶችን በአቅራቢያችን እናገኛለን። ተመሳሳዩ ዕጣ እንዳይገጥመን ሁላችንም ትኅትናና መልካምነትን ገንዘባችን ልናደርግ ይገባል።

ሌላኛው የጥምቀት ምሳሌ የመዳንና የንስሐ ምልክት መሆኑ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ፈለገ ዮርዳኖስ ከመውረዱ በፊት በኃጢአት የተሸፈነውን አዳም የኃጢአቴ ልብሱን ከላዩ ላይ ሊጥልለት የሞከረ አልነበረም። ጌታ ኢየሱስ በማዕከለ ዮርዳኖስ የመቆሙ ምክንያት የአዳምን ውርደት ለመቀበል፣ ኃጢአቱን ወስዶ ከመከራው ለማዳን፣ የሚነትበውን ልብስ ጥሎ በማይነትብ ዘላለማዊ ልብስ ለመተካት ነበር። በየዓመቱ ጥምቀቱን የምናከብረውም ከፊት - ቀድሞ ከመከራ የታደገን ክርስቶስን እያሰብን ነው።

ዛሬ የምናያቸውና የምንረማመድባቸው መንገዶች በአንድ ወቅት ጢሻ የነበሩና በፊት ቀደሞች መሥመር የወጣላቸው ናቸው። ዛሬ የሠለጠኑ ሀገሮች የሥልጣኔ ከፍታ ላይ የደረሱት በአንድ ወቅት ፊት አውራሪዎቻቸው በመከራ ውስጥ አልፈው፣ ችግርና ፈተናውን ተሻግረው መሠረት ስላኖሩላቸው እንጂ አዲስ ተዓምር ተፈጥሮላቸው አይደለም። ድኅነት፣ መታደስና ብልጽግና የሚመጣው ፊት ቀዳሚዎች ችግርና መከራውን ተጋፍጠው መንገድ ማስመር ሲችሉ ብቻ ነው። እኛ የዛሬው ትውልዶች ለሀገራችን ፊት ቀዳሚዎቿ እንደሆንን ማመን ይገባናል። እኛ መከራዋን ሳንቀበል ለኢትዮጵያችን ምቾት፣ ዝቅታውን ሳናይ ለሀገራችን ከፍታ፣ ጭለማውን ሳንጎበኝ ለልጅ ልጆቻችን ብርሃን እንደማይመጣ ማወቅ አለብን። ሀገራችን በድህነትና እርዛት የጠየመ ፊቷን፣ በኋላቀርነትና በጉስቁልና ያደፈ ልብሷን እኛ ወስደን በአዲስና በሚያበራ የመተካት ኃላፊነት እያንዳንዳችን ትከሻ ላይ ወድቋል። ኃላፊነታችንን በአግባቡ ከተወጣን የማናፍርባትን ሀገር፣ የሰለጠነች ኢትዮጵያን፣ የምንኮራበት ታሪክን ለልጅ ልጆቻችን ማስተላለፍ እንችላለን። ቅድመ አያቶቻችን ዋጋ ከፍለው በማለፋቸው ዛሬ የምንኮራባቸውን ሀገራዊ እሴቶች እንዳገኘን ሁሉ፤ እኛም ለመጪው ትውልድ ተመሳሳዩን ማድረግ ይጠበቅብናል።

**ውድ የሀገሬ ሕዝቦች፣**

በዓለ ጥምቀቱ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ከሃይማኖታዊ ክብረ በዓልነቱ በዘለለ ባህላዊ እሴቶቻችን የሚስተናገዱበት በዓል ጭምር ነው። ከጎንደር እስከ ሐረር፣ ከመቀሌ እስከ ባሌ፣ ከመተማ እስከ ጅማ በየስፍራው ኢትዮጵያውያን ወደ አደባባይ ይወጣሉ። አያሌዎች ዘመድ ለመጠየቅ ከቦታ ቦታ ይተምማሉ። ማኅበራዊ ኑሯችን የሚደምቅበት፣

በልዩ ልዩ አልባሳት የምናጌጥበት፣ ልዩ ልዩ ኅብረ ዜማዎችን የምንሰማበት ዕለት ነው። ጥምቀት የአደባባይ የባህል ሙዝየማችን ነው።

ኢትዮጵያ ምን ዓይነት ብሔሮች፣ ቋንቋዎች፣ አለባበሶች፣ የፀጉር አሠራሮች፣ ዜማዎች ወዘተ አሏት ብሎ ለሚጠይቅ፤ የጥምቀትን በዓል ተመልከት! ብሎ መመለስ ይቻላል። በዚህ ምክንያት ከዓለም በተለየ ጥምቀትን የእኛ ቅርስ ማድረግ ችለናል። ይሄንን ልምድ በሌሎች ዘርፎችም ልንደግመው ይገባል። ዴሞክራሲን በእኛው ቁመትና ወርድ ሰፍተን ካበጃጀነው፣ ቴክኖሎጂዎችን ኢትዮጵያዊ ለዛ ሰጥተን ከሠራነው፣ በኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች እኛን የሚመስሉ እሴትና ወረቶችን ካዳበርን በርግጥም ዓለም ፊቱን ወደእኛ ማድረጉ አይቀርም። ዛሬ ባሕረ ዮርዳኖስ ከሚገኝበት ሀገረ እስራኤል ጨምሮ ከመላው ዓለም ጥምቀትን ለመታደም በየዓመቱ ቱሪስቶች ወደ እኛ ይመጣሉ። የሀገር ውስጥና የውጭ ጎብኚዎችን የሚስብ ታላቅ ቀን በመሆኑ ጥምቀት ኢኮኖሚያዊ ፋይዳም እናገኝበታለን።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ አንድ ማወቅ ያለብን እውነት የኢትዮጵያ በዓላት የኢትዮጵያውያን ሁሉ በዓላት መሆናቸው ነው። በእምነቱ ብናምንም ባናምንም፣ በዓሉ ግን በዜግነት የሁላችንም ነው። የጥምቀትም፣ የዒድ አል ፈጥርም፣ የፋሲካም፣ የዒድ አልአድሐም፣ የገናም፣ የመውሊድም በዓል የሁላችንም ናቸው። የሀገራችን ሀብት የወገኖቻችን ደስታ ናቸውና እንኮራባቸዋለን። ሁላችንም ኢኮኖሚያዊ ፋይዳና እና ማኅበራዊ ጥቅም እናገኝባቸዋለን። በተለይ እንደ ጥምቀትና አረፋ ያሉ የአደባባይ በዓሎቻችንን በአማረና በደመቀ ሁኔታ እንዲከበሩ ሁላችንም እኩል ልንደክም ይገባል። መቼም ቢሆን፣ ጥምቀት ተስተጓጉሎ አረፋ፤ አረፋ ተስተጓጉሎ ጥምቀት አይሠምርምና። ለሁላችንም ደስታ እያንዳንዳችን የምንችለውን ሁሉ ማድረግ ይገባናል። በዓሉ በሰላም፣ በድምቀትና በክብር እንዲከናወን የምትተጉ ሁሉ ምስጋና ይገባችኋል።
በድጋሚ፣መልካም የከተራና የጥምቀት በዓል እንዲሆን እመኛለሁ።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!**

**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

**ጥር 10፣ 2015 ዓ.ም**

# “የትናንት ዘር፣ የዛሬ ፍሬ፣ የነገ ስንቅ ! ”

ጥር 25፣ 2015 ዓ.ም

አንድ ነገር የሚፈጠርበትና የሚታወቅበት ወቅት ሊለያይ ይችላል። ጽንስ ከተፈጠረ ከወራት በኋላ እርግዝና ሆኖ ይታያል፤ ሕጻን ሆኖ ለመወለድ ደግሞ ተጨማሪ ጊዜያትን ይወስዳል። የተወለደ ሕጻን አድጎና ጎልብቶ፣ ስብዕናውና ባህርይው ሙሉ ለሙሉ የሚታወቀው ደግሞ ከዓመታት በኋላ ነው። የሕይወት ትልቁ ምስጢር፣ ትናንት በማይታየው ጽንስና በጨቅላው ሕጻን ውስጥ የዛሬው ትልቅ ሰው ተሰውሮ መኖሩና ማደጉ ነው። የነገውን ማንነትና ውጤት ዛሬ የሚደረጉ እርምጃዎችና ማስተካከያዎች ሊቀርጹትና ሊያርሙት መቻላቸው ደግሞ ተስፋ የሚሰጥ እውነታ ነው።

የሰብልም ሆነ የአረም ዘር በእርሻ መሬት ውስጥ የሚኖርበትና፣ በቅሎና አድጎ የሚገለጥበት ጊዜ የተለያየ ነው። ዛፉ በዘሩ ውስጥ ይኖራል፤ እንደሚያገኘው አፈር፣ አየር፣ ብርሃንና እንክብካቤ በጊዜ ሂደት ውስጥ ሙሉ ማንነቱ ይገለጣል። ልክ እንደ ሥነ ሕይወታዊ ዘር ሁሉ፣ በማኅበረሰብ ውስጥ የሚዘራ የሐሳብ ዘርም አድጎና ጎልብቶ፣ አብቦና አፍርቶ በሰዎች ዙሪያ ተጨባጭ ሆኖ ለመገለጥ ዘለግ ያለ ጊዜ ይፈጃል። ለዚያም ነው ያልተገለጠን ነገር እንደሌለ አድርጎ የመውሰድ፣ አልፎ ተርፎም ነገሩ በተገለጠበት ጊዜ እንደ ተፈጠረ አድርጎ የመገንዘብ ዝንባሌ ስህተት የሚሆነው።

በተለይ ሥርዓታዊ ለውጥ፣ በጎም ሆነ ክፉ ውጤቱ በአጭር ጊዜ አይታይም፤ አይመዘንምም። ለለውጡ መነሻ የሆኑ ሐሳቦች በግለሰቦች ውስጥ ሠርጾ፤ ልማድና ሥርዓት ሆኖ፤ የማኅበረሰቡ ማንነት መገለጫ ባህል እስከሚሆን ድረስ ዘመናት ይፈጃል። ለውጡ የሚያስከትላቸው ስብራቶችም ሆኑ ትሩፋቶች የሚታወቁት በትውልድ ቅብብሎሽ ውስጥ ነው። ጉዳዩ ከግለሰቦች ሐሳብነት ተነስቶ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ዕቅድ ሆኖ ሲተገበር÷ ቀስ በቀስ እየተዋሃደ አሠራር፣ አኗኗር፣ ልማድና ባህሪይ ይሆናል። እንደ ወረርሽኝ በጥቂቶች ጀምሮ ብዙኃንን ይወርሳል። ከአንድ አካባቢ ተነስቶ ሀገርን ያዳርሳል። ይሄንን የለውጥ ሂደት መረዳት ላልቻሉ፤ ጅማሬውንና ዕድገቱን በትክክል ለማያስተውሉ የሚፈጠሩ ለውጦች ሁሉ ድንገቴና ማኅበረሰባዊ ድንጋጤን የሚያስከትሉ ናቸው።

በቅርቡ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የመልቀቂያ ፈተና የተገኘው ውጤት ለዚህ ጥሩ ማሳያ ነው። ከብዙ ጥናትና ሙግት በኋላ ኩረጃና ሥርቆትን በከፍተኛ ሁኔታ ለመቀነስ ተግባራዊ የተደረገው የተማከለ የፈተና ስልት ያስገኘው ውጤት ከፍተኛ ማኅበረሰባዊ መደናገጥን ሲፈጥር ታይቷል። ከተፈታኞቹ ሃምሳ ከመቶና ከዚያ በላይ ጥያቄዎቹን መልሰው ለማለፍ የቻሉት ተማሪዎች ቁጥር እጅግ አናሳ ናቸው። በሺህ የሚቆጠሩ ትምህርት ቤቶች አንድ ተማሪ እንኳን ለማሳለፍ ያልቻሉበት ሁኔታ ተፈጠረ። ይህም የትምህርት ጥራት ላይ ያሉብንን ችግሮችና ያለንበትን ቀውስ ፍንትው አድርጎ አሳየን። የችግሩን ልክ በአግባቡ፣ በአሐዝ መረጃ የተገነዘበነው እና ያየነው አሁን ቢሆንም፣ ችግሩ ግን በፈተናው የተገለጠ እንጂ የተፈጠረ አይደለም። የትምህርት ሥርዓቱ ስብራት ዛሬ የተፈተኑትን ተማሪዎች የሚያስተምሩ አስተማሪዎች ከተመለመሉበት፣ ከሠለጠኑበት መንገድ፣ አጠቃላይ የትምህርት ሥርዓቱ ከተመራበት ፖሊሲና አቅጣጫ እና ከሌሎች ብዙ ጉዳዮች ጋር የተያያዘ፤ ባለፉት አሥርት አመታት የሄድንበት የተንሻፈፈ ጉዞ ውጤት ነው። ዛሬ የችግር ሰብሉን ብናጭድም ዘሩ አፈር ነክቶ መብቀል ከጀመረ ዘመናት ተቆጥረዋል። ከዚህ ጋር ተያይዞ አንድ እውነት ማወቅ አለብን፤ ችግሩ በአንድ ሌሊት እንዳልተፈጠረ ሁሉ መፍትሔውም በአንድ አዳር ሊመጣ አይችልም። ዛሬ ከአበባ አልፎ ፍሬውን ያየነውን የትምህርት ችግር ቀልብሶ ለማስተካከል ረጅም ጊዜና ከባድ ዋጋ ይጠይቃል። እንዲህ ያለው ስብራት በአንድ ዘርፍ ብቻ ያለ ችግር ነው ብሎ ማሰብ ሥህተት ነው።

ልክ በትምህርት ዘርፉ ላይ መዛነፎች እንዳሉብን ሁሉ÷ በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚው፣ በማኅበራዊው፣ በፍትሕም ሆነ በጸጥታ ዘርፍ በተመሳሳይ ለረጅም ጊዜ የዘለቁ ስብራቶች አሉብን። ዘላቂነትንና አዋጪነትን ታሳቢ ያላደረጉ ብድሮች፣ ደካማ የፕሮጀክት አፈጻጸሞች፣ ብክነትና ሥርቆት፣ የተቋማት መቀንጨር፣ እጅግ ከፋፋይ የፖለቲካ ትርክትና ጽንፍ የወጣ ብሔርተኝነት፣ በእምነት ተቋማትና በማኅበራዊ ተቋማት ውስጥ ያሉ ፈተናዎች፣ በውጭ ግንኙነት የነበሩ ድክመቶች፣ በሞራልና ዕሴቶች ላይ የደረሱ ስብራቶች፣ ወዘተ . ባለፉት ብዙ አሥርት ዓመታት በሂደት ተፈጥረውና ተንሰራፍተው ቆይተዋል። እነዚህን ስብራቶች ልክ እንደ ትምህርት ሥርዓቱ የሚጋፈጣቸው ካላገኙ ሳይገለጡ የመኖርና ለድርብርብ ችግሮች መነሻ የመሆን ዕድላቸው ሰፊ ነው።

አንድ ገበሬ ዘሩን ከመዝራቱ በፊት በእርሻ ወቅት ነቅሎና ጎልጉሎ ያልጣላቸው የአረም ሰርዶዎች ሥርአቸውን ከመሬት በታች ቀብረው የሌሉ ቢመስሉም፤ ዋናውን ችግር የሚፈጥሩት የኋላ ኋላ ለመልካም ዘሩ የሚፈስሰውን ውሃና ማዳበሪያ ተሻምተው ካደጉ በኋላ ነው። በዚህም የተነሳ ያ ገበሬ ቀድሞ መንቀልና መጎልጎል በተገባው ጊዜ

ከሚያፈስሰው ጉልበት በላይ ዋጋ ከፍሎ በአረም ወቅት ለዳግም ልፋት ይዳረጋል። ለዚያም ነው ማኅበረሰባችን ለረጅም ዘመን ካዳበረው እውቀት ተነስቶ “አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ” የሚለው። ትናንት እንደ ሀገር ነቅሰን ያልጣልናቸው ፖለቲካዊና ማኅበራዊ አረሞች የሌሉ እስኪመስሉ ድረስ ሥራቸውን ደብቀው በመቆየታቸው፣ አሁን ምቹ አጋጣሚዎችን እየጠበቁ ለመልካም ልምምዶች የምናፈሳቸውን ፖለቲካዊ ወረቶች ሲሻሙ እያስተዋልን ነው።

ባለፉት ብዙ አሥርት ዓመታት በአፈናና በጉልበት ችግሩን ሸፋፍነነው የሌለ ቢመስለንም፣ ከፋፋይ የሆነው ትርክትና ጽንፍ የረገጠው ብሔርተኝነት ወርሶን ነበር። ዛሬ አንጻራዊ ነጻነት ሲኖር የችግሩን ልክ አካል ነሥቶ አየነው። የጸጥታና የፍትሕ ተቋሞቻችን በአግባቡ ተቋም ሆነው ተገቢው ዐቅምና ቁመና ሳይኖራቸው፣ በማስፈራራትና በአምባገነናዊ ዐውድ ልክ እንደ ፀጉራም ውሻ ከባድ ጡንቻ ያላቸው መስለው ይኖሩ ነበር። በነጻነትና ዴሞክራሲያዊ ዐውድ ሲፈተኑ ግን ስብራታቸው ጎልቶ ፈጥጦ ወጣ። በምዝበራ ተቦጥቡጦ፣ በብድር ጫና ደቅቆ የነበረው ኢኮኖሚ በዕድገት አመላካች ቁጥሮች ተጀቡኖ ሲጨበጨብለት ነበር፤ የተበደራችሁትን ክፈሉ ሲባል፣ የሕዝን ኑሮ ማሻሻል ሲሳነው፣ የሥራ ፈላጊዎችን የሥራ ፍላጎት በከፊል እንኳን ማሟላት ሲያቅተው የስብራቱ ልክ ተጋለጠ። ችግሮቹ ሥር የሰደዱ ቢሆኑም፤ ልካቸው ጎልቶ የታየውና የወጣው ሥርዓቱ በአንፃራዊ ነጻነት ሲፈተሽ ነው። ነጻነት በሌለበት፣ ሁሉም ታፍኖና ተዘግቶ በፍርሃት በተሸበበበት፣ ጭራሽ ችግሮቹ ጌጥ መስለው ሊታዩ ይችላሉ። እውነቱ ግን ውስጥ ለውስጥ ሥሩ መሬት ሲቆነጥጥና ድር ሲያደራ ቆይቶ የሀገርን ህልውና ሊገዘግዝ ጥርስ ሲያበቅል ነበር።

አሁን ከትምህርት ሥርዓቱ አንፃር ላለፉት ብዙ ዓመታት የሄድንበት መንገድና ውጤቱን መረዳት ብንችልም፣ ችግሩን ለማሻሻል ግን ገና ብዙ ጊዜ የሚፈጅ ሥራ ይጠብቀናል። ችግሩን ዐውቀነዋል ማለት ዛሬዉኑ ፈትተን እንጨርሰዋለን ማለት አይደለም። በኢኮኖሚውምና በፖለቲካ ሥርዓታችን ተመሳሳይ ሥራ ይጠብቀናል። በዴሞክራሲና በነጻነት ጥያቄዎች ምክንያት ሲንገዳገዱ ያየናቸው ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ተቋሞቻችን አቅማቸው የት ድረስ እንደሆነ እያየን ነው። የሥራ ፈጠራና የብድር አከፋፈል አቅማችንም የኢኮኖሚያዊ ሥርዓታችንን ደካማነት ቁልጭ አድርገው አሳይተውናል። የችግሩን ልክ ዛሬ ብንረዳም፣ ችግሩ ዛሬ እንዳልተፈጠረ እያሰብንና የመፍትሔ ምንጮች እኛ የዛሬዎቹ ትውልዶች መሆናችንን እያመንን በኃላፊነት እንሠራለን። የስብራቶቻችንን ልክና የችግሮቻችንን ጥልቀት በሚገባ ተረድተን የማሻሻያ

ርምጃዎችንም ተግባራዊ በማድረግ ላይ እንገኛለን።
ለረዥም ዘመን ሳይገለጥ፣ አልፎ ተርፎም እንደ ትክክለኛ ነገር ሲቆጠር የኖረን ማኅበራዊ ስብራት በሆነ አጋጣሚ ተገልጦ ፊት ለፊት ሲጋፈጡት በመጀመሪያ በድንጋጤ ተውጦ የሚያደርጉት ቢጠፋ እምብዛም አይደንቅም፤ ተፈጥሯዊ ምላሽም ነው።

ነገር ግን ጉዳዩንና የነገሩን መሠረት ለመካድ መሞከር ወይም ሰንካላ ሰበብ እያስቀመጡ ማለፍ ለችግሮች ዘላቂ መፍትሔ አያመጣም። ለወባ በሽታ የወባ መድኃኒት እንጂ፣ ገና ለገና በሽታው እንደ ራስ ምታትና ብርድ ብርድ የማለት ምልክቶችን አሳየ ተብሎ የብርድና የራስ ምታት ማስታገሻ መድኃኒቶችን እንደ ዘላቂ መፍትሔ አይወሰድም። ችግሮች ሲገጥሙ ጣት መጠቆምና በቀዳዳ ሾልኮ ማምለጥ የሞኞችና የፈሪዎች መፍትሔ ሲሆን፤ ትክክለኛው የብልህና የጀግኖች መንገድ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ፊት ለፊት ተጋፍጦ በጥበብ ለመርታት መፍጨርጨር ነው።
የትናንት ሥህተታችን የፈጠረውን የዛሬ ስብራታችንን ተረድተን ዘላቂ መፍትሔ ከሚፈጥሩት ወገን ለመሆን መዘጋጀት አለብን። በቅርብ ጊዜያት የሚያጋጥሙን ችግሮች ጥልቀታቸው በሙሉ ዐቅምና ቆራጥነት ወደ መፍትሔው እንድንገባ ሊገፋፉን ይገባል። በአዲስ ሃሳብና ጉልበት ለመገስገስ ተስፋ ሰንቀን እንነሳ፤ ለላቀ ለውጥና ለተሻለ ነገ እንትጋ። እንደ ሀገርና እንደ ማኅበረሰብ የሚያዋጣን መንገድ ይሄ ነው። ከትናንት የወረስናቸውን ሥህተቶች ነቅሰን ከጣልንና በምትኩ ዛሬ መልካም ዘር ከዘራን፥ ያለ ጥርጥር ልፋታችን መልካም ፍሬ ያፈራል፤ ለልጅ ልጆቻችንም የተስፋ ስንቅ ይሆናቸዋል።
ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር ! !

**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ !**
**ጥር 25፣ 2015 ዓ.ም**

# እንኳን ለ127ኛው የዐድዋ ድል በዓል በሰላም አደረሳችሁ !

የካቲት 22፣ 2015 ዓ.ም

የዐድዋን ድል ከፍ አድርገን እንድናከብረው የሚያደርጉን ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩም ዋነኛው ምክንያት ድሉ የሁላችንም በመሆኑ ነው። በየትኛውም የኢትዮጵያ አካባቢ ላይ ብንዘዋወር በዐድዋ ጦርነት ያልተሳተፉ ቀደምቶች የበቀሉበት ምድር አይገኝም። ሁሉም እንደ አቅምና ችሎታው ደምና ላቡን አፍስሷል፤ አጥንት - ሥጋውን ገብሯል፤ እውቀት ችሎታውን አዋጥቷል። አያት ቅድመ አያቶቻችን ያንን ሁሉ ዋጋ የከፈሉት ለግዛት አንድነት፤ ለኢትዮጵያዊነት ክብር እና ለሀገር ሉአላዊነት ነው። ዛሬ የምንኩራበት ማንነት፣ እንዳሻን የምንቦርቅበት ነጻነት፣ ውስን የምናድርባት ሀገር ያገኘነው በእነሱ መስዕዋትነት ነው። ዐድዋ የሁላችን አርማ ነው የምንለውም በዚህ ምክንያት ነው።

በሁላችን እውን የሆነ፣ ለሁላችን የተበረከተ ውድ ስጦታችን በመሆኑ ዐድዋን እንደ ከበረ እንቁ በስስት እናየዋለን። በብዙ ነገሮች ላንተሳሰር እንችላለን፤ ዐድዋ ገመድ ሆኖ ያስተሳስረናል። በብዙ ጉዳዮች ላንመሳሰል እንችላለን፤ ዐድዋ ቀለምና ቅርጽ ሰጥቶ ያመሳስለናል። በብዙ ነገሮች ላንግባባ እንችላለን፤ ቅድመ አያቶቻችንን አግባብቶ በአንድ አውድማ ያጋደለ “የዐድዋ ድል” ያግባባናል።

ዛሬ የግዛት አንድነታችንን የሚፈታተኑ ኃይሎች ከጉያችንም ይብቀሉ ከውጭ፣ የቅድም አያቶቻችንን አደራ ትቢያ ላይ ሊጥሉ የተነሱ ናቸውና የሁላችንም ጠላቶች ናቸው። በነጻነትና ሉአላዊነታችን ላይ የሚሰነዝሩ እኩይ እርምጃዎች በመከራ የወረሰናት ኢትዮጵያ ጫንቃ ላይ እንደበቀሉ እባጮች ቆጥረን እንፋለማቸዋለን። ኢትዮጵያን ለማሳነስና ኢትዮጵያዊነትን ለማኮሰስ ሌት ተቀን ሴራ የሚጎነጉኑ አካላት፤ ዐድዋ ያጋመደንን ማንነት ሊበጥሱ እንደተሳሉ ምላጮች አስበን በጋራ እንታገላቸዋለን።

ዐድዋ የጎራዴና የመድፍ፣ የጦርና የጠብመንጃ፣ የጋሻና የባሩድ ፍልሚያ የፈጠረው ድል ብቻ አይደለም። ወኔና ጀግንነት፣ ጥበብና መደመር የተባሉ እሴቶች ውጤት ጭምር እንጂ። በመሣሪያ ብዛትና ጥራት የሚበልጠንን ጠላት ያሸነፍነው በእነዚያ እሴቶች የበላይነት ስለነበረን ነው። ጣልያን የቱንም ያህል ዘመናዊ ጦር መሳሪያ

ቢታጠቅ የኢትዮጵያውያንን ወኔና ጀግንነት መርታት አልቻለም፤ የቱንም ያህል ጠንካራ ምሽግ ቢገነባ የቀደምቶቻችን ድምር ጉልበት አልመከተም፤ የቱንም ያህል ባንዳዎችን በጥቅምና በድርጎ ቢያባብል ከጦር መኮንኖቻችን ዘዴና ብልሃት አላመለጠም።
በብዙ ምክንያቶች የዐድዋ ድል ለኢትዮጵያውያን ያለው ትርጉም ከጊዜ ጋር ዋጋው እየጨመረ እንደሚሄድ ተቀማጭ ገንዘብ ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል። ትውልድ ሁሉ እየመነዘረ ሰላም፣ ልማት፣ ፍቅር፣ አንድነት፣ ጽናት፣ ጀግንነት፣ ክብርና ልዕልና ሊገዛበት የሚችል፤ ኩራትም እራትም የሚሆን፤ ቀደምቶቻችን ያስቀመጡልን አንጡራ ሀብት ነው። ይህ አንጡራ ሀብት ባለፉት መቶ ዓመታት በተደጋጋሚ የተቃጣብንን ወረራ እንድንመክት አድርጎናል። ይህ አንጡራ ሀብት ቅኝ ግዛትንና ቅኝ ገዥዎችን እንድንመክት አድርጎናል። ይህ አንጡራ ሀብት ሊፈርሱ ነው ከተባልን በኋላም እንደ ንሥር ታድሰን እንድንበረታ አስችሎናል። ይህ አንጡራ ሀብት በማይከፋፈል ኅብረ ብሔራዊነት፣ በማይጠቀለል አንድነት ጸንተን እንድንኖር አብቅቶናል።

**ውድ ኢትዮጵያውያን፣**

የዐድዋን ድል ስንዘክር አራት አካላትን ልናስታውስ ይገባል። የዘመቻው መሪዎችን፣ የጦር ዘማቾችን፣ የጦሩ ደጀኖችን እና የዘማቾቹ መሠረት የሆነውን ሕዝብ። የዐድዋን ዓይነት ድል ለማምጣትም እነዚህ ኃይሎች ተስማምተው፣ ተቀናጅተውና ተናብበው ለአንድ ሀገራዊ ዓላማ መሥራት ነበረባቸው።

ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱ መላውን የኢትዮጵያን ጦር አስተባብረው መርተዋል። ተገቢውን ጊዜና ሁኔታ መርጠው፣ የውስጥ ዐቅምና የውጭ ድጋፍን አስተባብረው፣ በአመራር ጥበብና በዲፕሎማሲ ብልሃት ችግሮችን እያለፉ፤ መቶ ሺዎችን ያስተባበረና ያስተሣሠረ፣ በዓለም በንቅናቄው እጅግ አስደማሚ የሆነ ዘመቻና ድል መርተዋል። የመሪ ብልህነት ቸኩሎ በመወሰን አይታወቅም። ተገውቢን ውሳኔ በተገቢው ጊዜና ሁኔታ በመወሰን እንጂ። ከ1881 ዓ.ም ጀምሮ በጣልያኖች ምክንያት የገባው የከብት በሽታ ለአራት ዓመታት ሕዝቡንም ከብቱንም ጎድቶት ነበር። ከፍተኛ ረሃብም ተከሥቶ ነበር። ምንም እንኳን ጣልያን ወሰን እየገፋ መምጣቱ ቢታወቅም ክፉው ቀን እስኪያልፍ፣ መሣሪያውም ከውጭ እስኪገባ መታገስ ይፈልግ ነበር።

ባለ ሦስት እርከን ከነበረው አመራር የምንወስደው ትምህርት አለ። ከላይ ንጉሠ ነገሥቱ፤ ቀጥሎ የየአካባቢው መሪዎች፣ ከዚያም የጦር አበጋዞቹ። የየአካባቢው መሪዎች አንዳንዶቹ ከንጉሡ ጋር የማይስማሙ ናቸው። ብሔራዊ ጥቅም ግን አንድ

አደረጋቸው። አንዳንዶቹ ሸፍተው ነበር። ሀገር ተወረረ፣ ድንበር ተደፈረ ሲባሉ ግን የግል ጠባቸውን ርግፍ አድርገው ለኢትዮጵያ ዘመቱ። አንዳንዶቹ በነበረው የአስተዳደር ሥርዓት የማይስማሙ ነበሩ። ሀገር የሚያጠፋ ጠላት ሲመጣ ግን ልዩነታቸውን ችለው፣ አለመስማማታቸውን ከኢትዮጵያ በታች አድርገው ዘመቱ። ያንን ሁሉ መኳንንትና መሳፍንት፣ ያንን ሁሉ የየአካባቢ ገዥ፣ ያንን ሁሉ የየማኅበረሰቡ መሪ ለአንድ ዘመቻ ያስተባበረው ምንድን ነው

ሥርዓቱ፣ አስተዳደሩ ወይም ርእዮተ ዓለሙ አይደለም። ከሁላችንም ኢትዮጵያ ትበልጣለች የሚለው እምነት እንጂ። ከክብራችንም፣ ከልዩነታችንም፣ ከቅሬታችንም፣ ከጠባችንም፣ ኢትዮጵያ ትበልጥብናለች ብሎ ማሰብ እንጂ። ከዚህ የምንወስደው ትምህርት አለ።

በዚህ ኅብረ ብሔራዊነትና ሀገራዊ አንድነት ጎልቶ በታየበት ታላቅ ዘመቻ ያልተሳተፈ ኢትዮጵያዊ ማኅበረሰብ አልነበረም። ከየአቅጣጫው የመጡትን ብሔር ብሔረሰቦች ያግባባቸው ቋንቋ "ነጻነት" ሲሆን፤ ያንን ሁሉ ጦር ወደ አንድ ዕዝ ያመጣው ሥርዓት "ኢትዮጵያዊነት" ይባላል። ከዚያ በፊት በዚያ መጠን፣ ከአራቱ ማዕዘን የመጡ ኢትዮጵያውያን በአንድ ቦታ ተገናኝተው አያውቁም። እንደ ዛሬው ብዙሃን - መገናኛ ባልነበረበት ዘመን የአዋጁ ዜና በፍጥነት እንዲዳረስ ያደረገው በሁሉም ዘንድ የነበረው የሀገር ፍቅር ስሜት ነው።

የዐድዋ ድል የፊት አውራሪዎች ድል ብቻ አልነበረም፤ የደጀኖች ድል ጭምር እንጂ። የጠላትን መረጃ ያመጡ የደኅነት ጀግኖች፤ ከተለያዩ ሀገራት የመሣሪያ ድጋፍ ያስገኙ የዲፕሎማሲ ጀግኖች፣ ጦሩን ሲያበረታቱ የነበሩ የኪነ ጥበብ ጀግኖች፤ ጦሩን ለዓላማ ሲያጸኑ የነበሩ የሃይማኖት አባቶች፣ ስንቅ ሲያዘጋጁና ሲያቀብሉ የነበሩ ሥራ ቤቶች፣ ቁስለኛ ሲያክሙ የነበሩ የሕክምና ጀግኖች፣ መንገድ ሲቀይሱና ሲያስተካክሉ የነበሩ የምሕንድስና ጀግኖች፣ ታሪክ ሲመዘግቡ የነበሩ ጀግኖች ነበሩ። ያልዘመተ ባለሞያ፣ ያልተሳተፈ ጥበብ አልነበረም። ልጆችና አዛውንቶች፣ ሴቶችና ወንዶች፣ ሁሉም እንደሙያና ችሎታው በተለያዩ ግዳጆች ዘምቷል። ኢትዮጵያ እዚህ የደረሰችው፤ ወደፊት የምትጸናውና የምትለማውም በዚህ መልኩ እንደሆነ ልብ ልንል ይገባል።

የዚህ ሁሉ ገድልና ድል መሠረቱ ግን ሕዝቡ ነው። ጀግኖቹን ያፈራው ሕዝቡ ነው። ጀግንነት ባህላችን እንዲሆን ያደረገው ሕዝቡ ነው። ልዩነት በኅብረ ብሔራዊ አንድነት፤

ግጭት በዕርቅ፣ ጠብ በፍቅር፣ የግል ጥቅም በሀገር ጥቅም እንዲሸነፍ ያደረገው ሕዝቡ ነው። ስንቁን ያዘጋጀው፣ እየሸለለና እየፎከረ ጀግኖቹን የሸኘው ሕዝቡ ነው። ከየቦታው መሣሪያ አፈላልጎ ጀግና ያስታጠቀው ሕዝቡ ነው። ጦሩ ግንባር ሲዘምት አካባቢውን የጠበቀው ሕዝቡ ነው። ከድል በኋላ ሀገር እንዳትራብ እህል ያመረተው፣ ከብቱን የጠበቀው ሕዝቡ ነው። የተሠዉትን ልጆች ያሳደገው፣ የቆሰሉትን ጀግኖች የተንከባከበው ሕዝቡ ነው። ድል አድራጊ ሕዝብ በሌለበት ድል አድራጊ ሠራዊት እንደማይፈጠር መዘንጋት የለበትም።

**ውድ የሀገሬ ልጆች፣**

የዛሬዋም ኢትዮጵያ አራቱ ኃይሎች ለአንድ ዓላማ እንዲቆሙላት ትፈልጋለች። መሪዎች፣ ዘማቾች፣ ደጀኖች እና መሠረቶች። ዓላማችን አንድ ነው፤ ኢትዮጵያን በሁለመናዋ የበለጸገች አፍሪካዊት ሀገር ማድረግ። በየደረጃው ያሉ መሪዎች፣ በየተቋማቱ ያሉ ዘማቾች፣ ዘማቾቹን በዕውቀት፣ በገንዘብ፣ በምክር፣ በተግሣጽ፣ በሐሳብ፣ በጥበብ የሚደገፉ ደጀኖች፣ የዚህ ሁሉ ባለቤትና ተጠቃሚ የሚሆነው ሕዝብ አንድ ሆነን ካልሠራን ግን ብልጽግና ምኞት እንጂ ሕይወት አይሆንም። እንኳን ታሪክ ሠሪ ታሪክ ዘካሪም አንሆንም።

የዐድዋ ዘማቾች ከወረርሽኝና ከተፈጥሮ ፈተና ጋር ታግለዋል፤ በአስተዳደርና በአገዛዝ መንገድ ልዩነት ነበራቸው። የውጭ ጫና ገጥሟቸዋል። የውስጥ ባንዳ ፈትኗቸዋል። ይህ ሁሉ ግን ከኢትዮጵያ በታች ነው ብለው ለአንድ ዓላማ ታግለዋል። ለአንድ ዓላማ ተሠዉተዋል። ካገኙት ይልቅ የሰጡን ይበልጣል። ከተጠቀሙት ይልቅ የጠቀሙን ይበልጣል። ለሀገሩ የሚሠራ ሰው መንገዱ ይሄው ነው።

ዛሬም ፈታኞችና ፈተናዎች ከፊታችን አሉ። የጀግኖች መለኪያ ግን እነዚህን ፈተናዎች ለነገው ተስፋ ብሎ ማለፍ ነው። በተከፈለልን ዋጋ እየኖርን ነውና እኛም ለሚመጣው ትውልድ ዋጋ መክፈል አለብን። በወቅቱ ኢትዮጵያ በአውሮፓ ቅኝ ገዥዎች መከበቧን፣ በውስጥ በከብት እልቂትና በረሃብ መፈተኗን ብቻ ብትመለከት ኖሮ ብርታትና ወኔ አይኖራትም ነበር። ችግሮቹን ብቻ የሚቆጥር ሕዝብ ዕድሎቹ ያመልጡታል። ዕድሎቹን ቆጥሮ የሚጸና ግን ችግሮቹን ያሸንፋል። ዐድዋ በችግር ተተብትቦ መቅረትን አላስተማረንም፤ ዕድልን ቆጥሮ ችግርን መሻገር እንጂ።

ከትናንት ይልቅ በነገ ላይ ካተኮርን፣ ሁሉን ነገር ከኢትዮጵያ በታች ካደረግን፣ ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችንን ካጸናን፣ እንደ ጉም የከበበን ፈተና ሁሉ እንደ ጢስ በንኖ ይጠፋል። ያኔ በድህነትና በኋላ ቀርነት ላይ፣ በመለያየትና በመከፋፈል ላይ የዐድዋ ድል ይደገማል።

**መልካም የድል በዓል ለሁላችንም ይሁን።**
**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
**የካቲት 22፣ 2015 ዓ.ም**

# “ከጊዜያዊ መፍትሄ ዘላቂ ጥቅም አይገኝም ! ”

ሚያዝያ 1 ቀን 2015 ዓ.ም

የዓለማችን ታላላቅ የውትድርና ጠበብት እንደሚናገሩት ከሆነ፤ የአንድ ሀገር ሠራዊት ጥንካሬ የሚወሰነው በዋናነት በማዕከላዊነቱና በጠንካራ የዕዝ ሰንሰለቱ ነው፡፡ እሥር ቦታ ተበጣጥሶ ከተዋቀረ መቶ ሠራዊት ይልቅ በአንድ ማዕከል በሥርዓት የተደራጀ ሠላሳ ሠራዊት ይበልጥ ጠንካራ እንደሚሆን በውትድርና አካዳሚ ውስጥ ያለፉ ሰዎች በትክክል ይገነዘቡታል፡፡ በመከላከያ ሠራዊት አደረጃጀት የቁጥር ብልጫ የሚጫወተው የራሱ ሚና እንዳለ ቢታመንም፤ ቁጥሩ በጠንካራ የዕዝ ሰንሰለት፣ በጥብቅ ዲሲፕሊን፣ በተደራጀ ስትራቴጂ እንዲሁም በረቀቁ መሳሪያዎችና ሥልጠናዎች እስካልታገዘ ድረስ የሠራዊት አቅም አስተማማኝ ሊሆን አይችልም፡፡ በተለይም በዘመናዊው ዓለም የሠራዊትን አቅም የሚለካው “ብዛት” ሳይሆን “ጥራት” እንደሆነ እሙን ነው፡፡ የሠራዊት ጥራት አንድም ከዶክትሪኑ፣ ከሥልጠናው፣ ከትጥቁና ከዕዝ ሰንሰለቱ የሚመነጭ ሲሆን፤ ወታደራዊ ማዕከላዊነት ለመከላከያ ሠራዊት “ጥራት” እጅግ ወሳኝ ነው፡፡

ሀገራት አጣዳፊ የጸጥታና የደህንነት ሥጋቶች ውስጥ በሚገቡበት ጊዜ፣ በማዕከላዊ የፀጥታና ደህንነት ተቋማት አማካኝነት የሚጋረጡባቸውን ሥጋቶች መመከት የማይችሉበት ሁኔታ ሲፈጠር፣ እንደ ሚሊሻና ልዩ ኃይል ያሉ፣ ለማቋቋም እምብዛም አዳጋች የማይሆኑ አነስተኛና መካከለኛ የጸጥታ ኃይሎችን አደራጅተው ለመንቀሳቀስ ይገደዳሉ፡፡ እነዚህ ኃይሎች በጥድፊያ ውስጥ በጊዜያዊነት እንደመቋቋማቸው መጠን የሚሰጡትም ጊዜያዊ መፍትሔ እንጂ ዘላቂ መፍትሔ እንዳልሆነ ይታወቃል፡፡ በውትድርና ብቻ ሳይሆን በሌሎች ዘርፎችም በጊዜያዊነት የሚቀመጡ መፍትሔዎችን ዘላቂ አድርጎ መውሰድ በራሱ አደጋ ሊጋርጥ እንደሚችል ታምኖበት ነው - ወደእነደዚህ ዓይነት የመፍትሔ አማራጮች የሚገባው፡፡ ትክክለኛ ጊዜው ሲደርስም፣ ዘላቂ ጥቅም የሚያስገኙ የመፍትሔ አማራጮች ቦታ ቦታቸውን እንዲይዙ ማድረግ የተለመደ አካሄድ ብቻ ሳይሆን እጅግ አስፈላጊ እርምጃ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አስቀድሞ በሪፎርም፣ አሁን ደግሞ በተደጋጋሚ ባደረጋቸው ውጊያዎች ጠንክሮና በቅቶ እየተገነባ ይገኛል፡፡ ይሄንን የመከላከያ ሠራዊት

ማዕከላዊ በሆነ መልኩ ማጠናከርና ለሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች እንዲበቃ ማድረግ ተገቢና ወቅታዊነቱ አያጠያይቅም። ይሄን መሠረት በማድረግ በተለያዩ ክልሎች የሚገኙ ልዩ ኃይሎች በተቻለ መጠን የሀገር መከላከያ ሠራዊቱን እንዲቀላቀሉ እየተሠራ ይገኛል። ወደ መከላከያ ሠራዊት ለመቀላቀል ያልፈለጉ ደግሞ ወደ ፌደራል ፖሊስ ወይም ወደ ክልሎች ፖሊስ እንዲገቡ ምርጫ ተቀምጦላቸዋል።

የየክልሉ ልዩ ኃይሎች ኢትዮጵያ አስቸጋሪ ፈተና በገጠማት ጊዜ ሕይወታቸውን ሠውተዋል። በየአካባቢው የተሰጣቸው ግዳጆችን በመወጣት ሕግና ሥርዓት ለማስከበር ታግለዋል። አሁን ባለችው ኢትዮጵያ የልዩ ኃይል አደረጃጀት አስፈላጊ አይደለም ማለት የልዩ ኃይል አባላት አያስፈልጉም ማለት አይደለም። ለሀገራችን የሚችሉትን ሁሉ ያደረጉ፤ የተጣለባቸውን ኃላፊነት በዐቅማቸው የተወጡ፤ ለወደፊትም በተሻለና ይበልጥ ኢትዮጵያን ማገልገል በሚያስችላቸው ቦታዎች ላይ እንደ የፍላጎታቸው ተመድበው ያገለግላሉ።

የልዩ ኃይል አባላትን ወደ መከላከያ ወይም ወደ ፖሊስ እንዲገቡ የማድረግ አጀንዳ ለረጅም ጊዜ ሲታሰብበትና ሲመከርበት የቆየ ጉዳይ ነው። አጀንዳው በተለያዩ ጊዜያት በአመራርም በሕዝብ መድረኮችም ተነሥቶ ነበር። ጉዳዩ እንዲነሣ ያደረጉት ሁለት ምክንያቶች ናቸው። አንዱ የልዩ ኃይል አባላትን ጥቅማ ጥቅም፣ ዕድገትና ማዕረግ የተመለከተ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ አደረጃጀቱን ምክንያት በማድረግ በተደጋጋሚ ያጋጠሙንን ፈተናዎች የተመለከተ ነው።

የልዩ ኃይል አመራሮችና አባላት ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ በተገቢው መንገድ መስተናገድ እንዳለባቸው ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ጉዳይ አይደለም። በሀገር ውስጥና በውጭ የሚሰጡ ወታደራዊ ትምህርቶችንና ሥልጠናዎች ሊደርሷቸው ያስፈልጋል። የላቁ ወታደራዊ መሣሪያዎችን ሊታጠቁ ይገባል። ከፍ ያሉትን ወታደራዊ ማዕረጎች በቆይታቸውና በጀብዱቸው ሊቀዳጁ ይገባል። ይህ መሆን የሚችለው ደግሞ ወደ መደበኛ የጸጥታና ደህንነት ተቋማት ማለትም በሀገር መከላከያ ሠራዊት ውስጥ አልያም በፌደራል ፖሊስ ሠራዊት ውስጥ እና በክልሎች ፖሊስ ሠራዊት ውስጥ መካተት ሲችሉ ብቻ ነው። እነዚህን የመሰሉ በውጊያ የተፈተኑ ኃይሎች በጊዜያዊ የልዩ ኃይል አደረጃጀት ብቻ ወስኖ ማስቀረት ሀገርንም አባላቱንም መጉዳት ነው።

**ውድ ኢትዮጵያውያን፣**

ጊዜያዊ የመፍትሔ አማራጭን በዘላቂነት መወሰድ የሚጋርጠው አደጋ ይኖራል ስንል በተጨባጭ መሠረት ላይ ቆመን እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል። ኢትዮጵያ ከክልል ልዩ ኃይሎች ጋር በተያያዘ ከአንዴም ሁለት ጊዜ የሀገርን ሉዓላዊነትና አንድነት የተገዳደሩ ፈተናዎች ገጥመዋት እንደነበር አይዘነጋም። ከአንድነትና ሉአላዊነት ሥጋትነት በመለስም በክልሎች መካከል የማያስፈልግ ተፎካካሪነትና ተገዳዳሪነት እንዲፈጠር መንስኤ ሲሆኑ እናያለን። ከሕገ ወጥ የኬላ ዝርጋታ፣ ከኮንትሮባንድ፣ ከሽፍትነት፣ ወዘተ ጋር የተያያዙ ፈተናዎችም እየተስተዋሉ ናቸው። እነዚህ ችግሮች የመነጩት ለጊዜያዊ መፍትሄነት የፈጠርናቸውን አደረጃጀቶች እንደ ዘላቂ መፍትሄ መቁጠር በመጀመራችን ነው። በመሆኑም ለዘላቂ ሀገራዊ ጥቅም ሲባል ነገሮችን በአግባቡ ፈትሾ አስፈላጊውን የመፍትሄ እርምጃ መውሰድ ተገቢ ነው።

የክልል ልዩ ኃይሎችን ጉዳይ በይደር ያቆየንበት ምክንያት ነበረን። አንደኛው የመከላከያ ኃይላችንን በበቂ መልኩ ለማደራጀት ጊዜና ዐቅም ስላስፈለገን ነበር። ሁለተኛው ደግሞ በወቅቱ በሀገራችን ላይ ከተጋረጠብን አደጋ አንጻር እነዚህን መሳይ ሥራዎች ለማከናወን የሚያስችል ሁኔታ ስላልተፈጠረ ነበር። ባለፉት ሦስት ዓመታትም ከሕዝብ ጋር በተደጋጋሚ በተደረጉ ውይይቶች ከሚነሡ ጉዳዮች አንዱ የልዩ ኃይሎች ጉዳይ ነበር። ካጋጠሙን ፈተናዎች በመነሣት ልዩ ኃይሎች ወደ መከላከያ እንዲጠቃለሉ ሕዝቡ ጠይቋል። የልዩ ኃይል አባላትም ከሜካናያዝድ ሥልጠና፣ ከደመወዝ፣ ከማዕረግ ዕድገት፣ ከትምህርት ዕድሎችና ከሌሎችም ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ነገሩን በተደጋጋሚ አንሥተውታል።

የልዩ ኃይል አባላትን ወደ ሌሎች የጸጥታ መዋቅሮች እንዲገቡ ለማድረግ ሲወሰን፣ ተገቢው ዝግጅት ተደርጎበት ነው። በመርሕ ደረጃ የተቀመጠውም የሚከተለው ነው።

- የልዩ ኃይል አመራሮችና አባላት እንዲወያዩበት ማድረግ
- ወደ ሌሎች ጸጥታ መዋቅሮች የማስገባቱ ተግባር በሁሉም የክልሎች ልዩ ኃይሎች ላይ እንዲተገበር
- አባላቱ ሦስት አማራጮች እንዲሰጣቸው (ወደ መከላከያ፣ ወደ ፌደራል ፖሊስ ወይም ወደ ክልል ፖሊስ እንዲገቡ)
- ጉዳዩ የትጥቅ መፍታት ጉዳይ ሳይሆን የበለጠ ሥልጠናና ትጥቅ አግኝተው ሀገርን በተሻለ ወደሚያገለግሉባቸው መዋቅሮች እንዲገቡ የሚያደርግ መሆኑን
- ይሄንን ሥራ ለማደናቀፍ የሚነሡ አካላት እንደሚኖሩ፤ መጀመሪያ በመወያየትና

በማሳመን፤ ከዚህ ያለፈ ተግባር የሚፈጽሙ ካሉም ሕግ የማስከበር ሥራ እንዲሠራ የሚሉ ናቸው።

የኢትዮጵያ ሠራዊት በብሔራዊ ደረጃ የተደራጀበትን ታሪክ ከተመለከትን የተለያዩ ወታደራዊ አደረጃጀቶችን ወደ ብሔራዊ የመከላከያ ሠራዊት በማዋሐድ የተከናወነ መሆኑን እናያለን። የሌሎች ሀገሮች ታሪክም ተመሳሳይ ነው። ከብሔራዊ የመከላከያ ሠራዊት ውጭ የሆኑ አደረጃጀቶች በተለያየ የታሪክ አጋጣሚ ሊፈጠሩ ይችላሉ። በዐማጽያን ትግል ምክንያት የሚፈጠርበት ጊዜ አለ። እነዚህ ዐማጽያን ወደ ሰላማዊ መንገድ ሲመለሱ ከሚከናወኑ ተግባራት አንዱ የታጠቁ አካላትን መርምሮና መልምሎ ወደ መከላከያ ሠራዊትነት መቀላቀል ነው። በ1983 ዓ.ም. መከናወን ነበረበት ብለን ለብዙ ዓመታት በተደጋጋሚ የኮነንነው አንዱ ጉዳይ ይሄ ነበር።

በሌላ በኩል ደግሞ ሀገር ፈተና ላይ ስትወድቅ የሚፈጠሩ ወታደራዊ አደረጃጀቶችም ይኖራሉ። ኢትዮጵያ በፋሺስት ጣልያን በተወረረችበት ጊዜ በታዋቂ ዐርበኞች ሥር የተፈጠሩ ወታደራዊ አደረጃጀቶች ለዚህ ምሳሌ ናቸው። ኢትዮጵያ ሀገራችን በፋሺስት ጣልያን በተወረረች ጊዜ የተለያዩ የዐርበኛ መሪዎች ጦር አደራጅተው በዱር በገደሉ ዘምተው ነበር። ጣልያን ድል ሆኖ ነጻነት ሲመለስ ከፊሎቹ ወደ መከላከያ ሠራዊት ሲገቡ፣ ሌሎች ወደ ሲቪል ሕይወት ተመልሰዋል።

ዛሬም የየክልሉ ልዩ ኃይሎችን እስከ ዛሬ ለሰጡት አገልግሎት አመስግነን፣ ወደ ሌሎች የጸጥታ መዋቅሮች የምናካትትበት ወቅት ላይ እንገኛለን። ይህ ውሳኔ በሁሉም ክልል አመራሮች በጋራ የተወሰነና በጋራ የሚተገበር ነው። አብዛኞቹ ክልሎችም ሠራዊት ለማስተዳደር የሚያስችል የኢኮኖሚ ዐቅም የላቸውም። ሁሉም ለማለት በሚያስደፍር ሁኔታ በፌዴራል መንግሥት ከሚሰጣቸው በጀት ለልዩ ኃይላቸው የሚጠቀሙ ናቸው። የዚህ ወይም የዚያ ክልል ልዩ ኃይል ብቻውን ትጥቅ ሊፈታ ነው፤ የዚህኛው ክልል ይቆይ ተብሏል፤ ይሄን ወይም ያንን ሕዝብ ለመጉዳት የተደረገ ነው የሚሉ ውዥንብሮችን የሚነዙ አካላት ገሚሶቹ ባለማወቅ ሲሆን፤ የተቀሩት ዓላማቸው ሕዝብ ከማበጣበጥ የዘለለ አይደለም። ጥቂት የማይባሉትም የክልል ልዩ ኃይል መፍረስ አለበት ብለው ሲጽፉና ሲሞግቱ የከረሙ ናቸው፤ ጠለቅ ብለን ብንፈትሻቸው፥ ይሁን ሲሏቸው አይሁን፣ አይሁን ሲሏቸው ይሁን የማለት ልማድ የተጠናወታቸው ሆነው እናገኛቸዋለን።

ከዚህ በኋላ ክልሎች የፖሊስ ኃይላቸውን አጠናክረው ወንጀልን በመከላከልና አካባቢያዊ ጸጥታን በማስከበር ላይ ብቻ ያተኩራሉ። ከየትኛውም ኃይል የሚሰነዘር፣ የሀገርን ድንበር፣ ህልውናና ሉዓላዊነት የሚዳፈር ኃይል ሲነሣ ደግሞ የመከላከያ ሠራዊቱ እርምጃ ይወስዳል። ለዚህ የሚሆን አደረጃጀትም በተግባር ላይ ውሏል። የክልሎች ፉክክርና ትብብር በልዩ ኃይል ግንባታ ሳይሆን በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊ ልማትና በዴሞክራሲያዊ ባህል ላይ ይሆናል። ይህ ውሳኔም ለኢትዮጵያ ኅብረ ብሔራዊ አንድነትና ለሕዝቡ ሰላም ሲባል ዋጋ ተከፍሎም ቢሆን ተግባራዊ ይደረጋል። ሳይገባቸው የሚቃወሙትን ለማስረዳትና ለማሳመን ጥረት እናደርጋለን። ሆን ብለው የአፍራሽነት ሚና በሚጫወቱት ላይ ደግሞ ተገቢው የሕግ ማስከበር እርምጃ ይወሰዳል። ለዚህም በቂ ዝግጅት ተደርጓል። በመሆኑም የሚመለከታቸው ተቋማትና ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በአጠቃላይ፣ የውሳኔውን ሀገራዊ ፋይዳና የሚያስገኘውን ዘላቂ ጥቅም ከግምት በማስገባት ለተግባራዊነቱ ርብርብ እንድታደርጉ በዚሁ አጋጣሚ ጥሪዮን አቀርባለሁ።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
**ሚያዝያ 1 ቀን 2015 ዓ.ም**

# እንኳን ለኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤ በዓል አደረሰን፣ አደረሳችሁ !

ሚያዝያ 7 ቀን 2015 ዓ.ም

በክርስቲያኖች ዘንድ ከፍተኛ ሥፍራ ተሰጥቷቸው ከሚከበሩ በዓላት መካከል በዓለ ትንሣኤው በቀዳሚነት ይጠቀሳል። የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የፍቅር ጥግ የታየበት፣ የዕርቅና የይቅርታ ትርጉም የተገለጠበት፣ ምሕረትና ድኅነት የተረጋገጠበት፣ የአዳም ተስፋ የተፈጸመበት ታላቅ በዓል ነው።

በቀዳሚዎቹ ዘመናት አባታችን አዳም አትብላ የተባለውን ዕጸ በለስ በልቶ የፈጣሪን ትእዛዝ ከተላለፈ በኋላ የሰው ልጅ የአምላክ ፍቅር ርቆት የፍዳ ዘመናትን አሳልፏል። በዲያቢሎስ ሤራ የተቆረጠው የፈጣሪና የፍጡር ፍቅር ዳግም እንዲታደስ አምላክ ከዙፋኑ ወደ ምድር ወረደ፤ በሰው ቁመትና ወርድ ተወሰነ፤ በደሙ አጥቦ የሰው ልጅን ከዘላለም ርግማን ሊያነጻ ክርስቶስ ታመመ፤ ስድብና ማንጓጠጡን፣ ውንጀላና ግርፋቱን፣ የዓለምን መከራ ሁሉ ያለ በደሉ ተቀበለ። ፍቅር በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ታየ። ፍጹም ፍቅር ከክብር ዙፋን ላይ መውረድን እንደሚጠይቅ፤ እውነተኛ መውደድ በቅድመ ሁኔታዎች እንደማይታጠር ክርስቶስ በተግባር አስተምሮናል።

የትንሣኤ በዓል የዕርቅና የይቅርታ በዓል ነው።

የክርስቶስ ትንሣኤ በአዳምና በእግዚአብሔር መካከል ለዘመናት ተገንብቶ የቆየውን የጸብ ግድግዳ እስከ ወዲያኛው አፈራርሶታል። ጸብ በሰው ልጆች ስሕተት ምክንያት የመጣ ነው። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በማንኛውም አጋጣሚ በሰው ልጆች መካከል ጸብ ሊፈጠር ይችላል። እንኳን ሰውና ሰው፣ ወንድምና እኅት ይቅርና፤ በፈጣሪና ፍጡር፣ በአምላክና ሰው፣ በመንፈስ አባትና ልጅ መካከልም ተከሥቷል። ዋናው ቁም ነገር የተፈጠረው ጸብ እስከወዲያኛው አራርቆ አለማቆየቱ፤ በዕርቅና በይቅርታ መቋጨቱ ላይ ነው። በትንሣኤው አዲስ የምሕረት ምዕራፍ ተከፍቶ የሰው ልጆች የርግማን ሰነድ ተሰረዘ እንጂ የበዳዩ በደል ተዘርዝሮ ሂሳብ ወደ ማወራረድ አልተገባም።

የተበደለ ፈጣሪ ሳለ ልጁን ለመሥዋዕት የላከው እሱ ነው። ዕርቅ አውራጁም እሱ፣ ይቅር ባዩም እሱ ነው። የዕርቅ ዓላማው ሰላም በማውረድ መከራን ማጥፋት ነውና

ተበዳዩ ይቅር ቢል የእሱን ታላቅነት ያሳያል እንጂ ተሸናፊ እንደማያደርገው የትንሣኤው ታሪክ ያስተምረናል።

ዛሬ በትንሣኤው በዓል ሰሞን ሆነን ባለፉት ረጅም ዘመናት በሀገራችን የተፈጠሩ ጸብና አለመግባባቶችን በዕርቅ ስለመቋጨት ማሰብና መወሰን አለብን። በታሪክ አጋጣሚ የተፈጠሩ የትናንት መቀራቀሶች የነገ ተስፋችንን እንዳያጨልሙ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መክረንና ዘክረን እንቋጫቸው። ከሂሳብ ማወራረድ አባዜ እንውጣ፤ ዳግም በምድራችን የታሪክ ዕዳ የተስፋ ምንዳችንን ቀረጣጥሞ አይብላው። የሐሳብ ልዩነቶች ከጠረጴዛ አልፈው የዐውደ ውጊያ መነሻ እንዳይሆኑ ለስሜቶቻችን ልጓም እናበጅላቸው፤ እልህና ክፋት ውድቀትን፣ ቅንነትና ምክክር ዕድገትን እንደሚያመጣ ዕንወቅ።

**ውድ የኢትዮጵያ ልጆች፣**

ሀገራችን የትንሣኤዋ ዋዜማ ላይ ነች። የምናያቸው ፈተናዎች የሕማማት ሰሞን ፈተናዎች ናቸው። እንደ ክርስቶስ ትንሣኤ ሁሉ የሀገራችን ብልጽግና እውን እንደሚሆን፣ የኢትዮጵያችን ትንሣኤ እንደሚሳካ ምንም ጥርጥር የለውም። ይኽ የሚሆነው ግን እንደ ኒቆዲሞስ ተስፋን ሰንቀው ወደ ትንሣኤው ብርሃን የሚገሠግሡ፣ እንደ ዮሐንስ ውኾ'ንብሩን ሁሉ በጽናት የሚያልፉ፣ እንደ ሮማዊው መቶ አለቃ እውነትን በድፍረት የሚመሰክሩ ዜጎች ሲበዙ ነው። ተስፋ ቆርጦ ጨለማው በራሱ ጊዜ እስኪገፈፍ፤ ድቅድቅ ሌሊቱ ተፈጥሯዊ ዑደቱን ጠብቆ እስኪነጋ እጅን አጣጥፎ በመቀመጥ ግን አይሳካም።

የትንሣኤው ጸጋ የግቡን ምንነት እንጂ ሂደቱን እንደማይጠቁም ሁሉ፤ "የኢትዮጵያ ብልጽግና እውን ከመሆን አይቀርም" የምንለው ጉዞው ቀላል እንደማይሆን በማመን ነው። ስለ ክርስቶስ መምጣት፣ ለአዳም ልጆች የመሥዋዕት በግ ሆኖ ስለመቅረቡና ሞቶ ስለ መነሣቱ አስቀድሞ ብዙ ትንቢቶች ተነግረዋል። ይሄንን ሁሉ ክደው ግን ከሄሮድስ እስከ ይሁዳ ብዙዎች ትንሣኤውን ለማስቀረት ሞክረዋል። በጉዞው ላይ ሰይፍ፣ ውንጀላ፣ መሳደድ፣ ክህደት፣ አሉባልታ፣ ሽብርና የመሳሰሉት ትንሣኤውን ሊገዳደሩት ሞክረው ነበር። የብልጽግና ጉዟችንም ከዕንቅፋቶች የጸዳ አይሆንም።

በተለይ በተለይ እንደ ይሁዳ ሀገርን በሽርፍራፊ ሳንቲም ለመሸጥ የማያመነቱ ሰዎችን ይዘን ጉዟችን ቀላል አይሆንም፤ ዜጎቻችን ቀናውን መንገድ የሚጠቁሙትን ትተው፣ እንደ ጸሐፍት ፈሪሳውያን ላሉ÷ ቅንነት በጎደለው ዕውቀት ለተሞሉ ሰዎች ሙሉ ጊዜያቸውን

መስጠት ከጀመሩ ሩጫችን ወደ ርምጃ መለወጡ አይቀርም። ስለዚህ በብልጽግና ጉዟችን ውስጥ ከፈተናችን በላይ መሆን እንድንችል የፈተናችንን ዓይነትና ፈታኞቻችንን ለይተን ማወቅ እና በጽናት ለመታገል መወሰን አለብን። መጨነቅና መጠበብ፣ ማወቅና መጠንቀቅ፣ መጽናትና ከክፋት መጠበቅ የሚያስፈልገን የሽግግር ሂደቱ በብዙ ውጣ ውረዶች የተሞላ በመሆኑ ነው። ትንሣኤ እውን የሆነው አያሌ ተግዳሮቶችን ድል ነሥቶ ነው። መንገዱ ግን አልጋ በአልጋ አልነበረም። ሕማማት የበዛበት ነበር።

ወደ ተራራ መውጣት ቁልቁለት እንደ መውረድ አይቀልም፤ ላብና ትንፋሽ ይጠይቃል። ወደ ትክክለኛ መዳረሻ የሚወስድን ትክክለኛ መንገድ መርጦ መጓዝን ይሻል፤ ከምንም በላይ በየምዕራፉ የሚገጥሙ እሾህና ጋሬጣዎችን፣ ቋጥኝና አውሬዎችን በሰላም ለመሻገር መተባበርና መደጋገፍ ከተጓዦች ይጠበቃል። የብልጽግና ጉዞ ሁሉም አሸናፊ የሚሆንበት የኅብረት ጉዞ እንጂ ጥቂቶች የሚያሸንፉበት የጥሎ ማለፍ ሩጫ አይደለም። ስለሆነም በትብብር ፋንታ መጓተትን፣ በመደጋገፍ ፋንታ መገፋፋትን ከመረጥን ጉዟችን አንድ ርምጃ ወደፊት መቶ ርምጃ ወደኋላ ስለሚሆን ካሰብንበት ግብ በፍጥነት እንደርሳለን ማለት ዘበት ነው። ትንሣኤው አይቀሬ ነው። ፈተናው ተሸናፊ ነው። የጸናም አሸናፊ ይሆናል።

በድጋሚ መልካም የትንሣኤ በዓል!
ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!

**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
**ሚያዚያ 7፣ 2015 ዓ.ም**

# እንኳን ለዒድ አል ፈጥር በዓል በሰላም አደረሳችሁ !

ሚያዝያ 2015 ዓ.ም

የዘንድሮውን ዒድ አልፈጥር ስናከብር ስለ ሰላም፣ ስለ ፍቅር፣ በአንድነት ስለመቆምና ስለወንድማማችነት እያሰብን መሆን አለበት። የእስልምና አባቶች የዒድ ሶላትን በጀመዓ ስለመስገድ ተገቢነት ሲያስረዱ፣ "የአላህ (ሱ.ወ) እጅ ሰብሰብ ባሉ ሰዎች መሐል ይገኛል" የሚለውን የእምነቱን አስተምህሮ ይጠቅሳሉ። በነጠላ ከመስገድ በላይ ሰብሰብ ብሎ አብሮ መስገድ ከፍ ያለ ምንዳ ከማስገኘቱ በተጨማሪ የወንድማማችነት ስሜት ያጠናክራል፤ ጠላት ሸይጧንንም መግቢያ ቀዳዳ ያሳጣል። በዚህም ምክንያት ሕዝበ ሙስሊሙ በስግደት ወቅት አቅሙ በፈቀደ ሰብሰብ ማለትን፣ በጋራ መስገድን ይመርጣል።

በአንድነትና በጋራ መቆም የሚጠቅመው ለጸሎት ብቻ አይደለም። እንደ ሀገር የሚገጥሙ ፈተናዎችን በድል ለመሻገርም አብሮ መቆም ያስፈልጋል። በተለይ በዚህ ወቅት እኛ ኢትዮጵያውያን ከምን ጊዜው በላይ አንድነትን አጠንክረን የምንቆምበት ጊዜ ላይ ነን። ሀገራችን ሽግግር ላይ ናት። ከጉስቁልና ወደ ብልጽግና ለመሻገር ከአያሌ ዕንቅፋቶች ጋር የሞት ሽረት ትግል እያደረገች ነው። ትግሉን በአሸናፊነት ለመወጣት እኛ ልጆችዋ በየትግል መስኩ የድክመቶቻችንን ቀዳዳ ለመድፈንና ከችግሮቻችን በላይ ለመሆን ተግባብተን በጋራ መቆይ ይኖርብናል። ወደ ከፍታው መውጣት የምንችለው በመጓተት ሳይሆን በመደጋገፍ፣ በንትርክ ሳይሆን በሰከነ መልኩ በመመካከር ነው።

በነቢዩ ዘመን ገናና የነበርን ሕዝቦች ዛሬ የኋላቀርነትን ካባ ስንለብስ ያሳዝናል። ለነቢዩ ዘመዶችና ተከታዮቻቸው መጠለያና መሸሸጊያ የሆንን ሕዝቦች ዛሬ የገዛ ወንድም እኅቶቻችንን ከየመንደሮቻችን ለማስወጣት እጃችን ሲነሣ ደስ አይልም፤ ስለ ሐቅና እውነተኛነታችን የተመሰከረልን ሕዝቦች አንደበታችን ለቅጥፈት መከፈቱ፤ ጆሯችን በፕሮፓጋንዳ ወሬ መፈታቱ ያስተዛዝባል። እንዲህ ያሉት እኩይ ጠባዮች አይጠቅሙንምና ዛሬውኑ አሽቀንጥረን እንጣላቸው፤ ወደ ከፍታችን የሚመልሱንን መልካም ባህርያትን ለመላበስም ከአሁኑ መትጋት እንጀምር።

የሮመዳን ወር የፈጣሪን ሰላም፣ እዝነትና በረከት ተጠይቆ የሚገኝበት ወር እንደሆነ የእምነቱ አስተምህሮ ያስረዳል። በዚህ የጾምና የበረከት ወር የተገኘውንም ስንቅ ሕዝበ ሙስሊሙ ከዒዱ እለት አንሥቶ እስከ ቀጣዩ የሮመዳን ወር ድረስ በዕለት ተዕለት ሕይወቱ ውስጥ እየተረጎመው ይቆያል ተብሎ ይታመናል። ሰላም፣ እዝነትና በረከት ደግሞ ለሰው ልጆች የሕይወት ጉዞ እጅግ አስፈላጊ ነገሮች ናቸው። ሰላም ኑሮን ያጣፍጣል፤ እዝነት የእርስ በርስ ግንኙነትን የሠመረ ያደርጋል፤ በረከት ደግሞ የኑሮን ጉድለት ይሞላል። ይኽ እንዲሆን ግን ከምንም በላይ ሦስቱን ጸጋዎችን መቀበል የሚያስችል ዝግጁ የሆነ ልብ ያስፈልጋል።

ሰላም ለሰላም የተዘጋጁ ብቻ ሳይሆን ለሰላም ዋጋ የሚከፍሉ ሰዎችን ይፈልጋል። ጦርነት እንኳን ለሰላም ሲባል የሚደረግና ለጠብ ጫሪነት ሲባል የሚደረግ በሚል በሁለት ይከፈላል። ለሰላም የሚደረግ ጦርነት ዓላማው የሰላም ዕንቅፋቶችን ማስወገድና ሰላም የሚበቅልበትን ምድር ማስተካከል ነው። ለጠብ ጫሪነት የሚደረግ ጦርነት ግን ዓላማው የበለጠ ጠብንና ግጭትን ማባባስ ነው። ሰላም የጦርነት ማብቃት ወይም አለመኖር ብቻ አይደለም። ሰላም ከጦርነት በመለስ በሆኑ ጉዳዮች ሊደፈርስ ይችላል፤ ሰላም የልቡና መስማማትን፣ ከሌሎች ጋር ተስማምቶ መኖርን እና ከፈጣሪ ጋር ታርቆ መኖርን ይጠይቃል። እነዚህ ሦስቱ ተሟልተው ባልተገኙበት ሁኔታ ሰላም አይጸናም። የሮመዳን ወርና የዒድ አልፈጥር በዓል የሚያስገኙልን እነዚህን ሦስቱን የሰላም አላባዎችን ነው። በዕለት ተእለት ሕይወታችን ትግልና ጥረታችን እነዚህን ሦስቱን ለማስገኘት የሚችል መሆኑን ርግጠኞች መሆን አለብን። ሰላም ከጦርነት በላይ ጀግና ይፈልጋል የሚባለው ያለ ምክንያት አይደለም። ጦርነት በሌላው ላይ በሚኖር የበላይነት ይደመደማል፤ ሰላም የሚሰፍነው ግን በራስ ላይ በሚኖር የበላይነት ነው።

እዝነት የሰው ልጆችን እርስ በርሳቸው ብቻ ሳይሆን ከተፈጥሮም ጋር ተግባብተው እንዲኖሩ የሚያደርጋቸው ነው። እዝነት ከራስ ቆርሶ ለሌላው መስጠትን የሚጠይቅ ነው። እዝነት ለሌሎች ማዘን፣ መራራትና መጨነቅ ነው። የሰው ልጆች የዓለምን ተድላና መከራ በልካቸው ተካፍለው፣ ጉድለትን ሞልተውና ድካምን አበርትተው መኖር የሚችሉት እዝነት በዓለም ሲሰፍን ብቻ ነው። እዝነት በሌለበት ስግብግብነት፣ ጭካኔና ራስ ወዳድነት ይሰፍናሉ። ሌብነት፣ ዋልጌነት፣ ጥላቻ፣ ግጭትና ጦርነት የእዝነት አለመኖር የሚያበቅላቸው አረሞች ናቸው።

በረከት የሁለቱ ትሩፋት ነው። ለሰላማውያን ሰዎች፣ አዝነት ገንዘባቸው ለሆኑ ሰዎች በረከት የእነርሱ ናት። በረከት ግን የሰዎችን ዝግጅት ትፈልጋለች። የሚሠሩ እጆችን፣ የሚታረቁ ልቦችን፣ የሚታገሉ ክንዶችን፣ ላብ የሚያፈስሱ ጉልበቶችን፣ የሚጨነቁ ጭንቅላቶችን፣ የሚፍጨረጨሩ እግሮችን፣ የሚፈለፍሉ ጣቶችን፣ የሚማትሩ ዓይኖችን፣ የሚያዳምጡ ጆሮዎችን ይፈልጋል።

ወጥተንና ወርደን መሬቱን ካላዘጋጀነው ዝናቡ ምን ይጠቅማል? መስኖ ጠልፈን ካላመረትንበት፣ ግድብ ገንብተን ኤሌክትሪክ ካላመነጨንበት የውኃ ማማነታችን ትርጉሙ ምኑ ላይ ነው? ፈትነን መርምረን ማዕድኑን ካላወጣነው ምድሩ ምን ይሠራል? በግብርናና በኢንዱስትሪ ምርት ሀገሩን ካላጥለቀለቅነው 120 ሚልዮን ሕዝብ መያዝ ምን ያተርፋል? ተወዳዳሪና ተመራጭ ምርት አምርተን ካልሸጥንበት በአፍሪካ ቀንድ መኖር ምን ይፈይዳል አልምተንና አውጥተን ለቱሪዝም ካላዋልነው ቅርስ፣ ታሪክ፣ ባህልና መልክአ ምድር ከዘፈን በቀር ለምን ይጠቅማል?

የፈጣሪ በረከት የሚሠሩ እጆችን ነው የምትኀበኛቸው። በዜሮ ላይ ተጨምራ አታውቅም። ከሰነፎች ጋር ተገኝታ አታውቅም። ከታካቾች ጋር ውላ አታውቅም። ፈጣሪ የሰማዩንም የገጸ ምድሩንም፣ የከርሰ ምድሩንም ሀብት አትረፍርፎልናል። በአራቱም የሀገሪቱ አቅጣጫዎች የሚፈስሱ ወንዞችን እንደ መቀነት አስታጥቆናል። አራቱንም የአየር ንብረቶች አጎናጽፎናል። ከርሰ ምድሩን በማዕድናት ሞልቶታል። ገጸ ምድሩን በዕጽዋትና በአትክልት ዓይነት አሽብርቆታል።

እንግዲህ የቀረ ነገር ቢኖር የእኛ ተግባብቶና ተስማምቶ መኖር ነው። ከትናንት ይልቅ ነገን፣ ካለፈው ይልቅ ዛሬን ተስፋ አድርጎ መነሣት ነው። የፈጣሪ በረከት እንዳንጠቀም የሚጋረጡብንን ፈተናዎች ለማሸነፍ ቆርጠን መነሣት አለብን። ፈተናዎቻችን የሚሸነፉት ዐቅማችንን ዐውቀን ራሳችንን መግዛት በቻልንበት ልክ ነው፤ ለዚህም ጾሙ ያቆናጸፈንን ዐቅምና ልምድ ልንጠቀምበት እንችላለን። ከፀሐይ መውጣት እስከ ፀሐይ መግባት መጾም ራስን የመግዛት ውጤት ነው፤ የሚያጓጉና የሚያባብሉ ነገሮችን ለዓላማ ሲሉ እምቢ የማለት ውጤት፤ ስሜትን የማሸነፍ ውጤት። ነገሮች ወደሚወስዱን ሳይሆን እኛ ልንሄድበት ወደምንፈልገው መንገድ ለመጓዝ የመወሰን ዐቅም ነው። ይኼንን ዐቅም ወደ ብልጽግና ለምናደርገው ሽግግር ትልቅ ግብዓት አድርገን ልንጠቀመው እንችላለን። እኛ ሀገር አለን። ሀገራችን ሰው እንዲኖራት እናድርግ። ኃላፊነት በማይወስዱ፣ የት እንዳሉ በማይታወቁ፣ እንጀራ ሲጋገር በማይኖሩ፣ እንጀራ ሲበላ ግን ሌላውን ሁሉ

ገፍተው እጃቸውን በሚዘረጉ፣ ከጤናችን ሳይሆን ከቁስላችን በሚያትርፉ፣ ከወዳጅ ይልቅ ጠላት ለመፍጠር በተሰለፉ ኃይሎች አንመራ። የእነርሱ ዓላማቸው ሰላምን፣ እዝነትንና በረከትን ከሀገራችን ማጥፋት ነውና።

ሀገራችንን የሚያጸኗት ሰላም፣ እዝነትና በረከት ናቸው። ሰላም ህልውናዋን ያጸናዋል። እዝነት ሕዝቦቿ ተከባብረው፣ ተፈቃቅደው፣ ተስማምተውና ተቻችለው እንዲኖሩ ያደርጋሉ። ለሰላም፣ ለእዝነትና ለበረከት ብቻ እጆቻችንን እንድንዘረጋና ልቦቻችንን እንድንከፍት አደራ እያልኩ በድጋሚ መልካም የዒድ አል ፈጥር በዓል እንዲሆን እመኛለሁ።

**ዒድ ሙባረክ!**

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
**ሚያዚያ 2015 ዓ.ም**

# ሐሳብን በሐሳብ ማሸነፍ ያቃታቸው አካላት የወንድማችንን የግርማ የሺጥላን ነፍስ ነጥቀዋል።

ሚያዝያ 19 , 2015

ሐሳብን በሐሳብ ማሸነፍ ያቃታቸው አካላት የወንድማችንን የግርማ የሺጥላን ነፍስ ነጥቀዋል። ልዩነትን በሠለጠነ መንገድ መፍታት ባህል በሆነበት ክፍለ ዘመን፣ በሐሳብ የተለየንን ሁሉ በጠመንጃ ለማሳመን መነሣት የጽንፈኝነት የመጨረሻው ጥግ ነው።

ተወልዶ ባደገበት አካባቢ ፣ ከእኛ የተለየ ሐሳብ ማሰብ አልነበረበትም ብለው የሚያምኑ ነውጠኛ ጽንፈኞች የፈጸሙት አስነዋሪና አሰቃቂ ተግባር፣ ጽንፈኝነትን በጊዜ ታግለን ካላስወገድነው ወደ መጨራረስ እንደሚወስደን ጉልሕ ማሳያ ነው።

**ነፍስህ በሰላም ትረፍ**
**ሚያዝያ 19 , 2015**

# እንኳን ለዐርበኞች ቀን (የድል በዓል) አደረሳችሁ

ሚያዚያ 27፣ 2015 ዓ.ም

ኢትዮጵያ የነጻነት ቀን ሳይሆን የድል ቀን ያላት ሀገር ነች። ነጻነታቸውን በምንም ነገር ለመቀየር ፈቃደኛ ያልሆኑት እናቶቻችን እና አባቶቻችን ለነጻነት ሲሉ ዋጋ ከፍለዋል።
እናቶቻችን እና አባቶቻችን ሕይወት ከፍለው ያቆዩልን ነጻነት ብቻቸውን አይቆምም። በሌሎች ነጻነቶች መደገፍ አለበት። ሀብት፣ ኅብረትና አገልጋይነት ሊደግፉት ይገባል። በኢኮኖሚው ዘርፍ በርትተን ሀገራዊ ሀብት ካልፈጠርንና ከርዳታ ካልተላቀቅን ነጻነት ብቻውን ሩቅ አይወስደንም። ኩሩ ድኻ ያደርገናል እንጂ። ኅብረት ፈጥረን መለያየትንና መከፋፈልን ካላሸነፍን ነጻነት ብቻዉን ኃይል አይሆነንም። በኅብረት ያገኘነው ነጻነት በመለያየት በፈቃዳችን እናጣዋለንና።

ሀገርንና ሕዝብን በቅንነትና በትጋትና በንጽሕና ለማገልገል ካልወሰንን ነጻነት ብቻውን ዕድገት አያመጣም። ሙስና፣ ኋላ ቀር አሠራርና ስንፍና ወደኋላ ይጎትቱናልና።
የድል ቀናችንን ስናከብር ከዐርበኞቻችን ድል በኋላ ያስመዘገብናቸውን ድሎች በመቁጠር መሆን አለበት። ድል የማይወልድ ድል ድል አይባልም።

ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!

**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
**ሚያዚያ 27፣ 2015 ዓ.ም**

# እንኳን ለታላቁ የዒድ አል አድሃ በዓል አደረሳችሁ !

ሰኔ 20 ቀን 2015 ዓ.ም

**ውድ ኢትዮጵያውያን ሙስሊም ወገኖቼ!**
**እንኳን ለታላቁ የዒድ አል አድሃ በዓል አደረሳችሁ!**

ዒድ አል አድሃ፣አረፋ ሙስሊሞች በታላቅ ክብር እና ፍቅር የሚያከብሩት፣ መሥዋዕትነትን የሚዘክር በዓል ነው። በዓሉ ከአምስቱ የእስልምና መሠረቶች መካከል አንዱ የሆነውና ማንኛውም ሙስሊም የገንዘብና የጉልበት ዐቅሙ እስከፈቀደ ድረስ በሕይወት ዘመኑ ቢያንስ አንዴ ወደ መካ በመጓዝ እንዲያከናውነው የሚጠበቅበት የሐጅ ሥርዓት የሚካሄድበትና የሚጠቃለልበት ታላቅ ምዕራፍ ነው። አረፋ፣ የሰው ልጅ ለፈጣሪው እና ለእምነቱ ሲል፣ መከራ ለመቀበል፣ ካስፈለገም ለመሠዋት ያለውን ፈቃደኛነት የምናስታውስበት፣ የምናከብርበት፣ የምንዘክርበት ልዩ ቀን ነው። አላህ (ሱብሀነሁ ወተአላ)፣ ነቢዩ ኢብራሂምን፣ ልጅህን መሥዋዕት አድርግልኝ ብሎ ሲያዛቸው፣ ነቢዩ ኢብራሂም፣ የአባት ኀዘን አላሸነፋቸውም፤ የልጅ ፍቅር አላጓጓቸውም፣ የቤታቸው መፍረስ አላሳሰባቸውም፤ የትኛውም ጉዳይ ከፈጣሪ ትእዛዝ አይበልጥምና፣ አንድዮ ልጃቸውን እስማኤልን መሥዋዕት ለማድረግ ተነሡ። ልጃቸው እስማኤልም ለመሠዋት ዝግጁ ነበር። ዒድ አል አድሃ የመሥዋዕት በዓል ነው የሚባለውም ለዚያ ነው።

ኢትዮጵያውያውያን፣ ከዚህ ጥንታዊ ኢስላማዊ ታሪክ ሁለት ታላላቅ ቁም ነገሮችን ተምረናል። ወርቅ በእሳት እንደሚፈተነው ሁሉ፣ ሰዎችም በአስቸጋሪ ጊዜያቸ ይፈተናሉ። እንደ እስማኤል ያለውን ነገር ሁሉ ሰጥቶ ለመሠዋት የቆረጠ ፈተናውን አልፎ፣ ትልቅ ታሪክ ጽፎ፣ እንደ ዒድ አል አድሃ ያለውን መታሰቢያ አትርፎ፣ ከዘመን ዘመን እየታወሰ ይኖራል። መሥዋዕትነትን ያልደፈረ፣ ከክብር ርቆ፣ ከታሪክ ተፋቆ እንደ አቧራ ይበናል።

ሁለተኛው ትምህርት፣ ታላቅ ግብ ላይ የሚደረሰው የሚወዱትን እንኳን ሳይቀር አሳልፎ በመስጠት መሆኑን ነው። ነቢዩ ኢብራሂም ለእስማኤል የማይለካ ፍቅር ነበራቸው።

ትልቁ ግባቸው ግን የፈጣሪያቸውን የአላህን ፈቃድ መፈጸም ነው። ይሄንን ግባቸውን ለማሳካት ሲሉ በምድር ላይ ትልቁ ሀብታቸው አድርገው የሚቆጥሩትን እስማኤልን ለመሠዋት ቆረጡ።
የመሥዋዕትነት በዓል በሚከበርበት በዚህ ልዩ ቀን፣ ኢትዮጵያውያን ‹እንኳን አደረሳችሁ› እንዲባባሉ ብቻ ሳይሆን፣ ሁለቱንም ቁም ነገሮች ልብ እንዲሉ አደራ እላለሁ። ለትልቅ ጉዳይ መፈተን፣ ለብርቱ ጉዳይ መሥዋዕት ለመሆን መዘጋጀት ታላላቅ ሰዎች የሚፈጽሙትና ታሪክ የሠሩበት ዕሴት ነው። ለታላቅ ግብ ሲባል የሚወዱትን ሳይቀር ለመሠዋት መቁረጥም ዓለምን የሚለውጥ ታሪክ የሚሠሩ ሁሉ የሚፈጽሙት ነው።

ሀገራችን፣ በተለያዩ ጊዜዎች የተለያዩ ችግሮች ገጥመዋት ያውቃሉ። የሚታለፉ የማይመስሉ ፈተናዎች በየወቅቱ ቢደቀኑባትም፣ ችግሮቹንና ፈተናዎቹን ተራ በተራ አልፋ፣ ወደ ፊት በመጓዝ ላይ ነች። መከራው በበዛ ጊዜም፣ ዜጎቿ የመጨረሻውን መሥዋዕትነት ለመክፈል ወደ ኋላ አላሉም። ንብረታቸውን ብቻ ሳይሆን፣ ሕይወታቸውን ለመስጠት አላቅማሙም። ኢትዮጵያን እዚህ ያደረሷት፣ ልጆቻቸውን ጭምር የከፈሉ ልጆቿ መሆናቸውን ሁሌም ሲዘከር የሚኖር ደማቅ ታሪካችን ነው። ኢትዮጵያውያን ራሳቸውንም መሥዋዕት ያደርጋሉ። የሚወዱትንም ነገር ለሀገራቸው ሲሉ ይሠዋሉ።

ዛሬ፣ በታላቁ የመሥዋዕትነት በዓል ላይ ቆመን፣ ሁለቱንም በክብር እናስታውሳለን።
በድጋሚ፣ እንኳን ለዒድ አል አድሃ/ አረፋ በዓል አደረሳችሁ!
ያለ መሥዋዕትነት የጸና ሀገር፣ የበለጸገ ሕዝብ በዓለም ላይ የለም። ዓለም የተራመደችበት የዕድገት ደረጃ ሁሉ የመሥዋዕትነት ውጤት ነው። አሁን የደረስንበት ደረጃ ላይ እንድንደርስ ብዙ ወገኖች ራሳቸውንም የሚወዱትንም ነገር መሥዋዕት አድርገዋል። ከመኖር ለሚበልጥ ግብ ሲሉ ሕይወትን ያህል ውድ ነገር ከፍለዋል።ሀገር ሀገር የምትሆነው ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ ዕውቀታቸውንና ከፍም ሲል ሕይወታቸውን ለመሥዋዕትነት የሚያቀርቡ ብዙ ልጆች ማፍራት ስትችል ነው። አንዱ ለሌላው መሞት፤ አንዱ ለሌላው መስጠት፤ አንዱ ለሌላው ማካፈል፤ አንዱ ለሌላው ሲል መሥዋዕትነትን መክፈል ነው የዓለምን ሥልጣኔ በጽኑ መሠረት ላይ ያቆመው።
ጥላቻ፣ ግጭት፣ መከፋፈልና መገፋፋት መሥዋዕትነት ባለበት ቦታ አይኖሩም። እነዚህ የስግብግብነት ውጤቶች ናቸው። እንዲህ ዓይነቱ ታላቅ በመሥዋዕትነት የተሞላ ፍቅር በሚከበርበት በዓል፣ የትም ይሁን የት፣ ጥላቻን መስበክ ሐራም ነው። መለያየትንና መገፋፋትን መስበክ ነውር ነው። ኢትዮጵያ ከምንም ነገር በላይ አሁን የምትፈልገው ፍቅርን እና የሕዝቦቿን አንድነት ነው።

አደምና ሐዋ ከገነት ከተባረሩ በኋላ በተገናኙበት የአረፋ ኮረብታ ከመላው ዓለም የተሰባሰቡ ሙስሊሞች የዒድ አል አድሃን በዓል በአንድነት ያከብራሉ። ምንጫቸው የተለያየ፣ ቀለማቸው የተለያየ፣ ዜግነታቸው የተለያየ፣ ማንነታቸው የተለያየ ቢሆንም፣ ሁሉም የሚያስቡት ሙስሊም መሆናቸውን ብቻ ነው። የተለያዩበትን ረስተው የተገናኙበትን፣ የተዛመዱበትን እያሰቡ፣ አንድ ይሆናሉ። እኛም ለምንለያይበትን ሳይሆን ለምንገናኝበት፣ ለምንገፋፋበት ሳይሆን ለምንሳሳብበት፣ ለምንሻኮትበት ሳይሆን ለምንተባበርበት ቅድሚያ ሰጥተን፣ አንድ ትልቅ ሕዝብ እንሁን። ከልዩ ልዩ ቦታ ብንመጣም፣ ልዩ ልዩ ማንነት ቢኖረንም፣ የተለያየ ቋንቋ ብንናገርም፣ የተለያየ ሃይማኖት ብንከተልም፣ ኢትዮጵያ ሲባል አንድ እንሁን።

ይህ መንደር ይህ ሠፈር የእኔ ነው ማለትን ትተው፣ ኢትዮጵያ የእኛ ናት የምንል ዜጎች እንድንሆን አደራ እላለሁ። ሁሉንም አካባቢ ለሁላችንም እንዲበቃ አድርገን ልናለማው፣ ልናበለጽገው እንችላለን። ከነካነው ያልነካነው ሀብታችን ይበልጣል፤ ከሠራነው ያልሠራነው ይበዛል።

ልጆቿ ተደማምጠው እና ተከባብረው፣ በሰላም እና በፍቅር የሚኖሩባትን ሀገር፣ በጋራ እንድንገነባ ሙስሊሞችን ብቻ ሳይሆን፣ የሁሉንም እምነት ተከታዮች በአክብሮት እጠይቃለሁ። ኢትዮጵያ ከምንም ነገር በላይ ዛሬ የምትፈልገው፣ መከባበርን እና መፋቀርን ነው። አንዳችን ሌላችንን እንድንሠዋ ሳይሆን፣ አንዳችን ለሌላችን ብለን እንድንሠዋ ነው። አንዳችን የሌላውን ሞት እንድንሞት ነው። ከዘመናት በፊት ነቢዩ ኢብራሂም ስለ እምነታቸው እንደተፈተኑት ሁሉ፣ እኛም ዛሬ ስለ ሀገራችን ስንል በፈተና ላይ ነን። ሰላምን ለማረጋገጥ፣ ከድህነት ለመውጣት፣ ኢኮኖሚያችንን ለማሳደግ፣ ሕዝባችንን ለማበልጸግ ትግል ላይ ነን። ተጋጭተን ሳይሆን ተነጋግረን፤ ተሻምተን ሳይሆን ተካፍለን፤ ተገፋፍተን ሳይሆን ተጋግዘን፤ ለሀገራችን ከሠራን፣ ፈተናችንን ያለምንም ጥርጥር በድል እንወጣዋለን። እኛ ተሠዉተን ኢትዮጵያን እናጸናለን። የነቢዩ ኢብራሂም ታሪክ ለትውልድ ሁሉ ተርፎ ሚሊዮኖችን ከመላው ዓለም ወደ አረፋ ተራራ እንደሚሰበው ሁሉ፣ የእኛም ታሪክ ለትውልድ ተርፎ ሚሊዮኖችን ከመላው ዓለም ወደ ኢትዮጵያ እንደሚሰባቸው አምናለሁ።

**ዒድ ሙባረክ !**

**መልካም የዒድ አል አድሃ በዓል !**

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘለዓለም ትኑር**

**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ !**

**ሰኔ 20 ቀን 2015 ዓ.ም**

# 500 ሚልዮን ችግኞች በአንድ ጀንበር

ሀምሌ 01 ቀን 2015 ዓ.ም

**የተከበራችሁ የሀገሬ ህዝቦች!**
**በአንድ ጀንበር ‘ነገን ዛሬ እንትከል’!**

አረንጓዴ ዐሻራ ለእኛ ብዙ ነገራችን ነው። የግብርና ምርታችንን ከፍ የሚያደርግና በምግብ ራሳችን እንድንችል የሚያበቃን ነው። ሁለት ሦስት ጊዜ አምርተን የምግብ ምርት በርካሽ እንዲገኝ የሚያስችል ነው። ወንዞች እስከ ወሰናቸው እንዲሞሉ አድርጎ የመስኖና የመጠጥ ውኃ እንዳይቋረጥ የሚያደርግ ነው። የደን ሽፋን አሳድጎ የአየር ንብረቱን የሚያስተካክል ነው። የሕዳሴ ግድባችንን ጤንነት የሚያስጠብቅ ነው።

<ኢትዮጵያ ለምለሚ> ብለን ያዜምንላትን ዜማ፣ እውነት እንዲሆን የሚያደርግ ነው። ድርቅና ረሃብ የሚባለውን ታሪክ ለማድረግ የሚያስችል ዐቅም ነው። በቁም እንስሳት ቁጥር ብቻ ሳይሆን፣ በቁም እንስሳት ምርት በዓለም እንድንታወቅ የሚያደርግ ነው። ፍራፍሬው ከጓሯችን፣ ቅመማ ቅመሙ ከደጃችን እንዲገኝ የሚያደርግ ነው። የተፈጥሮ ቱሪዝም ገቢያችን እንዲያድግ ዕድል የሚያሰፋ ነው። አረንጓዴ ዐሻራ ለእኛ ብዙ ነገራችን ነው።

አረንጓዴ ዐሻራ አሁን ያለው ትውልድ የትናንት ዕዳውን ይከፍልበታል። በደን ተሸፍና የኖረች ሀገር ዛሬ ራቁቷን እንድትሆን ያደረግናት እኛ ነን። ከተከልነው የቆረጥነው በልጧል። ከተከባከብነው ያነደድነው በዝቷል። ስለዚህም የትናንቱ ደን በታሪክ መዛግብት ላይ ብቻ የሚገኝ ሆኗል። ዐረንጓዴ ዐሻራ ይሄንን የቀደምቶቻችን ዕዳ እንድንከፍል ያደርጋል።

አረንጓዴ ዐሻራ የዛሬን ሕይወት ማስተካከያ ነው። የዘመናችን የሰው ልጆች ሕይወት አረንጓዴ ሕይወት ነው። ከተፈጥሮ የተስማማ፤ ለተፈጥሮ ዋጋ የሚሰጥ፤ በተፈጥሮ ውስጥ የመሸገ። ሰው ከተፈጥሮ በመጣላቱ አስከፊ ዋጋ እየከፈለ ነው። በቀላሉ የማይድኑ በሽታዎች፣ በየጊዜው የሚዛባ የአየር ንብረት፣ የውኃ አካላት መቀነስና ንጥፈት፣ የዋልታዎች በረዶ መቅለጥ፣ የሰውን ሥልጣኔ እየተገዳደሩት ይገኛሉ። በተለይ

አዳጊ ሀገሮች የበለጸጉ ሀገሮችን የሥልጣኔ ዕዳ እንዲሸከሙ እየተደረጉ ነው። የሚያዋጣን ዕድገታችን ከተፈጥሮ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ማድረግ ነው። ከኋላ የተነሣን ሀገሮች ይሄን ትምህርት ከቀደሙት ወስደናል። ሥልጣኔ ከተፈጥሮ ጋር ሲጣላ የሚያስከትለውን መከራ ቀምሰናል። ያውም ያለ ዕዳችን።

አረንጓዴ ዐሻራ ለነገ ትውልድ ወረት ነው። የምናስረክባት ሀገር በሁለንተናዋ ሉዓላዊነቷ የተጠበቀ መሆን አለበት። የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የዲፕሎማሲ፣ የማኅበራዊ ኑሮ፣ የተፈጥሮ ሉዓላዊነቶቿ ተሟልተው መከበር አለባቸው። ስድስት በር ያለው ቤት አንዱን ከፍቶ እስከዋለ ድረስ የሌሎቹ በሮች መዘጋት ደኅንነቱን አያስጠብቅለትም።
የሀገር ሉዓላዊነትም በሁለንተናዊ መስኮች እስካልተጠበቀ ድረስ በተከፈተው በር የሚገባው ብዙ ነው። ታዳሽ ኃይልን የኢነርጂ ዋና ምንጭ ለማድረግ ቆርጠን ለተነሣን ሕዝቦች፤ አረንጓዴ ዐሻራ እንደ ዐድዋ ዘመቻ የሉዓላዊነታችን ማስጠበቂያችን ነው።
ባለፉት አምስት ዓመታት 25 ቢልዮን ችግኞችን ተክለናል። መትከል ብቻ ሳይሆን በተቻለን መጠን ተንከባክበናል። ከባቢያችን እየተቀየረ ነው። የአፈር መሸርሸር እየቀነሰ ነው፤ አዕዋፍና አራዊት እየተመለሱ ነው፤ የዝናብ ሁኔታ እየተስተካከለ ነው። የወንዞቻችን ጤንነት እየተጠበቀ ነው። ከተሞቻችን በደን እየተሸፈኑ ነው። የፍራፍሬ ዛፎችን ተክሎ ማምረት ባህል እየሆነ ነው።

ዘንድሮም 6.5 ቢልዮን ችግኝ ለመትከል በየክልሉ፣ በየዞኑና በየወረዳው ክረምቱን ከምንሠራቸው ሥራዎች አንዱ አረንጓዴ ዐሻራችንን ማኖር ብለን እየሰራን ነው።
ተራሮች፣ የወንዝ ግራና ቀኞች፣ የመንገድ አካፋዮች፣ የቤቶቻችን ግቢዎች፣ የሠፈሮቻችን ባዶ ሥፍራዎች፣ የቤተ እምነቶች ቅጽረ ግቢዎች፣ የየትምህርት ቤቱ እና የየመሥሪያ ቤቱ ግቢዎች፣ ለግብርናና ለእንስሳት ግጦሽ የማይውሉ መሬቶች በደን መሸፈን አለባቸው።
ቦታ የሌለን ሰዎች በዕቃዎች ላይ መትከል አለብን። ሕንጻዎቻችን አረንጓዴ መልበስ አለባቸው። ኢትዮጵያ ዓመቱን ሙሉ አረንጓዴ እስክትለብስ ድረስ መትከላችንን እንቀጥላለን።

**ውድ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ!**
ሐምሌ 10 ቀን 2015 ዓ/ም በአንድ ጀንበር 500 ሚሊዮን ችግኞችን በመትከል ታሪክ እንድንሰራ ጥሪ አቀርባለሁ!

ሐምሌ 10 ቀን ኢትዮጵያውያን የራሳችንን ሪከርድ እንሰብራለን።ከዚህ በፊት ከ350 ሚልዮን በላይ ዛፎች በአንድ ጀንበር ተክለን ዓለምን ጉድ አስብለናል።

ዘንድሮ 500 ሚሊዮን ችግኞችን በአንድ ጀንበር በመትከል የራሳችንን ሪከርድ እናሻሽላለን፤ታሪክ ሰሪ ትውልድነታችንን በተግባር ለዓለም እንገልጣለን።

ከተደመርን በሁሉም መስኮች ኢትዮጵያዊያን ያሰብነውን ማሳካት እንደምንችል አምናለሁ። ሐምሌ 10 ቀን 2015 ዓ/ም ጀንበር ወጥታ እስክትገባ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ቤቱ አይውልም። በዕቅፍ ካለ ሕጻን፣ በድካም ካለ አረጋዊ፣ በአልጋ ከሚገኝ ታማሚ በስተቀር ቤቱ ማንም አይውልም። ምክንያቱም ይህ የፖለቲካ ጉዳይ አይደለም፤ የፓርቲ ፕሮግራምም አይደለም፤ የመንግሥት ጉዳይም አይደለም። ይህ የኢትዮጵያ ጉዳይ ነው። የምትለብሰው ኢትዮጵያ ናት። ትርፉም ከእኛ አልፎ ለዓለም የሚተርፍ ነው። ስለዚህም የእምነትና የባህል፣ የፖለቲካ ፓርቲና አስተሳሰብ፣ እድሜና ጾታ፣ የትምህርትና የኑሮ ደረጃ ሳይለየን ሐምሌ 10 ቀን ከጀንበር ቀድመን እንውጣ። ከጀንበር በኋላ እንመለሳን። ኢትዮጵያን አረንጓዴ እናለብሳለን።
የአረንጓዴ ዐሻራ ትሩፋቱ ለዓለም ሁሉ ነው።

በኢትዮጵያ የምትኖሩ የውጭ ሀገር ዜጎች፣ ኤምባሲዎች፣ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ሠራተኞች፣ በኢትዮጵያ በኩል የምታልፉ መንገደኞች፣ ለተለያየ ጉዳይ በአጋጣሚ ወደ ኢትዮጵያ የመጣችሁ የውጭ ሀገር ሰዎች - ሐምሌ 10 ቀን አረንጓዴ ዐሻራችሁን አኑሩ። ዓለምን በኢትዮጵያ በኩል አልብሱ፤ኢትዮጵያ ታሪክ ስትሰራ የታሪኩ አካል ሁኑ።

**500 ሚልዮን ችግኝ በአንድ ጀንበር እንተክላለን -**
**አረንጓዴ ዐሻራችንን እናኖራለን!**
**ሐምሌ 10 ቀን 2015 ዓ.ም በአንድ ጀንበር ዳግም ታሪክ እንስራ!**

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘለዓለም ትኑር**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
**ሀምሌ 01 ቀን 2015 ዓ.ም**

# ዓላማችን ሪከርዳችንን መስበር ነው!

ሀምሌ 10 ቀን 2015 ዓ.ም

የአረንጓዴ ዐሻራ ጉዳይ ኢትዮጵያን የመጠበቅ፣ የማክበርና የማበልጸግ ጉዳይ ነው። ታሪክ የመቀየር ጉዳይ ነው። ለትውልድ የመትረፍ ጉዳይ ነው።

ከማኅበራዊ እና ሃይማኖታዊ ተግባራት ነጻ የሆነ ቀን የመረጥነው ይህ ቀን ሊያልፈው የሚገባ ኢትዮጵያዊ ስለሌለ ነው። ሰኞን ስንመርጥ የሥራ መጀመሪያችንን ተፈጥሮን በመታደግ እንድንጀምር ነው።

ፉክክራችን ከራሳችን ጋር ነው። ክልሎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎች እና መንደሮች ከአምናው የበለጠ በመትከል የየራሳቸውን ሪከርድ እንደሚሰብሩ እናምናለን። እያንዳንዳችንም የየራሳችንን ሪከርድ መስበር አለብን።

ችግር የራሱን ሪከርድ እንዲሰብር ልንፈቅድለት አይገባም። ችግር የራሱን ሪከርድ ከሰበረ ተሸንፈናል ማለት ነው። ችግርን የምናሸንፈው መጀመሪያ የራሳችንን ፣ ቀጥሎ የአካባቢያችንን፤ በመጨረሻም የዓለምን ሪከርድ ስንሰብር ነው።

እኔ ነገ በተደጋጋሚ ለመትከል ተዘጋጅቻለሁ። እናንተስ?
ነገ ሐምሌ 10 ቀን 2015 የራሳችሁን ሪከርድ በብዙ መጠን እስክትሰባብሩ ድረስ ዛፎችን ለመትከል ተዘጋጁ።

# ታሪክ ሠርታችኋል

ሀምሌ 10 ቀን 2015 ዓ.ም

500 ሚልዮን ዛፎችን በመትከል የራሳችንን ሪከርድ እንድንሰብር የቀረበውን ጥሪ ተቀብላችሁ የወጣችሁ ሁሉ ምስጋና ይገባችኋል። አረንጓዴ ታሪክ ሠርታችኋል። አረንጓዴ ታሪክ ጽፋችኋል።

የተዛባ አየር፣ የተራቆተ ምድር ለትውልድ አናወርስም ብላችሁ፤ ጎሕ ሳይቀድ ወደ ተራሮችና ሸለቆዎች፣ ወደ ሜዳዎችና ሸንተረሮች ተሠማርታችሁ 566 ሚልዮን ዛፎች ተክላችኋል። ሪከርዳችሁን ሰብራችኋል።

በሁሉም ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች ዛፎች ተተክለዋል። ከ9 ሺ በላይ የተለዩ ቦታዎች ተዘጋጅተው ነበር። ከ3600 በላይ የሚዲያ ባለሞያዎች በመላ ሀገሪቱ ተሠማርተው ነበር። የቴሌና የግብርና ባለሞያዎች የመረጃ አያያዙ ዘመናዊ እንዲሆን ሠርተዋል። የአዲስ አበባ ታክሲዎች ነጻ ትራንስፖርት ለችግኝ ተካዮች ተሰጥተዋል። ሕጻናት፣ እናቶች፣ አባቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ በነቂስ ወጥተው ተክለዋል። በኢትዮጵያውያን አረንጓዴ ታሪክ ተሠርቷል።

ኢትዮጵያውያን ከተባበርን የማንሰብረው ሪከርድ የለም።

**ሐምሌ 9 ቀን 2015 ዓ.ም**

# እንኳን ለ2016 አዲስ ዓመት አደረሳችሁ

ጳጉሜን 6 ቀን 2015 ዓ.ም

በፈጣሪ ቸርነት 2015ን አልፈን ወደ አዲሱ ዘመን ደርሰናል። ኢትዮጵያ በውጣ ውረድ ውስጥ እያሸነፈች ተጉዛለች።

ጽኑ መርሕ፣ ብርቱ ሕዝብና የማይሸነፍ አምላክ ስላለን እዚህ ደርሰናል። ብዙ ነገሮችን አሳክተናል፤ አያሌ ፈተናዎችን በድል ተወጥተናል፤ እልፍ መሰናክሎች ቢደረደሩም ጠንካራ መሰረት ሆነውን አልፈዋል።

የተሳኩልን ሁሉ የኅብረ ብሔራዊ አንድነታችን ውጤቶች ናቸው። የተፈተንባቸው ደግሞ በመለያየት የተነሣ የመጡ ናቸው። በቀጣዩ ዓመት ፈተናዎቻችን እጅግ ቀንሰው፤ ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችንን ከአልማዝ ጠንክሮ፤ የኢትዮጵያን ሰላምና ደኅንነት በጽኑ መሠረት ላይ እናጸናዋለን።

ልማትና ብልጽግናዋን ወደሚመጥናት ደረጃ እናሻግረዋለን።
አዲሱ ዓመት የኢትዮጵያ ብልጽግና ዓመት እንዲሆን እመኛለሁ።
ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!

**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
**ጳጉሜን 6 ቀን 2015 ዓ.ም**

# እንኳን ለመውሊድ በዓል አደረሳችሁ

መስከረም 15 ቀን 2016 ዓ.ም

## ውድ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች!

እንኳን ለየነቢዩ መሐመድ የልደት በዓል በሰላም አደረሳችሁ! መውሊደል ነቢ በሚከበርበት እለት፣ ሙስሊሞች መስጂድ ሄደው፣ በጋራ፣ ጸሎት ያድርጋሉ። የታላቁን ነቢይ ስራዎች፣ አስተምህሮቶች ይዘክራሉ። ነቢዩ በህይወት ሳሉ የነበራቸውን፣ ትህትና፣ ደግነት፣ ይቅር ባይነት ያስታውሳሉ። ከመስጂድ ከወጡም በኋላ፣ ያላቸውን ከሌላቸው ጋር በመካፈል፣ ለወገኖቻቸው ሁሉ ትሁት በመሆን፣ የበደላቸውን ይቅር በማለት፣ እንደ ዲናቸው መሪ፣ ትህትናን፣ ደግነትን እና ይቅር ባይነትን በተግባር ይፈጽማሉ።

የየትኛውም እምነት ተከታዮች የሆንን እኛ ኢትዮጵያውያን፣ በዚህ ታላቅ በዓል ከሙስሊም ወገኖቻችን ጋር ውድ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች!
እንኳን ለየነቢዩ መሐመድ የልደት በዓል በሰላም አደረሳችሁ!
አንድ ሆነን፣ ትህትናን፣ ደግነትን እና ይቅር ባይነትን ገንዘባችን በማድረግ፣ መንፈሳዊ ህይወታችንን እናበለጽጋለን። አንድ ሆነን፣ በፍቅር እና በሰላም እናድጋለን። ትህትና፣ ደግነት እና ይቅር ባይነት የማይፈቱት ችግር የለም። የማያሻግሩት ወንዝ የለም።

ውድ የእስልምና እምነት ተከታዮች እና መላ ኢትዮጵያውያን!

ይህን ታላቁን መውሊደል ነቢ ስናከብር ለሌሎች እምነት ተከታዮች፣ ወንዱ ለሴቱ፣ ትንሹ ለትልቁ፣ በሀገር ውስጥ ያለው ኢትዮጵያዊ፣ የትም ላለው ኢትዮጵያዊ፣ ሁሉም ለሁሉም ትሁት ይሁን! ደግ ይሁን! በደልም ሲኖር፣ ይቅር ባይነት ይኑር!
ትህትና፣ ደግነት እና ይቅር ባይነት ብዙዎቹን ችግሮቻችንን ይፈቱልናል። ብዙ ይቅርታዎች ብዙ ርቀት ወደፊት ያራምዱናል።

በየቦታው የሚነሱ አንዳንድ ችግሮችን እያየ፣ ሁሉ ነገር ጨለማ የሚመስለው ወገን አለ። ከየትኛውም ጨለማ በኋላ ግን ብርሀን አለ! ከየትኛውም ቋጥኝ እና ተራራ ባሻገር መንገድ አለ። ወንዙ፣ መሻገሪያ አለው፣ አቀበቱ ቁልቁለት አለው። ትሁት ብንሆን፣ ብርሀን ይታየናል። ደግ ብንሆን፣ መንገዱን እናገኘዋለን። ይቅር ባይ ስንሆን፣ መሻገሪያው ይታየናል።

ነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) መልካም ነገሮችን ለማስተዋወቅ፣ መጥፎ ተግባራትን ሊቃወሙ የተሰጡ ናቸው። የሳቸውን አስተምሮ የሚከተል ሁሉ በዚህ ደረጃ ለመገኘት የሚደክም ነው። በጎ ነገሮች ተጓድለው ሲገኙ ወገኖችን ለማስተማርና ለመመለስ የሚደክም ነው።
በዓሉን ስናከብር የነቢዩ መሐመድን በረከቶች በማስተዋልና የትህትና መንገዶችን በማሰብ ማሳለፍ ይገባል።
በድጋሚ መልካም መውሊደል ነቢ!

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘለዓለም ትኑር**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
**መስከረም 15 ቀን 2016 ዓ.ም**

# እንኳን ለብርሃነ መስቀሉ አደረሳችሁ!

መስከረም 16 ቀን 2016 ዓ.ም

ደመራ፣ መደመር፣ ደመረ፣ አከማቸ ማለት ነው። ደመራ የመለወጥ ምልክትነትም ነው። ለወንጀለኞች ስቅላት ይውል የነበረ መስቀል ዋጋና ምልክቱ የተለወጠበት ነው። ደመራ ብዙ ሰዎችን ሰብስቦ በኅብረት የሚያቆም ነው። ደመራ ባነሰው ላይ መጨመር ነው። ደመራ የተበተነውን መሰብሰብ ነው። የተዘረዘረ ነገርን የሚደምርና የሚያገናኝ ነው። ጸጋዬ ገ/መድኅን በግጥሙ...

ነጋ አዲስ ዘመን ችቦ፤<br>
ምድር ሕይወት አፈለቀች፤<br>
የምሥራች አዝርዕቷን፤ አዲስ ቡቃያ ወለደች፤<br>
የአደይ አበባን ለገሰች፣<br>
ለአዲስ ዘመን አዲስ ብርሃን፤ አዲስ መስከረም ገበየች፣

...እንዳለው የአዲስ ዘመን ችቦ በአዲስ የፈካ ዘመን የሚጀመርበት ነው። የሰዎችም አዲስ ተስፋ አዲስ ጅምር የሚታይበት ነው። የመስቀል ወፍ የምትታሰርበት፤ አዝዕርት የሚበቅልበትም ነው።

ደመራ ለበዓለ መስቀል ዋዜማ እንጨቶች የሚደመሩበት ነው። እንጨቶች ተሰብስበው ችቦ፤ ችቦዎች ተሰብስበው ደመራ የሚሆኑበት ነው። የችቦ እንጨቶችና ጭራሮዎች ምን ቢበዙ ወደ አንድ ካልመጡ ችቦ አይሆኑም። እንጨቶቹን የሚያስተሳሥራቸው የማሠሪያ ልጥ አለ። ችቦዎቹም በጋራ ተደጋግፈው ካልቆሙ ደመራ አይሆኑም። ችቦዎቹን አንድ አድርጎ የሚያቆማቸው የመሐሉ እንጨት አለ። ይህ እንጨት ጠንካራና በዙሪያው የተሰባሰቡትን ችቦዎች መሸከም የሚችል ነው። ይህ መሰሶ ኢትዮጵያን የሚወክልም ነው።

የችቦው ሁሉም ጭራሮዎች አንድ ዓይነት አይደሉም። ከአንድ ቦታም አይለቀሙም። ሁሉም ችቦዎችም ተመሳሳይ አይደሉም፤ ከአንድ ቤት አይመጡም። ሁሉም እንጨቶች

በየራሳቸው ይቆማሉ፤ ግን ደግሞ ብርታትና ጥንካሬ፣ ዐቅምና ጉልበት እንዲኖራቸው ችቦ ሆነው ይደመራሉ። እንጨቶቹን እንደሚያስተሰሥረው ልጥ፣ ኢትዮጵያውያንን የሚያስተሣሥሩ ልዩ ልዩ ማንነቶች አሉ። ደመራ በመሰባሰብ የሀገራችንን ከፍታ እውን ለማድረግ የምንሰባሰብበት ተምሳሌታችን ነው።

ኢትዮጵያ እንደ ችቦ እንጨቶች ብዙ ባህሎች፣ እምነቶች፣ ሀብቶች፣ ዕሴቶች፣ አመለካከቶች፣ ታሪኮች አሏት። ሁላችንም የግድ አንድ ዓይነት ማሰብ አይጠበቅብንም፤ የግድ ከአንድ ባህል፣ ከአንድ ቋንቋና ከአንድ ማንነት መገኘት አይኖርብንም። እነዚህን ሁሉ ጸጋዎች ከደመርናቸው፣ መጀመሪያ እንደ ችቦው አካባቢያዊ ዐቅም ይሆኑናል። ቀጥሎ ደግሞ እንደ ደመራው አስተሳሥረን በአንድ ዓምድ ላይ ካቆምናቸው ትልቅ ሀገር እንገነባለን። ይህ ችቦዎቹን አንድ አድርጎ የሚያቆመው የመሐል እንጨት አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማኅበረሰብ የምንፈጥርበት የፌዴራል ሥርዓት ነው። ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችን ነው። ኢትዮጵያዊነታችን ነው። በዚህ የኢትዮጵያዊነትና የኅብረ ብሔራዊ አንድነት ደመራ፣ ግርማዋ የሚያስፈራ፣ የበለጸገች፣ ጠንካራ፣ ታላቅ የጋራ ሀገር መገንባት እንችላለን። የዚህ ሁሉ ቀመሩ ግን - እንደ ደመራው፣ መደመር ነው። ችቦውን በየግልና በየአካባቢያችን ልንሠራው እንችላለን። ደመራውን ግን በጋራ ካልሆነ አንደምረውም። የመጣንበት መንገድ ለየቅል ሊሆን ይችላል። እምነታችን፣ ምርጫችንና ምኞታችንም የየብቻችን ችቦ ሊሆን ይችላል። ሀገራችን ግን የጋራችን ደመራ ናት። ያለሁላችን አትኖርም። ምን ብንጓጓ ደመራውን ቆኩለን ለብቻችን አንለኩሰውም። የግድ ሌላውን እንጠብቃለን። እንደ ሀገር እንጂ እንደ ንዑስ አከባቢ፣ ወይም እንደ ሠፈር እኔና የኔ ብቻ ማለት አንችልም። ደመራው ለሁላችን በሚሆን ሥርዓት የሚመራ የሁላችንም ሀገር መስታወት ነው።

ደመራው በኔ ችቦ በኩል ቀድሞ ይለኮስልኝ አንልም። ደመራው ሲለኮስም ‹የኔ ችቦ ትቀጣጠል› ይሆን ብለን አንሠጋም። ከየትም ይጀመር ከየት፣ሙቀትና ብርሃኑ ለሁሉም እንጨቶችና ችቦዎች በሂደት ይዳረሳል። የኢትዮጵያ ሠናይ እሳት የሆነው የኢትዮጵያ ዕድገት፣ የትም መንደድ ቢጀምር፣ በጊዜ ሂደት ለሁላችን ይደርሳል። አንዱ እንጨት ለሌላው፣ አንዱ ችቦ ሌላው ብርሃን እንዲሆን በማጋራቱ ከእርሱ የሚጎድልበት ነገር የለም። ነገር ግን የሚጨምረው ዐቅም አለ። ሁሉም እየተለኮሱ በሄዱ ቁጥር፣ የብርሃኑ ዐቅም እየጨመረ ይሄዳል።

እኛም ለሌላው ወገናችን ባካፈልን ቁጥር የሚጎድልብን ነገር የለም። የኢትዮጵያ ዐቅም ግን እየጨመረ፣ እየጠነከረ ይሄዳል። ትኩረታችን የገዛናት ወይም ሠርተን ያመጣናት ችቢችን ሳትሆን ትልቁ ደመራ ነው። የበዓሉ አመስጥሮ ያለውም ከዚሁ ነው።

ችቦውን ልንገዛውና ልንሸጠው እንችላለን። ደመራው ግን ልክ እንደ ኢትዮጵያ ነው። አይሸጥም አይለወጥም። ሁሉም በግል ይገዩው ልሂድ አይልም። እዚያው በጋራ ደምረን፣ በጋራ ልቦናችን ይዘነው የምንሄደው - የወል እውነታችን ነው። የኛነታችን ካስማችንም ጭምር ነው።

ደመራ እውነተኛው መስቀል የተገኘበት ጠቋሚ ኮምፓስ ነው። ለሀገራችን እድገትና ብልጽግና በአንድነት የመቆም ምሳሌያችን ነው። ደመራ አቅጣጫ ነው። እውነተኛው መስቀል የተለየበት። ኢትዮጵያም ልጆቿ የሚቆሙበትና የሚሄዱበት እውነተኛ አቅጣጫ ለተስፋዋ ብርሃን፣ ለጥንካሬዋም ፈለግ ይሆናታል። ልክ መስቀሉን ፈልጎ ማግኘት እጅግ ከባድ ሆኖ ጊዜ እንደወሰደው ብልጽግናን መሻትም እንዲሁ ብዙ ድካምና ጥረት ይፈልጋል። መስቀሉን ማግኘት የብዙዎችን መተባበርና ምክር እንደመፈለጉ በሀገራችን ብልጽግናን ማረጋገጥም በዚሁ ልክ መተባበርና አብሮነትን መፈለጉ ከልቦናችን ይቀመጥ። የዘንድሮውን የደመራ በዓል እነዚህን ታላላቅ ዕሳቤዎች እያሰላሰልን እንደምናከብረው ተስፋ አደርጋለሁ።

**መልካም የደመራና የመስቀል በዓል ለሁላችን ይሁን።**

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!**

**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ**

**መስከረም 16 ቀን 2016 ዓ.ም**

# ክፍል ሁለት፤
# የኦሮምኛ መልዕክቶች

# Boqochuu Doktara kabajaa Artisti Alii Birraan Gadda keessookoo ibsaa

Boqochuu Doktara kabajaa Artisti Alii Birraan Gadda keessookoo ibsaa; - Maatii, Hiriyootaafi dinqisiifattootasaa guutuu Adunyaarra jiraniifis jajjabinan hawwa.

**IBSAA HIN DHAAMNE**

Alii Birraa sajoo guddaa, Qabeenya Biyyaafi Addunyaati. Artistii dhugaa isa Afaanota torbaan Jaarraa walakkaa oliif mirga namoomaafi hacuucamtootaaf sagaleeti.

Aartistii, Aartiin kan Addunyaa ta'uusaa sirriitti hubatee, Aartiin sabaafi Afaaniin, qabeenyaafi dhabeenyaan akka nama hin qoodne qal-beeffatee, daddarba jiruu, Sadoofi Qananii dhala namaa waliin qooddateedha.

Hambaa Aartiifi wabii cunqurfamtootaaf sagaleeti, Doktarri Kabajaa Dachaafi Aartist Alii Birraa. Sirbi isaa Sirna Abbaan Lafaa qonnaan bulaa ittiin miidhee mormuun diddaan bara sanaa akka finiinuufi jijjirama sirnaa warra fedhaniif hirkoo ta'ee, hardhummaa Itiyoophiyaa hawwuu bira darbee, Wallee isaatiin suuraa guyyaa boruu kaasuun nu agarsiiseera.

Sirboonni isaa warra hardha dhaggeeffatamanii boruu nuffaman osoo hin taane, Walleelee ce'oo warra kaleessaas turanii, hardhas jiraatanii, boruuf ammoo galaa ta'aniitu baay'atu.

Alii Birraan mootii muuziqaa ta'uu isaatiif ragaan, Qinyiitiiwwan muuziqaa hundarratti sirbuu isaati. Kanaanis Aartistii gameessaa

Afrikaa ta'uun badhaafameera. Isaaf muuziqaan salphaadha. Makkoofi rakkoo sabaa tuulame taa'ee daqiqaa 5 keessaatti akka daawwitiitti namatti muldhisa.

Walleewwan isaa jechoota halluu miidhagaan faayaman, daran waalta'oofi jechoota sonaafi simboo hawaasaan kan guutamanidha. Yeedaloon isaammoo gurra namaa hin quuqani, suuta jedhanii akka Dhiigaa qaama namaa keessa yaa'aanii nama waldhaanu. Sirboonni isaa warreen jaalala labsan ammoo qaamaafi qalbii namaaf sugu, xiinsammuu jaalalaan qabameefis sifa ta'u.

Kana qofaas miti; inni Aartii biyyaafi Afrikaaf wabiidha. Umrii isaa raage kanatti Weellistoota dargaggoota Itiyoophiyaa waliin sirbuun labata dhufuuf baallii darseera. Muuxannoo isaa jaarraa walakkaa oliif tuulames dhalootaaf galaaseera.

Itiyoophiyaafi Afrikaan Aartistoota akkanaa barbaaddi. Warra Aartiif dhalatanii Aartiif jiraatan. Warra Afaan isaan hin daangeessine; warra jijjiiramni sirnaafi siyaasaa isaan hin danqine. Warra dhugaaf sirbaniifi dhugaadhaaf jiraatan.

Aliin waanniifi mata dureen inni irratti hin sirbine hin jiru. Sirboonni isaa hedduun utubaa qabsoo, uummataati. Warri kaan ammoo jaalala leellisu, Gariin ammoo barnoota jabeessu, kaanis Ispoortiin fayyaaf jechuun sochii qaamaa jajjabeessu. Kanneen hafanimmoo duudhaa, Sansakaafi qabeenya guddaa biyyaa leellisu, uumaa dinqisiifatu.

Hundaa'ol ammoo sirbi Alii Birraa "Haati teenya tokkoo maaltu addaan nu baase" jedhu, Ulfinaafi guddina Alii Birraaf ragaa baha. Aliin wallee isaa kana keessatti namni nama hin caalu

jedha. Hundi keenya haadha tokko irraa dhalanne. Dhalli namaa Addunyaa kana guutee dambali'e kun haadha tokkorraa dhalate. Tiruu tokkos boraafate. Garuummoo gara garummaa yaadaafi siyaasaatiin addaan faca'e. Gara garummaan yeroofi sirnaan uumame kun ammoo haadha tokkorraa dhalachuu Uummata Addunyaa kana jijjiruu hin danda'u. kanaaf "haati teenya tokko" maaltu addaan nu baase kan inni jedhe.

kanaaf Alii Birraa "Ibsaa hin dhaamnedha." Isatu nurraa boqote malee Hojiin inni nuuf gumaache bara baraan jiraatu.

Boollasaa Daadhiin haa guutu, lubbuun isaammoo Jennata keessatti haa qananiitu.

# Akkuma Kaleessaa Har'as Qormaatota Injifinnoon Ceenee, Harka Keenya Galataaf ni Bal'ifna

**Kabajamtoota Ummattoota Biyya Keenyaa Hundaaf**

Maqaan Itoophiyaa jedhu maqaa kabajaa rakkoodhaaf harka osoo hin kennin, qormaataaf osoo hin jilbiiffannee fi gufuuwwan cehuudhaan injifannoo ittii gonfatanidha. Seenaa ishee keessatti biyyi keenya yeroon isheen qormaata malee dabarsite muraasa. Tattaaffii cimina ijoollee isheetiifi gargaarsa waaqayyootiin, rakkoowwan mudatan heddu damdamattee as geessee jirti.

Har'as cimina biyya keenyaa qoruuf rakkoo baay'een yoo nu marsanis, qaamoleen adda addaa halkaniifi guyyaa lubbuu keenya rakkoo keessa galchuuf walitti yoo dhufanis, gara fuulduratti deemuu keenya hin dhaabnu. Nuti yoomiyyuu, warri cimina eenyummmaa keenyaatiifi gargaarsa Waaqayyootti amannu, bacaqii gannaa keessa darbinee, ifa birraa abdachiisutu nutti mul'ata, dukkanaan gamatti ifa boonsaan akka jiru ni beekna.

Dukkana kaleessaa akkuma darbine, rakkoo har'a nu quunname sababni cehuu dadhabnuuf akka hin jiraanne amanaa, har'as ciminaa fi jabina uumaaan nuu keenneef galata galchuuf duubatti hin jennu.

Galateeffachuun humna guddaa bara darbe injifannoon, yeroo keessa jirru carradhaan, yeroo dhufu immoo abdiidhaan akka eegnu kan nu taasisuudha. Gama biraatiin galata waakkachuun, xiin-sammuu mo'atamuu fi carraa dhabuu uuma. Ofii keenyaa fi namoota biroo ilaalcha gaariifi jaalalaan akka hin ilaalle nu

taasisa. Qaamni dhuunfaas ta'ee uummanni waan argatetti hin quufneefi hin galateeffanne, hir'uu malee kennaan addaa inni qabu itti hin mul'atu. Rakkoo irra gahe malee, carraan kennameef guddaa ta'ee itti hin mul'atu. Rakkoo gara fuulduraa dhufu malee, gammachuun fuuldura isaa jiru sammuu isaa keessatti hin katabamu.

Namni galata galchu, rakkoo hamaa keessatti injifannoo fi carraa isaa nama ilaaluu danda'uudha. Bubbee fi danbalii caala jabeenya doonii ilaala. Baay'ina qormaataa fi rakkoo caala, hundumaa tokkummmaa fi gargaarsa uumaatiin mo'achuun akka danda'amu yaada.

Qaroomina Aksuumiifi bara durii, iccitii ogummaa ijaarsaa Laalibalaa fi naannawa sanatti argaman, Gimbii Hararii fi naannawa isheetti kaka'umsaa fi guddina magaalotaa biqilan, Gibee fi naannawa laga Gibeetti  qaroomina mootummaa giddugaleessaa hundeessuuf yaalii taasifamemeefi daldala qonnaan walitti hidhuuf yaalame, tattaffiiwwan sirna Gadaatiin dimokirasii ijaaruu, Walaayittaa, Halabaa, Haadiyyaa, Daawuroo fi naannawa Kafaatti bulchiisa waliitti dhufeenya daldalaa fi dippiloomaasii giddu galeessa bahaa hanga Awurooppaatti uuman, Gondaritti tattaaffii bulchiinsa mootummaa giddugaleessaa ijaaruu, Affaarii fi Somaaleetti sirna bulchiinsa odeeffannoo fi giddugaleessummaa bu'uura godhate, Gambeellaatti qaroomina dubartootaaf kabaja addaa kennuu, Benishaangul Gumuzitti muuziqaa fi fayyadama meeshaa muuziqaa akkasumas iddoowwan adda addatti qaroomina mul'achaa turan duubatti deebinee ilaaluudhaan qabeenya keenya itti boonuu qabnuudha.  Warroota kaleessaa itti boonnu kan nuuf kenne Waaqayyo waan ta'eef kanaaf isa galateeffanna. Walqoqqoodinsa bara 'Zamana Masaafinti' biyya keessa turee fi dhiibbaawwan alaa gama koloneeffataan dhufan, biyyi keenya humna hin mul'annneen damdamatte. Seenaan ishee

fi eenyuumman ishee osoo hin badin, bara dheeraaf turuun ishee waan nama dinqisiisuu danda'uudha. Yeroo Itoophiyaa ammayyaa adeemsa bittinnahuu irraa gara walitti dhufuutti deemte kanattis, waraanni fi walitti bu'iinsi, aggaammii fi shirri siyaasaa heddumminaan uumamaa jiru. Ijaarsi mootummaa biyyaa seeraan osoo hin xumuramiin, waggota 50 darban keessatti jijjiiramni saffisaa ta'ee fi walitti fufiinsa qabu biyya keenya mudatee jira.

Warraaqsi, walitti bu'iinsi, weerarri, beelli hamaan, akkasumas balaan namtolchee fi uummaa yoo baay'atanis, Itoophiyaa ni sochoosan malee hin kuffisne. Diinonni seenaa keessatti beekaman, kan fagoo fi dhiyootti argaman yeroo yeroon ka'anii biyya kana cicciranii diiguuf dhagaan isaan hin fonqolchine hin jiru. Maqaa ishee cilee dibuuf, sadarakaa idil-addunyaatti irra deddeebiin haqa akka hin aganne taasisuuf, buufata doonii qabdu dhabsiisuun akka ukkaamamtu taasisuuf yaalaniiru. Lageen ishee keessaa maddan akka hin fayyadamne waliigaltee hamaa ta'e akka mallatteesitu taasisanii jiru. Kana hunda keessa taatee Itoophiyaan akka warqii ibiddan qoramtee, tattaaffii ijoollee isheetiifi fedha Waaqaatiiin eegamtee akka biyyaatti itti fufuu danda'uun ishee waan baay'ee nama dinqisiisuudha. Biyyi keenya rakkoowwan armaan olii hunda darbuu ishee yoo yaadannu, Waqayyoof galata akka galchinu sababa nuuf ta'a.

Itoophiyaan seenaa ishee keessatti, waggottan afran darban keessa haala mul'atee hin beekneen abdii fi rakkoo, tokkummaa fi garaagarummaa, sadarkaa idil-addunyaatti dinqisiifannaa fi balaalefannaa, waliin ta'uu fi walxaxuu, bilisummaa fi walitti bu'iinsa yeroo itti keessummeessitedha jechuun ni danda'ama. Itoophiyaan ijoollee murteessoo yeroo itti argatte qofa osoo hin taane, yeroo itti dhabdeedha. Hidhi Haaromsa Guddichi Itoophiyaa kanaan booda hin fayyadu yeroo jedhameetti guutinsi bishaanii xumuramee ibsaa kennuu eegalee jira.

Biyyi hiyyoomtuu fi duubatti haftuu jedhamtee waamamatu biqiltuuwwan biiliyoonaan lakka'aman dhaabuudhaan, bakka addaddaatti paarkii ijaaruun imala ishee dachii lalisaa ta'uu tti fuftee jirti.

Wabiin jiraachuu keenyaa qamadii biyyoota dhihaa ta'uu yoommuu isaan yaadanitti, Itoophiyaan qamadii bonaa jallisiin oomishuu fi lafa qonnaa bal'aa irratti midhaani fi fuduraalee oomishuun ofii ishee irra darbitee biyyoota biraa gargaaruuf qophooftee jirti. Finfinneen yeroo tokko maqaa ishee wajjjin haala wal hin gitneen Afrikaatti iddoo balfi itti gatamu jedhamuuf xumurarra geessee turte. Qormaatileen nu mudatan gatii guddaa nu kafalchiisanii jiru. Isaan kana yoo yadannu baay'ee nutti dhagahama. Garuu, kan dhabnerra kan arganne ni caala. Rakkooleen duubatti nu hin hambisne, qormaatni nu hin mo'anne. Kanaaf Waqayyoof galata guddaa galchina.

Jaalatamtoota Ijoollee Biyya koo,

Obboleessi obboleessarratti yoo garaa jabaatu, wajjin jiraachuun hafee nama wajjiin oolee hin beeknee hamma fakkaatutti yeroo itti walitti buune, wanta sababa hin qabneef lubbuun namaa yoo darbu, namoota qiyyaafannoo malee galma hin qabneen dhiigni lammiilee keenyaa akkasumaan dhangala'uu waggoota xiqqoo duubatti deebinee yoo yaadannu, garaan keenya gaddaan caba. Akka dhalootaattis qaaniitu nutti dhagahama. Waraanni fi walitti bu'iinsi kutaa biyyattii kaaba fi dhiyaatti labbuu namaa galaafatee fi qabeenya biyyaa barbadeesse yoo yadannu, ija keenya qofa osoo hin taane, lubbuu keenyatu boo'a.

Badiin yeroo tokko kutaa biyyattii bahaa fi kibbaatti uumamee, rakkoo fi gidiraa akkamii akka fide kan irraanfannu miti. Ijji keenya osoo boochus yoo ta'e in galateeffanna. Sababni isaas wanta nurratti ta'erra, kan nuti arganne waan caaluuf. Biyya keenya

Itoophiyaa, mataa ishee gadi qabanii, dugda kutuuf yoo yaalanis ba'aa irratti fe'ame dandeessee, aarii ishee garaatti qabattee, qormaatashee harkatti baattee dabartee, har'as kutannoodhaan itti fuftee, daandii ishee osoo hin lakkisiin deemuun ishee dhuguma icciitii dinqisiisaadha. Badii keessatti, misooma, gadda keessatti jabina, rakkoo keessatti eebba, dukkana keessatti ibsaa ta'ee kan nu eege fi biyya keenyaaf gargaarsa fi humna kan ta'e Waaqa Itoophiyaati. Waaqa dawoofi golgaa, baḳka itti baqatanii oolaniifi gaachana nuu ta'e kana galateeffachuun, faaruu Itoophiyaanota hundaa ta'uu qaba.

Jijjiiramni kan dhufe faayidaa Itoophiya qofa kabachiisuuf ta'uu warri hubatan, keessumattuu qaamooleen Abbayyaa fi Gaanfa Afrikaa irratti fedhii guddaa qaban, gama nageenyaa fi karaa adda addaatiin daandii badii nuuf baasaa turan. Miidiyaleen biyya gurguddoo fi dhaabbileen isaaniitis dandeettii mootummoota isaanii abdatanii, biyya keenya irrattii waraana gaggeessaa turan. Diinagdee fi maqaa biyyatti sadarkaa idil-addunyaatti balleessuuf waan danda'an hunda raawwachaa, firootiin keenya akka nurraa fagaatan harka lafa jalaatiin dhiibbaa taasisaa turan. Haata'u malee, tattaffii fi yaaliin isaanii tokkummaa Itoophiya riphe dammaqsee dheekkamsa kakaase malee hin kuffisne. Injifannoon Aduwaatis bara keenyatti irra deebi'ame. Duumessi gurraachi biyyi akka diigamtu nurra naanna'e ni hurke. kunis uumaan Itoophiyaa yommiyyuu taanan nu waliin ta'uusaa bara itti arginee dha.

Waggottan lamaan darban keessatti, dhiibbaa idil-addunyaa Itoophiyaa irratti taasifame biyyonni baachuu dadhaban baay'een isaanii bittinaa'anii jiru. Uumaan Itoophiyaa garuu diinotaaf dabarsee nu hin kennine. Kufnee akka hin hafne, hirkannees akka dhaabbanu, dadhabnees akka jabannu humnaa fi cimina nuuf ta'ee jira. Har'a Itoophiyaan gama tokkon addunyaa dinqisiisaa, gama biraatiin taajjabaa ittii fuftee jirti. Yeroo dhufu

jabina ishee cimsitee ceehuf abdiidhaan faggeessitee ilaalti. Jabeenya Itoophiyaa seenaan dhageenye ijaan akka agarru kan nu taasise, bara keenyattis seenaa kan nuuf hojjate, uumaa Itoophiyaa fi Waaqa Itoophiyaa galanni haa gahu.

Biyyi akka Itoophiyaa rakkoo bara baraan mudate irra darbee kabajaan dhaabbatu biyya kami? Biyyoonni garaagarummaa afaanii, aadaa, fi amantaa tokkummaan walsimsiisanii bara dheeraadhaaf turan meeqa? Qabeenya lafa irraa fi lafa keessaatiin kan guutaman, qilleensi fi bishaan isaanii kan eebbifameef, onnee gootummaa fi qaxalee sammuutiin kan badhaafaman, biyyoonni akka Itoophiyaa jiran meeqa? Bifa uummata gurraachaa hundaa fi bareedina addaatiin kan badhaate, Itoophiyaa malee eenyu? Bilisummaa fi abbaa biyyummaatiin biyyi afrikaadhaaf fakkeenya ta'u Itoophiyaa malee eessaatti argama? Bara durii jalqabee hanga har'aatti baqattoota biyya biraa akka ijoollee isaaniitti ilaaluun kan keessumeessan biyyoonni akka Itoophiyaatti waamaman eenyu fa'i?

Rakkoo keessaa fi dhiibbaa alaa damdamachuun waltajjii ispoortii addunyaa irratti injifannoo irratti injifannoo kan gonfatan Itoophiyaanotaa mitii? Addabaabaayii ispoortii irratti alaabaa biyya abbaa isaanii kan olkaasanii mirmirsan, dirree injifannoo argamsiisanitti harka isaani olkaasanii uumaa isaanii kan galateeffatan Itoophiyanota mitii? Suuta jennee yoo yaadne fi eebba keenya xiyyeffannoon yoo lakkoofne, nuti Itoophiyaanonni kan waakkannu irra wantoonni galateeffatoota akka taanu nu taasisan baay'ee heddu dha.

Kanaafi, waan lapheen keenya hubatee fi wantoota hedduu yaadnee hin arganne hunda irra dhaabbannee uumaa kabajuu fi galateeffachuun kan nurra jiraatu. Rakkoowwan har'a Itoophiyaa mudatan masilaalii olka'umsaa yaabbachuu fi riqicha guddinaa ce'aa jiraachuu keenya malee kufiinsa ishee saffisuuf hin oolani.

Humni diinotaa kun hundi kan nutti baay'ataniif, yeroon dhufu abdachisaa ta'uu waan araganiif malee, hiyyeessa abdi hin qabne ta'uun keenya isaan cinqee miti. Mana warqeen guutame malee, manni duwwaan qalbii diinaa hawwachuu hin danda'u waan ta'eef. Yoo xiqqaate, diinotaa fi qaamoolee gaarii keenya hin hawwineef, humna keenya isaanitti mul'atee fi dandeettii dhokataa akka biyyaatti qabnu nuttis mul'achuu qaba. Sababni isaas, gara fuuldurratti daandiin gara guddinaatti nu ceesisu galateeffannaa fi qabeenya qabnu dinqisiifannaa fi kabajaan fudhachuu danda'uu dha. Karaa walxaxaa irra darbitee dhufte hunda keessatti biyya keenya uumaatu tiksee jira, har'as galanni isaaf haa ta'u.

Qabeenya biyya lafaa hunda, amantaa hanga qabeenya seenaa qabeessaa, uumama qilleensaa hanga garaagarummaa aadaa, gootummaa hanga bilisumma jaalachuu, Waaqayyo badhaadhina kana hunda kan nu badhaase ta'uu yaaduun haa galateeffannu. Ofii keenya waljibbuu fi walitti bu'uu irraa bilisa taanee tokkoon keenya kan biraa dinqisiifachuu aadaa keenya haa taasifnu. Wantoota darbanii fi hir'ataniif walyaaddessaa dhaloota dhufu dadhabsuu haa dhiisnu. Kana caala, tokkoon keenya isa biraa, warri har'aa isaan kaleessaa haa galateeffanu. Hunduma caalaa fi dursa immoo baroota gidduun kan nu garagaare Uumaa keenya bakka jiruutti haa galateeffannu. Firoonni keenya yommuu jijjiiraman, gargaartonni keenya fuula yoommuu nu dhoowwatan, ollaan keenya alagaa yommuu nutti ta'an arginee jirra. Kan hin jijjiiramne humni Itoophiyaa, uwwisaan keenya uumaa qofaa dha.

Guyyoota jiran 365 keessaa guyyaa tokko galata keenya waliin taanee osoo dhiyeessinee, oolmaa inni nuu ooole yaadachuuf osoo murteessinee waan baay'atu natti hin fakkatu. Guyya tokko keessatti yoo baay'ate daqiiqaa tokkoof wanta hojjannu hunda dhiisnee bakka jirrutti ol jennee, wanta inni nuuf ta'e

yaadannee, Uumaa Itoophiyaa galateeffachuu qabna. Waggaa fi bara haaraa waakkii fi aariidhaan, gadoofi haaloodhaan qooda keessumeessinu, dinqisiifannaa fi galataan, walgargaaruu fi dhiifamaan simachuu qabna.

Uumaa addunyaa hundaa fi madda arjoominaa kan ta'e, akka biyyaa fi uummataatti, akka hogganaa fi lammiitti afaan beeknuu fi akkaataa amantaa keenyaatiin garaa qulqulludhaan haa galateeffannu. Weerara hamaa irraa nu eegee jira. Afaan bineensaa keessaa nu baasee jira, Hongee balaa hamaa akka nutti hin taane nu fuuldura dhaabbatee jira, diina fagoo fi dhiyoo biyya diiguuf tattaffatu nurraa hambisee jira. Piroojaktoota gurguddoo jalqabnee fi ijaarsa Hidha Haaromsaa Guddicha akka dhugoomsinu nu gargaaree jira, bara durii kaasee hanga har'aatti biyya keenyaa fi uummata keenya icciitii cimaan nuuf tursiisee jira. Ulfinni fi kabajni guddan bara baraan isaaf haa ta'u jennee daqiiqaa tokkoof bakka jirrutti dhaabbanne umaa Itoophiyaatiif galata akka galchinu waamicha kiyyan dabarsa.

Itoophiyaan tattaffii ijoollee isheetiin kabajamtee bara baraan haa jiraattu!

**Uumaan Itoophiyaa fi uummata ishee haa eebbisu!**
**Irreecha Hiree Wayyoomaa**

# Akkuma Kaleessaa Har'as Qormaatota Injifinnoon Ceenee, Harka Keenya Galataaf ni Bal'ifna

***Kabajamaa Abbaa Sirna Gadaa Ummata Oromoo,***
***Kabajamtoota Ummattoota Itoophiyaa,***

Hunda dura, baga bacaqii gannaa dabartanii, booqaa birraa arguuf geessan, baga gammaddan jechuun fedha. Uumaan rakkoo uumamaafi namtolchee nu dandamachiisee, diina xiqqaafi guddaa irra nu aansee, ifa birraa nu agarsiise haa ulfaatu!

Oromoon duudhaa Sirna Gadaarraa dhaaleen, ganni darbee birraan yammuu bari'u, Uumaa galateeffata. Waaqa dukkana gannaa dabarsitee, midhaan magarsitee, oyiruu miidhaqsitee, barii birraa nu agarsiifteef galata jechuun yaadata. Jiidha qabatee, 'Mareehoo' 'Mareehoo' jechaa Malkaa bu'uun irreeffata. Irreechi birraa hiree galateeffannaa Uumaa ganni darbee birraan yammuu bari'u sirna guddaadhaan kabajamuudha. Irra deebiin, Ummanni Oromoofi Itoophiyaanonni hundi baga geessan yammuun jedhu gammachuu guddaatu natti dhaga'ama.
Irreechi hiree nagayaati.

Jamaan irreeffannaaf Malkaa bu'u, irreecha/jiidha harkatti qabate malkaa cuuphee osoo hin irreeffatin dura gaaffii gurguddoo sadii deebisuu qaba. Abboottan Gadaa, "Isin waliif Nagayaa?", "Isin Uumaaf Nagayaa?", "Isin Uumamaaf Nagayaa?" kan jedhu gaafatu. Jamaan irreecha qabatee Malkaa bu'es, Malkaa tuquun dura "Nagayaa" jechuun deebisa. San booda irreechaan Malkaa

tuqee “Mareehoo……. Mareehoo” jechuudhaan Uumaa isaa galateeffata.

Kanaafis, namni Irreecha beeku gadoo lagatee, Nagaa lallaba. Jaalalaafi tokkummaa, waltumsaafi obbolummaa utuba. Kenna kabajamaa Uumaarraa argateef beekamtii kenna. Waloomaafi waliin jireenya uumamaa dinqifachaa Uumaaf galata galcha. Waaqni Irreecha magarse namarraa galata argata. Namni ammoo jiidha Uumaan isaaf kenne qabatee Uumama dinqifata; Uumaa galteeffata. Namni Irreeffatu waliif, ollaaf, alaafi manaaf, biyyaafi alaalaaf nagaa ta’uu qaba.

